

ማዕዶት
መጽሐፈ ዐዋጅ ወአገባብ

በመጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ እና
በመሪጌታ መሠረት ዐሥራት

ማዕዶት

መጽሐፈ ዐዋጅ ወአገባብ

የቅኔን ታሪካዊ አመጣጥ ጨምሮ ዐዋጅንና ሰባቱን አገባባት አጠቃሎ የያዘ የግእዝ ሥርዐተ ሰዋስው መጽሐፍ

በመጋቤ ምሥጢር ማቸው ንጋቱ
እና
በመሪጌታ መሠረት ዐሥራት

መጋቢት ፳፻፱
ባሕር ዳር

የአዘጋጆቹ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ለመጀመሪያ ጊዜ መጋቢት ፳፻፱ ዓ. ም ታተመ
C Simachew Nigatu And Meseret Asrat

አስተያየት ለመስጠት፣
መጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ ስልክ ቁጥር፣
0943384930
የኢሜል አድራሻ፣
simachew1952@gmail.com
ባሕር ዳር
መሪጌታ መሠረት ዐሥራት፣ ስልክ ቁጥር፣
0918000139

የሸፋን፣ ሥዕል አቤሜሌክ ስማቸው ንጋቱ
ትርጉም፣ የወንዙ ምንጭ እውነተኛው የአበው ትምህርት ሲሆን ድልድይ ወንዝ እንደሚያሻግር ሁሉ ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሁሉ ካለማወቅ ወደማወቅ የሚሸጋገሩበት በመሆኑ ማዕዶት /መሸጋገሪያ/ ተባለ።።

መሪጌታ መሠረት ዐሥራት ከፊደል እስከ ጸመ ድጓ፣ የቃል ትምህርት ከውዳሴ ማርያም እስከ መወድስ በባሶ ሊበን ወረዳና በደባይ ጥላትግን ወረዳ ካጠናቀቁ በኋላ፣ የቅኔ ትምህርታቸውን ከመሪጌታ ስብሐት፣ ከመሪጌታ ሻረው፣ ከመሪጌታ ወልደ ኢየሱስ፣ ተምረው እስከማስነገር ደረጃ ደርሰዋል። በመቀጠልም ከግጨው መንክር የተለያዩ የቅኔ መንገዶችን፣ እርባ ቅምርን፣ ዐዋጅንና አገባብን ተምረው እስከ ዘረፋ ደረጃ ደርሰዋል። እንዲሁም በቆላ ደጋ ዳሞት አውራጃ በሰከላ ወረዳ ረቡዕ ጽዮን ያስተምሩ ከነበሩት በኋላም የዋሸራ የቅኔ መምህር ከነበሩት መምህር ገድሉ ወለላው /ጥዑመ ልሳን/፣ የዋድላን እርባ ቅምርና የግስን አወራረድ፣ ዐዋጅ፣ አገባብና የተለያዩ የቅኔ መንገዶችን ተምረዋል። በመቀጠልም ወደወሎ በመሄድ ከተለያዩ መምህራን የዋድላን የቅኔ መንገድ ተምረዋል። እንደገና ወደጎጃም በመመለስ በጃቢ ጠህናን ወረዳ አፍራ ጽዮን በምትባል ቦታ ያስተምሩ ከነበሩት መምህር ዲበ ሥሉ አምባዬ የዋድላን የቅኔ መንገድ፣ እርባ ቅምር፣ ዐዋጅና አገባብ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል።

የመጀመሪያውን ጉባኤ በናዝሬት ደብረ ኢየሱስ ዘርግተው በርካታ ደቀ መዛሙርትን ካፈሩ በኋላ ወደአዲስ አበባ በመሄድ በመካነ ሕያዋን ጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ከመልአከ ብርሃን ጳውሎስ ቀጸላ የሐዲሳትን ትርጓሜ በመማር ላይ እንዳሉ በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ /በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ/ ትእዛዝ በቅኔ መምህርነት ወደ ደብረ ኤልያስ ተልከው ሰፊ ጉባኤ በመዘርጋት በጣም በርካታ የቅኔ መምህራንን አፍርተዋል። ከዚያም ደብረ ማርቆስ በሚገኘው ፊለገ አርዝ ትምህርት ቤት

በመምህርነት በመቀጠር ግእዝና ቅኔ ለበርካታ ዓመታት አስተምረዋል። በመቀጠልም ባሕር ዳር ሽምብጥ ሚካኤል በሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት መርጃ ማዕከል በልዩ ልዩ ሥራ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ባለቤቱ የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት በሆነው ብፁዕ አቡነ በርናባስ ቤዛ ብዙኃን ትምህርት ቤት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

መጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ትምህርት መሠረት ከንባብ እስከ ድጓ፣ ከውዳሴ ማርያም እስከ መወድስ ድረስ የዜማ ትምህርት የተከታተሉ ሲሆን ከመሪጌታ አድሙ /ገደብ ጊዮርጊስ/ ፣ ከመሪጌታ ወልዴ /ጫቢ/ የሰምና ወርቅ ቅኔ ተምረዋል። ከመሪጌታ ይትባረክ /በደምበጫ ወረዳ ደብረ ምጥማቅ/፣ የጎዳና ቅኔ ተምረዋል። እንደገና ወደጫቢ በመመለስ፣ እርባ ቅምር፣ ዐዋጅና አገባብ ተምረው አስጎጋሪ ሆነዋል፣ በመጨረሻም በደብረ ኤልያስ ከመሪጌታ መሠረት ዐሥራት የዋድላን ቤተ ጉባኤ ልዩ ልዩ የቅኔ መንገዶች፣ እርባ ቅምር፣ ዐዋጅና አገባብ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል። የወንጌል ትርጓሜ ትምህርትም በደብረ ሊባኖስ ከመምህር መዘምር /በኋላ አቡነ ቶማስ/ ተከታትለዋል።

ዘመናዊ ትምህርትን በተመለከተ፣ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርት በ6 ዓመት ብቻ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ አዳሪ ትምህርት ቤት ከአጠናቀቁ በኋላ በፖለቲካል ሳይንስ፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና በሕዝብ አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በድርጅታዊ አመራር የማስተርስ ዲግሪ ተመርቀዋል።

በአዲስ አበባና በአማራ ክልል ከባለሙያ እስከ ከፍተኛ የኀላፊነት ደረጃ ድረስ አገልግለዋል። ከነዚህም መካከል የአማራ ገጠር መንገዶች

ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪጅ፣ በካቢኔ ደረጃ የርእሰ መስተዳድርና ክልል መስተዳድር ም/ቤት ጽ/ቤት ኀላፊ፣ የአፈ ጉባኤ ጽ/ቤት ኀላፊ፣ የዐቅም ግንባታ ቢሮ ም/ኀላፊ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ቢሮ፣ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ኀላፊ፣ የኢትዮጵያ አስመጪና ላኪ ኮርፖሬሽን /አዲስ አበባ/ ባለሙያ በመሆን በነሐሴ 2007 ዓ/ም ከዕድሜ ጣራ በፊት በራሳቸው ፈቃድ ጡረታ እስከ ወጡበት ድረስ ለ33 ዓመታት ያህል አገልግለዋል።

የክልል ምክር ቤት አባል በመሆንና የባሕር ዳር ከተማ ምክር ቤት አባል በመሆን ለ20 ዓመታት አገልግለዋል። በተለያዩ ቦርዶችና ማኅበራዊ የልማትና የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች በሰፊው ተሳትፈዋል። አሁንም በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።

ከ18 በላይ በሆኑ የውጭ አገሮች ሥልጠናና የልምድ ልውውጥ ትምህርት በመቅሠምና ሙያቸውን በማዳበር 12 የማሠልጠኛ ማንዋሎችን አዘጋጅተዋል። በዐቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ በወቅቱ ለነበረው አመራር ሰፊ ሥልጠና ሰጥተዋል። አገር አቀፍ የለውጥ ፕሮግራሞች በፌደራል ደረጃ ሲቀረጹም ክልሉን ወክለው ለረጂም ጊዜና በተደጋጋሚ ተሳትፈዋል። በዚህና በሌሎችም አገር አቀፍና ክልል አቀፍ ተሳትፎዎች 22 የምስክር ወረቀቶችን አግኝተዋል።

በአሁኑ ጊዜ ኩሉሐ ሃይማኖት የተባለው የካህናት ማሠልጠኛ መምህርና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዐባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማእከል የጥንታዊ ጽሑፎች ተርጓሚና ተመራማሪ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ስናዘጋጅ በርከታ ሰዎች የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠትና ላደረግንላቸው ቃለ መጠይቅ ቀጥተኛ መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ ያገዙንን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

በተለይ የዋድላ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የሆኑት መጋቤ ሐዲስ አእመረ ዐወቀና ሌሎች ባለሙያዎች የዮሐንስ ገብላዊ የትውልድ ቦታ የሆነችውን ገብለ መንደርን እንዲሁም የነጃ ሚካኤልን ተዘዋውረው በማስጎብኘትና መረጃ በመስጠት ላደረጉልን ከፍተኛ ድጋፍ ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ እንዲሁም የወረዳው ዋና አተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ቦታውን እንድንጎበኝ በማነሣሳትና ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሚናቸው የላቀ በመሆኑ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ እንዲሁም የዋድላ የቅኔ የአብነት መምህር የሆኑትና እዚያው ዋድላ ውስጥ ቁራ አንበሳ በተባለ ቦታ ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ላይ የሚገኙት መሪጌታ አብርሃም ወርቁ ለሰጡን መረጃ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

የዋሸራ የቅኔ መምህር የሆኑት መምህር ጥዑመ ልሳን ልየው የተላያዩ መረጃዎችን በመስጠትና በተለያየ ጊዜ ለተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ሰፊ ማብራሪያ በመስጠት እገዛቸው ከፍተኛ ነበርና ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ ወጣቱ የሰምና ወርቅ የቅኔ መምህር መሪጌታ ኪዳኑ አበራ የተላያዩ አገባቦችን በማዋስና ማብራሪያ በመስጠት ላደረጉልን ድጋፍ ምስጋናችን ይድረሳቸው፡፡

የጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር የሆኑት ሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው፣ የጎንጅን የቅኔ ባሕርይ ተንትኖ በማስረዳት፣ የተለያዩ መረጃዎችንና ቅኔዎችን በመስጠት ላደረጉልን ያልተቆጠበ ትብብር

ከልብ እናመሰግናለን፡፡ የፈለገ ፀሐይ ሸምብጥ ቅ/ሚካኤል ገዳም የቅኔ መምህር የሆኑት መሪጌታ መንግሥቱ ዘለዓለም፣ የባሕር ዳር መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የቅኔ መምህር የሆኑት መሪጌታ ቅዱስ ያሬድ፣ በሰላም አርጊው ደብረ ጽዮን ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን የጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር የሆኑት መሪጌታ ሃይማኖት አድማስ፣ በቃለ መጠይቅ ለሰጡን ማስረጃና ሙያዊ ማብራሪያዎች ከልብ እናመሰግናለን፡፡

በመጨረሻም ወ/ሮ ኢየሩሳሌም ደገፉ /የመ/ም/ሥጢር ስማቸው ንጋቱ ባለቤት/ የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በኮምፒዩተር ጽሕፈት በማገዝና ሥነጽሑፋዊ ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ፣ እንዲሁም ሁሉም ቤተሰቦቻችን መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ላደረጉልን ያልተቆጠበ ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

ማ ው ጫ

ተ.ቁ	ርዕስ	ገጽ
፩	መግቢያ	
፪	የቅኔ ትርጉም	
፫	ቅኔ የት፣ መቼና በማን ተጀመረ	
፬	የዋሸራ ቤተ ጉባኤ	
፭	የዋድላ ቤተ ጉባኤ	
፮	የገንጂ ቤተ ጉባኤ	
፯	ዐዋጅ	
፲	አገባብ	
፲.፩	ዐቢይ አገባብ	
፲.፪	ደቂቅ አገባብ	
፲÷፫	ደቂቅ ርባታ አገባብ	
፲.፬	ንዑስ አገባብ	
፲.፭	ተረፈ ንዑስ	
፲.፮	የሰምና ወርቅ መንገድ	
፲.፮.፩	የሰምና ወርቅ ቅኔ	
፲.፮.፪	የጎዳና ቅኔ	
፲.፮.፫	የሦስቱ አብያተ ጉባኤ ዋና ዋና መለያዎች	
፲.፯	የአኃዝ አገባብ	
፱	ዋቢ መጻሕፍትና ሊቃውንት	

፩ መግቢያ

ቅኔ መቼ ተጀመረ? የት ተጀመረ? በማን ተጀመረ? የሚሉ ጥያቄዎች ለዘመናት ሲነሱ ኖረዋል። ለእነዚህ ያቄዎችም መልስ ለመስጠት ምሁራን ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል። በሚሰጡ መልሶች ግን አንድነትን መፍጠር አልተቻለም። መቼ ተጀመረ ለሚለው ጥያቄ አንዳንዶቹ ዘመኑን ወደዘመነ ነቢያት ሲወስዱት ሌሎቹ ደግሞ ፲ኛውን ክፍለ ዘመን መነሻ ያደርጋሉ። በሌላ በኩልም ወደ ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን የሚያቀርቡ ምሁራንም አሉ።

ቦታውን በሚመለከትም ሰሜን ጎንደር ጠለምት፣ ደቡብ ወሎ ሳይንት ደብረ ታቦር፣ ሰሜን ወሎ ዋድላ፣ ምዕራብ ጎጃም ዋሸራ እና ጎንጅ መነሻ ናቸው እየተባለ ይጠቀሳሉ። ሁሉም መነሻ ሊሆኑ አይችሉም ከተጠቀሱት መካከል አንዱ ነው መነሻ ሊሆን የሚችለው። ይህን በተመለከተ መጽሐፉ መልስ ይሰጣል። ይበልጥ አከራካሪ የሆነውና ሁሉንም ሰው የሚያግባባ መልስ ለመስጠት የሚያስቸግረው ቅኔን ማን ጀመረው ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ነው። የቅኔን መሠረተ ሐሳብ ማመንጨትና ቤተ ጉባኤ መመሥረት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ይህ መጽሐፍ ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን መልሶቹ በጥናትና በመረጃ ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ በሙያው የተሠማሩ ምሁራንን ሊያግባቡ ወይም ሊያቀራርቡ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል።

የቅኔ መሥራች ዋና ዋና ጉባኤ ቤቶች ሦስት ስለመሆናቸው ክርክር የለም። የዋሸራ፣

የዋድላ እና የጎንጅ አብያተ ጉባኤ ተብለው መከፈላቸውን ምሁራን ሁሉ ይስማማሉ፡፡ የማይስማሙት ግን ማን ቀደመ? ማን ተከተለ? ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው መልስ ላይ ነው፡፡ ጀማሪውን ሊቅ በሚመለከትም ስምምነት የለም፡፡ ቅዱስ ያሬድ ነው፣ ዮሐንስ ገብላዊ ነው፣ ተዋነይ ዘጎንጅ ነው፣ ድህሪም ዘዋሸራ ወይም ዕዝራ ሱቱኤል ነው በማለት ክርክሮች ሲካሄዱ ኖረዋል፡፡ ይህ መጽሐፍ ለዚህ ጥያቄ ታሪክንና ማስረጃን መሠረት ያደረገ መልስ ይሰጣል፡፡

በእያንዳንዱ ቤተ ጉባኤ፣ ለራሱ ለቤተ ጉባኤው ቅኔን ከጀመረው መምህር ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ ያለው የመምህራን ዝርዝር በመጽሐፉ ውስጥ ተካቷል፡፡ የጉባኤ ቤቶች በሦስት ቢከፈሉም ቅኔ የሚከፈለው በሁለት ነው፡፡ እነርሱም ሰምና ወርቅና ጎዳና ናቸው፡፡ የሰምና ወርቅ ቅኔዎች በየጉባኤ ቤቶች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን የጎዳና ቅኔዎችም በተመሳሳይ ተለይተው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተመልክተዋል፡፡

የቅኔ ጉባኤ ቤቶች ለምን ተለያዩ? መሠረታውያን የሚባሉ ልዩነቶችስ ምንድን ናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች መጽሐፉ መልስ ይሰጣል፡፡ አንድነቱ በእጅጉ የሚበልጥ ቢሆንም በሁሉም የቅኔ ሙያዎች ልዩነቶች አሉ፡፡ መምህራን ልዩነቶቻቸውን ይዘው በውይይትና በምክክር ለመፍታት ባለመቻላቸው ልዩነቶች ዘመን ተሻጋሪ ሆነዋል፡፡ ልዩነቶችን ማጥፋት ወይም ማጥበብ አለመቻል ብቻ ሳይሆን ልዩነቶችም በአግባቡ ተቀምረው አይታወቁም ነበር፡፡ ልዩነቶችን ለማጥፋት ወይም ለማጥበብ

የመጀመሪያው እርምጃ ልዩነቶችን ፈልፍሎ ማውጣት ነው። ይህ መጽሐፍ ይህን ክፍተት ይሞላል።
የቅኔ ሙያ አሰጣጥ፣ ቅኔን ልዩ ጥበብ ያለውና ውስብስብ ከሚያደርጉት ሙያዎች ወይም ይዘቶች አንዱ ነው። ቅኔ ሰምና ወርቅን ስለያዘ ወይም የዜማ ልኩ ስለተጠበቀ ትክክለኛ ቅኔ ሊሆን አይችልም። ለእያንዳንዱ ሐረግና ቃል ሙያ መስጠት የግድ ነው። የቅኔ ሙያ አሰጣጥ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ያህል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቦታ ተሰጥቶታል።
መንግሥታዊ ሥርዐት በሕግ እንዲመራ ዐዋጅ ይወጣለታል። ከዐዋጁ በመነሣትም ደንቦችና መመሪያዎች ይዘጋጃሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ቅኔም በሕግ ሰዋስው እንዲመራ ለማድረግ ዐዋጅ አለው። ይህ መጽሐፍ ከያዛቸው ዐበይት ርእሶች መካከል አንዱ ዐዋጅ ነው። በመጽሐፉ ከባለሁለት አዐጆች እስከ ሙሻዘር ድረስ ያሉት ዐዋጆች ተዘርዝረውና ተተንትነው በምሥክር ቀርበዋል። በመቀጠልም ሙሽዘርን ጨምሮ ሊሎች ስድስቱ ዐዋጆች በዝርዝር በቅደም ተከተል ቀርበዋል።
ቅኔ የሚቀመረው ወይም የሚደረሰው አናቅጽን፣ ዘርን፣ ዐዋጅን፣ ነባርንና አገባባትን አዋሕዶ ነው። አገባብ በሰባት ታላላቅ ዘርፎች የሚከፈል ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰፊ ቦታ ተሰጥቶታል። ዐቢይ አገባብ፣ ደቂቅ አገባብ ፣ ደቂቅ ርባታ፣ ንዑስ አገባብ፣ ተረፈ ንዑስ፣ የሰምና ወርቅ መንገድና አጎዝ በዝርዝር በመጽሐፉ ውስጥ በሰፊው ቀርበዋል።

ምዕራፍ አንድ፣
የቅኔ ታሪካዊ አመጣጥ

፪ የቅኔ ትርጉም

በመጀመሪያ ቅኔ የሚለውን ቃል ትርጉሞ መግባቱ ደራሲንና አንባቢን የበለጠ ያግባባል። በዚህ መሠረት ለቅኔ የተለያዩ ምሁራን የሰጡትን ትርጉም እንመልከት። አንዳንድ ምሁራን ቅኔ ማለት መገዛት ማለት ነው በማለት የሚተረጉሙ ሲሆን ቀነየ ገዛ ካለው ግስ የወጣ ጥሬ ዘር ነው ይላሉ። ለዚህ ትርጉም አሰጣጥ የሚያቀርቡት ማስረጃም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ቁሙ እንከ ወኢትሐሩ ዳግመ ውስተ አርዑተ ቅኔ። እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ፡ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ፣ /አድማሱ ጀንበሬ፣ 1963፣ 9፣ ገላ፡ 5፣1/ የሚለውን ነው። አርዑተ ቅኔ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው መገዛትን ስለሆነ ቅኔ ማለት በተመስጠ ሕሊና መላ አካላትን ለእዚአብሔር አስገዝቶ የሚደረስ ጥበብ ነው በማለት በርካታ የሙያው መምህራን ቅኔን ከመገዛት ጋር አያይዘው ይተረጉሙታል። ሊቀ ሊቃውንት ያሬድም ይህንኑ ትርጉም ወስደው ተጠቅመውበታል /2002፣ መቅድም፣ 8/። መገዛት ሲባል ለራስ ሕሊናዊ ተመስጠ መገዛትንም ይጨምራል። ይህንንም መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ሲያብራሩ፣ ሕዋሳተ አፍአን፣ ሕዋሳተ ውስጥን ለሕሊና አስገዝቶ በተወሰ ቁርጥ ሐሳብ የሚታሰብ ስለሆነ ቅኔ ተብሏል ይላሉ /1963፣ 9/።

በሌላ በኩልም ተቀነዩ ለእዚአብሔር በፍርሀት የሚለውን የዳዊት መዝሙር በመጥቀስ ለእግዚአብሔር በግጥም የሚቀርብ ምስጋና ነው በማለት ትርጉም የሚሰጡም አሉ። በተጨማሪም መምህር ይኄይስ ወርቁ /1960፣ 9/ ሰብሕዎ

ለእግዚአሔር ስብሐተ ሐዲሰ /እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት/ ብሎ ልበ አምላክ ዳዊት የተናገረው ስለቅኔ ነው፡፡ ቅኔ በየቀኑ ለዘመናት በተለያዩ መምህራን የሚደረስና አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝ ሁሌም አዲስ ጥበብ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከቅኔ በስተቀር ምስጋናዎች ሁሉ አዲስ አይደሉም፡፡ ቅኔ ግን ሁልጊዜ አዲስ ነው፡፡ ይህ የቅኔ ልዩ ባሕርይና መገለጫ ነው፡፡ ስለዚህ ቅኔ ቀነየ አመሰገነ ካለው ግስ የወጣ ጥሬ ዘር ነው፡ ይላሉ፡፡
ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው /2002፣ 8/ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በገለጹበት አግባብ፣ መገዛትና ማመስገንን ከገለጹ በኋላ በተጨማሪ ቅኔ ቃነየ ቃኘ፣ ደረደረ፣ አዜመ፣ መራ፣ ገጠመ፣ አራቀ ተናገረ ካለው ግስ የወጣ ጥሬ ዘር ነው ብለው ተርጉመውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ /1963፣ 9/ ቅኔን ከዚህ እንደሚከተለው ውበትን አላብሰው ገልጸውታል፣

> ሰው ከራሱ አንቅቶ ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ላቅርብ ባለ ጊዜ ምሳሌ መስሎ፣ ምሥጢር አሻሽሎ፣ ግጥም በመግጠም የልቡናውን ዕውቀት የአእምሮውን ርቀት፣ የሚገልጽበት፣ የዕውቀቱን ደረጃ የሚያስታውቅበት፣ የሰሚንም ልቡና የሚያነቃቃበትና የሚያራቅቅበት ድርሰት ማለት ነው

ጠቅላይ ቤተ ክህነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፮ ዓ/ም ድረስ በሚል ርእስ ባሳተመው መጽሐፍ ገጽ 131 ላይም ከላይ በመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ የተገለጸውን ትርጉም ተጋርቶታል /2000፣ 131/፡፡ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ /ያሁኑ አቡነ መልከጼዴቅ/ ደግሞ ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ ቅኔ ቆንቆነ ነቀዘ ከሚለው ግስ የወጣ ጥሬ ዘር ነው ካሉ በኋላ ቁንቁን እንጨትን እንደሚበላ

ሁሉ ቅኔም የሰውን አእምሮ ይበላልና ብለው አራቀውታል /1963፣ 172/ ። ሆኖም የሚደግፉት ምስጋና የሚለውን እንደሆነ ጽፈዋል። በዚህ መሠረት ቅኔ መገዛትም፣ ምስጋናም ቢባል ትክክል ነው። ምክንያቱም መገዛቱም ለእግዚአብሔር ነው፣ ምስጋናው የሚቀርበውም ለእግዚአብሔር ነው። ባለቅኔ ራሱን ማስገዛቱንና ለራሱ ለእዚአብሔር መገዛቱን የሚገልጽበት የምስጋና ድርሰት ነው። ስለዚህ ቅኔ ማለት ቀነየ ገዛ ከሚለው ሥርወ ቃል የተገኘና በምሥጢር ግን ተቀነየ ተቀኘ፣ ምስጋና አቀረበ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ አዲስ ምስጋና ወይም ራስን ለእዚአብሔር ማስገዛት ማለት ነው ብለን ልናጠቃልለው እንችላለን።

አንድ ቅኔ፣ ቅኔ ነው ለመባል፣ አዲስ መሆን አለበት፣ ሰምና ወርቅ ያለው መሆን አለበት፣ ቤት ያለው መሆን አለበት፣ የፍልስፍና ሐሳብ ያለው መሆን አለበት፣ ውስጠ ተሳሳቢውን የጠበቀና ሙያ ያለው መሆን አለበት።

፫ የቅኔ አጀማመር
ቅኔ የት መቼና በማን ተጀመረ?

በሦስቱም አብያተ ጉባኤ ከተያዘው መረጃና ከተለያዩ የሙያው ምሁራን ጋር በተደረገው ውይይት ከተገኘው መረጃ ተነስተን ስንገመግመው ቅኔ መቸ፣ የት፣ በማን እንደ ተጀመረ ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል። ቅኔን ማን ጀመረው? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ቀድመው ከሚጠሩት መካከል አንዱ ቅዱስ ያሬድ ነው። ቅዱስ ያሬድ በሕይወት የነበረው ከ505 እስከ 571 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ይታወቃል /በላይ መኮንን፣ 2006፣ 22/። ቅዱስ ያሬድ ከአጎቱ ከመምህር ጌዲዎን የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት ትርጓሜን ተምሮ በ20 ዓመቱ ማስተማር

እንደጀመረና /ጥዑመ ልሳን ካሳ፣1981፣123/ በሂደትም በ30 ዓመቱ አካባቢ ዜማን እንደ ደረሰ እንጂ ቅኔን በምን አግባብ እንደ ፈጠረ፣ ቀጥሎም ለማን እንዳስተማረ ዘርዝሮ የሚያስረዳ ሁነኛ ምንጭ ባይኖርም ቅኔን የደረሰው ቅዱስ ያሬድ አይደለም ብሎ ለመከራከር የሚያስችል በቂ ማስረጃም የለም። በዚህም የተነሳ የቅዱስ ያሬድ የቅኔ አጀማመር ሁልጊዜም አወዛጋቢ ነው። ቅዱስ ያሬድ ምዕራፍ በተባለው የዜማ ድርሰቱ ዛሬ የቅኔ መጠሪያ አድርገን የምንጠቀምባቸውን ስሞች ጠቅሷል። ለምሳሌም ዘአምላኪየ፣ ሚ በዝኑ፣ ዋዜማ፣ ዘይእዜ፣ መወድስ፣ ሑልክሙ፣ ሕንጼሃ፣ የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከዚህ በመነሳት ቅኔን ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው በማለት ብዙ ሊቃውንት ጽፈዋል። ነገር ግን ቅዱስ ያሬድ የፈጠረው ቅኔ ቤት የማይመታና የዜማ ልክም ያልነበረው እንደሆነ አያሌ ሊቃውንት ሲግባቡበት ኖረዋል። መምህር ይኄይስ ወርቁም /1960፣ 88/ ራሱ ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው ናቸው በማለት ያቀረቧቸውን ቅኔዎች ስንመለከት የያሬድ ቅኔዎች ቤት እንዳልነበራቸው እንረዳለን። ለምሳሌ ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ እንመልከት፣

ወአንተሰ ጸላእከ ተግሣፅየ፤
ወአግባእከ ድኅሬከ ቃልየ
እመኒ ርኢከ ሰራቄ ትረውጽ ምስሌሁ
ወረሰይከ መክፈልተከ ምስለ ዘማውያን

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬም ይህን ቅኔ ጠቅሰውታል። ይህ ቅኔ የተወሰደው ከመዝሙረ ዳዊት 49፡17-20 ሲሆን በግልጽ እንደሚታየው ቤት አይመታም። ቅዱስ ያሬድ ይህን ከጻፈ በኋላ በየዓመቱ የጸሎተ ኀሙስ ዕለት ክብር ይእቲ ሆኖ እንዲያገለግል ተደርጓል። ሌላው በቅዱስ ያሬድ የተደረሰ ነው የሚባለውና ለፋሲካ ዋዜማ የሚቀርበው ክብር ይእቲ ቅኔ ከዚህ የሚከተለው ነው።

ተሰቅለ ወተቀትለ
በኢየሩሳሌም ተቀብረ
ከመ ይቤዙ ኪያነ፣ ሃሌ ሉያ

እንደዚሁ ቅዱስ ያሬድ ነው የደረሰው ተብሎ የሚነገር ዕጣነ ሞገርም አለ፡፡

ሃሌ ሃሌ ሉያ
ኩልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ
ከመ ተንሥአ ክርስቶስ እምኔክሙ
በትፍሥሕት ንግበር በዓለ
ወበሐሴት ንግበር በዓለ

ቅዱስ ያሬድ ደረሳቸው የተባሉ እና እስከአሁን ያየናቸው ቅኔዎች ሁሉ ቤት የማይመቱ፤ የዜማ ልክ የሌላቸውና የሐረጋቸው ብዛት ተለይቶ የማይታወቅ እንደ ሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ ቅኔን የፈጠረው ቅዱስ ያሬድ ነው ብለው የሚያምኑ ሊቃውንት ቅኔዎቹ መስፈርት ያልነበራቸው ናቸው የሚለውን ለመግለጽ ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡ ቅኔውን የደረሰው ደቀ እስጢፋ ነው እየተባለ የሚነገርለት ሲሆን ቅኔው አጭር መወድስ ሆኖ እንዲህ ይላል፡፡

ተትሕተ ያሬድ ዘኢተትሕተ
ለቅኔያቲሁ ደቂቅ እስመ ኢሐነጸ ቤተ

በሌላ በኩል ደግሞ ያሬድ ቤት የሚመቱ ቅኔዎችም እንዳሉት ማስረጃ ጠቅሰው የሚከራከሩ አሉ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ በ1980 ባሳተመው መጽሐፍ ከዚህ የሚከተሉት ቅኔዎች ለማስረጃነት ተጠቅሰዋል፤

ሀገረ ክርስቶስ ሐዳስ ንድቅ
ዘበውስቴታ የኀድር ጽድቅ
ጻድቃን ኪያሃ አብደሩ እምወርቅ

ሌላም ቤት ያለውና የቅዱስ ያሬድ ነው ተብሎ የሚነገር ባለሦስት ቤት ቅኔ አለ፡፡

በዜወ መለኮት ቀሰሙ ዓለመ
ውስተ ቤተ መርዓ አውሐዙ ሰላመ

ሐዋርያት እምሕዝብ አእተቱ ፀራዌ ርጉመ
የያሬድ ቅኔዎች ቤት ይመታሉ ከሚለው ወገን ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንንም ይገኙበታል፡፡ ቤት የሚመቱ ቅኔዎችን ከድጓ ወስደው ከዚህ የሚከተሉትን ጽፈዋል፡፡

ዮሐንስ እዴከ መጥወኒ
ወበርተሎሜዎስ አቡየ ለባርኮ ቅረበኒ፣
ወለተ ብርሃን ለአድኅኖትነ ረዲ፣
ውስተ ጽርሐኪ በስብሐተ ወልድኪ ዑዲ
/በላይ መኮንን፣ 2006፣ 66/

ቅኔን የፈጠረው ቅዱስ ያሬድ ነው በማለት ጠንክረው የሚከራከሩ ጥቂት መምህራን የያሬድ ቅኔዎች ቤት የላቸውም የሚለውን አይቀበሉም፡፡ ለቅኔያቲሁ ደቂቅ እስመ ኢሐነጸ ቤተ የሚለውም ስሕተት ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ነገር ግን ከላይ ቤት ይመታሉ ተብለው የተጠቀሱት ቅኔዎች በትክክል ቅኔዎች ናቸው ወይ? ተብሎ መጠየቅ አለበት፡፡ ቤት የሚመታ ግጥም ሁሉ ቅኔ ከተባለ አስቸጋሪ ነው፡፡ ጥበብ ወይም ፍልስፍና መሆኑም ይቀራል፡፡ በእርግጥ ከላይ የተጠቀሱት የግእዝ ግጥም መሰል የዜማ ድርሰቶች የተወሰዱት ጸመ ድጓ እና ድጓ ከተባሉት የያሬድ ድርሰቶች ሲሆን የመጀመሪያዎቹ የሚገኙበት ክፍልም ከደብረ ዘይት የዐርብ አርያም ነው፡፡ በቅኔ ፍልስፍና ከተመለከትነው እነዚህ ግጥሞች ቅኔ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ መስፈርቱንም አያሟሉም፡፡ ይህ ዐይነቱ ግጥም ሁሉ ቅኔ የሚባል ከሆነ ቅኔ የሚባል ነገር የለም፡፡ ወይም በግእዝ ቋንቋ የተነገረና በአጋጣሚ ቤት የሚመታ ሁሉ ቅኔ ይባላል ማለት ነው፡፡ መምህር ዓለማየሁ ሞገስ /1950፣ 116/ የዜማ ቤት ሰዎች ቅዱስ ያሬድ ነው የደረሰው ይላሉ፣ ግን የሱው ተራ ግጥም እንጂ ቅኔ ስላልሆነ ጉንጭ አልፋ ክርክር ከመሆን አይዘልም በማለት ቅኔን የጀመረው ቅ/ያሬድ እንዳልሆነ ይከራከራሉ፡፡

ቅዱስ ያሬድ ቅኔን ከፈጠረ በኋላ ሐዊራ፣ መንከራ፣ እስክንድራ፣ ፖእስክንድራ እና አቢዲራ ለተባሉ ተማሪዎች አስተምሯል /ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ 1963፣ 172/ ይባላል፡፡ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ይህን ይበሉ እንጂ ማስረጃ አልጠቀሱም፡፡ እንዲሁ በደፈናው ቅኔን ያስፋፉት እነዚህ ስማቸው የተጠቀሰው ደቀ መዛሙርት ናቸው መባሉ በቂ አይደለም፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬም እንደርሳቸው ያሬድ ቅኔን ለእነ ሐዊራ አስተማረ ይባላል ብለው ጽፈዋል፡፡ አስተማረ ይባላል አሉ እንጂ አስተማረ አላሉም፡፡ እነዚህ ደቀ መዛሙርት ቅኔን ማስተማር ቢጀምሩ ኖሮ እስከ ድህሪም ድረስ ዳብዛው ጠፍቶ ሊኖር አይችልም ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የቅኔን ፍንጭ ቅዱስ ያሬድ አሳየ ማለት ቢቻልም፣ ቅኔን ለእነ ሐዊራ አስተማረ የሚለው አሳማኝ አይደለም፡፡ ያሬድ የቅኔን ሐሳብ አመነጨ እንጂ ለማንም አላስተማረም፡፡ እነሐዊራ ከያሬድ የተማሩትን ዜማ አስተማሩ እንጅ ቅኔን አላስተማሩም፡፡ እነርሱም አልተማሩም፡፡ ከዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት እስከ ዐፄ አንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ድረስ /ከ340 ዓመታት በላይ/ የቅኔ አድራሻ አይታወቅም፡፡ በዚህ ቦታ ተከፈተ የሚባል የቅኔ ጉባኤ ቤትም በጭራሽ የለም፡፡ ቅኔ በእርግጥም ቤትና ወሰን ኖሮት ቢፈጠር ኖሮ እንደ ዜማው ትውልድ እየተቀባበለውና እየሰፋ መሄድ ይችል ነበር፡፡ ያሬድ እኮ በአብዛኛው መዝሙረ ዳዊትን ነው እንዳለ የጠቀሰው፡፡ ይህ ደግሞ ቅኔን ዳዊት እንጂ ያሬድ አልደረሰውም እስከማለት ያስኬዳል፡፡ ቅኔን ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሱት ነቢያት ናቸው የሚሉ ወገኖችም መኖራቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ ለዚህ አባባል መዝሙረ ዳዊት አንድ መነሻ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሰሎሞንም ከመ ፍሕሦ ቀይህ ከናፍርኪ፣ ንባብኪ አዳም፣ ከመ ቅርፍተ ሮማን መላትሕኪ፣

እንበለ አርምሞትኪ እያለ ተቀኝቷል፡፡ በመሳፍንት 5፡1 ላይም እኔ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ ይላል፡፡ ኢሳይያስም በ5፡1 ላይ አሁን ስለወዳጄና ስለወይን ቦታው ለወዳጄ ቅኔ እቀኛለሁ፡፡ ለወዳጄ በፍሬያማው ኮረብታ ላይ የወይን ቦታ ነበረው፡ ይላል፡፡ ስለዚህ የቅዱስ ያሬድ ቅኔ፣ ቅኔ ነው ከተባለ ከእርሱ የተሻሉ ቅኔዎችን ነቢያት ተቀኝተዋል፡፡ ያሬድ የዜማ እንጂ የቅኔ ቤተ ጉባኤ እንዳልከፈተ ሊሠመርበት ይገባል፡፡

ቅዱስ ያሬድ በመጀመሪያ ጉዞው ከአክሱም ወደ አማራ ክልል መጥቶ የዜማ ትምህርቱን በሰሜንና ደቡብ ጎንደር /ደምቢያ፣ ጋይንት፣ ጠለምት/ እየተዘዋወረ ያስተምር በነበረበት ዘመን /ጥዑመ ልሳን ከሳ፣ 1981፣ 123/ ቅኔን እንዳልጀመረ መናገር ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በመጨረሻዎቹ ዓመታት የደረሳቸውን የዝማሬና መዋሥዕት ድርሰቶቹን በዙር አባ፣ 14ቱን የቅዳሴ ዜማዎች በአክሱም /እንደገና ወደ ትግራይ ተመልሶ/ ከደረሰ በኋላ ምዕራፍ የተባለውን የዜማ ድርሰቱን ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አማራ ምድር /ጠለምት/ መጥቶ እንደ ደረሰ ይታወቃል /ጥዑመ ልሳን ካሳ፣ 1981፣ 124/፡፡ የቅኔ ስሞች የተገለጸበትን የምዕራፍ ድርሰት አጠናቀቀ የሚባለውም ሊሞት ሲል ነው፡፡ የሞተው ደግሞ በ571 ዓ/ም ስለሆነ ያሬድ ቅኔ የሚመስል ነገር የደረሰው ከ550 ዓ/ም በኋላ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የመጨረሻዎችን 22 ዓመታት በጠለምት አካባቢ ዜማ እየደረሰና እያስተማረ እንደ ቆየ በተለያዩ ጸሐፊዎች ተገልጿል፡፡ ስለዚህ በስም ደረጃም ቢሆን ለቅኔ ስም ስያሜ መሠረት ያስቀመጠ ቅዱስ ያሬድ ነው በሚለው መስማማት ይቻላል፡፡

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ በኋላም ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው ቅኔን ያሬድ ጀመረው ስለሚለው ከዚህ የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡

> ምዕራፍ በተሰኘው ድርሰቱ ዋዜማ፣ ሚ በዝኑ፣ ይትባረክ፣ ዘይእዜ፣ መወድስ፣ ኦልክሙ፣

እያለ መመሥረቱ ይታወቃል። ይኸስ እንዳይሆን ቅኔ ማለት ዘወትር በየቀኑ ከየሰው ልቡና ሲፈጠር የሚኖር እንግዳ ድርሰት ነው። ያው ደራሲው ቢሆን እንኳ አንድ ቀን ከተናገረውና ካሰማው ሁለተኛ ጊዜ መልሶ ሊጠቀምበት አይችልም። የያሬድ ድርሰት ግን ምቅናዩም ሆነ ሌላው ያው እየተመላለሰ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ይቃኛል። ድርሰቱ ይዘመራል እንጅ እንደ ቅኔ ዘወትር የሚታሰብ እንግዳ ድርሰት አይደለም። ስለዚህ ግብሩን ሳይሆን ስሙን ብቻ አስጠግቶ ቅኔን ያሬድ ጀመረው ማለት አጥጋቢ ታሪክ ሆኖ አይገኝም። ከዚህ ይልቅ በቅኔ ድርሰት የያሬድ ድርሰት መቅደሙ የማይካድ ነው። ቅኔ በያሬድ መዝሙር አልፎ አልፎ እንደ ጌጥ እንደ ፊርጥ እየገባ የሚዘመር ስለሆነ ዋዜማ፣ ሚ በዝኑ፣ መወድስ፣ ዅልክሙ፣ መባልን ስሙን ከያሬድ ይትበሀል ወስዶታል ቢባል አጥጋቢ መልስ ሳይሆን አይቀርም በማለት የሰጡት ትንታኔ ሚዛን የሚደፋ ነው /አድማሱ ጀንበሬ፣ 1963፣ 10፣ ያሬድ ሽፈራው፣ 2002፣ መቅድም 8/ ።

ትልቁ የመከራከሪያ ነጥብም ቅኔ ሁልጊዜ አዲስ እንጂ እንደ ዜማ አንድ ጊዜ ተደርሶ በየጊዜው እየተመላለሰ ለአገልግሎት የሚውል አይደለም የሚለው ነው። አለቃ ይኄይስ ወርቁም ለቅኔ ትርጉም ሲሰጡ እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት የሚለውን የጠቀሱት ለዚህ ነው።

የቅኔን ሐሳብ ያመነጨው ቅዱስ ያሬድ ቢሆን ኖሮ የዋሸራ፣ የዋድላ እና የጎንጅ አብያተ ጉባኤ ቅኔን የፈጠርነው እኛ ነን እያሉ ለምን ይከራከራሉ? የሚለውን ቀጥለን እንመልከት።

፬ የዋሸራ ቤተ ጉባኤ

ዛሬ ያሉትም ሆነ ቀደሞ የነበሩት የዋሸራ የቅኔ መምህራን ቅዱስ ያሬድ ቅኔን አልጀመረም ብለው ባይከራከሩም አሁን ካሉት ሦስቱ ቤተ ጉባኤዎች ቀዳሚዎቹ እነርሱ ለመሆናቸው ታሪክ ጠቅሰው ይከራከራሉ /መምህር ጥዑመ ልሳን፤የዋሸራ የቅኔ መምህር፣ 2008/፡፡ በምሁራኑ አባባል መሠረት ቅኔ የተጀመረው በዋሸራ ገዳም ነው፡፡ ታሪኩም ከዚህ አንደሚከተለው ነው፡፡ ቅኔን የጀመረው ድህሪም የተባለ የአገው ምድር ወይም የደጋ ዳሞት ተወላጅ ሲሆን ዘመኑም በአንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ነው /882 እስከ 902 ዓ/ም/፡፡ ድህሪም በነበረበት ዘመን በዳሞት የአማራና የጋፋት፤ በአገው ምድር የአገው ሕዝቦች፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከእስራኤል ከመጡ ሕዝቦች ጋር ተቀላቅለው ይኖሩ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን ሁሉም ሕዝቦች የኦሪትን እምነትና ሥርዓት አጥብቀው ሲከተሉ የኖሩ ሕዝቦች እንደ መሆናቸው መጠን ድህሪም ሐዲስ ኪዳንን ለማስረጽ በደጋማው አካባቢ እየተዘዋወረ ወንጌልን ያስተምር እንደ ነበረ ይነገራል፡፡

ከዚህ ተነሥተን የድህሪምን የኋላ ማንነት ስንገምት የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ዕውቀት ያለው ሰባኬ ወንጌል ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ቅዱስ ያሬድም የሐዲስና የብሉይ ትርጓሜ መጻሕፍት መምህር ሞኮር ስለነበረ በዘመን ባይገናኙም ድህሪም በያሬድ የትርጓሜ መጻሕፍትና የቅኔያዊ ግጥም ተጽዕኖ ሥር ያረፈ ሰው ነበር ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ለነገሩ እሥራኤላውያን በግጥም የማመስገንና የመዘመር ልማድ ስለነበራቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ካህናተ ኦሪት ጊዜው ቢረዝምም ባህሉን ይዘወት ስለቀጠሉ ድህሪም ለመንፈሳዊ ግጥም ቅርብ ሰው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ግን ቅኔ ከእስራኤል ተወሰደ ተብሎ ትርጉም ሊሰጠው አይገባም፡፡

የአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ አገውኛና ጋፋትኛ ተናጋሪ ስለነበር ድህሪም ከግእዝ ቋንቋ በተጨማሪ አገውኛና ጋፋትኛ ሊናገር እንደሚችልም መገመት ይቻላል። ይህም ዕውቀቱ የኩሽና የሴም ቋንቋዎችን የሰዋስው አካሄድ ይበልጥ ለመረዳት ቅርብ የነበረ ሰው መሆኑን ያሳያል። ድህሪም የአካባቢው ሕዝብ በሚናገረው ቋንቋ ሐዲስ ኪዳንን እየተዘዋወረ ሲያስተምር ትንቢትም ይናገር እንደ ነበር የዋሸራ ሊቃውንት ይነገራሉ /መምህር ጥዑመ ልሳን ልየው/።

የዘር ግንዱን በተመለከተ ድህሪም ከቀዳማዊ ምንይልክ ጋር ከመጡት የካህናት ወገን የዘር ግንድ ያለው እንደ ሆነ እነመምህር ጥዑመ ልሳን ዘዋሸራ ያስረዳሉ። ምክንያቱም ቀዳማዊ ምኒልክን አጅበው ከመጡት ሕዝቦች መካከል ካህናትን የሚወክሉት ጋፋቶች የዐባይን ወንዝ ተከትለው እስከ ዳሞት፣ ቡሬና ወንበርማ ድረስ ተስፋፍተው ይኖሩ ስለነበር /አለቃ ታየ ገብረ ማርያም፣ 1943፣ / ዝርያው ከአማራ፣ ከጋፋትና ከአገው ሊወጣ አይችልም። ድህሪም የካህናት ወገን መሆኑ አሪትንም ሆነ ወንጌልን ለማወቅና ለማስተማር ቅርበት ያለው ሰው መሆኑን መገመት ይቻላል።

ወንጌላዊውና ነቢዩ ድህሪም እንደተለመደው ሕዝቡን ለማስተማር ከሰከላ ደጋማው አካባቢ ተነስቶና በደጋ ዳሞት በኩል አቆራርጦ በዳባ ተራራ ላይ ወደ ዋሸራ ሲወርድ ቆም ብሎ አካባቢውን ተመለከተ። ተራራማው የዋሸራ አካባቢ በደን የተሸፈነ ነበር። በዚያም ደን ውስጥ አንድ ዋሻ ተመለከተና በዚያ ለማረፍ አሰበ። ዋሻው ዛሬ በግልጽ ቅርጹን እንደያዘ ባይታይም የሚገኘው ቁራ ገደል እየተባለ በሚጠራው የተራራ ሰንሰለት መካከለኛ ቦታ ላይ ነው። ወዲያውም የእግዚአብሔር መንፈስ መጥቶ በዋሻው ውስጥ ሱባዔ እንዲገባ ነገረው። ዋሻው የራጉኤል ዋሻ እየተባለ ይጠራ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን አብዛኛው የአካባቢው ሕዝብ ቁራ ገደል እያለ ይጠራዋል።

የዋሸራ ካህናት ግን የራጉኤል ዋሻ በሚለው ስም ይጠሩታል።።
ድህሪም በዋሻው ውስጥ በሱባዔ ላይ እያለ አንድ አስገራሚ ነገር ተመለከተ።። የአካባቢው ሕዝብ የሚያመልክባቸው ሁለት ዘንዶዎች የዋሸራን አካባቢ ከሸፈነው ባሕር አጠገብ በነበረው ጫካው ውስጥ ይኖሩ ነበር።። እነዚህ ዘንዶዎች በየቀኑ ወደ ዘማ ወንዝ እየወረዱ ውሃ ይጠጡ ነበር።። ወደ ወንዝ ሲወርዱ መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል ሰይፍ ይዞ ከዘንዶዎቹ በላይ ረቦ ሲታየው ሲመለሱ ደግሞ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደዚያው ሰይፍ ይዞ ይታየዋል።። በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ሲወርዱ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ሲመለሱ መላኩ ቅዱስ ራጉኤል ሰይፋቸውን ይዘው ከዘንዶዎቹ በላይ በቅርብ ርቀት ይታዩታል።። ይህ ሁኔታ እየተፈራረቀ ተደጋገመበት።። ጉዳዩ ያስጨነቀውና ያስገረመው ድህሪምን ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የሚኖሩና ከሩቅም ዝናውን ሰምተው ሁኔታውን ለመረዳት በዙሪያው የተሰባሰቡ ምሁራንም ነበሩ።። አንዳንዶቹ መንፈሳዊ ሀብተ ጥበብ ይገኝባቸዋል ብለው፣ ሌሎች ደግሞ ከምድራዊ ጥበብ ጋር በማያያዝ የጥንቆላ ጥበብ ይገኛል ብለው ይከታተሉ እንደነበር የዋሸራ የቅኔ መምህር ጥዑመ ልሳን ልየው ያልታተመ ጽሑፍ ጽፈዋል /2008/።። የዘንዶዎቹ፣ የመልአኩና የሰማእቱ ሰይፍ ይዞ መታየት ትርጉም እንዲገለጽለት እግዚአብሔርን ሲጠይቅ ሕዝቡ ከአምልኮተ ዘንዶ ወጥቶ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ይመለስ ዘንድ እዚያው ሱባዔ በያዘበት አካባቢ በመልአኩ በቅዱስ ራጉኤልና በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ በመንፈስ ቅዱስ ተነገረው።። ዘመኑም የዐፄ አንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ነው።። ድህሪም በመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን መልእክት አልተጠራጠረም።። ቸልም አላለም።። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኑን በዚያ አካባቢ ለማነጽ ሲያስብ

ቦታው በውሃ የተሸፈነ ስለነበር ትክክለኛ ቦታውን ለመምረጥ ሌላ ሱባዔ መግባት ጠየቀው፡፡ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የሚተከልበትን ትክክለኛ ቦታ ለማወቅ በተገባ ሱባዔም ሌላ አዲስ ነገር ተፈጠረ፡፡ እርሱም በቅዱስ ያሬድ ጊዜ ፍንጬ ታይቶ የጠፋው ቅኔ ለድህሪም ተገለጸለት፡፡ ቅኔው በቦታው ይገለጻል፡፡ ድህሪም ብሉይንና ሐዲስን የሚያውቅ ሰባኬ ወንጌል ስለነበር የግእዝ ቋንቋ ዐዋቂ ከመሆኑም በላይ በአካባቢው የሚነገሩ ሌሎች ቋንቋዎችንም ይናገር እንደ ነበር ከላይ መገለጹ ይታወሳል፡፡ ድህሪም በተደጋጋሚ ሱባዔ የያዘበት ቦታ ወይም ዋሻ ድሮ በነበረው ቅርጹ ባይሆንም ዛሬም አለ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የቦታውን ምስል መመልከት ይቻላል፡፡



ዋሸራ የሚገኘው ቁራ ገደል/የራጉኤል ዋሻ

ዋሻው የሚገኘው አሁን የዋሽራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ካለበት ቦታ ትንሽ /በግምት ሁለት ኪሎ ሜትር/ ወደዳባ ተራራ ከፍ ያለ ሲሆን በዚያ የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን አሠራ። ገዳሙ አሁን ያለበት ቦታ በባሕር የተሸፈነ ነበር፡ ባሕሩ እንደሚሸሽና በዚያ ቦታ ላይ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እደሚታነጽበት በራእይ ተገለጸለት። ራእዩም የተገለጸለት ከዚህ በሚከተለው ቅኔ ነው።

ርኢኩ ሕልመ ዘኮነ መንክረ
ዕዝራ ዘርእየ ወነጸረ
ባሕርኒ ርእየት ወጐየት ድኅረ
ወለብሰት ምድረ ወኮነት ደብረ፣

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ባሳተመው መጽሐፍ /2000፣ 136/ ደግሞ የዘሱቱኤል ቅኔ ከዚህ የሚከተለው ነው ብሎ ጽፏል።

ማዕከለ አራዊት ንኬልሕ ወአልቦ ዘይሰምዐነ፣
እስመ አራዊት ይበዝኑ እምኔነ፣
መኑ ጠቢብ ወመለብው፣
ከመ እግዚአብሔር አግው፣

የሚሉ የቀጠፉ ቅኔዎች ከመታወቃቸው በስተቀር ሌሎቹ ጠፍተዋል ይላል። ዘመኑንም ከያሬድ በፊት ያደርገዋል። ስሙንም ዘሱቱኤል ብሎታል። ዕዝራ የዘሱቱኤል ተማሪ መሆኑንም ይገልጻል /2000፣ 137/። ነገር ግን ዕዝራ ሱቱኤል የአካባቢው ሕዝብ ያወጣለት ስም እንጂ መደበኛ ስሙ ድህሪም እንደሆነ ይታወቃል። ድህሪም በቅኔው ዕዝራ ዘርእየ ወነጸረ ሲል ዕዝራ የሚባል ተማሪ እንዳለ ያመለክታል። ሆኖም ከዋሽራ የተገኘው መረጃ የድህሪም ደቀ መዛሙርት ሁለት ብቻ /ዘርእየ እና ነጸረ/ እንጂ ሦስት መሆናቸውን አይገልጽም። ዮሐንስ አድማሱ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባቀረበው ጥናት ድህሪም አገው መሆኑንና ቅኔ የተፈጠረውም በአገው ምድር ውስጥ እንደሆነ የጻፈ መሆኑ ከላይ በተገለጸው መጽሐፍ ተጠቅሷል። ዋሽራ በወቅቱ በአገው ምድር አስተዳደር ውስጥ ከሆነች ብቻ ታሪኩ እውነት ሊሆን ይችላል። “መኑ ጠቢብ ወመለብው፣ ከመ እግዚአብሔር አገው” የሚለው ቅኔም የታሪኩን ተቀባይነት ለማጉላት ተብሎ የተደረሰ ይመስላል።

ድህሪም በዋሻው ውስጥ በሱባዔ ላይ እያለ የሚያገለግሉት ሁለት ደቀ መዛሙርት አብረውት ነበሩ። የአንዱ ስም **ዘርእየ** ሲሆን የሁለተኛው ደግሞ **ነጸረ** ይባል ነበር። በቅኔው ዕዝራ ዘርእየ ወነጸረ ብሎ የጠቀሳቸው እነርሱን ነው። ድህሪም ነቢይ ስለነበር በመንፈስ ቅዱስ ተገልጸለት በቅኔው የተናገረው ትንቢት ነው። ትንቢቱም በወቅቱ በባሕር ተሸፍኖ የነበረውና ዛሬ የዋሽራ ገዳም ያለበት ቦታ ወደ የብስነት እንደሚቀየርና ገዳሙም በዚህ ቦታ እንደሚመሠረት የተገለጸለት መሆኑ ነው። በትንቢቱ መሠረትም ውሃው ሸሽቶ መሬቱ ወደ የብስነት ከተቀየረ በኋላ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ታንጾበታል። ዛሬም የቅዱስ ራጉኤል ጽላት ከማርያም ጽላት ጋር ተደርቦ በገዳሙ ይገኛል። ድህሪም ከላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ያሬድ ጀመር አድርጎ በተወው ቅኔ ላይ ተመስጦ አድሮበት ከወንጌል ትምህርት ጎን ለጎን ሲፈላሰፍ እና ሱባዔ ሲገባ ቆይቶ በትንቢት መልክ እንደ ገለጸው መገመት ይቻላል። ቅኔውን ስንመለከተውም ቤት ይኑረው እንጂ የዜማ ልክ ያልነበረውና ምን ተብሎ ሊጠራ እንደሚችልም የሚያስቸግር ቅኔ ነው። በውስጡ ግን ፍልስፍና አለው።

የድህሪም ደቀ መዛሙርት የነበሩት ዘርእየ እና ነጸረም በበኩላቸው የመምህራቸውን የመሰለ ቅኔ ተቀኝተዋል። ዋሽራዎች እንደሚሉት ግን እነርሱም የመምህራቸውን የመሰለ ቅኔ የተቀኙት በራእይ

እየተገለጸላቸው ነው። ነገር ግን ለብዙ ጊዜ ከድህሪም ጋር አብረው እስከ ቆዩ ድረስ በትምህርት ያገኙት ነው ማለትም ይቻላል። ለምሳሌ ዘርእየ ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ እንደ ተቀኘ ይነገራል፤

ርኢኩ ሕልመ ዕዝራ ከመ ነጸረ
ጸሎተ ቅዱሳን ከፈለ ባሕረ
ወበባሕር ሣረረ ደብረ
ዕዝራኒ አዘዘ ነምረ
ከመ ያስተዳሉ መቃብረ
ወበመቅበርት እምአርዌ ተሠወረ

ይህ ቅኔ ደግሞ ሌላ ትንቢት በውስጡ ይዟል። ነብር መቃብር እንደሚያዘጋጅና ዕዝራ በዚያ እንደሚቀበር ያመለክታል። ሁለተኛው ደቀ መዝሙር ነጸረም የመመህሩን የድህሪምን እና የጓደኛውን የዘርእየን የመሰለ ቅኔ ተቀኝቷል።

ርኢኩ ሕልመ ዘተሠወረ
ወነጸርኩ ሕልመ ተአምረ ወመንክረ
ዕዝራ በከመ ዘመረ
ሐመረ ኖኅ ሰፈፈት ባሕረ
ወጥበብ ሐነጸት ማኅደረ
ዕዝራኒ ተረክበ እምኀበ ተቀብረ
ወበመቅበርት ቀበረ ነምረ

የነጸረ ቅኔም ትንቢት አለበት። ዕዝራ ነብር ቆፍሮ ባዘጋጀው መቃብር እንደሚቀበርና በኋላም ከተቀበረበት ቦታ እንደሚገኝ፤ በምትኩ ግን ነብሩ እንደሚቀበር በቅኔው ትንቢት ተናግሯል። ጊዜው ሲደርስ በትንቢቱ መሠረት ዕዝራ መቃብሩን በነብር ካስቆፈረ በኋላ ሞቶ በአንድ ግራር ሥር ተቀብሮ ጠፋባቸው። ሕልማቸውን መሠረት አድርገው እዚያው በዋሻው ዙሪያ ሲፈልጉ ግን ዐፅሙን አገኙት። አውጥተውም በቤተ ክርስቲያን አስቀምጠው ይጸልዩበት ነበር። በመቃብር ቦታውም መቃብሩን የቆፈረው ነብር ተቀበረበት። ይህም አስቀድሞ በትንቢት ተገልጾ ነበር።

በቅኔው ላይ ዕዝራ የሚል ስም ተጠቅሷል። ድህሪም ጻድቅና የበቃ ሰው ስለነበር ትንቢት የሚናገርና አንዳንድ ጊዜም ተሠውሮ ቆይቶ ሕዝቡ ጠፋ እያለ ሲያዝን ድንገት ከተፍ ይል ስለነበር ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ537 እስከ 460 ዓ/ዓ አካባቢ ይኖር ከነበረው የእስራኤል ነቢይ ዕዝራ ጋር በማመሳሰል ዕዝራ ሱቱኤል የሚል የቅጽል ስም አውጥተውለታል። ዕዝራ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ከካህኑ ከአሮን ወገን ተወልዶ ከምርኮኞች ጋር ያደገ ሲሆን ፈጣን ጸሓፊና ካህንም እንደነበር በመጽሐፈ ዕዝራ ምዕራፍ 7 እና 8 ላይ በዝርዝር ተጽፎ ይገኛል። በ458 ዓ/ዓ ንጉሡን አርጤክስስን በማስፈቀድ 1800 እስራኤላውያንን አስከትሎ ወደኢየሩሳሌም ከመጣ በኋላ በእግዚአብሔር መንገድ የሚመራቸው አጥተው ሲቸገሩ የነበሩ ከምርኮ ተመላሽ እስራኤላውያንን በኦሪት ሕግ ዳግም እንደ አነጸና ከአምልኮ ባዕድ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እንደ መለሰ ሁሉ ድህሪምም አምልኮተ እግዚአብሔርን ትተው በዘንዶ ያመልኩ የነበሩ የዋሸራና የአካባቢውን ሕዝብ አስተምሮ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለ መለሰ ዕዝራ ሱቱኤል ብለው ሰይመውታል። በተጨማሪም ነቢዩ ዕዝራ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ጠፍተው የነበሩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ሰብስቦ እንዳጻፈ ሁሉ /መዓልተ ይጽሕፉ ወሌሊተ ይዴረሩ እንደተባለው/ በዮዲት ጉዲት ጊዜ /842 እስከ 882/ በቃጠሎ ጠፍተው የነበሩ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በቃሉ ይዞ ስለ አስተማራቸውና ዳግም እንዲታወቁ ስለ አደረገ ከዕዝራ ሱቱኤል ጋር አመሳስለውታል። እንዲሁም በያሬድ ጊዜ ብቅ ብሎ የጠፋውን ቅኔ መልሶ እንደ ደረሰው ለማጠየቅ /በአጥኚው የተጨመረ/ ዕዝራ ሱቱኤል የሚል ስም በሕዝቡ ወጥቶለታል። ስለዚህ የቅኔ ፍንጭ ከ340 ዓመታት በላይ ማለትም ከ560 እስከ 900 ዓ/ም ድረስ ወይም ከዐፄ ገብረ መስቀል

ዘመነ መንግሥት እስከ ዐፄ አንበሳ ውድም /882 እስከ 902/ ዘመነ መንግሥት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ጠፍቶ ቆይቶ እንደገና በአዲስ መልክ የተደረሰው **<u>በድህሪም / ዕዝራ ሱቱኤል/ በ900 ዓ/ም ነው።</u>** /የዋሽራ ታሪክ በሚል ርእስ የተጻፈና በዋሽራ የሚገኝ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ/። ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ዕዝራ ድህሪም እንጂ የድህሪም ወይም የዘሱቱኤል ተማሪ አይደለም። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በዋሽራ ቅኔ አንድም ጊዜ አልተቋረጠም። በዋሽራ ሊቃውንት መሠረት፤ ድህሪም /ዕዝራ ሱቱኤል በመጀመሪያ ቅኔውን ያስተማረው አብረውት ለነበሩት ሁለት ደቀ መዛሙርት ለዘርእየ እና ለነጸረ ነው። ነጸረ ጉባኤ መሥርቶ ቅኔ ለማስተማሩ መረጃ የለም። ዘርእየ ግን የዋሽራ ቅኔ መሥራች ከሆኑት አባቱ ከድህሪም ያገኘውን ዕውቀት ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ አስፋፍቶታል፤

መምህር	ተማሪ
ድህሪም/ ዕዝራ ሱቱኤል	ለዘርእየና ለነጸረ
ዘርእየ	ለዘከመዝ
ዘከመዝ	ለዕዝራ ቀዳማዊ
ዕዝራ ቀዳማዊ	ለዜና አዳም
ዜና አዳም	ለየማነአብ
የማነአብ	ለሕላዌ ዘአብ እና ለዜናአብ
ሕላዌ ዘአብ	ለሠረቀ ብርሃን
ሠረቀ ብርሃን	ለኃይለ መዊዕ
ኃይለ መዊዕ	ለጌዴዎን ቀዳማዊ
ጌዴዎን ቀዳማዊ	ለበኩረ ጥበብ
በኩረ ጥበብ	ለነደ እሳት
ነደ እሳት	ለኤልያስ
ኤልያስ	ለሠረገላ ጥበብ
ሠረገላ ጥበብ	ለግሩም ቀዳማዊ
ግሩም ቀዳማዊ	ለጌዴዎን ዳግማዊ
ጌዴዎን ዳግማዊ	ለአብነት

አብነት
ነአምን በአብ
አሚናዳብ
ዘርዐ ዮሐንሰ
በኵረ ልደት
አካለ ወልድ
ሠረቀ ብርሃን ዳግማዊ

ተወከል
ዘከማየ
ለይኩን ኩሉ
ተክለአብ ዳግማዊ

ገብረ ማርያም
ተክሥተ ብርሃን
ጥበበ ሥላሴ
ፈለገ አብ
ገብረ ማርያም ቀዳማዊ
ከተማ
ፀምሩ
ጌዴዎን

ቀስሙ

ተክሌ ፍቅሩ

ለነአምን በአብ
ለአሚናዳብ
ለዘርዐ ዮሐንስ
ለበኵረ ልደት
ለአካለ ወልድ
ለሠረቀ ብርሃን ዳግማዊ
ለተወከል እና

ለዮሐንስ ገብላዊ/ዋድላ/
ለዘከማየ
ለለይኩን ኩሉ
ለተክለአብ ዳግማዊ
ለገብረ ማርያም እና

ለተዋነይ /ጎንጅ/
ለተክሥተ ብርሃን
ለጥበበ ሥላሴ
ለፈለገ አብ
ለገ/ማርያም ቀዳማዊ
ለከተማ ገ/ማርያም
ለፀምሩ
ለጌዴዎን
ለቀስሙ
ለስለኔ ጥበብ እና
ለፍቅሩ
ለተክሌ ፍቅሩ
ለገ/ማርያም ሣልሳዊ
ለድማሀ ገነት ወንድምሁነኝ
ለገ/ማርያም ራብዓዊ /ዋድሌ/

ለአለቃ ጥበቡ ዘደብረ ታቦር

ለመ/ጌታሁን ዘአዴት

ለመ/ግ/መስቀል ዘዋድላ
ለመ/ያሬድ ዘደብረ ቀልሞን
ግ/ማርያም ራብዓዊ ለግጨው ገብሬ

ለመ/መንግሥቱ /ደ.ማርቆስ/

ለማዕበል ፈንቴ ዋሴ ወዘተ
ማዕበል ፈንቴ ለለይኩን ዘድንግራ
ለመምህር ገድሉ
ለመ/ር ተስፋ ዘቀራንዮ
መምህር ተስፋ ለመ/ር ጥዑመ ልሳን ልየው
መምህር ጥዑመ ልሳን ልየው በአሁኑ ጊዜ ጥንታዊውንና ከ900 ዓ/ም ጀምሮ ሳይቋረጥ ለ1109 ዓመታት የቀጠለውን የዋሽራ ወንበር ይዘው በርካታ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ዋሽራ የሚጠቀምበትን የመጽሔተ አእምሮ አገባብ የተማሩትም ከመ/ተስፋ ዘቀራንዮ ነው፡፡ ለ5 ዓመታትም የመ/ተስፋ ዘራፊ ነበሩ፡፡ መምህር ገድሉ የተማሩት ኢጋባብ የዋድላን አገባብ ነው፡፡ ይህንኑ የዋድላ አገባብም ያስተምሩ እንደነበር ዛሬ በሕይወት ያሉ አንጋፋ መምህራን ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ መምህር ገድሉ ከዋሽራ ቤተ ጉባኤ በተጨማሪ የዋድላንም እርባ ቅምርና አገባብ ተምረው ከመምህር ጥዑመ ልሳን በፊት በዋሽራ ያስተምሩ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የዋሽራ አገባብ ማለት የአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ ነው፡፡ ዛሬም መምህር ጥዑመ ልሳን የሚያስተምሩት የአለቃ ታየን አገባብ ነው፡፡ አለቃ ታየ ግ/ማርያም ይህንን አገባብ የጻፉት ከዋሽራ ተምረው ሊሆን ይችላል፡፡
የዋሽራን ቤተ ጉባኤ ለማጠናከርና ከጎንጅ ቤተ ጉባኤ ጋር ለማቀራረብ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበሩት የቅኔና የቋንቋ ሊቁ ዓለማየሁ ሞገስ መምህር ጥላሁንን ከጎንጅ፣ መምህር ተስፋን ከአረፋ፣ መምህር

ብዙአየሁን ከአይባር፣ እመይቴ ገላነሽን ከጽላሎ፣ መምህር ጌቴ አድገህን ከአዴት እና መምህር ገድሉን ከዚያው ከዋሸራ ከሁለት ከሁለት ተማሪዎቻቸው ጋር ሰብስበው ለሦስት ወራት ያህል በጋራ ቅኔ እንዲያስነግሩ አድርገዋል። በዚህ ወቅትም የቤት ኪራይ ከመሸፈን በተጨማሪ ለመምህራኑ የኪስ ገንዘብ ለእያንዳንዳቸው ብር 40.00 እና ለተማሪዎች ደግሞ ብር 20.00 ሲከፍሉ እንደነበር የዋሸራ መምህራን ይናገራሉ። በመጨረሻም ለመምህራኑ ካባ ሸልመው የተሻለ ቅርርብ ለመፍጠር ችለው ነበር። ከመምህር ጥላሁን በስተቀር ሁሉም የዋሸራ ቤተ ጉባኤ መምህራን ናቸው። ይህ ጅምር ተጠናክሮ ቢቀጥል ኖሮ ዛሬ እንደባላንጣ የሚተያዩት ጉባኤ ቤቶች ተባብረው በመሥራት ቅኔን አንድ እርምጃ ወደፊት ማስኬድ ይችሉ ነበር።

የዋሸራ ቤተ ጉባኤ ለግእዝ ቋንቋና ለቅኔ ዕድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። አንዱና ዋናውም የግስ ቅደም ተከተልና ቅንብር ነው። ነጠላ ግስን **ሀለሀ** ወደረ ብለው ጀምረው **ዴፐ** ሸመቀ በማለት ጨርሰው አሁን ባለበት መልኩ እንዲሆን ያደረጉት /የፈጠሩት/ እና ከአበገደ ቅደም ተከተል ያወጡት የዋሸራ መምህራን ናቸው። ግስ ዘዋሸራ እየተባለ የሚጻፈውም በዚህ ምክንያት ነው። ደራሲው ወይም ፈጠሪውም አበ ብዑዳን ተክሌ ፍቅሩ ናቸው። ይህን ለማስታወስ የአሁኑ የዋሸራ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር የሆኑት መምህር ጥዑመ ልሳን ከዚህ የሚከተለውን አጭር ኩልክሙ ዘርፈዋል።

ኢታምልክ ግስ አምላከ ሕሳዌ መቅለሌ
እንዘ ፈጣሪከ ፈጣሪከ ተክሌ

የነጠላ ግስ ቅርፅ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ መደረጉ በቅኔ ዓለም ውስጥ ታላቅ እመርታ ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የግስን ባሕርይ ሲገልጹ በገጽ 61 ላይ /መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣1948/ ከዚህ የሚከተለውን ጽፈዋል። ዘር

በቋንቋ ሁሉ የግስ ጥንት፣ የርባ መሠረት ስለሆነ ከአንቀጽ በፊት ይጻፋል። ከርባታ በፊት ይነገራል። ዘርን አንቀጽና ጥሬ አይቀድመውም፡ ፡ በአፈ ታሪክም የቀድሞ መምህራን ዘርን ሳያስቀድሙ አይገሱም ነበር ይባላል፡ በማለት ዛሬ ያለው የነጠላ ግስ ቅርፅ አዲስ መሆኑን እና ቋንቋን ካለማወቅ የተነሳ የተፈጠረ ስህተት እንደሆነ በክርክር ገልጸውታል። የጥንቱ የግስ ቅደም ተከተል በማን እና መቼ እንደተቀየረ ግን አልገለጹም። አለቃ ተክሌ ፍቅሩ በሕይወት የነበሩት በዐፄ ምንይልክ ዘመነ መንግሥት ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም የርሳቸው ተማሪና ወራሴ መንበር የሆኑት መምህር ገብረ ማርያም ራብዓዊ ወይም ገበረ ማርያም ዋድሌ ከአለቃ ተክሌ ተቀብለው ግስን አሁን ባለው አቀማመጥ መሠረት ለማዕበል ፈንቱ እና ከ230 በላይ ለሚሆኑ ሌሎች ደቀ መዛሙርት ከአስተማሩ በኋላ በጣሊያን ወረራ ወቅት በዚያው በዋሸራ በጣሊያን ወታደሮች መስዋዕትነት የተቀበሉበትን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። /ያልታተመ በዋሸራ የሚገኝ የእጅ ጽሑፍ/።

የዋድላ ቤተ ጉባኤ መምህራንም አንቀጽ ካለ ዘር መኖሩ አይቀርም በማለት ከአንቀጽ ተጀመረ እንጂ በዋድላ እርባ ቅምርም ከዘር ጀምሮ ወደ አንቀጽ መምጣት የተለመደ ነበር ይላሉ። ለምሳሌ ነድ፣ ንደት፣ ነዲድ ነዲዶት፣ ነደ፣ ይነድድ፣ ይንድድ፣ ይንድድ፣ ንዱድ፣ ነዲድ፣ የሚለውን አካሄድ በመጥቀስ ያስረዳሉ። ይህ በዋድላ እርባ ቅምር ላይም በግልጽ ተጽፎ ይገኛል /ያልታተመ የአለቃ ቡሩኬ አገባብ/። አንቀጽ ማለት በር ወይም መግቢያ ስለሆነ ከቤት ውስጥ ያለን ነገር ለማወቅ በመጀመሪያ ወደቤቱ ውስጥ መግባት እንደሚያስፈልግ ሁሉ በአንቀጽ ገብቶ ሌላውን እርባታ ማውጣት የተሻለ አካሄድ መሆኑንም ያብራራሉ /መሪጌታ መሠረት ዐሥራት፣ 2008/። አለቃ ተክሌ ፍቅሩ ዘዋሸራ

በኢትዮጵያ የቅኔ ትምህርት ላይ የሰምና ወርቅ ጥበብን ብቻ ሳይሆን የግስ አረባብ ዘዴንም ለትውልድ አስተላልፈዋል። አሁን ያለው ነጠላ ግስ በዚህ ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑን ምንጩን ሳናውቀው እጽሕፍ ግስ ዘዋሽራ እያልን ስንጽፍ ኖረናል። እንኖራለንም። አለቃ ተክሌ የቅኔን የዜማ ልክና ውስጠ ተሳሳቢን በራሳቸው መንገድ በመቀየር በቅኔ ዓለም እመርታ የፈጠሩ ታላቅ ሊቅ ናቸው /ዓለማየሁ ሞገስ፣ 1967/። አለቃ ተክሌ ዜማ ልኩን በራሳቸው መንገድ ደፍረው በመሄድ የገለባበጡ ፋና ወጊ ሊቅ ናቸው። ቅኔን ብቻ ሳይሆን ትርጓሜ መጻሕፍትንና ዜማንም ጨምረው ያስተምሩ እንደነበር በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ /1982/ የተጻፈው ታሪካቸው ያስረዳል።

ከ900 ዓ/ም እስከ 2008 ዓ/ም ድረስ ለ1109 ዓመታት በዋሽራ ያስተማሩት መምህራን ብዛት 41 ሲሆን አንድ መምህር በአማካይ ለ27 ዓመት አስተምሯል ማለት ነው። ይህም ስሌት የመረጃውን ተአማኒነት የበለጠ ያጎላዋል።

ከዋሽራ ሳንወጣ በቦታው ስለሚገኙት ሁለት ታቦታት ታሪክ ጥቂት ነገሮችን እንጥቀስ። ዛሬ በዋሽራ ገዳም ውስጥ የሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ባይሠራም በዐፄ ዳዊት ወልደ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት በ1372 ዓ/ም እንደ ተተከለ የዋሽራ ታሪክ ያስረዳል። ቦታውም ከባሕሩ ባሻገር በስተደቡብ ባለው ኮረብታማ ሥፍራ ነው። በኢትዮጵያ 3ኛው ቦታ እንደሆነም ይነገራል። ታቦተ ጊዮርጊስ ወደኢትዮጵያ እንዲመጣ የተደረገው ገባሬ ተአምር በመሆኑ ነው ይባላል።

ታቦተ ማርያም ቀደም ሲል ሲነገር በነበረው አረቦን መሠረት፣ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በ1434 ከሰሜን አካባቢ ዋጅራ ከሚባል ቦታ ተነሥታ፣ 300 በሚሆኑ የበቁ መነኮሳትና ባሕታውያን በመታጀብ ወደ ዋሽራ መጣች። አገሩ ጫካ፣ መንገዱ

ስንክልክል ከመሆኑ የተነሳ ጉዞው ስምንት ወራት ፈጅቷል። ከዋጅራ ግንቦት 1 ቀን 1433 ዓ/ም ተነስታ፣ በግንደ በረት አድርጋ፣ ጎዳር 30 ቀን ደብረ መድኃኒት ደረሰች። ታኅሣሥ 20 ቀን 1434 ዓ/ም ዋሸራ ደርሳ በባሕሩ አናት ዳርቻ በግልገል ዳባ ግርጌ በጎን መንጌና ቁራ ገደል አካባቢ በኮረብታው ላይ እንድታርፍ ተደረገ። ስሟም ደብረ ምዕራፍ ተባለ፡ በማለት መምህር ጥዑመ ልሳን ይተርካሉ።
መንክር ኃይላ፣ የምትባለው ስዕልም የተሳለችው በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ሲሆን ስሙን ላለመግለጽ የፈለገ አንድ ባሕታዊ በአራቱ ማዕዘን ጀምሮ እየሳለ ሄዶ በስተምሥራቅ በኩል መሳል ሲጀምር፣ ለምን ዝም ብለህ ትስለኛለህ? ዳዊት፣ ኪዳን፣ ውዳሴ ማርያም እየደገምክ በአቡነ ዘበሰማያት እያሳረግክ ሳለኝ አለችው። ለበቁት ሁሉ ሲማጸኗት ታነጋግራቸው ነበር። ተአምርም ታደርግ ነበር። በዚህ የተነሳ መንክር ኃይላ ትባላለች። በአገር ደረጃ እጅግ ብርቅየ ቅርሶች ከሚባሉት መካከል አንዷ እንደሆነችም ይታወቃል።



የዋሸራ የቅኔ አብነት ትምህርት ቤት ዛሬ ይህን ይመስላል

፮ <u>የዋድላ ቤተ ጉባኤ</u>

የታላቁ ፈላስፋ የዮሐንስ ገብላዊ ታሪክ በተለያዩ ሊቃውንት በቁንጽል የተጻፈ ቢሆንም ትክክለኛ ታሪኩ ተጽፏል ማለት አይቻልም፡፡ በተለይ የትውልድ ቦታው የት እንደ ሆነና፣ እናቱና አባቱ እነማን እንደ ሆኑ በትክክል ሳይታወቅ ኖሯል፡፡ አሁን ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት በተደረገ ሰፊ ጥናት ታሪኩን ለማሟላት ረጂም ርቀት ተሂዷል፡፡ የቀረ ነገር ካለ ደግሞ መጪው ትውልድ ከዚህ የተሻለ ጥልቅ ጥናት በማድረግ ሊያሟላው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

የዋድላ ወረዳ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና የሰንበት ት/ቤት ኃላፊ የሆኑት መሪጌታ ተውህቦ ዘውዴ ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ትውፊት መሠረት በማድረግ እንደሚናገሩት፣ የዮሐንስ ገብላዊ የአያቱ አገር ጎንደር ሲሆን በሥራ ምክንያት የነገሥታት ቦታ ወደ ነበረችው ወደ ብልባላ ጊዮርጊስ በመሄድ ከአካባቢው ተወላጆች መካከል አንዲት ሴት አግብቶ ገብሬ የተባለ ልጅ ወለደ፡፡ ገብሬም ለአካለ መጠን ሲደርስ ወደ ዋድላ መጥቶ ኒሩት የምትባል ሴት አገባ፡፡ እግዚአብሔር ትዳራቸውን ባርኮ ዮሐንስ የሚባል ልጅ ሰጣቸው፡፡ ይህም ታላቁ ሊቅ ዮሐንስ ገብላዊ ነው ይላሉ፡፡

ብልባላ ጊዮርጊስ የሚገኘው በቡግና ወረዳ ውስጥ ሲሆን ይህ አካባቢ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሚታወቀው ላስታ ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ዮሐንስ ገብላዊ በአባቱ የጎንድርና የላስታ ቅልቅል ነው፡፡ በእናቱ ግን የዋድላ ሰው ከመሆኑም በላይ የትውልድ አገሩም ዋድላ ያውም የነጃ ሚካኤል ቀበሌ ነው፡፡

ዮሐንስ ገብሬ እንዴት ዮሐንስ ገብላዊ ተባለ?

እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ዋድላ የቅኔ ታሪክ የሚጽፉ ሰዎች ሁሉ ዮሐንስ ገብላዊ እያሉ ከመጻፍና ገብሎ ወይም ገብላት በሚባለው የትውልድ ቦታው ምክንያት ገብላዊ ተባለ ከማለት ባለፈ ገብሎ የት እንደሚገኝና ዛሬ ስለ አለበት ሁኔታ አልነገሩንም፡፡ ከቦታው ድረስ በመሄድ በጥናት እንደ ተረጋገጠው ገብሎ የሚባል ቦታ በሦስት ወረዳዎች ውስጥ ይገኛል፡፡ አንዱ በቡግና ወረዳ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዳውንት ወረዳ ውስጥ ይገኛል፡፡ ሦስተኛውና ከዮሐንስ ገብላዊ ስያሜ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ገብሎ የሚገኘው በዋድላ ወረዳ ውስጥ ከደብረ ታቦር ወደ ወልድያ በሚወስደው መንገድ ዐርቢት ከምትባል ትንሽ ከተማ ወደ ቀኝ

ተገንጥሎ 7.5 ኪሎ ሜትር ላይ ነው፡፡ ዐርቢት የምትገኘው ከወረታ ተነሥተን በ172 ኪሎ ሜትር፣ ወይም ከባሕር ዳር 230 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው፡፡ ገብሎ በአሁኑ ጊዜ የምትጠራው ሰጠኝ መንደር እየተባለች ሲሆን ከገብሎ ወደ ሰጠኝ መንደር የተቀየረችበትን ምክንያት፣ የዋድላ ወረዳ ቤተ ክህነት ጎላፊ የሆኑት መጋቤ ሐዲስ አእመረ ዐወቀ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡፡ በዮሐንስ ገብላዊ ዘመንም ሆነ ከዚያ በኋ አካባቢው ገብሎ እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡ በጊዜ ሂደት አካባቢውን ያስተዳድር የነበረ አንድ ሀብታም ሰው፣ አንድ የቅርብ አገልጋይ ነበረው፡፡ በቅንነት ስለ አገለገለውም የገብሎን አካባቢ እንዲጠቀምበት ርስት አድርጎ ሰጠው፡፡ አገልጋዩም ይህ ቦታ ጌታዬ የሰጠኝ ቦታ ነው በማለት ሰጠኝ ብሎ ሰየመው፡፡ ከዚያ በኋላ ገብሎ የሚለው ታሪካዊ ስም ጠፍቶ በምትኩ ሰጠኝ መንደር እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህን ጥናት ስንጀምር ገብሎ የሚባል ቦታ በትክክል በዋድላ ስለ መገኘቱ በወቅቱ የዋድላ ቤተ ክህነት ጎላፊ የነበሩትን መምህር ጠይቀናቸው በዚህ ስም የሚጠራ ቦታ በዋድላ ወረዳ እንደ ሌለ ገልጸውልን ነበር፡፡

ለዚህ አባባል ዋናው ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ገብሎ መንደር ወደ ሰጠኝ መንደር መቀየሩ ነው፡፡ ታሪኩን ከመነሻው ጀምሮ ያልተከታተለ ማንም ሰው ሊያውቀው አይችልም፡፡ በዚህ የተነሳ እኛም በዋድላ ወረዳ ውስጥ አሁን ገብሎ እየተባለ የሚጠራ ቦታ የለም ብለን ጽፈን ነበር፡፡ በባሕር ዳርና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች በቀረበው የጥናት ጽሑፍም፣ “ከዳውንት ወረዳ አስተዳደር በተገኘ መረጃ መሠረት በዋድላ ሳይሆን በጎረቤት ወረዳ በዳውንት ጎብላ የሚባል ቦታ /መንደር/ እንዳለ ገልጸን ነበር፡፡ ይህ ቦታ የሚገኘው ከዋድላ ወደ ደላንታ ከሚወስደው መንገድ ወደ ዳውንት ተገንጥሎ በግምት 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው፣” የሚለው አስተያየት ሠፍሮ

እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ነገር ግን የጽሑፉ ረቂቅ ሲቀርብ የሰሙ ተሳታፊዎች በሰጡት ጥቆማ መሠረት ከዋድላ ወረዳ የስልክ ጥሪ ደርሶን እንደገና ወደ ዋድላ ሄደን ስናጠና የየነጃ ሚካኤል ሊቃውንትና የወረዳው ቤተ ክህነት ጎላፊ፣ መጋቤ ሐዲስ አእመረ ዐወቀ፣ እንደዚሁም የመድረክ ባለሙያው ኩንስንስና /ትክክል ማረፊያው/ የወረዳው የመንገድና ትራንስፖርት ጎላፊ ባሉበት በተደረገው ውይይትና የቦታ ምልከታ የዛሬዋ ሰጠኝ መንደር የቀድሞ ስሟ ገብሎ መንደር እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ቦታ ከደርግ ዘመን ጀምሮ የቅኔ ትምህርት አይሰጥበትም፡፡



ገብሎ መንደር /ሰጠኝ መንደር/ ዛሬ ይህን ይመስላል ከላይ በፎቶ ግራፍ እንደሚታየው ገብሎ መንደር በአሁኑ ጊዜ የእርሻ ቦታ ሲሆን አልፎ አልፎ የአርሶ አደር ቤቶች አለበት፡፡ ገብሎ መንደር ሰፋ ያለ

አካባቢ የሚያካትት ሲሆን በውስጡ አስታ አምባ የምትባል ቦታ አለች። ይህች ቦታ ዮሐንስ ገብላዊ በየነጃ ሚካኤል ደበሎ ማልፊያ አርፎ ከቆየ በኋላ ጉባኤውን ለመጀመሪያ ጊዜ የተከለባት ቦታ ናት። ገብሎ መንደር የሚገኝበት ቀበሌ ስም የነጃ ሚካኤል ይባላል። የነጃና አስታ አምባ ቀደም ሲል አንድ ደብር ነበሩ። አስታ አምባ በአሁኑ ጊዜ የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበት ለብቻው አንድ ደብር ሆኗል። ዮሐንስ ገብላዊ የተወለደውና የዋድላን ቤተ ጉባኤ የመሠረተው በዚሁ በገብሎ መንደር ውስጥ በላስታ አምባ ላይ ነው። ከላይ ለማብራራት እንደ ተሞከረው የአባቱ ስም ገብሬ ሆኖ ሳለ ገብላዊ እየተባለ የሚጠራው ጉባኤውን በጀመረበት ቦታ በገብሎ ነው። በስመ ማኅደር ይጼዋዕ ኀዳሪ እንደሚባለው መሆኑ ነው።

መምህሬ ደምሴ ዋሴ፣ መሪጌታ ጥላሁን ብርሃኔና ሌሎችም የየነጃ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት፣ ዮሐንስ ገብላዊ ለመጀመሪያ ጊዜ መጥቶ ያረፈው ከዚህ ቦታ ነው ብለው የሚያመለክቱት ቦታ አለ። ቦታው ዛሬ የየነጃ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የታነጸበት ደቡባዊ ክፍል ነው። ከግርጌው የታላቁ ኾጣ ሽለቆ የሚገኝበት የገደል ጫፍ ሲሆን ልዩ ስሙ ደበሎ ማልፊያ ወይም ደበሎ መወጠሪያ ይባላል። ለምን ደበሎ ማልፊያ ተባለ? ተብለው ሲጠየቁም የዮሐንስ ተማሪዎች ደበሎ ያለፉበት ስለነበረ ነው ይላሉ። በወቅቱ የዋድላ ተማሪዎችም እንደ ጎጃም ተማሪዎች ልብሳቸው ደበሎ ነበር። ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው መምህሬ ደምሴ ዋሴ ከ150 በላይ የሚሆኑ የዋድላ መምህራን /የነቀኛዝማች ተካልኝ/ ቅኔዎችን በቃላቸው ይዘው በጣፋጭ አንደበት ይናገራሉ። የዋድላ ቅኔ ሲነገር /ሲነበብ/ ምን እንደሚመስል መምህሬ ደምሴ ዋና ማሳያ ናቸው። ረጋ ብለው ተነሽ ተጣዩን፣ ሰያፍ ወዳቂውን ጠብቀው በየቤቱ ቆም በማለት ይናገራሉ እንጂ ዛር እንደ

ያዘው ሰው እየዘለለና እየተወራጨ በፉከራ መልክ አይናገሩም።።
ዮሐንስ ገብላዊ ለመጀመሪያ ጊዜ መጥቶ ያረፈው እዚህ ነው የሚለው አባባል አንድ ነገር ያጭራል።። ዮሐንስ እዚያው የተወለደ ሳይሆን ከሌላ ቦታ የመጣ ያስመስላል።። ለየነጃ ሚካኤል ካህናት፣ ከየት ነው የመጣው? የሚል ጥያቄ ሲቀርብላቸው ሳያመነቱ ከወደ ጎንደር የሚል መልስ ይሰጣሉ።። አንዳንዶቹ እንዲያውም አለፍ ብለው ቅኔውም የጎንደር ቅኔ ነው ይባላል እስከ ማለት ይሄዳሉ።። ከወደ.... የሚለው ቃል የሚያመለክተው አቅጣጫን ነው።። በአጠቃላይ ይህ አባባል የሚያመለክተው ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔን ከሌላ ቦታ እንደ ተማረ ነው።። እውነትም ነው።። ዮሐንስ ገብሬ /ዮሐንስ ገብላዊ/ የቅኔን ሙያ ከሌላ ቦታ ከቀሠመ በኋላ ጉባኤውን ለመጀመር መጥቶ ያረፈበትን ቦታ ነው ደበለ ማልፊያ ብለው የሚጠሩት።። ቅኔውን የተማረውም ከዋሸራ መሆኑን ያመለክታል።። ምክንያቱም ጎንደርና ዋሸራ ለዋድላ በአንድ አቅጣጫ የሚገኙ ናቸው።። ከዋድላ ቀጥሎ መቄትን ካለፉ በኋላ ወዲያው የሚገኘውም ከዋሸራ ይልቅ ጎንደር ነው።። ስለዚህ ዋሸራን ካላወቁት ጎንደርን መጥራታቸው ትክክል ነው።። የተሰጠው መረጃ ትክክል ከሆነ ጎንደር የአባቱ አገር ስለሆነ

ከወደጎንደር መጣ ለማለት አብቅቶ ሊሆን ይችላል፡፡



የነጃ የሚገኘው ደበሎ ማልፊያ ይህ ነው፡፡ ቦታው የሚገኘው አስፈሪ ከሆነ የገደል ጫፍ ላይ ሲሆን ከግርጌው የቸጣ ሽለቆ ይታያል፡፡

ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በጻፉት ዝክረ ሊቃውንት መጽሐፍ መሠረት ተዋነይ፣ ለዕዝራ ሱቱኤል 20ኛ፣ ለዮሐንስ ገብላዊ /ለዋድላ/ 6ኛ መምህር ነው ያሉትን እንደ መነሻ ወስደን ስንመረምር፣ የዋድላው የቅኔ፣ የእርባ ቅምር፣ የዐዋጅና የአገባብ አባት የሆነው ዮሐንስ ገብላዊ የዋሸራ 14ኛ መምህር ነው ማለት ነው። /ዝክረ ሊቃውንት፣ 1963፣ 379/። የጠቅላይ ቤተ ክህነት መጽሐፍ ደግሞ ዮሐንስ ገብላዊ የ18ኛው መምህር የአካለ ወልድ ቀዳማዊ ተማሪ ነው ስለሚል የዋሸራ 19ኛ ተማሪ ተዋነይ ደግሞ፣ ከዋሸራው ተክለ አብ የተማረ 25ኛ ተማሪ ነው ይላል። እኛ ባገኘነው ማስረጃ ደግሞ ዮሐንስ ገብላዊ 23ኛ የዋሸራ ተማሪ ሲሆን ተዋነይ የዋሸራ 27ኛ ተማሪ ነው። ዮሐንስ ገብላዊ የዋሸራ ተማሪ በመሆኑ ሁላችንም ተስማምተን ልዩነቱ 14ኛ፣ 19ኛ፣ ወይም 23ኛ በሚለው ነው /የዋሸራ ታሪክ፣ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ/። ዮሐንስ ገብላዊም ሆነ ተዋነይ ከዕዝራ ሱቱኤል ጀምሮ ሲቆጠር ስንተኛው መምህር እንደሆኑ ልዩነት መምጣቱ ያን ያህል የሚያስገርም አይደለም። ዋናው ነገር ዮሐንስ ገብላዊም ሆነ ተዋነይ የዋሸራ ተማሪዎች መሆናቸው ነው።

ዮሐንስ ገብላዊ ግስን ከነእርባ ቅምሩ፣ ቅኔን ከነአገባቡ ከሠረቀ ብርሃን ዳግማዊ በዋሸራ በወቅቱ በነበረበት ደረጃ ከተማረ በኋላ ወደ የነጃ ሚካኤል መጥቶ ቆይታ አደረገ። ተማሪዎችን በማሰባሰብም በዚያው በየነጃ ቀበሌ ውስጥ ገብሎ መንደር አስታ አምባ ላይ ዝነኛውን የዋድላ ቤተ ጉባኤ መሠረተ።

ብዙ ሊቃውንት ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔውን የጀመረው በገብሎ ሳይሆን አማራ ሳይንት ውስጥ በምትገኘውና የዐፄ ይኩኖ አምላክ ከተማ በሆነችው በደብረ ታቦር ነው ይላሉ። ሁኔታውንም ሲገልጹ፣ በደብረ ታቦር ከተማ ሱባዔ ገብቶ ሲጸልይ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅኔ ተገለጸለት በማለት ነው። በቁራ አንበሳ ጊዮርጊስ

የቅኔ ጉባኤ ከፍተው በማስተማር ላይ የሚገኙትንና በአሁኑ ጊዜ የዋድላ ቤተ ጉባኤ ምሥክር የሆኑትን መሪጌታ አብርሃም ወርቁን ጨምሮ ዋድላዎች፣ ቅኔን ዮሐንስ ገብላዊ የደረሰው በደብረ ታቦር ነው የሚለውን አይቀበሉትም፡፡ ከደብረ ታቦር በፊት ዋድላ፣ ገብሎ መንደር ውስጥ አስታ አምባ ላይ ቅኔን ያስተምር ነበርና፡፡ ወደሳይንት የሄደው በገብሎ ሲያስተምር ከቆየ በኋላ ጉባኤ ለማስፋፋት ነው ይላሉ፡፡ ቅኔውን በሳይንት ቢጀምር ኖሮ ስሙም ገብላዊ አይባልም ነበር፡፡ ወደማያውቀው አገር ወደ ሳይንት የሚያስኬደው ምክንያትም የለም በማለት አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ አጥኝዎችም ይህንኑ አምነን ተቀብለነዋል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔን ራሱ ፈጠረው እንጅ ከማንም አልተማረውም ይላሉ፡፡ ከዋሸራ ከሠረቀ ብርሃን ተማረ የሚለውንም አይቀበሉም፡፡ ከመካከላቸው ደግሞ ቅኔውም የጎንደር ቅኔ ነው ይባላል የሚሉ አሉ፡፡ እንደሚታወቀው በዚያ ዘመን በጎንደር ቅኔ ስለአልነበረ ለዋድላ የጎንደርና የዋሸራ አቅጣጫ አንድ በመሆኑ ጎንደር ያሉት ዋሸራን ነው፡፡ ከዋሸራ ወደ ዋድላ ለመሄድም መንገዱ በጎንደር በኩል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔን ከዋሸራ ከተማረ በኋላ ወደ የነጃ መጥቶ በማረፍ ቆይታ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎችን አሰባስቦ በገብሎ መንደር ጉባኤውን መሥርቷል፡፡ በዚያም በራሱ ፈጠራ ቅኔን በረቀቀ፣ እርባ ቅምርንና አገባብን በጠለቀ መንገድ ማስተማር ጀመረ፡፡ በዚህ ጥናት መሠረት ትክክለኛው ታሪክ ይህ ነው፡፡

ዮሐንስ ገብላዊ ማስተማር የጀመረበትን ጊዜ ወደ 1408 ዝቅ የሚያደርጉ አሉ፡፡ ነገር ግን ዮሐንስ ገብላዊ የነበረው በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ጊዜ እንደ ነበረ ስለሚታወቅ ትክክለኛው ጊዜ በ1427 እና በ1460 መካከል ነው፡፡ በዋድላው አገባብ ላይ የተጻፈውም ይሄው ነው /ጌቱ ገሞራው፣

ያልታተመ የዋድላ አገባብ/፡፡ ከዋድላ ሊቃውንት መካከል /መሪጌታ ተውህቦ ዘውዴ/ ማስተማር የጀመረበት ጊዜ የዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ነው ይላሉ፡፡ እንደሚታወቀው ዐፄ ሱስንዮስ የነበሩት በ17ኛው ክፍለ ዘመን ስለነበረ ይህ አባባል አያስኬድም፡፡ ስለዚህ ትክክለኛው ጊዜ በ15ኛው ክፍለ ዘመን፣ በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡

የዋድላ ቤተ ጉባኤ መሥራች ዮሐንስ ገብላዊ መሆኑን ሊቃውንት ሁሉ የሚስማሙበት ሲሆን ሲያከራክር የቆየው በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅኔን የፈጠረው ዮሐንስ ገብላዊ ነው የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደ ተገለጸው የዋድላ ቤተ ጉባኤ ተከታዮች ዛሬም ቅኔን የፈጠረው ዮሐንስ ገብላዊ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ነገር ግን ከሌሎች መረጃዎች በመነሳት ቅኔን ዮሐንስ ገብላዊ እንዳልፈጠረው ያለምንም ማቅማማት መናገር የሚቻል ሲሆን ዋድላዎች ቅኔን ዮሐንስ ገብላዊ ፈጠረው ሲሉ አንድ እውነት አላቸው፡፡ ከየትም ያምጣው ከየት፣ በዋድላ አካባቢ ቅኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጸው በዮሐንስ ገብላዊ ነው፡፡ ከእርሱ በፊት ቅኔ የሚባል ነገር ይኑር አይኑር ሰምተው አያውቁም፡፡ ለእነርሱ የመጀመሪያው ሰው ዮሐንስ ገብላዊ ነው፡፡ ስለዚህ ቅኔን ዮሐንስ ገብላዊ ፈጠረው ብለው ቢያምኑ ቀዳሚውን እስካላወቁ ድረስ ትክክል ነው፡፡ ጎንጆችም ቅኔን የፈጠረው ተዋነይ ነው ማለታቸው በተመሳሳይ ቅኔን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተዋነይ በመስማታቸው ሊሆን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል በ10ኛው ክፍለ ዘመን በዐፄ አንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ቅኔ በዋሸራ በድህሪም አማካይነት መጀመሩ የታወቀ ስለሆነ ቅኔን ወይም የቅኔን ቤተ ጉባኤ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የጀመረው ድህሪም እንጂ ዮሐንስ ገብላዊ አይደለም፡፡ ከላይ እንደ ተገለጸው ዮሐንስ ገብላዊ ራሱ የዋሸራ ተማሪ እንደ ነበረ የሚገልጽ ማስረጃም አለ፡፡ ዮሐንስ

ገብላዊ ዋሸራ መጥቶ ከመምህር ሠረቀ ብርሃን እንደ ተማረ ከታወቀ ሱባዔ ገብቶ ተገለጸለት የሚለውን ለመቀበል በጣም ያስቸግራል፡፡ ይህን አባባል ዋድላዎችም አይቀበሉትም፡፡

ዮሐንስ ገብላዊ፤ ዮሐንስ ፍልሱፍ እየተባለም ይጠራል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሰውዬው ተመራማሪ እንደ ነበረና ቀደም ሲል ከዋሸራ ያገኘውን ትምህርት በራሱ መንገድ እያሰፋው እንደሄደ ነው፡፡ የጉባኤ ቤት መለያየት የመጣውም ለዚህ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንፊቱ አንድ ነው፡፡ እርሱም ዋሸራ ነው፡፡ ዮሐንስ ገብላዊ ግን ፈላስፋ ስለነበር ቅኔን ከነጓዙ በራሱ መንገድ አሳድጎታል፡፡ በኋለኛው ዘመን የተነሱ ዋሸራዎችም እንደገና ወደዋድላ እየሄዱ ዐዋጅ፣ እርባ ቅምርና አገባብ ይማሩ እንደ ነበር ከእነአለቃ ተክሌ ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ አለቃ ተክሌ የዋድላን እርባ ቅምር በደበሏቸው የውስጠኛው ክፍል ጽፈው መጥተው እንደገና ወደብራና በመገልበጥ ያስተምሩ እንደ ነበር ይነገራል፡፡ እርባ ቅምር ዘአበ ብፁዓን ተክሌ የሚለውም ከዋድላ እርባ ቅምር ጋር ይመሳሰላል፡፡



ዋድላ ቁራ አንበሳ የሚገኘው የቅኔ አብነት ትምህርት ቤት

አሁን ካሉት ሦስቱ ቤተ ጉባኤዎች ሰፊ እርባ ቅምር፣ የተደራጀ ዐዋጅና ጥልቅ አገባብ ያለው የዋድላ ቤተ ጉባኤ ነው፡፡ እንዲያውም በ6ኛው ድድቅ ወልደ ማርያም /ድድቅ የሚለው ቃል ስም እንጅ የደደቀ ዘር ስላልሆነ ይጠብቃል፡፡ ዋድላዎች ሲያነቡትም አጥብቀው ነው/ ጊዜ ጉባኤ ሰፍቶ እርባ ቅምሩ፣ ዐዋጁና አገባቡ ሰባት ደርሶ ነበር ይባላል /ያልታተመ

የዋድላ አገባብ፣ ያሬድ ሽፈራው፣ 2002፣ 8/። ከዚህ በመነሳት፣ ዮሐንስ ገብላዊ ከዋሸራ የተማረውን እርባ ቅምር፣ ዐዋጅ እና አገባብ በራሱ ፈጠራ በማሻሻልና በማስፋፋት ቅኔን ከነጓዙ አሳደገው፤ አመነጠቀው ብሎ ዕውቅና መስጠት ተገቢ ነው።።

ከላይ እንደ ተገለጸው፣ ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔን ማስተማር የጀመረው በዐፄ በእደ ማርያም አባት በዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት /1927-1460/ ዓ/ም ሲሆን ዘመነ መንግሥቱ የማን እንደሆነ ይታወቅ እንጅ ጉባኤ ከፍቶ ያስተማረበት ዓመት ግን በትክክል አይታወቅም።። በግምት ከ1440 እስከ 1450 ባለው ጊዜ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም።። ምክንያቱም የቀለም የልጅ ልጁ ሠምረ አብ ቅኔ ያስተምር የነበረው በ1460 ስለ ነበረ ሁለት መምህራን በተከታታይ የቅኔ መምህር ለመሆን የሚወስድባቸውን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።። ይህም ማለት ቅኔ በዋሸራ ከተጀመረ ከ540 ወይም ከ550 ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው።። ከዮሐንስ ገብላዊ ትምህርቱን ቀስሞ ለተከታዮቹ ያስተላለፈው አባ ወልደ ገብርኤል የተባለ መነኩሴ ነው።። ዐፄ በእደ ማርያም በ1460 በአባታቸው እግር ተተክተው ሲነግሡ ቅኔን ያስተምር የነበረው ሠምረ አብ ወይም ሠምረ ክርስቶስ እየተባለ የሚጠራው መምህር ሲሆን እርሱም የአባ ወልደ ገብርኤል ደቀ መዝሙር ነው።። ዮሐንስ ገብላዊ በዘመነ ዘርአ ያዕቆብ ጊዜ ከዚህ የሚከተለውን ጉባኤ ቃና እንደ ተቀኘ ይነገራል።።

> በመዝሙር እቀኒ በዘዐሠርቱ አውታር
> ለዘርአ ያዕቆብ ጎር ዕበዮ በከመ ያሬድ መምህር

የዮሐንስ ገብላዊ ቅኔ በአወቃቀሩ በዚህ ዘመን ካለው ቅኔ አይለይም።። ቤት መምታቱ ብቻ ሳይሆን የዜማ ልኩን የጠበቀና ሁለተኛው ስንኝ የማረፊያ ሐረግ ያለው ስለሆነ ዕዝል ጉባኤ ቃና ነው።። ዮሐንስ ገብላዊ የተቀኘው ሌላው የዕጣነ ሞገር ቅኔ ደግሞ

በዚህ ዘመን ካለው ቅኔ የተለየ ነው። ቅኔው ከዚህ የሚከተለው ነው።

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ
ቃየል አበሰ እንበይነ ሉድ በላዕለ እኁሁ ቀኒያ
ሶምሶን ተሠግረ በደሊላ ምሥጢረ ነገሩ ኀቡዐ ኀቢያ
ምስለ ፀጉረ ርእሱ ላጸየት ጽንያ
ብጹዕ እምአንስት ዘነየ ተንሢኦ
ለንጉሥነ ዘርዐ ያዕቆብ ከመ ይርድኦ

ስለዚህ ዮሐንስ ገብላዊ ለሁለም ቅኔዎች ልኬታ ያልወሰነላቸውና የዜማ ልክ ያልሠራላቸው መሆኑን ማየት ይቻላል። ሁለተኛው ቅኔ ዛሬ ከሚታወቀው ዕጣነ ሞገር ቅኔ የተለየ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የቤት አመታት ስልቱን ስንመረምረውም አልፋው አ እና ዐይኑ ዐ እየተቀላቀለ የቤት መምቻ ሆነዋል። ስለዚህ ምንም እንኳ የጉባኤ ቃና ቅኔው በሂደት የአደገውን ቅኔ የመሰለ ቢሆንም ዕጣነ ሞገሩ ግን ልክና ወሰን ያልነበረው መሆኑን ያሳያል። ከዮሐንስ ገብላዊ ጀምሮ ባለፉት 550 ዓመታት ውስጥ በአንድ መሥመር ብቻ 22 የመምህራን ትውልድ ተፈራርቋል።

ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔን ማስተማር የጀመረው ከዚህ ቀደም እንደሚባለው በሳይንቱ ደብረ ታቦር ሳይሆን በዋድላ መሆኑን አስረግጦ ማለፍ ተገቢ ነው። ዋድላ የምትገኘው በሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ውስጥ በመቄት ወረዳና በዳውንት ወረዳ መካከል ነው። ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ትውፊት መሠረት በንጉሡ በዐፄ በዕደ ማርያም ጊዜ የዮሐንስ ገብላዊ የቀለም የልጅ ልጅ የሆነው ሠምረ አብ ቅኔን ሲያስተምር ንጉሡ ሰምተው አንተም ሆንክ አባትህ እንዲያው ትቀባጥራላችሁ እንጂ ይህን ትምህርት ከየት አገኛችሁት? ብለው ሠምረ አብን ጠየቁት። ሠምረ አብም ንጉሥ ሆይ ይህ ትምህርት ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለጉ አብረን ሱባዔ ብንገባ

ምሥጢሩ ይገለጽልዎታል ብሎ መለሰላቸው፡፡ በዚያ ዘመን የነበሩ ነገሥታት ፈሪሀ እዚያብሔር ያደረባቸውና ሱባዔን የሚያዘወትሩ ስለነበሩ ንጉሡ ሱባዔ ለመግባት አላመነታም፡፡ በሱበዔ ላይ እንዳለም ለንጉሡ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጸለት ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኘ፣

ድኅረ ተሰብረ አጽንኦ ለሰብእናነ ልሕኵት
ለብሐዊ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት

ዕለቱም ጥር 12 ቀን ስለነበር ጉዳዩን ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምር ከገለጸበት ከቃና ዘገሊላ ጋር በማያያዝ ዐፄ በእደ ማርያም ቅኔውን ጉባኤ ቃና ብሎ ሰየመው፡፡ በመቀጠልም መምህሩ ሡምረ አብና ንጉሡ ዐፄ በእደ ማርያም እየተቀባበሉ እስከ ዕጣነ ሞገር ድረስ ዘርፈዋል፡፡ ንጉሡም ትምህርቱ ደኅና ትምህርት መሆኑን አረጋገጠ በማለት ባልታተመው የዋድላ አገባብ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ /1982/ እና በሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም መጽሐፍ /1963/ ተጽፎ ይገኛል፡፡ መምህራንም ይህንኑ አባባል በቃል ከትውልድ ወደትውልድ ሲያስተላልፉት ኖረዋል፡፡

የጉባኤ ቃናን ትርጉም በተመለከተ ሌሎች መምህራን ደግሞ ሌላ የሚሉት አባባል አላቸው፡፡ ጉባኤ ተቃና፣ ተሳካ ማለት ነው የሚሉ ሲኖሩ በሸዋ ውስጥ ቃና ዘገሊላ በሚባል ቦታ የተደረገ ጉባኤ ማለት ነው የሚሉም አሉ /ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ 1963፣ 172/፡፡ የጉባኤ ቃና ትርጉም ምንም ይሁን ምን ለቅኔዎች ሁሉ ስም ያወጡላቸው ሡምረ አብ እና ዐፄ በእደ ማርያም ናቸው የሚል እሳቤ ግን መያዝ የለበትም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ቅዱስ ያሬድ በዜማ ድርሰቶቹ ለቅኔዎች ስም እንደ ሰጣቸው ተመልክተናል፡፡ ቅዱስ ያሬድ ቅኔን እንደ ጀመረ ማስረጃ ሆኖ የሚጠቀስለትም የቅኔዎችን ስም በዜማ ድርሰቱ በመጥቀሱ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የዋድላ ቅኔ ራሱን የቻለ ቤተ ጉባኤ

ሆኖና ከዋሸራ ተለይቶ መስፋፋት ጀመረ። ከላይ እንዳየነው እነዮሐንስ ገብላዊ /ሠምረ አብ/ የዜማ ልክ ያለው ቅኔ ይቀኙ እንደ ነበር መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ዮሐንስ ገብላዊ ቅኔን በአንድ ደረጃ አሳድጎታል ማለት ይቻላል። የዋድላን ቅኔ ከነአርባ ቅምሩ፣ ከነዐዋጁ እና ከነአገባቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፉት መምህራን ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው /መ.መሠረት፣ የዋድላ አገባብ፣ ያሬድ፣ 2002/፣

መምህር	ተማሪ
ዮሐንስ ገብላዊ	ለአባ ወልደ ገብርኤል
አባ ወልደገብርኤል	ለሠምረ አብ
ሠምረ አብ	ለልሂብ
ልሂብ	ለኤልያብ
ኤልያብ	ለተዋነይ እና
	ለድድቅ ወ/ማርያም
ድድቅ ወ/ማርያም	ለድድቅ ወልደማርያም
ድድቅ ወልደማርያም	ለድድቅ ወልደማርያም
ድድቅ ወልደማርያም	ለድድቅ ወልደማርያም
ድድቅ ወልደማርያም	ለድደቅ ወልደማርያም
ድድቅ ወልደማርያም	ለድድቅ ወልደማርያም
ድድቅ ወልደማርያም	ለድድቅ ወልደማርያም
ድድቅ ወልደማርያም	ለሶልያና
ሶልያና	ለሶልያና ካልዕ
ሶልያና ካልዕ	ለማዕበል ወ/ሕይወት
ማዕበል ወ/ሕይወት	ለጌቱ ገሞራ /ጎንደር/
	ለሊቀ ጎሩያን ዘገየ
	ለተክለማርያም
	ለአለቃ ገብረኢየሱስ
አለቃ ገ/ኢየሱስ	ለአለቃ ቡሩኬ
አለቃ ቡሩኬ	ለአለቃ መርዓዊ/ተንታ
አለቃ መርዓዊ	ለቡሩኬ ወልደ ቡሩክ
ቡሩኬ ወልደ ቡሩክ	ለመ/ር ዲበኩሉ አምባዬ

መ/ዲበኩለ አምባዬ ለመሪጌታ መሠረት ዐሥራት

መሪጌታ መሠረት ዐሥራት ለመ/ዲበኩለ ካልእ /የአሁኑ አቡነ ማርቆስ/ ለመጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ ለመ/ጎሩይ ዘአማኑኤል ለመ/ፌንቴ ዘቢቸና ለቄ/ገ/ሐረገወይን ዘ/ማ ለመ/አብርሃም ዘሞጣ ለመ/በከመ ይቤ እና ለበርካታ ደቀ መዛሙርት የዋድላን ቅኔ ከነአገባቡ አስተምረው ለመምህርነት አብቅተዋል።

መ/ዲበ ኩለ /የአሁኑ አቡነ ማርቆስ/ በጎዛምን ወረዳ ልዩ ስሙ አባ ሊባኖስ በተባለ ቦታ ጉባኤ መሥርተው ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል። ለቅኔ መምህርነት በቅተው ከተመረቁት የቅኔ መምህራን መካከልም አባ ገ/ሥላሴ፣ በደብረ ማርቆስ ገዳመ አስቄጥስ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ የነበሩና አሁን ኢየሩሳሌም የሚገኙ፤ መሪጌታ ዐሥራት አዲስ አበባ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ፤ እና መሪጌታ ዮሐንስ ሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚገኙ ተጠቃሽ የዋድላ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህራን ናቸው።

በዋድላ የመምህራን ሐረገ ትውልድ ውስጥ ከላይ እንደ ተገለጸው ከሚጫው ማዕበል ወልደ ሕይወት የተማሩትን እነ ጌቴ ገሞራውን እና እነ ሊቀ ጎሩያን ዘገየን የመሳሰሉ ታላላቅ ሊቃውንት ይገኛሉ። ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንን እንደሚያስረዱት ጌቴ ገሞራው አባ ነብሮን /ገብረ ሕይወት/ ያስተማሩ ሲሆን አባ ነብሮም መምህር መርዓዊን /ዳንግላ/ አስተምረዋል። መምህር መርዓዊ አሁንም በሕይወት አሉ። ሊቀ ጎሩያን ዘገየም ካፈሯቸው በርካታ መምህራን መካከል መምህር ቃለ ማዕነቅ ይገኛሉ። መምህር ቃለ ማዕነቅ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፊታሒን፣ መምህር

ኃ/ኢየሱስን፣ መምህር ኃ/ኢየሱስም መምህር ወ/ሰንበትንና ሌሎችንም አስተምረዋል፡፡
ሊቀ ጎሩያን ዘገየ በጎዳና ቅኔ አንቱ የተባሉ ታላቅ ሊቅ ነበሩ፡፡ ብዙ የጎዳና ቅኔ ስሞች የሚነገሩት ከእርሳቸው ቅኔዎች ጋር እየተያያዙ ነው፡፡ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህም ይህን መስክረዋል፡፡ የሰበሰቧቸው የጎዳና ቅኔዎችም በአብዛኛው የሊቀ ጎሩያን ዘገየ ቅኔዎች ናቸው፡፡ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚሊኒየሙ መጽሐፍም ሊቀ ጎሩያን ዘገየ ከ500 በላይ የቅኔ ጎዳና ያውቁ እንደነበር መስክሯል፡፡
በሌላ በኩል ደግሞ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው ከመምህር ዲበ ኩሉ አምባዬ በመቀጠል የሚመዘገዝ የዋድላ መምህራንን ሐረገ ትውልድ ይዘው ጉባኤውን በጨጎዴ በማስቀጠል ላይ እንደሆኑ በመጽሐፋቸው አስፍረዋል፡፡ ከቀለምና ከሥጋ ልጃቸው ከመምህር ቅዱስ ያሬድ ጋር በተደረገ ውይይትም ይህንኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ይህ መረጃ በተጠናቀረበት ጊዜ /2008 ዓ/ም/ በቋሪት ወረዳ በጨጎዴ ሐና በርካታ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ሲገኙ መምህር ቅዱስም በባሕር ዳር ከተማ በመንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይህ መረጃ በተወሰደበት ጊዜ /መጋቢት፣ 2008/ እስከ 500 የሚደርሱ የቅኔ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ የዋድላ ቤተ ጉባኤ ዛሬም በእነሊቀ ሊቃውንት ያሬድ በጎጃም እንደ ቀጠለ ነው፡፡
በሌላ በኩልም አለቃ ቡሩኬ አለቃ ከበደን፣ አለቃ ከበደ፣ መርጡለ ማርያም ይሚገኙትን መሪጌታ ሀብተ ኢየሱስ ጋርደውን፣ ሀብተ ኢየሱስ ጋርደውም እዚያው መርጡለ ማርያም ያሉትን ቄሰ ገበዝ ሐረገ ወይን አሻግሬን አስተምረዋል፡፡
ከሁሉም በላይ በጣም አስደሳች ዜና የሆነው የዋድላ ቤተ ጉባኤ በደላንታ ወረዳ፣ ወገልጤና ከተማ

አጠገብ፣ **መስቀለ ክርስቶስ** በተባለ ቦታ በአዳሪ ትምህርት ቤት ደረጃ እንዲቀጥል መደረጉ ነው፡፡ በደላንታ መስቀለ ክርስቶስ የተከፈተው የዋድላ የቅኔ አዳሪ ትምህርት ቤት በመልአከ ሰላም ወልደ ሐና ሲሳይ መምህርነት ፴ ተማሪዎችን ይዞ የተቋቋመ ሲሆን እየሰፋ ይሄዳል የሚል ግምት አለ፡፡ በዋድላ ወረዳም 15 የቅኔ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ በአሁኑ ጊዜ ተማሪ ያላቸው አምስቱ ብቻ ናቸው፡፡ ከእነርሱም ከፍተኛው የተማሪ ቁጥር 66 ነው /መሪጌታ አብርሃም ወርቁ፣ ዋድላ፡ ቁራ አንበሳ፣ የቅኔ መምህር፤ መጋቤ ሐዲስ አእመረ ዐወቀ፣ የዋድላ ቤተ ክህነት ጎላፊ/፡፡ በዚህ ሁኔታ የዋድላ ቤተ ጉባኤ የቅኔ ትምህርቱን እንደ ቀጠለ ነው፡ ሌሎችም የቅኔ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ሊከፈቱ ይችላሉ የሚል ተስፋን ያጭራል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ የዋድላ ቤተ ጉባኤ አስቀጣይ መምህራን እኛ ነን በማለት የሚከራከሩ በሁሉም አካባቢ ብዙ መምህራን ያሉ ቢሆንም ከላይ የተጻፈውን ቅደም ተከተል ወይም ታሪክ የሚያፋልስ አይሆንም፡፡ አንድ ግንድ ብዙ ቅርንጫፍ ስላለው ከግንዱ እስከ ተነሱ ድረስ ትክክል ናቸው፡፡ አስቸጋሪ የሚሆነው ከየትኛውም የዋድላ ቤተ ጉባኤ ገብተው በወጉ ቅኔውን፤ እርባ ቅምሩንና አገባቡን ሳይማሩ ወይም ሙያውን ሳይላበሱ ከሌላው ጋር እየቀላቀሉ ዋድላ ነኝ የሚሉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ እንደተባለው ዋድላ ሰው ሳይናገርለት ራሱ ቅኔው ይናገራል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መነሻቸው ዋድላ ከሆነ ግን ከፈለጉበት ሐረግ ትውልድ ላይ እየተነሱ መቀጠል ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም አንድ መምህር በአንድ ጊዜ በርካታ ደቀ መዛሙርትን አስተምሮ ስለሚያስመርቅና እነዚያም በየበኩላቸው በተለያዩ አካባቢዎች እየሄዱ ጉባኤ መዘርጋት ስለሚችሉ የግድ አንድ ቀጭን ሐረግ መኖር አለበት አይባልም፡፡ በዚህ ጉዳይ መምህራን

እርስ በእርሳቸው መጨቃጨቅ የለባቸውም። ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረው ሐረገ ትውልድ ከአገባቡ ሊቅ ከአለቃ ቡሩኬ በኋላ ዋድላን ጨምሮ በወሎ ያለውን የመምህራን ዝርዝር አላካተተም። በዚህ ጥናት ቅደም ተከተል መሠረት፤ በዋድላ ቤተ ጉባኤ ሐረገ ትውልድ ከ1440/60 ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በአንድ መሥመር 22 መምህራን ጉባኤውን ይዘው ያስቀጠሉ ሲሆን በአማካይ አንድ መምህር ለ25 ዓመታት አስተምሯል ማለት ነው። ይህም ቀደም ሲል ካየነው ከዋሸራ ቤተ ጉባኤ ጋር ተመሳሳይ ነው።

፮ የጎንጅ ቤተ ጉባኤ

የጎንጅ ቤተ ጉባኤ መሥራች ተዋነይ እንደሆነ ሁሉም የሚስማማበት ሲሆን ዘመኑም በ1470 አካባቢ እንደሆነ ይታወቃል /ያልታተመ የዋድላ አገባብ፣ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም 1963፡ 175፣ አድማሱ ጀንበሬ፣ 1963፣ 179፤ መ/ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ፣ 1989፣ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ፤ 2002፣ ሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው፤ 2008፣ መ/ር ሃይማኖት አድማስ፣ የጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምር 2008/። በዘመኑ የነበረው ንጉሥ ዐፄ እስክንድር ይባላል። የዐፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት ከ1470 እስከ 1486 እንደሆነ ስለሚታወቅ /ፍሥሐ ያዜ፣ 2003/ ተዋነይ የጎንጅን ቤተ ጉባኤ በጎንጅ የመሠረተው በዚህ ጊዜ ነው የሚለው የሚያጠራጥር አይደለም።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ደግሞ ግእዝ በቀላሉ በተባለው መጽሐፋቸው /፳፻፷/ ቅኔን የደረሰው ደቀ እስጢፋ እንደሆነ ከዚህ እንደሚከተለው ጽፈዋል። “ወበዘመኑ ለዐፄ እስክንድር ተወጥነ ቅኔ። ወነበረ አሐዱ ኢትዮጵያዊ ዘስመ ደቀ እስጢፋ። ወሖረ ሀገረ ጽርዕ ወተመይጠ ተምሂሮ ፍልስፍና በኋ ሸህ

ወ፱፻፫ወ፪ ዓመተ ዓለም ወደረሰ ቅኔ ውእቱ ወመሀሮ ለዐፄ እስክንድር፡" እንደ ፕሮፌሰር ጌታቸው አጻጻፍ የቅኔ ጀማሪ ያሬድ ወይም ድህሪም ወይም ዮሐንስ ገብላዊ ወይም ተዋነይ ሳይሆን ደቀ እስጢፋ ነው ማለት ነው፡፡ የተለየ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም በላይ እስከዛሬ ድረስ ከአበው ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ዕውቀትና ትውፊት ስለሚያፋልስ አያስኬድም፡፡

በሌላ በኩልም ተዋነይ ቅኔን ያስተምር የነበረው በዐፄ በካፋ ዘመነ መንግሥት /1713-1723/ እንጂ ከዚያ በፊት አልነበረም፣ የጎንጅን ቤተ ጉባኤ የመሠረተውም ተዋነይ ሳይሆን ደቀ እስጢፋ ነው የሚል ተመሳሳይነት ያለው ክርክር አለ፡፡ ይህ ክርክር የታሪክን ፍሰት ስለሚያዛባና ቅኔም ከዐፄ በካፋ በፊት እንዳለ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የጎንጅ ቅኔ ጀማሪ ደቀ እስጢፋ ነው የሚለውን አባባል በጭራሽ አትቀበለውም፡፡ በየትኛውም ቤተ ጉባኤ አገባብ ላይ የጎንጅ ቤተ ጉባኤ መሥራች ደቀ እስጢፋ ነው ብሎ የጻፈ የለም፡፡

ስለዚህ የጎንጅ ቤተ ጉባኤ መሥራች በማያሻማ ሁኔታ ተዋነይ ነው፡፡ ተዋነይ በመጀመሪያ በዋሸራ ከ27ኛው መምህር ኩተክለአብ ዳግማዊ ቅኔን ከነአገባቡ ጠንቅቆ ኩተማረ በኋላ /በዋሸራ የሚገኝ፣ የዋሸራ ታሪክ የእጅ ጽሑፍ/ ወደዋድላ በመሄድ የዋድላ 5ኛ መምህር ከሆነው ከኤልያብ እንደገና ቅኔን ከነአገባቡ በመማር በወቅቱ ተወዳዳሪ የሌለው ሊቅ መሆን እንደቻለ ይነገራል /የዋድላ አገባብ፣ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ ዝክረ ሊቃውንት፣ 1963፣ ሊቀ ሥልጣናት ሀብቱ ማርያም፣1963፣ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ፣ 2002፣ መ/መንገሥቱ ዘለዓለም የፈለገ ፀሐይ ሽብጥ ቅ/ሚካኤል ገዳም የቅኔ መምህር፣ 2008/፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣

ተዋነይን በተመለከተ ዝክረ ሊቃውንት በተባለው መጽሐፋቸው፣ እንደገለጹት ከሆነ፣ ተዋነይ ለዋሸራ 20ኛ፣ ለዋድላ 6ኛ፣ ለጎንጅ ግን 1ኛ ወይም መሥራች ነው /1963፣ 279/፡፡ የጎንጅ መሥራች በመሆኑና ለዋድላ 6ኛ መሆኑ ላይ ልዩነት ባይኖርም ለዋሸራ 20ኛ ነው የሚለው ግን አያስኬድም፡፡ ምክንያቱም የዋሸራ መምህራንን የትውልድ ሐረግ ተከትለን ስንመጣ ተዋነይን የምናገኘው በ27ኛው ሐረግ ትውልድ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ተዋነይ የዋሸራን ቤተ ጉባኤ እና የዋድላን ቤተ ጉባኤ አጣምሮ በመያዝና የራሱን ድንቅ ፍልስፍና በመጨመር አዲስ ቤተ ጉባኤ የመሠረተ የጎንጅ የቅኔ አባት ነው፡፡ ሆኖም ጎንጆች ቅኔን ከዮሐንስ ገብላዊም ሆነ ከዋሸራ ተማረ ብለው አይቀበሉም /ሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው፣ መ/ሃይማኖት አድማስ፣ መምህር ዜና ሥላሴ ዘሊበን፣ የጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር/፡፡ ሁሉም የጎንጅ ሊቃውንት ቅኔን የፈጠረው ተዋነይ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ አባባላቸውን ማክበር ተገቢ ቢሆንም ታሪኩን ለመቀበል ግን በጣም ያስቸግራል፡፡ ትክክል የሚሆነው የጎንጅን ቤተ ጉባኤ የመሠረተው ተዋነይ ነው ካልን ብቻ ነው፡፡

ተዋነይ ከ1470ዎቹ ጀምሮ ግራኝ አህመድ አካባቢውን እስከ ተቆጣጠረበት እስከ 1528/1529 ድረስ ከ50 ዓመታት በላይ ቅኔ የማስተማር ሥራውን በጎንጅ እንደቀጠለ የሚገመት ሲሆን በ1470 ዓ/ም ቅኔ ማስተማር ሲጀምር የ20 ዓመት ወጣት ቢሆን ከግራኝ ሞት በኋላ ከደቅ ገዳም ሲወጣ ዕድሜው ከ80 ዓመት እንደማያንስ መገመት ይቻላል፡፡

ተዋነይ ቅኔውን በጎንጅ እያስተማረ እያለ ግራኝ አህመድ ዐፄ ልብነ ድንግልንና የአካባቢውን ሸማምንት ሁሉ በጦር እያንበረከከ ጎጃም አካባቢ ሲደርስ /ፍሥሓ ያዜ 2003/ ተዋነይ ግራኝን ፊርቶ ወደ ደቅ ሸሸ ይባላል፡፡ ደቅ ማለት በጣና ሐይቅ ውስጥ የሚገኘው ገዳመ ደሴት ሳይሆን በአዊ ዞን

ውስጥ በበላያ በርሀ አካባቢ የሚገኝ ታላቅ ገዳም ነው /አባ ገብረ ሥላሴ የሸንብጥ ፈለገ ፀሐይ አገልጋይ፣ 2008፣ መሪጌታ መንግሥቱ ዘለዓለም፣ 2008፣ መምህር ዜና ሥላሴ የሊበን መድኃኔ ዓለም የቅኔ መምህር፣ 2009፣ መሪራስ አማን በላይ፣ 2000/፡፡ በርካታ የበቁ አባቶች ለምነና የሚመርጡት ቦታ እንደሆነም ይታወቃል፡፡

ተዋነይ ተደብቆ የቆየበትን የደቅን ገዳም በተመለከተ ከታሪክ ጋር አመሳክሮ ማየት ጥሩ ይሆናል፡፡ የታሪክ ተመራማሪና ጸሓፊ የሆኑት መሪራስ አማን በላይ መጽሐፈ አብርሂት በተባለው መጽሐፋቸው /2000፣ 583-590/ እንደገለጹት በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በአክሱምና በአካባቢው በነበሩ ሊቃውንትና በጎጃም አካባቢ በነበሩ ሊቃውንት መካከል የሃይማኖት ክርክር ተነሣ፡፡ ጳጳሱን አቡነ ሚካኤልን፣ ምክትል ጳጳሳቱን አቡነ ገብርኤልንና አቡነ በርተሎሜዎስን ጨምሮ የተወሰኑ የአክሱምና የአካባቢው የሰሜን ኢትዮጵያ ሊቃውንት ቅዳሜ ሰንበተ አይሁድ እንጅ ሰንበተ ክርስቲያን ስለአልሆነች መከበር የለባትም፡፡ ለድንግል ማርያምና ክርስቶስ ለተሰቀለበት መስቀል መስገድና መሳለም አለብን ሲሉ የተድባበ ማርያም ሊቃውንትን ጨምሮ የጎጃም ሊቃውንት ደግሞ ይአቡነ ኤዎስጣቴዎስን ሐሳብ በመከተል ቅዳሜ ሰንበት ናት መከበር አለባት አሉ፡፡ አባ እስጢፋኖስን በመከተል ደግሞ ለቅዱሳን ሥዕልና ለመስቀል መስገድና በጳጳሳትና በቀሳውስት እጅ የሚገኘውን መስቀል መሳም ግን አይገባንም አሉ፡፡ ከዋልድባ መነኮሳትም የዚህ ሐሳብ ደጋፊዎች ነበሩ፡፡ ይህ ክርክር ምእመናንን ለሁለት ስለከፈለ ሁለቱን ወገኖች ለማከራከር ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሰሜን ሸዋ በሞጃና ወደራ ወረዳ ውስጥ ደብረ ምጥማቅ በተባለች ቦታ /አሁን ከሰላ ድንጋይ ከተማ ትንሽ ከፍ ብላ የምትገኝ ቦታ ናት/ ጉባኤ ጠሩ፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ በግብፃዊው በአቡነ ሚካኤል የሚመራው የጳጳሳትና የሊቃውንት

ቡድንና በሊቀ ሊቃውንት ቃለ ወልድና በመምህር አትሮናኦስ የሚመራው የጎጃምና የተድባበ ማርያም የሊቃውንት ቡድን /150 ሊቃውንት/ በንጉሡ ሰብሳቢነት ተሰበሰቡ፡፡ በሊቀ ሊቃውንት ቃለ ወልድ እንዳለ እና በመምህር አትሮናኦስ የሚመራው ቡድንም እነአቡነ ሚካኤል ላቀረቡት የሃይማኖት ክስ መልስ እንዲሰጥ ተጠየቀ፡፡ ከብሉይና ከሐዲስ መጻሕፍትን እየጠቀሱ ረጂም ጊዜ ወስደው ቅዳሜ ሰንበት መሆኗንና ለመስቀል መስገድም ሆነ መስቀልን መሳለም ትክክል እንዳልሆነ፣ ነገር ግን መስቀሉ በተተከለበት ቦታና በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን መስገድ እንደሚገባ መልስ ሰጡ፡፡ በዚህ ጊዜ ጳጳሱ ተናደው እንዲገደሉላቸው ወይም ምላሳቸው እንዲቆረጥ ለንጉሡ አመለከቱ፡፡ ንጉሡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም የጳጳሱን ጥያቄ ሳያቅማሙ ተቀበሉት፡፡ ሆኖም ለጊዜው እርምጃ ከመውሰድ ታግሰውና አስቡበት ብለው በግዞት እንዲቆዩ አደረጉ፡፡ በጎጃም ሊቃውንት ዘንድ የአቋም ለውጥ ስለአልመጣ አፍንጫቸው፣ ምላሳቸውና እግራቸው እየተቆረጠ እንዲሁም በድንጋይ እየተደበደቡ እንዲገደሉ ንጉሡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ወሰኑ፡፡ ብዙዎቹም በውሳኔው መሠረት ተገደሉ፡፡ እነዚህ ከሐዲ /አይሁድ/ ተብለው የተፈረጁት ሊቃውንት በድንጋይ ተወግረው በሞቱበት ቦታ ላይ ድንገት ብርሃን ወረደ፡፡ ዐፄ ዘርአ ያዕቆብም የወረደውን ብርሃን ከተመለከቱ በኋላ በእርሳቸው ጥሩ ሥራ /ከሀድያንን በመግደላቸው/ ብርሃን የወረደ መሆኑን ስላመኑ ቦታውን ደብረ ብርሃን አሉት / የዛፊው የደብረ ብርሃን ከተማ/፡፡ ከዚያ በፊት የደብረ ብርሃን ስም ኤባ ነበር፡፡

የንጉሡና የጳጳሳቱ አቋም በእስጢፋኖሳውያን ላይ በከፋበትና መሥዋዕትነትን በሚጠይቅበት በዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የእንቅስቀሴው መሪ አባ እስጢፋኖስ የተባለው ሊቅ የተረፉትን ሊቃውንት ይዞ ወደጎጃም መጣ፡፡ ከእርሱ ጋር የመጡት

ሊቃውንትም ደቂቀ እስጢፋ ተባሉ በማለት አማን በላይ ጽፈዋል። ይህን ስም ያሰጣቸው አንድም እንደ እስጢፋኖስ በድንጋይ እየተወገሩ እንዲሞቱ በመደረጋቸው፤ ሁለትም የአባ እስጢፋኖስ ተከታይ በመሆናቸው ነው። እነዚህ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሊቃውንት ወደጎጃም አምልጠው ከመጡ በኋላ የመሠረቱት ገዳም ተዋነይ ሸሽቶ የተደበቀበት ገዳም የበለያው ገዳመ ደቅ እስጢፋ ነው። በስመ ጎዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር እንደሚባለው በደቂቀ እስጢፋ /ደቀ እስጢፋ/ ቦታው ደቅ እስጢፋ ገዳም ተባለ። ይህ ታሪክ ጦማረ ትስብእት በተባለው የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ታሪክ ጸሓፊው መሪራስ አማን በላይ ይናገራሉ /መሪራስ አማን በላይ፣ 2000/።

መሪራስ አማን በላይ እንደጻፉት ከእነ አቡነ ሚካኤል ጋር ሊከራከሩ ከሄዱት የጎጃም ሊቃውንት መካከል ከደብረ ወርቅ፣ ከጎንጅና አካባቢው የተመረጡ ሊቃውንት ነበሩበት። ከሞት ተርፈው የደቅን ገዳም ከመሠረቱት መካከልም የጎንጅ ሊቃውንት ይገኙበታል። ስለዚህ ተዋነይ ሸሽት የሄደው አባቶቹ ወደመሠረቱት ገዳም ነው። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ /2007/፣ እንደጻፉት ደግሞ አባ እስጢፋኖስ ተከታይ ሳይሆኑ ለማርያም ሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም የሚለው ንቅናቄ መሪ ነበሩ። በዚህ ሐሳብ ብዙ ሊቃውንት ይስማማሉ። በደረሰባቸው ስቃይ ብዛት የሞቱትም ወደአክሱም ተመልሰው ለስድስት ወራት ከቆዩ በኋላ ስለሆነ ወደጎጃም መጥተው ደቅ እስጢፋ ገዳምን አለመሠረቱም። ገዳሙን የመሠረቱት ሌሎች የእርሳቸው ተካታዮች የሆኑ የጎጃም መነኮሳት ናቸው።

የተዋነይን ፈርቶ መሸሽ በተመለከተ ግን አንድ ጥያቄ ማንሳት የግድ ይላል። በአፈ ታሪክ እንደሚባለው ሲፈልግ ትጓን፣ ሲፈልግ አይጥ፣ ሲፈልግም ሌላ እየመሰለ ማምለጥ የሚችለውና፣

ሲፈልግ ደግሞ በደመና እየተጫነ ከቦታ ወደቦታ መዘዋወር የሚችለው፤ ሲፈልግ ደግሞ መሠወር የማይሳነው ሰው ለምን ግራኝ አህመድን ፈርቶ ወደ ደቅ እንደሸሸ ግልጽ አይደለም፡፡ እንደሚባለው በእርግጥ እስከ መሠወር የሚደርስ ጥበብ የነበረው ሰው ቢሆን ኖሮ ግራኝን ፈርቶ ሊሸሽ አይችልም ነበር፡፡ በቀላሉ እየተሠወረ ሊያመልጠው ይችል ነበርና፡፡ ይህ አባባል በተዋነይ ታሪክ ላይ ሌላ ነገር ያጭራል፡፡ ተዋነይ በእርግጥ ዓለማዊ ጥበበኛ ነበር ወይ? ነበረም አልነበረም ለማለት ያስቸግር ይሆናል፡፡ ይህ ጉዳይ ሰፊ ጥናት ይጠይቃል፡፡ በእኔ እምነት የጎንጅ ቤተ ጉባኤ መሥራቹ ተዋነይ የመሠወርም ሆነ ሌላ ምድራዊ ጥበብ የነበረው ሰው አይመስለኝም፡፡ እርሱ የቅኔ ፈላስፋና ገዳማዊ ሰው የነበረ መሆኑ እንጅ የጥበብ ሰው ስለመሆኑ ማስረጃ ጠቅሶ የሚከራከር ሰው የለም፡፡ መሠወር የሚችል ጥበበኛ ሰው ቢሆን ኖሮ ግራኝን ፈርቶ ወደ ደቅ ሊሸሽ አይችልም ነበር፡፡ ጥበበኛው ወይም አንዳንዶቹ እንደሚሉት ጠንቋዩ ተዋነይ ሌላ ሰው ነው፡፡ በቦታው እንመለከተዋለን፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ግራኝ በወይና ደጋ በጦርነት እስከተገደለበት እስከ የካቲት ወር 1535 ዓ/ም ድረስ በደቅ ቆይቶ የማስተማር ሥራውን ለመጀመር ወደ ጎንጅ ተመለሰ፡፡ ግራኝ አህመድ አካባቢውን የተቆጣጠረው ከ10 ዓመት ጦርነት በኋላ እንደሆነ በተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ተጽፏል /ፍሥሓ ያዜ፤ 2003/፡፡ ስለዚህ ተዋነይ ወደደቅ የገባው በ1528/29 አካባቢ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ግራኝ አህመድ ደግሞ በ1535 የካቲት ወር ላይ ከፖርቹጋል ወታደር በተተኮሰ ጥይት ጎንደር ወይና ደጋ ውስጥ መገደሉ ስለሚታወቅ ተዋነይ በደቅ የቆየው 7 ወይም 6 ዓመት ብቻ ነው፡፡ ተዋነይ የስደት ጊዜውን ጨርሶ ወደ አገሩ ወደጎንጅ እንደተመለሰ የማስተማር ሥራውን ቀጠለ፡፡ ነገር ግን ከደቅ ሲወጣ አገባቡን

አጥፍቶ ቅኔውን ይዞ ስለወጣ ቅኔውን በጥልቀት ከማስተማር አልፎ አገባብና እርባ ቅምር በስፋት ማስተማር አልተቻለውም። በዚህ ምክንያት የጎንጅ አገባብ አጭር ሆነ ይባላል /የዋድላ አገባብ፣ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ 1963፣ 379፣ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ 1963፣ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው 2002/።

ተዋነይ ብዙ የደከመበት እርባ ቅምርና አገባብ ጠፋው ከተባለ ለምን እንደገና መቀጸል አልቻለም? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ለዚህ የሚሰጠው ምክንያት፣ ተዋነይ በደቅ እያለ መምህሩ ኤልያብ ሞቶ ስለነበር እንደገና መቀጸል አልቻለም የሚል ነው። ነገር ግን አብሮት የተማረው የመጀመሪያው ድድቅ ወልደ ማርያም በዳውንት ወረዳ የጨረቃ በምትባል ቦታ እርባ ቅምሩንና አገባቡን እያስተማረ ስለነበር /የዋድላ አገባብ/ ከእርሱ ጠይቆ የጠፋውን ማሟላት ይችል ነበር። ለዚህ የሚሰጥ መልስ ቢኖርም በቂ አይደለም። ስለዚህ ምክንያቱ የመምህሩ መሞት አይደለም ማለት ነው።

በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ተዋነይን ያህል ታላቅ ሊቅ እርባ ቅምርና አገባብ ጠፋው ማለት በእኔ እምነት ዘበት ነው። የጎንጅ እርባ ቅምር እና አገባብ አጭር የሆነበት ምክንያት ሌላ መሆን አለበት። ምንአልባትም በጎንጅ እንደባህል ተወስዶ መምህሩ ከተማሪው ምሥጢር ይደብቅ /ቀለም ይደብቅ/ እንደነበር በገሀድ ይታወቃል። እስከ ዛሬም ድረስ ይህ ሁኔታ አለ። ስለዚህ የእርባ ቅምሩና የአገባቡ ማነስ ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ተዋነይ ገዳም በነበረበት ጊዜ በገዳሙ ያለ መጻሕፍትን ለማገላበጥና የአገባብን ምሥጢር ይበልጥ ለማራቀቅ ዕድል ነበረው። ምክንያቱም አገባብ የወጣው ከ81ዱ መጻሕፍት ስለሆነ በተረጋጋ መንፈስ በገዳም ሲቀመጥ እንደሊቅነቱ ምርምር ማድረጉ አይቀርም። ይህም

ቢቀር ከዋሸራ እስከ ዋድላ እየተንከራተተ ያጠናው አገባብ በ7 ዓመቱ ጠፋው ማለት አያስኬድም፡፡ አገባቡና እርባ ቅምሩ ከጠፋው ቅኔውም አብሮ ይጠፋው ነበር፡፡ እርባ ቅምርና አገባብ የሌለው ቅኔስ ምን ቅኔ ይባላል? እንዲህ ዓይነት ልምድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የለም፡፡ መባል ያለበት ጎንጆች ሙያቸውን ለሌላ ሰው በቀላሉ መግለጽ ስለማይችሉ አገባቡ አሮር ሊሆን ቻለ ነው፡፡ ለጎንጅ አገባብና እርባ ቅምር ማነስ ይህን ይዘን ወደቤተ ጉባኤው ስንመጣ ከጎንጅ ውጭና በተቆራረጠ መልኩ ደግሞ በጎንጅ እስከዛሬ ድረስ ጉባኤው እንደቀጠለ ነው፡፡

ተዋነይ በቦታው እያለ እና ከተዋነይ ቀጥሎ የጎንጅን ቤተ ጉባኤ በመምህርነት የመራው ደቀ እስጢፋ ነው፡፡ ደቅስዮስ እየተባለም ይጠራል፡፡ ዘመኑም የዐፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ ካስተማራቸው ደቀ መዛሙርት መካከልም አንዱ ንጉሡ ዐፄ እስክንድር እንደሆነ ተጽፏል /መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ 1963፤ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፤ 1963፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ 2008/፡፡ ደቀ እስጢፋ ሐዊራ፣ መንክራ፣ እስክንድራ፤ ጳእስክንድራ፤ ብሑር እና አቢዳራ የተባሉ ደቀ መዛሙርትን እንዳስተማረ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ጽፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባሳተመው መጽሐፍም /1980/ እንደዚሁ እነሐዊራ የደቀ እስጢፋ ተማሪዎች እንደሆኑና ድጓውንም በአራት የከፈሉት እነርሱ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ አቋም ወጥ አይደለም፡፡ አንድ ጊዜ ተዋነይን የደቀ እስጢፋ ተማሪ ያደርገዋል፡፡ ቆይቶ ደግሞ ተዋነይን ቀዳሚ ያደርገዋል፡፡ ተዋነይ የነበረበት ዘመን የዐፄ እስክንድር ዘመን መሆኑን ግን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ አረጋግጦ ጽፏል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ደቀ መዛሙርት የቅዱስ ያሬድ ተማሪዎች እንደነበሩ

/መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ፣ ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ፣ 1989፣ 184፣ ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን፣ 1981/ ስለሚታወቅ ታሪኩን ተቀባይነት ያሳጣዋል። እነ ሐዊራ የደቀ እስጢፋ ተማሪዎች ነበሩ የሚለው ስሕተት ነው። እንዲህ ዓይነት ስምም በጎጃም አካባቢ የተለመደ አይደለም።

የተዋነይ ደቀ መዝሙር በነበረው በደቀ እስጢፋ እና በንጉሡ በዐፄ እስክንድር መካከል የወዳጅነትም የመጠፋፋትም ግንኙነት ነበር። ዐፄ እስክንድር በልጅነት ያገቧት ሚስታቸውን ደቀ እስጢፋ በፍቅር ማርኮ ይዟት እንደጠፋ ይነገራል። ንጉሡ ባለቤታቸውን ፍለጋ ብዙ ቢደክሙም ማግኘት አልቻሉም። በዚህ ሁኔታ አገር መታመስ ጀመረ። ምክንያቱም ንግሥትን ያህል ታላቅ ሰው እንደዋዛ ዳብዛው ሲጠፋ አጠያያቂ መሆኑ አይቀርምና። አንድ አዝማሪ ግን ንግሥቲቱን ደቀ እስጢፋ /ደቅስዮስ/ አጥፍቶ በደቅ ደሴት /ጣና ሐይቅ ውስጥ/ ይዟት እንደተቀመጠ መረጃ አገኘ። ለንጉሡ የሚነግርበትን መንገድ ሲፈልግ በአማርኛ ጎብር ቅኔ በዘፈን መልክ ብገልጽ ጥሩ ሳይሆን አይቀርም ብሎ አሰበ። እንዳሰበውም አልቀረ ከዚህ የሚከተለውን ግጥም በዘፈን አዜመ፡

ንግሥቲቱ ንግሥቲቱ
እጇን ተሰብራ ከመሀሉ
ደቃለች አለ ደቃለች አለ

አሁንም ሌላ የታሪክ መምታታት እንዳይፈጠር ማስተዋል ተገቢ ነው። ደቅ የተባለው ጣና ሐይቅ ውስጥ ያለው ደሴት ነው። እስክንድር በዕድሜው ልጅ ቢሆንም ቅኔ በሚገባ ያውቅ ስለነበር /ከደቀ እስጢፋ ተምሮ/ የአዝማሪውን ግጥም መረዳት አላቃተውም። ስለዚህ አጃቢዎቹን አስከትሎ ወደደቅ እስጢፋ ደሴት ተጓዘ። ደቀ እስጢፋንና ወጣቷን ንግሥትም በአንድ ላይ አገኛቸው። በዚህ ጊዜ ደቀ

እሰጢፋ በመርበትበት ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ ዘረፈ ይባላል፤

ይቤ አጋግ ከመዝኑ ሞት መሪር
በጊዜ ረገዞ ሳሙኤል መምህር
ወሰራቁ ንግሥት አነ ደቀ እስጢፋ ጎሡር
አንበሳ እስክንድር እጓለ አንበሳ እንዘ ትጥህር
እምእርአይከ ተጎጠኒ ምድር አለ ይባላል።

ንጉሡም በበኩሉ የደቀ እስጢፋን ቅኔ ካዳመጠ በኋላ ከዚህ በሚከተለው ቅኔ አጻፋውን መለሰ ይባላል፤

ምንት አገበረከ ቁንጽለ ገዳም አንተ ቤተ
አንበሳ በዊአ
ኢትሰምዕኑ ጥሕረቶ በአፍአ
እስመ እምኔየሰ ተጋንዮትከ ጠፍዐ
አንበሳ በሃይሉ እምድኅረ ሞዐ
ጎድግሰ ዘለከ ብፅዐ
ጽንሑ ለእሳት ከዊነከ ብርዐ

ንጉሡ ዐፄ እስክንድር ይህን ቅኔ እንደጨረሰ ደቀ እስጢፋና ንግሥቲቱ ያለበትን ቤት በእሳት አያያዘው። ነገር ግን ጥበበኛው ደቀ እሰጢፋ በጢስ መልክ ንግሥቲቱን ይዞ ጠፋ እየተባለ ይነገራል። ዐፄ እስክንድር ደቀ እስጢፋንና ንግሥቲቱን ያገኛቸው ወደ ደቅ እስጢፋ ደሴት ሂዶ ሳይሆን እዚያው በቤተ መንግሥቱ ግቢ በአንድ እልፍኝ ውስጥ እንደሆነ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ የጻፈው መጽሐፍ ይተርካል። ደቀ እስጢፋ ወደ ደቅ ደሴት የሄደው፣ ደቀ እስጢፋ እና ንግሥቲቱ የነበሩበትን እልፍኝ ንጉሡ፤ በእሳት ሲያቃጥለው በጢስ ተመስሎ ነው የሚል ታሪክም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ጽፏል። ይበልጥ ተቀባይነት ያለው ግን ወደ ደቅ እስጢፋ ደሴት ይዟት ኮበለለ የሚለው ነው። በቤተ መንግሥት ውስጥ ከሆነ ያገኛቸው ቦታው ሰሜን ሸዋ ደብረ ብርሃን ወይም ደቡብ ወሎ አትሮንሰ ማርያም ነው። ቦታው የትም ይሁን የት የነበሩበትን ጎጆ ጽንሑ ለእሳት ከዊነከ

ብርዐ ብሎ በእሳት እንዳያያዘው ያለልዩነት ይተረካል /የዋድላ አገባብ፣ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ 1963፣ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ 1963፣ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው 2002/።።
ደቀ እስጢፋ በእርግጥም ጢስ ሆኖ ከእሳት አምልጦ ከሆነ ከዚያ በኋላ ቅኔውን በጎንጅ ሊያስተምር አይችልም።። ምክንያቱም ንጉሡ ሊያሳድደው ስለሚችል ነው።። ስለዚህ ጌዴዎን ቀዳማዊን ያስተማረው ወደ ደቅ እስጢፋ ንግሥቲቱን ይዞ ከመኮብለሉ በፊት ነው ከተባለ የታሪክ መዛባት አያጋጥምም።። ዐፄ እስክንድር ከንግሥቲቱ ጋር በእሳት አቃጥለው ገድለዋቸው ከሆነ የሞቱት ከ1486 በፊት መሆኑ አያጠራጥርም።። ምክንያቱም ዐፄ እስክንድር የሞቱት ዘሥላስ ከሚባለው የቀድሞ የጦር አበጋዛቸው ጋር በተደረገ ጦርነት በ1486 ስለሆነ ነው።። ዐፄ እስክንድር በአባታቸው በዐፄ በእደ ማርያም እግር ተተክተው የነገሡት ገና በስድስት ዓመታቸው ሲሆን 16 ዓመት አገልግለው በ22 ዓመታቸው በጦርነት ተገድለዋል /ፍሥሓ ያዜ 2003/።። ቅኔውን ከደቀ እስጢፋ የተማሩትም በንግሥናቸው ዘመን ነው ማለት ነው።። ለብሕትውና ግሸን ማርያም ገብተው በዚያው ሞቱ የሚል ታሪክም ተጽፏል /መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ 1989/።።
በሌላ በኩልም ደቀ እስጢፋ ራሱ ተዋነይ ነው የሚሉ እና ተዋነይ የደቀ እስጢፋ ተማሪ ነው ብለው የሚከራከሩ ሁለት ወገኖችም አሉ /ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ 1963/።። ደቀ እስጢፋ የተባለው ተዋነይ ነው የሚለውን ለመቀበል ያስቸግራል።። ምክንያቱም ደቀ እስጢፋ ተዋነይ ከሆነ የንጉሡን ሚስት ይዞ የኮበለለውም ተዋነይ ነው ማለት ነው።። ከታሪክ አኳያ ዘመን ባያፋልስም ለታላቁ ሊቅ ለተዋነይ የሚመጥን ስም አይሆንም።። ተዋነይ የደቀ እስጢፋ ተማሪ ነው የሚለው አባባል

ለጎንጆችም ሆነ ለዚህ መጽሐፍ ደራሲዎች በጭራሽ የሚዋጥ አይደለም። በሌላ በኩልም ደቀ አስጢፋ ቅኔን ከማን ተምሮ ተዋነይን እንዳስተማረ ምንጭ ጠቅሶ የሚከራከር ሰው የለም። ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህም ከደቀ እስጢፋ ተማሪዎች አንዱ ተዋነይ ነው ከማለት ባለፈ ያቀረቡት ትንተና የለም። ማስረጃም አልጠቀሱም።

ደቀ አስጢፋ ወደጽርዕ ወርዶ ጥበብ ተምሮ እንደመጣ ብዙ ሊቃውንት ጽፈዋል። ዘመኑም የዐፄ እስክንድር ዘመን ነው በማለት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ /1980/ ጽፏል። መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ደግሞ ወደ ጽርዕ ወርዶ ጥበብ ተምሮ የመጣው ተዋነይ ነው የሚሉ እንዳሉ ጽፈው አባባሉ ትክክል ሊሆን እንደማይችል የበኩላቸውን ድምዳሜ አስቀምጠዋል /1963፣ 12/። በዚህ መሠረት የጽርዕን ጉዳይ ለደቀ እስጢፋ መተው የተሻለ አካሄድ ነው። የጽርዕን ጥበብ ደቀ እስጢፋ ማምጣቱ አእምሮን በማስፋት ረገድ ለቅኔው መዳበር አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል መገመት ይቻላል። በእኔ እምነት የጎንጅ ቅኔ እንደ ዋድላ ረቀቅ እና ጠበቅ ያለበት ዋናው ምክንያት ደቀ እስጢፋ ወደ ጽርዕ ወርዶ አዲስ ጥበብ በማምጣቱ ሳይሆን የራሱ የተዋነይ የፍልስፍና ብቃት እንዳለ ሆኖ አስቀድሞ የሁለቱም አብያተ ጉባኤ ተማሪ በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም።

ደቀ አስጢፋ ወደጽርዕ ወርዶ ካጠናቸው ሰባት ፍልስፍናዎች መካከል አንዱ ዮናኒ የተባለው ቋንቋ ሰዋስው እንደሆነ ይነገራል። በደመና ተጭኖ መሄድን ጨምሮ ሌሎች ስድስት ጥበቦችንም ይዞ ተመልሷል እየተባለ በስፋት ይነገርለታል /መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣1963፣ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ፣ 2002/። ከሰባቱ ፍልስፍናዎች ተቀባይነት ያገኘው አንዱ ቅኔ ብቻ ነው። ምክንያቱም ቅኔ አስቀድሞ በኢዮጵያ በሚገባ የታወቀ ስለነበረ ነው

ብሎ መውሰድ ይቻላል። ሌሎቹ ከቤተ ክርስቲያን ዓላማ ጋር አብረው የማይሄዱ ስለሆኑ ተቀባይነት አላገኙም ይባላል። በዚህ አባባል መሠረት ቅኔ ከውጭ ሀገር የመጣ ፍልስፍና ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ጭራሽ ሊሆን የማይችል ነው። ድሮም ሆነ ዛሬ የኢትዮጵያን ቅኔ የመሰለ በየትም የለም /አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤1948፤ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፤ 1963/። መምህር ዓለማየሁ ሞገስም በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ሐተታ መጻፋቸውን ምልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ከላይ በተገለጸው መጽሐፍ ጽፈዋል።

ከላይ በዝርዝር በተገለጸው አመክንዮ መሠረት የመጀመሪያዎቹ የደቀ እስጢፋ ተማሪዎች እነሐዊራ ሳይሆኑ እነጌዴዎን ናቸው የሚለውን ይዘን የመምህራኑን የትውልድ ሐረግ መቀጠል የተሻለ ነው።

ተዋነይ ደቅስዮስን /ደቀ እስጢፋን/ አስተማረ ብሎ ተነስቶ ደቀ እስጢፋ በበኩሉ ጌዴዎን ቀዳማዊንና ሌሎችን አስተማረ ከተባለ ታሪኩ ይቃናል። የመምህራኑን የትውልድ ሐረግ ከማየታችን በፊት ግን ስለተዋነይ ካልዕ ማንነትና ዘመነ ሕይወት ማብራራት ተገቢ ነው። ምክንያቱም የተዋነይ ማንነት ብዙ ሰዎችን እያወናበደ ስለሆነ ነው።

ጥበብና ተዋነይ ካልእ

ለመሆኑ ተዋነይ ካልእ ማነው? ተዋነይ ካልእ እንደተዋነይ ቀዳማዊ የጎንጅ ተዋላጅ ሲሆን አባቱ ድልያኖስ፣ እናቱ አቡዬ፣ ወንድሙ አርኪለደስ፣ እኅቱ ደግሞ አደይ ይባላሉ። ይህ ታሪክ በአካባቢው ሕዝብ በስፋት ይነገራል /መምህር ሃይማኖት አድማስ፤ ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንን፣ መምህር አንተነህ/። የነበረበት ዘመንም የ18ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነው። በዚህ ጥናት መግንዘብ እንደተቻለው አንድ የተምታታ ታሪክ ተፈጥሯል። ፍሥሓ ያዜ የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ

ኢሕአዴግ 2003 በሚል ርእስ በጻፈው አንደኛ መጽሐፍ ገጽ 356 ላይ በዐፄ በካፋ ዘመን ተዋነይ የሚባል ደብተራ ነበር ካለ በኋላ ከንጉሡ መጥፎነት ጋር አያይዞ ከዚህ የሚከተለውን ጽፏል፤

ከመጥፎ መናፍስት ትምህርት እንደቀሰመ ከሚነገርለት ከደብተራ ተዋነይ ጋርም ገጠሙ፡፡ ልዩ ልዩ የመናፍስት ጥበብን ለማወቅና ለመማርም ተጉ፡፡ በመሐልም የደብረ ብርሃን ሥላሴ ካህናት ሌት ተቀን ሱባዔ ገብተው እየተላቀሱ በነበረበት ጊዜ ድንገት የዐፄ በካፋ ሞት ተሰማ፡፡ በ1723 ዓ/ም የሞቱበት ምክንያት /ዐፄ በከፋ/ ተብሎ የሚነገረውም የአስማተኞችን ጥበብ ለማድነቅና ለመተግበር ሲሉ በደብተራ ተዋነይ ጥበብ በአየር ላይ ሲሄዱ ድንገት የተሰጣቸውን ትእዛዝ /ገቢር/ ተላልፈው ኖሮ አለት ላይ ተፈጥፍጠው ነው ይላል፡፡ በመጀመሪያ ይህ የሐሰት ወሬ ነው ዐፄ በካፋ በሱባዔ ላይ እንዳለ ታሞ ነው የሞተው /መሪራስ አማን በላይ፤ 2009፤ 265/፡፡

ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንንም ዕሴተ ትሩፋት ዘቅዱስ ያሬድ ወትምህርተ ቃል በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ ገጽ 49 ላይ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጂራ በገጽ 176/177 ላይ ያሰፈሩትን /ዶ/ር ሥርግው ገላው፣ 2008/ ጠቅሰው እንደጻፉት ዐፄ በካፋ በዘመኑ ከክፉ ሥራ በቀር አንድ ቀን በጎነት ሥራ አልሠራም፡፡ ያን ጊዜ ተዋነይ የሚባል የጎንጅ ደብተራ ጠንቋይ ነበረው በማለት አለቃ ተክለ ኢየሱስ የታላቁን የቅኔ አባት ታሪክ አጉድፈው በመጻፋቸው ቁጭታቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደሚታወቀው የጎንጅ የቅኔ አባት ታላቁ ሊቅ ተዋነይ ያስተምር የነበረው ከዐፄ እስክንድር /1470-1486/ እስከ ዐፄ ገላውዴዎስ /1532-1551/ ድረስ ነው፡፡ ግራኝ አህመድ ከ1519 እስከ 1527 በተደረገው ጦርነት ዐፄ ልብነ ድንግልን አሸንፎ ወደመሪነት የመጣውና ቤተ መንግሥቱን ደንቢያ ላይ የመሠረተው ከ1527 እስከ 1535 ዓ/ም አጋማሽ

ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ዐፄ በካፋ ደግሞ በመሪነት ላይ የቆየው ከ 1713 እስከ 1723 ዓ/ም ነው /ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል አሰከ ዐፄ ቴዎድሮስ፤ 1953/፡፡ ቀዳማዊ ተዋነይ የቅኔ ትምህርቱን ይከታተል የነበረበት ዘመን 1460 መሆኑ ከታወቀ የተወለደው ደግሞ በ1446 አካባቢ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በዚህ ስሌት መሠረት በዐፄ እስክንድር ዘመን /1470-1486/ ጉባኤውን በጐንጅ የመሠረተው ተዋነይ እና በዐፄ በካፋ ዘመን የነበረው ተዋነይ አንድ ሰው ነው ከተባለ ተዋነይ በሕይወት የቆየው ከ270 ዓመት በላይ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የማይታመን ነው፡፡ ስለዚህ ተዋነይ በሚል ስም የተጠሩ **ሁለት ሰዎች ነበሩ** ማለት ነው፡፡ እንደአጋጣሚ ሆኖ የጥበብ ነገር ከጐንጅ መምህራን ጋር ሁልጊዜ አብሮ ይወራል፡፡ ይህ የጥበብ ሥራ ከደቀ እስጢፋ ጋርም ይያያዛል፡፡ በዚህ መሠረት የሦስቱ የቅኔ ሊቃውንት ታሪክ ባልጠራ መንገድ ከጥበብ ጋር እየተያያዘ በተምታታ ሁኔታ ስለሚነገር የጐንጅ ቅኔ መሥራች የተዋነይ ታሪክ እየጎደፈ ነው፡፡ ችግሩም የሚመነጨው ከጎንጅች ድብቅነት ጋር ተያይዞ ነው፡፡

ስለዚህ ሌላ ተዋነይ የሚባል የጎንጅ የቅኔ ፈላስፋ በዐፄ በካፋ ዘመን እንደነበር በታሪክ ተረጋግጧል /ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፣ በዶ/ር ሥርግው ገላው እንደ ተዘጋጀ ፣2008፣ 176፣ ፍሥሓ ያዜ 2003፣256፣ ሊቀ ጎሩያን በላይ መኮንን 2006፣ 49፣ መሪራሰ አማን በላይ፣ 2009፣ 262/፡፡

መሪራስ አማን በላይ /2009፣ 262-263/ እንደሚለው፣ ተዋነይና ዐፄ በከፋ በልጅነታቸው በደብረ ወርቅ፣ በደብረ ጺማ /አዴት አቡነ ዘርአ ቡሩክ/ እና በጎንጅ አብረው ቅኔ ከመማራቸውም በላይ በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ዐፄ በካፋና ተዋነይ ከዕለታት አንድ ቀን በሜዳ ላይ ደጅ እየወጡ እያሉ ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ በማለት ተዋነይ ለበካፋ

ጥያቄ አቀረበለት፡፡ የጉሥ ልጅ ስለነበር እኔማ በአባቴ በኢያሱ ዙፋን ተቀምጬ የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆን እፈልጋለሁ ሲል ተዋነይ ደግሞ በተራው እኔስ የቅኔ መምህርና የደብር አለቃ መሆን ነው የምፈልገው አለ፡፡ ዐፄ በካፋ ምኞቱ ተሳክቶለት ንጉሥ ከሆነ በኋላ ተዋነይ የቅኔ ስጦታ ሊያቀርብለት ወደጎንደር ሄዶ ሳለ በለበሰው ልብስ የተነሣ ወደግብር ቤት አትገባም ተብሎ ተከለከለ፡፡ እርሱም በስጨት ብሎ የጓደኛዬን የበካፋን ግብር ለምን ትከለክሉኛላችሁ ብሎ በመናገሩ ክብረ ነክ ነገር ተናግረኻል ተብሎ ታሰረ፡፡ በካፋ እስረኞችን ሲጎበኝ ተዋነይ በእስር ቤት ሆኖ ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ አቀረበለት፣

በካፋ ኢተርሣዕ ዘተዋነይነ ክልኤነ
እንዘ አበ አብርሃም አንተ ወብእሲተ
አብርሃም አነ፡፡

በዚህ ቅኔ ምክንያት በካፋ የልጅነት ጓደኛውን አስታውሶ ከእስር ቤት አውጥቶ ብዙ ነገር ሰጠው፡፡ ተዋነይ፣ መሰወር፤ በደመና ተጭኖ መሄድ ወዘተ ቢችል ኖሮ አይታሰርም ነበር፡፡ ስለዚህ ሁለተኛው ተዋነይም ጠንቋይ ወይም ባለጥበብ አልነበረም፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ግን ሁለት ተዋነይ የሚባሉ የጎንጅ ሊቃውንት መኖራቸው አይታወቅም ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ተዋነይ የሚለው ስም እንኳ የወጣለት በጥበቡ ምክንያት ነው ይባላል፡፡ ጉዳዩም እንደዚህ ነው፤

ከዕለታት አንድ ቀን ተዋነይ ካልእ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ እየሄደ እያለ ሽፍታዎች አላሳልፈው ይላሉ፡፡ ተዋነይም በጥበቡ ራሱን ወደትኋን በመቀየር በነጋዲዎች አቆማዳ ላይ ተለጥፎ አለፋቸው፡፡ እንዴት እንዳለፈ ነጋዴዎች ሲጠይቁትም ትኋን ሆኜ /መስዬ/ አለፍኩ አላቸው፡፡ አንተ ትኋን ነህ እንዴ ብለው ደግመው ሲጠይቁት አዎ ትኋን ነኝ ብሎ ደገመላቸው፡፡ ይህን ሲገልጽ የሰሙ ነጋዲዎች ትኋን ነኝ የሚለውን ሐረግ ሸረፍ አድርገው ተዋነይ

አሉት ይባላል፡፡ አፈ ታሪኩን መቀበል ቢያስቸርም ይህን አባባል የአካባቢው ሕዝብ በስፋት ያወራዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ተዋነይ የጭዋታ ለዛ ያውቅ ስለነበር በዚህ ምክንያት ተዋነይ ተባለ እንጂ መደበኛ ስሙ ይስሐቅ ነው ይላሉ /መምህር ጥዑመ ልሳን ልየው ዋሽራ/፡፡ ስለተዋነይ ጥበብ የሚነገረው እጅግ ብዙ ነው፡፡ ከጥበቦቹ መካከል ትምህርት እንዲገባ የሚያደርግ አብነትም ይችል ነበር ይባላል፡፡ እንደማስረጃም የሚነገረው ከዚህ የሚከተለው አፈ ታሪክ ነው፤

ትምህርት አልገባው ብሎ ለሰባት ዓመታት ያህል ጉባኤ ቃና እየቆጠረ የተቀመጠ አንድ ተማሪ ነበር፡፡ ይህ ተማሪ ከዕለታት አንድ ቀን ሁሉም ተማሪዎች ወደክብረ በዓል ሄደው ሳለ ብቻውን በግቢው ውስጥ ነበር፡፡ ተዋነይም በአካባቢው ያለ ተማሪ እርሱ ብቻ ስለነበር በቅሎውን ከታሠረበት ፈትቶ እንዲያመጣለት አዘዘው፡፡ ተዋነይ ተማሪውን ስምህ ማነው ብሎ ሲጠይቀው **አህዮ** ነው የምባለው አለው፣ ለምን አህዮ እንደተባለም ታሪኩን በዝርዝር ሲነግረው አዘነለትና በሌላ ቀን በወጥ አድርጎ መድኃኒት ሰጠው፡፡ መድኃኒቱ እንቅልፍ ስለሚያስወስድ ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ ቅኔ እንዲዘርፍላቸው ተዋነይን ጠየቁት፡፡ ተዋነይም አህዮ ይዝረፍላችሁ አላቸው፡፡ የሚቀልድ መስሏቸው ደጋግመው ጠየቁት፡፡ የዕውነቱን እንደሆነ ሲረዱ አህዮን ከተኛበት ቀስቅሰው ዝረፍልን አሉት፡፡ እርሱም ከእንቅልፉ እንደነቃ ሙሉ ቤት ዘረፈላቸው ይባላል /መ.ሃይማኖት እና የአካባቢው ሕዝብ/፡፡ በሌላ በኩል ግን ለአህዮ ትምህርት እንዲገባ የሚያደርግ መድኃኒት የሰጠው ተዋነይ ሳይሆን የእመይቴ ገላነሽ ሐዲስ አያት የሆኑት መሪጌታ ኪዳናት ናቸው የሚል ክርክር አለ /መሪጌታ ኪዳኑ/፡፡ ቦታው ቅርብ ለቅርብ ከመሆኑ የተነሳ የታሪክ መወራረስና መነጣጠቅ ሊኖር ይችላል፡፡ የእመይቴ

ገላነሽ አያት የሚለው ግን ሌላ ነገር ያሞራል። እሱም ተዋነይ ካልእ የቅርብ ዘመን ሰው መሆኑን ያመለክታል። ወደ ተዋነይ ስንመለስ አደይ የምትባል እኅት እንደነበረችው ይታወቃል። አደይ ከእለታት አንድ ቀን ለሌላ ሰው በወጥ የተዘጋጀ መድኃኒት አግኝታ ሳታውቅ ከምግብ ጋር ወሰደችው። እርሷም በበኩሏ ምሥጢር ተገልጸላት እንዲህ አለች ይባላል፣

ጌጤር እንበለ ጌጤር
ለልብከ አልቦቱ ምሥጢር

ጌጤር ማለት የተዋነይ ጥበብ ስም ነው። ተዋነይ ይህን ከእኅቱ ሲሰማ መድኃኒቱን በድንገት አግኝታ እንደተጠቀመችበት ገብቶት እንዲህ ብሎ በቅኔ መለሰላት ይባላል

አደይ እንበለ አደይ
ለገጽኪ አልቦቱ ላሕይ

ተዋነይ እንደ አኅቱ አደይ የምትባል ላም ነበረችው። እኅቱ አደይ የላሚቱን የአደይን ቅቤ እየተቀባች ፊቷን ታወዛ ነበር። ስለዚህ አመዳም ነሽ ለማለት ይህችን ቅኔ ተቀኘላት። ለዚሁ ጥናት ከአካባቢው ተወላጆች ጋር በተደረገ ውይይት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እና ሌሎችም ጉዳዮች ከተዋነይ ጋር ተሳስረው ይነገራሉ። ተዋነይ በጥበቡ የማይሆነው እንዳልነበረ በስፋት ቢነገርም፡ በዚህ መጽሐፍ አዘጋጆች እምነት ውሸት ነው። መልአከ ነበልባል በሚል የማዕርግ ስም እና ፈለገ ቅኔያት በሚል የሙያ ስም ይጠራ የነበረው ተዋነይ በካፋ ኢትርሳዕ ዘተዋነይነ ክልኤነ የሚለውን ቅኔ ለዐፄ በካፋ ያቀረበው እስር ቤት ሆኖ ነው። ዕፀ መሰውር ቢኖረው ኖሮ ለምን ታሰረ? /አማን በላይ 2009፣ 262-263/።

ተዋነይ ካልእ ጊዜው ሲደርስ በዚያው በጎንጅ ሞቶ እንደተቀበረ ይነገራል። ተዋነይ አልሞተም፣ እስከዛሬ ድረስ በሕይወት አለ የሚሉም አሉ።

ሌሎቹ ደግሞ ሥራዬን አልጨረስኩም ብሎ የመጣውን መልአክ ሞት ለሰባት ዓመታት ከደጁ ገትሮት ነበር ይላሉ፡፡ የሚባለውን ጻፍነው እንጂ እንደ ነቢዩ ኤልያስ፣ እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ መንፈሰ እግዚአብሔር ያደረበት ኃይል መንፈሳዊ ያለው ሰው ካልሆነ በስተቀር እግዚአብሔር የላከውን መልአክ አንድ ሥጋዊ ጥበብ ያለው ደብተራ ያቆመዋል ማለት ትክክል እንዳልሆነ መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡ ታሪኩን የሚያውቁ የአካባቢው ተወላጆች እንደሚናገሩት /መምህር ሃይማኖት፣ መምህር አንተነህና ሌሎች/ ግን ተዋነይ አርኪለደስ ከተባለው ወንድሙ ጋር እንደሞተና እህቱ አደይ ስታስለቅስ ከዚህ የሚከተለውን እንደተቀኘች ይነገራል፤

ተዋነይ ጨረቃ አርኪለደስ ጸሐይ
ደመና ሞት መጥቶ ሰወራችሁ ወይ
ተዋነይ ወይናችን አብቦ ሳያፍር
በረዶ ሞት መጥቶ ደባለቀው ካፊር

በማለት የሰምና ወርቅ ቅኔ በአማርኛ አስለቀሰች ይባላል፡፡

ተዋነይም አስቀድሞ ሞቱን አውቆ ስለራሱ ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ እንደ ተቀኘ ይነገራል፤

እፈርህ አንሰ ወእርዕድ፤ እምነ ኀምስቱ ግብራት እለ ሀለዉ ምስሌየ፤
አሐዱ በሞት እንዘ ትትፈለጥ ነፍስየ፤
ወካልእ መቃብረ ሥጋ ትወርድ ሥጋየ፤
ወሣልስ ለአምላኪየ፤ እንዘ ቅድመ ገጹ እቀውም ይርዕዱ አባላትየ፤
ራብዕሂ ፍትሐ ኩነኔ አመ ትሰምዕ እዝንየ፤
ወኀምስ መንግለ ደይን እንዘ ይወስዱኒ አፅራርየ፤
ወዝ ኩሉ፤ ነገር እምይኩን ብየ፤
ከሢኖተ ማይ እምኀየሰኒ በማሕፀነ ቅድስት ወላዲትየ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ይህ ቅኔ የቀዳማዊ ተዋነይ ቅኔ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ፡፡ በአጥኚው እምነት በሁለት ምክንያት ይህ ቅኔ የዳግማዊ ተዋነይ ቅኔ ነው፡፡

1ኛ/ ቅኔው የዜማ ልኩን የጠበቀና የመወድስን የቅኔ ወሰን የተከተለ ነው፡፡

2ኛ/ ቀዳማዊ ተዋነይ ገዳማዊ ስለነበር ሞትና ኩነኔ የሚያስፈራው ሰው አይደለም፡፡ ዳግማዊ ተዋነይ ግን ቅስጥ አብዝቶ ስለነበር ሞትና ኩነኔን መፍራቱ አይቀርም፡፡ ሌላም ይህን የመሰለ ቅኔ አለው፡፡

ስለዚህ ቅኔው ወደኋለኛው ዘመን ማለትም ወደ 18ኛው ክፍለ ዘመን ሄዶ የሚመደብ ቅኔ ነው፡፡ የታሪክ ፍሰቱን ተከትለን፣ የታተሙና ያልታተሙ መጻሕፍትን ዋቢ አድርገን፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የአባቶቻችንን ትውፊት መሠረት ይዘን ስንመለከተው **እርግጠኛ መሆን የሚቻለው ተዋነይ የሚባሉ ሁለት የቅኔ መምህራን ስለመኖራቸው ነው፡፡** ታሪኩን በየፈርጁ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡

ቀዳማዊ ተዋነይ የቅኔን ትምህርት ያስተማረው ለረጂም ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ትውልድ በትውፊት መልክ የተላለፈ አንድም ቅኔ አልተገኘም፡ በይዘታቸው የሁለተኛው ተዋነይ ማለትም የ18ኛውን ክፍለ ዘመን ቅኔዎች የሚመስሉ ሌሎች ቅኔዎችም አሉ፣ ቅኔዎችም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ዋዜማ ቅኔ /ዘተዋነይ ካልእ/

የአምን ወይገኒ፣ ኵሉ ዓለም በዘፈጠረ ለሊሁ፣
ካልኣን እንዘ ይትኤዘዙ ይስግዱ ቅድሜሁ፣
ለጠይቆ ዝኒ ነገር ከመ እስራኤል ይፍርሁ
ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ
ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ

ይህ ቅኔ በይዘቱ አነጋጋሪ ቅኔ ነው፡፡ በመጀመሪያ ሙሴ ፈጣሪውን እንደፈጠረ እና በኋላ ደግሞ ፈጣሪ ሙሴን እንደ ፈጠረ ይገልጻል፡፡ ፈጠረ አወቀ የሚል

ግስ ባይኖርም አወቀ፣ መሰለ፣ አከበረ የሚል ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሞጋች /ተፎካካሪ/ ቅኔ በትክክል የ18ኛው ክፍለ ዘመን ቅኔ ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

መወድስ ቅኔ /ዘተዋነይ ካልእ/

ቦኑ ተአምር ከመ ይትቀነዩ፣ ለበረድ በረድ ወመብረቅ ለመብረቅ?
ለምንት ውእቱ ተቀንዮትከ በወርቅ
ዕሩቅ ብእሲ ለብእሲ ዕሩቅ
ዓለመ ሕይወቱ ዘየኀልቅ
ወሰማየ ዐፅሙ ይትከደን፣ ደመና-መቃብር ዕሙቅ
በኢዮር እንዘ ሀሎ አምላከ ኢዮር ምጡቅ
ዘይፈትሕ በኃጥዕ ወይፈትሕ ለጻድቅ
አምጣነ ጽጌ ዓለም ሠርፀ መደልዋን አዕጹቅ
ጽባሐ ይሠርፅ ወሠርከ ይወድቅ

ተዋነይ ለረጂም ዓመታት ቅኔን ማስተማሩ የጎንጅ ቅኔ ሥር እንዲሰድ አድርጎታል ብሎ ማደማደም ይቻላል፡፡ ደቀ መዝሙሩ ደቅስዮስም /ደቀ እስጢፋ/ ለቅኔ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህም ለጎንጅ ቅኔ ምጥቀት ሌላው ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በኋላ የጎንጅ መምህራንን የትውልድ ሐረግ መናገር ተገቢ ነው፡፡ እርሱም እንደሚከተለው ቀርቧል፣

መምህር	ተማሪ
ተዋነይ	ለደቀ እስጢፋ
ደቀ እስጢፋ	ለጌዴዎን ቀዳማዊ
ጌዴዎን ቀዳማዊ	ለጌዴዎን ዳግማዊ
ጌዴዎን ዳግማዊ	ለጌዴዎን ሣልሳዊ
ጌዴዎን ሣልሳዊ	ለጌዴዎን ራብዓዊ
ጌዴዎን ራብዓዊ	ለተዋነይ ዳግማዊ
ተዋነይ ዳግማዊ	ለመምህር ሳህሉ

መምህር ሳህለ
መምህር ወሰኔ
መ/ተክለ ሕይወት
ገ/ማርያም
ኪዳነ ማርያም
ገብረ ዮሐንስ
አለቃ ዶሪ

ዕቡይ ካሳ
ገብረ ሕይወት አዲስ
ዕጹብ
ጥበቡ ደስታ

ለመምህር ወሰኔ
ለመምህር ተ/ሕይወት
ለገ/ማርያም
ለኪዳነ ማርያም
ለገ/ዮሐንስ
ለአለቃ ዶሪ
ለቄሰ ገበዝ በቃ እና
ለዕቡይ ካሣ
ለገብረ ሕይወት አዲስ
ለዕጹብ /ጎንደር
ለጥበቡ ደሰታ/ሜጫ
ለሊቀ አእላፍ ገዳሙ

ሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው በአሁኑ ጊዜ በዚሁ በባሕር ዳር የካህናት ማሠልጠኛ ኮሌጅ ጎላፊ ሆነው ቤተ ክርስቲያኗን በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ አብዛኛው የመምህራን ዝርዝር የተገኘውም ከእርሳቸው ነው፡፡ በጎንጅ አገባብ ላይ ናሁ ወጠንኩ ጽሒፈ ሰዋስው ዘተክለ ሕይወት፣ ወገብረ ማርያም፣ ወኪዳነ ማርያም፣ ወገብረ ዮሐንስ መምህራነ ጎንጅ ስለሚል ለመምህራን ቅደም ተከተል ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ከዝርዝሩ እንደምንረዳው ተዋነይ ካልእ 7ኛ የጎንጅ መምህር ነው፡፡ መምህር ዶሪ በጎንጅ ያስተምሩ ነበር የሚለው መረጃ የተገኘው ከመሪጌታ ጥዑመ ልሳን ገ/ጊዮርጊስ መጽሐፍ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መምህር ዶሪ የጎንጅ ቅኔ ባለሙያ እንጂ በጎንጅ ጉባኤ ዘርግተው አላስተማሩም የሚሉ አሉ፡፡

ምንም እንኳን ወደላይ ርቆ መሄድ የሚችል መረጃ ማግኘት ባይቻልም በቅርብ ዘመን መሪጌታ ጥላሁን በጎንጅ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ዘመኑ መምህር ጥበቡ ደስታ በሜጫ የጎንጅን የቅኔ ሙያ ያስተምሩ የነበረበት ጊዜ ነው፡፡ በመቀጠልም መሪጌታ ሞላ የሚባሉ መምህር በቦታው ተተክተው እንደተለመደው የጎንጅን ቤተ ጉባኤ መሠረት አድርገው ቅኔ ያስተምሩ እንደነበረ አሁን

በሕይወት ያሉ ሰዎች ሁሉ ያውቃሉ። ከእርሳቸው በመቀጠልም አባ ወልደ ጊዮርጊስ የሚባሉ መምህር የጎንጅን ቅኔ ሲያስተምሩ ቆይተው መሪጌታ ሃይማኖትን በቦታቸው በመተካት ወደባሕር ዳር መጥተዋል። አሁን በሕይወት የሉም። መሪጌታ ሃይማኖትም በበኩላቸው በባሕር ዳር የሰላም አርጊው ማርያም የቅኔ መምህር ሆነው ቦታ ሲቀይሩ በቦታው ማለትም በጎንጅ መሪጌታ ይባቤ የተባሉት ወጣት መምህር ተተክተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ሆኖም ጉባኤው በጣም ቀዝቃዛ ከመሆኑ የተነሳ አለ የሚባል አይደለም። አልፎ አልፎ ተማሪዎች ቢኖሩም ቁጥራቸው በጣም ትንሽ ነው።

በሌላ በኩልም የሸምብጥ ፈለገ ፀሐይ አንድነት ገዳም የቅኔ መምህር የሆኑት መሪጌታ መንግሥቱ ዘለዓለም እንደሚያስረዱት የዕቡይ ካሳ ተማሪ የሆኑት መምህር ገብረ ሕይወት፣ መምህር ዕፀብንና መምህር ስብሐቱን አስተማሩ። መምህር ስብሐቱ መንክር ግጨውን፣ መንክር ግጨውም መሪጌታ መንግሥቱን፣ መሪጌታ መሠረት ዐሥራትንና ሌሎችንም አስተምረዋል። መሪጌታ መንግሥቱ አሁንም በማስተማር ላይ ይገኛሉ። መሪጌታ መሠረት ዐሥራትም የዋድላን ሙያ ከመማራቸው በፊት ቅኔና አገባብ ከግጨው መንክር ተምረዋል።

በጎንጅ በአንድ መስመር 19 መምህራን ማስተማራቸውን የሚገልጽ ማስረጃ በብዙ ድካም የተገኘ ሲሆን አንድ መምህር በአማካይ ሲወሰድ ለ28 ዓመታት ያህል አስተምሯል። ከቀዳማዊ ተዋነይ እስከ ዳግማዊ ተዋነይ ድረስ የነበሩ መምህራን በአማካይ ያስተማሩት 36 ዓመት ሲሆን ከዳግማዊ ተዋነይ እስከ ሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው ወይም እስካለንበት ዘመን ድረስ ያሉት መምህራን በአማካይ ያስተማሩት 24 ዓመት ነው። ይህም ከዋሸራና ከዋድላ ጋር ተቀራራቢ ነው።

በመረጃ አያያዝና ታሪኩን ጠብቆ በማስተላለፍ በኩል በጎንጅ ትልቅ ክፍተት አለ፡፡ ከቦታው ድረስ ሄዶ መረጃ ለመሰብሰብ ሲሞክር እንኳ ለማነጋገር ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ ይህም ባለመሆኑ ቤተ ጉባኤውን እየጎዳው ነው፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ታሪኩ ጭራሽ ሊጠፋ ይችላል የሚል ሥጋት አለ፡፡ የጎንጅ የቅኔ ሙያና ታሪክ የጎንጅ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሙያና ታሪክ ነው፡፡ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክም ነው፡፡ የጎንጅ ታሪክ መታወቅ በመጀመሪያ የሚያስከብረው ራሱን ደብረ ጥበብ ጎንጅን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ በሚል ርእስ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ባሳተመው መጽሐፍ ገጽ 138 ላይ ጎንጆች ሙያቸውን ለማካፈል እንደማይፈልጉ ተገልጿል፡፡
የዋሽራን፣ የዋድላንም ሆነ የጎንጅን የመምህራን የትውልድ ሐረግ በአንድ ወጥ ዝርዝር ማጠቃለል አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድ የቅኔ መምህር በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ መምህራንን አስተምሮ ሊሸኝ ስለሚችል ነው፡፡ እነዚህ መምህራንም በየቦታው ጉባኤ ሲተክሉ የየራሳቸውን የትውልድ ሐረግ እየመዘዙ የማይቆጥሩበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህም የተነሳ በአሁኑ ጊዜ እያንዳንዱን ቤተ ጉባኤ የምንወክል እኛ ነን እያሉ የሚፎካከሩ መምህራን ብዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በጣሊያን ተገድለው እዚያው ዋሽራ የተቀበሩት መምህር ገብረ ማርያም/ዋድሌ/ ማዕበል ፈንቴን፣ ግጨው ገብሬን፣ ወ/ዮሐንስ ዘላስታን፣ አለቃ ደለለኝ ካሳ ዘአዴትን፣ አለቃ ብሩ ዘዳውንትን፣ አስካል ዘበጌምድርን፣ አለቃ በቀለ ዘደብረ ወርቅን፣ መምህር ይኄይስ ወርቁ ዘደብረወርቅን፣ ውቤ ገ/ማርያምን፣ ፀቃውዕ ገ/ማርያምን፣ ነቢየ ልዑል በጽሐን፣ /ነቢየ ልዑል መንግሥቱ/ መሪጌታ መንግሥቱ ዘደብረ ማርቆስን

እና ሊሎች ከ230 በላይ የሆኑ የቅኔ መምህራንን አስተምረው በወሎ፣ በጎንደር እና በጎጃም ጉባኤ እንዲተክሉ አድርገዋል /በዋሽራ የሚገኝ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ/፡፡ እነዚህ ሁሉ የዋሽራን ሐረግ ከገብረ ማርያም ጀምሮ እየመዘዙ ቢቆጥሩ ስሕተት ነው ሊባል አችልም፡፡

በዚህና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የመመህራን የትውልድ ሐረግ መፋለሱ አያስገርምም፡፡ በተለይ የቅኔ ሙያ ይበልጥ እየተዳከመ ከመጣበት ከደርግ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ያለው የየጉባኤ ቤቱ የትውልድ ሐረግ ይበልጥ እየተፋለሰ መጥቷል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም በአቱን /ቦታውን/ ሳይለቅ የቀጠለው የዋሽራ ቤተ ጉባኤ ብቻ ነው፡፡ የዋድላን ብንወስድ ከመምህር ዲበ ኩሉ አምባየ ጀምሮ በአብዛኛው ወደ ጎጃም መጥቷል፡፡ በእርግጥ በዋድላም እንደቀጠለ ነው፡፡

የጎንጅ ቤተ ጉባኤም በመምህር ገ/ሕይወት አዲስ አማካይነት ወደትግራይ ሄዶ ከቆየ በኋላ በመምህር ዕፁብ ዘትግራይ አማካይነት በጎንደር በኩል ተሸጋግሮ በመምህር ጥበቡ ደስታ አማካይነት እንደገና ወደ ጎጃም /ሜጫ/ ተመልሷል፡፡ የትግራይ ሊቃውንት ለጎንጅ ቅኔ ትልቅ ፍቅር እንዳላቸው ማየት ይቻላል፡፡ ከመምህራን ዝርዝር እንደምንመለከተው አብዛኛዎቹ የትግራይ ተወላጆች ናቸው፡፡ ስለዚህ ታሪኩ በስፋት ቢጠና ዛሬም በትግራይ የጎንጅ ቅኔ በብዙ ቦታ ሊገኝ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

በጎንጅስ የቅኔ ትምህርት የተቋረጠበት ዘመን አለ ወይ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ትክክለኛ መልስ መስጠት የሚቻል አይመስለኝም /ከጎንጆች ድብቅነት የተነሳ/፡፡ በሌላ ጥናት መረጋገጥ አለበት፡፡ ወደትግራይና ወደጎንደር ተሰዶ ሄዶ ቆይቶ በመምህር ዕጹብ ደስታ ተመልሶ የተባለው በመረጃ እጥረት ምክንያት እንዳይሆን ሥጋት አለኝ፡፡ ምክንያቱም በጎንጅ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩ መምህራን

መካከል፣ ከቅርቡ ብንነሳ፣ አሁን በጎንጅ የሚገኙት መምህር ወሀቢ፣ መምህር ሃይማኖት አድማስ፣ መምህር ወልደጊዮርጊስ፣ መምህር ሞላ፣ መምህር ጥላሁን የሚባሉ መምህራን እንደነበሩ ይታወቃል። ይህን መሥመር ተከትሎ እስከ ላይ ድረስ ቢኬድ ከላይ ከተገለጸው ውጭ የሆነ የመምህራን ሐረግ ትውልድ ሊገኝ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ስለዚህ ከላይ የተገለጸው የጎንጅ የመምህራን ሐረግ ትውልድ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መሥመሩን ጠብቆ የተዘጋጀ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ይህን ዝርዝር አይቶ እነእገሌ ቀርተዋል የሚል ጥያቄ ቢነሳ ስሕተት ነው ሊባል አይችልም። ምክንያቱም በየመሥመሩ በርካታ ዝርዝር ማዘጋጀት ይቻላልና። ቅኔን ነቢያት ይጀምሩትም ቅዱስ ያሬድ ይጀምረው ደልዳላ አገሩ ጎጃም ነው። መነሻውም ዋሸራ ነው። እርግጥ ነው ዋድላዎች እርባ ቅምርንና አገባብን እንደገና ፈጠሩት ማለት ይቻላል። እስከ ዛሬም ድረስ ዋድላን በሰዋስው ዐዋጅ፣ በእርባ ቅምርና በአገባብ የሚወዳደር የለምና።

ምዕራፍ ሁለት
፯ ዐዋጅ

ዐዋጅ የአንድ ድንጋጌ ይዘት አጭር መግለጫ ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዐዋጅን ሲተረጉሙ ለሕዝብ የሚነገር፣ የንጉሥ ሕግና ደንብ፣ ውሳኔ፣ ማለት ነው ይላሉ። ዐዋጅ እያንዳንዱን ነጠላ ሕግ በዝርዝር እንዲገልጽ አይጠበቅም። ዐዋጅ በጣም ጥቅል በመሆኑ እርሱን የሚተረጉሙ ሌሎች ሕጎች ያስፈልጉታል። ለምሳሌ ዐዋጅን ተከትሎ ደንብ፣ መመሪያና ማንዋል ይወጣል። በዐዋጅ ያልተብራሩ ጉዳዮች ሁሉ በደንብና በመመሪያ ግልጽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በቅኔ ትምህርት ዐዋጅ ማለት መባል ያለባቸውንና የሌለባቸውን፣ ትክክል የሆኑትንና ያልሆኑትን በአጭሩ ለይቶ የሚያሳይ፣ የሚነገርና የሚያሳውቅ ሕግ ሰዋስው ማለት ነው፡፡ ዐዋጅ ወደዝርዝር ሳይገባ ጠቅለል ያሉ ጉዳዮችን በማሳየት ዝርዝሩን ለእርባ ቅምርና ለአገባብ ያስተላልፋል፡፡

ዐዋጅ በሰባት የሚከፈል ስለመሆኑ፤

ከዚህ ቀደም ሲነገር እንደምንሰማው በ6ኛው ድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ በዋድላ ጉባኤ ሰፍቶ ሰባት እርባ ቅምር፣ ሰባት ዐዋጅ፣ ሰባት አገባብ ደርሶ ነበር፡ ይባላል፡፡ እርባ ቅምር እና አገባብ በሌላ ምዕራፍ ይገለጻለ፡፡ ዐዋጅን ግን በተወሰነ ደረጃ ገባ ብቦ መዘርዘር ተገቢ ነው፡፡ በመጀመሪያ ሰባቱ ዐዋጆች እነማን እንደ ሆኑ ዝርዝራቸውን ላስቀድም፣

1. ከመነሻው / ሰዋሰው በሁለት ይከፈላል ከሚለው ጀምሮ እስከ ነገረ ሙሻዘር ድረስ/፣
2. ነገረ ሙሻዘር፣
3. ዘመድ ዝርዝር
4. ባዕድ ዝርዝርና ባዕድ በራሱ፣
5. ደላይ ተደላይ
6. ባዕድ ቅጽል
7. ነገረ ሠረገ ናቸው

ሀ. ዐዋጅ የሚጀምረው ከባለሁለት ጉዳዮች ወይም ርእሶች ሲሆን ሁለት ጉዳዮችን የያዙ ርእሶችን ሲያጠቃልል ወደባለ ሦስት ጉዳዮች ይሸጋገራል፡፡ በመቀጠልም ወደ አራት፣ አምስት፣ ስድስት ወዘተ

እያለ አንደኛው ዐዋጅ እስከ አስራ አንድ ድረስ ይዘልቃል። በዚህ መሠረት በዚህ መጽሐፍ የተገለጹት የመጀመሪያዎቹ ዐዋጆች ይዘትና ቅደም ተከተል ከዚህ የሚከተለውን ይመስላል።

፩. ሰዋስው በሁለት የሚከፈል ስለመሆኑ

፪. ሰምና ወርቅ በሁለት ባለቤቶች የሚመሰል ስለመሆኑ፤

፫. ዘማች ግስ የማይነሳባቸው ቀለማት ሁለት ስለመሆናቸው

፬. የዘማች ግስ ሁሉ መድረሻዎች ሁለት ስለመሆናቸው

፭. ወ በማጫፈር የሚያወርዳቸው ሦስት ስሞች ብቻ መሆናቸው

፮. ሳይጠሩ የሚያሥሩ አንቀጾች ሦስት ብቻ ስለመሆናቸው

፯. ተጠርተው የሚያሥሩ አናቅጽ ሦስት ብቻ ስለመሆናቸው

፰. ባዕድ ቀለማት ሦስት ስለመሆናቸው

፱. ዘርፍ ከባለቤት በሦስት ነገሮች የሚያያዝ ስለመሆኑ

፲. አሥራው ትንቢት/አሥራው ቀለማት አራት ስለመሆናቸው፣

፲፩. የመጠሪያ ስሞች ዓይነት አራት ስለመሆናቸው፣

፲፪. ሰሚ የሚሆኑ ተውላጠ ስሞች አራት ስለመሆናቸው

፲፫. አሰሚ የሚሆኑ ጉዳዮች አራት ስለመሆናቸው

፲፬. ወደፊት እንጅ ወደኋላ የማይስቡ ርእሶች አራት ስለመሆናቸው

፲፭. ተናባቢያን አራት ስለመሆናቸው

፲፮. አፅማድ የሚባሉት አምስት ስለመሆናቸው

፲፯. ነባር የሚባሉት አምስት ስለመሆናቸው፣

፲፰. ፍርቅ የሚባሉት አምስት ስለመሆናቸው፣
፲፱. ን የሚሆኑ ደቂቅ አገባባት አምስት
ስለመሆናቸው፣
፳. የዘማች ግስ መነሻዎች አምስት
ስለመሆናቸው፣
፳፩. ሰ የሚያነሳቸው ቀለማት አምስት
ስለመሆናቸው፣ /ዝ እና ዘ ከተጨመሩ ፯
ናቸው/፣
፳፪. በራሳቸው ጀምረው በራሳቸው የሚጨርሱ
ግሶች አምስት ስለመሆናቸው፣
፳፫. መሣገር የሚባሉት አምስት
ስለመሆናቸው፣
፳፬. ዝርዝር የሚሆኑ ቀለማት ስድስት
ስለመሆናቸው፣
፳፭. ግስ ሁሉ ከሰባት የማይወጣ ስለመሆኑ፣
፳፮. ቅጽሎች ሰባት ስለመሆናቸው፣
፳፯. አራት ቀለማት ሰባት አገባባትን
የሚያመጡ ስለመሆናቸው፣
፳፰. ምእላድ የሚባሉ ስምንት ስለመሆናቸው፣
፳፱. የሚስቡ አናቅጽ ስምንት ስለመሆናቸው፣
፴. ለ በዘጠኝ ነገሮች የሚፈታ ስለመሆኑ፣
፴፩.በ በዘጠኝ ነገሮች የሚፈታ ስለመሆኑ፣
፴፪. ወደ የሚሆኑ አገባባት ዐሥር
ስለመሆናቸው፣
፴፫. ችልታ የሚሆኑ አገባባት ዐሥራ አንድ
ስለመሆናቸው፣

በመጨረሻም በሰምና ወርቅ ምሳሌ ጊዜ ጸያፍ የሚሆኑና የማይሆኑ ነገሮች ተተንትነዋል። በዚህ ዐዋጅ ውስጥ በአጭር በአጭሩ ትንታኔ እና ድንጋጌ ይሰጣል። ከዚህ የተረፈው ደግሞ በእርባ ቅምር እና በአገባብ በዝርዝር ይገለጻል።

ወደ ዐዋጅ ከመግባታችን በፊት ሰዋስው የሚለውን ቃል ተርጉመንና የጋራ አድርገን ማለፍ ተገቢ ነው።

ለመሆኑ ሰዋስው ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መጻሕፍትን ማገላበጥ ስንጀምር፣ አለቃ ታየ ገብረ ማርያም፣ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ የዋድላ ዐዋጅና የጎንጅ ዐዋጅ ለሰዋስው የሰጡት ትርጉም ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሰዋስው መሰላልና መሸጋገሪያ ተብሎ በሁለት ነገር ይፈታል፡፡ ሰዋስው ስለምን መሰላል ተባለ? ቢሉ፤ በመሰላል ከታች ወደላይ ይወጡበታል፣ ከላይ ወደታች ይወርዱበታል፡፡ በሰዋስውም በእግረ ሕሊና ሰማየ ሰማያት ወጥቶ፣ ዕመቀ ዕመቃት ወርዶ በዐይነ ልቡና ምሥጢረ ሥላሴን ያዩበታል፡፡ መሸጋገሪያ /ድልድይ/ ያለውስ እንደ ምንድን ነው? ቢሉ በመሸጋገሪያ ከወዲህ ወዲያ፣ ከወዲያ ወዲህ ይመላለሱበታል፡፡ በሰዋስውም ከድንቁርና ወደጥበብ፣ ካለማወቅ ወደማወቅ ይመላለሱበታልና ሰዋስው ተባለ በማለት ይመሠጠራል / ታየ፣ 1943፣ 9/፡፡

ሰዋስው ቋንቋን በትክክል ለመግለጽና ለመግባባት ያስችላል፣ መጻሕፍትን አቃንቶ በትክክል ለማንበብ ያስችላል፣ እንዲሁም መጻሕፍትን ለመተርጎምና ለማመሥጠር ያስችላል፡፡

በጎንጅ ዐዋጅ ደግሞ በተጨማሪ ደብር ወይም ተራራ ተብሎም ይመሰላል፡፡ ተራራ ከወጡት በኋላ ሁሉን ያሳያል፡፡ ሰዋስውም ከተማሩት በኋላ ሁሉን ያሳውቃል፡፡ ሰዋስው በመጽሔትም /መስትዋት/ ይመሰላል፡፡ መስትዋት ክፉና በጎውን ማለትም የሰውነትን ጉድፍ እንደሚያሳይ ሁሉ ሰዋስውም ከተማሩት በኋላ ክፉና ደጉን፣ ጸያፉንና ትክክለኛውን ያሳያልና፡፡ ሰዋስው ቋንቋን በትክክል ለመግለጽና ለመግባባት ያስችላል፡፡ መጣሕፍትን አቃንቶ በትክክል ለማንበብ ያስችላል፣ መጻሕፍትን ለመተርጎምና ለማመሥጠር ያስችላል፡፡ ስለዚህ ዐዋጅ በስነፍጥረት ጀመረ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ዐዋጅ፣ ሁለት ጉዳዮችን በያዙ ድንጋጌዎች ጀምሮ ዐሥራ አንድ ጉዳዮችን

በሚያብራሩ አገባባት፣ ክፍል አንድን ይጨርሳል። በመቀጠልም ሙሻዘርን፣ ዘመድ ዝርዝርን፣ ባዕድ ዝርዝርን እና ባዕድ በራሱን፣ ባዕድ ቅጽልን፣ ደላይ ተደላይን፣ ሠረገን፣ እንዲሁም በሚመሰሉና በማይመሰሉ ጸያፎች ትንታኔዎች ይጨርሳል። ዐዋጅን በሁለት ጉዳዮች መጀመር ስለተለመደ ነው እንጂ የግስ ሁሉ መድረሻ አንድ ብቻ ነው ብሎ አንድ ጉዳይ ብቻ በያዘ ዐዋጅ ቢጀምር የተሻለ ነበር። ሆኖም በአብነት ትምህርት ቤቶች በተለመደው አግባብ በመቀጠል መሆን የሚገባውን በማብራሪያ ማስተካከል መርጠናል።

ክፍል አንድ

ሁለት ሁለት ጉዳዮችን የያዘ ዐዋጅ፤

፩. ሰዋስው

በመጀመሪያ ሰዋስው የሚለውን ቃል ተርጉሞ መግባቱ ተገቢ ነው። ሰዋስው ማለት ቃል በቃል ሲተረጎም ወይም ምሳሌያዊ ትርጉሙ መሰላል ማለት ሲሆን ምሥጢራዊ ትርጉሙ ግን ከዚህ እንደሚከተለው ነው፤

- ፩፥ የቋንቋ መጽሐፍ /መዝገበ ቃላት/ ማለት ነው።
- ፪፥ ሥርዐተ ትምህርተ ግእዝ /ሕገ ልሳነ ግእዝ/ ማለትም የቋንቋን ሕግና ሥርዐት የምናጠናበት የትምህርት ዓይነት ነው። ሊቃውንት ሰዋስውን በተለያዩ ምሳለየዎች ማለትም በተንከተም /ድልድይ/፤ በመጽሔት/መስታወት/፤ በመነጽር/ መነጸር/፤ በደብር/ተራራ/፤ በሐመር/መርከብ/ እና በመሳሰሉት መስለውታል።
- ፫፥ ሰዋስው በያዘው ቃል ሲተረጎም ወይም በመሰላልነቱ ሲተረጎም ሰዎች ለሥራ ጉዳይ ወደ ላይ የሚወጡበት፣ ወደ ታች የሚወርዱበት፤ ባለብዙ ዕርከን ከእንጨት

ወይም ከብረት የሚሠራ መሣሪያ ነው። በመሰላል ወደ ላይ ኤኔደሚወጣበትና እንደሚወረድበት በሰዋስውም ከሰሚዕ ወደ ለብዎ፣ ከርእይ ወደ ነጽሮ፣ ከኢያእምሮ ወደ አእምሮ ይሄዱበታል።

፪፥ በድልድይ መመሰሉ በተንከተም ከወዲያ ወዲህ፣ ከወዲህ ወዲያ እንደሚሸጋገሩበት በሰዋስውም ካለማወቅ ወደ ማወቅ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከጥበብ ወደ ጥበብ ይሸጋገሩበታልና።

፫፥ በመጽሔት መመሰሉ፣ በመጽሔት የፊት ነውርን፣ የዐይን ጉድፍን ያዩበታል። በሰዋስውም የተዛባውን ንባብ፣ ይጠመመውን ምሥጢር ያቀኑበታል።

፬፥ በመነጽር መመሰሉ፣ መነጽር የዐይን ቤዛ እንደ መሆኑ የብርሃን ጨረር፣ የምድር አቧራ እንከላከልበታለን። በተጨማሪም የራቀውን አቅርቦ፣ የረቀቀውን አጉልቶ ያሳየናል። በሰዋስውም የከበደውን ንባብ እንተረጉምበታለን፣ ረቂቁን ምሥጢር እናመሠጥርበታለን።

፭፥ በደብር /ተራራ/ መመሰሉ፣ ከተራራ ላይ በወጣን ጊዜ ሜዳው፣ ኮረብታው፣ ወንዙ፣ ሸንተረሩ፣ ሸለቆው ሁሉ እንደሚታየን ሰዋስውንም በአግባቡ ተምረን ካወቅነው የተሰወረውን ንባብ ትርጓሜና ምሥጢር እናውቅበታለን።

፮፥ በሐመር /መርከብ/ መመሰሉ፣ በመርከብ ተሳፍረን ጥልቅና ሰፊ ሐይቆችንና ታላላቅ ውቅያኖሶችን አቋርጠን እንደምንሻገር፣ በሰዋስውም መጻሕፍትን እንተረጉምበታለን። በእግረ ልቡና ወደ ዕመቀ ዕመቃት እንወርድበታለን። ከአድማስ እስከ አድማስ

እንደርስበታለን። በክንፉ ሕሊና አየረ አየራትን እንመጥቅበታለን።

ሰዋስው ሁለት ዓይነት ሲሆን በውስጡ ዐዋጅን፣ አገባብን፣ ነጠላ ግስንና እርባ ቅምርን ያጠቃልላል።
ከላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ሰዋስው የሚባሉት ሁለት ናቸው። እነርሱም ዘር እና ነባር ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ሰዋስው የሚባሉት ሁለት ሳይሆኑ አምስት ናቸው የሚሉ አሉ። አምስት የተባሉትም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩. ዘር /ሳቢ ዘር/ ፬. ቦዝ አንቀጽና ዘንድ አንቀጽ
፪. ንዑስ አንቀጽ ፭. ቅጽል
፫. ዐቢይ አንቀጽ

በዋድላ አገባብም ሆነ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዐዋጅ መሠረት ሰዋስውን በአምስት መክፈል አያስኬድም። ምክንያቱም፣ ከላይ የተጠቀሱት አምስቱ ሁሉ ዘር ብቻ ናቸው እንጂ ነባርን አያጠቃልሉም፣ ከዘር ቀጥሎ የተዘረዘሩት አራቱም ከመጀመሪያው ከዘር የሚገኙ ናቸው። ምክንያቱም ከዘር ንዑስ አንቀጽ፣ ከንዑስ አንቀጽ ዐቢይ አንቀጽ፣ ከዐቢይ አንቀጽ ቦዝ አንቀጽና ዘንድ አንቀጽ፣ ከቦዝ አንቀጽና ዘንድ አንቀጽ፣ ቅጽል /ግልስ ቅጽል፣ ሳድስ ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል ወይም ፣ መስም ቅጽል፣ መድበል ቅጽል/ ይገኛሉና። ስለዚህ አምስት ናቸው የሚለው አከፋፈል ነባርን ስለማያካትት ትክክል ነው ተብሎ አይወሰድም። አናቅጽ ከርባታ ጋር በተያያዘ ያላቸው ስያሜ የተለያየ ቢሆንም በዚህ መጽሐፍ ዐበይት አናቅጽ ማለት ትንቢት፣ ትእዛዝ ሲሆኑ ንዑሳን አናቅጽ ደግሞ ዘንድ፣ ቦዝ፣ እርእስት ናቸው። ከንዑስ አንቀጽ ቀጥለው የሚገኙት ርባታዎች በሙሉ ደቂቅ ናቸው።
ዘር ሲባልም፣ ዘመድ ዘር፣ ጥሬ ዘር፣ ጥሬ ምዕላድ፣ ባዕድ ዘር፣ ባዕድ ከምዕላድ፣ ጥሬ ምዕላድ ተካተው

መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ከላይ የተገለጸው ቀመር በምሳሌ ሲገለጽ፣ ነደ የሚለውን ግስ ወስደን ብንመለከት፣ ንዴት ከሚለው ሳቢ ዘር፣ ነዲድ ነዲዶት የሚለው ንዑስ አንቀጽ ይወጣል፡ ከነዲድ ነዲዶት፡ ነደ የሚለው ዐቢይ አንቀጽ ይወጣል፡፡ ከነደ፣ ነዲዶ የሚለው ቦዝ አንቀጽ፣ ይንድድ የሚለው ዘንድ አንቀጽና ትእዛዝ፣ እንዲሁም ቅጽል ይወጣሉ፡፡ ቅጽል ማለትም ሣልስ ቅጽል፣ ሳድስ ቅጽ፣ ባዕድ ቅጽል /መስም ቅጽል/፣ መድበል ቅጽል ተጠቃለው ነው፡፡ ይህም በአዳም ተፈጥሮ ይታወቃል፡፡ አዳምን አርባዕቱን ባሕርያት ፈጥሮ ፈጥሮታልና፡፡ ስለዚህ እርባ ቅምር በዐቢይ አንቀጽ፣ ዐዋጅ በዘር /በስነ ፍጥረት/ ይጀምራል፡፡ እርባ ቅምር በዐቢይ አንቀጽ መጀመሩ ቀዳማይ አንቀጽ በአብ፣ ካልኣይ አንቀጽ በወልድ፣ ሣልሳይ አንቀጽ በመንፈስ ቅዱስ፣ ዘንድ በአዳም፣ ቦዝ አንቀጽ በሔዋን ይመሰላሉና፡፡ ዘንድ ለምን በአዳም ተመሰለ ቢሉ አዳም አምላክነትን ሽቶ እንደቀረ ዘንድም አያሥርምና፡፡ ቦዝ አንቀጽ በሔዋን ይመሰላል መባሉ ሔዋን አምላክነትን ሽታ እንደቀረች ቦዝም ፈዞ ሳያሥር ይቀራልና፡፡

ነባር ካልሆነ በስተቀር ከዘር ውጭ ሌላ ሰዋስው አይገኝም፡፡ ስለዚህ ዘር ሲባል ብዙ ነገር ነው፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዘርን ከዚህ እንደሚከተለው ገልጸውታል፤

ነጠላ ግስን ከነርባው የሚያስገኝ፣ ጥሬ ዘርን ሁሉ የሚወልድ፣ ለምሳሌ በሊዕ፣ ሰትይ፣ ጸጊብ፣ ሰኪር፣ መዊት፣ ሐዪው፣ እያለ በሦስት ፊደል በቅሎ የሚሄድ፣ ይህን የመሰለ ሕጠተ ቃል አባት፡ ዘር ይባላል፡፡ አባትነቱም አዳምን ይመስላል፡፡ አባት ዘር እርሱ ራሱ እንደ ሥር ሆኖ ሌላውን ፍሬ ቃል ቢያስገኝ እንጅ ለእርሱ አስገኝና አባት የለውም፡፡ ሁለተኛም ሥረ ነገር፣ መሠረተ ቃል፣ ስለሆነ አርእስት ይባላል፡፡ ስሞቹ እንደፊደሎቹ ሦስት ናቸው፡፡ አባት ዘር፣ አርእስት፣ /ንዑስ አንቀጽ/

ናቸው፡፡ ዘር በቋንቋ ሁሉ የግስ ጥንት፣ የርባታ መሠረት ስለሆነ ከአናቅጽ በፊት ይጻፋል፡ ከርባታ በፊት ይነገራል፡፡ ጸሓፊም አንባቢም ወንጌል ዘዮሐንስ ሳይል ቀዳሚሁ ቃል እንደማይል ሁሉ አርእስትን በጽሕፈትም በንግግርም ንባብ እንደማይቀድመው ዘርንም አንቀጽና ጥሬ አይቀድሙትም፡፡ እናት ዘር ሳትቀበል እንደማትፀንስ ሁሉ ዘር ሳይቀድም አንቀጽ አይጻፍም፡፡ ምንጩን አሳይቶ ውሃውን፣ ዛፉን አሳይቶ ፍሬውን እንደሚሰጥ ሁሉ ዘሩን በፊት አንቀጹን በኋላ ያመጣዋል፡፡ የቀድሞ መምህራንም ዘር እያስቀደሙ ይገሱ እንደነበር ይታወቃል /ኪዳነ ወልድ፣ 1948 62/፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የቀድሞ መምህራን የሚጀምሩት ከዘር ነበር ያሉት እውነት ነው፡፡ መሠረተ ሐሳቡን የወሰዱት ከዋድላ አገባብ ነው፡፡ በዋድላ መምህራንም ግስ ካለ ዘር አይታጣም ተብሎ የግስ እርባታ ዘዴውን ቀላል ለማድረግ ሲባል ከግስ /ከአንቀጽ/ ተጀመረ እንጅ ትክክለኛው አካሄድ ከዘር መጀመር ነው ይላሉ፡፡ በዋድላ ዐዋጅ ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩልም አንቀጽ ማለት መግቢያ ማለት ነውና ከውስጥ ያለውን ለማወቅ በመጀመሪያ በበሩ መግባት ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ በአንቀጽ ጀምሮ ዘርን መፈለግ ቀላል ነው ብሎ በማሰብ ከአንቀጽ መጀመር ተለመደ በማለት ዋድላዎች ያብራራሉ፡፡ የተጀመረውም በአበ ብዑዓን ተክሌ ዘዋሽራ ሳይሆን አይቀርም፡፡

በዋድላ አገባብ መጀመሪያ ላይ ከዚህ የሚከተለው ሐተታ ይህን ያመለክታል፣ ከዘር ሳቢ ዘር፣ ከሳቢ ዘር፡ ንዑስ አንቀጽ፣ ከንዑስ አንቀጽ ዐቢይ አንቀጽ እየበረታ ይሄዳልሳ ቢሉ፣ ይህንስ በምሳሌ ተናግረውታል፡፡ ገበሬ ውሽቦ ዘርቶ ፍሬ ያጭዳል፡፡ እንደጊዜው ነው እንጅ ፍሬስ ዘርቶ ውሽቦ ያጭድ የለምን? ብለው የቀደሙ አባቶቻችን መስለውታል፡፡ በመቀጠልም ይሄውስ ቢሆን ምነው መምህራን ከልጅ

ወደ አባት ይገሱታል? ቢሉ ይህስ አባቴ ቆይ እኔ ልናገር ማለት ነው። የኋላ መምህራን ግን ግስ ተገኝቶ ዘር አይታጣም ፡ ቢታጣም የንዑስ አንቀጹ መጀመሪያም ሆነ ሳቢ ዘሩ ዘር ይሆንለታል ብለው ከዐቢይ አንቀጽ ጀምረዋል። ለምሳሌ አእመረ ብሎ አእምሮ፣ እምረት፣ ሀለበ ብሎ ሀሊብ የሚለው ዘር ሊሆን ይችላልና።

በዋድላ አገባብ አካሄድ ዐዋጅ በሥነ ፍጥረት ይጀምራል፣ እርባ ቅምር ግን በዐቢይ አንቀጽ ይጀምራል። ታዲያ መቅደም ያለበት ዘር ከሆነ ከቀዳማይ አንቀጽ መጀመርን ማን አመጣው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ ጥያቄ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መልስ ሰጥተውበታል። እሱም ማን እንዳመጣው አይታወቅም የሚል ነው። ነገር ግን ከላይ በመላምት እንደተገለጸው የተጀመረው በዋሸራው ተክሌ ፍቅሩ ሳይሆን አይቀርም። በአጠቃላይ በእርባ ቅምር ከቀዳማይ አንቀጽ ስንጀምር በዐዋጅ ደግሞ በዘር እንጀምራለን። ይህ ማለት ግን ሁለቱ የተለያዩ ናቸው ማለት ሳይሆን በእርባ ቅምር አንቀጽን የምናስቀድመው የአገሳስ አካሄዱን ቀላል ለማድረግ እንጅ የዘርን ቀዳሚነት የሚሸረሽር አይደለም።

ነባር ማለት ዘርነት የሌለው፣ ከዘር ከአንቀጽ የማይገኝ፣ የቋንቋ ቤተሰብ እየሆነ በውጥንቅጥነት የሚገኝ ጥሬ ቃል ነው በማለት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ተርጉመውታል። የዋድላ ዐዋጅ ደግሞ ነባርን መካን ዘር ብሎ ተርጉሞታል። መካን ዘር ማለትም የማይወልድ፣ የማይረባ ማለት ነው። ነባር እንደ ዘር እርባታ የለውም። የማይፈልስ፣ የማይናወጥ፣ የማይጠፋ፣ የማይለወጥ ስም ነው በማለትም ይተረጎማል። የዋድላ ዐዋጅ ለነባር ምሳሌ ሲሰጥ፣ ከመላእክት ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ከሰው፣ ዳንኤል ፣ ዮናስ የመሳሰሉ ስሞች፣ ከሀገር፣ ኢትዮጵያ፣ ግብፅ፣ ኢየሩሳሌም የመሳሰሉ ስሞች፣ ከተራራ፣ ሲና፣ ደብረ

ታቦር፣ አርሞንኤም፣ ከወንዝ ስም ግዮን፣ ኤፍራጥስ፣ ኤፌሶን፣ ከአገባብ ስም፣ እስመ፣ ከመ፣ አመ፣ መኑ፣ አይ፣ ዲበ፣ ውስተ እና የመሳሰሉ ይገኙበታል። ከግስ እንደ ውእቱ፣ አኮ፣ አልቦ፣ ቦ፣ እና የመሳሰሉት ነባር አናቅጽ፤ ከባሕር፣ ውቅያኖስ፣ ጥብርያዶስ፣ ገሊላ የመሳሰሉ፣ ከብትን ሰዋስው፣ እብን፣ እሳት፣ ኮከብ፣ ያም፣ አንበሳ፣ ነምር የመሳሰሉ ዝርው ወይም ብትን ሰዋስው በማለት ዘርዝሯቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ግስ ዘር የለውም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዘር ተገኝቶ አንቀጽ ይታጣል። በዚህ የተነሳ ነባር ይባላል በማለትም ያብራራል። በአጠቃላይ ነባር የባሕርይ ስም፣ የተጸውዖ ወይም የተቀብዖ ስም፣ የቦታ /የሀገር/ ስም፣ ብትን ሰዋስው፣ አገባብ፣ ነባር አንቀጽ ወዘተ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ከነባር የሚገኝ ስም ብቻ አይደለም። አንቀጽና አገባብም ይገኛል። ከዘሩ ዘር የመሰለ አንቀጽ እንደሚገኝ ሁሉ ከነባሩም ነባር የመሰለ ይገኛል በማለት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጽፈዋል። በምሳሌ ሲያብራሩም ሰብእ ብሎ ተሰብአ፣ ወይን ብሎ ወየነ፣ አውየነ፣ እብን ብሎ አበነ፣ አእበነ፣ ደብተራ ብሎ ደብተረ፣ ተደብተረ፣ እያለ ግስ ያወጣል / ኪዳነ ወልድ 1948፣ 63/።

በአለቃ ታየ ዐዋጅ ደግሞ ከዚህ የሚከተለው ተጽፏል። አንቀጽ የሌለው ሁሉ ነባር ይባላል። ነባር ማለት እርባ የሌለው፣ በቁም ቀሪ፣ ነገር ነው። ከሀ ጀምሮ እስከ ፐ ድረስ እንደ ግስ በፊደሉ ተራ በየፊደሉ ከግስ እየቀጠለ፣ በየቤቱ በግእዝ፣ በካዕብ፣ በሣልስ፣ በራብዕ፣ በኀምስ፣ በሳደስ፣ በሳብዕ ቤት እየመላ ይሄዳል። ስለዚህ ነባር በመነሻ የፊደል ገደብ የለበትም። በመድረሻ ግን አንድ ገደብ አለበት። እርሱም ግእዝ ነው። ነባር በግእዝ አይጨርስም። ሆኖም እንደ ሶበ፣ ከመ፣ አመ፣ እመ የመሳሰሉ አገባባት መድረሻቸው ግእዝ ነው የሚል ክርክር ይነሳል። አወ፣ መድረሻቸው ግእዝ ቢሆንም ተናበው

እንጅ በራሳቸው መቆም ስለማይችሉ በግእዝ ይደርሳሉ አያሰኝም። ነባር ዘርዘር ተደርጎ ሲታይ የባሕርይ፣ የተፈጥሮ፣ የተጸውዖ፣ የተቀብዖ፣ የንብረት፣ የግብር፣ የመዋዕል፣ የጎዳሪ፣ የማኅደር፣ የአካል፣ የተዘምዶ፣ የወገን፣ የዓይነት፣ የቁሳቁስ ወዘተ የሚታይና የማይታይ ነገር ስም ሁሉ ነባር ይባላል /ታየ 1958፣ 6/።

ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ አጠቃለን ስንመለከተው ሰዋስው የተባለ ሁሉ ከዘርና ከነባር አይወጣም። በዚህ መሠረት ምንጩ ሁለት ብቻ ነው። የፍጥረት ሁሉ ዓይነት ሁለት ሁለት ብቻ እንደሆነ ያውም ወንድና ሴት /ተባትና እንስት እንዲባል/ ሰዋስው ተብሎ የሚጠራው ሁሉ የቋንቋም ዓይነት ሁለት ነው በማለት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አጠቃለውታል።

፪. የሰምና ወርቅ አመሳሰል፣

የሰምና ወርቅ አመሳሰል ሁለት ነገሮችን ይይዛል። አንዱ ሰም ሲሆን ሁለተኛው ወርቅ ነው። ሲመሰሉ ሰም ይቀድማል ወርቅ ይከተላል። ሰም ቀድሞ ወርቅ የሚከተለው ተናበው ለሚመሰሉ ኢነባብያን እንጅ ይህ ድንጋጌ ነባብያንን አይመለከትም። ለምሳሌ፣

ማዕደ ሃይማኖት ተሠርዐ ይላል እንጅ፣ ሃይማኖተ ማዕድ ተሠርዐ አይልም። ብሎ ቢገኝ ጸያፍ ነው። ጸያፍነቱም <u>ግንባር ጸያፍ</u> ይባላል። ሰምና ወርቁ ሳይናበብ ተሠርዐ ሃይማኖት ኀብስት፣ ወይም ሠርዐ ሃይማኖተ ማዕደ ቢል ጸያፍ አይሆንም።

ሳይናበቡ የሚመሰሉ ነባብያንን በተመለከተ ማንኛውም ሊቀድም ይችላል። ለምሳሌ ጊዮርጊስ ኀያል ወይም ኀያል ጊዮርጊስ ሰተየ ወይነ ሃይማኖተ ቢል ጸያፍ አይሆንም። ሰምና ወርቅ ሲመሰል ቤት አልፎ አይመሰልም። ቤት አልፎ ተመስሎ ቢገኝ ጸያፍ ነው። ጸያፍነቱም <u>ዝርው ጸያፍ</u> ይባላል። ለምሳሌ ቤቱ ል ቢሆንና ነግሠ እግዚአብሔር ልዑል። ሰሎሞን ብሎ ቢገኝ አያስኬድም። መባል

ያለበት ነግሠ እግዚአብሔር ሰሎሞን ልዑል ነው /ለወጣንያን/።።

፫. ሳቢ ከተሳቢ በሁለት ነገር የሚያያዝ ስለመሆኑ፡ ሳቢ ከተሳቢ በሁለት ነገሮች ይያያዛል።። እነርሱም አንዱ ተናባቢ ቀለም ሲሆን ሁለተኛው ለ እና ዘ /አንድ ወገን/ ነው።። ተናባቢ የሚባሉት አራት ሲሆኑ ንዑስ አንቀጽ፣ ሳድስ ቅጽል፣ ሣልስ ቅጽልና ሳቢ ዘር ናቸው።። ንዑስ አንቀጽ ከዚህ ቀጥሎ ይገለጻል።። ለምሳሌ፤

አእምሮቱ ለመጽሐፍ ተፈቅረ በጎበ ጴጥሮስ፤
አፍቀረ ጴጥሮስ አእምሮቶ ለመጽሐፍ፤
አፍቀረ ጴጥሮስ አእምሮተ መጽሐፍ፤
አእምሮ መጽሐፍ ተፈቅረ በጎበ ጴጥሮስ
አእምሮ ዘመጽሐፍ አፍቀረ ጴጥሮስ፣
አእምሮ ዘመጽሐፍ ብሎ የመጽሐፍ ትርጓሜን ማወቅ ብሎም ዘን በቂ ማድረግ ይቻላል።። ለመጀመሪያው ንዑስ አንቀጽ ለ፣ ለሁለተኛው ንዑስ አንቀጽ ዘ የለውም።። ምክንያቱም አእምሮቱ ለመጽሐፍ ይላል እንጂ አእምሮት ዘመጽሐፍ አይልም።። እንዲሁም አእምሮ ዘመጽሐፍ ይላል እንጂ አእምሮሁ ለመጽሐፍ አይልም።።
ሣልስና ሳድስ አእማሪሁ ለመጽሐፍ፣ እሙሩ ለመጽሐፍ፣ እእማሬ መጽሐፍ ከብረ ጴሮስ ይላል።።

፬. ግስ የማይነሳባቸው ቀለማት፣

ዘማች ግስ የማይነሳባቸው ቀለማት ሁለት ናቸው።። እነርሱም ካዕብና ሣልስ ናቸው።። ለምሳሌ ለሀ ጻፈ፣ ቱሐ ቀላወጠ ይላል እንጅ ለሀ፣ ቲሐ አይልም።።

፭. የግስ መድረሻዎች፣

የግስ መድረሻዎች ሁለት ናቸው፡፡ እነርሱም ግእዝና ኀምስ ናቸው፡፡ ከሀ እስከ ፐ ድረስ ያሉ ግሶች ሁሉ መድረሻቸው ግእዝ ሲሆን ኀምስ ግን አንድ ይቤ ብቻ ነው በማለት የዋድላ ዐዋጅ ይደነግጋል፡፡ አዋጁ የባለሁለት ጉዳዮች ዐዋጅ በመሆኑ ከአበው መምህራን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ተከትለን ሁለት አልን እንጂ በመሠረቱ የዘማች አናቅጽ መድረሻ አንድ ብቻ ነው፡፡ በዋሽራ እርባ ቅምርም የግስ ሁሉ መድረሻ ግእዝ ብቻ ነው ተብሎ ተገልጿል፡፡ አንዳንድ የቀድሞ መምህራን ኀምስ የግስ መድረሻ ይሆናል በማለት ይቤን ምሥክር አድርገው ከገለጹ በኋላ እንደገና ተመልሰው በነባር ይመድቡታል፡፡ ይቤ የተለየ ባሕርይ ስላለው ዘማችም፣ ነባርም አይደለም፡፡ የራሱ አገሳሰስ ያለው ልዩና መደብ የለሽ ግስ ነው፡፡ በነባር አንቀጽነት እንዳይመደብ ካልኣይ፣ ዘንድ፣ ትእዛዝ አለው፡፡ በዘማች አንቀጽነት እንዳይመደብ፣ ከዘንድና ከትእዛዝ ባለፈ የማይዘምት /ሩቅ የማይሄድ/ ደካማ የመንደር ዘማች ነው፡፡ ስለዚህ ይቤ በዘማችም፣ በነባርም የማይመደብና ሕገ ወጥ አገሳሰስ ያለው ግስ ነው፡፡ ይቤ ዘማች አንቀጽ ነው በማለት የሚከራከሩም አሉ፡፡ የዚህም ክርክር መነሻ፣ የይቤ ቀዳማይ አንቀጽ “ቤለ” ነው በማለት ነው፡፡ ሲወርድም ቤለ፣ ይቤ፣ ይበል፣ ይበል፣ በዪል በዪሎት ይላል ይላሉ፡፡
ክፍል ሁለት፣
በሦስት ጉዳዮች የሚነገሩ ዐዋጆች፣

፮. በየ የሚነሱ ግሶች ሦስት ስለመሆናቸው፣

በየአገባቡ እንደተገለጸው፣ በየ የሚነሱ ግሶች ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም የብሰ፣ የበበ፣ የውሀ ናቸው፡፡ ይቤስ መነሻው የየ ሳድስ አይደለም ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይቤ ያልተካተተው ስርዋጽ ስለሆነ ነው፡፡ ስርዋጽ ማለትም የጠመመ

ማቅኛ፣ የጎደለ መሙያ ማለት ነው። የጠመመውን ማቅኛ ማለት ዘንዱን ሲሞላ ሲሆን የጎደለውን መሙያ ማለት ደግሞ ንዑስ አንቀጹን ሲሞላ ነው። በነዚህ ባሕርያት የተነሣ ይቤ አልተካተተም።

፯. ተጠርተው የሚያሥሩ አናቅጽ፣

ተጠርተው የሚያሥሩ አናቅጽ ሦስት ናቸው። እነርሱም ቀዳማይ አንቀጽ፣ ካልኣይ አንቀጽና ትእዛዝ አንቀጽ ናቸው። ለምሳሌ፣

ቀዳማይ አንቀጽ ተጠርቶ ሲያሥር፣ አእመረ ጴጥሮስ መጽሐፈ ይላል፣

ካልኣይ አንቀጽ ተጠርቶ ሲያሥር ያአምር ጴጥሮስ መጽሐፈ ይላል፣

ትእዛዝ አንቀጽ ተጠርቶ ሲያሥር ያእምር ጴጥሮስ መጽሐፈ ይላል።

እነዚህ አናቅጽ ይስባሉ እንጂ አይሳቡም። ንኡሳን አናቅጽ ግን ይስባሉም ይሳባሉም። የሚሳቡትም በዐበይት አናቅጽ ነው። እርስ በእርሳቸውም ይሳሳባሉ። ዐበይት አናቅጽን ግን ከይቤ፣ ከከብሀለና ከብሂል በቀር የሚስባቸው የለም። ንኡሳን አናቅጽ ሲሳቡ፣

መምህር ያፈቅር አንብቦ መጽሐፍ።

መምህር ያፈቅር አንብቦተ መጽሐፍ ይላል።

ጠቢብ ኮነ አንባቤ መጽሐፍ።

ዮሐንስ ተሰምየ ራእየ ኅቡኣት።

ዕዝራ ተሰምየ በላጌ ማጻሕፍት።

ዳንኤል ኮነ መተርጉመ ሕልም ይላል።

ሳቢ ዘር ሲስብ አፍቀረ ኤልያስ ዕርገተ ሰማይ።

ዘንድ ስቦ ሲሳብ ነዐ ወልድየ እፈኑከ ኀበ ካልእ ብእሲ ይላል።

ቦዝ ሲስብ ሶበሰ ሀሎከ ዝየ መጺእየ እምርእይኩከ ይላል።

ዐበይት አናቅጽ በይቤ፣ በብሀለና በብሂል ሲሳቡ፣

ይቤ እግዚአብሔር ኢታምልኩ ባዕደ አምላክ ዘእንበሌየ፡
ይቤ መጽሐፍ ይቤ ሙሴ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ፡
ተብህለ በሙሴ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ፡፡ ወይቤ እግዚአብሔር ለሙሴ ምንት ዝ ዘውስተ እዴከ? ወይቤ ሙሴ በትር፡፡
ብሂል ሜልኮል ኢወለደት ወልደ ብሂል አድግ አብቆለ ቀርነ፡፡

፰. ሳይጠሩ የሚያሥሩ አናቅጽ፣

ሳይጠሩ የሚያሥሩ አናቅጽ ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም ሀሎ፣ ይደሉ፣ ውእቱ ናቸው፡፡ ሳይጠሩ እንዴት እንደሚያሥሩ ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፤
አቡነ ዘበሰማያት፣ በሰማያት የምትኖር አባታችን /ሀሎ ሳይጠራ ሲያሥር ነው/
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት፣ ለእግዚአብሔር በሰማይ ምስጋና ይገባል / ይደሉ ሳይጠራ ሲያሥር ያሳያል/፡፡
አምላክ ሰብእ፣ ወሰብእ አምላክ፣ አምላክ ሰው ሆነ፤ ሰውም አምላክ ሆነ በማለት ውእቱ ሳይጠራ ያሠረ መሆኑን ያሳያል፡፡
ረዳት ግሶችም ሳይጠሩ በሚያስሩ አናቅጥ ውስጥ ሊካተቱ የችላሉ፡፡ እነርሱም ሀለወ፣ ሀሎ፣ ኮነ ናቸው፡፡ ሲነገሩም፣ ሀለወ እና ኮነ በዐሥሩ መራሕያን ሁሉ ከካልኣይ፣ ከትንቢት ጋር እየገቡግስን ይረዳሉ፡ ወይም ያጠናክራሉ፡፡ ኮነ በቀዳማይም፣ በካልኣይም እየገባ ይገኛል፡፡ ሀሎ ግን ነባር አንቀጽ እንደ መሆኑ መጠን በካልኣይ ብቻ ይገባል፡፡ ምሳሌ፣
ወሀለዉ ኖሎት ይተግሁ ወይኄልዉ፣
ወሀለዉ ይጼልዩ ወጸንሕዋ ለማርያም ይላል፡፡

ኮነ ሲገባ፣ ኮነ ይትናገር፣ ኮነ ይጎይይ፡ ኮነ ይበኪ ይላል፡፡ ኮነ በቀዳማይ ሲነገር፣
ወኮነ እምድኅረ ሞተ ሙሴ ተናገሮ እግዚአብሔር ለኢያሱ፡፡ ትርጉሙ፣ ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ ሲል አናገረው፡፡ ኢያ. ፩፡ ፩፡፡
ወኮነ እምድኅረ ሞተ ሳኦል ተመይጠ ዳዊት እምቀትለ አማሌቅ፡፡ ሳኦል ከሞተ በኋላ ዳዊት አማሌቃውያንን ድል አድርጎ ተመለሰ ይላል፡፡ 2ኛ ነገ. ፩፡ ፩፡፡
ሀለ ሲነገር፣ ዮሐንስኒ ሀለ ያጠምቅ በሄኖን ቅሩበ ኢየሩሳሌም፡፡

፱. በወ /ዋዌ/ የማይወርዱ ቀለማት፣

በወ /ዋዌ/ የማይወርዱ ቀለማት ሦስት ናቸው፡፡
ሦስቱ ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ ዝርዝር፣ የግእዝ ወራሽ፣ /ሀ/፣ የሙሻ ዘር ውስጠዘ /ዊ/ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣
ጸውዐ ሚካኤልሀ ወገብርኤልሀ ይላል እንጅ፣ ሚካኤልሀ ወገብርኤል አይልም /ሀ ሲወርድ/፡ ወይም ጸውዐ ማርያምሀ ወማርታሀ ይላል እንጅ ወማርታ አይልም፡፡
አምላክ ቀዳማዊ ወደኃራዊ ይላል እንጅ፣ አምላክ ቀዳማዊ ወደኃሪ አይልም /ዊ ማለትም የሙሻዘር ውስጠዘ ሲወርድ/፡፡
በተጨማሪም ነአምን ሕማሞ ለቃል ሥግው ወሞቶ ቢል እንጅ ወሞተ አይልም፣ /ዝርዝር ሲወርድ/
አክብር አባከ ወእመከ ይላል እንጅ አክብር አባከ ወእመ አይልም /ዝርዝር ሲወርድ/፡፡ አክብር አባከ ወባዕደ ግን ይላል፡፡ ምክንያቱም ባዕድ የተባለው ሌላ ሰው ነው፡፡
ነአምን ሕማመከ ወሞተከ ይላል እንጅ ወሞተ አይልም፣ /ዝርዝር ሲወርድ/፡፡ ዝርዝር ሲባል

ሁሉንም ዓይነት ዝርዝሮች ይመለከታል። ለምሳሌ፣ በዐረፍተ ነገር ሲገቡ፣
ኪ፣ አክብሪ አባኪ ወእመኪ ይላል እንጂ ወእመ አይልም፣
ክሙ፣ አክብሩ አበዊክሙ ወእማቲክሙ ይላል እንጂ ወእማተ አይልም፣
ክን፣ አክብራ አበዊክን ወእማቲክን ይላል እንጂ ወእማተ አይልም፣
የ፣ አክበርኩ አቡየ ወእምየ ይላል እንጂ ወእመ አይልም፣
ነ፣ አክበርነ አበዊነ ወእማቲነ ይላል እንጂ ወእማተ አይልም፣ እነዚህ በሙሉ ዝርዝር ናቸው።
ምንም እንኳ ከአበው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው አስተምህሮ መሠረት በዐዋጅ የሚጠቀሱት ከላይ የተገለጹት ብቻ ቢሆኑም በወ የማይወርዱ ቀለማት ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ከዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፣

ኢ	በበ	ለለ	እፎ	ለምንት	አይቴ	መኑ	እፍንቱ
ቦኑ	ሚ	መጠን					
አ	ሶ	ኬ	ኑ	ሁ	ዘዘ	አኮ	

አልቦ ዘ ስም ወራሽ ሲሆን ፣ እለ ስም አብዝ ሲሆን፣ በዘ ገንዘብ ሲሆን በወ አይወርዱም። በዐረፍተ ነገር ሲገለጹም፣
ኢ፣ ኢይበልዕ ወኢይሰቲ ይላል እንጂ ወይሰቲ አይልም፣ ወይም
ኢበልዐ ወኢሰትየ ይላል እንጂ ወሰትየ አይልም፣
በበ፣ በበጊዜሁ ወበበዘመኑ ይላል እንጂ ወዘመኑ አይልም፣
ለለ፣ ለለዕለቱ ወለለጊዜሁ ይላል እንጂ ወጊዜ አይልም፣
እፎ፣ እፎ መጻእከ ወእፎ ተመየጥከ ይላል እንጂ ወተመየጥከ አይልም፣
ለምንት፣ ለምንት ትተክዚ ነፍስየ ወለምንት ተሀውክኒ ይላል እንጂ ወተሀውክኒ አይልም፣

አይቴ፣ አይቴ ብሔራ ለጥበብ ወአይቴ ማኅደራ ይላል እንጂ ወማኅደራ አይልም፣
ማእዜ፣ ማእዜ ተወልደ ወማእዜ ሞተ ይላል እንጂ ወሞተ አይልም፣
መኑ፣ መኑ ስምክ ወመኑ ስመ አቡከ ይላል እንጂ ወስመ አቡከ አይልም፣
እስፍንቱ፣ እስፍንቱ ኃያላን ሞቱ ወእስፍንቱ ድኩማን ቆስሉ ይላል እንጂ ወድኩማን ቆስሉ አይልም፣
ቦኑ፣ ቦኑ ለዓለም ይገድፍ እግዚአብሔር ወቦኑ ለግሙራ ይመትር ለትውልደ ትውልድ ይላል እንጂ ወይመትር ለትውልደ ትውልድ አይልም፣
ሚ መጠን፣ ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት ወሚ መጠን መደንግፅት ይላል እንጂ ወመደንግፅት አይልም፣
አ፣ ፈንዎሙአ ለሕዝብየአ ይምጽኡ ይላል አንጂ ፈንዎሙአ ለሕዝብየ ይምጽኡ አይልም።
ሶ፣ አድኅንሶ ወሠርሕሶ ይላል እንጂ ወሠርሕ አይልም፣
ኑ፣ ዘፈጠራሁ ለዐይን ኢይሬኢኑ ወዘተከላሁ ለእዝን ኢይሰምዕኑ ይላል እንጂ ኢይሰምዕ አይልም፣
ዘዘዚአሁ፣ ዘዘዚአሁ ፍሬሁ ወዘዘዚአሁ ጣዕሙ ይላል እንጂ ወጣዕሙ አይልም፣
ዘ ስም ወራሽ ሲሆን፣ ዘይሁዳ በይሁዳ፣ ወዘሰማርያ በሰማርያ ይላል እንጂ ወሰማርያ በሰማርያ አይልም፣
እለ ስም አብዝር ሲሆን፣ እለጴጥሮስ ወእለጳውሎስ ይላል እንጂ ወጳውሎስ አይልም፣
በዘ ገንዘብ ሲሆን፣ በዘበልዐ ወበዘሰትየ ይላል እንጂ ወሰትየ አይልም፣
ካዕብ ቀለም በዝርዝር ጊዜ አቡሁ ወእሙ ይላል እንጂ ወእም አይልም፣
ራብዕ ቀለም በዝርዝር ጊዜ አቡሃ ወእማ ይላል እንጂ ወእም አይልም፣
ኀብዕ ቀለም በዝርዝር ጊዜ ነአምን ዕርገቶ ወዳግመ ምጽአቶ ይላል እንጂ ወምጽአተ አይለም።

ሀ፣ ኬ በተመሳሳይ ይገባሉ።።
የግእዝ ወራሽ የተባለው ሀ ነው።። ሲገባም ጎረዩ እስጢፋኖስሀ ወፊልፖስሀ ቢል እንጅ ወፊሊፖስ አይልም።።
የሙሻዘር ውስጠዘ የተባለው ዊ ነው።። ሲገባም ክርስቶስ ሰማያዊ ወምድራዊ ቢል እንጅ ወምድር አይልም።። በዘርፍ ጊዜ ግን አምላክ ሰማያዊ ወምድር ቢል ፀያፍ አይሆንም።። ሰማያዊ መልአክ፣ ምድር አዳምን አድርጎ ለአምላክ መንታ ዘርፍ ይሆናል።። ዘምድረ ሰብእ እብዲል።።
በተጨማሪም እም፣ ተምኔትና ፀፀት ሲሆኑ በወ አይወርድም።። እም ሲነገር እምነስሐ ይሁዳ እምጸድቀ ወእምኢተኮነነ ይላል እንጅ ወኢተኮነነ አይልም።።
የግእዝ ወራሽ የሚለውን መሠረተ ሐሳብ አብራርቶ ማለፍ ተገቢ ነው።። እንደሚታወቀው የተጸውያ ስም በግእዝ ወራሽ ካልተንተራሰ በቀጥታ አይሳብም።። ታዲያ ግእዝ ወራሽ ማነው? አብዘኛዎቹ የቅኔ አብነት መምህራን ግእዝ ወራሽ ማለት "ሀ" ነው ሲሉ ጥቂቶች ደግሞ "ሃ" ነው ይላሉ።። ይህ ክርክር ዘመናትን ያሳለፈ ክርክር ሲሆን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከዚህ ተነስተው ለወንድ ሀ፣ ለሴት ሃ ይሁን ብለው ጽፈዋል።። በመሠረቱ ሃ ለአንዲት የሩቅ ሴት ዝርዝር እንጂ ግእዝ ወራሽ አትሆንም።። ግእዝ ወራሽ የሚለው አሳብ የመነጨው፣ በገቢር ጊዜ መድረሻው ሳድስ የነበረው ስም ወደግእዝ ስለሚለወጥ ሲሆን የተጸውያ ስም ግን በባሕርዩ መድረሻውን መቀየር የማይችል በመሆኑ ነው።። ግእዝን ሊወርሰው የሚችለው ደግሞ ግእዝ እንጂ ራብዕ ሊሆን አይገባውም።። ስለዚህ ሃን ግእዝ ወራሽ ማድረጉ ከአንዲት ሩቅ ሴት ዝርዝር ጋር ከማደናገሩም በላይ ሌላ በቂ ምክንያት ስለሌለ የቆየውን የአበው ትምህርት ተከትሎ ግእዝ ወራሽ የሚባለው ሀ ነው የሚለውን ይዞ መቀጠሉ ተገቢ ነው።።

በመሠረቱ ክርክሩ ለብዙ ዓመታት ያህል የኖረ እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩን ከሕገ ሰዋስው አኳያ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የቀረበውን ክርክር ስንመረምረው በሁለት ነጥቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ አንደኛው ሀ ባዕድ ሆሄ ሲሆን ሃ ግን የሥርወ ቃሉ አካል ነው የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሃ የአንዲት ሩቅ ሴት ዝርዝር እንጂ የወንድ ስም የሥርወ ቃል አካል የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ አዋጁም የሚለው የተጸውዖ ስም በገቢር ጊዜ በባዕድ ይነገራል ነው፡፡ ግዕዙም ሆነ ራብዑ ባዕድ ሆሄ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ክርክር ስም በሀ ከጨረሰ መነሳት አለበት የሚል ነው፡፡ የስም ተነሽና ወዳቂ ራሱን የቻለ ዐዋጅ ያለው ሲሆን መድረሻው ግእዝ የሆነ ስም ሁሉ ሲነበብ ይነሳል የሚል ዐዋጅ የለም፡፡ ሚካኤልሀ ተብሎ ስለተጻፈ ሲነበብ ሚካኤል'ሀ ተብሎ እንዲነሳ የሚያስገድድ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የተጸውዖ ስምን ተሳቢ ለማድረግ "ግእዝ ወራሽ" ማለት ራብዑ ሆሄ ሳይሆን ግዕዙ ሆሄ ነው በሚለው የአበው ትምህርት እንገፋበታለን፡፡ ስለዚህ ለወንድ ፊነወ ሙሴሀ ወአሮንሀ፣ ለሴትም ኢያቄም ወሐና ወለዱ ማርያምሀ እያለ መቀጠሉ ተገቢ ነው፡፡

፲. ተናበው የማይመሰለ ቀለማት፣

ተናበው የማይመሰለ ቀለማት ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም፤
ስምና ስም፤ ስምና ግብር፤ ጎዳሪና ማጎደር ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣
ዳዊት ጊዮርጊስ እንጅ፤ ዳዊተ ጊዮርጊስ አይልም /ስምና ስም ሲሆን ነው/፣
ሰማዕት ጊዮርጊስ ይላል እንጅ፤ ሰማዕተ ጊዮርጊስ አይልም / ስምና ግብር/፤
ቤት አዳም ይላል እንጅ፤ ቤተ አዳም አይልም /ጎዳሪና ማጎደር/፡፡

፲፩. የማይመሰሉ ቀለማት፣

የማይመሰሉ ቀለማት ሦስት ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ ሴትና ወንድ፣ ሩቅና ቅርብ፣ አንድና ብዙ ናቸው። ምሳሌ፣
ጴጥሮስ ማርታ አእመረት መጽሐፉ አይልም። ጴጥሮስ ሙሴ አእመረ መጽሐፉ ይላል እንጅ፣ /ሴትና ወንድ/፣
ሰሎሞን ዘነገሥከ እግዚአብሔር ዘተወልደ አይልም፣ ሰሎሞን ዘነገሥከ እግዚአብሔር ዘተወለድከ ይላል እንጅ / ቅርብና ሩቅ/፣
ጴጥሮስ ነቢያት አእመሩ መጽሐፉ አይልም፣ ነቢያት ሐዋርያት አእመሩ መጽሐፉ ይላል እንጅ /አንድና ብዙ/።

፲፪. ባዕድ ዘር የሚሆኑ ቀለማት፣

ባዕድ ዘር የሚሆኑ ቀለማት ሦስት ናቸው። እነርሱም መ፣ ተ፣ አ ናቸው። መ ከግእዝ እስከ ሳብዕ ያሉትን ፊደላት ሁሉ ይጨምራል። ተ እና አ ግን በግእዝ፣ በራብዕ፣ በሳድስ ይነገራሉ። ካዕብም፣ ሣልስም፣ ኀምስም፣ ሳብዕ ከመጻሕፍት ከተገኙ አይሆንም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ተኬነወ ብሎ ሜኮኖት የሚለውን ማየት ይቻላል።
መ ባዕድ ሲሆን፣ ቀደሰ ብሎ መቅደስ፣ ወረደ ብሎ ሙራድ፣ ኀደረ ብሎ ማኅደር፣ ዐርገ ብሎ ምዕራግ፣ ወፀፈ ብሎ ሞፀፍ፣ ሞጠሐ ብሎ ሞጣሕት ይላል።
ተ ባዕድ ሲሆን፣ ገብረ ብሎ ተግባር፣ ቤተ ብሎ ታቦት፣ መሀረ ብሎ ትምህርት፣ ይላል። በዋሸራ ዐዋጅ ግን በርሀ ብሎ ቶማስ፣ ተፈሥሐ ብሎ ዮሐንስ፣ ሐና የሚል አስተምህሮ አለ። በእኛ በኩል ግን ይህ አባባል አያስኬድም።

አ ባዕድ ሲሆን፣ መሰለ ብሎ አምሳል፣ በቄለ ብሎ አብቁልት፣ ገዝአ ብሎ እግዚእ ይላል።

፲፫. ዘርፍና ባለቤት በሦስት ነገር ስለመያያዙ፣

ዘርፍና ባለቤት በሦስት ነገሮች ይያያዛሉ። በምንና በምን ቢሉ፣ በለ፣ በዘ/እንተ/እለ፣ በተናባቢ ነው። በደቂቅ አገባብ አምስት እያለ እዚህ ሦስት ማለቱ አይጣላም ወይ የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልሱ አይጣላም ነው። ምክንያቱም ደቂቅ ዘርዝሮ መናገር ልማዱ ስለሆነ ዘን፣ እንተን፣ እለን ለየብቻ ዘርዝሮ ቆጠረ። ዐዋጅ ደግሞ ተግባራቸው አንድ ዓይነት በመሆኑ ዘን፣ እንተን፣ እለን አንድ ወገን በማድረግ ቆጠረ። ልዩነቱ ይህ ነው።
ዘ እና ለ መክብብ ናቸው። ሁሉንም ያያይዛሉ። ዘ ሲያያይዝ አንዱን ከአንድ፣ አንዱን ከብዙ፣ ብዙውን ከአንድ፣ ብዙውን ከብዙ ነው።
ለምሳሌ ዘ ሲያያይዝ፣ አምላክ ዘሰማይ፣ አምላክ ዘሰማያት፣ አማልክት ዘሰማያት፣ አማልክት ዘሰማይ፣ ይላል
እንተ ሲያያይዝ አንዱን ከአንድ እና አንዱን ከብዙ ብቻ ነው። አምላክ እንተ ሰማይ፣ አምላክ እንተ ሰማያት ይላል።
እለ ሲያያይዝ ብዙውን ከብዙ እና ብዙውን ከአንድ ብቻ ነው። ለምሳሌ አማልክት እለ ሞአብ፣ አማልክት እለ አሕዛብ ይላል።
ለ ሲያያይዝ፣ አንዱን ከአንድ፣ አንዱን ከብዙ፣ ብዙውን ከአንድ፣ እና ዙውን ከብዙ ነው፡ ለምሳሌ አምላኩ ለሰማይ፣ አምላኮሙ ለሰማያት፣ አማልክቲሁ ለሞአብ፣ አመልክቲሆሙ ለአሕዛብ በማለት ለአንድም ለብዙም ይሆናል። ዘርፍ አያያገሮች ሁለት ቃላትን ሲያያይዙ ወደ ኋላ ያለውን እንጂ የወደቁበይን ስም አይመለከቱም።

ከላይ የተጠቀሱት አገባቦች በአዋጁ ቋንቋ አገላለጽ ሰባት የዘርፍና የባለቤት አማርኛ ይከታሉ፡፡ ይህም ማለት እግረ መንገዱን ለመግለጽ በሰምና ወርቅ አመሳሰል ጊዜ ዘርፍና ባለቤት ለን፣ ዘን፣ እንተን፣ እለን እና ተናባቢን በመጠቀም ሰባት የተለያዩ ሥርዓቶች አላቸው ማለት ነው፡፡ በአዋጁ አገላለጽ ባለቤትና ዘርፍ፣ በሰምና በወርቅ፣ አካሂድ ሲነገሩ ብዙ ስም አላቸው፡፡ እነዚህም፣
ውስጠ ወይራ፣ ክብ፣ ዝምድ፣ ፍላፃ፣ ጥምዝ፣ ድፋት፣ ተራ ምሳሌ፣ ናቸው፡፡
ውስጠ ወይራ ስምንት ናቸው፡ ምንና ምን ቢሉ የስምና የስም፤ የግብርና የስም፤ የአንድና የብዙ፤ የሴትና የወንድ፤ የአኅዝ፤ የድርድር፤ የቅጽል እና የአጻፋ ናቸው፡፡ እያንዳንዱን በአግባቡ ለመረዳት ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፣

፩፡ የሰም ባለቤት ከወርቅ ዘርፍ ተናቦ የወርቅን ባለቤት ሲያመጣ ውስጠ ወይራ ይባላል፡፡ ምሳሌ ነዳያን ሮማውያን በልዑ ኀብስተ ጴጥሮስ ሲል ሃይማኖተ ጴጥሮስ ማለቱን ያሳያል፡፡
፪፡ ክብ ውስጠ ወይራ ሲሆን በሰም ባለቤት ይከበባል፣ ምሳሌ ጳውሎስ በልዐ ኀብስተ ጴጥሮስ ባዕል ይላል፡፡
፫፡ የወርቅ ባለቤት እየቀደመ የሰም ባለቤት ተከትሎ ከወርቅ ዘርፍ ሲናበብ ዝምድ ይባላል፡፡ ለምሳሌ ተሠርዐ ሃይማኖት ኀብስተ ጴጥሮስ፡፡ ይህ ነጠላ ዝምድ ነው፡፡ ባዕል ሲጨመር ድርብ ዝምድ ይባላል፡፡
፬፡ የሰም ባለቤት ከወርቅ ዘርፍ ተናቦ እየቀደመ የወርቅ ባለቤት ሲከተል ፍላፃ ይባላል፡፡ ምሳሌ ተሠርዐ ኀብስተ ጴጥሮስ ሃይማኖት ሲል ነጠላ ፍላፃ ይባላል፡፡ ተሠርዐ ኀብስተ ጴጥሮስ ባዕል ሃይማኖት ሲል ድርብ ፍላፃ

ይባላል። የተጸውያ ስምና የሀገር ስም ዝምድና ፍላጻ አይሆንም። ፈርያን ማዕረረ ዓሣ፣ ግብፅ ማዕረረ ፈርያን አይልም ሸሸ ምክንያቱም ፈርያነ ዓሣ፣ ግብፀ ፈርያን ማለት ነውና።

ማሳሰቢያ፣ ዝምድና ፍላፃ ተቃራኒ ናቸው። የሰም ባለቤት በወርቅ ባለቤት ላይ በሚናበብበት ጊዜ በወርቅ ዘርፍ ሲጠበቅ ጥምዝ ይባላል። ምሳሌ ተሠርዐ ጎብስተ ዘጴጥሮስ ሃይማኖት ሲል ጥምዝ ይባላል። ክብ፣ ውስጠ ወይራ፣ ዝምድ፣ ፍላፃ፣ ሲነገሩ የወርቁ ባለቤት ከወርቁ ዘርፍ ላይ ከወደቀ ወይም የሰሙ ባለቤት ከሰሙ ዘርፍ ላይ ከወደቀ ጸያፍ ነው። ጸያፍነቱም ነቅዕ ነው።

ቅጽል በሰምና ወርቅ የቅኔ አደራደር ውስጥ የሚኖረው አገባብ

ቅጽል ወይ ለባለቤት ወይ ለዘርፍ ይሆናል። ለምሳሌ ከዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፣

፩ ፦ ተራ ቅጽል ሲሆን፣ ጎብስተ ጴጥሮስ ዘከብረ ባዕል ተሠርዐ በሚልበት ጊዜ ቅጽሉ ወይ ለጴጥሮስ ተራ ቅጽል ወይም ለባዕል ተቀዳሚ ቅጽል ይሆናል።

፪ ፦ ጎብስተ ዘከብረ ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ ሲል ለጴጥሮስ ተቀዳሚ ቅጽል ይሆናል።

፫ ፦ ጎብስተ ዘአክበሩ ሐዋርያት ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ ሲል ለጴጥሮስ ባዕድ ቅጽል ይሆናል

፬ ፦ ጎብስተ ዘዘሕዝብ አክበሩ ጳውሎስ አክበረ ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ ሲል ገፊ ቅጽል ይሆናል።

፭ ፦ ዘከብረ ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ ሲል ለጎብስት ተቀዳሚ ቅጽል ይሆናል።

፮፥ ጎብስተ ጴጥሮስ ዘከብረ ተሠርዐ፣ /ተራ ቅጽል/፣
፯፥ ጎብስተ እንተ ከብረ ጴጥሮስ ተሠርዐ /ተቀዳሚ ቅጽል/፣
፰፥ ጎብስተ እንተ ሕዝብ አክበሩ ጴጥሮስ ተሠርዐ /ባዕድ ቅጽል/።።
፱፥ ጎብስተ እንተ እንተ ሕዝብ አክበሩ ጳውሎስ አክበረ ጴጥሮስ ተሠርዐ /ገፊ ቅጽል/ ይላል።።

፲. በዝምድ ውስጥ ቅጽል ሲገባ /የዝምድ ቅጽል/፣

ሃይማኖት ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ዘከብረ ተሠርዐ ሲል ዝምድ ቅጽል ይሆናል።።

ሃይማኖት ጎብስተ ዘከብረ ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ
ሃይማኖት ጎብስተ ዘአክበሩ ሕዝብ ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ
ሃይማኖት ጎብስተ ዘዘአክበሩ ሕዝብ ጳውሎስ አክበረ ጴጥሮስ ባዕል ተሠርዐ ይላል።።

፲፩፥ ቅጽል በፍላፃ ውስጥ ሲገባ /የፍላፃ ቅጽል/፣

ጎባውዘ ሐዋርያት እለከብሩ ሕገጋት ተሠርዑ ሲል ነጠላ ፍላፃ ይባላል፣

፲፪፥ ጎባውዘ ሐዋርያት ብዑላን እለከብሩ ጥዑማን ሕገጋት ተሠርዑ ሲል ድርብ ፍላፃ ይባላል።። ቅጽሎቹ የተቀጸሉት በውስጥ ነው።።
፲፫፥ ጎባውዘ እለ ከብሩ ሐዋርያት ብዑላን ጥዑማን ሕገጋት ተሠርዑ።።
፲፬፥ ጎባውዘ እለ እለ አክበሩ ሕዝብ አርድዕት አክበሩ ሐዋርያት ብዑላን ጥዑማን ሕገጋት ተሠርዑ።።

ማሳሰቢያ፣ የፍላፃ ቅጽል በውስጥ እንጅ በውጭ አይሆንም /አይቀጸልም
ምሳሌ፣ ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ሃይማኖት ዘከብረ ተሠርዐ አይልም፡፡ ብሎ ቢገኝ ፍርቅ ጸያፍ ይባላል፡፡ በምትኩ ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ዘከብረ ሃይማኖት ተሠርዐ ይላል፡፡
እንዲሁም፣
ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ሃይማኖት ጥዑም ተሠርዐ አይልም፡፡ በምትኩ ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ጥዑም ሃይማኖት ተሠርዐ ይላል፡፡

፲፫፡ **በዘርፍ ደፊ ውስጥ የቅጽል አጠቃቀም** ፣

የለ ድፋት ሲገባ፤ ለጴጥሮስ ባዕል ጎብስቱ ተሠርዐ
ለጴጥሮስ ዘከብረ ባዕል ጎብስቱ ተሠርዐ
ለዘከብረ ጴጥሮስ ባዕል ጎብስቱ ተሠርዐ
ለዘሕዝብ አክበሩ ጴጥሮስ ባዕል ጎብስቱ ተሠርዐ
ለጴጥሮስ ባዕል ክቡር ጎብስቱ ተሠርዐ
ለዘዘሕዝብ አክበሩ ጳውሎስ አክበረ ጴጥሮስ ባዐል ጎብስቱ ተሠርዐ እያለ ይቀጥላል፡፡

፲፬፡ **የዘ ድፋት ሲገባ፤** የዘ ድፋት ከዚህ እንደሚከተለው ይገለጻል፣

ዘጴጥሮስ ባዕል ዘከብረ ጎብስት ተሠርዐ
ዘዘከብረ ጴጥሮስ ባዕል ጎብስት ተሠርዐ
ዘዘሕዝብ አክበሩ ጴጥሮስ ባዕል ጎብሰት ተሠርዐ
ዘዘዘሕዝብ አክበሩ ጳውሎስ አክበረ ጴጥሮስ ጎብስት ተሠርዐ እያለ ይቀጥላል፡፡

ማሳሰቢያ፣ በድፋት ጊዜ ዝምድ ፍላፃ፣ ፍላፃ ዝምድ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፣

የዝምድ ድፋት፣ እንተ ጴጥሮስ ባዕል እንተ ከብረ ሃይማኖት ጎብስት ተሠርዐ

እንተ እንተ ከብረ ጴጥሮስ ባዕል ሃይማኖት ጎብስት ተሠርዐ

እንተ እንተ እንተ ሕዝብ አክበሩ ጳውሎስ አክበረ ጴጥሮስ ባዕል ሃይማኖት ጎብስት ተሠርዐ ይላል፡፡

የፍላፃ ድፋት፣ ሕገጋት እለ ሐዋርያት ብዑላን እለ ከብሩ ጎባውዝ ተሠርዑ

ሕገጋት እለ ሐዋርያት እለ ከብሩ ጥዑማን ጎባውዝ ተሠርዑ

ሕገጋት እለ እለ ከብሩ ሐዋርያት ብዑላን ጥዑማን ጎባውዝ ተሠርዑ

ሕገጋት እለ እለ እለ አክብሩ ሕዝብ አርድዕት አክበሩ ሐዋርያት ብዑላን ጥዑማን ጎባውዝ ተሠርዑ

ሕገጋት ለሐዋርያት እለ ከብሩ ጥዑማን ጎባውዞሙ ተሠርዑ እያለ ይቀጥላል፡፡

፲፭፥ የድፋት ቅጽል፣ በውስጥ እንጅ በዕዳሪ ወይም በውጭ አይቀጸልም፡ ለምሳሌ፣ ዘድንግል መናስግት ኢያርጊዎ ዘኪሩቤል ኢርእዮ አይልም፡፡ ዘድንግል ዘኪሩቤል ኢርእይዎሙ መናስግት ኢያርጊዎ ይላል እንጅ፡፡
ለጴጥሮስ ባዕል ጎብስቱ ጥዑም ተሠርዐ አይልም፡፡ ለጴጥሮስ ባዕል ጥዑም ጎብስቱ ተሠርዐ ይላል እንጅ

፲፮፥ ጥምዝ፣ ጎብስተ ዘጊርጊስ ክሳድ ጥዑመ ሠርዐ ይላል እንጅ ጥዑም አይልም፡፡ ነገር ግን ጎብስተ ዘጊዮርጊስ ክሳድ ጥዑም ተሠርዐ ይላል፡፡
ማሳሰቢያ፣ የጥምዝ ቅጽል በውጭ እንጂ በውስጥ አይሆንም፡፡ ከዘርፍ ድፋት /ዝምድና ፍላፃ/ ቅጽል ጋር ተቃራኒ ነው፡፡ ለምሳሌ፣

ኅብስተ ዘጊዮርጊስ ጥዑም ክሳድ ብሎ ቢገኝ ተኩላ ፀያፍ ነው። ይህም ማለት ነጣቂ ማለት ነው። ሲቃና ኅብስተ ዘጊዮርጊስ ክሳድ ጥዑም ይላል።

የንዑስ አንቀጽ ዝምድና ፍላፃ፣

አእምሮ ኅብስተ ጴጥሮስ መጽሐፈ ባዕል ተሠርዐ አይልም። ኅብስተ አእምሮ ጴጥሮስ መጽሐፈ ተሠርዐ ይላል እንጂ፣

ኅብስተ ጴጥሮስ ባዕል አእምሮ መጽሐፈ አይልም። ኅብስተ አእምሮ ጴጥሮስ መጽሐፈ ተሠርዐ ይላል እንጂ።

ጥምዝ፣ ኅብስተ ዘጊዮርጊስ ክሳድ ጥዑም ተሠርዐ፣

ኅብስተ ዘጊዮርጊስ ክቡር ክሳድ ጥዑም ተሠርዐ፣

ኅብስተ ዘጊዮርጊስ ክቡረ ሕዝብ ነዊኅ ክሳድ ጥዑም ተሠርዐ፣ ይላል።

ኅብስተ ለጊዮርጊስ ክሳዱ አይልም። ቢል ጸያፍ ነው። ጸያፍነቱም ተኩላ ነው።

ተራ ምሳሌ፣ አምላከ ሰማይ ንጉሥ ይላል። **ተቻቻይ፣** አምላከ ሰማይ ንጉሠ መንበር ይላል። ጸያፍ አይሆንም።

አምላከ ሰማይ ወምድር ንጉሠ መንበር አይልም። ብሎ ቢገኝ የአንድና ብዙ ጸያፍ ነው። አምላከ ሰማይ ወምድር ንጉሠ መናብርት ይላል እንጂ።

አምላከ አዳም ልዑል ንጉሠ ሀገር ቅድስት አይልም። ብሎ ቢገኝ ፍናፍንት ጸያፍ ይባላል። አምላከ አዳም ልዑል ንጉሠ ሀገር ቅዱስ ይላል እንጂ።

አምላከ ሰማይ ወምድር ንጉሠ ቀላይ ወየብስ አይልም። ቢል ጸያፍ ነው ጸያፍነቱም ጸአት፣ ጎርማን፣ መደብ ድልድይ ማለት ነው

፲፱፥ የንዑስ አንቀጽ ዝምድና ፍላፃ /የብሂል/

ንዑስ አንቀጽ /ብሂል/፣ ፍላፃ፣ ዝምድ፣ አጭር ዘርፍ፣ ረጂም ዘርፍ፣ ዐውደ ጥበብ ክብ፣ ጥምዝ፣ የለ ዘርፍ፣ የዘ ዘርፍ፣ የለ ድፋት፣ የዘ ድፋት ይሆናል፡፡ ሲነገርም፣

ነጠላ ፍላፃ፣ ፀአነ ቴዎድሮስ ፈረሰ ኢሳይያስ ብሂለ ድንግል ትወልድ ወልደ ይላል፡፡

ድርብ ፍላፃ፣ ፀአነ ቴዎድሮስ ፈረሰ ኢሳይያስ ባዕል ብሂለ ድንግል ትወልድ ወልደ ይላል፡፡

ነጠላ ዝምድ፣ በልዐ ቴዎድሮስ ብሂለ ተወልደ አምላክ ኀብስተ ቁርሎስ

ድርብ ዝምድ፣ በልዐ ቴዎድሮስ ብሂለ ተወልደ አምላክ ኀብስተ ቁርሎስ ባዕል ይላል፡፡

አጭር ዘርፍ፣ ባዕለ እስክንድርያ ይላል

ረጂም ዘርፍ ፣ ባዕለ እስክንድርያ ሀገር ይላል፡፡

ዐውደ ጥበብ፤ ኀብስተ ኢበሊዕ ኀብስተ በልዐ ወጸግበ፤ ወልብሰ ኢለቢስ ልብሰ ወተገልበበ፤ ተከለ ሐይመተ ብሂል ተወልደ አምላክ ንጉሥ፤ ዕፀወ ሊባኖስ ነገፉ ቆጽለ ኢያስርዖ ብዙኀ አርአያ ሠናይ ይላል፡፡

ጥምዝ፣ ኀብስተ ዘጴጥሮስ ብሂል ተሰቅለ አምላክ ይላል፡፡

የለ ዘርፍ፣ ተመዝበረት ብሂል አልባቲ ሠራዒ ወመጋቢ ለዛቲ ዓለም ሀገሩ ለማኒ አማፂ ይላል፡፡

የዘ ዘርፍ፣ ተፈቅረ ብሂል አድኅን ዓለመ መንግሥት ዘአምላክ ሰሎሞን ይላል፡፡

የለ ድፋት፣ ተበልዐ ለጳውሎስ ኀብስቱ ብሂል ተወልደ አምላክ ይላል፡፡

የዘ ድፋት፣ ተሐንጸ ዘጴጥሮስ ባዕል ቤት ብሂል አምላክ አድኅነ ዓለመ ይላል

ክፍል ሦስት፣

አራት ጉዳዮችን የያዙ ድንጋጌዎች፣

፲፬. አሥራው ቀለማት፣

አስራው ቀለማት የሚባሉ አራት ናቸው። እነርሱም ተ፣ ነ፣ አ፣ የ ናቸው። ግዕዛቸው፣ ራብዓቸው፣ ሳድሳቸው አይቀርም።
የተ ግእዝ በ፲፬ አንቀጽ በ፮ ሠራዊት ይነገራል።
ለምሳሌ ሐንረ እሸኮኮ አለ የሚለው ግስ ሲረባ፣
ሐንገርከ፣ ተሐነግር፣ ተሐንግር፣ ሐንግር
ሐንገርክሙ፣ ተሐነግሩ፣ ተሐንግሩ፣ ሐንግሩ፣
ሐንገረት፣ ተሐነግር፣ ተሐንግር፣ ተሐንግር፤
ሐንገርኪ፣ ተሐነግሪ፣ ተሐንግሪ፣ ሐንግሪ፣
ሐንገርክን፣ ተሐነግራ፣ ተሐንግራ፣ ሐንግራ፡ እያለ ይረባል።
የየ ግእዝ በ፱ አንቀጽ በ፫ ሠራዊት ይነገራል።
ለምሳሌ፣
ሐንገረ ብሎ የሐነግር፣ የሐንግር፣ የሐንግር።
ሐንገሩ፣ የሐነግሩ፣ የሐንግሩ፣ የሐንግሩ፣
ሐንገራ፣ የሐነግራ፣ የሐንግራ፣ የሐንግራ እያለ ይነገራል።
የነ ግእዝ በ፫ አንቀጽ፣ በ፩ በ፩ ሠርዌ ይነገራል።
ሐንገርነ፣ ነሐነግር፣ ነሐንግር፣ ነሐንግር ይላል።
የተ ግእዝ፣ ሐንገረት፣ ተሐነግር፣ ተሐንግር፣ ተሐንግር ይላል።
የአ ግእዝ ሐንገርኩ፣ አሐነግር፣ አሐንግር፣ አሐንግር ይላል።
የየ ራብዕ አንገለግ፣ ያንጌልግ፣ ያንገልግ፣ ያንገልግ ይላል።
የተ ራብዕ፣ አንገለግሙ፣ ታንጌልጉ፣ አንገለግት፣ ታንጌልግ፣

የነ ራብዕ፣ አንገለግነ ናንጌልግ፣ ናንገልግ፣ ናንገልግ ይላል።።
የተ ሳድስ ቀተልከ፣ ብሎ ትቀትል፣ ትቅት፣ ቅትል ይላል።። ቀተልክሙ፣ ቀተለት፣ ቀተልኪ፣ ቀተልክን የሚሉት ግሶች ሁሉ ትን ሳድስ ያደርጋሉ።።
የየ ሳድስ ሲሆን ቀተለ፣ ቀተሉ፣ ቀተላ፣ ይቀትል፣ ይቀትሉ፣ ይቀትላ ይላል።።
የነ ሳድሰ ሲሆን ቀተልነ፣ ንቀትል፣ ንቅትል ንቅትል ይላል፤
የአ ሳድስ ሲሆን ቀተልኩ፣ እቀትል እቅትል፣ እቅትል በሚሉት ግሶች ይገለጻል።።

፲፩. ስም አራት ስለመሆናቸው።።

ስም የሚባሉት አራት ናቸው።። ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ የግብር፣ የባሕርይ፣ የተቀብያ፣ የተጸውያ ናቸው።።
የግብር ስም ማለት ጠቢብ፣ ሐራሲ፣ ካህን የመሳሰለውን ነው።።
የባሕርይ ስም ማለት የእግዚአብሔር ስም ነው።። አሀያ፣ ሸራሀያ፣ ወዘተ ይላል።። ለፍጡርም የባሕርይ ስም አለው።። ለምሳሌ እናትና አባት ያላወጡት ስም ሆኖ እንደ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሰብእ የመሳሰሉት ማለት ነው።።
የተቀብያ ስም፣ እንደ ሀገራችን ወልደ ማርያም፣ ገብረ ማርያም፣ ጽጌ ድንግል፣ ዘአማኑኤል፣ እንደ ሀገራቸው ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ፣ ዲዲሞስ ወዘተ ነው።። ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ፣ ዲዲሞስ በጓላ በጌታ የተሰጣቸው ስያሜ ስለሆነ ነው።። የመጀመሪያው ስማቸው፣ ስምዖን፣ ሳያል፣ ቶማስ፣ ነበር።።
የተጸውያ ስም የሚባሉት ኤልያስ፣ ሙሴ፣ ዘካርያስ፣ ናትናኤል፣ አበበ፣ ከበደ፣ የመሳሰሉት ናቸው።።
የተጸውያ ስም በገቢር ጊዜ ሲጠራ በባዕድ፣ በተገብሮ ጊዜ በራሱ፣ አማርኛ ይነገራል።። ለምሳሌ፣

ጸውዐ ሙሴሀ፣ ተጸውዐ ሙሴ ይላል። የግብር ስሞች በግቢር ጊዜ በራሳቸው ይነገራሉ። ለምሳሌ ጠቢበ፣ ካህነ፣ ሰማዕተ ይላል።

የተቀብየ ስሞች ተናበው ሲነገሩ ለግቢርም ለተገብሮም ይከታሉ። ጴጥሮስን፣ ጳውሎስን፣ ዲዲሞስን፣ የመሳሰሉ የተቀብየ ስሞች በግቢር ጊዜ ጴጥሮስሀ፣ ጳውሎስሀ፣ ዲዲሞስሀ ይላል።

የመድበል ስሞች በግቢር ጊዜ በራሳቸው ይነገራሉ። ለምሳሌ አይሁዳ፣ ሱራፌል፣ ኪሩቤል፣ እስራኤል ይላል እንጂ አይሁድሀ፣ ሱራፌልሀ፣ ኪሩቤልሀ፣ እስራኤልሀ አይልም። በግቢር ጊዜ በራሳቸው ይነገራሉ። ይሁዳ ግን የተጸውዖ ስም ስለሆነ በግቢር ጊዜ ይሁዳሀ ይባላል።

የቦታ ስም፣ ከነዓን፣ ሠማርያ፣ ፋርስ፣ ይሁዳ፣ ባቢሎን፣ አክሱም፣ ግብፅ፣ ፅርዕ፣ ምስር እና የመሳሰለው።

የቦታ ስም ፍጹም ሳድስ ከሆነ ግብፅን፣ ምስርን፣ ፅርዕን ከመሰለው በስተቀር ለግቢር ለተገብሮ ይከታል። ምሳሌ፣

አብርሃም ሖረ ከነዓን፣
ሮብአም ኮነነ ይሁዳ፣
ናቡከደነፆር አገተ ኢየሩሳሌም፣
ያዕቆብ ወረደ ግብፀ፣ ምስረ፣ ፅርዐ፣ ይላል።
ሶምሶን ወረደ ኢሎፍሊ ይላል።

ማሳሰቢያ፣

የተጸውዖ ስም ገቢር ሲሆን ግእዝ እንደሚለወጥለት በዐዋጅ ተነግሯል። ስለዚህ ከተጸውዖ ስም መጨረሻ የሚገባው ሀ ግእዝ እንጂ ራብዕ ሊሆን አይችልም።

፲፮. ሰሚ የሚሆኑ አራት ነገሮች፣

ሰሚ የሚሆኑ አራት ነገሮች ናቸው። እነርሱም
የቅርቡ ወንድ፣ የቅርቦቹ ወንዶች፣ የቅርቢቱ ሴት፣
የቅርቦቹ ሴቶች ናቸው። ለምሳሌ፣

አፍቀርከ ጽድቀ እግዚኦ ወአመፃ ጸላእከ፣
ኦ አርድእት አእመርክሙ ምሥጢረ፣
ኦ ብእሲት አእመርኪ ፈትለ ወጸብሐ፣
ኦ አንስት አእመርክን ጥበባተ ይላል።

፲፯. አሰሚ የሚባሉ አራት ስለመሆናቸው፣

አሰሚ የሚባሉ አራት ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ
የአንቀጽ፣ የአገባብ፣ የዘርፍ፣ የባለቤት ናቸው።
አንቀጽ ከፈቀደው ሆኖ ያሰማል። የተቀሩት ግን ወይ
በመጀመሪያ፣ ወይ በመጨረሻ ሆነው ያሰማሉ።
አገባብ ከመጀመሪያ ብቻ ሆኖ ያሰማል።
በመጀመሪያ፣ በመካከል እና በመጨረሻ እየተባለ
የተጠቀሰው ቦታ የባለቤቱ ቦታ ነው።
አንቀጽ በመጀመሪያ ሲያሰማ አምላክ ባዕለ ጸጋ
ብዙኃን አይሁድ ሰቀሉከ ውስተ ቀራንዮ።
አንቀጽ በመካከል ሲያሰማ ሰቀሉከ ውስተ አፍኣ
እግዚአብሔር ንጉሥ ብዙኃን አይሁድ፣
አንቀጽ በመጨረሻ ሆኖ ሲያሰማ፣ ሰቀሉከ ውስተ
አፍኣ ብዙኃን አይሁድ እግዚአብሔር ንጉሥ፣
አገባብ በመጨረሻ ሲያሰማ መጽኡ መንግሌከ
ምሥጢራተ ሥጋ ይስምዑ ቅንዋተ ሥጋ አርድእት
ሲል ስህተት ነው። ምክንያቱም ከላይ አገባብ
ከመጀመሪያ ሆኖ እንጂ ከመጨረሻ ሆኖ
አያሰማምና።
አገባብ በመጀመሪያ ሲያሰማ፣ ኦ አምላክ ባዕለ ፀጋ
መንግሌከ መጽኡ ቅንዋተ ኀጢን አርድእት ሲል
ይቃናል።
ዘርፍ በመጨረሻ ሲያሰማ ተክእወ ደመ ግቦከ
በኢየሩሳሌም ቀትል ምዕላደ በሊህ ኩናት
እግዚአብሔር ንጉሥ።

ዘርፍ በመጀመሪያ ሲያሰማ አምላክ ባዕለ ጸጋ ደመ ገቦክ ተክእወ በኢየሩሳሌም ፍኖት፣
ባለቤት በመጨረሻ ሲያሰማ ተዘርኡ አጽራሪክ በኢየሩሳሌም ፍኖት እግዚአብሔር ንጉሥ ይላል፡፡
ባለቤት በመጀመሪያ ሲያሰማ ኦ አምላክ ባዕለ ጸጋ ደምክ ውሕዘ በኢየሩሳሌም ፍኖት ይላል፡፡
ሌሎቹ ግን በመጀመሪያ ወይም በመጫረሻ ሆነው ያሰማሉ መባሉ በመካከል የሆኑ እንደሆነ ሰዋስው ይጠቀጥቃቸዋል፡፡ አምላክ ደምክ ውሕዘ ሲል በሩቅ፣ ዘርፍ ነበረና የባለቤት ሰሚ ነው፡፡ አምላክ ደመ ገቦክ አድኀነ ዓለመ ሲል በሩቅ የዘርፍ ዘርፍ ነበረና የዘርፍ ሰሚ ተብሏል፡፡
ማሳሰቢያ፣ በመጀመሪያ፣ በመሀል፣ በመጨረሻ ሲባል የባለቤቱን እንጂ የአሰሚውን አለመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

፲፰. አገባብ ወድቆባቸው ዘርፍ ይዘው ወደኋላ የማይስቡ አናቅጽ፣

አገባብ ወድቆባቸው ዘርፍ ይዘው ወደኋላ የማይስቡ አናቅጽ አራት ናቸው፡፡ ምን እና ምን ናቸው ቢሉ ሳቢ ዘር፣ ንዑስ አንቀጽ፣ ሣልስ ቅጽል፣ ሳድስ ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል ውስጠ ዘ፣ ናቸው፡፡ ወይም ሳቢ ዘር፣ ንዑስ አንቀጽ፣ ሣልስና ሳድስ ቅጽል፣ መስም እና መድበል ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል ናቸው፡፡ ሲቆጠሩ ሣልስና ሳደስ አንድ ወገን፣ መስምና መድበል አንድ ወገን፣ ሆነው ነው፡፡ አገባብ ሳይወድቅባቸው ግን ዘርፍ ሳይዙ አርፈው ተነስተው ወደኋላም ወደፊትም ይስባሉ፡፡ ለምሳሌ፣

መጽሐፈ በእሙር፣
መጽሐፈ በአእማሪ፣
መጽሐፈ በአእምሮ ከብረ ጴጥሮስ፣

ሰማየ በዕርገት ከብረ ኤልያስ አይልም።
ጸያፍ ነው፡ ጸያፍነቱም ከፍሎ ጠብቅ ነው።
ከኋላ መሳብ ነው።
ማለት ያለበት፣
እሙረ ልብ መጽሐፈ፣
አእማሬ ልብ መጽሐፈ፣
አእምሮ ልብ መጽሐፈ፣
ኤልያስ በዕርገተ ሠረገላ ሰማየ ከብረ ነው።
እንዲሁም ኤልያስ ዕርገተ ሠረገላ ሰማየ
አፍቀረ ይላል።
ገነተ ለበዊእ ጻድቀን ተግሁ አይልም /ከኋላ መሳብ ነው/።
ተግሁ ጻድቃን ለበዊአ ገነት ይላል እንጅ።
ገነተ በዊአ ጻድቃን ተዐውቀ አይልም።
በዊአ ጻድቃን ገነተ ተዐውቀ ይላል እንጅ።
ምሥጢረ ለአእማሪ ጴጥሮስ ጸውዖ እግዚኡ አይልም።
ለጴጥሮስ አእማሪ መጽሐፈ ጸውዖ እግዚኡ ይላል እንጅ።
ምሥጢረ አእማሬ ልብ ጴጥሮስ ተጸውዐ አይልም።
ተጸውዐ ጴጥሮስ አእማሬ ልብ መጽሐፈ ይላል እንጅ።
ስለሳድስ ቅጽል መሳብና አለመሳብ በደቂቅና ዐዋጅ መካከል የተለያየ አስተያየት አለ። ደቂቅ፣ ሳድስ ቅጽል ይስባል ሲል ፈለገ እግዚአብሔር ምሉዕ ማያተ ያለውን ሲያውጅ ነው። ዐዋጅ አይስብም ማለቱ፣ ፈለገ እግዚአብሔር ምሉዕ ማያተ ሲል ስህተት ነው ማለቱ ነው ወይም መባል የለበትም ማለቱ ነው። ነገር ግን ንዑሳን አናቅጽ ሁሉ ይስባሉ፣ አያሥሩም የሚለውን ዐዋጅ መሠረት በማድረግ ሳድስ ቅጽል አይስብም የሚለውን ትተን ይስባል የሚለውን ልንከተል ይገባል።

፲፱. ተናባብያን ቀለማት፣

ተናባብያን ቀለማት አራት ናቸው። እነርሱም ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ ናቸው። ግእዝ፣ አምላክ አማልክት፣ ራብዕ፣ ደብተራ ብርሃን፣ ኀምስ፣ ብእሴ እግዚአብሔር፣ ሳብዕ መሰንቆ አርጋኖን ይላል።

፳. በዝርዝር ጊዜ በግዒርም በተግብሮም የሚከቱ ቀለማት፣

በግዒርም በተግብሮም የሚከቱ ቀለማት አራት ናቸው። ምንና ምን ናቸው ቢሉ፣ የሩቆቹ ወንዶች፣ የሩቂቱ ሴት፣ የሩቆቹ ሴቶች፣ አነ እና ንሕነ ናቸው። የሩቁ ወንድ ግን ሁ እና ኡ በመጨረሻ ሲሆኑ ካዕብ፣ ሳልስ ራብዕ፣ ኀምስ ሲከተሏቸው በግዒርም በተግብሮም ይከታሉ። ለምሳሌ፣
ሐነጹ ቤቶሙ፣ ተሐንጸ ቤቶሙ፣ ሐነጸት ቤታ፣ ተሐንጸ ቤታ፣ ሐነጻ ቤቶን፣ ተሐንጸ ቤቶን፣ አነ ሲሆን፣ ስምኢኒ እግዚኦ ጸሎትየ፣ የሩቁ ወንድ ሲሆን፣ ከብረ አቡሁ፣ አክበረ አቡሁ፣ ከብረ እግዚኡ፣ አክበረ እግዚኡ፣ ወረደ መናሁ፣ አውረደ መናሁ፣ ተመትረ እዴሁ፣ መተረ እዴሁ፣ ተእኅዘ መሰንቆሁ፣ አኅዘ መሰንቆሁ ይላል።
ማሳሰቢያ፣ ይህ የሚሆነው በዝርዝር ጊዜ ብቻ መሆኑን አስተውል።
ክፍል አራት፣
አምስት ነገሮችን የያዙ አዋጆች

፳፩. አርእስተ ሰዋስው /አዕማድ/፣

አርእስተ ሰዋስው የሚባሉ አምስት ናቸው። ቅደም ተከተላቸውን በተመለከተ የተለያየ አመለካከት አለ።

በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት የያዙት ቅደም ተከተል፣ አድራጊ፣ አስደራጊ፣ ተደራጊ፣ ተደራራጊ፣ አደራራጊ /1948፣ 49/ ሲሆን፣
በአለቃ ታየ መጽሔት ደግሞ አድራጊ፣ አስደራጊ፣ አደራራጊ፣ ተደራራጊ፣ ተደራጊ ነው። በዋድላ /ቡሩኬ እና ጌቴ ገሞራው/ እና በጎንጅ አገባብ ደግሞ የተሰጣቸው ቅደም ተከተል አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ፣ ተደራራጊ፣ አደራራጊ ነው።
ዋሽራዎች ደግሞ ቅደም ተከተላቸው እንደአለቃ ታየ አድራጊ፣ አስደራጊ፣ አደራራጊ፣ ተደራራጊ፣ ተደራጊ መሆኑን በመግለጽ ድርጊት ፈጻሚ፣ ድርጊት አቀባይ፣ ድርጊት አቀባባይ፣ ድርጊት ተቀባባይ፣ ድርጊት ተቀባይ የሚል ስያሜ ጨምረውላቸዋል። በአጠቃላይ ሦስቱ የገቢር ግሶች ከቀደሙ በኋላ ሁለቱ የተገሮ ግሶች ይከተላሉ። እነዚህ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው በእኛ በኩል ግን የጉባኤ ቤቱን ይዘን ማብራሪያውን እናስከትላለን።
ተደራጊ፣ ፩ ፩ ይስባል፣ አድራጊና ተደራራጊ ሁለት ሁለት ይስባል። አስደራጊና አደራራጊ ሦስት ሦስት ይስባሉ።
አድራጊ ሲገባ፣ ዳዊት ቀተለ ያርዮንሀ ይላል።
ተደራጊ ሲገባ፣ ተቀትለ ያርዮ ይላል።
አስደራጊ ሲገባ፣ ይሁዳ አቅተለ አምላክ በአይሁድ ይላል።
ተደራራጊ ሲገባ፣ ተቃተለ ጊዮርጊስ ምስለ አሕዛብ ይላል፣
አደራራጊ ሲገባ፣ ኢዮአብ አስተቃተለ ሰብአ ምስለ ሰብእ ይላል።
በውድ ሲስቡ ተደራጊ አምስት፣ አድራጊ ተደራራጊ ስድስት ስድስት፣ አስደራጊ አደራራጊ ሰባት ሰባት ይስባሉ። ተሳቢ ማለት የግድ ን የሚወጣበት ቀለም ማለት አይደለም። በሰዋስው ሁሉም ነገር በአንቀጽ ይሳባል። ስለዚህ መቆጠር ያለባቸው ባለቤቱን ጨምሮ ሁሉም ሐረጎች ናቸው።

በውድ ሲስቡ፣
አድራጊ፣ ዳዊት ቀተለ ያርዮህ በሰይፍ እምነገረ
ቤርሳቤሕ ጊዜ ጸብእ ማዕከለ ጉባኤ።።
ተደራጊ፣ ተቀትለ ያርዮ በሰይፍ እምነገረ ቤርሳቤሕ
ጊዜ ጸብእ ማዕከለ ጉባኤ፣
አስደራጊ ሲስብ፣ ይሁዳ አቅተለ አምላከ ለአይሁድ
በመስቀል እምነገረ ብሩር ጊዜ ጸብእ ማዕከለ ጉባኤ።።
ተደራራጊ፣ ጊዮርጊስ ተቃተለ ምስለ አሕዛብ በሰይፍ
እምነገረ ሃይማኖት ጊዜ ጸብእ ማዕከለ ጉባኤ።።
አደራራጊ ሲስብ፣ ኢዮአብ አስተቃተለ ሰብአ ምስለ
ሰብእ በሰይፍ እምነገረ መንግሥት ጊዜ ጸብእ ማዕከለ
ጉባኤ ይላል።።

፷፪. ፍርቅ የሚሆኑ ነገሮች፣

ፍርቅ የሚሆኑ ነገሮች አምስት ናቸው።። እነርሱም
የሰምና ወርቅ፣ የሳቢና የተሳቢ፣ የአንቀጽና የአገባብ፣
የዘርፍና የባለቤት፣ የቅጽልና የባለቤት ናቸው።።
የሰምና የወርቅ ፍርቅ ሲገባ፣ ዝናም መጽአ ሆሣዕና።።
የሳቢና የተሳቢ ፍርቅ ሲገባ፣ ኢያቄም ወስኮ ኢክህለ
በቆመ ሐና አሐደ እመቱ።።
ኢያቄም ወስኮ ኢክህለ አሐደ እመቱ እምዲበ
ቆሙ።።
የአንቀጽና የአገባብ ፍርቅ ሲገባ፣ ዳዊት ተፈሥሐ
እስመ አመ ነግሠ ሳያል ሞተ።።
የዘርፍና የባለቤት ፍርቅ፣ ሲገባ ደሙ ተክዕወ
ለአምላክ።።
የቅጽልና የባለቤት ፍርቅ ሲገባ፣ እስመ ናሁ ንጉሥኪ
በጽሐ ዘያበርህ ለኪ በኃይሉ አይልም።። ዘያበርህ
ቸልታ ሆኖ ከተፈታ ይሆናል፡ የሚሉ አሉ።። ነገር
ግን ንጉሥኪ በውስጠ ተሳሳቢ ጊዜ ለዘያበርህ ለኪ
ስለሚሳብ ይህም አይሆንም።። እስመ ናሁ ንጉሥኪ
ዘያበርህ ለኪ በኃይሉ በጽሐ ብሎ ዘያበርህ /ዘን/
ለንጉሥኪ ቀጽሎ ቢተረጎም የተሻለ ይሆናል።።

፷፫. ነባር አምስት ስለመሆናቸው፣

ነባር የሚባሉ አምስት ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ የአንቀጽ፣ የአገባበ፣ የቦታ፣ የስም፣ የዝርው ሰዋስው ናቸው። የአንቀጽ ነባሮች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ የጽድቅና የአሉታ ይባላሉዕዕ የጽድቅ፤ ቦ፣ ውእቱ፣ ሎ ሲሆኑ የአሉታ ደግሞ አልቦ፣ አኮ፣ ኢ፣ ሐሰ ወዘተ...ናቸው። የአገባብ፣ እስመ፣ አኮኑ፣ የስም አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ የቦታ፡ ይሁዳ፣ ሰማርያ፣ የዝርው ሰዋስው፣ እብን፣ ዕፅ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ /ጉልት ናቸው/።

እነዚህን እንደገና በሁለት መክፈል ይቻላል። እነርሱም፣

ሀ. ነባር አንቀጽ /ቦ፣ አልቦ፣ አኮ፣ ውእቱ፣ ወዘተ፣

ለ. አንቀጽነት የሌላቸው ነባሮች፣ ናቸው።

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አንቀጽነት የሌላቸውን ነባሮች ደግሞ በአምስት መክፈል ይቻላል።

፩÷ የባሕርይ ስም /የአምላክ ስሞች፣ የመላእክት ስሞች፣ ተፈጥሮን የሚገልጹ ስሞች/፣

፪÷ የሰው ስሞች /የተጸውዖ ስሞች፣ የተቀብዖ ስሞች/፣

፫÷ የቦታ ስሞች /ኢትዮጵያ፣ ግብፅ፣ አስክንድርያ፣ ኢየሩሳሌም/፣

፬÷ ብትን ሰዋሰው /እብን፣ ዕፅ፣ ያፍ፣ አንበሳ፣ እክል፣ ሣዕር/፣

፭÷ አገባብ /አመ፣ ከመ፣ እመ፣ አምጣነ፣ ዲበ፣ አይቴ ወዘተ/።

፳፬. ን የሚሆኑ ቀለማት፣

ን የሚሆኑ ቀለማት አምስት ናቸው። ምንና ምን ቢሉ ለ፣ በ፣ እንተ፣ ውስተ፣ ላዕለ፣ ናቸው።
ለ ሲገባ ሰብሑ ለስመ እግዚአብሔር፣
በ ሲገባ ወርእየት ዐይንየ በጸላዕትየ፣
እንተ ሲገባ ወአዕረጎሙ ደብረ ነውኅ እንተ ባሕቲቶሙ፣
ውስተ ሲገባ ወረገዘኒ ውስተ ኵልያትየ፣
ላዕለ ሲገባ አበስኩ ላዕለ እግዚአብሔር ይላል።

፳፭. የግስ መነሻ የሚሆኑ ቀለማት፣

የግስ መነሻ የሚሆኑ ቀለማት አምስት ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ ናቸው። በቅኔ ምሁራን መራኁት የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል። መራኁት ማለትም መከፈቻዎች ማለት ነው። መረኁት በር እንደሚከፍቱ ሁሉ የግስ እርባታ የሚከፈተውም በእነዚህ ነውና።

፳፮. በራሳቸው ጀምረው በራሳቸው የሚጨርሱ ቀለማት፣

በራሳቸው ጀምረው በራሳቸው የሚጨርሱ ቀለማት አምስት ናቸው። ምንና ምን ቢሉ፣ ሰ፣ ተ፣ አ፣ ወ፣ ፈ ናቸው።
ሰ፣ ሰደሰ፣ ተ፣ ተትሕተ፣ አ፣ አስተጋብአ፣ ወ፣ ወርዘወ፣ ፈ፣ ፈልሰፈ ማለቱን ያሳያል።

፳፯. ሰ የሚያነሳቸው ቀለማት፣

ሰ የሚያነሳቸው ቀለማት አምስት ናቸው። እነርሱም ግእዝና ሳድስ ሲቀሩ በሌሎች ፊደላት

የሚጨርሱትን ሁሉ ነው። ለምሳሌ ካዕብ፣ ዝንቱሰ፡ ሣልስ፣ ብንያሚሰ፡ ራብዕ ደብተራሰ፡ ኀምስ፣ ሙሴሰ፡ ሳብዕ መሰንቆሰ፣ ቀራንዮሰ ማለቱን ያሳያል። በሳድስ ግን ዝ ብቻ ይገኛል። ዝሰ ብሎ ያነሳልና። ሌሎች በሳድስ የሚደርሱ ቀለማት ሁሉ አይነሱም።
ይህን ዐዋጅ የሚያፈርሱ አሉ። ካዕቡን በገቢር ጊዜ ግእዝ ይወርሰው ነበር። ሰ አዋጁን በግእዝ ያፈርሰዋል። አሐደሰ፣ ክልኤተሰ፣ ብሎ ያነሳል። ሳድስና ግእዝ አንድ ቀለም ቢገኝ ወዳቂ ነውና ስለሚያነሳ ዝሰ፣ ዘሰ፣ ብሎ ያነሳል። አገባብ ሲሆን ግን እለሰ፣ እመሰ፣ ኀበሰ፣ ብሎ አይነሳም። ምክንያቱም አገባብ ራሱን ችሎ ስለማይቆምና ወዳቂ ይሁን ተነሽ ይሁን አይታወቅምና አይነሳም።

፳፰. የቅጽል አወዳደቅ፣

አገባብ ሲወድቅባቸው፣

እምአምላክ ዘተሰቅለ በመስቀልተክዕወ ደም ይላል።
እምአምላክ ዘበመስቀል ተሰቅለ ተክዕወ ደም ይላል።
እምአምላክ በመስቀል ዘተሰቅለ ተክዕወ ደም ይላል።
እምዘተሰቅለ በመስቀል አምላክ ተክዕወ ደም ይላል።
ግን እምዘተሰቅለ አምላክ በመስቀል ተክዕወ ደም፣ ወይም እምዘአምላክ ተሰቅለ በመስቀል ተክዕወ ደም አይልም። ምክንያቱም በመስቀል የሚለው አምላክን አልፎ ለእምዘተሰቅለ መሳብ ስለማይችል ነው። ብሎ ቢገኝ የባለቤት ግስግስ ጸያፍ ነው።
ቅጽል ሳይወድቅባቸው፣
አምላክ ዘተሰቅለ በመስቀል አድኅነ ዓለመ፣
አምላክ ዘበመስቀል ተሰቅለ አድኅነ ዓለመ
አምላክ በመስቀል ዘተሰቅለ አድኅነ ዓለመ
ዘተሰቅለ በመስቀል አምላክ አድኅነ ዓለመ
ዘበመስቀል ተሰቅለ አምላክ አድኅነ ዓለመ
በመስቀል ዘተሰቅለ አምላክ አድኅነ ዓለመ ይላል።

ክፍል አምስት፣
ስድስት ነገሮችን የያዙ አዋጆች፣

፳፱. የሰምና ወርቅ አመሳሰል፣

ሰምና ወርቅ ሲመሰሉ ፊትና ኋላ ይነገራሉ፡፡ ሰም ይቀድማል ወርቅ ይከተላል፡፡ ወርቅ ቀድሞ ሰም ቢከተል ካልተናበበ ጸያፍ አይባልም፡ ከተናበበ ግን ግንባር ጸያፍ ይባላል፡፡ ለምሳሌ ጎብስተ ጎይማኖት እንጅ ጎይማኖተ ጎብስት አይባልም፡፡
ሰም ተናቦ ለወርቅ ሦስት ፊደላት ያስቀርለታል፡፡ ፊደላቱም ግእዝ፣ ጎምስ እና ሳብዕ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ሐነጸ መቅደሰ ደሙ ሲል ግእዝን ያስቀራል፡፡
ባይናበብ ኖሮ ደመ ይል ነበር፡፡
ሐነጸ መቅደሰ ደሙ ማሕየዊ ሲል ጎምስን ያስቀራል፡፡ ባይናበብ ኖሮ ማሕየዊ ይል ነበር ደሙ የሚለውም ደሞ ይሆን ነበር፡፡ በዚህም ሳብዕን አስቀርቷል፡፡
ሰም ለወርቅ ስድስት ነገር ያተርፍለታል፡፡ እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩. ዝርዝር ፬. አፈታት/አቅራቢ
፪. ቅጽል ፭. አንቀጽ
፫. ተናባቢ ፮. ተጠቃሽ

ከዚህ የሚከተለው ምሳሌ ሰም ለወርቅ ስድስት ነገሮችን እንዳተረፈለት ያሳያል፡፡
እመ ርኅራኄ ቤተ ክርስቲያን፡ ትወግዕ ጥዑመ፡ ሥጋዌ፡ ሀሊበ እግዚእነ፡ ለደቂቃ ምእመናን በይነ ዘአእመረት ከመ ይከውኖሙ ሕይወተ ዘለዓለም፡ ጎይለ ሥጋ፡፡
ትወግዕ በማለት ማሠሪያ ማትረፉን፣ ጥዑመ በማለት ቅጽልን፣ ሀሊበ እግዚእነ በማለት
ተናባቢን፣ ሥጋዌ ወትትን በማለት አፈታትን፣ በይነ ዘአእመረት በማለት አንቀጽን፣

ለደቂቃ በማለት ዝርዝርን እንዳተረፈለት ያሳያል።
በተጨማሪም ሰም ለወርቅ ዝርዝር ሲያተርፍ ተፈሥሐ ጴጥሮስ እስመ ተሠርዐ ሃይማኖት ኅብስቱ ይላል። ሃይማኖቱ ቢል ወርቅ ለሰም ዝርዝር አይተርፈውምና ጸያፍ ነው።
አቅራቢ ሲሆን ተፈሣሕከ ጴጥሮስ ባዕል እስመ ተሠርዐ ሃይማኖት ኅብስትከ ይላል። ሃይማኖትከ አይልም። ብሎ ቢገኝ **የስርቅ** ኅዳና ጸያፍ ይባላል።
ተናባቢ ሲሆን ኅብስተ ሃይማኖት ጥዑም ተሠርዐ ይላል።
ቅጽልን ጥዑም በሚለው፣ አንቀጽንም ተሠርዐ በሚለው ማየት ይቻላል።
የአገባብና የፍች አምላክ ኅብስተ ሕይወት ተሠርዐ በመሶብ መስቀል ይላል። ይህ አባባል በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። የሚሰጠው ምክንያትም በ በወርቁ ላይ መውደቅ አለበት የሚል ነው። ነገር ግን በመስቀል መሶብ ወይም በመሶብ መስቀል ቢል የሚከለክል ሕግ ሰዋስው የለም። አገባብ በወርቅም በሰምም ላይ ይወድቃልና።
ተጠቃሽ ሲሆን ጳውሎስ በላኢሁ ለወንጌል ኅብስት ይላል።

፴. ዝርዝር ስድስት ስለመሆናቸው፣

ዝርዝር ስድስት ናቸው። ምንና ምን ቢሉ ኀምስ ሲቀር በስተቀር ሌሎቹ ስድስት ፊደላት ይዘረዝራሉ። ቤት የሚለውን ቃል ወስደን ብንዘረዝረው ተሐንጸ ቤትየ፣ ቤትነ፣ ቤቱ፣ ቤቶሙ፣ ቤትኪ፣ ቤታ፣ ቤቶን፣ ቤቶ፣ ቤትከ፣ ይላል። ቤታዬ፣ ቤቴ ግን አይልም። በአንቀጽ ግን መምህራን አቅንተውታል። ለምሳሌ ፣ አእመረከ፣ አእመሮሙ፣ አእመረክሙ፣ አእመረኒ፣ አእመረኪ፣ አእመርክኒ፣ አእመራ፣ አእመርካ፣ አእመሮን፣ አእመረክን፣ አእመሮ፣ አእመርኮ፣ ይሉታል።

በባዕድ ሲዘረዝር እዴሁ ያለውን እዴሆሙ ብለው ወስደውታል። ሙ የባዕድ ዝርዝር ድርብ ነው። እንዲሁም ዔሊ ወድቀ እመንበሩ ወተሰብረ እምዘባኑ እስመ ልሂቅ ብእሲሁ፣ ማርያም ተፈጥረት ለቤዛ ዓለሙ በማለት ይዘረዝራል። ግን ብእሲሁ ለእገሌ፣ ብሎ፣ ለቤዛ ዓለሙ ለእገሌ ብሎ ዘርፍ አይቀበልም፣ ወይም ለ የለውም።

፴፩. ተቃራንያን /ተወራራሽ/ ቀለማት፣

ተቃራንያን ቀለማት ስድስት ናቸው። ምንና ምን ቢሉ፣ ራብዕ ሲቀር ሌሎቹ ማለትም፣ ግእዝ፣ ካዕብ፣ ሣልስ፣ ኀምስ፣ ሳድስ፣ እና ሳብዕ ናቸው። ለምሳሌ፣
ተሐንጸ ቤት ያለውን ሐነጸ ቤተ፣
ተሐንጸ ቤቱ ያለውን፣ ሐነጸ ቤቶ፣
ተቀትለ ብእሲ ያለውን ቀተለ ብእሴ፣ ይላል።
ራብዑ ግን ተፈቃቃሪ ነው። ተተክለ ደብተራ ያለውን ተከለ ደብተራ ይላል።
ካዕብ፣ ሣልስ እና ሳድስ ተገብሮ ናቸው። ለፍጹማን ግን ሰባቱም ገቢር ናቸው። ለምሳሌ፣ ሐነጸ ቤተ፣ ተቀብዐ ናርዱ፣ ኰነነ ኢሎፍሊ፣ ተከለ ደብተራ፣ ቀሠመ ጽጌ፣ ስምዐኒ እግዚኦ ጸሎትየ፣ ሰንቀወ መሰንቆ፣ ማለቱን ያሳያል።
አቅንተውም ተናግረውታል። ለምሳሌ ከሠተ አፉሁ፣ ቀተለ ጸላኢሁ፣ ተከለ ደብተራሁ፣ ተጎዕበ እዴሁ፣ ሐነጽኩ ቤትየ፣ ሰንቀወ መሰንቆሁ፣ ማለቱን ያሳያል።
<u>የሀገር ስም በገቢር ተገብሮ ጊዜ</u>፣ በግእዝ፣ በራብዕ፣ በኀምስ፣ በሳብዕ፣ በካዕብ፣ በሣልስ የሰየፈ የሀገር ስም አይቃረንም። ለገቢር ለተገብሮ ይከታል። ለምሳሌ ወረደ ባቢሎን፣ ኰነነ ኢሎፍሊ፣ ኰነነ ሳሌም፣ ሖረ ኢየሩሳሌም ይላል። ፍጹም ሳድስ የሆነ ሀገር ስም ሲሆን ግን ይቃረናል ማለትም የመጨረሻውን ግእዝ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ ግብፅ፣ ምሥር፣ ፅርዕ ያለውን፣ ግብፀ፣ ምሥረ፣ ፅርዐ ይላል። ያለተወራራሽ የሚገቡ

አጎዝና አጻፋ ቅጽል ናቸው፡፡ ምሳሌ አሐዱ ያለውን አሐደ፣ አሕቲ ያለውን አሐተ፣ ይላል፡፡ ዜንቱ ያለውን ዘንተ፣ እሎንቱ ያለውን እሎንተ ይላል፡፡

ክፍል ስድስት፣
ሰባት ነገሮችን የያዙ አዋጆች፣

፴፪. ቅጽል ሰባት ስለመሆናቸው፣

ቅጽል ሰባት ናቸው፡፡ ምንና ምን ቢሉ ጥሬ ዘርና ነባር፣ ደቂቅና ንዑስ፣ አጎዝና ወገን፣ ግልጸ ዘ እና ውስጠ ዘ /አንድ ወገን/ ናቸው፡፡ ሲቀጸሉም ጥሬና ነባር ዘርፍ ይዘው፣ ንዑስና ደቂቅ አገባባት ከፊት ለፊት ማለትም ከመጀመሪያ ሆነው፣ አጎዝ ለዘርፍ ካልሆነ ከመካከል ሆኖ አይቀጸልም፡፡ ወገን ከፊቀደው ሆኖ ይቀጸላል፡፡ ግልጸ ዘ እና ውስጠ ዘ **መከዳ** ሆነው ይቀጸላሉ፡፡ ሁሉም ከዘ ጋር መከዳ ሆነው ይቀጸላሉ፡፡ ንዑስ፣ ደቂቅና አጎዝ ከፊት /ከመጀመሪያ/ ሆነው ይቀጸላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

አይ ልሳን፣ አይ ልቡና፣ ምንት ነገር፣
ተፈነወ ጎቤነ ውእቱ ሚካኤል እስመ ውእቱ ያድኅነነ፣
አሐዱ አምላክ፣ ሠለስቱ ደቂቅ፣ ይላል፡፡
ወገን ቅጽል ሲሆን ኢየሱስ ናዝራዊ፣
ከለዳዊ አብርሃም፣
ሙሴ ኦሪታዊ፣
ዮሐንስ ወንጌላዊ ይላል፡፡

አጎዝ ሲቀጸል፣ ክርስቶስ አሐዱ ሙሴ አይልም፡፡ ከመሀል ስለገባ ጸያፍ ነው፡፡ አሐዱ ክርስቶስ ሙሴ ይላል እንጅ፡ አምላክ ሰማያት ሰባቱ ሙሴ፣ አምላክ ወንጌል አሐዱ ሙሴ ይላል፡፡ አሐዱ የተቀጸለው ለወንጌል መሆኑን አስተውል፡፡ ይህ ማለት ለዘርፍ ሲቀጸል ነው፡፡

ዘር /ጥሬ ዘር/ እና ነባር አጎዝ ይዘው ሲቀጸሉ፣ ዘር፣ ሲቀጸል እስራኤል ዘርዐ አብርሃም፣ ዘርዐ ያዕቆብ፣ ዘርዐ ይስሐቅ፣ ዐይን ተቋመ ብርሃን፣ አእዛን መሳክወ ሰሚዕ ይላል።።

ነባር ሲቀጸል፣ ቤተ ልሔም ሀገረ ዳዊት፣ ጊዮርጊስ ኮከበ ልዳ፣ ዘርዐ ያዕቆብ፣ ዘርዐ ይስሐቅ፣ ይላል።።

ውስጠ ዘ እና ግልጸ ዘ ሲቀጸል፡ ክቡር አብርሃም ዘተለዐለ እምኵሉ ይላል።። ሁሉም በዚህ መልክ መከዳ ሆነው ይቀጸላሉ።። መከዳ ማለት አንዱ ከስም ቀድሞ ሌላው ደግሞ ስምን ተከትሎ ሲቀጸል ነው።።

በተጨማሪም ውስጠ ዘ እና ግልጸ ዘ በቂ ሲሆኑ ቅጽል ይቀበላሉ።። ለምሳሌ ፩ዱ ዘያርዎ ፬ቱ፣ ክቡር ውእቱ፣ እያለ ይገባል።።

ደቂቅ በቂ ሲሆን ወይም አጻፋ ሲሆን በመጀመሪያ አይሆንም።። ቅጽል ሲሆን ግን ይቻላል።። በመጨረሻ ሆኖም አይቀጸልም።። ለምሳሌ ፈነወ ሚካኤለሀ እስመ ውእቱ ሚካኤል ያድኅነነ ይላል እንጅ እስመ ሚካኤል ውእቱ ያድኅነነ አይልም።። በተጨማሪም በሰምና ወርቅ መንገድ ክፍል ውስጥ ቅኔ የሚያስጀምሩና የማያስጀምሩ የሚለውን ተመልከት።።

ንዑስ በቂ ይሆናል።። ለምሳሌ መኑ አምጽኣ ለጽድቅ ሲል በቂ ነው።።

ንዑስና ደቂቅ፣ አጎዝና ጎብር ከመካከል ሆነው አይቀጸሉም።። ድንበር ናቸው።። ለምሳሌ ሚካኤል ውእቱ መምህረ ሰማይ አይልም።። አምላክ አሐዱ ዳዊት፣ አምላክ መገሥጸ ኵሉ ዳዊት አይልም።።

ለቅጽል ከቦታው ተነሥቶ ስም ይሰጠዋል።። ቅጽል በፊት ሲገባ ፊታውራሪ፣ በኋላ ሲገባ ደጀን ይባላል።። መምህራነ ሐዲስ ወንጌል ሲል ደግሞ ጥምዝ ዘርፍ ወይም ጠምዛዥ ቅጽል ይባላል።።

፴፫. የግስ ጠባይ፣

ግስ ከሰባት አይወጣም፤ ከሁለት አይወርድ። ሰባት ሲሆን አስተሰነአለ፣ ስድስት ሲሆን ቀበያውበጠ ይላል። ሁለት ሲሆን ነደ፣ ነበ፣ ቆመ፣ ሜመ ወዘተ ማለቱን ያሳያል። በአደራራጊ ጊዜ ግን ከሰባት ሊያልፍ ይችላል። ለምሳሌ አስተቀበያውበጠ የሚለውን ግስ ማየት ይቻላል።

፴፬. ሰባት አገባባትን የሚያመጡ ቀለማት፣

፬ ቀለማት ፯ አገባባትን ያመጣሉ። እነርሱም ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ ናቸው። አገባባቱም፡ ለ፣ በ፣ እም፣ ምስለ፣ ከመ፣ ኀበ፣ እስከ ናቸው። ለምሳሌ

ለን ሲያመጣ፤

አብርሃም መሐከ ነዳየ፣ ወይምሕክ ነዳየ ወምስኪነ ይላል።

ላሕመ አብርሃም በጽሐ ቅዳሴ፣ ሦዐ አብርሃም አምላኮ ይስሐቅሀ፣ ይላል።

በን ሲያመጣ፤

ቆመ ምድረ፣ ቆመ ቢታንያ፣ ቆመ ሕንደኬ፣ ቆመ ደማስቆ፣ ይላል።

ምስለን ሲያመጣ፤

አማኑኤል ተሰቅለ ፈያተ፣ አምላክ ወዐለ እንግዳ፣ አምላክ ተሰቅለ ብእሴ፣ አምላክ ተሰቅለ ፍጥረቶ፣ ይላል።

እምን ሲያመጣ፤

ተንሥአ ደብረ፣ ተንሥአ ሰማርያ፣ ተንሥአ ተሰሎንቄ፣ ተንሥአ ደማስቆ፣ ይላል።

ከመን ሲያመጣ፤

ኪሩቤል ቆሙ ሰብአ፣ ገጸ ኪሩብ ቆመ አንበሳ፣ ገጸ ኪሩብ ቆመ ብእሴ፣ ድምፀ ኪሩቤል ይነቁ መሰንቆ ይላል

ኀበን፣ አስከን ሲያመጣ፤

በጽሐ ሀገረ፣ በጽሐ አንጾኪያ፣ በጽሐ ሕንደኬ፣
በጽሐ ደማስቆ ይላል።።
ይህ ለወጣንያን ነው እንጅ ለፍጹማን ለን በተሳቢ
ሲያወጣ ነው።። በትርፍ አማርኛ አህሎ፣ መስሎ፣ ሆኖ፣
ብሎ፣ ተብሎ፣ አድርጎ፣ አሰኝቶ፣ ኛ፣ ነት ይሆናል።።
ለምሳሌ፣
አህሎ፣ መስሎ ሲሆን ወጽአ ሰይጣን ደብረ፣
መጽአ ሰይጣን አንበሳ ይላል።።
ብሎ፣ አስመስሎ ሲገባ፣
ሰይጣን ወሀበ ለነዳይ እብነ ወርቀ ይላል።።
ባዕል ጸውያ ለብእሲ ኬንያ፣
ይሁዳ አስቀሎ ለእግዚኡ አማዔ፣
ሙሴ ቀጥቀጦ ለወርቅ ግልፎ፣ ይላል።።
ተብሎ ሲሆን፣
ተሰቅለ ክርስቶስ ጎጥአ፣
ሥላሴ ጎደሩ ቤተ አብርሃም እንግዳ፣
ነበረ ብእሲ ቁልኤ ይላል።።
አድርጎ አሰኝቶ ሲሆን፣
ንጉሥ ለገብሩ ሊቀ ሜሞ፣ ኬንያ፣ ፍቁሮ
እያለ ይገባል።።
ኛ ሲሆን፣
ሐንካስ የሐውር ዝዕበ፣ ውርዝው የሐውር
አንበሳ፣ መልአክ ይትረአይ ብእሴ፣ ሕፃን
ቀነጸ ሐለስትዮ ይላል።።
ነት ሲሆን፣
ጴጥሮስ ተሠይመ ሊቀ ካህናት፣
ካህን አፍቀረ ሐራ፣
ረድእ አፍቀረ ረድዐ፣
ወልድ ከሠተ አምላኩ ይላል።።
የበ፣ የእም አወጣጥ በቦታና በጊዜ ነው።። ከነዚህ ውጭ
በስድስት ግሶች ይወጣል ግሶችም ዐብየ ቁመተ፣ ዐረየ
ክብረ፣ ጎበረ ምክረ፣ ሰክረ ወይነ፣ ቀደመ ሩጸተ፣
ወይም ዐብየ ሳያል ቁመተ፣ ንእሰ ዘኬዎስ ቁመተ፣

ቀደመ አሳሄል ሩጸተ፣ ጎብሩ /ጎበሩ/ ቃለ፣ ሰክረ ኖኅ ወይነ፣ ዐረየ ክብረ፣ ይላል።።
እም ከቦታና ከጊዜ በተረፈ ከሰባት ግሶች ይወጣል።።
ለምሳሌ ተጸነሰ ወርቀ፣ ነደየ ወርቀ፣ ርኅበ እክለ፣ ጸምአ ማየ፣ ተአርዘ ልብሰ፣ ተሀረመ ነገረ፣ ጸመ እክለ፣ ዐብየ ሰብአ፣ ንእሰ ሰብአ፣ ማለቱን ያሳያል።።
ክፍል ሰባት፣
በስምንት ነገሮች የሚነገር ዐዋጅ፣

፰ኛ. ሳቢዎች፣

ሳቢዎች ስምንት ናቸው።። ምንና ምን ናቸው ቢሉ፤ ሦስቱ ዐበይት አናቅጽ /ቀዳማይ ካልኣይ፣ ሣልሳይ/ ሲሆኑ አምስቱ ንዑሳን አናቅጽ /ዘንድ አንቀጽ፣ ቦዝ አንቀጽ፣ አርእስት ወይም ንዑስ አንቀጽ፣ ሳቢ ዘር፣ ቅጽል ማለትም ሳድስ ቅጽል፣ ሣልስ ቅጽል፣ መስም ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል፣ መድበል ቅጽል/ ናቸው።።
ንዑሳን አናቅጽ ሲሰቡ፣ አፍቀረ ጴጥሮስ ያእምር መጽሐፈ፣ ከብረ ጴጥሮስ አእሚሮ መጽሐፈ፣ ጴጥሮስ አእማሪ መጽሐፈ አፍቀረ፣ ጴጥሮስ እምረተ መጽሐፍ አፍቀረ፣ አፍቀረ ኤልያስ ዕርገተ ሰማይ ይላል።።
ዐበይት አናቅጽ ሲሰቡ አእመረ ነገረ፣ ያአምር ነገረ፣ ያእምር ነገረ ይላል።።
ሣልሳይ አንቀጽ ከቀዳማይና ከካልኣይ አንቀጽ ተለይቶ ከወ፣ ከለ፣ ከኢ፣ በስተቀር የሚጫነው አገባብ የለም።። ለ፣ ኢ፣ ወ ሲወድቁበት እንዲህ ይላል፣ ለያእምር፣ ኢ.ያእምር፣ ወያእምር ይላል።።
ከንዑሳን አናቅጽ አንዱ /ዘንድ/ ዐበይት አናቅጽን ይመስላል።። ሲመስልም፣ ዘእንበለ ያእምር፣ እምቅድመ ያእምር፣ ኢ.ያእምር ይላል።።
ቦዝን ያለ ኢ እና ያለ ወ የሚጫነው አገባብ የለም።። ሲነገርም፣ ኢ.ተዘኪሮ አበሳ ዚአነ፣ ወጸቢሖ ተማከሩ ይላል።።

ከአምስቱ ንኡሳን አናቅጽ ተለይተው ዘርፍ
የማይስማማቸው ዐበይት አገባባት፣ ደቂቅ አገባባት፣
ንኡስ አገባባት አለ፡፡ የማይወድቅባቸውም ዘንድ፣
ትእዛዝና ቦዝ ናቸው፡፡ እንዲህ ስንልም
የሚስማሟቸውና የሚጫኗቸው አገባባት አለ፡፡
እነርሱም እንበለ፡ ቅድመ፣ ከመ፣ እም፣ ኢ ናቸው፡፡
እም በዘንድ፣ ለ በትእዛዝ፣ ወ በዘንድ፣ በትእዛዝና
በቦዝ ላይ ይወድቃል፡፡ እንበለ፣ ቅድመ፣ ከመ
ለዐበይት አገባባት አውታር በጣሽ ሆነው ሲወድቁ
እስመ ከመ ይብላዕ ሐረ፣ እስመ እንበለ ይብላዕ
ሐረ፣ እስመ ቅድመ ይብላዕ ሐረ ይላል፡፡ እም
በዘንድ ሲነገር፣ እምትደቅ አሐቲ ቃል እም ኦሪት
ወእምነቢያት ይላል፡፡
ለ በትእዛዝ ሲወድቅ ለይኩን ብርሃን ይላል፡፡
ወ በዘንድ ሲወድቅ፣ መጻእኩ እምሀር ቃለ ወንጌል
ወእጸውዕ ኃጥኣነ ለንስሓ ይላል፣
ወ በትእዛዝ ሲወድቅ ይሕይወኒ ወልድየ
ወኢይሙተኒ ይላል፣
ወ በቦዝ ሲወድቅ ወተወሊዶ እግዚእ ኢየሱስ፣
ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ይላል፡፡
ኢ በዘንድ ሲወድቅ ሞተ ኢይሕምም /ሳይታመም
ሞተ/ ይላል
ኢ በቦዝ ላይ ሲወድቅ ኢተዘኪሮ አበሳ ዚኣነ ይላል፡፡
ከላይ ለተጠቀሱት /ቅድመ፣ እንበለ፣ ከመ፣ እም፣ ኢ/
ሙያ ሲሰጥ ንደሚከተለው ነው፣
እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ሲል፣ እም ቅድመን
አዳማቂ፣ ቅድመ ፍችው ሳ፣ ሙያው አለታ፡፡
ይትፈጠር ዘንድ አንቀጽ፣ ይስባል እንጂ አያስርም፡፡
ቅድመ ይብላዕ ሲል፣ ዝኒ ከማሁ፡፡
ዘእንበለ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ፣ ሲል ዘ
እንበለን አዳማቂ፣ እንበለ ፍችው ሳ፣ ሙያው
አለታ፡፡ ይትወለድ ዘንድ አንቀጽ፣ ይስባል እንጂ
አያስርም፡፡
እንበለ ይትወለድ አብርሃም ሲል፣ ዝኒ ከማሁ፡፡

ከመ ሲገባ፤ ተወልደ እምድንግል ከመ ያድኅኖ ለአዳም /አዳምን ያድነው ዘንድ ተወለደ/ ከመ ያድኅኖን አዳማቂ፤ ያድኅኖ ዘንድ አንቀጽ ይስባል እንጂ አያስርም፡፡ እም ሲገባ፤ እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእምነቢያት ሲል /አንዲት ቃል ክትወድቅ ወይም ከምትወድቅ/ እም ፍቸው ክ፤ ሙያው አበላላጭ፤ አብላጭ፤ ትደቅ ዘንድ አንቀጽ፡ ይስባል እንጂ አያስርም፡፡
ኢ በዘንድ ሲገባ፤ ኢይብላዕ ሐረ፤ ፍቸው ሳ፤ ሙያው አለ፡ታ፡ ይብላዕ ዘንድ አንቀጽ፡ ይስባል እንጂ አያስርም፡፡
ኢ በቦዝ ሲገባ፤ ኢተዘኪሮ አበሳ ዚኣነ /በደላችንን ሳያስብ/ ሲል፤ ኢ ፍቸው ሳ፤ ሙያው አለ፡ታ፤ ተዘኪሮ ቦዝ አንቀጽ
ወ በቦዝ አንቀጽ ላይ ሲወድቅ፤ ወጸቢሑ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት /በነጋ ጊዜ፤ ሲነጋ/ ወ ፍቸው ጊዜ፤ ሙያው አዳማቂ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ሙያ መስጠት ይቻላል፡፡
ይቤ እና ብህለ ዘማች አናቅጽንና ነባር አናቅጽን በሙሉ ይስባሉ፡፡ ይቤ ነባር አንቀጽ ሲስብ፤ አነ ውእቱ ወኦ፤ አልፋ ይቤ እግዚአብሔር፤ ዘማች አንቀጽ ሲስብ፤ ይቤ እግዚአብሔር ኢታምልኩ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ፡፡
ብህለ ሲስብ፤ ተብህለ በኦሪት አክብር አባከ ወእመከ፤ ይቤ እና ብህለ እርስ በእርሳቸው ይሳሳባሉ፡፡ ምሳሌ፤ ትቤ ኦሪት አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ይቤ ወንጌል፡፡ ተብህለ በኦሪት አፍቅሩ ጸላእተክሙ ይቤ ወንጌል፡፡ ይቤ መምህር ተብህለ በኦሪት ኢትቅትል ነፍሰ፡፡ ብህለ ሙሴ ይቤ እግዚአብሔር ኢታምልኩ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ ተብህለ በወንጌል፡፡

፴፮. አብዥዎች፣

አብዥር ቀለማት ስምንት ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢለ፣ አ፣ ን፣ ት፣ ሙ፣ ይ፣ ው፣ ህ፣ ል ናቸው።
ለምሳሌ፣

አ ሲሆን፣ ደብር ያለውን አድባር፣
ን ሲሆን፣ ጻድቅ ያለውን ጻድቃን፣
ት ሲሆን፣ ካህን ያለውን ካህናት፣
ሙ ሲሆን፣ አንተ ያለውን አንትሙ፣ ኩሉ ያለውን ኩሎሙ
ይ፡ ያ ሲሆን፣ አንስት ያለውን፣ አንስትያ፣ ሌሊት ያለውን ለያልይ
ው ሲሆን፣ አብ ያለውን አበው፣
ህ/ሕ ሲሆን፣ መጥባሕት ያለውን መጣብሕ፣
ል ሲሆን፣ ኪሩብ ያለውን ኪሩቤል ማለቱን ያሳያል። ስማቸው ምዕላድ ተባለ እንጅ አብዥዎች ናቸው።

አብዥዎች ስድስት ናቸው የሚሉም አሉ። ምንና ምን ቢሉ ት፣ ን፣ እ፣ ው፣ ይ፣ ል ናቸው። ት፣ መላእክት፣ ን፣ ጻድቃን፣ ዕ መዛርዕ፣ ይ፣ ላዕላይ፣ ው፣ አበው፣ ል፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌል ማለቱን ያሳያል። ገራህት ያለውን ገራውህ ይል የለምን ቢሉ ሀ እና አ በእርባ ቅምር አንድ ስለሆኑ ብሎ ለብቻው አልቆጠረውም። ህሉና፣ ልቡና ይል የለምን ቢሉ ሳድሱን ከተናገረ ራብዑንም ይጨምራል ብሎ፣ ሐዳስዩ ይል የለም ቢሉ ይን ከተናገረ ብሎ በዚያው አካቷቸዋል የሚል ማብራሪያ ይሰጣሉ። ሆኖም ትክክለኛው ዐዋጅ ምዕላድ ስምንት ናቸው የሚለው ነው።

ክፍል ስምንት፣
በዘጠኝ ነገሮች የሚነገር ዐዋጅ፣

፴፯. ለ ዘጠኝ ነገር ስለመሆኑ፣

ለ ዘጠኝ ነገር ይሆናል። ምንና ምን ቢሉ፣ በቁም ቀሪ፣ አዳማቂ /አቀብሎ ሸሸ/፣ ተሳቢ፣ ተጠቃሸ፣ ወደ፣ በ፣ ከ፣ ጋራ፣ ጊዜ፣ ናቸው።
በቁም ቀሪ ሲሆን በርህ ሠረቀ ለጻድቃን ይላል።
ተሳቢ ሲሆን ሰብሑ ለስመ እግዚአብሔር ይላል።
አዳማቂ ሲሆን ለእመ ሀሎ ጳጳስ ይባርክ ይላል።
አቀብሎ ሸሸ ሲሆን ለይኩን ብርሃኑ ለዓለም ይላል።
ተጠቃሸ ሲሆን ቃኤል ቀታሊሁ ለአቤል፣
ተጠቃሸ መባሉ ዘርእና ባለቤት በማያያዙ ነው።
በ ሲሆን አምጽአ ርኀበ ለብሔር ይላል።
ወደ ሲሆን ወኮነ ዐፅመ ያዕቆብ እም ግብፅ ለከንአን ይላል።
ከ ሲሆን በአኀዝ ይነገራል። ለምሳሌ አካለ ኢሳይያስ ተከፍለ ለክልኤ ይላል።
ጊዜ ሲሆን ሀበነ ረድኤተ ለምንዳቤነ ወይም ወረዳኢነ ውእቱ ለምንዳቤነ ይላል።
ጋራ ሲሆን ወኰነ ራፋስቂስ እንዘ ይትቃተል ለሎምና ይላል።
ን ሲሆን ዮሐንስ በደሮ ለጴጥሮስ በጺሐ ኀበ መቃብር ይላል።

፴፰. በ ዘጠኝ ነገር ስለመሆኑ፣

በ ዘጠኝ ነገር ይሆናል። ምንና ምን ቢሉ፣ ጋራ፣ እንደ፣ ጊዜ፣ ዘንድ፣ ወደ፣ ላ/ ለ፣ ን፣ ቸልታ/ ቦዝ፣ በቁም ቀሪ ናቸው።
በቁም ቀሪ ሲሆን ተሰቅለ በመስቀል ይላል።
አዳማቂ ሲሆን በከመ ይቤ ዳዊት።
እንደ ሲሆን ጽድቅ በወልታ የዐውደከ ይላል።
ወደ ሲሆን ወመንፈስ ቅዱስ ይመርሐኒ በምድረ ጽድቅ ይላል።
ጊዜ ሲሆን ተዘከረኒ እግዚኦ በምንዳቤየ፣ ወታቀንተኒ ኃይለ በጸብእ ይላል።

ጋራ ሲሆን እግዚአብሔር ይመጽእ በአእላፍ መላእክቲሁ ይላል።።
ቸልታ ሲሆን ሐዋርያት መሀሩ በዘብድዎ ጠሊ ወበሐሜለት ይላል።።
ተሳቢ ሲሆን ወኢይሠምር እግዚአብሔር በአቁያጽ ብእሲ።።
ዘንድ ሲሆ በእግዚአብሔር ትከብር ነፍስየ፣ ተዐውቀ እግዚአብሔር በይሁዳ ይላል።።
ለ ሲሆን ኢይትናጸሩ ኪሩቤል ገጸ በገጽ ይላል።።
ላ ሲሆን አ በሚል አማርኛ ይገባል።። ዐይነ በዐይን ይላል።።
ቦዝ ሲሆን ዘነበበ በነቢያት ይላል።።

ክፍል ዘጠኝ፣
በዐሥር ነገሮች የሚነገር ዐዋጅ፣

፬፱. ወደ የሚሆኑ አገባባት፣

ወደ የሚሆኑ አገባባት፣ ዐሥር ናቸው።። ማን ማን ናቸው ቢሉ ኀበ፣ መንገለ፣ እንተ፣ ውስተ፣ ለ፣ በ፣ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ ናቸው።።
ኀበ/መንገለ ወደ ሲሆን ሖረ ኀበ፣ መንገለ ሀገር፣
እንተ ሲገባ ፈነወ እዴሁ እንተ ስቁረት፣
ውስተ ሲገባ ወዐርገ ሰናክሬም ውስተ ኩላ ኢየሩሳሌም፣
ለ ሲገባ ተመይጠ ዐፅመ ያዕቆብ እም ግብፅ ለከንአን፣
በ ሲገባ መንፈስ ቅዱስ ይመርሐኒ በምድረ ጽድቅ፣
ግእዝ ሲገባ ዐርገ ደብረ፣
ራብዕ ሲገባ በጽሐ ሎዛ
ኀምስ ሲገባ በጽሐ ቴቁሔ
ሳብዕ ሲገባ በጽሐ ሴሎ ማለቱን ያሳያል።።

ክፍል ዐሥር፣

በ፲፩ ነገሮች የሚነገር ዐዋጅ፣

፴. ቸልታ የሚሆኑ ቀለማት ፲፩ ናቸው። እነርሱም እንዘ፣ ኢ፣ ወ፣ እም፣ ምስለ፣ በ፣ ቦዝ፣ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ ናቸው።
እንዘ ቸልታ ሲሆን እንዘ ይለብስ ሥጋነ ይላል፣
ኢ ቸልታ ሲሆን አልቦ አምላክ ኢ በሰማይ ወኢ በምድር ዘእንበለ አምላክነ፣
ወ ቸልታ ሲሆን ትጸርሕ ወትብል የአምር እግዚአብሔር፣
እም ቸልታ ሲሆን አምላክ አድኅነ ዓለመ እምድንግል፣
ምስለ ቸልታ ሲሆን ተሰደ ዮሴፍ ምስለ ማርያም፣
ቦዝ ቸልታ ሲሆን አእሚሮ ዮሴፍ ንጽሕና ሥጋሀ ለማርያም፣
በ ቸልታ ሲሆን በዘብድወ ጠሊ ወበሐሜለት፡
ግእዝ ቸልታ ሲሆን አምላክ አንሶሰወ ሰብአ፣
ራብዕ ቸልታ ሲሆን ተከለ እብነ ለአዳም ደብተራ፣
ኀምስ ቸልታ ሲሆን ተሰቅለ ብእሴ፣
ሳብዕ ቸልታ ሲሆን ተሰቅለ አምላክ ለአዳም ፍቁሮ ይላል።

ሁለተኛ ዐዋጅ፤

<u>ነገረ ሙሻዘር፣</u>

ሙሻዘር ማለት ማያያዣ፣ ማጣበቂየ ማለት ነው። ሙሻዘር የሚባሉት ፲፪ ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ ቀዳማይ አንቀጽ ብሎ እስከ መድበል ድረስ ያሉት ሲሆኑ እነርሱም እየዘረዘሩና እየተናበቡ ፱ አገባባትን ያመጣሉ። ከዚህ የሚከተሉት ሰባቱ ማለትም ንዑስ አንቀጽ /በሁለት ይቆጠራል/፣ ሳቢ ዘር፣ ሣልስ ቅጽል፣ ሳድስ ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል፣ መድበል ዘርዝረውም ሆነ ሳይዘረዝሩ ተናበው

አገባባን ያመጣሉ፡፡ ሌሎች አምስቱ ደግሞ ማለትም ቀዳማይ፣ ካልአይ፣ ሣልሳይ፣ ዘንድ፣ ቦዝ አንቀጽ እየዘረዘሩ አገባባትን ያመጣሉ፡፡ እነዚህ ፲፪ቱ ሙሻዘሮች የሚያመጧቸው ዘጠኝ አገባባት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣
በይነ፣ እንበይነ፣ በእንተ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ ተውላጠ ቤዛ፣ ዕሴተ ዐስበ፣ በ፣ ለ፣ እም፣ ኀበ፣ እስከ፣ ምስለ፣ ከመ፣ እንበለ ናቸው
ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ስለ የሚል ትርጉም ያላቸው ማለትም በይነ፣ እንበይነ፣ በእንተ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ ተውላጠ ቤዛ ዐስበ፣ ዕሴተ የሁሉም ትርጉም ስለ ስለሆነ አንድ ወገን ናቸው፡፡ ሌሎቹ ስምንት ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ ጠቅላላ ሲቆጠሩ ዘጠኝ ይሆናሉ፡፡
እንበለ አፍራሽ ሆኖ ይነገራል፡፡ ዝርዝር አገባቡ በቦታው ይቀርባል፡፡
ሳድስ ቅጽል፣ በአንድ ርእስ፣ ሳቢ ዘር፣ በሁለት ርእስ፣ በሁለት ሠራዊት፣ ሣልስ፣ ውስጠዘ እና ንዑስ አንቀጽ፣ በአምስት በአምስት አርእስት በአምስት በአምስት ሠራዊት ይነገራሉ፡፡
ሀ/ ንዑስ አንቀጽ በባለቤትነት ከተደራቢ ገብቶ ያለአገባብ ሲነገር፣ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣
አድራጊ፣ ለንጉሥ አዳም ቀዲሐ አማኑኤል መኰንን ወይነ ደመ እምድንግል ልሕኵት፣
ደም ወይንን ከድንግል ማሰሮ የአማኑኤል መኮንን መቅዳት ለአዳም ንጉሥ ይገባዋል፡፡
ተደራጊ፣ ለንግሥት ሔዋን ተቀድሐተ አማኑኤል ወይን በድንግል ፅዋዕ፣
በድንግል ፅዋ የአማኑኤል ወይን መቀዳት ለሔዋን ንግሥት ነው፡፡
አስደራጊ፣ ለአዳም አብ አቅድሐተ አብ ንጉሥ አማኑኤልሀ ላእከ ሥጋ ወይነ እምድንግል ልሕኵት፣
ተደራራጊ፣ ለአዳም መስፍን ተቀድሐተ አማኑኤል መአር ምስለ ሥጋ ማይ እማርያም ቀሱት፣

አደራራጊ፣ ለፍቁር አዳም አስተቃድሖተ አብ ንጉሥ አማኑኤልሀ ወይነ ምስለ ሥጋ መአር እምድንግል ልሕኵት ማለቱን ያሳያል።።
የዚህ ምሳሌ ከመለኮትና ከሥጋ ድኅነት የመገኘቱ ምሳሌ ነው።። አንድም ከወንድና ከሴት መካከል ልጅ የመገኘቱ ምሳሌ ነው።።
በአገባብ ሲገባ ግንብ ሠሪ ድንጋይና ድንጋይን ለማያያዝ ጭቃን በመካከል እንደሚያደርግ በግንብ ሠሪው ደቀ መዝሙሩን፣ በድንጊያው ሰዋስውን፣ በጭቃው አገባቡን መስለዋቸዋል።።
ከባለቤትና ከዘርፍ መካከል ከዝርዝር አንቀጽ ሽኟ አገባባት ሳቢና ተሳቢን አያይዘው ያመጧቸዋልና ስለዚህ ነው።። ከአገባብ ጋር ሲነገር /አገባብ ሲያመጣ/ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣
አድራጊ፣ ለይሁዳ እኩይ ቀቲለ ብሩር አማኑኤልሀ፡ /ስለ፣ ለ ሲወጣ/
ተደራጊ፣ ለዘካርያስ አብ ተቀትሎተ ዮሐንስ ወልድ /ስለ/
አስደራጊ፣ ለይሁዳ ገብር አቅትሎተ ብሩር አማኑኤልሀ ፍቁራኒሁ አይሁደ፣
ተደራራጊ፣ ለናቡቴ አምላክ ተቃትሎተ አዳም አፀደ ወይን ምስለ አይሁድ አክአብ ወኤልዛቤል፣
አደራራጊ፣ ለይሁዳ አክአብ አስተቃትሎተ ብሩር አፀደ ወይን ናቡቴሀ አምላክ አግብርቲሁ አይሁደ፣ /እነዚህ ሁሉ ለን፣ በይነን፣ እንበይነን፣ እንዳወጡ አስተውል/።።
በ ሲገባ፣
አድራጊ፣ ለአምላክ ዳዊት ቀቲለ መስቀል እብን ኅልያድሀ መልአከ ሞት፣
ተደራጊ፣ ለአምላክ ተሰቅሎተ መስቀል
አስደራጊ፣ ለአብ ሳያል አቅትሎተ መስቀል እብን ኅልያድሀ መልአከ ሞት፣
ተደራራጊ፣ ለዳዊት አምላክ ተቃትሎተ መስቀል እብን ምስለ ኅልያድ መልአከ ሞት፣

አደራራጊ፣ ለአዳም ሳያል አስተቃትሎተ መስቀል
እብን ዳዊትሀ መሐላ ጎልያድሀ መልአከ ሞት፣
እም ሲገባ፣
አድራጊ፣ ለአማኑኤል ላእክ ቀዲሐ ድንግል ልሕኵት
ትስብእተ ወይነ፣
ተደራጊ፣ ለአማኑኤል ወይን ተቀድሖተ ድንግል
ልሕኵት፣
አስደራጊ፣ ለባዕል አብ አቅድሖ ማርያም ልሕኵት
አማኑኤልሀ ወይነ፣
ተደራራጊ፣ ለመለኮት ወይን ተቃድሖተ ድንግል
ቀሱት ምስለ ትስብእት መዓር፣
አደራራጊ፣ ለአብ ባዕል አስተቃድሖተ ማርያም
ልሕኵት አማኑኤልሀ ወይነ ትስእተ ላዕከ ምስለ ሥጋ
መዓር፣
ከመ እና ምስለ ሲገቡ፣
አድራጊ፣ ለሄሮድስ እኩይ ቀቲለ ዘካርያስ ሕፃናተ
/እንደ፣ ከ.....ጋር/፣
ተደራጊ፣ ለዘካርያስ አብ ተቀትሎተ ሕፃናት በሰይፍ፣
አስደራጊ፣ ለዳዊት ንጉሥ አሩጸተ ፈረስ አሳሄልሀ
ገብረ፣
ተደራራጊ፣ ለአሳሄል ገብር ተራውጸተ ፈረስ ምስለ
አግብርት ቅድመ ንጉሥ፣
አደራራጊ፣ ለዳዊት ንጉሥ አስተራውጸተ ፈረስ
አግብርቲሁ ረዋጽያነ ይላል።።
ኀበ እና እስከ ሲገቡ፣
አድራጊ፣ ለአብ ንጉሥ ፈንዎተ ድንግል ገብርኤልሀ
ላእከ ፣
ተደራጊ፣ ለገብርኤል ላእክ ተፈንዎተ ድንግል
ንግሥት፣
አስደራጊ፣ ለአብ ንጉሥ አፈንዎተ ድንግል ንግሥት
ገብርኤልሀ፣
፣ አምጽኦተ ድንግል መና ወወይነ
ፋኑኤልሀ ላእከ

ተደራራጊ፣ ለረዋጺ ፈረስ ተራውጾተ ዐውደ ቀትል ምስለ ረዋጽያን ሠረገላት፣
አደራራጊ፣ ለአብ ንጉሥ አስተፋንዎተ ድንግል ንግሥት ኀብርኤልሀ ላእከ ምስለ ብሥራት አምኃ ማለቱን ያሳያል፡፡
ለ/ ሳቢ ዘር፣
ሳቢ ዘር ያለአገባብ ባለቤትነት ሲገባ፣
ለአዳም ዮሐንስ ሙተተ ኢየሱስ ዘካርያስ፣
ለመርዓት ሔዋን ቅድሐተ አማኑኤል ወይን ሲል በሁለት አርእስት መፈታቱን አስተውል፡፡ አማኑኤል ወይንን መቅዳት ለሔዋን ሙሽራ ነው፣ ወይም የአማኑኤል ወይን መቀዳት ለሔዋን ሙሽራ ነው ተብሎ ይተረጎማል፡፡
በአገባብ ሲገባ፣ /በይነን፣ ለን ሲያመጣ/፣
ለአማኑኤል ኦርዮ ሙተተ ሔዋን ቤርሳቤህ፣
/ስለሔዋን ቤርሳቤህ ወይም ለሔዋን ቤርሳቤህ መሞት ለአማኑኤል ቤርሳቤህ ነው/፡፡
በን ሲያመጣ፣ ለክርስቶስ ስቅለተ መስቀል ይላል፣
ከን ሲያመጣ፣ ለያዕቆብ ወልድ ልደተ ድንግል ርብቃ ይላል፡፡
ምስለ፣ ከመ፣ ሲገቡ፣ ለአማኑኤል ላእክ ሙተተ ፈያት ኃያላን፣
ኀበ እና እስከ ሲገቡ፣ ለገብርኤል ላእክ ብሥሐተ ድንግል ንግሥት ይላል፡፡
ሐ/ ሣልስ ቅጽል፣
ሣልስ ቅጽል በባለቤትነት ሲገባ በውእቱ ያሣሥራል፡፡ ሲገባ፣
አድራጊ፣ ኦርዮ ቀታሌ ኢዮአብ /ኢዮአብ የገደለው ኦርዮ ነው/፣
ተደራጊ፣ አዳም ተቀታሌ ወልድ/ወልድ የሞተለት/፣
አስደራጊ፣ ኦርዮ አቅታሌ ዳዊት/ዳዊት ያስገደለው ኦርዮ ነው/
ተደራራጊ፣ ዳዊት ተቃታሌ ኢዮአብ ምስለ ኢሎፍላውያን/ኢዮአብ የተገዳደለለት/

አደራራጊ፣ አሳሄል ገብር አስተራዋጼ ንጉሥ ዳዊት ምስለ ረዋጽያን ይላል፣
በይነን፣ ለን፣ እንዳመጣ አስተውል።።
አድራጊ፣ ዳዊት ቀታሌ ቤርሳቤህ ኦርዮህ ተፈሥሐ፣
ተደራጊ፣ ኦርዮ ተቀታሌ ቤርሳቤህ ተቀብረ፣
አስደራጊ፣ ዳዊት አቅታሌ ቤርሳቤህ ኦርዮህ ነስሐ፣
ተደራራጊ፣ ኦርዮ ተቃታሌ መንግሥት ምስለ አሕዛብ ወድቀ፣
አደራራጊ፣ ኢዮአብ አስተቃታሌ ቤርሳቤህ ኦርዮህ ምስለ አሕዛብ ተፈሥሐ ይላል።። በይነን እና ለን እንዳመጣ አስተውል።።
በ ሲወጣ / ሙሻዘር በን ሲያመጣ/፣
አድራጊ፣ ይሁዳ መስፍን ቀዳሔ መስቀል ፅዋዕ ወይነ ኢየሱስ ደመ፣
ተደራጊ፣ ተክዕወ ማየ አማኑኤል ተቀዳሔ መስቀል ፅዋዕ፣
አስደራጊ፣ ተኰነነ ይሁዳ አቅዳሔ መስቀል ፅዋዕ ወይነ አማኑኤል ደመ፣
ተደራራጊ፣ ተክዕወ ወይነ አማኑኤል ደም ተቃዳሔ መስቀል ፅዋዕ ምስለ ማይ መዓር፣
አደራራጊ፣ ጸግበ አዳም አስተቃዳሔ ኩናት ፅዋዕ ኡራኤልሀ ገብረ ይላል።።
እም ሲገባ /ከሙሻዘር ሲወጣ/፣
አድራጊ፣ ደንገፀ ይሁዳ ገብር ከዐዌ ገቦ ልሕኩት ደመ ኢየሱስ ወይነ፣
ተደራጊ፣ ያስተፈሥሐ ልበ ሰብእ ደመ ኢየሱስ ወይን ተቀዳሔ ገቦ ልሕኩት፣
አስደራጊ፣ ተፈሥሐ ለንጊኖስ ገብር አቅዳሔ ገቦ ቀሱት ደመ ኢየሱስ ወይነ፣
ተደራራጊ፣ አቁረረ ጽምዐ ኃጥኣን ደመ ኢየሱስ ወይን ተቃዳሔ ገቦ ቀሱት ምስለ መዓር ማይ፣
አደራራጊ፣ ኀዘነ ይሁዳ ገብር አስተካዓዌ ገቦ ልሕኵት ደመ ኢየሱስ ወይነ አይሁድ አግብርተ ምስለ ማይ መዓር፣ ይላል።።

ምስለ እና ከመ ሲገቡ፣
አድራጊ፣ ኀዘነ ይሁዳ ሰቃሌ ፈያት አምላከ፣
ተደራጊ፣ ወረደ ገብርኤል ተፈናዌ ሚካኤል ሰማየ፣
አስደራጊ፣ ክቡር ውእቱ ጲላጦስ አቅታሌ ፈያት
አይሁደ አማኑኤልሀ፣
ተደራራጊ፣ ሥሙር ውእቱ አማኑኤል ወልታ ተሰቃሌ
ፈያት መጣብሕ ውስተ ቤተ መንግሥት ቀራንዮ፣
አደራራጊ፣ ክቡር ውእቱ ጲላጦስ አስተሳቃሊ ፪ቱ
ፈያት መጣብሕ አማኑኤልሀ ወልታ አግበርቲሁ
አይሁደ፣
ኀበ እና እስከ ሰገቡ፣
አድራጊ፣ ክቡር ውእቱ ጳውሎስ በጻሔ ደማስቆ፣
ተደራጊ፣ ክቡር ውእቱ ገብርኤል ተፈናዌ ማርያም፣
አስደራጊ፣ ግሩም ውእቱ ፍቅር አብጻሔ ሞት ወልደ
ኀያለ፣
ተደራራጊ፣ ትጉህ ውእቱ ገብርኤል ላእክ ተባጻሔ
ማርያም ምስለ ብሥራት ቃለ መልእክት፣
አደራራጊ፣ ክቡር ውእቱ መንፈስ ቅዱስ አስተባጻሔ
ደማስቆ ጳውሎስሀ ወንጌለ ምስለ ተጋድሎ ይላል፡፡
እንበለ ሲገባ፣ /በንዑስ አንቀጽ/
አድራጊ፣ አፍቀሩ አይሁድ ቀቲለ ኃጢአት አምላክ
/ያለኃጢአት አምላክን መግደል/፣
ተደራጊ፣ አፍቀረ ወልድ ተወልዶተ አብ
እምድንግል/ያለአባት ከድንግል መወለድን/፣
አስደራጊ፣ አፍቀረ አክአብ አቅትሎተ ሰይፍ ናቡቴሀ
/ያለሰይፍ/፣
ተደራራጊ፣ አፍቀረ ጊዮርጊስ ተቃትሎተ ፍርሀት
ምስለ አሕዛብ /ያለፍርሀት/፣
አደራራጊ፣ ኢፈርሀ ዳዊት አስተቃትሎተ ኃጢአት
ኦርዮሀ ኢዮአብሀ ምስለ ሰብአ ኢሎፍሊ
/ያለኃጢአት/ ይላል፡፡
እንበለ በሳቢ ዘር ሲገባ፣
አፍቀሮ ለዓለም ወልድ እስከ ቅትለተ ኃጢአት ፣

ግሩም ውእቱ በጎበ ወልድ ልደተ አብ እምድንግል ይላል፣
እንበለ በሣልስ ቅጽል ሲገባ፣
አድራጊ፣ ተኰነነ አይሁዳዊ ሰቃሌ ኃጢአት አምላክ፣
ተደራጊ፣ ሞየ ለሞት ወልድ ተሰቃሌ ኃጢአት ዲበ ዕፀ መስቀል፣
አስደራጊ፣ ኢጸድቀ ይሁዳ አግባኤ ኃጢአት ንጹሐ ደመ፣
ተደራራጊ፣ ሞተ ኦርዮ ተቃታሌ ኃጢአት ምስለ ፀሩ፣
አደራራጊ፣ ኢዮአብ ወአቢሳ አስተቃታልያነ ኃጢአት ኦርዮሀ ኢሎፍላውያነ ነስሑ፣ ሌሎችም በዚህ መንገድ ይገባሉ።።
መ/ ሳድስ ቅጽል፣
ሳድስ ቅጽል በሙሻ ዘር እየገባ አገባብ ሲያወጣ ከዚህ የሚከተለውን ይመስላል።።
ለአዳም፣ ስለአዳም ፈንታ ሲል አምላክ ቅቱለ አዳም ይላል።።
ቤዛ ሲሆን ክርስቶስ ስቁለ አዳም፣ አብርሃም ጥቡሐ ይስሐቅ በግዐ ይላል።።
አድራጊ፣ አይሁዳዊ ስቁለ መስቀል አምላክ ተኰነነ /አምላክን በመስቀል ያሰቀለ አይሁዳዊ ማለት ነው/፣
ተደራጊ፣ አምላክ ስቁለ አዳም በመስቀል / ለ፣
በእንተ፣ ቤዛ ማለት ነው/፣
ተደራጊ፣ በ ሲሆን አምላክ ስቁለ መስቀል ይላል።።
እም ሲሆን አምላክ ውሩደ ሰማይ ይላል።።
ምስለ፣ ከመ፣ ሲሆን አምላክ ቅቱለ ፈያት ይላል።።
እስከ፣ ጎበ፣ ሲሆን ጳውሎስ ብጹሐ ደማስቆ ከብረ ይላል።።
እንበለ ሲሆን አምላክ ቅቱለ አበሳ ይላል።። በቀር ሲጨመር አምላክ ቅቱለ መሐላ፣ አምላክ ቅቱለ አዳም ተሰብሐ ይላል።።
አስደራጊ፣ ለ፣ ስለ ሲሆን ይሁዳ ቅቱለ ብሩር አምላክ ተኰነነ ይላል።።
አዳም ቅቱለ መሐላ አምላክ በመስቀል ተፈሥሐ።።

ይሁዳ ቅቱለ ብሩር ዐላውያነ አምላከ ተኰነነ።።
አብርሃም ውሩደ ይስሐቅ መልአከ በግዐ ተፈሥሐ።።
ይሁዳ ቅቱለ መስቀል ዐላውያነ አምላከ ተኰነነ።።
አዳም ውሩደ ሰማይ አምላከ መሐላ ተፈሥሐ።።
ይሁዳ ቅቱለ ፈያት ዐላውያነ አምላከ ተኰነነ።።
አምላክ ብጹሐ ደማስቆ ወንጌለ ጳውሎስሃ ።።
ይሁዳ ቅቱለ አበሳ ዐላውያነ አምላከ።።
አዳም ቅቱለ መሐላ ዐላውያነ አምላከ ተፈሥሐ።።
ይሁዳ ቅቱለ አምላክ በመስቀል ተኰነነ።።
ተደራራጊ፣ ጊዮርጊስ ቅቱለ መንግሥተ ሰማያት ምስለ አሕዛብ።።
ጊዮርጊስ ቅቱለ ቢሩታዊት ምስለ አርዌ።።
ጊዮርጊስ ቅቱለ ሃይማኖት ምስለ አሕዛብ።።
ጊዮርጊስ ውኩፈ አምላክ ስቃያቲሁ ።።
ጊዮርጊስ ቅቱለ አሕዛብ በሃይማኖት ።።
ጊዮርጊስ ቅቱለ መርቆሬዎስ ምስለ አሕዛብ።።
ጊዮርጊስ ብጹሐ ባቢሎን ምስለ መላእክት ።።
ጊዮርጊስ ቅቱለ አበሳ በሃይማኖት።።
ቂዮርጊስ ቅቱለ ሃይማኖት ምስለ አሕዛብ።።
ጊዮርጊስ ቅቱለ አሕዛብ በሃይማኖት።።
አደራራጊ፣ ከብረ ኢዮአብ ቅቱለ መንግሥት ሰብአ ምስለ ሰብእ።።
ኢዮአብ ቅቱለ ዳዊት ሰብአ ምስለ ሰብእ።።
ኢዮአብ ጎቡአ ለኪሶን ሰብአ ምስለ ሰብእ።።
ኢዮአብ ቅቱለ አቢሳ ሰብአ ምስለ ሰብእ ።።
ኢዮአብ ብጹሐ ለኪሶን ሰብአ ምስለ ሰብእ።።
ከብረ ዳዊት ቅቱለ አቢሳ ሰብአ ምስለ ሰብእ።።
ኢዮአብ ቅቱለ መንግሥት ሰብአ ምስለ ሰብእ ከብረ ይላል።።

<u>መስም ውስጠዘ /ባዕድ ቅጽል/፣</u>

መስም ውስጠዘ መድረሻው ሣልስና ሳድስ ስለሆነ ቁጥሩ ከሳድስ ቅጽል ነው።። በመሆኑም ዘጠኙን

የሙሻዘር አገባባት ያወጣል፡፡ ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፣

፲፥ አርመመ ባሕር መገሥጸ ኢየሱስ ክርስቶስ /በኢሱስ ክርስቶስ የተገሠጸ/ ፣
፩፥ አርመሙ ባሕር ወነፋሳት መገሥጻነ ክርስቶስ፣
፪፥ ኢየሱስ መገሥጸ ሥልጣን ባሕረ ወነፋሳተ፣

የሙሻዘር አገባብ ሲወጣ

፫፥ መልአክ መንጽሔ እሳት ኢሳይያስሀ እምለምፅ፣
፬፥ ድንግል መፍርይተ ምእመናን መብልዐ ሕይወት ወመንቅዒተ ፅሙዓን ስቴ ሕይወት፣
፭፥ በትረ ሙሴ መንቅዒተ ኰኵሕ ማየ ማለቱን ያሳያል፡፡

እስከ ዚህ ድረስ ያለው ሙሻዘር፣ ዘመድ ሙሻዘር፣ ዘመድ ቅጽል፣ ዘመድ ዝርዝር ይባላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው አገባቡን እስከ ዝርዝሩ አውጥቶ ዝርዝሩን ወደ ኋላ ይዘረዝራል፡፡ ይህም ባዕድ ዝርዝር፣ ባዕድ ሙሻዘር፣ ባዕድ ቅጽል ይባላል፡፡
በንዑስ አንቀጽ ሲነገር፣
ለአዳም መዊተ አምላክ፣ ለን፣ በእንተን ሲዘረር ነው፣ /የአምላክ ስለእርሱ መሞት/
ለመስቀል ተሰቅሎተ አምላክ፣ በን ሲዘረዝር ነው፣ /በእርሱ /
ለቤት ወጺአ ነጋዲ፣ እምን ሲዘረዘር ነው፣ /ከእርሱ/
ለፈያት ተሰቅሎተ አምላክ፣ ምስለን፣ ከመን ሲዘረዘር፣
ለባቢሎን ወሪደ ንስር፣ ኀበን፣ እስከን ሲያመጣ/ሲዘረዘር/፣
ለድንግል ፈንዎ አብ፣ ገብርኤልሀ፣
ለድንግል ተፈንዎ አብ አማኑኤልሀ፣

ለድንግል ተፋንዎ ገብርኤል ምስለ ብሥራት፣
ለድንግል አስተፋንዎ አብ ገብርኤልሀ ምስለ ብሥራት፣
ሠ/ ሳቢ ዘር ሲገባ፣
ለአዳም ልደተ አማኑኤል፣ /ለን፣ በእንተን፣ ሲዘረዝር/ /ስለእርሱ/
ለመስቀል ዐረፍት ስቅለተ አማኑኤል ወልታ፣ / በን ሲዘረዘር/፣
ለድንግል ጽርሕ ፀአተ አማኑኤል ንጉሥ፣ /እምን ሲዘረዝር/፣
ለፈያት መጣብሕ ስቅለተ አማኑኤል ወልታ፣ /ምስለን፣ ከመን ሲዘረዝር/፣
ለድንግል ንግሥት ሉረተ አማኑኤል ንጉሥ፣ /ኀበን አስከን ሲዘረዘር/፣
በሣልስ ሲገባ፣
ድኅነ አዳም መዋቴ እግዚእነ፣ ከዓዌ እግዚእነ ደመ /በእንተን፣ ለን ሲዘረዝር/፣
ተፈሥሐ አዳም ነዳይ አፍታሔ መሐላ ንጉሥ ደመ ፍትሐ አማኑኤልሀ ሥዩመ፣
ተመክሐ አዳም ተቃታሊ አምላክ ምስለ ፀሩ፣
ተፈሥሐ አዳም አስተጻባኤ አብ አማኑኤልሀ ሥዩመ ምስለ መልአከ ሞት፣
በን ሲዘረዘር፣
መስቀል ሰቃሌ ይሁዳ አምላክ
መስቀል ተሰቃሌ አምላክ፣
ጢስ አውፃኤ እሌኒ ንግሥት መስቀለ፣
ሠናይት ይእቲ አፀደ ወይን ተቃታሊ ናቡቴ፣
ኀይማኖት አስተቃታሊ አምላክ ጊዮርጊስሀ ምስለ አሕዛብ፣
ምስለን፣ ከመን ሲዘረዝር /ሲያመጣ/፣
ፈያታይ ዘየማን ተሰቃሌ ፈያታዊ ዘፀጋም ከብረ፣
አምላክ አስቃሌ አይሁዳዊ ፈያተ አድኅነ ዓለመ፣
ገላውዴዎስ ተቃታሊ ቴዎድሮስ ምስለ አሕዛብ ከብረ፣

ፊረስ አስተራዋጼ ንጉሥ እግብርተ ምስለ አግብርት
ረዋጺ ውእቱ ከመ ነፋስ፣
ኀበ፣ እስከ ሲገቡ/ኀበን፣ እስከን ሲያመጣ/፣
ደማስቆ በጻሔ ጳውሎስ ፣
ደማስቆ አብጻሔ ጳውሎስ ወንጌለ፣
ገሊላ ተፈናዌ ገብርኤል ምስለ ብሥራት፣
ደማስቆ ተበጻሔ ወንጌል ምስለ ጳውሎስ፣
ደማስቆ አስተባጻሔ መንፈስቅዱስ ጳውለስሀ ወንጌለ፣
እንበለ በንዑስ አንቀጽ በአሉታ ሲገባ፣
አድራጊ፣ ለይሁዳ ኢሰቂለ መስቀል አምላክ
/ያለመስቀል አምላክን አለመስቀል ለይሁዳ ነው/፣
ተደራጊ፣ ለአምላክ ኢተሰቅሎ መስቀል፣
አስደራጊ፣ ለይሁዳ ኢያስቅሎ መስቀል አምላክ፣
ተደራራጊ፣ ለአምላክ ኢተሰቅሎ መስቀል ምስለ
ፈያት፣
አደራራጊ፣ ለይሁዳ ኢያስተሰቅሎ መስቀል አምላክ
ምስለ ፈያት፣
በሳቢ ዘር ሲገባ፣
ለአይሁድ ኢስቅለተ መስቀል አምላክ፣ /አምላክ ያለ
መስቀል/፣
ለአምላክ ኢስቅለተ መስቀል /ያለመስቀል፣ ከመስቀል
በስተቀር ያልተሰቀለ/፣
እንበለ በሣልስ ቅጽል ሲገባ፣
አድራጊ፣ ተኰነነ አይሁዳዊ ኢሰቃሌ መስቀል
አምላክ፣
ተደራጊ፣ አድኅነ ዓለመ አምላክ ኢተሰቃሌ መስቀል፣
አስደራጊ፣ ተኀንኮለ ይሁዳ ኢያስቃሌ መስቀል
አምላክ፣
ተደራራጊ፣ አምላክ ኢተሳቃሌ መስቀል ምስለ ፈያት
አድኅነ ዓለመ፣
አደራራጊ፣ ተኰነነ ይሁዳ ኢያስተሳቃሌ መስቀል
አማኑኤልሀ አይሁደ ምስለ ፈያት ማለቱን ያሳያል።
ስምንቱን አገባባት ዘጠነኛው አገባብ እንበለ
ይበዘብዛቸዋል።

በንዑስ አንቀጽ ሲበዘብዝ፣
ለመስቀል ኢተሰቅለ አምላክ /በ፣ ለ/፣
ለአዳም ኢመዊተ አምላክ /በ፣ ለ/፣
ለቤት ኢወሚአ ነጋዲ /እም ሲበዘበዝ/፣
ለፊያት ኢተሰቅለ አምላክ /ምስለ፣ ከመ/፣
በሳቢ ዘር ሲበዘብዛቸው፣
ለዮሐንስ ኢመ·ተተ ዘካርያስ /በይኔሁ፣ ለ·ቱ/፣
ለመስቀል ኢስቅለተ ወልድ /ቦቱ/
ለቤት ኢፀአተ ነጋዲ /እምኔሁ·/፣
ለፊያት ኢስቅለተ ወልድ /ከመ፣ ምስለ/፣
ለድንግል ኢብጽሐተ ገብርኤል /·ነበ፣ እስከ/፣
በግልስ ቅጽል ሲበዘብዛቸው፣
ድኅነ አዳም ኢተሰቃሌ ወልድ /በይኔሁ፣ ለ·ቱ/፣
መስቀል ኢተሰቃሌ ወልድ ፈወሰ ዱያነ /ቦቱ/፣
ያድኅን ዝናመ ቤት ኢወጻኤ ነጋዲ /እምኔሁ·/፣
ቤዘወ ዐለመ ወልድ ኢተሰቃሌ ፊያት / ምስሌሆመ·፣
ከማሆመ·/፣
እምነ ይእቲ ድንግል ኢተፈናዌ ገብኤል
/·ነቤሃ ኢስከኔሃ/፣
አቡነ ውእቱ አዳም ኢፈናዌ አብ ወልደ /እምኔሁ·/፣
እግዝእትነ ይእቲ ድንግል ኢፈናዊተ አብ ገብርኤልሀ
/·ነቤሃ፣ አስከኔሃ/፣
ቀሪዎችንም እንዲህ እያልክ በንዑስ አንቀጽ፣ በሳቢ
ዘር፣ በሳድስ ቅጽል አግባ፡፡ የእንበለ መንገድ
ለማያውቀውና ለማይመረምረው የመናፍቃን መንገድ
ይመስላል፡፡ ለምሳሌ፣
አብ ኢተወላዴ ወልድ ሲል ፍችው ያለ ነው፡፡
በጽድቅ ሲነገር የመናፍቃን መንገድ ይመስላል፡፡
ወልድ ስቁለ አበሳ ሲል ፍችው ያለ አበሳ ማለት
ነው፡፡
ዘመድ ዝርዝርና ባዕድ ዝርዝር በሙሻዘር
አይለይም፡፡
**<u>ዘመድ ዝርዝርም ሆነ ባዕድ ዝርዝር ሲገባ ለአገባብ
አንድና ብዙ፣ ወንድና ሴት የለውም፡፡</u>**

አእመሮ ለብእሲ፣ አእመራ ለብእሲት፣
አእመሮሙ ለእደው አእመሮን ለአንስት
ሲል ለ በሴት፣ በወንድ፣ በአንድ፣ በብዙ ስም ላይ
መውደቁን ያሳያል፡ ይህ ለወጣንያን ነው እንጂ
ለፍጹማን ግን አገባቡና ዝርዝሩ ጠፊ ነው ብለው
አንድና ብዙ፣ ሴትና ወንድ፣ ሩቅና ቅርብ፣
ያናግሩበታል፡፡
እስከአሁን ድረስ ሰዋስውን ከሰዋስው፣ ሳቢን ከተሳቢ
እያናበቡ ሙሻዘርን፣ አገባባትን እያወጡ መጥተው
ነበር፡፡ አሁን ግን የሙሻዘር አገባባትን ከዝርዝር
አንቀጽ ያወጧቸዋል፡፡ ይህም ማለት አንቀጽን
በመዘርዘር ሙሻዘርን ማውጣት ይቻላል ማለት
ነው፡፡ አንቀጾችም የሚገለጹት በዘመድ ዝርዝር እና
በባዕድ ዝርዝር ነው፡፡

ሦስተኛ ዐዋጅ ዘመድ ዝርዝር፤ ዘመድ ዝርዝር፣

ዘመድ ዝርዝር ማለት ባዕድ ፊደል ሳይጨምር
የመጨረሻ ፊደሉን በራሱ የሚዘረዝር ማለት ነው፡፡
ዘመድ ዝርዝር የሚገኘው በአብዛኛው ከሳድስ ዘርና
ነባር ነው፡፡ ይህ በዘርና በነባር ነው፡፡ አንቀጽ
ሲሆን አንቀጹ ባለቤቱን መስሎ ሲዘረዝር ነው፡፡
ለምሳሌ፣
ብእሲት ብእሲቱ፣ እም እሙ፣ ውሉድ
ውሉዱ፣ ደቅ ደቁ ይላል፡፡
የመጨረሻ ፊደላቸው ሳድስ ሆኖ ዘመድም
ባዕድም ዝርዝር የሚሆኑ አሉ፡፡ ለምሳሌ፣
አዕይንት አዕይንቱ/አዕይንቲሁ
አርድእት አርድእቱ/አርድእቲሁ
አርዳእ አርዳኡ/አርዳኢሁ
አብ አቡ/አበዊሁ

እድ እዱ/እደዊሁ
ምግባር ምግባሩ/ምግባሪሁ፡፡

ዘመድ ዝርዝር፣ በአንቀጽ ሲገለጽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

አእመሮ ለብእሲ፣ አእመራ ለብእሲት፣
አእመሮሙ ለእደው አእመሮን ለአንስት

ተሳቢ አንድና ብዙ፣ ሴትና ወንድ፣ ሩቅና ቅርብ አይለይም፡፡ የአንቀጽም ሆነ የነባር ዘመድ ዝርዝር የተለመደና ከጀማሪ እስከ አእማሪ ድረስ ስለሚታወቅ ከዚህ በላይ መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም፡፡

አራተኛ ዐዋጅ
ባዕድ ዝርዝር

ባዕድ ዝርዝር ማለት ዘርም ሆነ ነባር ከመጨረሻ ፊደሉ በኋላ ሌላ ባዕድ ፊደል ጨምሮ ሲዘረዝር ነው፡፡ ባዕድ ዝርዝር በግእዝ ፊደል ከሚጨርስ ቃል በስተቀር በካዕብ፣ በሣልስ፣ በራብዕ፣ በኀምስ፣ በሳድስ፣ በሳብዕ ይገኛል፡፡

ከንቱ ከንቶሁ	ከንቱኪ
ከንቶሃ	ከንቱክሙ
ከንቶሆሙ	ከንቱክን
ከንቶሆን	ከንቱየ
ከንቱከ	ከንቱነ

በሣልስ፣ በራብዕ፣ በኀምስ፣ በሳብዕ የሚጨርስ ዘር ወይም ነባርም እንደዚሁ በባዕድ ይዘረዝራል፡፡

ብእሲ ብእሲሁ	ቅዳሴ ቅዳሴሁ
ደብተራ ደብተራሁ	መሰንቆ መሰንቆሁ

አገባብም ዘርና ነባር በመሆኑ በዘመድም በባዕድም ይዘረዝራል፡፡ ምሳሌ፣

ተውላጥ	ተውላጡ	ላዕል	ላዕሌ
ኀበ	ኀቤሁ	ሶበ	ሶቤሁ

ከመ ከማሁ ላዕለ ላዕሌሁ
አመ አሜሁ አይቴ አይቴሁ
አንቀጽ ሲሆን ደግሞ አንቀጹ ተሳቢውን ሳይመስል ሲዘረዝር ነው። ለምሳሌ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፣
አምላክ ፈጠሮ ኪያሆሙ መላእክተ፣ /አምላክ ለእርሱ፣ ስለእርሱ መላእክትን ፈጠረ/
ኪያክሙ መላእክተ፣
ኪያሁ አዳምሀ፣
ኪያከ አዳምሀ፣ /አንተን አዳምን ለእርሱ፣ ስለእርሱ ፈጠረ/
ኪያሃ ሔዋንሃ፣ ኪያኪ ሔዋንሃ፣ በሚልበት ጊዜ በይኄሁ፣ ሎቱ፣ እንደተበዘበዙ አስተውል።
ንጉሥ አንበሮ ኪያሆሙ አክሊላተ፣ /ንጉሥ ለራሱ አክሊላትን ደፋ/።
ኪያክሙ አክሊላተ፣
ኪያሁ አክሊለ፣
ኪያከ አክሊለ፣
ኪያሃ አክሊለ፣
ኪያኪ አክሊለ፣ በሚልበት ጊዜ ላዕሌሁ፣ ቦቱ እንደመጡ አስተውል።
አብ አፍቀሮ ንዑሰ ሕፃነ፣ /አባት ለራሱ ትንሽ ሕፃን ልጅ ወደደ/።
ንዑሳነ ሕፃናተ፣ /አባት ለራሱ ትንሾችን ሕፃናት ወደደ/።
ንዕስተ ሕፃነ፣
ንዑሳተ ሕፃናተ፣ ይላል።
ንጉሥ አክበሮ ምሁራነ ካህናተ፣
ምሁረ ካህነ፣
ሠናይተ ብእሲተ፣
ሠናያተ አንስተ በሚልበት ጊዜ ከማሁ እንደወጣ አስተውል።
ንጉሥ አቅረቦ በጊዜ ማዕድ ኪያሆሙ ካህናተ፣
ኪያክሙ ካህናተ፣

ኪያሁ መምህረ፣
ኪያከ መምህረ፣
ኪያሃ መምህርተኪያኪ መምህርተ፣
ኪያሆን መምህራተ፣
ኪያክን መምህራተ በሚልበት ጊዜ
ምስሌሁ እንደወጣ አስተውል።።
ንግሥት አብጽሐታ እለ ተለዉ አግብርተ፣
እለተለውክሙ አግብርተ፣
ዘተለወ ገብረ፣
ዘተለውከ ገብረ፣
ዘተለወት ብእሲተ፣
ዘተለዋ አዕማተ፣
ዘተለውክን አዕማተ በሚልበት ጊዜ፣ ጎቤሃ፣ እስከኔሃ፣ እንደወጣ አስተውል።። በአጠቃላይ በባዕድ ዝርዝር ጊዜ ባለቤቱ፣ አንቀጹና ተሳቢው አይናበቡም።። ባዕድ መባሉም ለዚህ ነው።።
ከባዕድ ዝርዝር ጋር አብሮ የሚነገረው **ባዕድ በራሱ** ነው።። ባዕድ በራሱ ማለት ድርጊቱ በራሱ በአድራጊው ላይ የሚፈጸም ማለት ነው።። ስለዚህ የኪያሁን፣ የሎቱን መንገድ ለውጦ አንቀጹና ተሳቢው እዚያው በራሱ ላይ ይቀራል።። ለምሳሌ፣ ሄሮድስ በልየ፡ ቴዎድሮስ ቀተሎ፣ ዳዊት አስተዋደዮ ጎበ እግዚአብሔር፣ አ ዳዊት አስተዋደይኮ ጎበ እግዚአብሔር ይላል።። ሲተረጎም ፈርያን ራሱን በላ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ራሱን ገደለ፣ ዳዊት ራሱን በእግዚአብሔር ዘንድ ከሰሰ፣ ዳዊት ሆይ ራስህን በእግዚአብሔር ዘንድ ከሰስክ ማለት ነው።።

አምስተኛ ዐዋጅ፣
ደላይ ተደላይ

ደላይ ተደላይ ማለት በለ መርከብነት አንቀጹ ባለቤቱን ወይም ተሳቢውን ወይም ሁለቱንም መስለሞ

የማይፈታ ማለት ነው፡፡ ሴትና ወንድ፣ አንድና ብዙ፣ ቅርብና ሩቅ ሳያናግር ያናገረ ይመስላል፡፡
ደላይ ተደላይ በዘመድ ዝርዝር እና በባዕድ ዝርዝር ይነገራል፡፡

ደላይ ተደላይ በዘመድ ዝርዝር በለ መርከብ ሲነገር፤

ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፣
አምላክ ሞቶ ለአዳም /በይኔሁ እንደወጣ አስተውል/
አምላክ ስለ አዳም ሞተ፡፡
አምላክ ተሰቅሎ ለመስቀል /ቦቱ እንደወጣ አስተውል/
አምላክ በመስቀል ተሰቀለ፡፡
ነጋዲ ወፅኦ ለቤት /እምኔሁ እንደወጣ አስተውል/፣
ነጋዴ ከቤት ወጣ፡፡
ገብርኤል ተፈነዋ ለማርያም /ኀቤሃ እንደወጣ አስተውል/፣
ገብርኤል ወደ ማርያም ተላከ፡፡
በተጨማሪም፣ ዘመድ ዝርዝር፣
እዋሕያ በበትር ለኃጢአቶሙ፣
ዕብን ዘመነንዋ ነደቅት ይላል፣
ሙያው ማርያም ለ የወደቀበት ተደላይ ነው፡፡
ገብርኤል ባለቤት ነው የለ ፍች የለውም፡፡ ደላላ ባለጉዳዮችን አገናኝቶ እንደሚጠፋ ሁሉ ወይም የጉዳዩ ባለቤት እንደማይሆን ሁሉ ለ ሁለቱን አገናኝቶ ሙያ ሳይሰጠው ይጠፋል፡፡
ደላይ ተደላይ በዘመድ ዝርዝር ጊዜ አንቀጹ ባለቤቱን ይመስላል፡፡

ዘመድ ዝርዝር፣ አምላክ ሞቶ ለአዳም /በይኔሁ እንደወጣ አስተውል/
አምላክ ተሰቅሎ ለመስቀል /ቦቱ እንደወጣ አስተውል/
ነጋዲ ወፅኦ ለቤት /እምኔሁ እንደወጣ አስተውል/፣
አምላክ ተሰቅሎሙ ለፈያት / ምስለ እንደወጣ አስተውል/፣

ገብርኤል ተፈነዋ ለማርያም /ጎቤሃ እንደወጣ አስተውል/፣
ሙያው ማርያም ለ የወደቀበት ተደላይ
ነው፡፡ ገብርኤል ባለቤት ነው የለ ፍች
የለውም፡፡ /ድጋሚ ነው/

ደላይ ተደላይ በባዕድ ዝርዝር በለ መርከብነት ሲነገር የሚከተለውን ይመስላል፤

ምሳሌ፣ አምላክ ሞቶ ለሔዋን፣ /ለሔዋን ሞተ/
አምላክ ተሰቅሎሙ ለመስቀል፣
አምላክ በመቀል ተሰቀለ
ነጋዲ ወፅኦን ለቤት፣
ነጋዴ ከቤት ወጣ
አምላክ ተሰቅሎ ለፈያት፣
አምላክ ከሽፍቶች ጋር ተሰቀለ
ገብርኤል ተፈነዎ ለማርያም፣
ገብርኤል ወደ ማርያም ተላከ
ዳዊት ነግሦን ለእስራኤል፣
ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሠ
ዮሴፍ አእመርኮ ለሰሎሜ፣
ዮሴፍ ሰሎሜን ዐወቃት፡፡
ማለቱን ያሳያል፡፡

አርብዓ ዐመተ ተቄጣዕክዎሙ ለይእቲ ትውልድ ሲልም ባዕድ ዝርዝር ነው፡፡
አርብዓ ዐመተ ተቄጣዕክዎ ለይእቲ ትውልድ የሚለው በስሕተት የተስተካከለ ነው፡፡ ደላይ ተደላይ በባዕድ ዝርዝር ሲነገር አንቀጹ ፈጽሞ ባለቤቱን አይመስልም፡፡
ይህንንም መምህራን ከልቡናቸው አንቅተው ከአፍ አግኝተው የተናገሩት አይደለም፡፡ ከብሉይ ከሐዲስ የተገኘ ነው እንጂ፡፡

ስድስተኛ ዐዋጅ

ነገረ ባዕድ ቅጽል፣

ባዕድ ቅጽል፣ አገባቡና ዝርዝሩ ለባለቤት፣ አንቀጹ ለተሳቢ ሲሆን ባዕድ ቅጽል ይባላል። ባዕድ ቅጽል በዘ ሲገለጽ /በአፈታት ሲለይ/ ተሳቢውን ይመስላል። ዘመድ ቅጽል ግን ሲነበብም ሲለይም ባለቤቱን ይመስላል። ዳግመኛም ባዕድ ቅጽል አንድና ብዙ፣ ወንድና ሴት ሩቅና ቅርብ ሳያናግር ያናገረ ይመስላል። ሦስት ነገሮችን ማለትም ተሳቢውን፣ አንቀጹን፣ አገባቡን ይዘረዝራል። አንቀጹ ሲዘረዘር፣

፩÷ የተደራጊ ቅጽል ከአድራጊ፣ ከአስደራጊ ተናቦ በአድራጊ በአስደራጊ ይፈታል።
፪÷ የአድራጊ ቅጽል ከአስደራጊ ተናቦ በአስደራጊ ይፈታል።
፫÷ የተደራጊ ቅጽል ከተደራራጊ፣ እንዲሁም የተደራራጊ ቅጽል ከአደራራጊ ተናቦ በአደራራጊ ይፈታል።ይህም በሰባት በሰባት ሠራዊት ይዘረዝራል።
፬÷ የአደራራጊ ቅጽል ከአድራጊ ተናቦ በአድራጊ ይፈታል።

ተሳቢና አገባብ በአምስት በአምስት አርእስት ይነገራል /ይዘረዘራል/፣
ተሳቢውን ሲዘረዝር የተጸውያና የተቀብያ ስሞች አይገቡም። ባዕድ ቅጽል ሲነበብ ባለቤቱን ሲለይ ተሳቢውን ይመስላል፡ ያልነው የተደራጊም ቅጽል ከአድራጊ ተናቦ በአድራጊ ይፈታል፡ ያልነው ሲገባ፣ ማርያም ወይን ትክልተ ሥላሴ ገባዕት ፈረየት አስካለ አምላክ ምሕረት ይላል።
ሲፈታም ሥላሴ ገበራርት የተከሏት ማርያም ወይን የምሕረት አምላክ ፍሬን አፈራች ተብሎ ይፈታል። ትክልት በአገባቡ ማርያም ወይንን ይመስላል።
ሲፈታም ዝርዝሩና አገባቡ የርሷ ነው። የተከሏት

የሚለው ዝርዝር ሲሆን በትርጉም እንጂ በንባብ አይዘረዝርም።
ሠናይት ማርያም ወይን ትክልተ ሥላሴ ገባዕት። ሥላሴ ገበራርት የተከሏት ማርያም ወይን ያማረች ናት ይላል። ሠናይት የመጭ ቅጽል ማሠሪያ መመርመሪያ ነው እንጂ የማርያም ወይን ቅጽል አይደለም። ሁሉንም እንዲህ ተመልከት። ሥላሴ ገባዕት አድራጊ ማርያም ወይን ተደራጊ ናቸው።
የተደራጊ ቅጽል ከአድራጊ ተናቦ በአድራጊ ይፈታል የተባለው ይህ ነው።

፩÷ የተደራጊ ቅጽል ከአስደራጊ ይናበባል የተባለው ሲገባ፣

ድንግለ ሙሴ መቅደስ ሕንጽተ መንፈስ ቅዱስ ሰሎሞን ንጽሕና ኪራምሀ፣
ሲፈታም መንፈስ ቅዱስ ሰሎሞን ንጽሕና ኪራምን ያሠራት የሙሴ ድንግል መቅደስ ናት ተብሎ ይፈታል።

፪÷ የተደራጊ ቅጽል ከአስደራጊ ተናቦ በአስደራጊ ይፈታል የተባለው ይህ ነው።

ኪራም አምላክ ሕኑጸ መሐላ ሰሎሞን ተሰቅሎተ መስቀል መቅደሰ፣ ሲል መስቀል መቅደስን መሐላ ሰሎሞንን ያሠራው አምላክ ኪራም ነው ተብሎ ይፈታል።

፫÷ የአድራጊ ቅጽል ከአስደራጊ ተናቦ በአድራጊ ይፈታል የተባለው ይህ ነው።

ነዳይ አዳም ወሃቤ አምላክ ንጉሥ መንግሥተ ሰማይ ወርቀ፣ ሲል አምላክ ንጉሥ መንግሥተ ሰማይ ወርቅን የሰጠው አዳም ችግረኛ ነው ተብሎ ይፈታል።

፬። የአድራጊ ቅጽል ከአድራጊ ተናቦ በአድራጊ ይፈታል የተባለው ይህ ነው።

አዳም ሰሎሞን ተጸባኤ በለስ ዳዊት ምስለ አምላክ ኢዮአብ፣ ሲል ከአምላክ ኢዮአብ ጋር በለስ ዳዊት ያጣላው አዳም ሰሎሞን ነው ተብሎ ይፈታል።

፭። የተደራራጊ ቅጽል ከአደራራጊ ተናቦ በአደራራጊ ይፈታል የተባለው ደግሞ ይህ ነው፣

አምላክ ዳዊት ተጸባኤ መልአከ ሞት አቤሴሎም፣ ሲል መልአከ ሞት አቤሴሎም የተጣላው አምላክ ዳዊት ነው ተብሎ ይፈታል። እንዲሁም፣

፮። የተደራጊ ቅጽል ከአድራጊ ተናቦ ሲገባ፣ ማርያም ወይን ትክልተ ሥላሴ ገባዕት ይላል። ሥላሴ ገበራርት የተከሏት ማርያም ወይን፣

፯። የተደራጊ ቅጽል ከአስደራጊ ተናቦ ሲገባ፣ በአስደራጊ ይፈታል።
ድንግለ ሙሴ መቅደስ ሕንጽተ መንፈስ ቅዱስ ሰሎሞን ንጽሕና ኪራምሀ ይላል።
ሲፈታም ንጽሕና ኪራምን መንፈስ ቅዱስ ሰሎሞን ያሠራት የሙሴ ድንግል መቅደስ ናት፡ ይላል።

፰። የአድራጊ ቅጽል ከአስደራጊ ተናቦ በአስደራጊ ሲነገር፣

ኪራም አምላክ ሕጉጸ መሐላ ሰሎሞን
ተሰቅሎተ መስቀል መቅደሰ ይላል።
ሲፈታም በመስቀል መሰቀል መቅደስን
መሐላ ሰሎሞን ያሠራው አምላክ ኪራም ነው
ተብሎ ይፈታል።
፬÷ የአድራጊው ቅጽል ከአድራጊው ተናቦ
በአድራጊ ሲፈታ፣
ነዳይ አዳም ወሃቤ አምላክ ባዕል መንግሥተ
ሰማይ ኀብስተ ይላል። ሲፈታም መንግሥተ
ሰማይ እንጀራን አምላክ ባለፀጋ የሰጠው
አዳም ችግረኛ ነው ይላል።
፭÷ የተደራራጊ ቅጽል ከአደራራጊ ተናቦ
በአደራራጊ ሲፈታ፣
አዳም ሰሎሞን ተጻባኤ በለስ ዳዊት ምስለ
አምላክ ኢዮአብ ይላል። ሲፈታም ከአምላክ
ኢዮአብ ጋር በለስ ዳዊትን ያጣላው አዳም
ሰሎሞን ነው ይላል።
፮÷ የተደራራጊ ቅጽል ከተደራራጊ ተናቦ
በተደራጊ ሲፈታ፣
አዳም ዳዊት ተጻባኤ መልአከ ሞት
አቤሴሎም ይላል። ሲፈታም፣ መልአከ ሞት
አቤሴሎም የተጣላው አምላክ ዳዊት ነው
ይላል።
፯÷ የተደራራጊ ቅጽል ከአደራራጊ ተናቦ
በአደራራጊ ሲፈታ፣
ሰሎሞን ተጻባኤ ዳዊት ምስለ ኢዮአብ
ይላል። ሲፈታም ዳዊት ከኢዮአብ ጋር
ያጣላው ሰሎሞን ነው ይላል።

ለማጠቃለል፣
፩÷ ተደራጊ አድራጊ፣
፬ አድራጊ አስደራጊ
፪÷ የተደራጊ አስደራጊ፣
፭ አድራጊው ከአድራጊው

፫፥ አድራጊ አስደራጊ፣
፮ የተደራራጊ አደራራጊ

የተደራጊ ቅጽል ከተደራራጊ ተናቦ በተደራራጊ
ይፈታል የተባለው ይህ ነው፣ እሊህም በሰባት
ሠራዊት ይዘረዝራሉ የተባሉት፣ ዘተጻብዐ፣ ዘተጻባዕከ፣
ዘተጻባዕክዎ፣ ዘተጻባዕክሙ፣ ዘተጻባዕኩከ፣ ዘተጻብዐኒ፣
ዘተጻባዕከኒ ማለቱን ያሳያል።
ትክልተ ሥላሴ ገባዕት ያልነውም፣
ዘተከልዋ፣ ዘተከልክምዋ፣ ዘተከልናሃ፣ ዘተከሉኪ፣
ዘተከልናኪ፣ ዘተከሉኒ፣ ዘተከልክኒ፣ ዘተከልክሙኒ
ይላል። ተሳቢም ሲዘረዝር ይህ ነው፣
አዳም ሰሎሞን ጽኑዐ አምላክ መንግሥት ሲል፣
አምላክ ዳዊት አምጻኤ ሐዋርያት አግብርት ወንጌለ
ዕፀ ምእመናነ አግብርተ ሲል ምእመና ለሊዎችን
ወንጌል ዕንጨትን ሐዋርያት አገልጋዮች ያመጡለት
አምላክ ዳዊት ነው ተብሎ ይፈታል። ሲዘረዘርም፣
ዘአምጽኡ ሐዋርያት አግብርት፣
ዘአምጻእነ ሐዋርያት አግብርት
ዘአምጻእክሙ ሐዋርያት አግብርት፣
ዘአምጽኡ ሐዋርያት አግብርቲሁ፣
ዘአምጽኡ ሐዋርያት አግብርቲከ፣
ዔሊ እግዚእ ተቃታሊ ሐዋርያት ደቂቁ ምስለ
ኢሎፍላውያን አይሁድ ሲል ከኢሎፍላውያን
ከአይሁድ ኢሎፍላውያን ጋር ሐዋርያት ልጆቹ
የተጋደሉ ጌታ ዔሊ ነው ተብሎ ይፈታል።
ሲዘረዝርም፣
ዘተቃተሉ ሐዋርያት ደቂቁ፣
ዘተቃተልክሙ ሐዋርያት ደቂቁ፣
ዘተቃተልነ ሐዋርያት ደቂቁ፣
ዘተቃተሉ ሐዋርያት ደቂቅከ፣
ዘተቃተልክሙ ሐዋርያት ደቂቁ፣
ዘተቃተሉ ሐዋርያት ደቂቅየ ይላል።

አክአብ አስተቃታሌ ብእሲቱ ደቂቀ እስራኤል ምስለ
ኤልያስ ሲል ከኤልያስ ጋር የእስራኤል ልጆችን
ሚስቱ ያጋደለች አክአብ ነው። ተብሎ ይፈታል።
ኤልዛቤሉ ብሎ አይዘረዝርም። አስተቃታሌ
ኤልዛቤል አለማለቱን አስተውል።
አገባብን /ለን/ ሲዘረዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣
ማርያም ንግሥተ አምላክ ሲል አምላክ ለእርሷ
የነገሠ ወይም የነገሠላት ማርያም ናት ማለት ነው።
ላቲ ማርያምን ይመለከታል። ግሱ አምላክን ያያል።
በዘ በዝርዝር ሲገለጽ ዘነግሠ ላቲ፣ ዘነገሥከ ላቲ፣
ዘነገሥኩ ላቲ፣ ዘነግሠ ለኪ፣ ዘነገሥኩ ለኪ፣ ዘነግሠ
ሊተ፣ ዘነገሥኩ ሊተ ይላል።
ሔዋን አቅራቢተ ሥላሴ ምሕረተ ሲል ምሕረትን
ሥላሴ ለእርሷ ያቀረቡ ወይም ያቀረቡላት ሔዋን
ናት ተብሎ ይፈታል። በዘ ተዘርዝሮ ሲገለጽ፣

ዘአቅረቡ ላቲ፣ ዘአቅረብነ ለኪ፣
ዘአቅረቡ ሊተ፣ ዘአቅረቡ ለኪ፣
ዘአቅረብነ ላቲ ዘአቅረብክሙ ላቲ
ዘአቅረብክሙ ሊተ ይላል።

እግዚአ ሰማይ አቅራቤ ጴጥሮስ ስብሐተ
ምእመናነ ሲል ምእመናን ምስጋናን ጴጥሮስ
ያቀረበለት የሰማይ ጌታ ነው። በዘ ተዘርዝሮ
ሲገለጽ፣

ዘአቅረብነ ሎቱ፣ ዘአቅረብኩ ለከ፣
ዘአቅረበ ለከ፣ ዘአቅረብከ ሎቱ፣
ዘአቅረበ ሊተ፣ ዘአቅረብኩ ሎቱ፣
ዘአቅረብከ ሊተ ይላል፣

አክሊላት ተጋዳልያተ ደናግል ምስለ አሕዛብ ሲል
ከአሕዛብ ጋር ደናግል ለራሳቸው የተጋደሉ ወይም
የተጋደሉላቸው አክሊላት ናቸው ተብሎ ይፈታል።
በዘርዝር ሲገለጽ፣

ዘተጋደላ ሎን፣ ሎቶን፣ ዘተጋደልነ ለክን፣

ዘተጋደልክን ሎን፣ ሎቶን፣ ዘተጋደላ ለነ፣
ዘተጋደልነ ሎን፣ ሎቶን ዘተጋደልክን ለነ
ዘተጋደላ ለክን፣ ይላል።።
አክሊል አስተጋዳሌ አምላክ ሰማዕተ ምስለ አሕዛብ ሲል ከአሕዛብ ጋር ሰማዕትን አምላክ ያጋደለለት አክሊል ነው ተብሎ ይፈታል።። ዝርዝሩ ከላይ እንደተገለጹት ነው።።
መስቀል ስቁለ አምላክ ሲል አምላክ በእርሱ የተሰቀለበት /የተሰቀለ/ መስቀል ነው ተብሎ ይፈታል።።
መስቀል ሰቃሌ ይሁዳ አምላክ ሲል አምላክን ይሁዳ በእርሱ የሰቀለበት መስቀል ነው ተብሎ ይፈታል።። ምዑዝ ውእቱ ዕጣን አውፃኤ ዕሌኒ መስቀለ ሠራዊተ ሲል ሠራዊትን መስቀልን ዕሌኒ በእርሱ ያወጣችበት ዕጣን ምዑዝ ነው ተብሎ ይፈታል።።
አፀደ ወይን ተጸባኤ ናቡቴ ምስለ አክአብ ሲል ከአክአብ ጋር ናቡቴ በእርሱ የተጣላ /የተጣላበት/ ርስት ነው ተብሎ ይፈታል።።
ወንጌል አስተጸባኢተ አምላክ ሰማዕተ ምስለ አሕዛብ ሲል ከአሕዛብ ጋር ሰማዕትን አምላክ ያጣላባት ወንጌል ናት ተብሎ ይፈታል።።
ምስለን ሲዘረዝር፣
አምላክ መዋቴ ፈያት /ምውተ ፈያት/ ፈያት ከእርሱ ጋር የተሰቀሉ አምላክ ነው ይላል።።
አምላክ ሰቃሊ አይሁድ ፈያተ ሲል ፈያትን አይሁድ ከራሱ ጋር የሰቀሉ አምላክ ነው ተብሎ ይፈታል።።
አምላክ አስቃሌ አይሁድ ፈያተ ሠራዊተ ሲል ሠራዊትን ፈያትን አይሁድ ከእርሱ ጋር ያሰቀሉ አምላክ ነው ተብሎ ይፈታል።።
ጎልያድ ተቃታሌ ዳዊት ሲል ዳዊት ከእርሱ ጋር የተጋደለ /የተዋጋ ጎልያድ ነው ተብሎ ይፈታል።።
ጎልያድ አስተቃታሌ ሳየል ዳዊትህ ሲል ዳዊትን ሳየል ከራሱ ጋር ያጋደለ ጎልያድ ነው ተብሎ ይፈታል።።

እንበይነ ሲዘረዝር፣
አዳም ምውተ እግዚእነ /መዋቱ እግዚእነ ሲል ጌታችን ስለራሱ የሞተ/የሞተለት/ አዳም ነው ተብሎ ይፈታል፡፡ አዳም ከዐቂ እግዚእነ ደመ ሲል ደምን አምላክ ለራሱ ያፈሰሰ አዳም ነው ተብሎ ይፈታል፡፡ ነዳይ አዳም አፍታሔ መሐላ ንጉሥ ደመ ፍትሐ ሥዩመ አምላክ ሲል አምላክ ሹምን ደም ፍርድን መሐላ ንጉሥ ስለራሱ ያስፈረደ አዳም ችግረኛ ነው ተብሎ ይፈታል፡፡
አዳም ተጻባኤ አምላክ ምስለ መልአክ ሞት ሲል ከመልአክ ሞት ጋር አምላክ ስለራሱ የተጣላ አዳም ነው ተብሎ ይፈታል፡፡
አዳም አስተጻባኤ አብ ወልዶ ምስለ መልአክ ሞት ሲል ከመልአክ ሞት ጋር ልጁን አምላክ ስለራሱ ያጣላ አዳም ነው ተብሎ ይፈታል፡፡
ኀበን ሲዘረዘር፣
ማርያም ተፈናዊተ ገብርኤል /ፍኑተ ገብርኤል/ እምሰማይ ሲል ከሰማይ ገብርኤል ወደእርሷ /እስከ እርሷ/ የተላከ ማርያም ናት ተብሎ ይፈታል፡፡
ማርያም ፈናዊተ አምላክ ገብርኤልሀ ሲል ገብርኤልን አምላክ ወደእርሷ /እስከ እርሷ/ የላከ ማርያም ናት ተብሎ ይፈታል፡፡
ማርያም አፈናዊተ አምላክ ገብርኤልሀ ብሥራተ ሲል ገብርኤልን የምሥራችን አምላክ ወደእርሷ /እስከ እርሷ ድረስ/ የላከ ማርያም ናት ተብሎ ይፈታል፡፡
መቃብረ እግዚእነ አስተራዋጺተ ዮሐንስ ምስለ ጴጥሮስ ሲል ከጴጥሮስ ጋር ዮሐንስ ወደእርሷ የተራወጠ መቃብር ናት ማለት ነው፡፡
መቃብረ እግዚእነ አስተራዋጺተ ትንሣኤሁ ጴጥሮስሀ ምስለ ዮሐንስ ሲል ከዮሐንስ ጋራ ጴጥሮስን ትንሣኤው ወደእርሷ ያራወጠ የጌታ መቃብር ናት ማለት ነው፡፡
ጴጥሮስ ምሁረ አርድዕት ወንጌለ ሲል ወንጌልን አርድዕቱ ያስተማሩ ጴጥሮስ ነው፡ ተብሎ ይፈታል፡፡

ሲዘረዘርም፣ ዘመሀሩ አርዳኢሁ፣
ዘመሀሩ አርዳኢከ፣
ዘመሀርክሙ አርዳኢሁ፣
ዘመሀርነ አርዳኢከ፣
ዘመሀርነ አርዳኢሁ፣
ዘመሀሩ አርዳእየ ይላል፡
እምን ሲዘረዝር፣
ሰማይ መጻኤ ገብርኤል እስከ ማርያም፣
ሰማይ አምጻኤ ገብርኤል አስከ ማርያም ብሥራተ፣
ሰማይ አምጻኤ አምላክ እስከ ማርያም ብሥራተ ገብርኤልሀ፣
መቃብረ እግዚእነ ተራዋዔ መግደላዊት ማርያም ምስለ አብያጺሁ እስከ ሐዋርያት፣
መቃብር አስተራዋዔ እግዚእ መግደላዊተ ምስለ አብያጺሁ እስከ ሐዋርያት፣ ይላል።
ከመን ሲዘረዝር፣
ዳዊት ነጋሤ ሰሎሞን፣
ዳዊት አንጋሤ አምላክ ሰሎሞንሀ፣
ፈያታዊ አስቃሌ ይሁዳ ክርስቶስሀ፣
ወይጠል ተራዋዪተ አሳሄል፣
ኢዮአብ አስተቃታሊ ዳዊት አሳሄልሀ ምስለ አፅራሪሁ ተቀትለ በእደ አቤሴሎም፣
እስከን ሲዘረዝር፣
ማርያም ተፈናዊተ ገብርኤል እምጎበ አብ መድኃኒተ ኵሉ ይእቲ፣
እስከ አሁን የመጣው ሁሉ ተለዋጭ ቅጽል ነው።
በአራቱ አርእስት ሁሉ እስከን እንዲህ እያስማማህ አግባ።
እንበለ ሲዘረዝር፣
እንበለ አሉታ ድረስ ሲዘረዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው።
አዳም ኢስቁለ አምላክ አበ ሥጋነ ባለ ጊዜ አምላክ ያለእርሱ ያልተሰቀለ አዳም የሥጋችን አባት ነው ተብሎ ይተረጎማል። /የያለ አሉታ ሲሆን ነው/፣

፪ቱ እሙንቱ ፈያት ኢስቁላነ አምላክ ባለ ጊዜ ያለ እነርሱ/ያለእርሳቸው/ ያልተሰቀለ ፈያት ሁለት ነበሩ ተብሎ ይፈታል /የከመ፣ የምስለ አሉታ ሲሆን ነው/፣ ማርያም ኢፍንውተ ገብርኤል ሲል የጎበ እና የእስከ አሉታ ነው።።
አብ ኢውሉደ ወልድ ሲል ወልድ ያለእርሱ ያልተወለደ ማለት ሲሆን የእም አሉታ ነው።።
መስቀል ኢስቁለ አምላክ ሲል አምላክ ያለእርሱ ያልተሰቀለ መስቀል ማለት ሲሆን የበ አሉታ ነው።።

ሰባተኛው ዐዋጅ፣
ሠረዝ፤

ሠረዝ የቅኔ መንገድ ስም ሲሆን ሁለት አርእስት ያለው ንባቡና ምሥጢሩ በዋዌ እየተጫፈሩ የሚሄድ ማለት ነው።። ሠረዝ ተዘዋሪ እየተባለም ይጠራል።።
ሠረዝ የሚባሉት ተደርበው ሲቆጠሩ ፲ ተነጥለው ሲቆጠሩ ደግሞ ፳ ናቸው።። እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።።

ሀ. ጎዳሪና ማጎደር	ረ. ልዑልና ትሑት
ለ. ገንዘብና ባለገንዘብ	ሰ. ሩቅና ቅርብ
ሐ. ወላጅና ተወላጅ	ቀ. ጋራጅና ተጋራጅ
መ. ለሚና አልሚ	በ. ተነሽና አስነሽ
ሠ. ጠፊና አጥፊ	ተ. ጠሪና ተጠሪ

ናቸው።።

ሀ. ጎዳሪና ማጎደር፤
ጎዳሪ ከማጎደር፣ ማጎደር ከጎዳሪ አይዛመዱም።።
ግብርና ነገር ጎዳሪ ይሆናሉ።። ቦታ፣ ጊዜ፣ ማጎደር ይሆናሉ።።

የማኅደር አገባብ ለ ነው፡፡ አገባቦቹ ደግሞ በጎበ፣ ዲበ፣ ላዕለ፣ መልዕልተ፣ ታሕተ፣ ቅድመ፣ ድኅረ፣ ውስተ፣ ውሳጤ፣ ማዕከለ ናቸው፡፡ እነዚህም በነጠላ፣ በሰም፣ በወርቅ በዘርዝር፣ በጥቅል፣ በክፍል፣ በሥረዝ ይነገራሉ፡፡ ማሰሪያቸው ውእቱ ነው፡፡
ለ. የገንዘብና የባለገንዘብ አገባብ፤ ለ፣ በ፣ በጎበ ናቸው፡፡
ሐ. የወላጅና የተወላጅ አገባብ፤ እም ነው፡፡ የተወላጅ አገባብ ለ ነው፡፡
መ. የለሚና የአልሚ አገባብ፤ የለሚ አገባብ ለ፣ በጎበ፣ ቅድመ፣ ናቸው፡፡
የአልሚ አገባብ፣ የአልሚ አገባብ በ ነው፡፡
ሠ. የጠፊና አጥፊ አገባብ፤ የጠፊና አጥፊ የሁለቱም አገባቦች በ፣ በጎበ፣ ቅድመ ናቸው፡፡
ረ. የልውልና የትሑት አገባቦች፤ የሁለቱም አገባቦች በ፣ በጎበ፣ ታሕተ፣ መትሕተ፣ ቅድመ፣ እም ናቸው፡፡
ሰ. የሩቅና የቅርብ አገባቦች፤ የሩቅ አገባብ እም ነው፡፡ የቅርብ አገባቦች ጎበ፣ መንገለ፣ ለ ናቸው፡፡ ውእቱ ይገለጽባቸዋል፡፡
ለአስረጅ፣ ለባለቤት፣ ቅጽል፣ ዘርፍ አይስማማቸውም፡፡ በወ፣ በከመ ይሠረዛሉ፡፡
እመ፣ ሶበ፣ ምስለ ይስማማቸዋል፡፡
የሠረዝ ቅኔ ምሳሌዎች፤
ሀ. ጎዳሪና ማኅደር፤
ማርያም መዝገብ ወበማርያም መዝገብ ለአማኑኤል ወርቅ ሰማይ ኮከብ፡ ወኮከብ ሰማይ አማኑኤል ወርቅ፡፡ ሲተረጎም፤

ማርያም መዝገብ ለአማኑኤል ወርቅ ሰማይ
ኮከብ ናት። በማርያም መዝገብም፡ ኮከብ ሰማይ
አማኑኤል ወርቅ ነው።
ማርያም መዝገብ ለአማኑኤል ወርቅ ሰማይ
ሙዳይ፤ ወአማኑኤል ወርቅ በማርያም መዝገብ፣
መንፈስ ቅዱስ ብሩር።
ማርያም መዝገብ ወአማኑኤል ወርቅ ለአማኑኤል
ወርቅ ወበማርያም መዝገብ ሰማይ ሙዳይ
ወመንፈስ ቅዱስ ብሩር ይላል።
በነጠላ ሲነገሩ፣
ማርያም ለአማኑኤል መዝገብ ወአማኑኤል
በማርያም ወርቅ።
የጎዳሪና ማኅደር ስድስት አወዳደቅ አላቸው፣

፩፡ ተክለ ሃይማኖት ብሩር ወገነት መዝገብ፣
በገነት መዝገብ ወለተክለ ሃይማኖት
ብሩር፡ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወርቅ
ወመንግሥተ ሰማይ ጽርሕ።
፪፡ ተክለ ሃይማኖት ወገነት መዝገብ ገብረ
መንፈስ ቅዱስ ወርቅ ወመንግሥተ ሰማይ
ጽርሕ በገነት መዝገብ ወተክለ ይማኖት
ብሩር።
፫፡ በገነት መዝገብ ወለተክለ ሃይማኖት ብሩር
ለተክለ ሃይማኖት ብሩር ወገነት መዝገብ
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወርቅ ወመንግሥተ
ሰማይ ጽርሕ።
፬፡ በገነት መዝገብ ወለተክለ ሃይማኖት ብሩር
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወርቅ ወመንግሥተ
ሰማይ ጽርሕ ተክለ ሃይማኖት ብሩር ወገነት
መዝገብ።
፭፡ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወርቅ ወመንግሥተ
ሰማይ ጽርሕ ተክለ ሃይማኖት ብሩር ወገነት

መዝገብ በግነት መዝገብ ወለተክለ ሃይማኖት ብሩር።።

፮። ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወርቅ ወመንግሥተ ሰማይ ጽርሕ በግነት መዝገብ ወለተክለ ሃይማኖት ብሩር ተክለ ሃይማኖት ብሩር ወግነት መዝገብ በማለታቸው ይታወቃሉ።።

፮ ገንዘብና ባለገንዘብ በሥረዝ ሲነገር፣

አዳም ንዋየ አማኑኤል ባዕል፣ ወአማኑኤል ባዕል አዳም ንዋይ፡ ይላል።።
ጊዜና ነገር ሲገቡ፤ ዘመነ ሊቃውንት ለትምህርተ ሃይማኖት ዘመነ ሐዋርያት፣ ወትምህርተ ሃይማኖት ለዘመነ ሊቃውንት መሥዋዕተ ወንጌል ይላል።።

፯ ቦታና ግብር ሲገቡ፣

ተክለ ሃይማኖት በለስ ለግነት ተክለ ወይን፣ ወግነት ለተክለ በለስ ደብር ውእቱ ይላል።።
አካል ግን ገንዘብም ባለገንዘብም ይሆናል።።
ሲገባም፣
ዳዊት ወልድ ለሚካኤል ኢዮአብ ለሰሎሞን አብ፣ ወሚካኤል ኢዮአብ ለዳዊት ወልድገብርኤል አቢሳ ውእቱ ይላል።።

፱ ወላጅና ተወላጅ ሲገባ፣

ራሔል ወዮሴፍ ለዮሴፍ ወእም ራሔል ያዕቆብ ወብንያም ይላል።።

፲። የለሚና የአልሚ ሠረዝ ሲገባ፣

ንጽሕና ነፋስ ሥጋ ማርያም እሳት ወንጽሕና ነፋስ አካለ ኪሩብ አርዝ ይላል።

፲፩። የጠፊና ያጥፊ ሠረዝ ሲገባ፣

አበሳ አዳም ቤት በጎበ ደመ ኢየሱስ ነፋስ አበሳ ሔዋን ደመናወደመ ኢየሱስ ነፋስ በጎበ አበሳ አዳም ቤት መስቀል ንስር ይላል።

፲፪። የልዑልና የትሑት ሠረዝ ሲገባ፣

ጴጥሮስ ወርቅ እም ይሁዳ በጎበ ይሁዳ ብሩር ክርስቶስ ዕንቄ ባሕርይ ወይሁዳ ብሩር እምነ ጴጥሮስ ወርቅ መልአከ ዝንቱ ዓለም ሐሚን ይላል።

፲፫ የቅርብና የሩቅ ሠረዝ አገባብ ሲገባ፣

ሥጋ ማርያም ኮከብ ለወርኀ ንጽሕና አካለ ኪሩብ ፀሐይ ይላል።
ሥጋ ማርያም ፀሐይ እምነ ምድር አበሳ አካለ ሱራፊ ሰማይ ይላል።
ሌሎችን በዚህ መንገድ ማስገባት ይቻላል።
የሠረዝ መንገድ ብዙ ቢሆንም ጥቂቶችን በጉት ቅኔ ለማሳየት እንሞክራለን።

፲፬ ጉት መንታ ሠረዝ፣

ኢየሱ ፀሐይ ወአሞሬዎን በረድ፣

፲፭ ሌባ ሠረዝ፣

አብርሃም ወዳዊት ዘይተ ቤተ ዳዊት አስካል
ወአስካለ አብርሃም ዘየት ይበልዑ ድኅረ ፍሬ
ትንሣኤ እንኅት ይላል።።

፲፮ አደናጋሪ ሠረዝ፣

በንጉሥ ደንገፀ ወኢደንገፀ ግሩም፣
ንጉሠ ሕዝባ ለባቢሎን በኤፍሬም ወኤፍሬም።።

፲፯ ተቻቻይ ሠረዝ፣

ደመና ዝናም ቄሪር ወእንተ ደመና ዝናም ጠለ
ደመና ወበደመና አድግ ብሔረ ግብፅ ወእክለ
ጣዕም።።

፲፰ የስም ሠረዝ፣

ኢያሱ ወአሞራዎን በረድ ወወይን እያለ
ይቀጥላል።።
ሠረዝ በቅኔዎች ሲገለጽ የሚከተለውን ይምስላል።።

፩። ነጠላ ሠረዝ፣ ዘአምላኪየ ቅኔ፣

ደመና ዘቆመ ቅድመ ገጸ ሙሴ በሲና፣ ወበታቦር
ቅድመ ገጸ ወልድ ዘቆመ ደመና፣
ጸዋሬ መና ምውቅ ወአኮ ጸዋሬ ምውቅ መና።

፪። መንታ ሠረዝ፣

መወድስ ከለዓለም ጀምሮ፣
እግዚአብሔር ታወርሶሙ ብሔረ ጥዒና መንክር፣
ዘይኤድም አርአየሁ ወልምላሜሁ ዘይትፈቀር፣
ለዕውር እግረ ሐንካስ ወለሐንካስ ዐይነ ዕውር፣

እምነጽሮ ፍና ገጸ ብእሲ ወእምሐዊረ ገጽ ፍና ብሔር።።

፫÷ ድርብ ሠረዝ፣ ሥላሴ፣

አስተብፅዑ ነፍስተ ዓሣ፣ ኢየሱስ ወጴጥሮስ ወሩፋኤል፣ ባሕረ ውቅያኖስ አኮኑ አመ ኢየሱስ ወፈረ፣
በኀዳጥ ዓሣ አጽገበ ማኅበረ፣
ወእምከርሠ ዓሣ አውፅአ ጸባሕተ ቄሳር ዲናረ፣
መሠግር ጴጥሮስ አመ አሥገረ፣
በዓሣሁ አሕየወ ዕውረ።።

የቀሩት ሠረዞች በኀዳሪና በማኅደር እንደ ተነገረው ይነገራሉ።።

የሰዋስው ጸያፎች፤

የሚመሰሉና የማይመሰሉ፣ ጸያፍ የሚሆኑና የማይሆኑ ነገሮችን እየተመለከትን የመጠን ቢሆንም በአንድ ቦታ ሰብሰብ አድርጎ መግለጹ ለግንዛቤ ስለሚረዳ ለይቶ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።። በሰዋስው የአካሄድ ሥርዓት መሠረት የማይመሰሉና ጸያፍ የሚባሉት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩. አንድና ብዙ
፪. ወንድና ሴት
፫. ቅርብና ሩቅ
፬. ነባቢና ኢነባቢ
፭. ቦታና ቦታ
፮. ስምና ግብር
፯. ከአንቀጽ ወዲያ ቅጽል
፲፩. የደቂቅ ድፋት
፲፪. ያለወገኑ ተናባቢ
፲፫. የዘርፍ ድፋት
፲፬. የተናባቢ ድፋት
፲፭. ሳቢና ተሳቢ ማስተላለፍ
፲፮. ገቢርና ተገብሮ
፲፯. ክፉና መልካም

፰. ፍርቅ ፲፰. የልጅ ልጅ
፱. ግንባር ፲፱. ከፍሎ ማስጠበቅ
፲. ዝርው

አንድና ብዙ፣ ወንድና ሴት፣ ቅርብና ሩቅ የማይመሰሉ በማሰሪያ አንቀጽ አንድ ስላልሆኑ ነው።። ለምሳሌ አእመረ የሚለውን ግስ ወስደን የወንድና የሴት የጋራ ማሠሪያ አንቀጽ ማድረግ አንችልም።። አእመረት የሚለውን ብንወስድም ተመሳሳይ ነው።። አእመሩ ብንል ደግሞ የብዙ እንጅ የነጠላ ቁጥር ማሠሪያ አይሆንም።። አእመርከ ብንልም የቅርቡ እንጅ የሩቁ ማሠሪያ አንቀጽ ሊሆን አይችልም።። ጸያፍ የተባሉት በዚህ ምክንያት ነው።። በቅጽልም በተመሳሳይ ሁኔታ አይገናኙም።። እያንዳንዱ ለየራሱ ተስማሚ ቅጽል አለው።። ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፣

ነሠቱ ሥላሴ ነፋስ ጥቅመ ሰናያር ቢል አንድና ብዙ በመሆኑ አንቀጹ አይስማማም

ብእሲት ጳውሎስ አነመ ፈትለ አሚን ቢል ወንድና ሴት በመሆኑ አንቀጹ ለሴት አይሆንም

ወድቀ ጳውሎስ ዘግባ ዘከደንከ ዐውደ ሮም ቢል አንቀጹ ለሩቅ አይሆንም።።

ተጠብሐ በግዐ ዮሐንስ ቢል ነባቢና ኢነባቢ ይሆናል፤ ዐርገ ዐቀበ ሰማይ ቢል የቦታ ጸያፍ ይሆናል፣

ለብሰ አነዳ ነዳየ መልከጼዴቅ ቢል የስምና ግብር ጸያፍ ይሆናል

ጳውሎስ ላሕም ተጠብሐ ነዊኀ ኀይማኖት ቀርን ቢል ከአንቀጽ ወዲያ ቅጽል ይሆናል

ዝናም መጽአ ሆሣዕና ቢል ፍርቅ ይሆናል፣ አንቀጹ በምሳሌዎች መካከል ገብቷል

ለተቀንዎ አምላክ ዘኢያኅጸርከ አእጋረ ቢል ግሥግሥ ጸያፍ ይሆናል

ቤት አልፎ ወይም ከቤት ወዲያ ቢመሰል ዝርው ጸያፍ ይሆናል

ነበረ አምላክ ንጉሥ ለኪሩብ ሠረገላ ላዕሌሁ ቢል የደቂቅ ድፋት ጸያፍ ይሆናል
አምላክ ምሕረት ወመዓት ቢል ያለወገኑ ተናባቢ ጸያፍ ይሆናል፣
ለነዌ መዛግብተ ወርቁ ቢል የዘርፍ ድፋት ጸያፍ ይሆናል፣
ፅዕድው ለጴጥሮስ መርዓዊ ልብሰ ጎይማኖቱ ቢል የተናባቢ ድፋት ጸያፍ ነው፣
ሳቢና ተሳቢን ማስተላለፍ የውስጠ ተሳሳቢ ጸያፍ ይሆናል/እንደ ግሥግሥ ነው/፣
ተበልዐ ጎብስተ፣ ወይም በልዐ ጎብስት ቢል የገቢር ተገብሮ ጸያፍ ይሆናል፣
ጎበ ማርያም ደንግል ምድረ ገሞራ ቢል የክፉና መልካም ጸያፍ ይሆናል፣
ተፈጸመ ዐዋጅ።።

ምዕራፍ ሦስት

፰ አገባብ

አገባብ /ሥርዐተ ሰዋስው/ ማለት የቅኔ ሙያ ማሳኪያ፣ ማስተካከያ እና ትርጉም እንዲሰጥ የማድረጊያ ስልት ነው።። አገባብ መጻሕፍትን አንብቦ ትርጉማቸውን ለመረዳትና ምሥጢራቸውን ለማወቅ ዋና መክፈቻ ቁልፍ ነው።። አገባብ የሌለውን ቅኔ መድረስም ሆነ መተርጎም አይቻልም።። በአጠቃላይ በቅኔ መግባባት የሚቻለው በአገባብ ነው።። ስለዚህ ለቅኔ ለዛና ውበት የሚሰጠው፣ ጥልቅ ምሥጢርና ምጡቅ ፍልስፍና እንዲኖረው የሚያደርገው አገባብ ነው።። ቅኔ ከነአገባቡ፣ ግስ ከነእርባ ቅምሩ እየተባለ የሚነገረውም ለዚህ ነው።። ከዚህ የምንረዳው ቅኔ ያለእርባ ቅምርና ያለአገባብ የተበተነ የቃላት ድርድር ሆኖ የሚቀር መሆኑን ነው።። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /1948/ አገባብን ከዚህ እንደሚከተለው ተርጉመውታል፣

አገባብ መፍትው፣ ርትዕ፣ ድሎት፣ ካለው የወጣ ነው፡፡ ዘይቤውም የተገባ፣ ግቡ፣ የሚገባ፣ ሥርዓት፣ የነገር አጣጣል፣ የንባብ አሰካክ፣ ወይም በይግባኝ መምህር የሚፈርደው ፍትሐ ሰዋስው ማለት ነው፡፡ ሁለተኛም አገባብ ማለት ጨው እንደማለት ነው፡፡ የብትን ቃል ሁሉ መሰብሰቢያና ማስማሚያ፣ የቋንቋ ቅመም፣ የንባብ መቃስም ወይም ማጣፈጫ፣ የምሥጢር መግለጫ ማለት ነው ብለውታል፡፡

አገባብን ዘርዘር አድርጎ የሚያስተምር የዋድላ ቤተ ጉባኤ ነው፡፡ ጎንጅም የራሱ አገባብ ያለው ቢሆንም ከሁሉም በጣም አጭሩ እርሱ ነው /አክሊለ ብርሃን ወ/ቂርቆስ፣ መርሐ ልቡና፣ 1943/፡፡ የዋሽራን አገባብ በተመለከተም ወጥነት የለም፡፡ መምህር ገድሉ የዋሽራ ቤተ ጉባኤ መምህር ሆነው ሳለ የዋድላን አገባብ እንደተማሩና እንዳስተማሩ ይነገራል፡፡ ከዋሽራ ተመርቀው የወጡት የደብረ ማርቆሱ መሪጌታ መንግሥቱ ደግሞ በአለቃ ታየ መጽሐፈ ሰዋስው ውስጥ የሚገኘውን አገባብ በዝርዝር ያስተምሩ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ለብዙ ተማሪዎችም ይህን አገባብ አስተምረዋል፡፡ የቀራንዮው መምህር ተስፋም እንደ መሪጌታ መንግሥቱ በመጽሐፈ ሰዋስው ውስጥ የሚገኘውን አገባብ ያስተምሩ ነበር፡፡ መምህር ጥዑመ ልሳን ልየውም ዛሬ በዋሽራ ይህንኑ እያስተማሩ ነው፡፡ ስለዚህ የትኛውን አገባብ የዋሽራ ብሎ መያዝ እንደሚቻል ያስቸግራል፡፡ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን ስንመለከት ደግሞ ከአለቃ ታየ ያጠረና ከዋድላ ጋር የሚቀራረብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የዋድላ አገባብም ቢሆን በስድስተኛው ድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ ሰባት ዓይነት ደርሶ እንደነበር ይነገራል /አክሊለ ብርሃን ወ/ቂርቆስ፣ መርሐ ልቡና፣ 1943፣ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት፣ 1963፣ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው፣ 2002/፡፡ ይህ ሰባት ዓይነት

የሚባለው አገባብ በተጨባጭ አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይልቁን ሰባት ዐዋጅ፤ ሰባት እርባ ቅምር፣ ሰባት አገባብ ማለት ትርጉሙ ሌላ እንደሆነ መምህራን ያስረዳሉ፡፡ ሰባት ዐዋጅ ማለት በአለቃ ቡሩኬ አገባብ እና በአለቃ ታየ መጽሐፈ ሰዋስው፣ መጽሔተ አእምሮ /1958/ እንደተገለጸው ከአንድ እስከ ስድስት በተራ ቁጥር የተዘረዘሩት አዋጆች እንደሆኑና ሰባት አገባብ ማለትም፤ ሰባት የተለያየ ጥራዝ ያለው አገባብ ሳይሆን ከዚህ የሚከተሉት ርእሶች መሆናቸውን ያብራራሉ፤

፩. ዐቢይ አገባብ
፪. ንዑስ አገባብ
፫. ደቂቅ አገባብ
፬. ተረፈ ንዑስ አገባብ
፭. ደቂቅ እርባታ
፮. ሰምና ወርቅ
፯. አጎዝ

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዋድላ ብቻ ግልጽ ልዩነት ያለው ማለትም አንዱ ከሌላው የማይገናኝ ሰባት አገባብ ነበረ ብለው የሚከራከሩ ወገኖችም እንዳሉ መዘንጋት የለበትም፡፡ በእርግጥ አንዱ ከሌላው የተለየ ሰባት አገባብ የነበረ ከሆነ አሁን እንዴት ላይገኝ ቻለ? ዛሬም በማያሳምን መንገድ የጌቱ ገሞራውንና የአለቃ ቡሩኬን አገባቦች እንዲሁም ሌሎችን በማጠረቃቀም ሰባቱ አገባቦች እነዚህ ናቸው ብለው የሚናገሩ አሉ፡፡
ዝርዝሮችም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣
፩. የስም አነሳስና አወዳደቅ ዐዋጅ፣
፪. አጎዝ፣
፫. የጎንጅ እርባ ቅምርና አገባብ
፬. የጌቱ ገሞራው አገባብ /ዋድላ/
፭. የአለቃ ቡሩኬ አገባብ /ዋድላ/
፮. የዋሸራው ተክሌ እርባ ቅምር

፮. የሜሮ፣ ቆመ አገባብ፣ የሚሉ ናቸው /በብራና ከተጻፉ የእመይቴ ገላነሽ አገባብ ውስጥ የተገኘ ተብሎ በመሪጌታ ኪዳኑ የቀረበ/፡፡

ሰባት አገባብ ደረሰ የሚባለው በነድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ ነው፡፡ አለቃ ተክሌ በሕይወት የነበሩት ደግሞ ትናንት እንጅ በስድስተኛው ድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ አይደለም፡፡ የጎንጅም ቢሆን የራሱ የጎንጅ እንጅ የዋድላ ሆኖ ሊቆጠር አይችልም፡፡ ከዚህ ሌላ እርባ ቅምርን፣ ዐዋጅንና አገባብን በመቀላቀል ሰባት ለማድረግ የተደረገ ሙከራ እንጅ ሰባት እርባ ቅምር፣ ወይም ሰባት ዐዋጅ፣ ወይም ሰባት አገባብ መኖሩን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛው አማራጭ ስህተት ነው፡፡

ሌላ ሦስተኛ አማራጭም አለ፡፡ እርሱም ከዚህ የሚከተለው ነው፤

፩. በአለቃ ቡሩኬ አገባብ ከሙሻ ዘር በፊት ያሉት ዐዋጆች፣

፪. ሙሻ ዘር

፫. አርእስትንና ሠራዊትን የሚዘረዝረው እርባ ቅምር፣

፬. የስም አነሳስና አወዳደቅ ዐዋጅ፣

፭. ዐቢይ አገባብ፣

፮. ደቂቅ አገባብ፣

፯. ንዑስ አገባብ፣ ናቸው የሚሉ አሉ፡፡

እነዚህ አገባቦችና አዋጆች በዚያው በዋድላ ቤተ ጉባኤ አንዱ መምህር የተወሰኑ አዋጆችንና አገባቦችን ከቀመረ በኋላ ሌላው ደግሞ በእግሩ ሲተካ የጎደለውን በዐዋጅና በአገባብ መልክ እየሞላ የሄደበት ሁኔታ እንዳለ መምህራኑ ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያው መምህር የሰዋስውን ትርጉምና የአናቅጽን ባሕርያት ዐበይት፣ ንዑሳን፣ ደቂቅ/ በመዘርዘር በዐዋጅ ደንግጎ አለፈ፡፡ ሁለተኛው መምህር ደግሞ ሙሻ ዘርንና ሌሎች ስለጸያፍ የሚያብራሩ አዋጆችን አዘጋጀ፡፡ ሦስተኛው መምህር

እርባ ግስን በአርእስትና በሥራዊት፣ እንዲሁም በሌሎች አፈንጋጭ የእርባታ ዘዴዎች ቀምሮ አዘጋጀ፡፡ አራተኛው መምህር ስም እንዴት እንደሚነሳና እንደሚጣል ሕግ አወጣ፡፡ አምስተኛው፣ ስድስተኛውና ሰባተኛው መምህር በየራሳቸው ዐቢይ፣ ደቂቅና ንዑስ አገባብን ፈጠሩ፡፡ በስድስተኛው ድድቅ ጉባኤ ሰፍቶ ሰባት ዐዋጅ፣ ሰባት አርባ ቅምር፣ ሰባት አገባብ ደርሶ ነበር ማለት ይህ ነው ብለው የሚያብራሩ መምህራን አሉ፡፡ ይህን አከፋፈል ስንመረምረውም ከላይ እንደተገለጹት እርባ ቅምርን፣ ዐዋጅንና አገባብን አቀላቅሎ የያዘ ስለሆነ ሰባት እርባ ቅምር፣ ሰባት ዐዋጅና ሰባት አገባብ የሚለውን አያሟላም፡፡ በዚህ መሠረት ይህም አከፋፈል ችግር አለበት፡፡

ስለዚህ ትክክለኛው ሰባት አገባብ ማለት በመጀመሪያ የተገለጸው ብቻ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ምንም እንኳ የተነሣንበት ዓላማ ስለርባ ቅምር ማተት ባይሆንም እግረ መንገዱን ገልጾ ለማለፍ፣ ሰባት እርባ ቅምር የሚባሉት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩፡ ዘማች አናቅጽ /አምስቱ አዕማድ/....አምስት፣
፪፡ ነባር አናቅጽ.....አንድ
፫፡ ከግስ፡የማይወጣ ነባር.....አንድ
ድምር ሰባት፡፡

እርባ ቅምርን በተመለከተ ይህ አከፋፈል ያስኬዳል፡፡ ምክንያቱም ዘማች አናቅጽ፣ ነባር አናቅጽና ነባር የተካተቱበት አከፋፈል ነው፡፡ እንደሚታወቀው አናቅጽ በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም ዘማች አንቀጽና ነባር አንቀጽ ሲሆኑ ዘማች አንቀጽ ደግሞ በአምስት አዕማድ ይከፈላል፡፡ ስለዚህ ይህ አከፋፈል ሚዛን የሚደፋና ምክንያታዊ ነው፡፡

ከእነዚህ ውጭ ሌላ ሰባት ርባ ቅምር፣ ሰባት ዐዋጅ፣ ሰባት አገባብ የሚባል ነገር ለጊዜው የለም። ማስረጃ አለኝ የሚል ካለ ማየትና መከራከር ይቻላል። እነዚህም በብዙ ድካምና ጥረት የተገኙ ናቸው።

እግረ መንገዱን ለመግለጽ፣ በግእዝ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝ ቃል ወይም ሐረግ ከነዚህ ከሦስቱ አይወጣም። ሰዋስውን መሠረቱት የሚባሉት ዘርና ነባርም የሚገኙት ከነዚህ ከሦስቱ ነው። ይህ ጉዳይ እንደዋዛ በአንድ አንቀጽ ተገልጾ የሚታለፍ አይደለም። ሰፊ ጥናትና ምርምር ያስፈልገዋል።

ከላይ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሰዎች እጅ የሚገኙት የዋድላ አገባቦች ሁለት ናቸው። ማጠርና መርዘም ወይም መግደፍና መጨመር ካልሆነ በስተቀር ይዘታቸው ግን አንድ ነው። እነርሱም የአለቃ ቡሩኬ እና የጌቱ ገሞራው አገባቦች ናቸው። በብዛት በየሰው እጅ የሚገኘው የጌቱ ገሞራው አገባብ ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ደጋግ መምህራን ያለምንም ንፍገት ስለአስተማሩና ስለአሰራጩት ነው። የሌሎቹ አብያተ ጉባኤ መምህራንም በተለይ ጎንጆች ይህንን አገባብ ይጠቀሙበታል። ለማንኛውም ለመጭው ትውልድና በመስኩ ምርምር ለሚያደርጉ ምሁራን ድካምን በሚቀንስ ሁኔታ የአለቃ ታየን፣ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን፣ የዋድላንና የጎንጅን አገባቦች በመመርመርና አንድ ወጥ በማድረግ አዘጋጅተን አቅርበናል። ነገር ግን መሠረታዊው የአገባብ ልዩነት ማነስና መብዛት ሳይሆን የአጠቃቀም ዘዴው ነው። ለምሳሌ ዐቢይ አገባብ የሆነ ሁሉ በአንቀጽ ላይ አይወድቅም። በር ከፋች የሚፈልጉ አሉ። ለምሳሌ በእንተ፣ በይነ፣ እንበይነ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ አስበ፣ እና ተውላጠ ስለ የሚል ትርጉም ይዘው በዘማችና በነባር አናቅጽ በታላፊ አንቀጽ ላይ ሲወድቁ የግድ ዘን፣ በር ከፋች አድርገው መግባት አለባቸው። ያለበር ከፋች በዘንድና በትዕዛዝ አናቅጽ ላይም ተናባቢ አድርጎ

ሌሎች ዐበይት አገባባትን መጫን አይቻልም። በአገባብ አጠቃቀም ዙሪያ መሠረታዊ ልዩነት የሚያመጣው እንዲህ ዓይነቱ የአገባብ ሥርዓት ነው። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አንዳንድ ጊዜ ወጣ ያለ አጠቃቀም እናገኛለን። በቅርቡ በሚታተሙ አንዳንድ መጻሕፍት ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት ዐበይት አገባቦች ያለበር ከፋች ገብተው ተገኝተዋል። እንዲህ ዓይነቱ አጠቃቀም በየትኛውም ቤተ ጉባኤ አይታወቅም።

በዋነኛነት የዋድላን አገባብ መሠረት አድርገን፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የአበው ትምህርት ምርኩዝ አድርገን፣ በዋቢነትም የአለቃ ታየንና የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን አገባቦች ደጋፊ አድርገን በመነሣት፣ አገባብ በሰባት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፣ እነርሱም፣

፩. ዐቢይ አገባብ ፭ ተረፈ ንዑስ አገባብ
፪. ደቂቅ አገባብ ፮ የሰምና ወቅር አጠቃቀም
፫ ደቂቅ ርባታ ፯ አንገዝ ናቸው።
፬ ንዑስ አገባብ

ዐቢይ አገባብ ሆነው ንዑስን ወይም ደቂቅ አገባብን የሚደርቡም አሉ። ዝርዝሩ ወደፊት ይቀርባል። በአጻጻፍ ከዐቢይ አገባብ ቀጥሎ ንዑስ አገባብን የሚያስከትሉና ደቂቅ አገባብን መጨረሻ የሚያደርጉ አሉ። የቅደም ተከተል ጉዳይ ስለሆነ የሚያመጣው ችግር ባይኖርም በዚህ መጽሐፍ ደቂቅ አገባብ የቀደመበት ምክንያት ዐቢይ አገባብና ደቂቅ አገባብ የሚወራረሷቸው አገባባት ስላሉ ሐሳቡን ተያያዥ ለማድረግ ነው።

እያንዳንዱን አገባብ በዝርዝር ከማየታችን በፊት መራሕያንን በቅድሚያ አብራርቶ መግባት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሁሉም አገባባት በሚነገሩበትና በሚዘረዝሩበት ጊዜ መራሕያንን መጠቀማቸው የግድ ነው። እነሱን በቅድሚያ ሳያብራሩ መግባት መደነጋገርን ሊፈጥር ይችላል።

መራሕያን

መራሕያን መርሐ መራ ከሚለው ግስ የተገኘ የብዙ ወንዶች ሣልስ ቅጽል ሲሆን መሪዎች የሚለውን ትርጉም ይይዛል። እነዚህም በቅኔ ቤተ ጉባኤ አጻፋና አጻፋ ቅጽል ይባላሉ። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ /፷፻፷/ ለእነዚህ መራሕያን “ተውላጠ ስም” የሚል ስም ሰጥተዋቸዋል። ትክክልም ነው። በግእዝ ሥርዐተ ሰዋስው መራሕያን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። የቅርብና የሩቅ፣ የአንድና የብዙ፣ የሴትና የወንድ ዐረፍተ ነገሮችን የሚያስለዩን መራሕያን ናቸው። አንድ ቃል ወይም አገባብ ሲዘረዝር መሠረት የሚያደርገውም መራሕያንን ነው። ዐይነ ሥውርን አንድ ሰው ከፊት ሆኖ እንደሚመራው ሁሉ አናቅጽን ከፊት ሆነው የሚመሯቸው መራሕያን ናቸው። መራሕያን በአብነት ትምህርት ቤት ቅደም ተከተል መሠረት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩	ውእቱ	እሱ፣ ያ፣ ያው፣
፪	አንተ	አንተ፣ በቁም
፫	ውእቶሙ	እነሱ፣እኒያ /ለወንዶች/
፬	አንትሙ	እናንተ /ለወንዶች/
፭	ይእቲ	እሷ፣ ያች፣ ያችው
፮	አንቲ	አንቺ
፯	ውእቶን	እነሱ፣ እኒያ፣ እኒያው /ለሴቶች/
፰	አንትን	እናንተ /ለሴቶች/
፱	አነ	እኔ
፲	ንሕነ	እኛ ናቸው።

የቀድሞ አባቶቻችን የአረባብ ቅደም ተከተል ደግሞ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

፩	ውእቱ	፯	ይእቲ
፪	አንተ	፰	አንቲ
፫	አነ	፱	አነ

ዉእቶሙ ፤ ውእቶን

ንሕነ ፤፪ ንሕነ ናቸው።።

በሁለተኛው ቅደም ተከተል መሠረት ቁጥራቸው ፤፪ ሲሆን በመጀመሪያው አካሄድ ግን ቁጥራቸው ፤ ነው።። በአገባብ አካሄድ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ በ፤፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በ፤፪ ይዘረዝራሉ የሚባልበት ምክንያትም መነሻው ይህ ነው።። ቁጥራቸው ከ፤ ወደ ፤፪ ያደገበት ምክንያት ወንዶችም ሴቶችን አነ፣ ንሕነ ስለሚሉ ነው።።

በዘመናዊ ትምህርት ደግሞ ቅደም ተከተላቸው ከዚህ እደሚከተለው ነው።።

አነ ፪ አንትን

ንሕነ ፫ ውእቱ

አንተ ፮ ውእቶሙ

አንቲ ፬ ይእቲ

አንትሙ ፤ ውእቶን

እነዚህ መራሕያን እንደገና በሦስት ወገን ይከፈላሉ፣ ሀ. በያታ / ሴትና ወንድ/ ለ. በአንድና በብዙ፣ ሐ፡ በቅርብና በሩቅ፣

በያታ ሲመደቡ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣

<u>ተባዕታይ መደብ</u>	<u>አንስታይ መደብ</u>
አንተ	አንቲ
አንትሙ	አንትን
ውእቱ	ይእቲ
ውእቶሙ	ውእቶን

አነ እና ንሕነ ለሁለቱም ያታዎች ይሆናሉ።። ወንድም ሆነ ሴት አነ፣ ንሕነ የማይል የለምና።። እንደዚሁም ብዙ ወንዶችና ብዙ ሴቶች በቅርብ ንሕነ ብለው ራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ።።

በአንድ ቁጥርና በብዙ ቁጥር /በነጠላና በብዙ ቁጥር/ ሲመደቡ፣

ነጠላ ቁጥር	ብዙ ቁጥር
አነ	ንሕነ
አንተ	አንትሙ
አንቲ	አንትን
ውእቱ	ውእቶሙ
ይእቲ	ውእቶን

በቅርብና በሩቅ መደብ ሲመደቡ የሚከተለውን ይመስላሉ፣

ቅርብ	ሩቅ
አነ	ውእቱ
ንሕነ	ይእቲ
አንተ	ውእቶሙ
አንቲ	ውእቶን
እንትሙ	አንትን ናቸው፡፡

በዘመናዊ ትምህርት አከፋፈል መራሕያንን በሦስት መደቦች መክፈል ይቻላል፡፡

እነርሱም፣

ቀዳማይ	ካልኣይ	ሣልሳይ
አነ	አንተ	ውእቱ
ንሕነ	አንቲ	ይእቲ
	አንትሙ	ውእቶሙ
	አንትን	ውእቶን

መራሕያን የስም ለውጥ /ተለዋጭ/ ወይም የስም ምትክ ሆነውም ያገለግላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ተውላጠ ስም ይባላሉ፡፡ እንደዚሁም ዐፃፋ ቅጽል ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ይህም ማለት ስም ሲጠራ ቅጽል፣ ስም ሳይጠራ ዐፃፋ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ዝርዝር አጠቃቀማቸው በደቂቅ አገባብ ውስጥ ተገልጿል፡፡

ከዐሥሩ መራሕያን ስድስቱ ማለትም አንተ፣ አንትሙ፣ አንቲ፣ አንትን፣ አነ፣ ንሕነ ተለይተው ለግዑዝ ዖታ በቅጽልነትም ሆነ በዐፃፋነት አያገለግሉም፡፡ ግዑዝ ዖታ የሚባሉትም ኢነባብያን የሆኑ ፍጥረታት ሲሆኑ እንደ ድንጋይ፣ እንጨት፣ እንስሳት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

ሦስቱ አገባባት በዋነኛነት አንዱ ከሌላው በምን እንደሚለይ በቅድሚያ ማብራራት ለግንዛቤ ይረዳል፡፡ ስለዚህ፣

፩÷ የዐቢይ አገባብ ዋና መገለጫ፣ በነባርና በዘማች አናቅጽ ላይ እየወደቀ ማሠሪያን ማስቀረት ሲሆን በዐበይት አናቅጽ ላይ ሁሉ ይወድቃል፡፡

፪÷ የደቂቅ አገባብ ዋና መገለጫ፣ ሲዘረዝር በባዕድ መዘርዘሩ ሲሆን ሌላው በሁሉም ዓይነት ስሞችና በብትን ሰዋስው እየገባ ማድረጊያ፣ አቀባይ፣ መነሻ፣ መገስገሻ፣ መድረሻ፣ ተሳቢ፣ አንጻር፣ ተወዳዳሪ፣ ተፎካካሪ፣ አዘውታሪ፣ ወዘተ መሆኑ ነው፡፡

፫÷ የንዑስ አገባብ ዋና መገለጫ፣ ከስም ማለትም ከሰው ስም፣ ከቦታ ስም፣ ከጊዜ ስም፣ ከብትን ሰዋስው ስም፣ ከነገር ስም በፊት እየገባ ቅጽል መሆኑ፣ እንዲሁም ከአንቀጽ ጋር ሲነገር አንቀጽ አጎላማሽ መሆኑ ነው፡፡ ሌሎች ዝርዝር መግለጫዎች በያንዳንዳቸው መግቢያ ላይ ተገልጸዋል፡፡

፷.፩. <u>ዐቢይ አገባብ</u>

ከሰባቱ አገባባት መካከል አንዱና የመጀመሪያው ዐቢይ አገባብ ነው፡፡ ዐቢይ ማለት ታላቅ ወይም ዋና ማለት ሲሆን ከሦስቱ አገባቦች ታላቅ ሚና የሚጫወተው ዐቢይ አገባብ ነው፡፡ ዐቢይ የተባለበት ምክያትም፣

፩÷ በነባር አንቀጽ፣ በዘማች አንቀጽ ማለትም በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ፣ በዘንድ /አውታር በጣሽ ይዞ/ በጽድቅ በአለታ፣ ማሰሪያነትን የሚያስለቅቅ ስለሆነ ነው፡፡

፪፥ በንዑሳን አናቅጽ /ከቦዝ አንቀጽ በስተቀር/ በተጨማሪም በባሕርይ ስም፣ በተጸውዖ ስም፣ ማለትም በሰው ስም፣ በሀገር ስም፣ በተቀብዖ ስም፣ በግብር ስም፣ በብትን ሰዋስው፣ ሁሉ እየገባ አንቀጽ በቅርቡ ካለ በቅርቡ ያለው አንቀጽ፣ አንቀጹ እሩቅ ከሆነ ደግሞ እሩቅ ዘምቶ እሩቅ ያለውን አንቀጽ ከማሰሪያነት ስለሚያስለቅቅ፡

፫፥ ዐበይት አገባባት በደቂቅ አገባባት ላይ የሚገቡ ወይም የሚወድቁ ከመሆናቸውም በላይ ዘን በር ከፋች ይዘው ከሚነገሩ አገባባት በስተቀር እርስ በእርሳቸው ተደራርበው ይነገራሉ፡፡ ዘን በር ከፋች ይዘው የሚነገሩ አገባባት እነርሱ በአገባበብ ላይ የመጫን ዐቅም የላቸውም፡፡ ሌላው ዐቢይ አገባብ ግን በእነርሱ ላይ የመጫን ዐቅም አለው፡፡ ሲደራረቡም ለማሳያ ያህል ከብረ ኢያሱ በ፡ነበ እስራኤል እስመ ከመ ከመ ሙሴ ከፊለ ባሕረ ተዐውቀ፡፡ እንደሙሴ ባሕርን እንደከፈለ ታውቋልና ኢያሱ ከበረ፡፡ ሀለዉ እደው ነቢያት እለ ኢጥዕምዎ ለሞት እስከ እስከ አመ ይመጽእ ክርስቶስ ይመውቱ ይላል፡፡

ዐቢይ አገባብ እንደ የጉባኤ ቤቱ የተለያየ ቢሆንም በአብዛኛው ተቀባይነት ያለው የዋድላ አገባብ ነው፡፡ ዐቢይ አገባብ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዐበይት አናቅጽ /ቀዳማይ፣ ካልዓይ፣ ዘንድ/ ላይ ሲገባ ያለ በር ከፋችም በበር ከፋችም የሚገባበት ስልት አለው፡፡ ለምሳሌ በእንተ፣ በይነ፣ እንበይነ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ ተውላጠ፣ ዐስበ፣ ያለ በር ከፋች በአንቀጽ ላይ አይወድቁም፡፡ ስለዚህ የዐቢይ አገባብ ዋና መለያ ባሕርዩ ከአንቀጽ ላይ እየወደቀ አንቀጹ እንዳያሥር ማስቀረት መቻሉ ነው፡፡

የአለቃ ታየን /ዋሸራ በአለቃ ታየ ውስጥ ተካቷል/፣ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን፣ የዋድላንና የጎንጅን ዐቢይ አገባብ በማጠቃለል በ፷ አርእስት እና በ፱፬ ዝርዝር ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ በመጽሐፍ ወይም በቅኔ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ አጠቃቀማቸው የተለያየ ነው፡፡ በጥቅል ሲታይ በጎላፊ በትንቢት እየገቡ ማሰሪያነትን የሚያስለቅቁ ቢሆንም በሌሎች አናቅጽም /በብትን ሰዋስው/ እየገቡና ዘምተው አንቀጽን እያስቀሩ አገግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ አለ፡፡ በአጠቃላይ ዐቢይ አገባብ የሚሆኑት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

እስመ አምጣነ አኮኑ በእንተ በይነ
ህየንተ እንበይነ ተውላጠ ፍዳ በቀለ ዐስበ
መጠነ ዐቅመ በዘ ኀበ መንገለ ወእደ
እንዘ ከመ ከመ ኀበ ኀበ ለለ እንበለ ሶበ
አመ ጊዜ እምዘ አርአያ አምሳለ
ሕገ እመ እስከ ዕለተ ዓመተ
መዋዕለ ዘ/እንተ/እለ አላ ዳዕሙ
ባሕቱ ዓዲ ድኅረ

ከላይ የተዘረዘሩት ፴ አገባባት በዐቢይ አገባብ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን በተጨማሪም ብሂል ዐቢይ አገባብ እንደሆነ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ላይ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በዋድላ አገባብ ንዑስ አገባብ እንጅ ዐቢይ አገባብ አይሆንም የሚል ክርክር አለ፡፡ ነገር ግን በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሐተታ መሠረት፣ እንደማንኛውም ዐቢይ አገባብ አንቀጽ ያስቀራል ብለው በዐቢይ አገባብ ውስጥ አካተውታል፡፡
በአለቃ ታየ አገባብ ውስጥ፣ ቤዛ፣ ተክለ፣ ዕሴተ፣ ዐይነ፣ እና ግእዝ ንባብ የዐቢይ አገባብ አካል ሆነው ተካተዋል፡፡ ነገር ግን አንቀጽ ላይ ወድቀው ማሠሪያነትን ስለማያስቀሩ መምህራን ከዐቢይ አገባብ

ውስጥ አያስገቧቸውም፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ደግሞ ዐስበ በዐቢይ አገባብ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ዐስበ ዘን በር ከፋች አድርጎ አንቀጽን ስለሚያስቀር በዚህ መጽሐፍ በዐቢይ አገባብ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በፕሮፌሰር ጌታቸው አዲስ መጽሐፍ /ግእዝ በቀላሉ፣ 2008፣ 123/ ሰዓ፣ ሰዓተ ከዐበይት አገባባት ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል፡፡ ነገር ግን በአንቀጽ ላይ ወድቀው ማሠሪያነትን ሲያስለቅቁ ስለማይገኙ በዚህ መጽሐፍ አልተካተቱም፡፡ ከላይ ከተገለጹት ከ፴፩ዱ አገባባት ውስጥ ደቂቅን የሚደርቡ አሉ፡፡ እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

በእንተ	ህየንተ	በይነ	ተውላጠ	
ፍዳ	ዐስበ	ጎበ	መንገለ	ወእደ
መጠነ	አምጣነ	ዐቅመ	ከመ	ሕገ
አርአያ	አምሳለ	አመ	ሶበ	ጊዜ
ዓመተ	መዋዕለ	እስከ	ለለ	እንተ
እስከ	ድኅረ	እለ	እንበለ	ዘ

እነዚህ ፴፱ አገባባት ደቂቅን መደረባቸው ወይም በሰዋስው ሁሉ መግባታቸው ዐቢይ አገባብነታቸውን አያስቀረውም፡፡ ሆኖም በተነገሩበት ዐረፍተ ነገር በሰዋስው ላይ ወድቀው ከተገኙ ደቂቅ አገባብ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መሠረት ከላይ የተዘረዘሩት አገባባት ዐቢይ ወይም ደቂቅ አገባብ ናቸው ብሎ መወሰን የሚቻለው የገቡበትን ዐረፍተ ነገር መርምሮ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በሰዋስው ላይ ወድቀው ከገቡበት ሰዋስው ቀጥሎ የሚመጣውን አንቀጽ ያስቀራሉ፡፡ ነገር ግን በሰዋስው ላይ ከወደቁ አልፈው አንቀጽ ማስቀረት አይችሉም የሚል የአበው ትምህርትም አለ፡፡ ባለቅኔዎች ደግሞ ይህን ሳይጠነቅቁ እነዚህን አገባባት በሰዋስው ላይ በመጫን ከሰዋስው በኋላ የሚመጣውን አንቀጽ ሲያስቀሩበት ይታያሉ፡፡ ከዚህም አለፍ ብሎ በሰዋስው ላይ ወድቀው በዘማችነት አንቀጽ ማስቀረት የሚችሉት

ሁሉም ሳይሆኑ እንደ እስመ፣ አኮኑ፣ ሶበ፣ እመ፣ የመሳሰሉት ብቻ ናቸው ብለው የሚከራከሩም እንዳሉ መገንዘብ ተገቢ ነው። ሁሉንም በየዘርፉ በአግባቡ ማየት የተሻለ ነው። ሶበ እና አምጣነ ደግሞ የተለየ ባሕርይ አላቸው። ስለዚህ በአፈታትና በሙያ አሰጣጥ ጊዜ አገባባቸውን አይቶ ዐቢይ ወይም ደቂቅ መሆናቸውን መወሰን ይቻላል። ከላይ ከተዘረዘሩት አገባባት ውስጥ እስመ፣ አኮኑ፣ እመ፣ አላ፣ ዳዕሙ፣ ወእደ፣ እንዘ፣ ባሕቱ አይዘረዝሩም። ሌሎቹ ግን ጥሬና ነባር ስለሆኑ በደቂቅነታቸው በ፲ በ፲ መደብ ይዘረዝራሉ። እስመ፣ አላ፣ ዳእሙ፣ባሕቱ፣ እንበለ እና ዓዲ ደግሞ ከሌሎቹ ተለይው በተጨማሪ ንዑስ አገባብ ይሆናሉ።
የዐበይት አገባባት ዝርዝር አጠቃቀማቸው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

፩ ና የሚሆኑ አገባቦች

ና የሚል ትርጉም ያላቸው አገባቦች ፭ ሲሆኑ እነርሱም፣
ሀ. እስመ፣ ሐ አኮኑ መ. ዘማች አንቀጽ፣ ነባር አንቀጽ፤
ለ. አምጣነ፣ ሠ. ወ፣ ሰ ናቸው።
አምጣነና እስመ ይናበባሉ። ነጂ አገባባት ናቸው። ና ሲሆኑ በእነርሱ ላይ አገባብ ወይም ሌላ አይወድቅም እንጂ እነርሱ ግን በጎላፊ፣ በትንቢት፣ በዘንድ፣ በትእዛዝ እና በማንኛውም ሰዋስው ላይ ይወድቃሉ። አኮኑ ግን አይናበብም። ራሱን ችሎ ስለሚቆም መናበብ አያስፈልገውም። እስመ እና አምጣነ ከአንቀጽ በፊት ተነበው ወይም ገብተው ኃላፊና ትንቢት አናቅጽን እንዳያሥሩ ያስቀራሉ። በጎላፊ ሲገቡ፣

ነስሑ ወእመኑ እስመ ቀርበት ይእቲ መንግሥተ ሰማያት፣

አምጣነ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት፣
አኮኑ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ይላል።
በትንቢት በአሉታ ሲገቡ፣
ድልዋኒክሙ ንበሩ እስመ ኢተአምሩ ጊዜ
ይመጽእ ሐዳስ በዓለ ቤት፣
ሐዋርያት መሀሩ ወንጌለ እስመ ይኤዝዞሙ
ወልደ አምላክ፣ ይላል።
አኮኑ ከፊት ተነግሮ የኋላውን፣ በኋላ ተነግሮ የፊቱን አንቀጽ ያስቀራል። በዚህ መሠረት ከአንቀጽ በፊትና ከአንቀጽ በኋላ እየገባ ማሠሪያነትን ያስለቅቃል። ነጂ ተነጂ አገባብ ነው። ሦስቱም አገባባት በኃላፊና በትንቢት አናቅጽ ብቻ ሳይሆን በንዑሳን አናቅጽ፣ በቅጽል፣ በቦታ፣ በስም፣ በግብር፣ በዐቢይ አገባብ፣ በደቂቅ አገባብ እየገቡ ያገለግላሉ። በአሉታና በአወንታ፣ በወንድና በሴት፣ በሩቅና በቅርብ፣ በአንድና በብዙ ይገባሉ። በዘማች አንቀጽ፣ በነባር አንቀጽ ሲገቡ በፅንዕ ይፈታሉ። በንዑስ አንቀጽ እየገቡ በነባር አንቀጽ ይፈታሉ። በጽድቅ እየገቡ በአሉታ ያሣሥራሉ። በአሉታ እየገቡ በጽድቅ ያሣሥራሉ። በፊት ሆነው የኋላውን፣ በኋላ ሆነው የፊቱን ያስረዳሉ። በትእዛዝ ሲያስረዱ ግን ጽድቅና አሉታ ብሎ አያስጠነቅቅም። ሲገባም፣
ኢያምሠጠ አዳም እምኵነኔሁ ለእግዚአብሔር።
አስመ በልዐ፣ አምጣነ በልዐ፣ አኮኑ በልዐ በለሰ ዘኢአዘዞ ይብልያ ይላል። በጽድቅ ገብቶ በአሉታ ሲያሣሥር ነው።
እስመ ኢአቀበ፣ አምጣነ ኢአቀበ፣ አኮኑ ኢአቀበ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ይላል። ተወክፈ አዳም በድልወት ፍትሐ ሞተ ሥጋ ወነፍስ ሲል በአሉታ ገብቶ በጽድቅ ሲያሣሥር ነው።
በካልአይም ሲገባ ሰማዕት ኢይፈርሀ ሞተ ሥጋ አስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ ይሬእይዋ በዐይነ ተስፋ ለመንግሥተ ሰማይ ይላል።

በነባር አንቀጽ ሲገቡ እስመ አኮ፣ አምላነ አኮ፣ አኮኑ አኮ ዛቲ ዓለም ዘትነር ለዓለም ይሬእይዋ ጻድቃን ከመ እዳው ይላል፡፡ ውሉደ እግዚአብሔር በእንተ ክርስቶስ ይትዔገሡ መከራ እስመ፣ አምላ፣ አኮኑ ውእቱ አርአያሆሙ ለዛቲ ትዕግሥት ዝንቱ ክርስቶስ በማለት ያሳያል፡፡
በነባር አንቀጽ ካልአይ ሲገቡ ብፁዓን ጻድቃን እስመ፣ አምጠነ፣ አኮኑ እሙንቱ ዘይቀውሙ በየማነ ክርስቶስ፡፡
ጻድቃን ይብልዎ ለክርስቶስ ፡ኄር ውእቱ አኮኑ ከመ ይኩን፣ እስመ፣ አምላነ ከመ ይኩን ዝ መከራ ሕይወተ ነፍሳቲሆሙ በል፡፡
በቅኔ ሙያ አሰላጥ አስረጅ ይባላሉ፡፡ ከማሠሪያ አንቀጽ በኋላ አስረጅ ሆነው ስለሚገቡ የቅኔ ማስጀመሪያ አይሆኑም፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት ግን ቅኔ ሊያስጀምሩ ይችላሉ ብለው ይከራከራሉ፡፡ ለምሳሌ በአማርኛ እገሌ ሞቷልና አቃብሩን ተብላችኋል የሚለው ማኅበራዊ፣ ባህላዊ አነጋገር እንዳለ ሆኖ በመጻሕፍትም “እስመ ብዙኃን እለ ወጠኑ ይንግሩ ወይምህሩ በእንተ ግብር ዘአምኑ በላዕሌነ በከመ መህሩነ እለቀደሙን ርእዮቶ በመትልው እጽሕፍ ለከ ኦ ታዎፊላ” የሚለው የዐረፍተ ነገር መጀመሪያ ነው፡፡ በዚህ መሠረት አስረጅ የቅኔ መጀመሪያ የማይሆነው ስለአልተለመደ እንጂ ሌላ ችግር የለውም፡፡ ለማንኛውም አብዛኛዎቹ መምህራን ስለአልተቀበሉት አስረጅ ቅኔ አያስጀምርም፡፡
በዘንድ ሲነገሩ እንበለ፣ ቅድመ፣ ከመ፣ አውታር በጣሽ ይሆኑላቸዋል፡፡ ለምሳሌ እስመ እንበለ ይብላዕ፣ እስመ ከመ ይብላዕ፣ እስመ ቅድመ ይብላዕ መጽአ ይላል፡፡ ያለ አውታር በጣሽ ሲነገሩ አውታር ጸያፍ ወይም ወልቃማ ይባላል፡፡
ሁሉም ዐበይት አገባባትና ደቂቅ አገባባት በቦዝ ላይ አይወድቁም፡፡

ሰ ተለይቶ በ፮ ግሶች ሣልሳይ አንቀጽ ይነገራል። ግሶችም ጸንሐ፣ ተርፈ፣ ተነድገ፣ ተዘንግዐ፣ ተረስዐ ናቸው። በአለታ የሆነ እንደሆነ ኢተሐለየ፣ ኢተጽሕቀ፣ ኢተዘከረ፣ ኢያስተሐመመ፣ ኮነ፣ ረሰየ ናቸው።

የኮነና የረሰየ ተሳቢዎች ሐሰት፣ ሕሳቄ፣ ሕብል፣ ዛውዕ፣ ተውኔት፣ ሰሐቅ፣ ስላት፣ ሥላቅ ናቸው። ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ፣ ስንኳን ሲሆኑ በ፪ኛ ማሠሪያ ሰ፣ ስ ሲሆን ይቀድሟቸዋል። ማሠሪያዎቻቸውም ኢ፣ አኮ፣ አልቦ፣ ናቸው። ሲገባም ገብረ ሕይወት ኢበልዐ እክለ አምላነ ምድራዊ መልአክ ውእቱ፣ ይጽናሕሰ፣ ይትርፍሰ፣ ነገረ ዝንቱ ኢጠበወ ጥበ እሙ፣ ወጥበ እሙ፣ ጥበ እሙሂ፣ ጥበ እሙኒ፣ ኢጠበወ፣ ይላል።

በአኮ ሲገባ አኮ መልአክ ገብረ ሕይወት እስመ ሞተ በሥጋሁ፣ ኢይትሐለይሰ፣ ኢይጸሐቅሰ፣ ኢይዘከርሰ፣ ኢያስተሐምምሰ ነገረ ዝንቱ ኀበ መቃበርሂ ወረደ ይላል። በአልቦ ሲገባ አልቦ ንጹሕ እምኃጢአት እስመ ጴጥሮስ ሥልሰ ክሕዶ ለወልድ ሶበ ለብሰ ሥጋ ሰብእ፣ ይኩንሰ፣ ይትረሰይሰ፣ ሐሰተ፣ ሕሳቄ፣ ሕብለ፣ ዛውዐ፣ ተውኔተ፣ ሰሐቀ፣ ስላቀ፣ ስላተ ነገረ ዝንቱ ሰማይኒ ኢኮነ ንጹሐ በቅድሜሁ ማለቱን ያሳያል። መምህራን ግን እንዳገኙ ያገቡታል። ኢበልዐ እክለ ገብረ ሕይወት አምላነ ምድራዊ መልአክ ውእቱ፣ ይትርፍሰ ነገረ ዝንቱ ኢነበረ ምስለ አቡሁ ወእሙ ይላል።

ወ ተለይቶ በሁለት ማሠሪያ የሚያሥረውን በ፩ ማሠሪያ፣ በ፪ አንቀጽ የሚያሥረውን በ፩ አንቀጽ ያሣሥራል። ማሠሪያና አንቀጽ አንድ አይደሉም። ስለምን ቢሉ፣ ሁለት ማሠሪያ፣ ሁለት አነቀጽ ቢሉ፣ ማሠሪያው አንቀጽ፣ አንቀጹ ማሠሪያ ይባላል ሲል ነው። አንድና ብዙ፣ ሴትና ወንድ፣ ሩቅና ቅርብ አንድ ያደርጋል። አንድ የሆነውም በምሳሌ ጊዜ ሰም ሆኖ ከወርቅ፣ ወርቅ ሆኖ ከሰም አይመሰልም፣ አይዛረፍም፣ አይናበብም። ቅጽል አያተርፍም።

ማሠሪያውን አንድ ሲያደርግ ሚካኤል መጽአ ወገብርኤል ወረደ የሚለውን ሚካኤል ወገብርኤል መጽኡ፣ ሚካኤል ወገብርኤል ወረዱ ይላል፡፡ አንድና ብዙ አንድ ሲያደርግ አምላክ ወፈያት ተሰቅሉ ይላል፡፡

ሴትና ወንድ አንድ ሲያደርግ /ሲያጫፈር/ አዳም ወሔዋን ተፈጥሩ ይላል፡፡ ሴት ቀድማ ወንድ ሲከተል ሐና ወኢያቄም ወለዱ ማርያምሀ ይላል፡፡ ወለዳ ማርያምሀ ቢል ግዕዛን ጸያፍ ይባላል፡፡ እሷ ተፈጥራ እሱ ተፈጠረ ማለት ነውና፡፡ ዳግመኛም እሱ ከእሷ ተገኘ ማለት ነው፡፡ ሐና ወኢያቄም ወለዳ ማርያምሀ ቢል ግን በቀና ነበር፡፡ እመቤታችን ከእነሱ ተገኝታ ጌታን አስገኝታለችና፡፡ ነገር ግን መጻሕፈትም መምህራንም ተባብረው ሴት ቀድማ ወንድ ሲከተል አንቀጽ በሴት አይነገርም ብለው ስለዐወጁ እንጅ፡፡

ወ በማሰሪያ አንቀጽ ብቻ የሚቀር ሳይሆን በዝርዝሮች ማለትም በደቂቅ አገባብ ዝርዝር፣ በዘርፍ ተቀባይ ዝርዝር እና በቅጽል ጊዜም ሴትና ወንድ በሚጫፈሩበት ጊዜ ሴት ቀድማ ወንድ ቢከተል ዝርዝሩም ቅጽሉም ወንድን እንጂ ሴትን አይመለከትም፡፡ ሲገባም ደቂቅ አገባብ ማርታ ወአልዓዛር ሰላም ለክሙ ይላል እንጂ ሰላም ለክን አይልም፡፡ አቅራቢ ሲሆን፣ ሐረ ኢየሱስ ኀቤሆሙ ለማርታ ወለአልዓዛር ይላል እንጂ ኀቤሆን አይልም፡፡ በዘርፍ ተቀባይ ጊዜም ሐረ ኢየሱስ ኀበ ቤቶሙ ለማርታ ወለአልዓዘር ይላል እንጂ ኀበ ቤቶን አይልም፡፡

ሴቶችና ወንዶች አብረው ባሉበት ጊዜም ሰላም ለኩልክሙ አንስት ወእደው ይላል እንጂ ሰላም ለክን አይልም፡፡ በቅጽል ጊዜም ሰላም ለክሙ አንስት ወእደው ክቡራን ይላል እንጂ ክቡራት አይልም፡፡ በተጫማሪም ማርታ ወአልዓዛር ቅዱሳን ይላል እንጂ ቅዱሳት አይልም፡፡ ብእሲት ወብእሲ አሐዱ አካል

እሙንቱ ቢል እንጂ እማንቱ አይልም። በተጨማሪም ሴት ቀድማ ወንድ ሲከተል አንቀጽ ለወንድ እንጂ ለሴት አይሆንም ማለት በወንድ የተነገረው አንቀጽ፣ የደቂቅ አገባብ ዝርዝር እና ቅጽል ሁሉ ለሴትም ይሆናል ማለት እንጂ የሴትን የተፈጥሮ መብት መንፈግ አለመሆኑ መታወቅ አለበት።

ሩቅና ቅርብ ሲገባ ጴጥሮስ አንተ ወአኀዊከ ሐዋርያት መሀርክሙ ወንጌለ፣ ሐዋርያት አንትሙ ወጴጥሮስ መሀርክሙ ወንጌለ ይላል። በምሳሌ ጊዜም አምላክ ወዳዊት አይመሰልም። አምላክ ወሰማይ ብሎ አይዛረፍም። ቅጽል አያተርፍም፡ ያለውም አዳም ወሔዋን ዘወጽኡ እምገነት አይልም። አዳም ዘወጽአ እምገነት ወሔዋን ዘወጽአት እምገነት ይላል እንጅ- የሚል ዐዋጅ በየአገባባቱ አለ። ነገር ግን ሰላም ለክሙ ሐና ወኢያቄም ዘወለድክምዋ ለማርያም፣ እሙንቱ ኪሩቤል ወሱራፌል እለአክናፊሆሙ ነበልባል ይላል። ቅጽል አያተርፍም ሲባልም በደቂቅ አገባብ ሲነገሩ ነው። ሲገባም ተሰብሐ እግዚአብሔር በሚካኤል ወበገብርኤል ሰባሕያን ቢል አያስኬድም። ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ሚካኤል ወገብርኤል ሰባሕያን ይላል እንጅ። ተሰብከ ዜና ልደቱ ለእግዚእነ በሙሴ ወበኢሳይያስ ነቢያት አይልም። ዜነውነ ዜና ሙሴ ወኢሳይያስ ነቢያት ይላል እንጅ። **<u>አስተውል</u>**፣

፩ኛ. ሰባሕያን ለሚካኤልና ለገብርኤል ወይም ሚካኤልና ገብርኤል ለሰባሕያን ቅጽል መሆኑን፣

፪ኛ. ነቢያት ለሙሴና ለኢሳይያስ ወይም ሙሴና ኢሳይያስ ለነቢያት ቅጽል መሆናቸውን አስተውል።

አገባብ በሰማይ ወምድር አይልም፡ ወበምድር ይላል እንጅ። በምሳሌ ጊዜ ግን ተጽዕነ እግዚእ በሰማይ ወበምድር አፍራሲሁ አይልም። ተጽዕነ በሰማይ ወምድር አፍራሲሁ ይላል እንጅ። ሙሴ ልደተ ቃል

እምድንግል ተፈነወ ለአዳም ወለሔዋን እስራኤል አይልም። ለአዳም ወሔዋን እስራኤል ይላል እንጅ። በዝርዝር ጊዜም አውዕኦሙ ለአዳም ወለሔዋን እስራኤል አይልም፣ ለአዳም ወሔዋን እስራኤል ይላል እንጅ። ጸያፍ የሚባልበት ምክንያት ደቂቅ አገባብ በወ ተጫፍሮ በመግባቱ ነው። ለምሳሌ በ እና ለ በሁለቱ ተጫፋሪዎች መካከል መግባታቸው ምሳሌውን ጸያፍ እንዳደረጉት መመልከት ተገቢ ነው።

ወ በሦስት ስም መካከል ተደርድሮ ሲገኝ የፊተኛው ወ፣ ና፣ የሁለተኛው ወ ም ተብሎ ይፈታል። ለዚህም ስም ይሰጣል። ዘርፍ ሲሆን፣ በወ እየተጫፈረ መከዳ ዘርፍ ይባላል። ተደራጊም በወ እየተጫፈረ መከዳ ተደራጊ ይባላል። ይህም ሲገባ፣ ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወያዕቆብ ላዕካኒሁ፣ ወለዮሐንስ ተላዊሁ ይላል እንጂ ነሥኦሙ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ፣ ወለዮሐንስ ላዕካኒሁ አይልም። ባለቤትም ቢሆን በወ እየተጫፈረ መከዳ ባለቤት ይባላል። ሲገባም ተጸውዑ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ ይላል። በሁለት ስም መካከል ሲገባ፣ በወ እየተጫፈረ መንታ ዘርፍ ይባላል። ይህም አምላክ ሰማይ ወምድር ማለቱን ያሳያል።

ወ እና ሰ ቁጥራቸው ከንዑስ አገባብ ነው። እዚህ የገቡት ና በሚለው ትርጉማቸው ነው።

፪ኛ. ስለ የሚሆኑ አገባባት

ስለ የሚል ትርጉም ያላቸው አገባባት በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ መሠረት ፲፰፣ በዋድላው ቤተ ጉባኤ አለቃ ቡሩኬ መሠረት ፲፰፣ በጌቱ ገሞራው አገባብ መሠረት ፲፩፣ በሳንጅ አገባብ መሠረት ፲ ናቸው። የአለቃ ታየ አገባብ በምስክር የበለጸገ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱን አገባብ ተራ በተራ በዝርዝር ስለሚያሳይ አቀራረቡ የተሻለ ነው። ከላይ

ለመግለጽ እንደተሞከረው የዐበይት አገባባት ዋና መለያ ባሕርይ በአንቀጽ ላይ ወድቀው ማሠሪያነትን ማስለቀቃቸው ሲሆን አንቀጽ ማስቀረት የማይችሉት ሁሉ ተጽፈው ስለተገኙ እንዲወጡና እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡ ለሁሉም አገባባት የጋራ የሆኑት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

፩ በእንተ ፮. እስመ
፪ እንበይነ ፯. በቀለ
፫ ህየንተ ፰. ፍዳ
፬ ተውላጠ ፱. ዐስበ

ስለ የሚሆኑ አገባባት በአንዱ አሥራ ስምንት በሌላው አሥራ አምስት፣ እንዲሁም ዐሥር እየተባሉ ቢገለጹም አንቀጽ ላይ ያለበር ከፋች ወይም በበር ከፋች እየወደቁ ማሠሪያነትን የሚያስቀሩ አገባባት አሥራ ሦስት ብቻ ናቸው፡፡ እነርሱም፤ በእንተ፣ ህየንተ፣ በይነ፣ እንበይነ፣ ፍዳ፣ ተውላጠ፣ ዐስበ፣ በቀለ፣ እስመ፣ መጠነ፣ አምጣነ፣ በዘ፣ ዐቅመ፣ ናቸው፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው፤ መጽሔተ አእምሮ በተባለው የአለቃ ታየ አገባብ ውስጥ ስለ የሚሆኑ ዐበይት አገባባት ተብለው የተገለጹት፣ ተክለ፣ ዓይነ፣ ዕሴተ እና ግእዝ ንባብ ደቂቅ አገባባት እንጂ ዐበይት አገባባት ተብለው በአብነት መምህራን አይወሰዱም፡፡ የየአገባባቱን ዝርዝር ስንመለከት ደግሞ፣ መጠነ፣ አምጣነ፣ ዐቅመ፣ በዘ፣ በጎንጅ አገባብ ውስጥ የሉም፡፡ በጌቴ ገሞራው አገባብ ደግሞ አምጣነ እና ዐቅመ የሉም፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ደግሞ ዐስበ አልተካተተም፡፡ በግእዝ ዐረፍተ ነገር እየገቡ ሲነገሩ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

ሀ. እስመ፣ መጠነ፣ አምጣነ፣ በዘ፣ በቀለ፣ ዐቅመ፣ በር ከፋች ሳይዙ በቀዳማይ አንቀጽ ይገባሉ፡፡ እንዲሁም በሰዋስው ሁሉ ያለበር ከፋች ይገባሉ፡፡

ለ. በይነ፣ እንበይነ፣ በእንተ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ ተውላጠ፣ ዘን በር ከፋች ይዘው በቀዳማይ አንቀጽ ይገባሉ፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ፣ እንበይነ፣ በእንተ፣ ሀየንተ ፈንታነትን ሳይለቁ፣ ፍዳ ብድራትን ሳይለቅ፣ ተውላጠ ለውጥነትን ሳይለቅ፣ በቀለ በቀልነቱን ሳይለቅ፣ ዐስበ ዋጋነቱን ሳይለቅ፣ እንደሚገቡ ማስተዋል ይበጃል።።
አገባባቱ ከላይ በተገለጸው መሠረት በዐረፍተ ነገር ሲገቡ ምን እንደሚመስሉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምስክሮች እንመልከት፣
በበር ከፋች ሲገቡ፣
፩ ዮም ንወድሳ ለማርያም በእንተ ዘተወልደ እምኔሃ እግዚአብሔር።።
፪ ሀየንተ ዘዐርገ ክርስቶስ ይመጽእ ዳግመ።።
፫ በይነ ዘተዋረደ አዳም ሞተ እግዚእ።።
፬ እንበይነ ዘተዘከረ ቴዎድሮስ ተቀንዎቶ ለኢየሱስ በቅንዋት ኀምስ ተቀነወ በቅንዋት
፭ ፍዳ ዘብዕለ ነዌ በብዕለ ሥጋ ውስተ ምድር ነደየ ውስተ ሰማይ።።
፮ ተውላጠ ዘበልዐ በለሰ አዳም ተኰነነ
፯. ዐስበ ዘተቀንየ ገብር ጊዮርጊስ ለእግዚኡ ረከበ ዐስበ መንግሥተ ሰማይ
ያለበር ከፋች ሲገቡ፣
፰ በፁዕ ዘይትቤቀለኪ በቀለ ተበቀልክነ።።
፱ እስመ በልዐ አዳም በለሰ ተሰቅለ አምላክ
፲ ከብረ ካህን መጠነ አእመረ ምሥጢረ።።
፲፩ ባዕል ከብረ መጠነ ገብረ/አምላነ ገብረ ትጉህ
፲፪ አዕረፈት ኢየሩሳሌም በዘ ነግሠ ዳዊት።።
፲፫ ዐቅመ ውስተ ልቡ ኀደረ ፍቅረ ቃል፡ ይላል።።
በእንተ በተጨማሪም ደስ አይበለው ብሎ አንዲሁም ደስ ይበለው ብሎ ይሆናል።። ደስ ይበለው ብሎ ሲሆን በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ተዘከር ኪዳነከ ይላል።። ደስ አይበለው ብሎ ሲሆን በእንተ ጸላእትየ አርትዕ ፍኖትየ ቅድሜከ እግዚኦ፣ በእንተ ዲያብሎስ መሐረነ ክርስቶስ ለሕዝብከ ይላል።። በእንተ ዲያብሎስ

መሐረነ የሚለው ምሥጢር ላደላደሉ ፍጹማን እንጅ ለሁሉም አይሆንም።።
ሁሉም ስለ የሚሆኑ አገባባት በ፫ አርእሰት፣ በፀሥሩ መራሕያን ይገባለ።። በ፫ አርእስት ማለትም ወንዶች፣ ሴቶች፣ አነ እና ንሕነ ናቸው።። በ፲ ሠራዊት በጽድቅ በአሉታ ይነገራሉ።። ለምሳሌ እስመ አእመረ፣ እስመ ኢያእመረ፣ እስመ አመርከ፣ እስመ ኢያእመርከ ብሎ እስመ አእመርነ፣ እስመ ኢያእመርነ እስከሚለው ይገባለ።። በተጨማሪም በንዑስ አንቀጽ አስነስተው በነባር በዘማች አንቀጽ ያሣሥራሉ።። ለምሳሌ በንዑስ አንቀጽ ሲያስሩ፣ ተወልዶቱ ለአምላክ እም ድንግል በይነ ዘመሐለ ለአዳም ይላል።። በዘማች አንቀጽ ሲያሣሥሩ ለነባሩ ፲፪ አገባባት ይስማሙታል።። አገባባቱም እስመ፣ እንዘ፣ ኀበ፣ ከመ፣ እመ፣ ሶበ፣ እምዘ፣ ድኅረ፣ እምከመ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው።/አለቃ ቡሩኬ/።። ለምሳሌ፣
፩ መዊቶቱ ለእግዚእነ እስመ እስመ በልዐ አዳም በለሰ ለሞቱ ስብሐት።።
፪ ይሴብሕዎ ኩሉ ፍጥረት ለወልድ አምጣነ አምጣነ ሞተ አዳም፡ሞቱ።።
፫ እፎ ይምሕል ሰብእ እንዘ በዘ መሐለ ለአዳም እግዚእ ሞቱ።።
፬ ይበክዩ ጻድቃን ኀበ በይነ ዘበልዐ አዳም በለሰ ተሰቅለሞቱ ለእግዚእነ ።።
፭ ዜነዉነ ሐዋርያት ከመ ህየንተ ዘበልዐ አዳም በለሰ ተሰቅለሞቱ ለወልድ ።።
፮ ተሰቅለሞቱ ለወልድ እምከመ ፍዳ ዘበልዐ አዳም በለሰ ትበኪ ወላዲቱ ይላል።።
ሶበ፡ ከእመ እና ከእምዘ፣ ድኅረ ከእምከመ ይደረባለ።። ይህም ማለት የሶበ፣ የእመ፣ እና የእምዘ አገባብ አንድ ዓይነት ሲሆን የድኅረ እና የእምከመ አገባብም ተመሳሳይ ነው ማለት ነው።። የሚከተለውን እንመልከት፣

፩ ተሰቅሎቱ ለወልድ ድኅረ ተውላጠ ዘተኮነነ አዳም ንዘክር ሞቶ በትንሣኤሁ፡
፪ ከብረ እግዚእነ ዘ መጠነ መሐለ ለአዳም ሞቱ፣
፫ ተኮነኑ አዳም ወሔዋን እለ ፍዳ ዘበልዑ በለሰ መዊቶቶሙ
፬ መዊቶቱ ለእግዚእ እስመ በልዐ አዳም በለሰ /በነባር ሲያሣሥር ነው/
በጌቱ ገሞራው አገባብ መሠረት ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩት ተደራቢ አገባባት /ከኋላ ተደርበው የሚገቡ/ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ እንዘ፣ ወእደ፣ መንገለ፣ ከመ፣ አመ፣ ሶበ፣ እመ፣ እምዘ፣ እምከመ፣ ድኅረ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው፡፡ በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ እና በጎንጅ አገባቦች እነዚህ የኋላ ተደራቢ አገባቦች አይገኙም፡፡ ስለ በአሉታ ጊዜ ስላ ይሆናል፡፡ ስለ የሚሆኑ አናቅጽ በጠቅላላው ሙያቸው ማንጸሪያ ነው፡፡

፫ኛ. ዘንድ የሚሆኑ

ዘንድ የሚሆኑ አገባባት ሦስት ሲሆኑ እነርሱም ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ /ውእደ/ ናቸው፡፡ በትርፍ አማርኛ ከ፣ ካ ይሆናሉ፡፡ ሙያቸው ማንጸሪያ ነው፡፡ አገባባቸው ከዚህ እደሚከተለው ነው፤
ሦስቱም አገባባት በቀዳማይ አንቀጽ፣ እየገቡ ይነገራሉ፡፡ በተጨማሪም በንዑስ አንቀጽ አስነስተው በነባር ያሣሥራሉ፡፡ ከዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፤
፩ ኀበ ወረደ ማይ ይቀድሕዎ
፪ መንገለ ፈረየ ሮማን ይቀስምዎ፡፡
፫ ወእደ ተናገረ ገብርኤል እንዘ ይብል ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ፣ ተወልደ አምላክ፡፡
በተጨማሪም

፩ ተለዐለ ገብር እስመ ተፈቅሮቱ ኀበ ተበውሐ በኀበ እግዚኡ።።
፪ ተጽሕፈ ኵሉ ሕዝብ ኀበ ወጽኡ ትእዛዝ እምኀበ አውግስጦስ ቄሳር።።
፫ ሰበከ ላቲ ዜና ለማርያም ገብርኤል መልአክ ኀበ ተፈነወ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አሐቲ ሀገር ዘገሊላ።።
፬ ይትፈሣሕ አብ ኀበ ወጽኡ እምኀቤሁ ወልዱ /ሲዘረዝር ነው/
በተጨማሪም፣
፭ መንግለ አሥመሮ ለእግዚአብሔር ሄኖክ ፈለሰ እምዝ ዓለም ወዐርገ ውስተ ሰማይ ምስለ ሥጋሁ።።
፮ መንግለ ተናገረ ኢዮብ አውስአ በልዳዶስ
፫ አዝነመ ዝናመ ኤልያስ መንግለ አዘዞ አምላክ ።።
፬ መንግለ ዜነወ፣ መንግለ ዜነውከ፣ መንግለ ዜነውነ፣ መንግለ ዜነውክሙ/ሲዘረዝር/።።
የወእደ አገባብ ከመንግለ ጋር ተመሳሳይ ነው።።
ለምሳሌ ገብር ይትቀነይ ወእደ በልዐ ንዋየ እግዚኡ ይላል።።
ለመንግለና ወእደ ስድስት አገባባት መነሻ፣ መግስገሻና መድረሻ እየሆኑ ይስማሟቸዋል። እነርሱም እም፣ እንተ፣ ውስተ፣ እስከ ለ፣ በ ናቸው። በአረፍተ ነገር ሲገለጹ፣
፩ ወእደ ወጽአ እም ሀገር
፪ መንግለ ሖረ፣ መንግለ ሀገር፣ ኀበ ሀገር፣ እንተ ሀገር፣ ውስተ ሀገር፣ ለሀገር፣ በሀገር፣ እስከ ሀገር ይላል።።
፫ ወእደ ገብረ ሰሎሞን ጥበበ በእዴሁ ተዐውቀ፣
፬ ጳውሎስ መሀረ ወንጌለ ኀበ በጽሐ እስከ ደማስቆ ይላል።።
በተጨማሪም ኀበ፣ መንግለ፣ ወእደ በዘማች አንቀጽ በነባር አንቀጽ በኀላፊ በትንቢት እየገቡ የ ይሆናሉ።። በምሥጢር የቦታ አገባባት ናቸው።። የበን ዝርዝር ይዘው ይፈታሉ።። ሲገቡም፣

ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ፣
ኀበሂ አመስጥ አልብየ በምድረ በድው ኀበ አልቦ ዕፅ ወማይ ፣
ኀበ አልቦ ደዌ ወአልቦ ሕማም፣
ናከብር መካነ ወእደ ተሰቅለ እግዚእነ፣
ሐሩ ሐዋርያት ኀበ ኀበ ተሰቅለ እግዚኦሙ.

በካልኣይ ሲገባ ቅዱስ ውእቱ መካን ወእደ ይትገበር መስዋዕተ ቅዳሴ ይላል፡፡ ዘን፣ እንተን፣ እለን ይዘረዝራሉ፡፡ ቅጽልም በቂም ይሆናሉ፡፡

፬ኛ. ወደ ፣ ወዳ የሚሆኑ አገባቦች

ወደ ወይም በአለታ ጊዜ ወዳ የሚሆኑ አገባቦች በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ መሠረት ፲፪ ሲሆኑ እነርሱም ኀበ፣ መንገለ፣ እንተ ውስተ፣ ለ፣ ዘ፣ እም፣ ግእዝ፣ ራብእ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ፣ ተናባቢ ቀለማት ናቸው፡፡ በዋድላ አገባብ መሠረት /አለቃ ቡሩኬና ጌቱ ገሞራው / ደግሞ ፲ ናቸው፡፡ እም እና ተናባቢ ቀለም የሉም፡፡ በጎንጅ አገባብ ደግሞ ራብእ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ፣ ተናባቢ ቀለማትና እም አይገኙም፡፡ ጎንጅ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ዲበን አስገብቷል፡፡ ከተዘረዘሩት አገባባት መካከል፣ ውስተ፣ ለ፣ ዲበ፣ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ፣ ተናባቢ ቀለማት በአንቀጽ ላይ እየወደቁ ማሠሪያነትን ስለማያስለቅቁ ዐቢይ አገባብ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ወደ የሚለውን ትርጉም ይዘው ደቂቅ አገባብ መሆን ግን ይችላሉ፡፡ ዝርዝር አገባባቸው በደቂቅ አገባብ ተገልጿል፡፡ በዚህ መሠረት ወደ ወይም ወዳ የሚሆኑ ዐበይት አገባባት፣ ኀበ፣ መንገለ፣ ብቻ ናቸው፡፡ በጎላፊ በትንቢት ይገባሉ፡፡ ምሥጢራቸው ቦታ ነው፡፡ ለምሳሌ፣

፩ ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ፣
፪ ሰሎሜ ሐረት መንገለ ሐረት ማርያም

፫ ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ ፈለሰት
እምዘይበሊ ኀበ ኢይበሊ

፭ኛ. እየ፣ እያ የሚሆኑ አገባቦች፣

እየ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ እያ የሚሆኑ አገባባት ስድስት ሲሆኑ እነርሱም ለለ፣ እንዘ፣ እንተ፣ ኀበ ኀበ፣ ከመ ከመ፣ አምጣነ ናቸው። ሙያቸው ማንጸሪያ ነው። በአለቃ ቡሩኬ፣ በሳንጅም ሆነ በአለቃ ታየ አገባቦች በበ እና ዘዘ ዐቢይ አገባብ ተብለው ተገልጸዋል። ሆኖም የሁለቱም አገባባት ባሕርይ የደቂቅ አገባብ ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልተካተቱም። እንተ በቀዳማይ፣ እንዘ እና ከመ ከመ፣ ኀበ ኀበ በካልኣይ ይገባሉ። በሳንጅ አገባብ ኀበ ኀበ፣ ከመ ከመ እና አምጣነ አልተካተቱም።
ለለ በኀላፊና በትንቢት አናቅጽ ይገባል። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፤

፩ ለለ ጸብሐ ሌሊት ወለለ መስየ መዓልት
ተሰብሐ እግዚአብሔር በአፈ ኩሉ ፍጥረት
/በኀላፊ ሲገባ /
፪ ለለ ይጸብሕ ሌሊት ወለለ ይመሲ መዓልት
ይሴባሕ እዚአብሔር በአፈ ኩሉ ፍጥረት
/በትንቢት ሲገባ/
፫ ለለከፈለ ሙሴ ባሕረ ኤርትራ ዐደዉ
እስራኤል ለለ ሠለስቱ ነገድ፣

፬ ለለ ሜመ፣ ለለ ይሠይም እያለ ይገባል።
፭ እንዘ በትንቢት ብቻ ይገባል። ለምሳሌ
ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ዮሐንስ መጥምቅ
እንዘ ይሰብክ በገዳመ ይሁዳ ይላል።

፮ እንተ በኀላፊ ብቻ ይገባል። ለምሳሌ ነፍስ
ርኅብት እንተ ጸግበት ተአኩተከ ይላል።

፮ ጎበ ጎበ እየ ሲሆን ማሠሪያው ሐረ ወይም የሐውር ነው። ለምሳሌ የሚከተለውን እንመልከት፡ ቤተ ሳያል ጎበ ጎበ የሐጽጽ ሐረ፣ ወቤተ ዳዊትሰ ጎበ ጎበ ይመልዕ ሐረ።
፯ ከመ ከመ በትንቢት እየ የሚል ትርጉም ይዞ ይገባል። ለምሳሌ ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ፡ ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሌብወከ ይላል።
፰ አምላኔ ሲገባ የሐምዮ ሰብእ ለእግዚአብሔር አምላኔ ይሁቦ ሲሳዮ ወልብሶ፣
ኢይክለ ጸመ ደቂቁ ለመርዓዊ አምላኔ ሀሎ መርዓዊ ምስሌሆሙ፡ ይላል። አምላኔ በተጨማሪም እያለ፣ ሳለ ተብሎ ይተረጎማል።

፮ኛ. ሲ የሚሆኑ አገባቦች

ሲ የሚሆኑ አገባባት በአለቃ ታየ፣ በጎንጅ፣ እና በዋድላ ሦስት ሲሆኑ እነርሱም እንዘ፣ ጎበ ጎበ፣ ከመ ከመ፣ ናቸው። በአረፍተ ነገር ሲገቡ በትንቢት አንቀጽ ነው። በሩቅ ወንድ፣ በሩቆች ወንዶችና በሩቆች ሴቶች ይገባሉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፣
፩ ኢፈርሀ ጊዮርጊስ እንዘ ይትጋደል ምስለ ሰብዓ ነገሥት፣
፪ ኢደንገጹ ጴጥሮስ ወጳውሎስ እንዘ ይትዋስኡ ምስለ ጸራግሞስ
፫ እለ ማርያም እንዘ የሐውራ በሌሊት ጎበ መቃብረ ወልድ ኢፈርሃ አራዊተ ሌሊት፣
፬ ሰሎሞን ጎበ ጎበ ይነውም ይከሥት ዓይኖ፣ ጎበ ጎበ ይነቅሕሰ ይከድኖ፣

፯ ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ፣ ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሌብወከ ይላል።።
ከመ ከመ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ አልተጠቀሰም።። በዋድላ፣ በጎንጅ እና በአለቃ ታየ ግን ተመሳሳይ ነው።።
ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ አመ፣ ሶበ፣ እና ጊዜ ሲ፣ ሳ፣ ስ፣ የ ይሆናሉ።። በአፈታታቸው ሁሉ የማድረጊያ አገባብ አይለያቸውም።። ጊዜ ሲሆኑ በጎላፊ ብቻ ይገባሉ።። በእንዘ አማርኛ ሲ፣ ሳ፣ ስ ተብለው ሲፈቱ ግን ምሥጢራቸው ከጊዜነት አይወጣም።። ለምሳሌ፣
ስ ሲሆኑ አመ፣ ሶበ ጊዜ ትመጽእ በመንግሥትከ፣
ሲ ሲሆኑ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ መሕያው ይላል።።
ሳ ሲሆኑ በትቢት አለታ ይገባሉ።። ለምሳሌ፣
አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ኢይትሜሀሩ ሰዋስወ ተምህሮ ትርጓሜ ከመ፣ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ኢይትበጥሑ ተሐግሞ ይላል።። ሲፈታም ሰዋስውን ሳይማሩ ትርጓሜን መማር ሳይበጡ እንደመታገም ነው፣ ማለት ነው።። ወይም ሐዊረ ፍኖት በጽልመት /በጨለማ መንገድ መሄድ/ ማለት ነው።። ሙያቸው ማንፀሪያ ነው

፯ኛ. ሳ የሚሆኑ አገባቦች

ሳ የሚሆኑ አገባባት በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ መሠረት ሰባት ሲሆኑ እነርሱም፣ አምጣነ፣ እንዘ፣ ቅድመ፣ እንበለ፣ ኢ፣ ሶበ፣ ሰ ናቸው።። በዋድላ አገባብ /አለቃ ቡሩኬ/ ደግሞ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ወ እና ኀበ፣ የተካተቱ ሲሆን ሰ ደግሞ ተዘላለች።። በጎንጅ አገባብ ሳ የሚሆኑ እንዘ፣ ኀበ ኀበ፣ ከመ ከመ፣ እንበለ እና ቅደመ ብቻ ናቸው።። አምጣነ፣ ኢ፣ ሶበ እና ሰ አልተካተቱም።። በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ አመ፣ ሶበ፣ እና ጊዜ ተካተዋል።። ከላይ ከተዘረዘሩት ዘጠኝ አገባባት ውስጥ ሁለቱ ማለትም

ወ እና ሰ፣ ሳ ሲሆኑ ንዑስ አገባቦች ናቸው። ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በዐቢይ አገባብ ና፣ ሆነው፣ በንዑስ አገባብ ሳ ሆነው ተካተዋል። በዚህ መሠረት ሳ የሚሆኑት ዐበይት አገባባት እንበለ፣ ቅድመ፣ አምላነ፣ እንዘ፣ ሶበ፣ አመ፣ ጊዜ ናቸው።
እንበለን ዘ፣ ቅድመን እም ያዳምቋቸዋል። እንበለና ቅድመ ፊት ባልተደረገ፣ ኋላ በማይቀር ነገር ይነገራሉ። በንዑስ አንቀጽ እንበለን ዘ ሲያዳምቅ ዘእንበለ ይቁም አድባር ወይትፈጠር ዓለም ማለቱን ያሳያል። ቅድመን እም ሲያዳምቀው እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ይላል። ፊት ባልተደረገ ኋላ በማይቀር ነገር ሲነገር፤
እምቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም አእመረ ግብሮ
እግዚአብሔር ይላል።
እግዚአብሔር ፈጠረ ኩሎ ዘእንበለ ይትርፍ ትንንያ በማለት ያሳያል።
እንበለ ከተሳቢ ላይ ወድቆ አንቀጽ ያመጣል። ይህም ይታወቅ ዘንድ ኢትብልዑ ሥጋ በጾም ዘእንበለ ዓሣ ይላል። እንበለ ይትርፍን እንዳመጣ ያሳያል። ምክንያቱም ሲተረጎም ዓሣ ሳይቀር ተብሎ ስለሚተረጎም ሳይቀር የሚለው አማርኛ በግዕዙ ይትርፍ ነው።
አምላነ ሲነገር፣ ኢይክሉ ጸዊመ ደቂቁ ለመርዓዊ አምላነ ሀሎ መርዓዊ ምስሌሆሙ። ኢይክል ሰብእ ሐይወ አምላነ አምላነ ኢይበልዕ ወኢይሰቲ /ሳይበላ ሳይጠጣ/ ይላል።
ሶበ፣ አመ፣ ጊዜ፣ ሲገቡ፣ ሶበ፣ አመ፣ ጊዜ ኢይትመሀሩ ሰዋስወ፣ ተምህሮ ትርጓሜ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ኢይትበጥሑ ተሐግሞ ይላል።
እንዘ ሲገባ፣ ኢታውጽእ አፍኣ እንዘ ቦ ርኁብ ውስተ ቤትከ ይላል።
ከመ፣ እንበለ፡ ቅድመ ለዐበይት አገባባት አውታር በጣሽ ይሆኗቸዋል። በዐረፍተ ነገር ሲነገሩም፣
እስመ እንበለ ይስተይ ማየ

እስመ እንበለ ይብላዕ ዕክለ
እስመ ቅድመ ይስተይ ማየ ሐረ ይላል፣
እስመ ከመ ይስተይ ማየ ወረደ ጎበ ቀላይ
ይላል።።

እንዘ ከሌሎቹ ተለይቶ ሳ፣ ሲ፣ ሲያ፣ ስ፣ እየ፣ እያ፣ ቸልታ፣ ይሆናል።። ሳ ሆኖ ሲገባ ኢን አለታ ይዘ ነው።። ሳ ሲሆን በ፲ ሠራዊት፣ ስ ሲሆን በ፷ ሠራዊት፣ ሲ፣ ሲያ ሲሆን በ፫ ሠራዊት፣ በ ቦ፣ በአልቦ፣ በ፹ ሠራዊት፣ በሀሎ በ፯ ሠራዊት፣ በሀለወ፣ በአኮ በ፲ ሠራዊት ይነገራል።። ለምሳሌ፤

ሙሴ እንዘ ሀለወ በግብጽ ተአምረ ገብረ።።
/ሳ/
ወእንዘ ኢሀለወ ሙሴ፣ እስራኤል አምለኩ ጣያተ።።
ወእንዘ ሀሎከ በግብፅ ተአምረ ገበርከ
እንዘ ኢኮኑ ግዙራነ ፣ እንዘ ኢኮነ ፍሉጠ እምኅፅነ አቡሁ ይላል።።

ሊቃውንት ግን ከኮነ እና ከሀለወ በቀር በዘማች አገባባት በካልኣይ ብቻ እንዲገባ ወስነዋል።። በንዑስ አንቀፅ አስነስቶ በነባር ያሣሥራል።። ለምሳሌ ተወልዶቱ ለአምላክ እምድንግል እንዘ ይምሕል ውእቱ።።

እንዘ ከሌሎች ተለይቶ ሲ፣ ሲያ፣ ሳ፣ ስ፣ እየ፣ እና እያ ሲሆን በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት በነባር፣ በዘማች፣ በትንቢት፣ በጽድቅ፣ በአለታ ይገባል።። በሀሎ እና በሀለወ ግን በቀዳማይ አንቀጽ ይገባል።። በዋድላ አገባብም ይሄው ከላይ ተጠቅሷል።። በ ቦ በሀሎ እና ሀለወ በቀዳማይ ሲገባ፣ እንዘ ቦ፣ እንዘ ሀሎ፣ እንዘ አልቦ፣ እንዘ አኮ፣ ይላል።። በትንቢት ሲገባ ያደ አድያመ ዮርዳኖስ እንዘ ይጸርሕ ይላል።።

ቸልታ ሲሆን ሞተ እንዘ የሐምም፣ ተቀብረ እንዘ ይመውት /ታሞ፣ ሞቶ / ይላል።። ሲ፣ ስ፣ እየ ሆኖ ቸልታ ሲሆንም እንዘ ይበልዕ፣ እንዘ ትበልዕ፣ ጸርሐ

እንዘ ይብል / ሲበላ፣ በልቶ፣ ስትበላ በልተህ፣ እያለ ብሎ በማለት ይፈታል/።።

፷ኛ፡ የ፣ እንደ፣ ጊዜ፣ ዘመን፣ ሳ፣ ያህል፣ ልክ፣ ስፍር ቁጥር የሚሆኑ አገባባት

መጠን፣ አምጣን፣ ዐቅመ፣ የ፣ እንደ፣ ጊዜ፣ ዘመን፣ ሳ ያህል፣ ልክ፣ ስፍር ቁጥር ይሆናሉ።።
እነዚህም ዘይቤአቸው ልክ፣ መጠን፣ ሲሆን ምሥጢራቸው ቁጥር፣ ስፍር፣ ልክ፣ ግምት ናቸው።። ልኩና መጠኑ፣ ቁጽሩና ስፍሩ፣ በታወቀና ባልታወቀ ነገር ሁሉ በውስጠ ብዙነት ይገባሉ።። የገቡበትን አንቀጽ ያጽፋሉ።። እነዚህም በጎላፊ በትንቢት በዘመዘች አንቀጽና በነባር አንቀጽ ይነገራሉ።። በገቡበት እደ ጊዜ፣ ሳ፣ ተብለው ሲተረጎሙ ሙያቸው ማንጸሪያ ነው።።
የ፣ ተብለው ሲተረጎሙ ደግሞ ሙያቸው ቅጽል ይሆናል።። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መጠነ እና አምጣነ ቅጽል ሆነው ሲገቡ ከበ ጋር ከተነገሩና የበ ዝርዝር ይዘው ከተፈቱ በቂ ሆነው የማድረጊያ ባለበየት ይሆናሉ።።
ልክ ሆነው ሲገቡ፤ መጠነ ነግሥ አምጣነ ነግሥ ዐቅመ ነግሥ ዳዊት ነግሥ ሰሎሞን ይላል።።
ከበ ጋር ሲነገሩ፣ በአምጣነ ሀሎኩ እሴብሐከ ይላል።።
ያህል ሆነው ሲገቡ፣ ብዕለ ሰሎሞን መጠነ ብለ ኪራም፣ ይላል።።
በቁጥር፣ ሲነገር በቁጥር ሲነገር ኢያእመረ አብርሃም አምጣነ ዘገበ ወርቆ፣ መጠነ ዘገበ ወርቆ፣ ዐቅመ ዘገበ ወርቆ ይላል።።
በቀዳማይ ሲነገሩ፣ አምጣነ ገፍዐት ወሳቀየት ከማሁ፤ በትንቢት፤ ኢትሬኢኑ መጠነ ይበልዕ ወይሰቲ ቤል፣ ቤል እንደሚበላና እንደሚጠጣ አታውቅምን
በጎላፊ መጠነ ጸለይኩ በሕይወትየ
በትንቢት አምጣነ ትበልየ ለዝንቱ ኅብስት፣

ይህን ኀብስት በምትበሉበት ልክ፣ ስለምትበሉት፣ እንደምትበሉት መጠን ተብሎ ይተረጎማል።
ዐቅመ በኀላፊ ይገባል። ሲገባም ዐቅመ ሰፈርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ፣
እንደ ሰፈራችሁት ይሰፈርላችኋል
ዐቅመ ውስተ ልቡ ኀደረ ፍቅረ ቃል ይላል።
ያደረበትን ያህል፣ ባደረበት ልክ፣ ስለ አደረበት፣ እንደ አደረበት መጠን ተብሎ ይተረጎማል።
ጊዜና ሳ አንድ ወገን ነው።
መጠነ ገብረ ላቲ ለነፍስየ /መዝ. 65/
ተአምር መጠነ ተለእክኂ
መጠነ ብክ፣ መጠነ ትክል እዴክ ይላል።
በአለቃ ታየ፣ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ እና በጎንጅም ተመሳሳይ ናቸው። በቀዳማይ አንቀጽ ይነገራሉ። አምጣነን በ ያዳምቀዋል። ስፍር ሲሆኑ ለዕህል፣ ቁጥር ሲሆኑ ለገንዘብ፣ ልክ ሲሆኑ ለዘመን፣ ነው። በምሥጢር እለን፣ ዘን፣ እንተን ያመጣሉ።
ወአፍቀርኪዮሙ ለደቂቀ ፋርስ እለ መጠነ ነፍስ ተአድገ ነፍስቶሙ ወከመ አስራበ ፈረሰ አስራቦሙ እንዲል /ሕዝቅ፡ ፳፫፡ ፳/።
መጠነ ተለይቶ በካልአይ ይገባል። መጠነ ትክል እዴክ ይላል።
ሦስቱም ያህል ሲሆኑ በራሳቸውና በባዕድ ያሳሥራሉ። ለምሳሌ ተዋርዶቱ ለፈርያን መጠነ፣ አምጣነ፣ ዐቅመ አስተዋረዶሙ ለእስራኤል ሲል በራሳቸው ሲያሳሥሩ ነው። ተዋረደ ፈርያን መጠነ፣ አምጣነ፣ ዐቅመ አስተዋረዶሙ ለእስራኤል ሲል ደግሞ በባዕድ ሲያሳሥሩ ነው /አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948/።
አገባባቱ ውጥን ይጨርሳሉ። ለምሳሌ ነግሠ ሰሎሞን መጠነ ዳዊት ከመ መጠነ ሳያል ዳዊት ይላል። ሙያቸው ውጥን ጨራሽ ነው

፱፮. እንደ፣ እንዳ፣ እንዲ፣ እንዲያ፣ እንድ የሚሆኑ አገባባት

እንደ፣ እንዲ፣ እንዲያ፣ እንዳ፣ እንድ የሚሆኑ አገባባት ዐሥር ሲሆኑ በቅድሚያ ሁለቱን ማለትም ከመን እና መጠነን እንመልከት፡፡ በቀጣይ ስምንቱን ማለትም ሕገን፣ አርአያን፣ አምሳለን፣ ህየንተን፣ በዘን፣ እምዘን፣ ሶበን እና መዋዕለን እንመለከታለን፡፡

ከመ፣ እንደ ሲሆን በቀዳማይ በ፫ አርእስት፣ በ፲ ሠራዊት ይነገራል፡፡ አጽምዐ፣ መሀረ፣ ተካየደ፣ ተወከለ፣ ነጸረ፣ ያቀ ይስማሙታል፡፡ ጎላፊን ለሐዋርያት፣ ትንቢትን ለነቢያት፣ ትእዛዝን ለአብ ይሰጣል፡፡

ከመ እንደ ሲሆን ከመ ተወልደ፣ ከመ ተወለድከ፣ እያለ ይቀጥላል፡፡

እንዳ ሲሆን አ በሚል አማርኛ በቀዳማይ አንቀጽ ይገባል፡ ፡ ለምሳሌ ከመ ገብረ፣ ከመ ገበርከ ወዘተ ይላል፡፡ እንድ ሲሆን በ፭ ሠራዊት ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ከመ ትትወለድ፣ ከመ ትትወለዱ፣ ከመ ትትወለድ፣ ከመ ትትወለዲ፣ ከመ ትትወለዳ፣ ከመ እትወለድ፣ ከመ ንትወለድ ማለቱን የሳያል፡፡

እንዲ ሲሆን በ፫ ሠራዊት ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ከመ ይትወለድ፣ ከመ ይትወለዱ፣ ከመ ይትወለዳ ይላል፡፡ እንዳ ሲሆን በ፲ ሠራዊት በአለ-ታ አ በሚል አማርኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ከመ ኢገብረ፣ ከመ ኢገበርከ፣ እያለ ይቀጥላል፡፡ እንዲያ ሲሆን አ ባለበት ከእንዲ ይደረባል፡፡ እነዚህም ማድረግና መደረግ አላቸው፡፡ በ፲፫ ግሶች ይነገራሉ፡፡ ለምሳሌ እንዲህ ይላል፣

> ጎለየ ዮሐንስ ከመ ይትወለድ እምድንግል ክርስቶስ
> ተዘከረ ስምየን ከመ ይመጽእ ወልድ ውስተ ዓለም፡፡
> አስተሐመመ ሄሮድስ ከመ የጎስስ ሕፃነ

ነበበ ተናገረ ኢሳይያስ ከመ ይትወለድ ክርስቶስ፡፡
ዐይድአ ዳዊት ከመ ይትነሣእ ክርስቶስ እመቃብር፡፡

እንደ ሲሆን አ በሚል አማርኛ በቀዳማይ አንቀጽ ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣
ከመ ገብረ፣ ከመ ገበርከ፣ ከመ ገበርነ እስኪል ድረስ ይዘረዝራል፡፡
በአሉታ ሲገባ፣ ከመኢገብረ፣ ከመኢገበርከ፣ ብሎ ከመኢገበርነ እስኪል ድረስ ይገባል፡፡
ሰበከ፣ መሀረ ጳውሎስ ከመ ተወልደ ክርስቶስ ይላል፡፡
ጠየቀ ያዕቆብ ከመ ተሰቅለ ክርስቶስ፡፡
ሰምዐ አጽምዐ ይሁዳ ከመ ሞተ ክርስቶስ ዘአሰቀሎ፡፡
ርእየ ነጸረ አስተሀየጸ ለንጊኖስ ከመ ሞተ ክርስቶስ፡፡
ተአመነ ተወከለ ተሰፈወ ጢባርዮስ ከመ ተሰቅለ ክርስቶስ፡፡
ተነበየ ኢሳይያስ ከመ ይትወለድ ክርስቶስ ፡፡
ጽህቁ መላእክት ይርአዩ ከመ ይትወለድ ክርስቶስ በሥጋ እም ድንግል ይላል፡፡
ይህም ማድረግ ነው፡፡ መደረግ ሲሆን ተሰብከ በነቢያት፡ ወተዐውቀ በሐዋርያት፣ ከመ አንተ በአብ፣ ወአብ ብከ ይላል፡፡ ምሥጢሩ ሀለወ ነው፡፡ ከዚህም የቀረ በአንጻር፣ በብትን ያሳሥራል፡፡ በአንጻር ሲያሳሥር፣ ሞተ ጴጥሮስ ከመ ሞተ ጳውሎስ ይላል፡፡ የኋላው በፊት እንዳነጸረ አስተውል፡፡

በካልኣይ ሲነገር በ፫ ግሶች ይሳባል፡፡ ለምሳሌ ክርስቶስ ከመ ይትወለድ ተማህለለ፣ ተሰካተየ፣ ተካየደ ምስለ አዳም፣፣
ተአመነ፣ ተወከለ፣ ተሰፈወ አዳም ከመ ይትወለድ ክርስቶስ እምድንግል፡፡
ተነበየ ከመ ትጸንስ ድንግል ኢየሱስሃ ወልደ ይላል፡፡
ከመ ተለይቶ ውጥን ጨራሽ ሲሆን በነባር ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ነበረ ወልድ ዲበ ኪሩቤል ከመ አብ ዲበ ኪሩቤል ይላል፡፡ የአንዱን በብዙ

የብዙውንም በአንድ፣ የሴቶችን በወንዶች፣ የወንዶችንም በሴቶች፤ የቅርቡን በሩቅ፣ የሩቁንም በቅርብ፣ የሎቱን በኪያሁ ውጥን ጨራሽ ይሆናል። በዐረፍተ ነገር ሲገባም፣

ቈጥሮስ መሀረ ወንጌለ ከመ ሙሴ ኦሪተ /ለኦሪት/፣
አገቱኒ ከመ ንህብ መአረ፣
ድንግል ታፈቅሮሙ ለሐዋርያት ከመ ኢየሱስ ዮሐንስሃ፣
ብእሲ ያፈቅር አባሁ ከመ ወለት ለእማ፣
ቈጥሮስ መሀሮ ለወንጌል ከመ እንተ ሙሴ ለኦሪት
አንተ ቈጥሮስ መሀርከ ወንጌለ ከመ ሙሴ ኦሪተ፣
ከፈላ ለኢያሪኮ ኤዎስጣቴዎስ ከመ ለኤርትራ ሙሴ፣
ተነግረት ወንጌል አመ ጳውሎስ ከመ አመ ሙሴ ኦሪት ይላል።

በጎንጅ አገባብ መሠረት፣ ከመ በተጨማሪም አብነት፣ ተፎካካሪ፣ ምጸት፣ መከታ፣ ይሆናል። በ እና ዘ ያዳምቁታል። እንተ ዘ በር ከፋች ይሆኑለታል። ከመ ይመስልም ይሆናል። ምሥጢሩ ከ ያህል ከጊዜ አይወጣም።

አብነት፣ ተፎካካሪ ሲሆን፣ ተመትረ ጊዮርጊስ ከመ ተመትረ ጳውሎስ ይላል

ምጸት ሲሆን፤

> አልዓዛር ብዕለ በምድር ከመ ብዕለ ነዌ በሰማይ።
>
> ጸድቀ ልዮን ከመ ይሁዳ።
>
> ቦ ፍርሀት በልበ ጊዮርጊስ ከመ ቦ ጽጌ በሰማይ
>
> በልዐ እክለ ተክለ ሃይማኖት ከመ በልዐ ሚካኤል፣
>
> እግዚአብሔር አሠርገዎ ለምድር በከዋክብት፡ ከመ አሠርገዎ ለሰማይ በጽጌያት፡ ይላል።

መከታ ሲሆን ፤

ዮሐንስ በልዐ መጻሕፍተ ከመ ሕፃን በልዐ ሀባውዘ።።

እግዚኦ ከመ ወልታ ስሙር ከለልከነ ይላል።።

ሞተ ጊዮርጊስ ከመ ጳውሎስ፣/ጎንጅ/

ተመትረ ጊዮርጊስ ከመ ተመትረ ጳውሎስ /ጎንጅ/

በአለቃ ታየ አገባብ መሠረት፣ ከመ በዐቢይ አገባብነቱ እንደ ሲሆን በጎላፊ፣ በትንቢት፣ ይገባል።።

በጎላፊ ሲገባ ተሰቅለ ጴጥሮስ ከመ ተሰቅለ ክርስቶስ፣

በትንቢት ሲገባ ተነበዩ ነቢያት ከመ ይትወለድ ክርስቶስ፣

እንዲ ሲሆን ያቀ፣ ጠየቀ፣ አእመረ፣ ለበወ፣ ኤልያስ ከመያወርድ ዝናመ እግዚአብሔር እምድኅረ ተገብረ መስዋዕት በቀርሜሎስ፣

እንድ ሲሆን ሰምዐ ሕዝቅያስ ዜና ሐዲሰ እምቃለ ኢሳይያስ ከመ ትፀንስ ድንግል ወትወልድ ወልደ እምነ ኀቱም ማኅፀን፣

እንዳ ሲሆን ርእየ፣ ነጸረ፣ አስተሐየጸ ኢሳይያስ በዐይነ ጸጋ መንክረ ራእየ ከመ የዐትትዎ ለኃጥእ ከመ ኢይርአይ ስብሐተ እግዚአብሔር ይላል።።

በ እና ዘ ሲያዳምቁት ዘከመ ይቤ፣ በከመ ይቤ ይላል።።

ከመ ውጥን ጨራሽ በሚሆንበት ጊዜም ከዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ በኋላ አንቀጽ አለ ማለት ነው።። ለምሳሌ ሞተ ጊዮርጊስ ከመ ሞተ ጳውሎስ ሲል ጊዮርጊስ ከመ ጳውሎስ ሞተ ማለት ነው።። ስለዚህ ከመ ውጥን ጨራሽ ሲሆን አንቀጽ እንደሚያስቀርና የዐቢይ አገባብነት ባሕርዩን እንደማይለቅ ማስተዋል ተገቢ ነው።።

ከመ ይመስል ሲሆን ተንባል ይጼሊ ከመ ዘይጸድቅ ይላል።። ዘ እንተ በር ከፋች ሲሆኑ ይስማሙታል።።

ለምሳሌ ከመ እንተ መብረቅ ዘይወድዕ እምጽባህ ወይሔውጽ ከመ እንተ ወርኅ ይላል። ከመ እንተ መብረቅ ሲል ጊዜ የወጣበት መሆኑን ያሳያል።
ከመ በጎንጅ አገባብ በተጨማሪም ሊ፣ ላ፣ ል ይሆናል። ከመ በ፱ መራኅያን ከማሁ፣ ከማከ፣ ከማኪ፣ ከማነ እያለ ይዘረዝራል።
መጠነ በኃላፊ በትንቢት ይገባል።
በኃላፊ ሲገባ መጠነ ገብረ ላቲ ለነፍስየ ይላል
በትንቢት ሲገባ፣ ርእዩ መጠነ ያፈቅሮ ለአልዓዛር፣
ኢተአምርኑ ዳንኤል መጠነ ይበልዕ ወይሰቲ አምላኪየ ቤል ይላል።
ከመ እና መጠነ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም እንደ፣ እንዳ፣ የሚሆኑ አገባባት አለ ለምሳሌ
በዋድላ አገባብ መሠረት በተጨማሪ አምስት አገባባት ማለትም በዘ፣ ሕገ፣ ህየንተ፣ አርዓያ፣ አምሳለ፣ አያተ፣ ጽላሎተ እንደ፣ እንዳ፣ ይሆናሉ። ሆኖም አያተ እና ጽላሎተ ደቂቅ እንጅ ዐቢይ አገባብ ሆነው አንቀጽ ስለማያስቀሩ ከዝርዝሩ ወጥተዋል። በዘ በቀዳማይና በካልአይ አናቅጽ ይገባል። ሌሎቹ በቀዳማይ አንቀጽ ብቻ ይገባሉ።
እንደ ሲሆኑ በ፯፣ እንዳ ሲሆኑ በ፫ አርአስት፣ በዐሥር ሠራዊት ይገባሉ።
በዘ ተለይቶ አንቀጽ አይወሰንበትም። የቀሩት ግን በ፰ ግሶች ይነገራሉ። ግሶችም፣ ሠርአ፣ ወሰነ፣ ሐገገ፣ ዐለመ፣ ረቀቀ፣ ጸሐፈ፣ መሀረ፣ ሰበከ ናቸው።
በዘ እንዲ ሆኖ ሲገባ በዘ የሐውር፣ በዘ የሐውሩ ይላል።
እንደ ሲሆን በልዐ በዘ መጽአ፣ በዘ ገብረ ጥበበ ተዐውቀ ይላል።
ሕገ በራሱ ይነገራል። በጎላፊ አንቀጽ፣ በግብር፣ በተቀብያ፣ በተጸውያ፣ በባሕርይ ስም ይገባል። ለምሳሌ፣
ሠርዐ ሐዋርያት ሥርዓተ ወንጌል ሐዲስ ሕገ ሠርዐ ሙሴ ሥርዓተ ኦሪት።

ሕገ ጸመ ሙሴ ጸመ ኢየሱስ፣
ሕገ ሐገገ እያለ ይገባል፡፡ በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራል፡፡ ሲገባ
ሕገ ሠርዐ ሕገ ኦሪት ሙሴ፣ ሠርዐ ኢየሱስ ሕገ ወንጌል፡፡
ሕገ ሌወወ ካህን ሌወወ ሐራዊ ይላል /በግብር ሲገባ/
ኮኑ እሳታውያነ መላእክት ሕገ ተፈጥሩ እምነፋስ ወእሳት /በፈጥሮ ሲገባ/
በአለቃ ታየ አገባብ መሠረት እንደ የሚሆኑ አገባባት ፳፩ ናቸው፡፡ እነርሱም ከመ፣ መጠነ፣ ሕገ፣ አርአያ፣ ምስለ፣ አምሳለ፣ ህየንተ፣ ጽላሎተ፣ አያተ፣ በዘ፣ እምዘ፣ በ፣ ሳቢ ዘር፣ አርእስት፣ ወ፣ ሶበ፣ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ፣ መዋዕለ /በስም ብቻ/ ናቸው፡፡
ምንም እንኳ በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ ፳፩ አገባባት ቢዘረዘሩም በመግቢያው ላይ እንዳመለከትነው ምስለ፣ ጽላሎተ፣ አያተ፣ በ፣ ሳቢ ዘር፣ አርእስት፣ ወ፣ ግእዝ ቀለም፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ በአንቀጽ ላይ ወድቀው ማሠሪያነትን ስለማያስለቅቁ በዚህ መጽሐፍ ከዝርዝሩ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ከ ፳፩ዱ ውስጥ ዐቢይ አገባብ የሚሆኑት ዐሥሩ ብቻ ናቸው፡፡ እንደዚህም ሆኖ ሁሉንም እንደ የሚሆኑ ዐበይት አገባባትን አጠቃሎ የያዘው የአለቃ ታየ አገባብ ነው፡፡
እምዘ እንደ፣ እንዲ ሲሆን በዘ አገባብ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ተዋረደ ፈርዖን እምዘ አስተዋረዶሙ ለእስራኤል ይላል፡፡ በካልኣይ እምዘያስተዋርድ ይላል፡፡ በዐሥር ሠራዊት ይዘረዝራል፡፡
አርአያ በኀላፊ ብቻ እንደ ሆኖ ሲገባ አርአያ ሠርአ፣ አርአያ ዐለመ፣ አርአያ ረቀቀ፣ አርአያ ሐገገ፣ አርአያ ወሰነ፣ አርአያ ጸሐፈ፣ አርአያ መሀረ፣ አርአያ ሰበከ ወንጌለ ተዐውቀ ማለቱን ያሳያል፡፡
አምሳለ በቀዳማይ አንቀጽ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በቀዳማይ አንቀጽ ሲገባ አምሳለ አእመረ፣ አምሳለ

አእመርክ፣ አምሳለ አእመርኩ እያለ በዐሥር መደብ ይዘረዝራል።።
በጎንጅ ደግሞ እንደ የሚሆኑ አገባባት ፱ ናቸው።። እነርሱም ከመ፣ ሕገ፣ አርዓያ፣ አምሳለ፣ ፣ ምስለ፣ አያተ፣ ህየንተ፣ መጠነ፣ በቀለ ናቸው።። በስም፣ በግብር፣ በቦታ ይገባሉ በማለት ያትታል።። ነገር ግን ከላይ ከተገለጹት መካከል ምስለ እና አያተ ደቂቅ እንጅ ዐቢይ አገባብ አይሆኑም።። ምክንያቱም በአንቀጽ ላይ ወድቀው ማሠሪያነትን ማስለቀቅ አይችሉም።። በዚህ መሠረት ሰባት ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው።።
አገባባቱ በ፤ መደብ ይዘረዝራሉ።። መጠነ እና በቀለ በጎላፊ እንደሚገቡ የተገለጸ ሲሆን በቀለ በሌሎች አገባቦች አይገኝም።። ከመ እና መጠነ እንደ ሲሆኑ ከላይ በዝርዝር ተነግረዋል።።
በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት እንደ፣ እንዲ፣ እንዲያ፣ እንድ የሚሆኑ አገባባት አርአያ፣ አምሳለ፣ ሕገ፣ በዘ፣ እምዘ፣ ከመ፣ መጠነ፣ አምጣነ፣ ዐቅመ ናቸው።። ሶበ እና ህየንተ የሉበትም።። ሙያቸውን በተመለከተ በዐቢይ አገባብነት ሲገቡ ማንዐሪያ፣ በደቂቅ አገባብነት ሲገቡ ደግሞ አንጻር፣ አስፈቺ ነው።።

፲ኛ. በ፣ ቢ፣ ቢያ፣ ባ፣ ብ የሚሆኑ አገባባት

በዋድላ አገባብ /አለቃ ቡሩኬ/፣ በጎንጅ አገባብ እና በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ እመ፣ ሶበ፤ በ፣ ቢ፣ ቢያ፣ ባ፣ ብ ይሆናሉ።። በአለቃ ታየ አገባብ መሠረት ደግሞ ፲፬ አገባባት ናቸው።። እነርሱም እመ፣ እም፣ አመ፣ ሶበ፣ እንተ፣ ዘ፣ ውስተ፣ ጊዜ፣ በ፣ መንገለ፣ ተናባቢ ቀለማት፣ ግእዝ፣ ጎበ፣ ወ ናቸው።። ነገር ግን ከተዘረዘሩት አገባባት መካከል ውስተ፣ በ፣ ተናባቢ ቀለማት፣ ግእዝ፣ እና ወ አንቀጽ ስለማያስቀሩ ዐቢይ አገባብ አይሆኑም።። ሌሎቹ

ደግሞ ማለት እም፣ አመ፣ እንተ፣ ዘ፣ ጊዜ፣ መንገለ፣ ኀበ፣ ዐበይት አገባባት ቢሆኑም በ፣ ቢ፣ ቢያ፣ ባ፣ ብ እንደሚሆኑ በአብነት መምህራን ዘንድ የታራ ስምምነት የለም። ስለዚህ በሁሉም አገባባት የተጠቀሱት ተለቅመው ሲዘረዘሩ በ፣ ቢ፣ ቢያ፣ ባ፣ ብ የሚሆኑ ዐበይት አገባባት እመ፣ እና ሶበ፣ ብቻ ናቸው።

በተጨማሪም በጌቱ ገሞራው /ዋድላ/ አገባብ እም በ ይሆናል። ሲገባም እምኔሶ ለሰብእ ሶበ ይምሕር ነዳየ ይላል። ይህም የማሠሪያ አጋዥ ስለሆነ መነገር ያለበት በንዑስ አገባብ ነው።

ስለዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት ሁሉ በ፣ ቢ፣ ባ፣ ቢያ፣ ብ የሚሆኑት እመ እና ሶበ ብቻ ናቸው። ሲገቡም፣

በ ሲሆኑ፣ ሶበ፣ እመ ሰትየ እምሰክረ ይላል/በጠጣ በሰከረ ነበር/።

ሶበ ሰገደ፣ እመ ሰገደ እምጸድቀ ይላል /በሰገደ በጸደቀ ነበር/፣

ቢ ሲሆኑ ይእዜ ያድኅኖ እመ፣ ሶበ ይፈቅዶ /ቢወደው ያድነው/

እምኔሶ ለሰብእ <u>ሶበ</u>፣ <u>እመ</u> ይምሕር ነዳየ

እመኒ ኩሎሙ የዐልዉከ አንሰ ኢይዐልወከ /ሂ፣ ኒ ትራስ/

እመሁ፣ ሶበሁ የአምር በዓለ ቤት /ምንአልባት ቢያውቅ፣ ያውቅ ቢሆን/

እመኒ ጳውሎስ ወእመኒ አጵሎስ /ጳውሎስም ቢሆን፣ አጵሎስም ቢሆን ተብሎ ይፈታል/

እመኒ እወ እወ፣ ወእመኒ አልቦ አልቦ

ቢያ ሲሆኑ፣ እመኒ ያበዝኅ ሰብእ ጥበበ ኢይክል ያእምር ዕለተ ሞቱ

ቢያ ሲሆኑ አ በሚል አማርኛ ነው። እምኔሶ ለሰብእ ሶበ ይምሕር ነዳየ ወምስኪነ፡ ወይገብር ሠናየ ማለቱን ያሳያል።

ባ ሲሆኑ እመ ኢተምህረ፣ ሶበ ኢተምህረ እምኢጸሐፈ

ብ ሲሆኑ እመ አኮ አንተ ኤልያስ፣ ወእመ አኮ አነ ኤልዛቤል /ወይ አንተ ኤልያስ ተብለህ ወይም እኔ ኤልዛቤል ተብዬ ተብሎ ይፈታል/
እረክበከኑ እመ፣ ሶበ እመጽእ?
እረክብኑ ዘይሰምዐኒ እመ፣ ሶበ እትናገር፣
ትበጽሑ ኀበ ዘፈቀድክሙ እመ፣ ሶበ ትሐውሩ
እመኒ ዐረጉ ውስተ ሰማይ ላዕለ ህየኒ ሀሎከ
ወእመኒ፣ ወሶበኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ
ብ ሲገባ በሁለት ንዑሳን አናቅጽ ይሳባል፡፡ ለምሳሌ ንጉሥ ወጽአ አፍዓ ይርአይ ሶበ ይትራወጽ ፈረስ ምስለ ፈረስ፡፡
ጌሠት ማርያም መግደላዊት እመ ትሬኢ ትንሣኤሁ ለወልድ ይላል፡፡
በ እና ባ ሲሆኑ በቀዳማይ አንቀጽ ብቻ ይነገራሉ፡፡ ሙያቸው ማንጸሪያ ነው፡፡
ቢ፣ ቢያ ሲሆኑ ምሥጢራቸው ከንዑስ አንቀጽ አይወጣም፡፡ ለምሳሌ ባዕል አፍቀረ እመ ይበልዕ ኀብስተ ሲል በሊያተ ኀበስት ማለት ነው፡፡ በንዑስ አንቀጽ አስነስተው በነባር አናቅጽ ያሣሥራሉ፡፡ በዘማች ሲያሣሥሩ ለነባሩ ፯ አገባባት ይስማሙታል፡፡ እነዚህም የውእቱ ግሶቸ ናቸው፡፡ በዐረፍተ ነገር ሲገቡም፣
ተፈቅሮቱ ለንጉሥ ሶበ፣ እመ ይከውን ዘመኑ ዘመነ ተድላ እስመ ኢይትቤቀልዎ ነዳያን ይላል፡፡
እመ ተለይቶ ሂን፣ ኂን ትራስ እየያዘ በካልኣይ ይገባል፡፡ በአይ በምንት አማርኛ ይፈታል፡፡ በዐረፍተ ነገር ሲገባም የአንቀጽ፣ የአስረጅ አፍራሽ ነው፡፡
እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ በላያቸው ላይ አይወድቁባቸውም፡፡ የቀሩት ዐበይት አገባባት ግን ይወድቁባቸዋል፡፡
አንቀጽን ሲያፈርሱ ነዳይ ኢ-ነሥሠ ዳግማዊ መብልዐ እመኒ ከርሱ ኢይጸግብ፡ እንዘ ይበልዕ ህዳጠ ኀብስተ ይላል፡፡

አስረጂን ሲያፈርስ ገብረ ሕይወት ኢበልዐ ዕክለ አምላነ መልአክ ውእቱ እመሂ ይመውት ድኅረ ለብሰ ሥጋ፣ በዘ ለብሰ ሥጋ ማለቱ ያሳያል።
በደጊመ ቃልም ይነገራል። በዚህ ጊዜ ማሠሪያው አለታ ነው። ጎያል እመ እመ ይረውጽ ኢይደክም ይላል። /ቢሮጥ ቢሮጥ ብለህ ፍታ/። አንቀጹም ይደግማል የሚሉ አሉ። አንቀጹ ሳይደግም ግን የውስጠኛው እመ አንቀጽ ጠባቂ፣ የኋለኛው እመ አማርኛ ጨራሽ ይባላል። በነገር ሲገባ ስለ ከሚሆኑ አገባባት ጋር ታይቷል።
እመ አጥፊ፣ አልሚ ይሆናል፡ አጥፊ ሲሆን አረጋዊ እመ የጎዝን ይቀትል ሰብአ ይላል። አልሚ ሲሆን እግዚአብሔር እመ ምስሌነ ተገፍዖተነ ንነግሮ ይላል።
በተጨማሪም ምንአልባት፣ እንደ ይሆናል። በቀዳማይ በካልኣይ ይነገራል። ለምሳሌ ንርአይ ለእመ ጸገየ ወይን፣ ወለእመ ፈረየ ሮማን ይላል። ማሠሪያው ይቤ ነው።
እንደ ሲሆን በቦ፣ በአልቦ ይደረባል፡ በንዑስ አቀጽ ይመረመራል። ምንአልባት ሲሆን ከእንደ ይደረባል። በካልኣይ ሲገባ በራሱ አማርኛ ይፈታል።
እም በ፣ ባ ሲሆን በቀዳማይ ይነገራል። በአለቃ ታየ አገባብ ከላይ ከሌሎቹ ጋር አብሮ ተነግሯል። ጸጸት ተምኔት ይሆናል። እስመ፣ አምላነ፣ አኮኑ ይስማሙታል። በዐረፍተ ነገር ሲገባ ማሠሪያ አጋዥ ነው።
እመ ኢሆረ ፈራህ ብእሲ ውስተ ዐውደ ቀትል እምኢረከቦ ሞት፣
ፀፀት ሲሆን አምላነ አኮኑ ረከቦ ሞተ ግብት፣
ተምኔት ሲሆን ነዳይ እመ ሖረ ውስተ ጽርሐ ንጉሥ እምረከበ ወርቀ፣ ሁሉም ንዑስ አገባብ ነው። እም ሙያው ማሠሪያ አጋዥ ነው።

፲፩ኛ. ከ፣ ካ፣ ኪ፣ ክ የሚሆኑ አገባባት፤

በዋድላ አገባብ መሠረት እም እና እመ፣ ከ፣ ኪ፣ ካ ይሆናለ፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ደግሞ ሶበ ተጨምሯል፡፡ በአለቃ ታየ አገባብ መሠረት ከ፣ ኪ፣ ካ፣ ክ የሚሆኑ አገባባት ዐሥር ናቸው፡፡ እነርሱም እም፣ እመ፣ ሶበ፣ ኀበ፣ መንገለ፣ ውእደ፣ ውስተ፣ ወ፣ በ፣ ተናባቢ ቀለማት ናቸው፡፡ የአለቃ ታየ አገባብ በተደጋጋሚ እንደ ታየው ፍችን እንጅ ሙያን አይጠነቅቅም፡፡ ደቂቅ አገባብ የሆነውን ሁሉ በፍች ወይም በትርጉም እየሄደ በዐቢይ አገባብ ውስጥ ያስገባል፡፡ ለምሳሌ ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ውስተ፣ ወ፣ በ፣ ተናባቢ ቀለማት ዐቢይ አገባብ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ፣ ደግሞ ዐበይት አገባባት ቢሆኑም የቅኔ መምህራን ከ ወይም ካ ይሆናሉ ብለው አይቀበሏቸውም፡፡ በዚህ መሠረት ከ፣ ወይም ካ የሚሆኑ እም፣ እመ፣ እና ሶበ ብቻ ናቸው፡፡ እመን ለ ያዳምቀዋል፡፡ እመ ተለይቶ በቀዳማይ ይነገራል፡፡ ማድረግ መደረግ አለበት፡፡

እም ከመን እና ዘን በር ከፋች አድርጎ በኀላፊ አንቀጽ ይገባል ለምሳሌ፣

እምከመ ወሀብከነ ሲሳየ ዘዕለት ወዓራዘ ዘዓመት የዐክለነ ዝንቱ ሀብት፣

ብእሲ እምዘ ተወክፈ ሃይማኖተ እምቤተ ክርስቲያን ወእምከመ ገብረ ግብረ ሠናየ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም፡

እመ ሰ እያጋነነውም ሳያጋንነውም ይገባል፡፡

እመ ሲገባ በር ከፋች አይፈልግም፡፡ ለምሳሌ፣

ከ ሲሆን እመ እግዚአብሔር ሐነጸ ቤተ ሠናየ ጸመው እለ የሐንጹ ቤተ፣

እመ ቀተልከ /ከገደልከ/፣ እመ ቀተለ /ከገደለ/፣

እመ፣ ሶበ ካ ሲሆኑ፣ ሶበ አምነ ወአእመነ /ካመነ፣ ካሳመነ/፣

እመ፣ ሶበ ያቀ ወአያቀ /ካወቀ፣ ካሳወቀ/፣

እመ አኮ፣ ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ /ከእኛ ጋር ካልሆነ/፣
እመ እግዚአብሔር ኢሐነጸ ቤተ ክንቶ ይጸምዉ እለ የሐንጹ ይላል፡፡

፲፪ኛ. እስከ፣ እስኪ የሚሆን አገባብ

እስከ በቁሙ እስክ እና እስኪ ይሆናል፡፡ እስከ በትርፍ አማርኛ ድረስ ይሆናል፡፡ ነን፣ አመን፣ ሶበን ኀበን በር ከፋች ይዞ በቀዳማይ በካልአይ ይገባል፡፡ በቀዳማይ ሲነገር ሲነገር ኀበን፣ ሶበን አመን ሳይዝ አይነገርም በማለት በጌቱ ገሞራው አገባብ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ካልኣይ ግን የውድ ነው፡፡ ሲነገርም አፈቅሮ እስከ አመ ፈቀደ ይላል፡፡ ብዝኅ ጽንእ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ አንብረኒ እግዚእየ እስከ ይከውን ምጽአትከ ይላል፡፡
እስከ ሲሆን እስከ ይመጽእ በዓለ ቤት ይላል፡፡
እስኪ ሲሆን አ በሚል አማርኛ ይነገራል እስከ ይገብዕ ፍትሕ ለዘይጸደቅ ይላል፡፡
አስክ ሲሆን እስከ እመጽእ ጽንሐኒ ይላል፡፡ ኀበ ሶበ ሲነገሩ እስከ ኀበ ይትገበር ኩሉ፣ እስከ ሶበ ያስተነፍስ ዕለት፣ አስከ አመ ትመጽእ በመንግሥትከ ማለቱን ያሳያል፡፡
ፍጻሜ ያለው ፍጻሜ የሌለው እስከ አለ፡፡ ፍጻሜ ያለው አስከ ሲገባ እስከ አመ ይመጽእ ወልደ ዕጓለ ዕመሕያው ይላል፡፡ ፍጻሜ የሌለው አስከ ሲገባ፣

> ኢወለደት ሚልኮል እስከ አመ ሞተት፤
> ኢተመይጠ ቋዕ አስከ አመ ነትግ ማየ አይኅ፣
> አንብረኒ እስከ አመ ይመውት ኪሩብ ይላል፡፡

፲፫ኛ. ጊዜ ዘመናት፣የሚሆኑ አገባባት

አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ፣ ዓመተ፣ ዕለተ፣ መዋዕል፣ ጊዜ፣ ዘመን ይሆናሉ። በዘማች አንቀጽ፣ በነባር አንቀጽ በጎላፊ፣ በትንቢት አንቀጽ ይነገራሉ። በገቡበት አንቀ በን ይዘረዝራሉ። ዘን፣ እንተ፣ እለን፣ በምሥጢር ያመጣሉ። ማለትም ለጊዜ፣ ለዕለት ለወራት፣ ለዓመት ለዘመን ቅጽልም በቂም ይሆናሉ።
አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ በጎላፊ ሲነገሩ፣
አመ ተንስአ ወንስአ ኵሎ ሙታን፣
ጊዜ በጽሐ እድሜሁ ፈነወ ወልዶ፣
ጊዜ ጸዋዕኩኪ በአስተቤቁየ፣
ሶበ ጸዋዕክዎ ለእግዚአብሔር ሰምአኒ ጽድቅየ
ተዘርኡ ሐዋርያት፣ ተእኅዘ እግዚእነ ይላል።
በትንቢት ሲገሩ፣
አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ይወቅሰነ በግርምት ዐውድ
አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ይመጽእ ሐዳስ በዓለ ቤት፣
አመ ዕለተ እጼውዐክ ፍጡነ ስምአኒ ይላል።
ዘመን ሲል ደግሞ አልቦ አመ ኢሀሎ ክርስቶስ ይላል።
በነባር ሲነገሩ፣ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ሀሎ፣
አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ አኮ፤ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ አልቦ ይላል።
በአሉታ ሲገቡ፣ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ኢሀሎ ይላል።
አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ፣ ዕለተ፣ ዓመተ መዋዕል ተደራርበው ይነገራሉ። ለምሳሌ፣
አመ ዐለተ እጼውዐክ ፍጡነ ስምአኒ፣ ይላል።
ዕለት ሲሆን፣ በዕለት አመ ተሰቅለ እግዚእነ
በዕለት አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ተሰቅለ እግዚእነ ፀሐይ ፀልመ፤
ምንተ ንግበር በዕለት አመ ይትናገሩ ባቲ፣ ይላል።
በዕለተ ጸዋዕኩክ በዕለተ ንጼውዐክ ይላል።
ለዚህ ማስረጃ የሚሆን የአበው ቅኔ፣
ይእዜ ዕለት ዕለተ ወልደ ዑኤዝ ነግሠ፤
አምጣነ አልቦ ዘሠቀ እንበለ አቤኔር ለብሰ።
ዕለተ መድኃኒት ይእቲ ዐርብ ዕለተ ተሰቅለ እግዚእነ

ዓመተ፣ በቀዳማይ አንቀጽ ሲገባ በአመ ሞተ ኦዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለልዑል ላል።።
በዓመተ በኀኀላፊ አንቀጽ ብቻ ይነገራል።። ዓመተ ምሕረት ተሰምየት ዓመት ዓመተ ተወልደ እግዚእነ፣ መዋዕለ፣ ምሥጢሩ በኀላፊ፣ በትንቢት ይነገራል።።
ሲነገርም፣ በመዋዕለ አበስከ፣ በመዋዕለ ትኤብስይላል፡ በበደልክበት፣ በምትበድልበት ወራት ተብሎ ይተረጎማል።።
ተደርበውም ይነገራሉ።። ሲገቡም፣
አመ አመ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም ተከፍለት ለክልኤ መንግሥተ ዳዊት፣
አመ ጊዜ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም ተከፍለት ለክልኤ መንግሥተ ዳዊት፣
ጊዜ አመ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም.....
ጊዜ ጊዜ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም.....
ሶበ አመ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም.....
ሶበ ጊዜ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም.....
አመ በአመ ሮብአም ነግሠ ኢዮርብአም.....
አመ በሶበ፣ አመ በጊዜ እያልክ ቀጥል።።
ከበ ጋር ሲነገሩ፣
በዕለተ በላዕክሙ እንትኩ በለሰ ሞተ ትመውቱ፣
በአመ በላዕክሙ እንትኩ በለሰ ሞተ ትመውቱ፣
በጊዜ በላዕክሙ እንትኩ በለሰ ሞተ ትመውቱ፣
በትንቢት ሲሆን፣ በዕለተ ትበልዑ እንትኩ በለሰ...
በአመ ትበልዑ.....
በጊዜ ትበልኡ.....እያለ ይነገራል።።
በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ መሠረት ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ በ፣ ወ፣ ግእዝ አፈ፣ ፍና፣ ወርሕ ተካተዋል።። ነገር ግን ሰዓተ፣ አፈ፣ ፍና፣ በ፣ ወ፣ ግእዝ ንባብ አንቀጽ ስለማያስቀሩ ጊዜ የሚል ትርጉም ቢኖራቸውም ደቂቅ አገባብ እንጅ ዐቢይ አገባብ ሊሆኑ አይችሉም።። ከላይ የተነገሩት እንደማንኛውም ዐቢይ አገባብ በቀዳማይ በካልአይ ይገባሉ።።

በን ይዘረዝራሉ፣ ዘን፣ እንተን፣ እለን በምሥጢር ያመጣሉ፡፡ በንዑስ አንቀጽ አስነስተው በነባር ያሳሥራሉ፡፡ በዘማች ሲያሳሥሩ ፯ አገባባት ይስማሟቸዋል፡፡ እነርሱም የውእቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፤

አመ ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታነ፣
አመ በጽሐ፣ ሶበ በጽሐ፣ ጊዜ በጽሐ እደሜሁ ፈነወ ወልዶ
ጊዜ ጸዋዕኩኪ በአስተብቁየ
ሶበ ጸዋዕክዎ ለእግዚአብሔር ሰምዐኒ ጽድቅየ፣
አመ ይወጽኡ እስራኤል እምግብጽ፣ /ካልኣይ/
ሶበ ትትሐወክ ነፍስየ እመንሱት፣

በጊዜ ሲገባ በጊዜ ይመጽአ ሐዳስ በዓለ ቤት ይላል፡፡ ዕለተ ሲገባ በዕለተ በላዕክሙ እንትኩ በለሰ ሞተ ትመውቱ፣

ወስምዐነ በዕለተ ንጼውዐከ፣ ስምዐኒ አመ ዕለተ እጼውዐከ ይላል፡፡

መዋዕለ ሲገባ በመዋዕለ ነግሡ ሰሎሞን ተፈሥሑ እስራኤል ይላል፡፡

ዓመተ ሲገባ በዓመተ ሞተ አዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለልዑል ይላል፡፡

አመ ይደረባል፡ እንዲህም ይላል፤ አመ አመ ንጉሥ ይሴኒ ይጸግቡ ርኁባን፡፡

ቅጽልም ይሆናሉ፡፡ አገባባቸው እንደ ዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ምሥጢራቸው ከጊዜነት ሳይወጣ ሲ፣ሳ፣ስ ሆነው በቅጽልነት ይገባሉ፡፡ ለምሳሌ ወአመ መጽእ ወልደ ዕጓለ መሕያው፣ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ትመጽእ በመንግሥትከ /ሲመጣ፣ ስትመጣ፣ ወይም በሚመጣበት ጊዜ፣ በምትመጣበት ጊዜ፣ በማለት ቅጽል ይሆናሉ/፡፡

፲፬ኛ. ኋላ የሚሆኑ አገባባት

ድኅረ ኋላ ይሆናል፡፡ በቀዳማይ ይነገራል፡፡ እንተን፣ እለን፣ ዘን በምሥጢር ያመጣል፡፡ በትርፍ አማርኛ ከ፣ ካ ይሆናል፡፡መደረግ ማድረግ አለበት፡፡ በዐረፍተ ነገር ሲገባም እምን ይዞም ሳይዝም ይነገራል፡፡ ድኅረ ሐረ፣ እምድኅረ ሐረ፡ ይላል፡፡ ማድረግ ሲገባ በቀዳማይ ነው፡፡ ለምሳሌ ድኅረ ሐረ ንጉሥ ይተልዉ አግብርት ይላል፡፡

በአለቃ ታየ መጽሔተ አእምሮ ግን በተጨማሪ ከዋላ እና እምዘ ኋላ ይሆናሉ፡፡ እምዘ ኋላ መሆኑ ትክክል ነው፡፡ ከዋላ ግን የሚገባው ከነገር በኋላ ስለሆነ ማሠሪያን አያሰቀርም፡፡ ስለዚህ ዐቢይ አገባብ አይሆንም፡፡ ድኅረና እምዘ ግን ከነገር በፊት እየገቡ ማሠሪያን ያስቀራሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ድኅረ ነግሠ ዳዊት ነግሠ ሰሎሞን፣
እምድኅረ ዐርገ እግዚእ ፈነወ ለአርዳኢሁ ጸራቅሊጦስሀ፣
እምዘ ረወዩ አግማሊሁ ሐረ ኢያቡር ውስተ ቤተ ባቱኤል፣
እምዘ ርእዩ ኮከበ በምሥራቅ መጽኡ ሰብአ ሰገል ውስተ ቤተ ልሔም

፲፩ኛ. ገንዘብ የሚሆኑ አገባባት

በዘ ዐቢይ አገባብ ሲሆን ፍችው ገንዘብ ነው፡፡ ምሥጢሩ እንደ፣ ስለ ይሆናል፡፡ በኀላፊና በትንቢት ይነገራል፡፡ ሲገባ፤

በዘወድአ ሞት ኵሎ /ሞት ሁሉን በጨረሰ ገንዘብ/
በዘቀነዮሙ ሞት /ሞት በገዛቸው ገንዘብ/ ይላል፡፡
ሙያው ማንጸሪያ ነው፡፡
በዘ በተጨማሪም ቅጽል ይሆናል፡፡ ሲነገርም፤
ለምነት ትትናገር በዘይሰምዑ ሕዝብ፡፡
ሰዎች በሚሰሙበት /የሚሰሙበትን/ ቋንቋ ለምን ትናገራለህ፡፡
በዘርኢነ ወበዘሰማዕነ ሰማዕተ ንኪውን ፡፡

ያየነውንና የሰማነውን እንመሠክራለን፣ ወይም ባየነውና በሰማነው እንሆናለን፡፡
ነሥአ ሰይፈ በዘይቀትል /የሚገድልበትን ሰይፍ አነሣ/፡፡
ኀሠሠ ምክንያተ በዘያስተዋርድ ሰብአ / ሰው የሚያዋርድበትን ምክንያት ፈለገ/፡፡
አንዳንድ መምህራንና አገባብ ዐዋቂዎች ነሥአ ሰይፈ በዘይቀትል ያለውን ዘ ቅጽል፣ በ፣ ዘን አዳማቂ ነው ብለው ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን በዘ አንድ አገባብ እንደመሆኑ መጠን በዘ ቅጽል እንጂ ተለያይተው ሁለት ትርጉምና ሙያ ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ በዘ በቀዳማይና በካልኣይ ይነገራል፡፡

፲፮ኛ. የ፣ ያ የሚሆኑ አገባባት

እንተ፣ እለ፣ ዘ፣ የ፣ ያ ይሆናሉ፡፡ በትርፍ አማርኛ የሚ፣ የም፣ የሚያ፣ ይሆናሉ፡፡ በዘማች አንቀጽ፣ በነባር አንቀጽ፣ በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በዘር፣ በነባር፣ ማለትም በባሕርይ ስም፣ በተጸውዖ ስም፣ በግብር ስም እየገቡ ቅጽልና በቂ ይሆናሉ፡፡
ዘ፣ ለነባቢ፣ ለኢነባቢ፣ ለወንድ፣ ለሴት፣ ለአንድ፣ ለብዙ፣ ለቅርብ፣ ለሩቅ ቅጽልና በቂ ይሆናል፡፡ ስለሆነም መክብብ አገባብ ይባላል፡፡
እንተ፣ ለአንድ ወንድ፣ ለአንዲት ሴት፣ በነባቢና በኢነባቢ አንቀጽ ለሚነገር ሁሉ ቅጽልና በቂ ይሆናል፡፡
እለ፣ ለብዙ ወንዶችና ሴቶች፣ ለሩቅና ለቅርብ፣ ለነባብያንና ለኢነባብያን ሁሉ ቅጽልም በቂም ይሆናል፡፡
ሁሉም የገቡበትን አንቀጽ በባዕድ ቅጽል ይዘረዝራሉ፡፡ አንዳንድ ባለ አገባቦች ዘ ለወንድ ብቻ፣ እንተ ደግሞ ለሴ ብቻ ይቀጸላል ይላሉ፡፡ እኛ ግን አበው ሊቃውንት ባስተማሩን መሠረት ከላይ በተገለጸው ሕገ ሰዋስው እንመራለን፡፡

ዘ ሲገባ፣ እግዚአብሔር ዘሀለ ወይሂለ፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመጽአ ወካይበ ይመጽእ፣
ማርያም ዘወለደት አምላክ
ማርያም ዘወለድኪ አምላክ
አክብሩ መኳንንቲክሙ ዘነገሩክሙ ቃለ እግዚአብሔር።።
ዘኦሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ ይላል።።
በቂ ሲሆን አልቦ ዘዐርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ
ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ።።
ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ፣ ይላል።። በስም ገብቶ በቂ ሲሆን ሀቡ ዘቄሳር ለቄሳር ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአሔር፣
በንኡስ አገባብ ላይ ወድቆ በቂ ሲሆን ዘሂ በልዐ ለግዚአብሔር በልዐ ወየአኩቶ ለእግዚአብሔር፣
በነባር ሲነገር አይቴ ውእቱ ዘትካት ሣህልከ እግዚኦ የገበቡበትን አንቀጽ በባዕድ ቅጽል ሲዘረዝሩ፣
አቤል ዘወለደት ሔዋን ተቀትለ በእደ ቃኤል፣
ወንጌል ዘሰበከ ዮሐንስ፣
ዳዊት ከዐወ ማየ ዘአመጽኡ አዲኖን ወኢያቡስቱ
ክርስቶስ ዘወለደት ማርያም አድኅነ ዓለመ ይላል።።
ዘ፣ አታላይ ሲሆን ነግሠ ቤርሳቤህ ዘአእመረ ዳዊት ዘወለደቶ ሰሎሞን፣ ይላል።።
በአንቀጽ ላይ ወድቆ በቂ ሲሆን ሞተ ዘኢይመውት ዘተወልደ እማርያም አድኅነ ዓለመ ይላል።።
እንተ፣ በዘማች አንቀጽ በነባር አንቀጽ በኀላፊ በትንቢት እየገባ ለአንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ለቅርብ፣ ለሩቅ ቅጽልም በቂም ይሆናል።። የገባበትን አንቀጽ በባዕድ ቅጽል ይዘረዝራል።።
ሲነገርም፣
በቀዳማይ አንቀጽ፣
አዳም እንተ በልዐ በለሰ ዘኢተአዘዘ ይብላዕ ተኰነነ።።
ሰሎሞን እንተ ነግሠ በኢየሩሳሌም ኰነነ ኢየሩሳሌም በካልኣይ፣

ዕፅ እንተ ኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይትገዘም ወውስተ እሳት ይትወደይ፡ ይላል፡፡
በነባር፣
ለዕፅ እንተ ቦ ውስተ ገነት ቦ ሠናይ መዓዛ፣
ለሴት፣ ሀገር እንተ ተሐንጸት መልዕልተ ደብር፣
ደብር እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ ይላል፡፡
የገባበትን አንቀጽ በባዕድ ሲዘረዝር ዕፀ እንተ ርእየ ሙሴ ትመስል ማርያም ድንግል ይላል፡፡
ሲተረጎምም ማርያም ሙሴ ያያትን እንጨት ትመስላለች ተብሎ ይፈታል፡፡
በዘር ላይ ወድቆ በቂ ሲሆን፣
ብእሲ ጠቢብ ውስተ ልቡ ሰወረ እንተ ልቡ፣
አንህብት ቀሠሙ እንተ ገዳም፣
እንተ ሠማርያ ኮነ ለሠማርያ ይላል፡፡
አታላይ ሲሆን፣
ዐርገ ማርያም እንተ ወለደ ኢያቄም እንተ ወለደት ወልድ በይባቤ ይላል፡፡
እንተ ቦ ኢየኀሥሥ እንተ አልባ፡፡
እንተ አልባ ተኀሥሥ እንተ ቦ፡፡
እለ በቀዳማይ አንቀጽ ሲነገር፣
ሠለስቱ ምእት ዐሠርቱ ወሰመንቱ እለ ተጋብኡ በኂቅያ፣
አዋልድ እለ ተለዋ ድኅሬከ ይላል፡፡
በካልኣይ፣ ውሉድ እለ ይመጽኡ ድኅሬከ፣
ሀለዉ እደው ነቢያት እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት
ቦ አንስት እለ ያጠብዋ ሐሊበ ይላል፡፡
በቂ ሲሆን ቦ እለ አልቦ በሕይወት፡፡
ወአልቦ እለ አልቦ በሕይወት፣
እለ ኢየሩሳሌም ተፄወዉ ኀበ ፋርስ፣
እለ ዓለም ያፈቅሩ ዓለመ ወዓለም ያፈቅር ሊአሁ ይላል፡፡
ዘ፣ እንተ፣ እለ ሲዘረዝሩ የ “አ” ን፡ ራብዕ ማለትም “አ” ን መንገድ መሪ ወይም በር ከፋች አድርገው

ይገባሉ።። ዚኣሁ፣ እንቲኣሁ፣ እሊኣሁ ይላል።። በዐሥሩ መራሕያንም ይዘረዝራሉ።።
ዘ፡ ከእንተ እና እለ ተለይቶ ብቻቸውን አንቀጽ ማስቀረት ለማይችሉ ዐበይት አገባባት በር ከፋች ይሆናል።። ለምሳሌ፣ ዮም ንወድሳ ለማርያም በእንተ ዘተወልደ እምኔሃ፣ በይነ ዘተወልደ እምኔሃ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።።
በተጨማሪም አንዳንድ ባለአገባቦች ዘ ስለ ይሆናል ይላሉ።። ለምሳሌ ነስሐ እግዚአብሔር ዘአንገሦ ለሳኦል።።
አአኵተከ እግዚአብሔር ዘኢረሰይከኒ ከመ ሰብእ ዐማፅያን የሚሉትንም እንደ ምስክር ያቀርባሉ።። ነገር ግን ስሕተት ነው።። የ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።።
ቀሪውን የዘ ባሕርይ ማለትም ዘርፍ ደፊ፣ ዘርፍ አያያዥ ወዘተ ሲሆን በደቂቅ አገባብ ተመልከት።።

ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ፣ ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ የ የሚል ትርጉም ይዘው የቦታ ቅጽል ይሆናሉ።። በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብብ ላይ በዝርዝር ተጠቅሰዋል።። ለምሳሌ፣ ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ ሲል ኀበ የቦታ ቅጽል ነው።። ትርጉሙም የ ነው።።
ወእደ ሲገባ ናክብር ወእደ ተሰቅለ እግዚእነ፣ /በኀላፊ ሲገባ/
ቅዱስ ውእቱ መካን ኀበ፣ ወእደ ይትገበር መሥዋዕት ይላል።። /በትንቢት ሲገቡ/።።
መንገለም ኀበ እና ወእደ በገቡበት ሁኔታ ይገባል።።

፲፯ኛ. እንጂ የሚሆኑ አገባባት

አላ፣ ዳእሙ፣ ባሕቱ፣ እንበለ፣ እስመ፣ አዲ እንጂ ይሆናሉ።። መነሻቸው በቀዳማይ በካልአይ፣ በነባር፣ በአገባብ፣ በግልሳይ፣ ሆኖ የአለታውን በጽድቅ፣ የጽድቁን በአለታ፣ የአንዱን በብዙ፣ የብዙውን

በአንድ፣ የወንዱን በሴት፣ የሴቱን በወንድ፣ የሩቁን በቅርብ፣ የቅርቡን በሩቅ፣ የገቢሩን በተገብሮ፣ የተገብሮውን በገቢር እያደረጉ ውጥን ይጨርሳሉ።። በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት ማሠሪያቸው አኮ፣ አልቦ፣ ኢ ናቸው።። በዐረፍተ ነገር ሲገቡም እንደሚከተለው ነው፤

አልቦ በመንግሥተ ሰማይ ምሥጢር ኀቡእ እምቅዱሳን አላ፣ ዳእሙ፣ ክሡት ለሙ ኩሉ።።

ኢሰዐረ እግዚእነ ሕገ ኦሪት ባሕቱ ፈጸመ

ኢፈነወ አብ ወልዶ ለኩነኔ ዓለም አላ፣ ዳእሙ፣ ባሕቱ ለሕይወተ ዓለም

ኢጸድቀ ይሁዳ ባሕቱ ሐዋርያት፣

ጸድቀ ኤልያስ ዳእሙ ኤልዛቤል፣

ኢመጽኡ ሐዋርያት በስቅለተ ወልድ ባሕቱ ዮሐንስ፣

በጽባሕ ጌሠት ማርያም መግደላዊት ኀበ መቃብር ዳእሙ ሐዋርያት፣

ኢርእያ አዋልድ ትንሣኤሁ ለወልድ ባሕቱ አንቲ መግደላዊት፣

ድንግል ኀዘንኪ በሞተ ወልድኪ ባሕቱ ቀያፋ፣

ኢርእየ ሙስናሃ አቤሜሌክ ፮ ዓመተ ባሕቱ ኢተርፈ ከመ ኖመ እስመ አንቅሆ ፈጣሪሁ።።

አኮ መልአክ ገብረ ሕይወት እስመ ሞተ በሥጋሁ ባሕቱ ኢወረደ ኀበ መቃብር እስመ ዐርገ ድኅረ ሞተ

ኢይመውት መፍቀሬ ነግድ ባሕቱ ቀታሌ ነፍስ

መሥዋዕት ኢኮነ ለሙ ለካህናተ ሐሰት፣ እስመ ኮነ ለቱ ለኤልያስ

እንበለ ተለይቶ ዘን፣ ዳእሙን በር ከፋች ይዞ ይነግራል።። በቀዳማይ በካልአይ በሰዋስው ሁሉ በሚገቡ አገባባት እየገባ ውጥን

ይጫርሳል፡፡ ዘ አዳማቂ ይሆነዋል፡፡ ለምሳሌ ኢ.ይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ፣
አልቦ ዘዐርገ ውስተ ሰማያት ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ ወልደ ዕጓለ ዕመሕያው
ኢ.ያንተጉ አይሁድ ዕርፈቶሙ እምድኅረ ዐርብ ዘእንበለ ዘወሰኩ
መኑ ውእቱ ሐሳዊ ዘእንበለ ዘይክሕድ ወይብል እስመ ኢየሱስ ኢኮነ መሲሐ ይላል፡፡ በአገባብ ሲገባ፣
ኢተሰቅለ ወልድ ከመ ያድኅን መላእክተ ዘእንበለ ከመ ያድኅን ሰብአ፡፡
ኢተወልደ አምላክ አመ ዳዊት ዘእንበለ አመ አውግስጦስ ቄሳር፡፡
ኢበጽሐ ሙሴ እስከ ኢየሩሳሌም ዘእንበለ እሰከ ደብረ ናባው፡፡
ኢተወልደ ወልደ በዘጸልአ ሰብአ ዘእንበለ በዘ አፍቀረ ሰብአ፡፡
ኢተሰቅለ ወልድ በእንተ መላእክት ዘእንበለ በእንተ ሰብእ፡፡
ኢነግሠ ሰሎሞን መጠነ ኬራም ዘእንበለ መጠነ ዳዊት፡፡
ኢተወልደ ወልድ ቅድመ ዮሐንስ ዘእንበለ ድኅረ ዮሐንስ፡፡
ኢተኀዘ ወልድ እንዘ ይሠርቅ ንዋየ ዘእንበለ እንዘ ይሰግድ፡፡
ኢኮነ ዮፍታሄ እምክረ ካልእ ዘእንበለእምክረ ባሕቲቱ፡፡
ኢቆመ ቃል ቅድመ ጢባርዮስ ዘእንበለ ቅድመ ጲላጦስ፡፡
ኢተሰቅለ ወልደ ምስለ ሐዋርያት ዘእንበለ ምስለ ፈያት፡፡
ኢሞተ ጴጥሮስ በሰይፍ ዘእንበለ በመስቀል፡፡
ኢሞተ ቃል አመ ተወልደ እም አብ ዘእንበለ አመ ተወልደ እምድንግል ይላል፡፡

በቀዳማይ በካልአይ በሣልሳይ በነባር በሰዋስው ሁሉ የሚገቡ አገባባት አላ፣ ዳእሙ፣ ባሕቱ፣ ባሉበት ቦታ ይሳባሉ፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት የሁሉም ማሠሪያቸው አኮ፣ አልቦ፣ ኢ ናቸው፡፡ ሙያቸው ማንፀሪያ ነው፡፡

፲፰ እንጂ፣ ም የሚሆን ዐቢይ አገባብ

ዓዲ እንጂ ፡ ም ይሆናል፡፡ ቀድሞ ተከትሎ ይነገራል፡፡ አላ፣ ዳዕሙ፣ ባሕቱ፣ በገቡበት ይነገራል፡፡ እንጂ ሲሆን ዋዌነቱ አይቀርም፡፡ አለታውን በጽድቅ ሲያናግር አኮ በመቁዶንያ ወአካይያ ባሕቲቱ ዓዲ በኵሉ በሐውርት፣፣ ያለታውን ውጥን በጽድቅ ሲጨርስ ምሕሮ ወአኮ ለዮ ለባሕቲቱ ዓዲ ሊተኒ፡፡ ዋዌ ሲሆን አኮ ክመ ሰንበተ ባሕቲቶ ዘይስእር ዓዲ አባሁ ይሬስዮ ለእግዚአብሔር ይላል፡፡

፲፱ እንጅ የሚሆን አገባብ

ባሕቱ እንጅ ይሆናል፡፡ እፎ፣ በእፎ፣ ለምንት መነሻ ይሆናሉ፡፡ እመ፣ ሶበ ቢ፣ ብ ሲሆኑ ይከተላል፡፡ ሲገባ ጴጥሮስ ጸድቀ ባሕቱ ይሁዳ ተኮነነ፣ ባሕቱ ተኮነነ ይሁዳ ይላል፡፡ ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ ስንኳን ሲሆኑ፣ ወ ድንበር ሲሆን ነገሩን እየከተተ ይነገራል፡፡ ሂ፣ ኒ አከላካይ፣ አሰናካይ፣ ገላጋይ ይባላሉ፡፡በዘርፍና በባለቤት በቅጽል መካከል ይነገራሉ፡፡ ሲነገሩም ብእሲሂ፣ ብእሲኒ መጽአ ይላል፡፡ ባሕቱ ነገር ግን ሲሆን ድንበር ከፋይ ይባላል፡፡ ከድንበርም ወዲያና ወዲህ ያለ ሰው እንዳይታይ ባሕቱም ሰዋስውን አያስተያያቸውምና፡፡ የድምጹ ጩኸት እንዲሰማ ምሥጢሩን አያርቅምና፡፡ ለምሳሌ ቦአ ውስተ ቤት፡ ባሕቱ ወጽአ ሲል የሚወጣው የሚገባው ነውና፡፡

ዐበይት አገባባት መነሻ እየሆኑት ይነገራሉ፡፡ ለምሳሌ ቆጥሮስ ነጋዲ ኢቦአ ብሔሮ እስመ ጽዑናን አግማሊሁ ባሕቱ እንዘ ያስተባዝኅ ንዋዮ፣ እንዘ ያስተባዝኅ ተርፈ፡፡ ይህ በአገባብ ላይ ሲወድቅ ነው፡፡ በተሳቢ ላይ ሲወድቅ ባሕቱ ንዋዮ እንዘ ያስተባዝኅ ተርፈ ይላል፡፡

፭ኛ. ማለት የሚሆን አገባብ

ብሂል ዐቢይ አገባብ እንደ ሆነ የተጠቀሰው በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ነው፡፡ በዋድላ አገባብ ግን ብሂል ደቂቅ እንጂ ዐቢይ አገባብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ብሂል አንቀጽ ይስባል እንጂ አንቀጽ እንዳያሥር አያስቀርም፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዐቢይ አገባብ ሲሆን ትርጉሙ ማለት ይሆናል፡፡ የብሀለ እና የይቤ ራስ ነው፡፡ ብሂል ሦስት ነገር ይሆናል፡፡ እነርሱም አገባብነት፣ አንቀጽነት፣ ሰዋስውነት ናቸው፡፡ ብሂል ቀድሞ፣ ተከትሎ፣ አርፎ፣ ተናቦ ይገባል፡፡ ለምሳሌ፤

ብሂል ሠረቀ፤ ብሂል ተወልደ፡
ሠረቀ ብሂል፤ ተወልደ ብሂል፡
ብሂለ ሠረቀ፣ ብሂለ ተወልደ ውእቱ፡
በካልኣይና በሣልሳይ ይገባል፡፡
ብሂለ ይሠርቅ ኮከብ እምያዕቆብ፡
ብሂለ ንበር በየማንየ፡
ብሂል በነባርም ይገባል፡፡ ለምሳሌ፤
ብሂል ቦ ትንሣኤ ሙታን ብሂል ቦ ሕይወት እምድኅረ ሞት፣
በብሂለ አብ ብነ ይላል፡፡

በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት፣ ዘማች አንቀጽና ነባር አንቀጽ እንዳያሥሩ በአገባብነቱ ይከለክላል፡፡ ለምሳሌ፤

ብሂል ከፈለ ሙሴ ባሕረ፡ ብሂል ዐደወ ብንያም ባሕረ ለሊቅ፡

ብሂለ ብሂል ተወልደ አምላክ እማርያም ለሊቅ ይላል፡፡ በዋድላ አገባብ መሠረት ደግሞ የተጠቀሱት ምሥክሮች አንቀጽን የሚስቡ እንጂ አንቀጽን የሚያስቀሩ አይደሉም፡፡
በዘመናዊ የአማርኛ ትምህርት አሰጣጥ አብዛኛዎቹ ዐበይት አገባባት መስተጻምር ይባላሉ፡፡ የመስተጻምር ሥራ ቃላትን፣ ሐረግን፣ ወይም ዐረፍተ ነገርን በማገናኘት ማጣመርና አንድ ዐረፍተ ነገር ማድረግ ነው፡፡ የዐቢይ አገባብ ባሕርይ በአጠቃላይ ሲታይ አንድ አንቀጽ በወደቀበት ቦታ እንዳያሥር አድርጎ ሁለት ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ዐረፍተ ነገሮችን አንድ ዐረፍተ ነገር ማድረግ ነው፡፡ የመስተጻምር ሥራም ይሄው ነው፡፡

፭፩ ቅጽል የሚሆኑ ዐበይት አገባባት፣

ዐበይት አገባባት ከዚህ እንደሚከተለው በየቦታቸው ቅጽል እየሆኑ ያገለግላሉ፡፡

፩፡ እንተ፣ ዘ፣ እለ የ በሚል ትርጉም ለሁሉም ነገር ቅጽል ይሆናሉ፣
፪፡ ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ ለቦታ ቅጽል ሆነው ያገለግላሉ፣
፫፡ መጠነ፣ አምጣነ፣ ዐቅመ ለልክ ወይም ለስፍር ቅጽል ይሆናሉ፣
፬፡ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ፣ ዕለተ፣ ዓመተ፣ መዋዕለ ለጊዜ ቅጽል ይሆናሉ፣
፭፡ ከመ፣ በዘ ለነገር ቅጽል ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ በከመ ፈቀደ ይገብር ሲል የፈለገውን ያደርጋል ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ከመ ቅጽል ነው፡፡

ተፈጸመ ዐቢይ አገባብ፡፡

፷፥፪፥ ደቂቅ አገባብ

ደቂቅ አገባብ ደቂቅ መባሉ ስለምንድን ነው ቢሉ እንደ ዐበይት አገባባት በዐበይት አናቅጽ እየወደቀ ማሠሪያነትን ስለአላስቀረ ነው። ታዲያ አገባብ መባሉ ለምንድን ነው ቢሉ ዐበይት አገባባት በአናቅጽ እንደሚወድቁ ደቂቅ አገባብም በሰዋስው ላይ እየወደቀ ማድረጊያ፣ መነሻ፣ መገስገሻ፣ መድረሻ፣ አቀባይ፣ ተሳቢ፣አንጻር፣ አስፈች፣ አቃላይ፣ አዘውታሪ፣ አንጻር አብነት፣ ተፎካካሪ፣ ተወዳዳሪ ስለሚሆን ነው። ደቂቅ አገባብን በአራት ዘርፍ ከፍሎ ማየት ይቻላል። እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

፩. ዐቢይ አገባብ ሆነው ደቂቅ አገባብን የሚደርቡ፤
፪. ፍጹም ደቂቅ አገባብ የሆኑ፤
፫. ለጊዜ ቅጽልና በቂ የሚሆኑ፤
፬. ለቦታ ቅጽልና በቂ የሚሆኑ ዘርና ነባሮች፣ ናቸው ከላይ ከተጠቀሱት መካከል ማድረጊያ፣ መነሻ፣ መገስገሻ፣ መድረሻ፣ አቀባይ፣ አንጻር፣ አስፈች፣ አቃላይ፣ አዘውታሪ የሚሆኑ በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ የተጠቀሱት ብቻ ሲሆኑ እያንዳንዱ አገባብ በዐረፍተ ነገር በሚገለጽበት ጊዜ ሰዋስዋዊ ትርጉሙ ከፍችው ጋር የሚስማማ ሙያ ይሰጠዋል ማለት እንጂ ሁሉም ሁሉን ይሆናሉ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ጎበ፣ መገስገሻ፣ እም መነሻ፣ እስከ፣ መድረሻ በ፣ ማድረጊያ

ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ደቂቅ አገባብ በባሕርዩ ውስብስብና በርካታ ነገሮችን አጠቃሎ የያዘ ስለሆነ በሰከነ አእምሮ ረጋ ብሎ ማንበብና መረዳት ይጠይቃል፡፡ ዝርዝሩ በቅደም ተከተል ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

፩. ዐቢይ አገባብነትን የሚደርቡ ደቂቅ አገባባት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

በእንተ በይነ ህየንተ ተውላጠ ዐስበ
ፍዳ ኀበ መንግለ ወእደ እንበለ
መጠነ አምጣነ ዐቅመ ከመ ሕገ
አርአያ አምሳለ እስከ አመ ሶበ
ጊዜ ዓመተ ዕለተ መዋዕለ ለለ
ዘ/እንተ እለ ድኅረ

፪. ፍጹም ደቂቅ አገባቦች፤

ላዕለ መልዕልተ ዲበ ታሕተ መትሕተ
ውስተ ውሳጤ ቅድመ ማዕከለ አፍኣ
ለ በ ምስለ በበ ዘዘ
ቤዛ ዕሴተ ተክለ ዐይነ ግእዝ

፫. ለቦታ ቅጽልና በቂ የሚሆኑ ዘርና ነባሮች፣

ላዕለ ላዕል መልዕልት መልዕል ላዕሊት
ለዓሌ ልዕልና ታሕት ታሕቴ መትሕት
ታሕቲት ትርአስ ትርጋጽ ውሳጢት
ውሳጤ ቅድም ፍጽም ገጽ
አንጻር መንጸር መልታሕት ከዋላ
ድኅር ድኅሪት ግንጽሊት ግፍትዒት
ቁልቁሊት የማን ይምን ፀጋም
ዕግም አክሊል ሕንብርት ማዕከል
ምዕያም ጽንፍ ጽነፍ አጽናፍ ጽንፈ
ጽነፈ ጸናፈ ክንፍ ክነፍ ክንፈ፣ ክነፈ አክናፍ
ሐይቅ ወሰን ከንፈር ድንጋግ አድያም ደወል
ብሔር ጥቃ ገቦ ሕፅን ጎር ጕንድ ጽጕ
ጽጎጕ ግድም ዝየ ከሃ ሕየ ለፌ ኑኅ

ዐውድ ዘውር ኵለሄ ኀበኵሉ ኵለንታ አካል አባል ሕዋስ መንፈስ ነፍስ ነፍስት ባሕርይ ጠባይዕ ህላዌ መሊሊት ውስተ ለ በ ዘ እንተ ግእዝ

፬. ለጊዜ ቅጽልና በቂ የሚሆኑ ዘርና ነባሮች ፡፡

ሁሉም በዐረፍተ ነገር እየገቡ የሚገልጹት ጊዜን ነው፡፡

ቅድም ቀዲሙ አቅዲሙ ቀዳሚ መቅድም ድኅር ደኃሪ ድኅሪት ወ በ ወርኀ ፍና ብሔር አፈ ፍጽም አኀዝ ጥንት መሠረት ፍጻሜ ተፍጻም ተፍጻሜት

ትካት ትማልም ዓለም አስፈር አሜር የም ኀሪፍ ገሪፍ ጌሠም ሳኒታ ይእዜ ዓዲ ናሁ ካዕበ ዳግመ እንከ እም ዮም እምይእዜ ንዕስ ናዕስ ንዕስና ርሥእ ርሥእና ርሥአን አንጻር መንጸር ኵለሄ ኩሎ ጊዜ ኩሎ ሰዓ ኩሎ ሰዓት ኩሎ አሚረ ኩሎ ዘመነ ወትር ዘልፍ ውቱረ ዝለፉ ለዝላፉ ዘልፈ ወትረ ኩለሄ ኀቡረ ደርገ ድርገተ መፍትው ፍትሕ ርትዕ ርቱዕ ድልወት ኩነት ጽድቅ ውርዙት ውርዛዌ ወዘተ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ደቂቅ አገባቦች መካከል የቦታና የጊዜ ዘርና ነባሮች መጠቀሳቸው ይታወሳል፡፡ ከእነዚህ የቦታና የጊዜ ዘርና ነባሮች መካከል አንዳንዶቹ በዐረፍተ ነገር ሲገቡ መድረሻቸውን ይለውጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እስከ መጨረሻው በመድረሻቸው ላይ ለውጥ አያመጡም፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ላይ በዝርዝር ተገልጸዋል፡፡

፩ መሠረታቸው ዐቢይ አገባብ ሆኖ ደቂቅን የሚደርቡ አገባባት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩ ስለ የሚሆኑ አገባባት

ስለ የሚል ትርጉም ያላቸው ተመርጠው ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል። እነርሱም በእንተ፣ ህየንተ፣ በይነ፣ ተውላጠ፣ ፍዳ፣ ዐስበ ሲሆኑ ዐቢይነታቸው በዐቢይ አገባብ ተነግሯል። እዚህ የሚነገረው ደቂቅነታቸው ብቻ ነው። ትርጉማቸው ስለ ነው። ። በሰዋስው ሁሉ ማለትም በስም፣ በነባር፣ በግብር፣ በአካል፣ በጥሬ ይገባሉ። ዝርዝር አጠቃቀማቸው ከዚህ እንደሚከተለው በምሥክር ቀርቧል።

፩ በእንተ ስለ ሲሆን የበነ፣ በ ሲሆን የክፉ ነው። ደስ አይበለው ብሎም ይሆናል። በእንተ ይሁዳ ወበእንተ ኢየሩሳሌም ሲል ስለይሁዳና ስለ ኢየሩሳለም ማለት ነው። በእንተ ዲያብሎስ መሐረነ ለሕዝብከ ሲል ዲያብሎስን ደስ አይበለው ብለህ ይቅር በለን ማለት ነው። ይህ ለፍጹማን እንጅ ለሁሉም አይሆንም።

በእንተ ጸላዕትየ አርትዕ ፍኖትየ ቅድሜከ ሲልም ጠላቴን ደስ አይበለው ብለህ መንገዴን አቅና ይላል። በእንቲአሁ ብሎ በእንቲአነ እስኪል በባዕድ ይዘረዝራል።

፪ በእንተ፣ በይነ፣ ህየንተ፣ በአርእስት፣ በስም፣ በቦታ፣ በግብር በብትን፣ በደቂቅ ቅጽል፣ በንኡስ አገባብ ይገባሉ። በአርእስት ሲገቡ በእንተ/ በይነ አፍቅሮቱ ሰብአ በጽሐ ለሞት ይላል።

በቦታ ሲገቡ ተቀትለ ናቡቴ በእንተ/ በይነ አፀደ ወይኑ ይላል።

፫ በይነ በግብር ሲገባ ጻድቅ ይፀንሕ ተስፋሁ በይነ ፃማሁ። ወበይነ ዝንቱ ኢዐርጉ ገነውቱ ለዳጎን ውስተ ምዕራግ ይላል።

፬ ህየንተ ሲገባ ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ፣ ተቀነየ ያዕቆብ ህየንተ ራሔል ፯ተ ዓመተ ይላል፡፡ ህየንተ፣ ህየንቴሁ፣ ህየንቴክ እያለ በዐሥር ሠራዊት ይዘረዝራል፡፡
፭ ተውላጠ ለውጥነት ባለው ነገር ሲገባ ረክበ ሚመተ ተውላጠ ዕርገቱ ወተቃትሎቱ
ይላል፡፡ በአገባብነቱ በባዕድ ይዘረዝራል፡፡ ለምሳሌ ተውላጢሁ፣ ተውላጢክ፣ ተውላጢነ እስኪል ድረስ ይዘረዝራል፡፡ በሰዋስውነቱ በዐሥር ሠራዊት ማለትም ተውላጡ፣ ተውላጥክ፣ ብሎ ተውላጥነ እስኪል በዘመድ ይዘረዝራል፡፡

፮ ፍዳ ብድርነቱን ሳይለቅ ስለ ሲሆን ፍዳ ወይን ይስተይ ማየ ዝናም ይላል፡፡ ፍዳሁ፣ ፍዳሆሙ፣ ፍዳሃ፣ ፍዳሆን፣ ብሎ በባዕድ ይዘረዝራል፡፡

፪. ወደ፣ ወዳ፣ አጠገብ፣ ዘንድ የሚሆኑ አገባባት

ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ፣ እንተ፣ ዘ፣ እም፣ ወደ ወይም ወዳ ይሆናሉ፡፡ ኀበ መንገለ ወእደ በስም በግብር ይገባሉ፡፡ የቀሩት በቦታ ይገባሉ፡፡ በዐረፍተ ነገር ሲገቡም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፤
ወደ ሲሆኑ፣
ሐሩ መንገለ መስዕ፣
ቃል ዘኮነ ኀበ ኢሳይያስ፣
እቱ ወእደ ሕዝብክ፣
ወተመየጥኩ መንገለ የማንየ፣
አንሰ አሐውር መንገለ ዮርዳኖስ እስመ ለአከኒ እግዚአብሔር፣
ሖረ ኀበ አብ፣
ሖረ እንተ ካልእ ፍኖት፣
ወይኔጽር እንተ መሳክው፣
ሖረ ባሕታዊ እንተ ገዳም፣

ተፈነወ ሙሴ ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ ፈርዖን ይላል።።
ሖረ እንተ፣ ዘ፣ ገዳም፣ ኀለፈ እንተ፣ ዘ፣ ቀራንዮ ይላል
አጠገብ ሲሆኑ፣
ነበረ ኀበ ዐዘቅት፣
ወአኀዘ ይምሀሮሙ በመንገለ ባሕር፣
ዘንድ ሲሆኑ፣
ኦ ድንግል አዘክሪ ኀበ መዘክር ወልድኪ፣
እንተ ሀለወት ኀበ አብ ይላል።።
ከወእደ በስተቀር ሁሉም በባዕድ ይዘረዝራሉ።።

፫ ያለ፣ በቀር የሚሆን አገባብ፣

እንበለ፣ ያለ፣ በቀር ይሆናል።። ለምሳሌ አልቦ ኄር እንበለ አብርሃም ይላል።። እንበለ የጽድቅ አሉታ ነው።። እንበለ ደቂቅ ሲል ከአሉታ ይደርሳል።። እንበለ መጠን ሲል ከልክ ያሳልፋል።። እንበለ ግብር ሲል ሥራ ፈች ያደርጋል።።
እንበለ፣ ዘ እያጋነነውም ሆነ ሳያጋንነው ያለ ይሆናል።። በስም፣ በብትን ሰዋስው ሁሉ ይገባል።። በተጨማሪም፣ በቀር፣ አለ፣ ያለ፣ እንጅ ይሆናል።። ሲገባም፣ በአሉታና በከፊል ይገባል።። ለምሳሌ፣
ወኢታገምር ፍኖታ ዘእንበለ አሐቲ ኪደተ እግር፣
አልብነ ዝየ ዘእንበለ ኀምስ ጎብስት ይላል።።
በከፊል ሲገባ፣
ወተዘርዉ ኵሎሙ ዘእንበለ ሐዋርያት ይላል።።
በስም ሲገባ፣ አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሳር፣
አልቦ ኄር ዘእንበለ አብርሃም ይላል።።
እንበለ፣ እም የጽድቅ አሉታ ናቸው።። ለምሳሌ እንበለ ጽድቅ ሲል ከአሉታ ያደርሰዋል።። እንበለ መጠን

ሲል ከልክ ያሳልፈዋል፡፡ እንበለ ግብር ሲል ሥራ ፈት ያደርገዋል፡፡
እም ሲገባ፣ ወጽአ ንጉሥ እምጽርሑ /ከቤት የሌለውን ነው/፡፡
እንበለ ሳይዘረዘር በአራት ሩቆች እንበለ ብእሲ፣ እንበለ እደው፣ እንበለ ብእሲት፣ እንበለ አንስት ይላል፡፡ በ፲ ሲዘረዘር እንበሌሁ፣ እንበሌክ፣ ፣ እንበሌሆሙ፣ እንበሌክሙ፣ እንበሌሃ፣ እንበሌኪ፣ እንበሌሆን፣ እንበሌክን እንበሌየ፣ እንበሌነ ይላል፡፡

፬ ያህል፣ ልክ፣ ስፍር፣ ቁጥር የሚሆኑ አገባባት

አምጣነ፣ መጠነ እና ዐቅመ ያህል፣ ልክ፣ ስፍር፣ ቁጥር የሚሆኑ አገባባት ናቸው፡፡
በልብስ ሲገባ ለብሰ ሕፃን አምጣነ ቆሙ፣ መጠነ ቆሙ ዐቅመ ቆሙ /ጸምረ/ ይላል፡፡
በስፍር ሲገባ፣ ኢያእመረ ሰሎሞን አምጣነ ብዕለ፣ መጠነ ብዕለ፣ ዐቅመ ብዕለ ይላል፡፡
በቁጥር ሲነገር፣ ኢያእመረ አብርሃም አምጣነ ወርቁ፣ መጠነ ወርቁ፣ ዐቅመ ወርቁ ይላል፡፡ አምጣኒሁ፣ አምጣኒክ፣ አምጣኒሆሙ፣ አምጣኒክሙ፣ አምጣኒሃ፣ አምጣኒሆን፣ አምጣኒክን፣ አምጣኒነ ብሎ በ፷ በባዕድ ይዘረዝራል፡፡

፭ እንደ፣ እንዳ፣ የሚሆኑ አገባባት

ከመ፣ ሕገ፣ ህየንተ፣ አርአያ፣ አምሳለ፣ እንደ፣ እንዳ፣ ይሆናሉ፡፡
ሕገ በግብር፣ በተቀብዖ፣ በተጸውዖ፣ በባሕርይ ስም ይገባል፡፡
ከመ በስም፣ በግብር፣ በብትን ቃል ሁሉ እየገባ እንደ ይሆናል፡፡ ምሥጢሩ አንጻርነት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ተቀስፈ ከመ ገብር፣ ወተሰቅለ ከመ እቡስ፣ ከመ በግዕ የዋህ፡ ወከመ ላሕም ንጹሕ፣

ኮንኩ ከመ ድምፀ ብርት ዘይነቁ፡ ወከመ ከበሮ ዘይዘበጥ ይላል፡፡ ሁለተኛም፣ በስም እየወደቀ ነባር አንቀጽን ያስመረምራል፡፡ በስም ሲገባ፣ ተሰቅለ ጴጥሮስ ከመ ክርስቶስ፣ አዕንቲሁ ከመ ነደ እሳት፣ ርእሱ ድሉል ወፀሊም ከመ ቋዕ፣
ሰማዕነ ኢያሱ ከመ ሙሴ በኦሪት፣ ወጳውሎስ ከመ ጴጥሮስ በወንጌል ይላል፡፡
ምፀት ሲሆን እምአፍቀርኩ ይሙት/ እመ ይመውት ጻድቅ ከመ ኪሩብ ይላል፡፡
መከታም ሲሆን እግዚኦ ከመ ወልታ ሥሙር ከለልከነ ይላል፡፡
በግብር ሲገባ ነስሕ እንከ ወእመሰ ኢተጋህከ እመጽአከ ግብተ ከመ ሰራቂ ይላል፡፡
ሕገ በተፈጥሮ ስም፣ በግብር ይገባል፡፡ በተፈጥሮ ስም ሲገባ፣ ሕገ ሚካኤል፣ ተሐረመ ዕክለ ገብረ ሕይወት ፡፡
ሕገ ካህን ሌወወ ሐራዊ፡ ይላል፡፡
ህየንተ በተቀብያ፣ በተፀውኦ ስም ይገባል፡፡
በተቀብያ ሲገባ፣ ህየንተ ጴጥሮስ ዘተውህቦ ሥልጣን አልቦ፡፡
በተፀውኦ ስም ሲገባ፣ ህየንተ አብርሃም፣ አልቦ ባዕል በዲበ ምድር ይላል፡፡
አርዓያና አምሳለ በሰዋስው ሁሉ ይነገራሉ፡፡ ለምሳሌ አርዓያ ገብር፣ አምሳለ ገብር ተሰይጠ እግዚእ በማለት በብትን ሰዋስው ይገባሉ፡፡

፮ ከ፣ የሚሆን አገባብ፣

እም ከ ይሆናል፡፡ በነገር በግብር በሰዋስው ሁሉ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ በግብር ሲገባ እምነ ካህን ይኄይስ ኖላዊ ይላል፡፡
በነገር ሲገባ እምአብዝኖ ነገር ይትነሣእ ጸብእ ይላል፡፡
እም በሰዋስው ሁሉ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ፣

ተንሥአ እምድር፣ ወጽአ እምሀገር ይላል፡፡
እንዲሁም እምዘመን ይ፞ኄይስ ዘመን ይላል፡፡
በተጨማሪም እም ጀምሮ፣ ወዲያ፣ ወዲህ፣ ኋላ፣ ይልቅ፣ እኩል፣ የተነሣ ይሆናል፡፡ በሰዋስው ሁሉ ይወድቃል፡፡ ተለዋጭ፣ ተከፋይ፣ መገኛ፣ ሰጪ፡ ተወላጅ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ጀምሮ ሲሆን፣

ቦ ግዝረት እም አብርሃም እስከኔነ፣
እምኢየሩሳሌም እሰከ ግብፅ፣
እምአጽናፍ እስከ አጽናፍ፣
እምአዳም እስከ ሙሴ፣
እምትንሣኤ እስከ ዕርገት ይላል፡፡
ኋላ ሲሆን ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ገዳመ ይላል፣
ወዲያ፣ ወዲህ ሲሆን ኢ፟ያብርሀ ፀሐይ እምአድማስ፣ አላ እምአድማስ ይላል፣
ይልቅ ሲሆን ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል፣ ወትፈደፍድ እምሱራፌል ይላል፡፡
ተወላጅ ሲሆን ተወልደ ቃል እምድንግል ይላል፡፡

መገኛ ሲሆን መጽአ ቃል እምደመና፣ ተሰብከ ወንጌል እምዮሐንስ ይላል፡፡
ሰጪ ሲሆን ተውህበ ወርቅ እምንጉሥ ለወዐሊሁ ይላል፡፡
ያለግሱ የተነበበ እም በቦዝ አንቀጽ ቀንቶ ይፈታል፡፡ ለምሳሌ ዜነዋ ለማርያም ገብርኤል እምእግዚአብሔር ሲል ከእግዚአብሔር ተልኮ ተብሎ ይፈታል፡፡

ለዘሐወፀነ እምአርያም፣
ተንሥአ እሙታን፣
ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እምሰማያት፣
እምከርስ ስሕቱ ወነበቡ ሐሰተ
አድ፞ነነ ዓለመ አምላክ እም ድንግል ይላል፡፡
በተወልዶ እንደተሳበ አስተውል፡፡ /በውስጡ ተወሊዶ የሚለው ቦዝ አንቀጽ አለ ማለት ነው/፡፡

ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ ፈለሰት እምዘይበሊ ጎበ ኢይበሊ ይላል።።

እም ይልቅ፣ እጅግ ሲሆን ይትበደር ሰብእ እምዕንቁ ክቡር ይላል።።

የተነሣ ሲሆን መንገለ በር ከፋች እየሆነው ይገባል።። ለምሳሌ ሰቀልዎ አይሁድ ለእግዚእነ እመንገለ ቅንዐቶሙ ይላል።።

እኩል ሆኖ ሲሆን፣

ነጋዲ ወጽአ እምአእዱጊሁ፣
መምህር መጽአ እምአርዳኢሁ፣
አልቦ ንጹሕ እማርያም /ከማርያም እኩል ንጹሕ የለም/ ይላል።።

እም በሰባት ፊደላት ሲገኝ አይናበብም።። ፊደላቱም ሰ፣ በ፣ ገ፣ ጠ፣ ጸ፣ ጸ ፈ ናቸው።። እም ከከመ ጋራ እየተናበበ እንደአጻፋ የመጨረሻ ቀለም ያስቀራል።። እም ምልዐት ሕጸጽ አለው።። ምላቱ እንደ ዐመፀኛ፣ ሕጸጹ እንደ አርበኛ ነው።። በሕጸጹ በሰዋስው ሁሉ ሲነገር ብኤልፈጎር፣ ብኤልዜቡል፣ ዮርዳኖስ፣ ኢየሩሳሌም ያለውን ይመስላል።። ምላቱ ግን በሰባት ፊደላት ይስማማል።። ሲነገርም፣ እምነ ሰማይ፣ እምነ ቤቱ፣ እምነ ግብር፣ እምነ ጴጥሮስ፣ እምነ ጽዮን፣ እምነ ፋሲካ ማለቱን ያሳያል።። መጻሕፍት በሕጸጽ ይገበብታል።። መምህራን ግን ሙጫ ጸያፍ ነው ለቅኔ አይሆንም ብለው አውጀዋል።። እም ከከመ ጋራ ሲነበብ እስከ ሳብዕ ድረስ ይገባል።።

እም ነን በር ከፋች ይዞ በ፤ ይዘረዘራል።። ለምሳሌ እምኔሁ፣ እምኔከ፣ እምኔሆሙ፣ እምኔክሙ፣ እምኔሃ፣ እምኔኪ፣ እምኔሆን፣ እምኔክን፣ እምኔየ፣ እምኔነ ይላል።።

በጎንጅ አገባብ እም በተጨማሪም ወዲያ፣ ወዲህ፣ ይልቅ፣ የተነሳ፣ ጀምሮ፣ ከፍሎ፣ አስከፍሎ፣ አውጥቶ፣ አውርዶ፣ ለይቶ፣ አሻሽሎ፣ ቀድሞ፣ አስቀድሞ፣ መርጦ፣ አስመርጦ ይሆናል።። ወዲያ ሲሆን ከመን ይዞ ነው።። ወዲህ ሲሆን ደግሞ አመን ይዞ ነው።።

በስም፣ በግብር፣ በቦታ፣ በቦዝ አንቀጽ ይገባል። በቦዝ አንቀጽ ይፈታል ማለት ራሱ በቦዝ ላይ ይወድቃል ማለት አይደለም።

፮ እስከ፣ እስኪ የሚሆን አገባብ፣

እስከ፣ በቁም ቀሪ አገባብ ነው። በራሱ ፍቺ ይፈታል። ድረስ የሚለውን የመድረሻ ቃል እየጨመረ መድረሻ፣ ፍጻሜ እየሆነ በቦታ፣ በጊዜ፣ በልክና በክፍል ይገባል። በተጨማሪም ብዝኀ፣ ጽንእ ይሆናል። ብዝኀ ሲገባ፣

እስከ ማእዜኑ ይትዔበዩ ጸላእትየ ላዕሌየ ይላል።
ጽንእ ሲገባ እስከ ማእዜኑ ይልህቅ ወልድየ ይላል።
በቦታ ሲገባ፣ እስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ፣
እምሥራቀ ፀሐይ እስከነዐረብ፣
አውጽኦሙ አፍኣ እስከ ቢታንያ ይላል።
እስከ በጊዜ ሲገደብ፣
እስከ ዐሠርቱ ወኀምስቱ ዓመት ትጠፍዕ መንግሥተ ኤፍሬም፣
ንስማዕ ዘንተ ቃለ እስከ ነፍስ ደኃሪት፣
እምዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ይላል።

በትርፍ አማርኛ በአይ፣ በማእዜ፣ እየገባ መመኘት፣ መወግሸት፣ መሰልቸት ይሆናል። መመኘት ከመ ጽንእ ነው። መወግሸት ሲገባ እስከ ማእዜኑ እረግዞ ለጸርየ ይላል። መሰልቸት ከመ ብዝኀ ነው። ማሠሪያው ይቤ ነው። በነባር በግብር ሲገባ ከለ ላይ እየወደቀ በጽሐን ያመጣል። በሰዋስው ይገባል።

ለምሳሌ ይቤ ነዳይ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት ይላል።።
ነ፣ ጎበ በር ከፋች እየሆኑት በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራል።። ለነገሩ በር ከፋች ጎበ ነው።። ነ ግንዘቡ ነው።። ሲዘረዝር እስከጎቤሁ እስከኔሁ፣ እስከኔከ፣ እስከኔሆሙ፣ እስከኔክሙ፣ እያለ እስከ ፲ ይዘረዝራል።። እስከ ጎቤሁ፣ እስከ ጎቤከ ወደእርሱ እስኪሆን ድረስ ተብሎ ይፈታል እንጅ በር ከፋች አይሆንም።።

፰ ጊዜ፣ ዘመን የሚሆኑ አገባባት፣

አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ፣ ሰዓተ፣ ጊዜ፣ ይሆናሉ።። ዐመተ፣ መዋዕለ፣ ዘመን፣ ይሆናሉ።። በሰዋስው ሁሉ ይነገራሉ።። አመ፣ ሶበ በንዑስ አንቀጽ በሳቢ ዘር፣ በጥሬ ዘር፣ በብትን ሰዋስው ሁሉ ይገባሉ።።
በንዑስ አንቀጽ ሲገባ፣ አመ ተንሥኡ እመቃብር ይላል።።
በሳቢ ዘር፣ አመ ሲገባ ወአመ ምጽአቱሰ ለወልደ ዕጓለ ዕመሕያው ይላል።።
ሶበ በሳቢ ዘር ሲገባ፣ ኤልያስ ባረኮ ለኤልሳዕ ረድኡ ሶበ ዕርገቱ ውስተ ሰማይ ይላል።።
ሶበ በንዑስ አንቀጽ ሲገባ፣ በራኮ ኤልያስ ለኤልሳዕ ረደኡ ሶበ ዐሪጎቱ ውስተ ሰማይ።።
ሰዓተ የሰዓ ብዛት ይሆናል።። ዘሩ ሰዓ፣ ሳዕ ነው።። የሰዓ ዝርዝር ሰዓሁ፣ ሰዓከ፣ ሰዓሆሙ፣ ሰዓክሙ፣ ሰዓሃ፣ ሰዓኪ፣ ሰዓሆን፣ ሰዓክን፣ ሰዓየ፣ ሰዓነ ነው።። የሳዕ ዝርዝር፣ ሳዑ፣ ሳዕከ፣ ሳያሙ፣ ሳዕክሙ ሳዓ፣ ሳዕኪ፣ ሳያን፣ ሳዕክን ሳዕየ፣ ሳዕነ ነው። እያለ በሰዋሰውነቱ በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራል።። ፍጹም ሰዋሰው ነው።። ደቂቅ አገባብነት የለውም።። የሚመደበው ከጊዜ ጥሬዎች ነው።። ዓመተ፣ መዋዕለ፣ ዕለተ ሲገቡ በን እየያዙ፣ ሳይዙም ጊዜ ይሆናሉ።። በአማርኛቸው ሲፈቱም ምሥጢራቸው ከጊዜ አይወጣም።። ለምሳሌ፣

ለምሳሌ፣

ሰዓተ ንጉሥ፣ በሰዓተ ንጉሥ ይትገበር ኩሉ ይላል።።

አመ ሰሎሞን፣ ዓመተ ንጉሥ፣ መዋዕለ ንጉሥ፣ በአመ ሰሎሞን፣ በዓመተ ንጉሥ፣ በመዋዕለ ንጉሥ ይትፌሣሕ ነዳይ።።

በመዋዕለ ሰላም፣ በመዋዕለ ቀትል፣

ሰዓ ጽባሕ፣ በሰዓ ጽባሕ፣ በሰዓተ ጽባሕ ይላል።።

አመ፣ ሶበ በሩቅ ወንድ እና በሩቂቱ ሴት አጻፋ ይሆናሉ።። በዚህ ጊዜም ስድስት አገባባት ይስማሟቸዋል።። እነርሱም ለ፣ በ፣ እም፣ እስከ፣ ዘ፣ ከመ ናቸው።። ለጊዜ ነው አንጅ ለሰው አይቀጸሉም።። አሜሃ፣ ሶቤሃ ብሎ ይዘረዝራል።። ከአገባባት ጋር በዐረፍተ ነገር ሲገቡም እንደሚከተለው ነው፣

ለሶቤሃ ዕለት፣ ለአሜሃ ዕለት፣ በአሜሃ ዕለት፣ በሶቤሃ ዕለት፣ እምአሜሃ ዕለት፣ እስከ አሜሃ ዕለት፣ ዘአሜሃ ዕለት፣ ከመ አሜሃ ዕለት ወዘተ ይላል።።

አመ በአጻፋ ሲገባ ቦ ትካት ብእሲ ዘይሰመይ ኖኅ ወአመ አሜሁ፣ ወበአሜሁ ዘመን ዘንመ ማየ አይኅ ይላል።።

ሳይዘረዝሩም አሜ፣ ሶቤ፣ ሲለ ጊዜ ተብለው ይፈታሉ።። ለምሳሌ፣

ዘአሜ ልደቱ ለክርስቶስ ሰገዱ ሰብአ ሰገል፣

ይትፌሥሑ ጻድቃን አሜ ሞቶሙ፣

አእመኖሙ ሶቤ፣

ወይእተ ሶቤ ይላል።።

ወለአሜሃ ዕለት ዘየዐብያ አልቦ ወበአሜሃ ፣ ወምስለ አሜሃ፣ ወእምአሜሃ፣ ወእስከ አሜሃ፣ ወድኅረ አሜሃ፣ ወቅድመ አሜሃ፣ ይላል።።

ብቻቸውን ሲፈቱም፣ ያን ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ፣ ወዲያውኑ፣ ፈጥኖ፣ ቶሎ፣ ይሆናሉ።። ምሥጢራቸው አጻፋነት ነው።። ዘይቤአቸውም ጊዜው፣ ጊዜዋ ያሰኛሉ።።

፱ እየ፣ እያ የሚሆኑ አገባባት፣

ለለ፣ ዘዘ፣ እንተ፣ እየ ይሆናለ። ሲገቡም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣
ለለ፣ ኵሉ ሰብእ የሐውር ለለብሔሩ፣
አደዉ እስራኤል ለለሠለስቱ ነገድ ባሕረ ኤርትራ ይላል።
ለለ በሰዓት በዘመናት ይዘረዝራል። ለምሳሌ ለለሰዓቱ፣ ለለዘመኑ፣ ይላል። በአጎዝም ይገባል። ለምሳሌ ተዘከር እግዚኦ ለለአሐዱ አሐዱ ስዕለቶ ይላል።
ዘዘ፣ እንተ፣ እለ በደቂቅ አገባብነት ሲነገሩ፣ አገባባቸው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።
ዘዘ፣ ደቂቅ አገባብ ሲሆን እየ፣ እየ እየ፣ ይሆናል። ምሥጢሩ ልዩ፣ ልዩነት ነው። ሲገባም፣
ወአጎዙ ይንብቡ ዘዘ ዚአሆሙ /እየራሳቸው፣ እያንዳንዳቸው/ ይላል።
በደኂመ ቃል እየራስ እየራሳቸው ያሰኛል። ለምሳሌ፣ ይፈልጦሙ ዘዘ ዚአሆሙ፣
አስተራሐቅዎሙ ዘዘ ዚአሆሙ /እየብቻቸው/፣
ወዘዘ ዚአሁ ጸጋሁ /ስጦታው እየቅሉ ነው ወይም ልዩ ልዩ ነው/ እያለ እንደየአመጣጡ ይፈታል።
በር ከፋቾና አገናኝ መሆኑም በየአገባቡ ተነግሯል።
እንተ፣ ደቂቅ አገባብ ሲሆን እየ፣ በ፣ ወደ፣ ለ፣ ን ይሆናል። እየ ሲሆን፣
የሀበነ ምሕረቶ ወትረ እንተ ጽብሐት /እየጧቱ፣ እየለቱ፣ ይላል/ ወይም እንደ ዘዘ በደኂመ ቃል ጧት ጧት፣ ዕለት ዕለት ያሰኛል።
እንተ ጸብሐ ካለ ግን እየነጋ ያሰኛል። በአንቀጽ ላይ ስለወደቀ ዐቢይ አገባብ ነው።
በ፣ ወደ ሲሆን በቦታ ይገባል። ለምሳሌ፣

እንተ ካልእ ገጽ፣
እንተ ካልእ ፍኖት፣

ወይሔውጽ እንተ መሳክው፣
ፈነወ እዴሁ እንተ ስቁረት /በ ሲሆን/ይላል፡፡ ለ፣ ን ሲሆን፣ እንተ ባሕቲቱ፣ እንተ ባሕቲታ፣ እንተ ባሕቲቶሙ፣ እንተ ባሕቲቶን ወዘተ እያለ በአካል ይገባል፡፡
አገናኝ ሲሆን እንተ ሶበ ጸዋዕክዎ፣ እንተ ጊዜ ተንሥአ ሰብእ ላዕሌነ እያለ ጊዜን፣ ሶበን ያዳምቃል፡፡

፲ እነ የሚሆን አገባብ፣

እለ፣ ደቂቅ አገባብ ሲሆን በጥያቄ አገባብና በተጸውዖ ስም እየገባ እነ ይሆናል፡፡ ስሙም አብገር ይባላል፡፡ ሲገባም፣
እለመኑ አንትሙ?
ወእምዝ ጎለፉ እለጳውሎስ እምነ ጳፉ ይላል፡፡ እለ ላልቶ ሲነገር የስም ተውሳክ ይሆናል፡፡ ሲገባም እለእስክንድሮስ፣ እለእስክንድርያኸ ይላል፡፡ እለ ተውሳከ ነገርም ይሆናል፡፡ ለምሳሌ እለቆሞሳት ይላል፡፡

፲፩ ኋላ የሚሆን አገባብ፣

ድኅረ ኋላ ይሆናል፡፡ በዐሥር ሠራዊት ይዘረዝራል፡፡ ድኅሬሁ፣ ድኅሬከ፣ ድኅሬሆሙ፣ ድኅሬክሙ፣ ድኅሬሃ፣ ድኅሬኪ፣ ድኅሬሆን፣ ድኅሬክን፣ ድኅሬየ፣ ድኅሬነ ይላል፡፡ በዐረፍተ ነገር ሲገባም ጎለፈ ጴጥሮስ ድኅረ ጳውሎስ ይላል፡፡
ፈረሱ ለፈርየን ይቤ ድኅረ ድኅረ፣ አስመ እግሩ ኢለመደ ባሕረ ይላል፡፡ ድኅረ ከስም በፊትም ሆነ በኋላ ይገባል፡፡
ድኅረ በደቂቅ አገባብነቱ በቦታ፣ በጊዜ በስም ይገባል፡፡ ለምሳሌ በቦታ ሲገባ፣

ድኅረ ማዕጸ፣ እምድኅረ ማዕጸ ይላል። እም ሲስማማው ነው።
እንተ ሲስማማው፣ መጽአት እንተ ድኅሬሁ ይላል።
በጊዜ ሲገባ ወድኅረ ኵሎሙ አስተርአየኒ ሊተ ይላል።
ድኅረ ሕቅ፣ እምድኅረ ሕቅ ይላል።
በስም ሲገባ፣ ሰሎሞን ነግሠ ድኅረ ዳዊት፣ እምድኅረ ዳዊት ይላል።
ድኅሬሁ፣ ድኅሬከ ብሎ ድኅሬነ እስኪል በባዕድ ይዘረዝራል።

፮ ፍጹም ደቂቅ አገባብ የሆኑ /ደቂቅነት ብቻ ያላቸው/፣

ከላይ እንደተገለጸው ደቂቅ አገባብ በአምስት የሚከፈሉ ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱ ፍጹም ደቂቅ አገባብ የሆኑትን የያዘው ክፍል ነው። ዝርዝር አጠቃቀማቸው ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል።

፲፫. **ላይ የሚሆኑ አገባባት**

ላዕለ፣ መልዕልተ፣ ዲበ፣ ላይ በላይ፣ከላይ፣ ወደላይ፣ እስከላይ ይሆናሉ። ዲበ ፍጹም አገባብ ነው። ላዕለ እና መልዕልተ በስም ከተለዐለ የተገኙ ዘር ወይም ሰዋስው ናቸው። በምሥጢር ቦታ ናቸው።
ዲበ ሲነገር ወዲበ ኪሩቤል ያንበለብል በርሁ፣ ወይትነሥኡ ሕዝብ ዲበ ሕዝብ፤ ወብእሲ ዲበ ብእሲ፣ ጸጋ በዲበ ጸጋ፣ እንዘ ይነብር እግዚእነ ዲበ ደብረ ዘይት ይላል።
ለዲበ ይወርድ የሚለው ግስ፣ እም እና በ ይስማሙታል። ለምሳሌ በዲበ ደብር፣ እምዲበ ደብር ይላል።
ላዕለ እና መልዕልተ ደቂቅነት ብቻ ያላቸው አገባባት ናቸው። ሲገቡም ላይ ባለው ነገር ይነገራሉ። ለምሳሌ ለሸመት ለቦታ ይሆናሉ። በሸመት ሲገቡ፣ ነበረ ጴጥሮስ ላዕለ ሐዋርያት ሲል በላያቸው ላይ

ወይም በነሱ ላይ ተቀመጠባቸው ማለት አይደለም፡፡ ከበላያቸው ተሾመባቸው ማለት ነው እንጅ፡፡
ነበረ ላዕለ ምድር ሲል አልጋ ነው፡፡
ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ፣ ላዕለ ማይ ፣
አርአየ ሥልጣኖ ላዕለ ሞት፣ መልዕልተ ሞት፣ በላዕለ ሞት፣ በመልዕልተ ሞት ይላል፡
ዕብን ዘተበትከ እምላዕለ ደብር፣ እመልዕልተ ደብር እምዲበ ደብር ይላል፡፡
እምና በ አዳማቂ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ራሳቸው እምንና በን ያመጣሉና፡፡
ዲቤሁ፣ ላዕሌሁ፣ መልዕልቴሁ፣ ዲቤነ፣ ላዕሌነ፣ መልዕልቴነ፣ እስከሚለው በዐሥር ይዘረዝራሉ፡፡
በጎንጅ አገባብ ዲበ፣ ላዕለ እና መልዕልተ አልተካተቱም፡፡ ዲበን፣ ላዕለን መልዕልተን በተመለከተ እንደ ዋድላ ከነምስክሩ በስፋት የዘረዘረ አገባብ የለም፡፡

፲፫፥ ታች የሚሆኑ አገባባት

ታሕተ፣ መትሕተ ታች፣ በታች፣ ከታች፣ ወደታች፣ እስከታች ይሆናሉ፡፡ ታች ባለው ነገር ይነገራሉ፡፡ በስም ዘሮች በምሥጢር ቦታዎች ናቸው፡፡ ሲገቡም፣ ኀደረ ታሕተ ምድር፣ መትሕተ ምድር ሲል ሞቶ መቀበሩን ያሳያል፡፡
ተርፈ ታሕተ፣ መትሕተ እግረ ደብር፣
ተሠልጠ ሚካኤል ታሕተ እግዚአብሔር፣
ማርያም ተበውሐት ታሕተ፣ መትሕተ ፈጣሪ ወመልዕልተ ፍጡራን ይላል፡፡
በታሕተ ሰማይ፣ በመትሕተ ሰማይ፣ እምታሕተ ሰማይ፣ እመትሕተ ሰማይ ይላል፡፡
ታሕቴሁ፣ መትሕቴሁ፣ እያሉ በ፲ ይረባሉ፡፡

፲፩ ውስጥ፣ በውስጥ፣ ከውስጥ፣ ወደውስጥ የሚሆኑ አገባባት

ውስተ፣ ውሳጤ፣ በውስጥ፣ ከውስጥ፣ እስከውስጥ ከውስጥ፣ ወደውስጥ ይሆናሉ። በስም ነባር፣ በምሥጢር ቦታ ናቸው። ውስተ ፍጹም አገባብ ነው። ውሳጤ አገባብ ከሰዋስው ነው። ሲገባም፣
ነበረ ውስተ ቤት፣ ውሳጤ ቤት
ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ፅልመት
ቦ አራዊት ዘይነብሩ ውስተ ያማዕት፣ ውሳጤ ያማዕት፣
ወቦ አራዊት ዘይነብሩ ውስተ፣ ውሳጤ ግብ፣
ኀደረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ይላል።
ውስቴቱ፣ ውሳጤሁ፣ ብሎ በ፲ሩ መራሕያን በባዕድ ይዘረዝራሉ።
አገባብ በባዐድ እንጅ በራሱ አይዘረዝርም ብለን አልነበረምን? ቢሉ ራሱን ወደነምስ መልሶና ባዕድነቱን አምጥቶ ዘርዝሯል እንጅ በራሱ ቢሆን ኖሮ ውስቱ ባለ ነበር። ውሳጣይ፣ ውሳጣዊ እያለም ወገን ቅጽል ይሆናል።

፲፪ ፊት፣ በፊት የሚሆኑ አገባባት፣

ቅድመ፣ ፊት፣ በፊት፣ ከፊት ይሆናል። አገባብ ከሰዋስው ነው። በስም ዘር በምሥጢር ቦታ ነው። ሲገባ፣

ቅድመ ቤተ እግዚአብሔር፣
ሚካኤል ይቀውም ቅድመ አምላኩ፣
ቆመ አቢሳ ቅድመ ዳዊት ይላል።

ቅድሜሁ፣ ቅድሜነ፣ ብሎ በ፲ ሠራዊት በባዕድ ይዘረዝራል።

፲፯ መሀል፣ መካከል፣ በመካከል፣ ከመካከል፣ በውስጥ የሚሆን አገባብ፣

ማዕከለ መሀል፣ መካከል፣ በመካከል፣ ከመሀከል፣ በውስጥ ይሆናል። አገባብ ከሰዋስው ነው። በስም፣ በግብር፣ በቦታ ይገባል። ሲገባም

ማዕከለ ክልኤ እንስሳ ርኢኩከ፣ ሰቀልዎ ለእግዚእነ ማዕከለ ክልኤቱ ፈያት፣ ይላል። /በግብር/

ማዕከለ ዳዊት ወሳኦል ነበረ ዮናታን ሲል /በስም፣/

ማዕከለ ጉባኤ፣ ማዕከለ ዐፀድ ሲል /በቦታ፣/

ይከውኑ ከመ አንበሳ ውስተ እንስሳ ሲል በግብር የገቡ መሆኑን ያሳያል።

ነበ፣ መንገለ፣ ውስተ፣ እንተ፣ ለ ይስማሙታል። በአገባብነቱ ማዕከሌሁ፣ ማዕከሌነ ብሎ በ፲ሩ መራሕያን በባዕድ ይዘረዝራል።

፲፰ እዳሪ፣ በእዳሪ፣ ከእዳሪ የሚሆን አገባብ፣

አፍኣ እዳሪ፣ በእዳሪ፣ ከእዳሪ ይሆናል። ቦታ ባለው ነገር ሁሉ ይገባል። አፍኣ ነባር ነው። በስም ዘር፣ በምሥጢር ቦታ ነው። ነበረ አፍኣ፣ ነበረ በአፍኣ፣ ነበረ አፍኣ ቤት ይላል። አፍኣ፣ አፍኣሁ፣ አፍኣከ ብሎ አፍኣነ እስከሚል በ፲ ሠራዊት በባዕድ ይዘረዝራል።

፲፱. ለ ደቂቅ አገባብ ሲሆን፣

ለ ፲፫ ነገሮችን ይሆናል። እነርሱም በቁም ቀሪ፣ አዳማቂ፣ ዘርፍ ደፊ፣ ዘርፍ አያያዥ፣ ዘርፍ አቅራቢ፣ ጋራ፣ ጊዜ፣ ተሳቢ፣ ተጠቃሽ፣ ወደ፣ በ፣ ከ፣ ን ናቸው። በሩቆቹ በአራት ይነገራል።

በቁም ቀሪ ሲሆን ለዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ይላል።

አቀብሎ ሸሸ ሲሆን በትእዛዝ ይነገራል።

ለምሳሌ ለይኩን ብርሃኑ ለዓለም ይላል።

ተጠቃሽ ሲሆን በዘርፍ በአንቀጽ ይነገራል። በአንቀጽ ሲነገር ተሳቢ፣ ተጠቃሽ ይሆናል ምሳሌ አእመሮ ለብእሲ ይላል።

በዘረፍ ሲነገር ጠቃሽ ይባላል። ለምሳሌ ቃኤል ቀታሊሁ ለአቤል ይላል።

ጠቃሾች ስድስት ናቸው። እነርሱም ከኀምስ በስተቀር ሲገቡ የዳር ስም ግእዝ፣ ለነ፣ ለከ፣ ካዕብ ሎሙ፣ ሎቶሙ፣ ሣልስ ላቲ፣ ለኪ፣ ራብዕ ላ፣ ይላል፡ ሳድስ ሎን፣ ሎቶን፣ ለክን፣ ሳብዕ ሎ፣ ሎቱ፣ ይላል።

ሳብዕ ሎ፣ ሎቱ ለአምላክ ሰቀልዎ አይሁድ ይላል። በራሱ ሲገባ፣ ግእዝ ለነ፣ ለከ፣ ሊተ፣ ራብዕ ላቲ፣ ሳድስ ልየ፣ ሳብዕ ሎቱ፣ ይላል። ራብዕ ገብርኤል ሰበከ ላ ለማርያም ዜና ማለቱን ያሳያል። ለአምላክ ሰቀልዎ አይሁድ ይላል። አገባቡንም አንቀጹንም ከዚህ ይናገሩታል። ይህም አእመሮ ብሎ በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራል። በነባር ሲነገር አልቦቱ ዘመድ ለብእሲ ይላል። አገባቡ ሲዘረዝር አይቶ ገብቷልና ተሳቢ ይባላል። በጥሬ ሲገባ፣ ንዋዩ ለባዕል፣ ንዋያ ለባዕልት፣ ንዋዩ ለብእሲ፣ ንዋያ ለብእሲት፣ ወያላዕት ምጉያዮን ለግሂ ማለቱን ያሳያል። በብዙ ግሂያት ነበር። ነገር ግን አገባቡ ሲዘረዝር ጠፊ ነው ብለው አንድና ብዙ ሴትና ወንድ ያናግሩበታል። በሳቢ ዘር ሲገባ ብልዐቱ ለኀብስት፣ በንዑስ አንቀጽ ሲገባ በሊያቱ ለኀብስት ማለቱ ያሳያል። ሳድስ ቅጽል ሲገባ እሙራ ለብእሲ፣ ማእምራ ለብእሲት ይላል።

ለ ሲጠቀስ፣ /ሲሳብ/ ሳድስ በአንድ ፊደል በ፲፮ ሠራዊት በ፷፬ አናቅጽ ይጠቀሳል። ሳድስ ፊደሉ ን ነው። ሠራዊት የቅርቦች ሴቶች፣ የሩቆች ሴቶች ናቸው ሲገባ፣
አእመሮን፣ አእመረክን፣ ሲሆኑ የወንዶች ፮፣ የሴቶች ፮ በድምሩ ፲፪፣ የአነ ፩፣ የንሕነ ፩፣ ፪፣ ጠቅላላ ድምር ፲፯ የሚባል ይህ ነው። ፲፯ ቀዳማይ፣ ፲፯ ካልኣይ፣ ፲፯ ዘንድ፣ ፲፯ ትእዛዝ ድምር ፷፬ ይሆናል። በዚህ ይሳባል።
ግእዝ በ፪ ፊደል በ፲፬ ሠራዊት፣ በ፹፮ አናቅጽ በ፪ ሠራዊት ይጠቀሳል። ፊደላቱም ነ፣ ከ ናቸው። ሠርዌው የቅርቡ ወንድና ንሕነ ናቸው። ሲገባ፣ ፲፬ ቀዳማይ፣ ፲፬ ካልኣይ፣ ፲፬ ሣልሳይ፣ ፲፬ ዘንድ ጠቅላላ ፹፮ ይሆናል። በዚህ ይሳባል።
ሣልስ በ፪ ፊደላት፣ በ፪ ሠራዊት በ፲፬ አናቅጽ ይጠቀሳል። ፊደላቱም ኪ፣ ኒ፣ ሠራዊቱ የቅርቢቱ ሴትና አነ ናቸው። ሲገቡ አእመረኪ፣ አእመረኒ፣ አእመርከኒ፣ አእመሩኪ፣ አእመሩኒ፣ አእመርክሙኒ፣ የወንዶች ፮ የሴቶች ፮፣ የአነና የንሕነ ፪፣ ጠቅላላ ድምር ፲፬ ሠራዊት ማለት ይህ ነው። አናቅጽ ከማሁ ራብዕ በ፲ ሠራዊት፣ በ፹ አናቅጽ በ፩ ሠርዌ በ፯ ፊደላት ይጠቀሳል። ፊደላቱም ከሀ ጀምረው እስከ የ ይጨርሳሉ። ሲገቡም፣ አእመራ፣ አእመርካ፣ አእርዋ፣ አእመርክምዋ፣ አመረታ፣ አእመርኪያ፣ አእመራሃ፣ አእመርክናሃ፣ አእመርክዋ፣ አእመርናሃ፣ ፲ሩ ይህ ነው። ፊደላቱም ራ፣ ካ፣ ዋ፣ ያ፣ ታ፣ ሃ፣ ና፣ ፲ ቀዳማይ፣ ፲ ካልኣይ፣ ፲ ሣልስ፣ ፲ ትእዛዝ በድምሩ ፹ አናቅጽ እነዚህ ናቸው። በነዚህ ይሳባል።
ካዕብ በሁለት ፊደላት በ፲፯ ሠራዊት፣ በ፻፪ አናቅጽ፣ በ፫ ሠራዊት ይጠቀሳል። ፊደላቱም ሁ፣ ሙ ናቸው። ሠራዊትም የሩቆች ወንዶች፣ የቅርብ ወንዶች ናቸው። ሲገባ አእመሮሙ አእመረክሙ፣ አእመርኩክሙ፣ የወንዶች ፮፣ የሴቶች ፮፣ ፲፪ የአነ እና የንሕነ ፬፣ ፲፯፣ አእመራሁ፣ አእመርክናሁ፣ ፪፣

ሲሆን ፲፰ ሠራዊት ይህ ነው። ቀደማይ ፲፰፣ ካልኣይ ፲፰፣ ሣልስ ፲፰፣ ዘንድ ፲፰፣ በድምሩ ፸፪ አናቅጽ ይሆናል። በዚህ ይሳባል።

ሳብእ በ፰፣ ሠራዊት፣ በ፸፪ አናቅጽ በ፮ ፊደላት በ፩ ሠርዌ ይጠቀሳል። ፊደላቱም ከሮ ጀምሮ እስከ ኖ ያሉት ናቸው። ሠርዌውም የሩቅ ነው። ሲገባ አእመሮ፣ አእመርኮ፣ የወንዶች ፬፣ የሴቶች ፪፣ የአነና የንሕነ ፪፣ በድምሩ ፰ ሠራዊት ያልነው ይህ ነው። ፊደላቱም ሮ፣ ኮ፣ ዮ፣ ቶ፣ ዎ፣ ኖ ናቸው። ይህም ቀዳማይ ፰፣ ካልኣይ ፰፣ ዘንድ፣ ፰ ትእዛዝ፣ ፰፣ በድምሩ ፸፪ አናቅጽ ይህ ነው። በዚህ ይጠቀሳል።

መላው ፫፻፸ ይሆናል። የአእመረ እርባታ የተሳቢ ቁጥር ይህን ያህል አይባልም። አንቀጽ በአገባብ ሲዘምት አገባብም በአንቀጽ ሲበተን እንደ ለ ነው። ቁልቁል ቢወርዱ ሽቅብ ቢወጡ ተሳቢ ከግእዝ አይወጣም። አእመረ ምሥጢረ አእመሮ ለምሥጢር ቢል ፪ቱም ግእዝ እንደሆኑ አስተውል።

በ ሲሆን ወአምጽአ ረኀበ ለብሔር ይላል።

ጋራ ሲሆን ትክውኑ ሱቱፋነ ለሐራ ሰማይ ይላል።

የተሳቢን ነገር ከዚህ ይናገሩታል። ለ ተሳቢ ሲሆን ብዙ አካሄድ አለው። ርሁብ በልዐ ኅብስተ ሲል እንጀራን በላ ተሳቢ ነው ይላል። በዋድላ አገባብ መሠረት ግን ተሳቢ አይደለም። ምክንያቱም ተሳቢማ ባለቤቱስ፣ አገባቡስ ተሳቢ አይደለምን ብለው ኅብስትን ተደራጊ ርሁብን አድራጊ አንቀጹን ሳቢ ብለውታል። አድራጊና ተደራጊ በአንቀጽ ይታወቃል።

ለ በሩቅ በ፲፣ በ፲ ፣ በቅርብ በ፮ ንሕነ ባለው፣ በ፰ በ፰ ማሠሪያ ይሆናል። ሲገባ፣ አእመሮ ብሎ ለሳብዕ እስከ አእመርኖ ድረስ ነው። ዝርዝሩ ለአገባቡ ሲሆን ግእዝ ያናግራል። ዝርዝሩ ለባለቤት ሲሆን አዳም አፍቀሮ ለአምላክ በአገባብ ብእሲ ይትበአስ ምስለ ብሲ እስመ የአምሮ ግብሮ ይላል። በማሠሪያ ሲሆን

በዝርዝር በቅጽል ይዘልቃል። ካልዘረዘረ ግን አይዘልቅም። ሲዘረዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣

አእመሮ ለብእሲ
አእመርኮ ለብአሲ፣
አእመረከ ለከ
አእመሮሙ ለደው፣
አእመረክሙ ለክሙ፣ እያለ በ፲ ሠራዊት ይዘልቃል።

በቅጽል አእመረ ኪያሁ ብአሴ፣ ኪያከ ብእሴ፣ ኪያየ ብሴ፣ ኪያየሙ እደወ፣ ኪያክሙ እደወ፣ ኪያነ እደወ፣ ይላል። ሳዘረዝር አእመረ ብእሴ፣ አእመረ እደወ፣ አእመረ ብእሲተ፣ አእመራ እንስተ፣ ብሎ ይቀራልም፣ ይዘልቃልም።

፪ኛም ለቅኔ ማሠሪያ ሲሆን፣ ፈቀደ ይብላዕ ኀብስተ፣ ቀርበ ይብላዕ ኀብስተ፣ በሊያ ኀብስተ መጽአ፣ ሲል ምሥጢሩ ይብላዕ ፈቀደን፣ ቀርበ ይብላዕን ቀርበን፣ በሊያ ቦታውን ያሳያል።

፰ ማድረጊያ ወይም በቁም ቀሪ የሚሆን አገባብ፣

በ በቁም ቀሪ፣ ጊዜ፣ ወደ፣ ጋራ፣ ከ፣ ቸልታ፣ ዘንድ፣ አብሮ፣ አዳማቂ፣ ለ/ላ ናቸው። ለ/ላ ሲሆን አደራራጊ፣ ተደራራጊ በሚገቡበት ሰዋስው ሁሉ ይነገራል።

ለምሳሌ ይትራወጽ ገብር ሀገረ በሀገር ይላል።

ለ ሲሆን ገጸ በገጽ ኢይትናጸሩ፣ አስተአኀዞሙ እደ በእድ ወእግረ በእግር አስተራወጸሙ ይላል።

ን ሲሆን ለምሁራነ ልብ በጥበብ፣ ኢቀባዕከኒ በዘይት ይላል።

ጊዜ ሲሆን ኢመፍትው አድልዎ በፍትሕ ይላል።

ጋራ ሲሆን ተዋሐደ ቃል በሥጋ ይላል።

ቸልታ ሲሆን ጸለየ ወሰአለ ኀበ እግዚእ በብካይ /አልቅሶ/፣ ከልብኑ አነ ከመ ትምጻእ ኀቤየ በአእባን ወበትር / ድንጋይና በትር ይዘህ/ ይላል።

በቁም ቀሪ ሲሆን ሳይዘረዝር በሩቆች በአራት በብእሲ፣ በእደው፣ በብእሲት በአንስት ይገባል።
ሲዘረዘር፤ ቦቱ፣ ብኪ፣ ብክሙ፣ ወዘተ ይላል።

፷፩ ጋራ፣ አብሮ የሚሆን አገባብ፣

ምስለ፣ ጋራ፣ አብሮ ይሆናል። ጋራ ሲሆን ምስለ አብርሃም ተዐረከ ይላል፣
እንዲሁም ዘእሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ይላል /አንድ ሆነ ማለት ነው/፣
አብሮ ሲሆን ተሰደት ማርያም ምስለ ዮሴፍ፣ ወዮሴፍ ተሰደ ምስለ ማርያም ይላል።
ሳይዘረዝር በአራት ይገባል፣ ይኸውም፣
ምስለ ወልድ፣ ምስለ ወለት፣ ምስለ ውሉድ፣ ምስለ አዋልድ ይላል።
ምስለ ሲዘረዘር፣ በ፲ ሠራዊት ይነገራል። ምስሌሁ፣ ምስሌከ፣ ብሎ ምስሌነ እስኪል ድረስ በባዕድ ይዘረዝራል። ለዚህም የውእቱ አገባብ ይስማማዋል።

፷፪ እየ፣ እያ የሚሆኑ አገባባት

በበ፣ ዘዘ፣ ለለ እየ፣ እያ ይሆናሉ። ሲገቡም ኩሉ ሰብእ የሐውር ለለ ብሔሩ/በብትን ሰዋስው ሲገባ/
ዐደዉ እስራኤል ለለ ሠለስቱ ነገድ ባሕረ ኤርትራ
ለለ በሰዓት፣ በዘመናት በጊዜ ይዘረዝራል። ለምሳሌ ለለ ሰዓቱ፣ ለለ ዘመኑ ይላል። በአኀዝ ይገባል፤ ለምሳሌ ተዘከር እግዚኦ ለለ አሐዱ አሐዱ ስዕለቶ ይላል።
ዘዘ በዘ ዝርዝር ይገባል። በራሱ ዝርዝር ይነገራል የሚሉም አሉ። ለምሳሌ ለኵሉ ዕፅ ፍሬሁ ዘዘዚአሁ ሲል በዘ ዝርዝር የገባ መሆኑን የዋድላ አገባብ ይገልጻል።

ዝብጠተ መሰንቆ ወእንዚራ እለ ቦሙ ሠናይ ዜማ ዘዘዚያሁ ይላል። ስድስት የውእቱ አገባቦች ይስማሙታል። ምሥጢሩን በሁለት ያሳያል። እነርሱም በየዋህ በሁለት ፀዋትው፤ በመሰርይ በአንድ ያታ፤ በ፫ ሠራዊት በ፴ መዓርጋት፤ በ፻፴ አናቅጽ ለውእቱ ሰዋስው እየሆነ ይረባል። ለምሳሌ ከላይ ለዕፅ ፍሬሁ ዘዘዚአሁ እስመ ይበልዕዎ ጻድቃን የሚለው ይህን ያሳያል። በቅጽል ማሠሪያ ውእቱን ያመጣል። በማሠሪያ ዚአየ ውእቱ ገለዓድ ወዚአየ ምናሴ ይላል።

በቅጽል ዘዚአነ ሞተ ነሥአ ይላል። በየዋህ በሁለት ፀዋትው ሲገባ ወንዶች አንድ ወገን፤ ሴቶች አንድ ወገን ሆነው ነው። በመሰርይ ሲገባ በአንድ ያታ በአንተ አዋቂነት ነው። በ፴ መዓርጋት ሲገባ ከአእማሪ ሁለት፣ ከአእማርያን ሁለት፣ ከአእማሪት ሁለት፣ ከአእማርያት ሁለት፣ ከአነ እና ከንሕነ አንድ አንድ፣ ቀዳማይ ፲፣ ካልአይ ፲፣ ሣልሳይ ፲ ሲሆን ፴ መዓርጋት ማለት ይህ ነው። ፻፲፴ አናቅጽ ያለው ቀዳማይ ፹፣ ካልአይ ፹፣ ሣልሳይ ፹ ተደምረው ነው።

በበ ከተጸውያ ስም በስተቀር በሁሉም ብትን ሰዋስው ይገባል። ለምሳሌ ኵሉ ሰብእ የኀድር በበሀብቱ፣ አምላክ ይሴባሕ በበብሔሩ ወበበዘመኑ ወበበማኅበሩ፤ እንዲሁም በበዕለት፣ በበዕለቱ፣ በበሰዓት፣ በበሰዓቱ እያለ ጊዜያትን ይዘረዝራል።

ያለ ዝርዝሩ ሲገባ በበሀቅ ልሀቀ ይላል። በአኀዝ ሲነገር ወፈነወሙ በበክልኤቱ ይላል። ይህ አማርኛ ጨራሽ ይባላል። ይህም ከአእማሪ ሁለት ያለው ያወቀ፣ ያወቅህ ብሎ ሩቅና ቅርቡን ቆጥሮ ነው።

፸፫ ስለ የሚሆኑ አገባባት

ቤዛ፣ ዕሴተ፣ ተክለ፣ ዐይነ፣ ግእዝ ንባብ፣ ስለ ይሆናሉ። ዐይን በሰዋስው ይገባል ሲባል በራሱ ማለት

ነው፡፡ ተክለ፣ በአካል፣ በተፈጥሮ፣ በስም ይገባል፡፡ ግእዝ ንባብ ተናቦም ሆነ ሳይናበብ በሰዋስው ሁሉ ይገባል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፣

፩ ቤዛ ይስሐቅ ወረደ በግዕ፡፡

፪ ጴጥሮስ መሀረ ወንጌለ እሴተ ኦሪት፣

፫ ተክለ አብ አውጽአ ስድስተ አክናፈ ተክለ እግሩ፡፡

፬ ዐይነ ዐይን ይጥፋእ ዐይን በማለት በራሱ ይገባል፡፡

፭ ሞተ አምለክ ሰብአ /ግእዝ ንባብ ሲሆን/፡፡

፫ ለቦታ ቅጽልና በቂ የሚሆኑ ዘርና ነባሮች

፭፬ ላይ የሚሆኑ አገባባት፣

ላዕለ፣ ላዕል፣ መልዕል፣ መልዕልት፣ ላዕሊት ላይ ይሆናሉ፡፡ በስም ዘር፣ በምሥጢር ግን ቦታ ናቸው፡፡ ላዕሊት ምዕላድ ናት፡፡ በሴት ትነገራለች፡፡ ሁሉም ተለዐለ ከሚለው ግስ የተገኙ ናቸው፡ ላዕለ፣ ላዕል፣ መልዕል፣ መልዕልት፣ ላዕሊት ከላይ እንደተገለጸው የቦታ ጥሬዎች ናቸው፡፡ መልዕል ባዕድ ዘር፣ ባዕድ ቅጽል ይሆናል፡፡ መልዕልት ደግሞ ባዕድ ከምዕላድና የሴት ባዕድ ቅጽል ነው፡፡ ላዕለ እና ላዕል ፍጹም ሰዋስው ናቸው፡፡ ላዕለ ጉልት ነው፣ የቦታ ቅጽል ይሆናል፡፡ ላዕል ዘር ነው፡፡

ላዕል፣ ላዕለ፣ መልዕልት፣ በሳድስ ቅጽል በአንድ ርእስ በአምስት ሠራዊት፣ በሳቢ ዘር በአንድ ርእስ በሁለት ሠራዊት፣ በንዑስ አንቀጽ፣ በሳልስ ቅጽል በአምስት በአምስት አርእስት በአምስት በአምስት ሠራዊት ይነገራሉ፡፡ በዐረፍተ ነገር ሲገባም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣

ተፈቅረ ጉሥ ንቡረ ላዕል
ሠምረ ባዕል ንብረተ ላዕል
በንዑስ አንቀጽ ሲገባ፣

ገብረ ወልድ ተሰቅሎተ ላዕሉ
አፍቀረ ባዕል አንብሮተ ላዕል ካህነ፣
አፍቀረ ንጉሥ አብልያተ መልዕልት ህብስተ ካህነ
ሠምረ ወልድ ተፈንዎተ መልዕልት ምስለ ቢጹ፣
አፍቀረ ንጉሥ አስተፋንዎተ ላዕል ላእከ ምስለ ቢጽ ይላል።

ላዕሉ ጉልት ቀለም ነው። በዘ እንጂ በለ አይየያዝም። አሁን በዘ የሚያያዝ ሆኖ አይደለም፤ እርሱ ራሱ እንደ ዘ መቀጸሉን ሲያይ ነው። ሲቀጸልም፤ በሰማይ ላዕሉ፤ በላዕሉ ሰማይ ይላል።
በቁራኛ ሲገለጽ ደግሞ በሰማይ በላዕሉ ወበምድር በታሕቱ ማለቱን ያሳያል። ቅጽልና በቂ ሲሆኑ ከላዕሉ በስተቀር ዘርፍ እየያዙ ይነገራሉ። ይህም ቁራኛ ይባላል። ለተገብሮ እንጂ ለገቢር አይቀጸልም። አይዘረዝርም፡ የቀሩት በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራሉ። ይህም መልዕሉ፣ መልዕልቱ፣ መልዕልከ፣ መልዕልትከ፣ ማለቱን ያሳያል። ላዕል ያለውን፣ ላዕሉ፣ ላዕልከ እያለ ይዘረዝራል። ላዕሉ ለወንድም ለሴትም፡ ለነገርም፣ ለብትን ሰዋስውም ይቀጸላል።
ላዕል ከላዕሉ አይገናኝም፤ ለገቢር ላዕለ ይላል። በቅጽልነት ይስማማቸዋል። መልዕልታ ለምድር ሰማይ፣ ላዕላ ለምድር ሰማይ ይላል። ሰማይ ላዕለ ምደር፣ መልዕልተ ምደር፣ ወይም ላዕለ ምድር ሰማይ፣ መልዕልተ ምድር ሰማይ እያለ ቅጽል ይሆናል። በቂ ሲሆን ላዕላ ለምድር ብሎ ሰማይን፣ መልዕልተ ወግር ብሎ ተራራን ያመጣል። ላዕል በደጊመ ቃል ይነገራል። ለዚህም አራት ግሶች ይስማሙታል። እነርሱም ርእየ፣ ነጸረ፣ አንቃዕደወ፣ አንፈርዓፀ ናቸው። ሲገቡም፤
ርእየ ነጸረ ላዕለ ላዕለ፤
አንቃዕደወ፣ አንፈርዓፀ ላዕለ ላዕለ ማለቱን ያሳያል።

አማርኛ ጨራሽ ይባላል። ላዕላይ፣ ላዕላዊ፣ ላዕላይያን፣ ላዕላውያን፣ ላዕላይያት፣ ላዕላውያት ብሎ በ፲፪ ሠራዊት፣ በ፷፬ አንቀጽ፣ ይረባል። ሲረባም ከላዕላዊት ሁለት፣ ከላዕላውያን ሁለት፣ ከላዕላዊት ሁለት፣ ከላዕላውያት ሁለት፣ ከአነ ከንሕነ ሁለት ሁለት፣ የሴቶች አነ ንሕነ ፲፪፣ ቀዳማይ ፲፪፣ ካልአይ ፷፬ አናቅጽ ማለት ይህ ነው። ይ እና ዊ የላዕል ምዕላድ ናቸው። የቦታ ጥሬዎች ወገን ቅጽልን እንደሚያመጡ ያሳያል።

የወገን ነገር ከዚህ ይነገራል። ወገን የሚሆኑ የሰው ስም፣ የሀገር ስም፣ ነባር፣ ሰዋስው ናቸው። የመጨረሻውን ቀለም ራብዕ ያደርጋሉ። ሲገባም ያልተባበረ ቃል ነው። የሰው ስም ሲሆን ያዕቆባዊ፣ እብራዊ፣ ይላል። ላዕላይ ሲል መምህራን ተባብረውበታል እንጂ እንደ ላዕላዊ ግልስ ቢሆን በቀና ነበር። ይህም በዝርዝር ቃል ቀዳማዪሁ፣ ሲል ግልሱ ነው።

ላዕለ እና መልዕልተ በሰዋስውነታቸው በሁለት ይዘረዝራሉ። በንዑስ አንቀጽ አስነስተው በነባር በዘማች ያሣሥራሉ። በዘማች ሲያሣሥሩ ለነባሩ የውእቱ አገባባት ይስማሙታል። ሲገባም ተሰቅሎቱ ለወልድ፣ እስመ ላዕለ መቃብረ አዳም ሎቱ ስብሐት።

፷፩ ከፍታ የሚሆኑ አገባባት

ሉዓሌ፣ ልዕልና ከፍታ ይሆናሉ። ልዕልና ምዕላድ ነው። ልዑል ያለውን ሀ እና ዐ በመካከል ሲሆኑ ካዕባቸውን ሳድስ ያደርጋሉና። ለምሳሌ ንዕስና፣ ትሕትና ማለቱ ያሳያል።

ሉዓሌ በባለቤት ሲገባ በሁለት ሠራዊት ይገባል። ለምሳሌ ሉዓሌ ብእሲ፣ ሉዓሌ ብእሲት፣ ሉዓሌ እደው፣ ሉዓሌ አንስት፣ ተፈቅረ፣ ተፈቀርከ፣ ተፈቅረት፣ ተፈቀርኪ ይላል። በዘርፍነት በ፲፪ ሠራዊት

ይነገራል። ብእሴ ሉዓሌ፣ ዕደወ ሉዓሌ፣ ብእሲተ ሉዓሌ፣ አንስተ ሉዓሌ፣ በማለት በሩቅ በቅርብ በአነ፣ በንሕነ ይገባል። ልዕልናም በተመሳሳይ መንገድ እንደ ሉዓሌ ይገባል፣ ይዘረዘራል። ሉዓላይ፣ ሉዓላዊ፣ በ፲፪ ሠራዊት በ፷፬ አናቅጽ ይረባል። ሉዓሌና ልዕልና በሌሎች አገባቦች ላይ የሉም።

፷፮ ታች የሚሆኑ አገባባት

ታሕት፣ ታሕቱ፣ ታሕቲት፣ መትሕት ፣ ታች ይሆናሉ። ታሕት ዘር ነው። ታሕቱ ጉልት ነው። መትሕት ባዕድ ከምዕላድ ነው። መትሕት የወንድ ባዕድ ቅጽል ነው። መትሕት /መድረሻው ጠብቆ/ ለአንዲት ሴት ባዕድ ቅጽል ይሆናል። በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ እነዚሁ አገባባት የተገለጹ ሲሆን በጎንጅ አገባብ ግን የሉም። በአለቃ ታየ አገባብ ደግሞ ታሕቲት እና ቁልቁሊት አቆልቁሎ የሚል ትርጉም ተሰጥቷቸው በተጨማሪ ገብተዋል። በስም፡ ዘሮች፣ በምሥጢር፡ ቦታ ናቸው። በምሥጢር ሁሉም የቦታ ጥሬዎች ናቸው። ከቁልቁሊት በቀር ሁሉም ተትሕተ ከሚለው ግስ የወጡ ናቸው። መትሕት ባዕድ ዘር ነው። ታሕቲት ምዕላድ እየሆነች በሴት ቃል ትነገራለች። ለሴት ትቀጸላለች። ዋቄ ሲያጫፍር በየደጃፉ ላዕሉ ወታሕቱ፣ ላዕል ወታሕት፣ ሰማይ ወምድር እያለ ይገባል። ምሕረት ወመዓት ቢል ጸያፍ ነው። ሲገባ ታች ባለው ነገር ነው። በሰዋስውኑ ጎደረ ታሕተ ምድር ቢል መቃብርን በቂ ሆኖ ያመጣል። ሞቶ ተቀበረ ማለት ነው። ታሕተ ቤት ሲል በቂ ሆኖ ምድር ቤትን ያመጣል። የምድር ቤት ማለት ነው። ቅጽል ሲሆን ምድር ታሕተ ሰማይ፣ ወግር ታሕተ ደብር ይላል።

ታሕተ/ መትሕተ ሳይናበብ ተነስቶ ከተነገረ ወደ የሚል ቃል ይወጣበታል። ለምሳሌ ወረደ ታሕተ /ወደቆላ ወረደ/፣ ወረደ መትሕተ /ወደጉድጓድ ወረደ/፣ ወረደ ታሕቲተ ሲል ወደ ታች ወረደ ማለት ነው።

ታሕቱ/መትሕቱ፣ እያለ በዐሥር ተገብሮ፣ ታሕቶ/መትሕቶ፣ እያለ በዐሥር ገቢር ይዘረዝራል። ታሕታይ፣ ታሕታዊ እያለ በዐሥር ወገን ቅጽል ይነገራል።

፷፮ ራስጌ እና ግርጌ የሚሆኑ አገባባት

ትርአስ ራስጌ፣ ትርጋጽ ግርጌ ይሆናሉ። በስም ዘሮች በምሥጢር ቦታ ናቸው። ፍጹም ሰዋስው ናቸው። ነበረ በትርአስ፣ ነበረ በትርጋጽ ይላል። ረሰየ ባዕልአሐደ ትርአሰ ወአሐደ ትርጋ። እንዲሁም ወኮኑ ሎቱ አሐዱ ትርአሰ ወአሐዱ ትርጋጸ በማለትም ይታወቃል። ትርአሱ፣ ትርአሲሁ ወዘተ፣ ትርጋጹ፣ ትርጋጺሁ እያሉ በባዐድ በዘመድ በ፲፪ ሠራዊት ይዘረዝራሉ።

፷፯ ውስጥ የሚሆኑ አገባባት

ውስጥ፣ ውሳጢት፣ ውሳጤ ውስጥ ይሆናሉ። በስም ነባር፣ በምሥጢር ቦታ ናቸው። ውስጥ ፍጹም ሰዋስው ነው። ዘርፍ ይሆናል እንጂ ዘርፍ አይዝም። ሲገባ ንዋየ ውስጥ፣ አምላከ ውስጥ፣ አምላከ ውሳጤ፣ አምላከ ውሳጢት ምድር ይላል። ውሳጤ ፍጹም ደቂቅ የሆኑ አገባባት ተብለው በተዘረዘሩት ውስጥ እንደተገለጸው አገባብ ከሰዋስው ነው። ውሳጤ፣ ውሳጢተ፣ ውስጠ ሲል ሰዋስው ነው። ወደ የሚል ትርጉም ይወጣባቸዋል። ለምሳሌ ቦአ ውስጠ፣ ቦአ ውሳጢተ፣ ቦአ ውሳጤ ይላል።
ውስጥ፣ ውስጡ፣ ብሎ በራሱ ይዘረዝራል። ውሳጤ ውሳጤሁ ብሎ በ፲፪ ሠራዊት በባዕድ ይዘረዝራል።
ውስጣይ፣ ውስጣዊ፣ ውሳጣዊ፣ ውሳጣይ፣ ውሳጣይት ወዘተ እያለ ወገን ቅጽል ይሆናል። ውሳጢት ምዕላድ ናት። በሴት ቃል ትነገራለች። ለሴትም

ትቀጸላለች፡፡ ይህም ውሳጤት ምድር ባለው ይገለጻል፡፡

፰፱ ፊት የሚሆኑ አገባባት

ቅድም፣ ፍጽም፣ ገጽ፣ አንጻር፣ መንጸር፣ መልታሕት፣ /መላትሕ/ ፊት ይሆናሉ፡፡ ስድስቱም ዘር ናቸው፡፡ ቅድም ለቦታ ነው፡፡ ሲገባም ነበረ በቅድም፣ ነበረ ቅድመ፣ ይላል፡፡
ቅድሙ፣ ቅድምከ ብሎ በዘመድ ይዘረዝራል፡፡
ገጽ አካል ከቦታ ነው፡፡ ቦታ ሲሆን ነበረ በገጽ ይላል፡፡ አካል ሲሆን ገጹ ለእግዚአብሔር ጎበ እለ ይገብሩ እኩየ ይላል፡፡
አንጻር፣ መንጸር አፍዛኝ /ትይዩ/ ይሆናሉ፡፡ ይህም ቦታ ነው፡፡ ነበረ አንጻረ፣ መንጸረ፣ በአንጻር፣ በመንጸር ማለቱን ያሳያል፡፡ ቅጽል ሲሆን ደብረ ታቦር አንጻረ አርሞኤም፣ አርሞንኤም አንጻረ ደብረ ታቦር ይላል፡፡ ባለቤቱ ሲቀር በቂ ይሆናል፡፡
አንጻርና መንጸር አቅጣጫን ያመለክታሉ፡፡ ማለትም ምሥራቅንና ምዕራብን፣ ሰሜንና ደቡብን፣ መስዕና አዜብን፣ ባሕርንና ሌብን ያመለክታል፡፡ ባለቤት ሲኖር ቅጽል ሳይኖር በቂ እየሆኑ ይነገራሉ፡፡ ሲነገሩም፣ ምሥራቅ አንጻረ፣ መንጸረ ምዕራብ፣ ምዕራብ አንጻረ፣ መንጸረ ምሥራቅ፡፡ ሰሜን አንጻረ፣ መንጸረ ደቡብ፣ እንዲሁም ደቡብ አንጻረ መንጸረ ሰሜን ይላል፡፡ መስዕ አንጻረ መንጸረ አዜብ ወይም አዜብ አንጻረ መንጸረ መስዕ ይላል፡፡ ባሕር አንጻረ መንጸረ ሌብ ወይም ሌብ አንጻረ መንጸረ ባሕር እየተባለ ይነገራል፡፡
ፍጽም በዐይን አውራጃ ያለው ነው፡፡ መልታሕት በዐይንና በጆሮ መካከል ያለው ነው፡፡ መላትሕ ግራና

ቀኝ ያለው ፊት ነው። ቅድሙ፣ አንጻሩ፣ ገጹ፣ መንጸሩ፣ ፍጽሙ፣ መልታሕቱ፣ መላትሒሁ፣ መልታሕቴሁ፣ እያለ በ፲ ይዘረዝራል።

በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ውስጥ መልታሕት አይገኝም። በሌሎቹ ከዋድላ አገባብ ጋር ተመሳሳይ ነው። በጎንጅ አገባብ አንጻር፣ መንጸር፣ መልታሕት አልተካተቱም። በአለቃ ታየ አገባብ ደግሞ መልታሕት አልተካተተም። አገባብ አይሆኑም እንጅ ዘርፍ ይይዛሉ።

፴. ኋላ የሚሆኑ አገባባት

ከዋላ፣ ድኅር፣ ኋላ ይሆናሉ። ድኅር በምሥጢር ጊዜም፣ ቦታም ይሆናል። በስም በግብር ይገባል። ለምሳሌ እምድኅረ ፀደይ ይመጽእ ክረምት ይላል። ከዋላ ነባር ነው፣ ድኅር ግን ዘር ነው።

ድኅርና ከዋላ ሰዋስው ናቸው። ሲገቡም ሐረ ድኅረ፣ ሐረ ከዋላ፣ በድኅር ሐረ፣ በከዋላ ሐረ ይላል። ድኅሩ፣ ድኅርከ፣ ከዋላሁ፣ ከዋላከ ብሎ በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራል። ደኃራይ፣ ደኃራዊ፣ ከዋላይ፣ ከዋላዊ ይላል። ከዋላ በጎንጅ አገባብ አይገኝም።

፴፩. የኋሊት፣ የግርግሪት የሚሆኑ አገባባት

ድኅሪት፣ ግንጽሊት፣ ግፍትዒት፣ ቁልቁሊት የኋሊት፣ የግርንግሪት ይሆናሉ። ድኅሪት የመታሠር፣ የመውደቅ ዐመል ነው። አሠርዎ ድኅሪተ፣ ወድቀ ድኅሪተ፣ ተዐስረ አምላክ በሥጋ ድኅሪተ፣ ማለቱን ያሳያል።

ግፍትዒተ ቁልቂሊተ የመሰቀል ዐመል ነው። ይህም ጴጥሮስ ተሰቅለ ቁልቂሊተ፣ ወድቀ ዔሊ ድኅሪተ፣ ግፍትዒተ፣ ግንጽሊተ ማለቱን ያሳያል። ሁሉም ዘር ናቸው። እነዚህ በጎንጅ አገባብ ውስጥ አይገኙም። ቁልቁሊተ ደግሞ ተለይቶ በአለቃ ታየ አገባብ

አልተካተተም። የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌና የዋድላ አገባቦች ተመሳሳይ ናቸው።

፴፪. ቀኝ የሚሆኑ አገባባት

የማን፣ ይምን፣ ቀኝ ይሆናሉ። ፍጹም ነባር ሰዋስው ናቸው። ቦታ ከአካል ናቸው። ቦታ ሲሆኑ ወነበረ በየማነ አቡሁ፡ ይላል። አካል ሲሆኑ ወያስተባሪ የማኖ ልዑል ይላል። የማናይ፣ የማናዊ፣ የማኑ፣ ይምኑ፣ ብሎ በ፲፪ ሠራዊት ይዘረዝራል። ወገን ቅጽልም ይሆናል። በጎንጅ አገባብ ደግሞ ሁለቱም አይገኙም። የአለቃ ታየ እና የዋድላ አገባቦች ተመሳሳይ ናቸው።

፴፫. ግራ የሚሆኑ አገባባት

ፀጋም፣ ፅግም፣ ግራ ይሆናሉ። ሁሉም ነባር ናቸው። ሲገቡም የማን ወፀጋም፣ ይምን ወፅግም፣ ይላል። ፀጋማይ፣ ፀጋማዊ በማለት ወገን ቅጽል ይሆናል። ፀጋሙ፣ ፅግሙ ብሎ በ፲፪ ሠራዊት በዘመድ ይዘረዝራል። በጎንጅ አገባብ ደግሞ ሁለቱም የሉም።

፴፬. መካከል የሚሆኑ አገባባት

አክሊል፣ ሕንብርት፣ ማዕከል፣ መካከል ይሆናሉ። ሕንብርታ ወአክሊላ ለምድር ኢየሩሳሌም ብሎ ቅጽልም በቂም ይሆናል። ይላል። ማዕከል አገባብ ከሰዋስው ነው። አገባብ ሲሆን ማዕከለ ምድር ይላል። ሰዋስው ሲሆን ነበረ ማዕከለ ሰብእ ይላል። አክሊልና ሕንብርት ነባር፣ ማዕከል ጥሬ ናቸው።

ማዕከለ በዋድላ ብቻ ሳይሆን በአለቃ ኪዳነ ወልድ፣ በአለቃ ታየ፣ እና በጎንጅ አገባቦች ተካቷል። አክሊልና ሕንብርት ግን በዋድላ አገባብ ውስጥ ብቻ ይገኛሉ።

፴፰ ውጭ ወይም እዳሪ የሚሆን አገባብ፣

ምዕያም፣ እዳሪ፣ ይሆናል። ምዕያመ ብሎ በእዳሪ፣ ከእዳሪ ይሆናል። ቦታ ባለው ነገር ሁሉ ይገባል። ምዕያም ጥሬ ዘር ነው። በምሥጢር ቦታ ነው። ነበረ ምዕያመ፣ ነበረ በምዕያም፣ ይላል። ምዕያም በራሱ ይዘረዝራል። ምዕያሙ፣ ምዕያምከ፣ ምዕያምየ ብሎ በ፲፪ ሠራዊት ይዘረዝራል። ምዕያም በጎንጅ፣ በአለቃ ታየና በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም አይገኝም። የሚገኘው በዋድላ አገባብ ብቻ ነው።

፴፱. ዳር የሚሆኑ አገባባት

ጽንፍ፣ ጸናፊ፣ አጽናፍ፣ ጽነፊ፣ ጽነፍ፣ ጽንፊ፣ ክንፍ፣ ክነፍ፣ ክነፊ፣ አክናፍ፣ ዳር ይሆናሉ። ሁሉም ነባር ናቸው። ዳር ባለው ነገር ይነገራሉ። ሲነገሩም ጽንፈ ሀገር፣ ጽንፈ ምድር፣ ጽንፈ ልብስ ይላል። አጽናፍ በብዙ፣ ጽነፍ በአንድም በብዙም ይሆናሉ። ጸናፊ በሴት ቃል ጸናፊት ተብላ ትነገራለች። ሲነገሩም ጸናፌ ጽልመት ይላል። እሊህም ቦታ ናቸው። ክንፍ፣ ክነፍ፣ ክነፊ፣ አክናፍ ክንፍ ባለው ነገር ይነገራሉ። ሲገቡም ክንፈ ዕፅ፣ ክንፈ ርግብ፣ ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ማለቱን ያሳያል። ከናፊት በሴት ቃል ትነገራለች። ክንፍ በአንድ፣ አክናፍ ብዙ፣ ክነፍ በአንድም በብዙም ነው።
በአለቃ ታየ አገባብ ጽነፊና ጽንፈ አልተካተቱም። በአለቃ ኪዳነ ወልድ አገባብ ከጽንፍና ከክንፍ በስተቀር ሌሎቹ አልተካተቱም። በጎንጅ አገባብ

ሁሉም የሉም። ስለዚህ በስፋት ዘርዝሮ የጻፈው የዋድላ አገባብ ብቻ ነው።

፴፯. ዳርቻ የሚሆኑ አገባባት

ሐይቅ፣ ድንጋግ፣ ወሰን፣ ገበዝ፣ ዘፈር፣ ጸድፍ፣ ጽባሕ ዳርቻ ይሆናሉ።
በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ፣ ገበዝ፣ ዘፈር፣ ጸድፍ፣ ጽባሕ አይገኙም። በአለቃ ታየ አገባብም፣ ዘፈር፣ ጸድፍ፣ ጽባሕ አልተካተቱም። በጎንጅ አገባብ ሁሉም ዳርቻ የሚሆኑ አገባባት የሉም
ሐይቀ ባሕር ሲል የውሀ ዳርቻ ነው። ድንጋግ ባሕር ሲል የውሃና የደረቅ መገናኛ ማለት ነው። ወሰን ከጎብስትና ከልብስ በስተቀር በሰዋስው ሁሉ ይነገራል። ሲነገርም ወሰነ ባሕር፣ ወሰነ ሀገር እያለ ይገባል። ገበዝ ለባሕርና ለወንዝ ብቻ ነው። ገበዘ ሀገር፣ ገበዘ ተከዚ ይላል።
ዘፈር ዳርቻ ሲሆን የሚነገረው ለልብስ ብቻ ነው። ሲነገርም ለመንዲልከ ዘፈሮ ማለቱን ያሳያል። ከንፈር ዳርቻ ሲሆን ከንፈር ባለው ነገር ሁሉ ይነገራል። ከንፈረ ሀገር፣ ከንፈረ ባሕር፣ ከንፈረ ጸድፍ ይላል።
ጽባሕ ለሊት ነው። በጽባሕ ጌሠት ማርያም መግደላዊት ኀበ መቃብረ እግዚእነ ይላል። ለምድርም ይሆናል። ጽባሓ ለምድር አድማስ ይላል።

፴፰. አውራጃ የሚሆኑ አገባባት

አድያም፣ ደወል፣ ብሔር አውራጃ ይሆናሉ። በቂም ቅጽልም ይሆናሉ /ለቦታ/ ሁሉም ነባር

ናቸው፡፡አድያም ለወንዝ ለሀገር ነው፡፡አድያመ ዮርዳኖስ፣ አድያመ ግብጽ ይላል፡፡ ደወል፣ ብሔር ለቤት ለሀገር ነው፡፡ ደወለ ቤት ደወለ ሀገር፣ ብሔረ ቤት፣ ብሔረ ሀገር ይላል፡፡

፴፱. አጠገብ የሚሆኑ አገባባት

ጥቃ፣ ገቦ፣ ጎር፣ ጉንድ፣ ሕፅን፣ አጠገብ ይሆናሉ፡፡ በቂም ቅጽልም ይሆናሉ፡፡ ጥቃ ሲነገር ነበረ በጥቃሁ ይላል፡፡ ገቦ አገባብ ሲሆን በራሱ ይነገራል፡፡አገባብ ከቦታ ነው፡፡ ገቦ ገቦየ በለኒ ይላል፡፡ ፍችው ከባለቤት ወደ ዘርፍ ነው፡፡ ቦታ ሲሆን አድባረ ጽዮን በገቦ መስዕ ይላል፡፡ አካል ሲሆን ተረግዘ ገቦሁ በኩይናት ይላል፡፡ ጎር ሲሆን በጎረቤት ባለው ይቀራል፡፡ ጉንድ ሲገባ ነበረ ጉንደ ዕፅ ይላል፡፡ ሕፅን ሲነገር ዮሐንስ ነበረ ወረፈቀ ውስተ ሕፅኑ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይላል፡፡ በአካል ሲገባ ስምዖን ተወክፎ ውስተ ሕፅኑ ለኢየሱስ ማለቱን ያሳያል፡፡

፵ ግድም/ አግድም የሚሆኑ አገባባት

ግድም አግድም ይሆናል፡፡ የአነጋገር የአካሄድ ነው፡፡ በደጊመ ቃል ይነገራል፡፡ ሲገባም ሀንካስ የሐውር ግድመ ግድመ /የአካሄድ/ ይላል፡፡ እንዲሁም አንትሙ ተሐውሩ ግድመ ግድመ፡ ወአነኒ አሐውር ግድመ ግድመ ይላል፡፡ የአነጋገር ሲሆን ብእሲ ይትናገር ግድመ ግድመ ይላል፡፡

፵፩ በዚህ፣ ከዚህ ወደዚህ የሚሆን አገባብ

ዝየ፣ በዚህ፣ ከዚህ፣ ወደዚህ ይሆናል፡፡ ፍጹም ነባር ነው፡፡ የቅርብ፣ ቅርብ ነው፡፡

ዝየ አጎድር፣ ምንት ብከ ዝየ፣ አምጽእዎን ሊተ ዝየ ይላል።።
ህየ በዚያ፣ ከዚያ፣ ወደዚያ ይሆናል።። ነባር ነው።። የቅርብ ሩቅ ነው።። ህየ የዝየ አንጻር ነው።። በቦታ፣ በነገር ዐጻፋ ይገባል።።
በቦታ ሲገባ ተከለ ገሃተ ወሜሞ ህየ ይላል።።
ንበር ህየ፣ ተንሥእ እምህየ፣ ህየ ንሰግድ ኩልነ ጎበ ቆመ እግረ እግዚእነ ይላል።።
ህየ በነገር ሲገባ፣ በህየኒ ሰመዮ ወልደ ይላል።።

፵፪ ወዲህ፣ ወደዚህ፣ የሚሆን አገባብ

ለፌ፣ ወዲህ፣ ወደዚህ፣ ይሆናል።። ነባር ነው።። ትመጽእ ለፌ ጎበ አነ እቀውም ይላል።። ተደጋግሞ፣ ተጫፍሮ ሲነገር ወዲህና ወዲያ፣ ግራና ቀኝ ይሆናል።። ሲገባም፣
ነጸረ ለፌ ወለፌ፣ ሰቀሉ ምስሌሁ ክልኤተ ፈያተ አሐደ እምለፌ ወአሐደ እምለፌ ይላል።።
ከሃ፣ ወዲያ፣ ወደዚያ፣ ከሃት ወዲያኞች ይሆናል።። ነባር ነው።። ሑር ከሃ፣ ዝርዎ ከሃ ይላል።። ከሃሁ፣ ከሃከ፣ ከሃቲሁ እያለ ይዘረዝራል።።
ዝየ፣ ለፌ፣ በዚህ፣ ከዚህ ወደዚህ ይሆናሉ።። ሲነገሩም፣ ንበር በዝየ፣ ተንሥእ እምለፌ ይላል።።
ከሃ፣ ህየ፣ በዚያ፣ ከዚያ፣ ወደዚያ ይሆናሉ።። የቅርብ ሩቅ ናቸው።። ሁሉም የቦታ ቅጽሎች ናቸው።። ቅጽል ሆነው ሲገቡም፣
ዝየ መካነ፣ ለፌ መካነ፣ ህየ መካነ። በዝየ መካን፣ በለፌ መካን፣ በህየ መካን ይላል።። ከሃ የቦታም የጊዜም ቅጽል ይሆናል።። ለምሳሌ በከሃ መካን፣ በከሃ ዓለም ይላል።። በታየ ነገር ድርስ ቅጽል፣ ባልታየ ዐጻፋ ይሆናል።። በዐጻፋ ሲነገር አምላክ ተሰቅለ በቀራንዮ እስመ ተቀብረ አዳም በህየ፣ እስመ ተቀብረ አዳም በከሃ፣ በዝየ ይላል።።

ለእነዚህም ስድስት አገባባት ይስማሟቸዋል። እነዚህም እም መነሻ፣ ጎበ መንገለ መገስገሻ፣ እስከ መድረሻ፣ በ በቁም ቀሪ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው። ሲነገሩም እምለፌ እስከ ለፌ፣ እምዝየ እስከ ዝየ ይላል። ከሃ ሲነገር መንገለ ከሃ እንተ ከሃ ይላል። እንተ እለ ዘ ቅጽል ናቸው።

፵፫ ዙሪያ የሚሆኑ አገባባት

ዐውድ፣ ዘውር ዙሪያ ይሆናሉ። አገባብነታቸው የቦታ ነው። ክበብ ባለው ሁሉ ይገባሉ።
ዐውደ ቤት፣ ዘውረ አክሊል፣ ይላል። ዐውድም ሆነ ዘውር በዝርዝር ይነገራሉ። ለምሳሌ ይቀውሙ ዐውዶ፣ ይላል። ዐውዱ፣ ዐውዳ፣ ዘውሩ፣ ዘውራ እያለ ይዘረዝራል። ዐውድ ተለይቶ አደባባይ፣ ሸንጎ፣ ዐውድማ ይሆናል። ለምሳሌ ነበሩ ዐውደ ለኰንኖቱ፣ ዘቦቱ ያነጽሕ ዐውደ እክሉ፣ ይላል። ሸንጎ ሲሆን ንንሥት ዐውደነ ይላል። ዐውድና ዘውር የሚገኙት በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ እና በአለቃ ታየ አገባቦች ነው። በዋድላና በጎንጅ አገባቦች አይገኙም።
ከዚህ በፊት የተነገሩት የቦታ አገባቦች በሙሉ ባለቤት ሲኖር ቅጽል፣ ባለቤት ሳይኖር በቂ ይሆናል።

፵፬ በሁሉ ዘንድ የሚሆኑ አገባባት

ኩለሄ፣ ጎበ ኵሉ በሁሉ ዘንድ ይሆናሉ። ነባር ነው። ኩለሄ ዘርፍ ከባለቤት፣ ጎበ ኩሉ አገባብ ነው። ለ፣ በ፣ እም ይስማሟቸዋል። ሲነገሩም ተገብረ ሠናይ በጎበ ኩሉ፣ ታቦት ልቡጥ በወርቅ እምኩለሄ፣ መጽአ ኩለሄ፣ ለጎበ ኩለሄ ይትገበር ሠናይ ይላል።

፵፭ ሁለመና የሚሆን አገባብ

ኵለንታ ሁለመና ሁለንተና፣ መላው፣ ጠቅላላው፣ ዙሪያ ገባው፣ አራት ማዕዘን ይሆናል። ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ያለውን ሰውነት ማለት ነው። ቅጽለ ኩሉ ወይም ኩላ ነው። ሐመ ኩለንታሁ፤ ሲል ሰውነቱን ሁሉ አመመው ማለቱ ነው። በዘርፍ ሲገባ ሰብአ ኵለንታ ይላል። እንተ ኵለንታሆሙ ምሉዐነ አዕይንት፤ ኵለንታኪ ሠናይት፤ ወኵለንታሃ በወርቅ ወበዕንቁ ፤ ተቋመ ማኅቶት ወኵለንታሃ ወርቅ፤ ኵለንታሃ ለዛቲ ምድር ይላል።

፵፮ አካል የሚሆኑ አገባባት

አካል፣ አባል፣ ሕዋስ፣ መንፈስ፣ ነፍስ፡ ነፍስት፣ ባሕርይ፣ ጠባይዕ፣ ሕላዌ፣ መሊሊት፣ አካል ይሆናሉ። አካል፤ ቆም ራእይ ነው። አባል አባለ ዘር ነው። ሕዋስ ስድስቱ በአፍኣ፣ ስድስቱ በውስጥ ያሉ ሰውነቶች ናቸው። እነርሱም ግራና ቀኝ እጅ፣ ግራና ቀኝ አፍንጫ፣ ግራና ቀኝ ዐይን፣ ታችና ላይ ከንፈር፣ ግራና ቀኝ እግር ናቸው። መንፈስ የሴት አካል፣ የወንድም ይሆናል። ነፍስ የሁሉም ነው። ነፍስት፣ አካል፣ ነፍስ፣ ባሕርይ የአነጋገር፤ ጠባይዕ የአራቱ ባሕርያት፤ ሕላዌ የአካል ነው። መሊሊት፣ አጽቅ፣ አጽቁ ነው። ነፍስ ረቂቅ አካል፣ የሥጋ ሕይወት ናት፣ መንፈስ ትንፋሽ፣ ረቂቅ ነገር ነው። ኩላን፣ ኩሎን እየያዙ ሁለንተና ይሆናሉ። ለምሳሌ ሐመ ኩሎ አካለ፣ ኩላ አካለ፣ ኩሎ ሕዋሰ፣ ኩላ ሕዋሰ ማለቱን ያሳያል።

፵፯ ወደ፣ ወዳ የሚሆኑ አገባባት

ውስተ፣ ለ፣ በ፣ ዘ፣ እንተ፣ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ፣ ተናባቢ ቀለማት፣ ወደ፣ ወዳ ይሆናሉ። ለ፣ በ፣ ዘ፣ እንተ፣ ወደ ወይም ወዳ ሲሆኑ ቀደም ሲል አሳይተናል። ከዚህ ቀጥሎ ከሌሎቹ በተጨማሪ

ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳብዕ ቀለማትና ውስተ በዐረፍተ ነገር እየገቡ ወደ ወይም ወዳ ሲሆኑ እናሳያለን፣

፩ ጸወዉ ሐዋርያት አሕዛበ ውስተ ንስሐ /ውስተ ወደ ሲሆን/

፪ ተመይጠ ለብሔረ ግብፅ /ለ ወደ ሲሆን/

፫ ዐርገ በሰማይ፣ ወረደ በምድር /በ ወደ ሲሆን/

፬ ዐርገ ኤልያስ ሰማየ፣ ወረደ እግዚአብሔር ምድረ። /ግእዝ ወደ ሲሆን/

፭ ሖረ ኢየሱስ ገሊላ፣ /ራብዕ ወደ ሲሆን/።

፮ ሖረ ጳውሎስ ተሰሎንቄ /ኀምስ ወደ ሲሆን/።

፯ ሖረ ጳውሎስ ደማስቆ /ሳብዕ ወደ ሲሆን/።

፬ ለጊዜ ቅጽልና በቂ የሚሆኑ ዘርና ነባሮች

፵፰ ፊት የሚሆኑ አገባባት

ቅድም፣ መቅድም፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ ፊት ይሆናለ። ቅድምና መቅድም ግእዝ ሆነው የቀሩት ጉልት ሆነው ሳይፋለሱ ይነገራሉ። ሲገቡም ከመቅድም እና ከአቅዲሙ በስተቀር እም፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ይስማሟቸዋል። ለምሳሌ መጽአ ይመጽእ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ መጽአ ቀዳሚ፣ መጽአ ዘእም ቀዲሙ፣ እንተ ቀዲሙ፣ እለ ቀዲሙ፣ እለ እምቅድም፣ ይላል። አምስቱም ለአንድና ለብዙ፣ ለወንድና ለሴት፣ ለቅርብና ለሩቅ እየሆኑ እንደየአንቀጻቸው ይፈታሉ። ለምሳሌ ቅድመ አሠኒ፣ መቅድመ ጎሠ፣ ቀዲሙ ዜነወነ፣ ዘነገሩክሙ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ ነገረ በአሪት፣ ቀዳሚ ጸሐፍኩ ለከ ይላል። ቅደመ እንደ ላዕለ፣ ድኅረ እና ግድመ በደኀመ ቃል ይነገራል። ቀዲሙ፣ አቅዲሙ ጉልት ናቸው።

በተጨማሪም ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ፣ ፊት፣ በፊት ተቀድሞ፣ ቀድሞ፣ አስቀድሞ፣ ተቀዳድሞ፣ አቀዳድሞ ይሆናሉ። ይህም ይታወቅ

ዘንድ ሲነገር መጽአ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ።።
ይመጽእ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ።።
ይምጻእ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ።።
ተቀድሞ ሲሆን ገብር ይመጽእ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ።። እም እንተ ባዕል ይላል።።
ቀድሞ ሲሆን ፈነወ ንጉሥ ገብሮ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ።። ይላል።።
አስቀድሞ ሲሆን ባዕል አብልዐ ካህነ ጎብስተ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ ይላል።።
ተቀድሞ፣ ሲሆን ገብር ይትራወጽ ቅድመ፣ መቅደመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ ምስለ በቅል ይላል።።
ተቀዳድሞ ሲሆን አግብርት ተራወጹ ቅድመ፣ መቅደመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ ድኅረ አፍራስ፣ ምስለ ወዐልት ይላል።።
አቀዳድሞ ሲሆን ንጉሥ አስተፋነወ ቅድመ፣ መቅድመ፣ ቀዲሙ፣ አቅዲሙ፣ ቀዳሚ አግብርተ እምአግብርተ ካልዕ ንጉሥ ይላል።።
እንደ አንቀጹ ይፈታል።። በፊት በኋላ ይነገራል።።
መቅድም ለአንድ ወንድ ባዕድ ቅጽል ይሆናል።። ሲበዛም መቅ ድም መቅድማን፣ መቅድምት መቅድማት ይላል።። መቅድም የመጽሐፍ መግቢያ፣ መጀመሪያ ይሆናል።። ሁሉም ቀደመ ከሚለው ሥርወ ግስ የተገኙ ናቸው።።

፵፱ ተከትሎ፣ አስከትሎ፣ ተከታትሎ፣ አከታትሎ፣ ኋላ የሚሆኑ አገባባት፣

ድኅረ፣ ደኃሪ፣ ድኅሪተ ተከትሎ፣ አስከትሎ፣ ተከታትሎ፣ አከታትሎ፣ ኋላ ይሆናሉ። በቀዳማይ፣ በካአይ ይነገራሉ። ለምሳሌ ተከትሎ ሲሆን፣
ነዳይ ይመጽእ ድኅረ ምስለ ንጉሥ ይላል።
አስከትሎ ሲሆን፣ ንጉሥ አብአ ድኅረ፣ ድኃሪተ፣ ድኅሪተ ነዳየ ቤቶ ይላል።
ተከታትሎ ሲሆን፣ ገብር ይትራወጽ ድኅረ፣ ድኃሪ፣ ድኅሪተ ምስለ ቢጹ ይላል።
አከታትሎ ሲሆን ንጉሥ ያስተራውጽ ድኅረ ፈረሰ ምስለ አፍራስ ይላል።
ኋላ ሲገባ፣ ድኩም ይመጽእ ድኅረ፣ ድኃሪ፣ ድኅሪተ ማለቱን ያሳያል።

፱ ጊዜ የሚሆኑ አገባባት

ወ፡ በ፣ ወርኀ፣ ፍኖ፣ ብሔር እና አፈ ጊዜ ይሆናሉ። ሲነገሩም ፍኖ ሰርክ፣ ፍኖ ኅሀ፣ አፈ ኅሀ፣ አፈ ጽባሕ፣ ፍኖ ጽባሕ በማለት በስድስት ጊዜያት ይነገራሉ።
ብሔር ጊዜ ሆኖ በዐረፍተ ነገር ሲገባ፡ እስመ ነግሕ ብሔሩ፣ ይላል።
ወ ጊዜ ሆኖ ሲገባ ወተወሊዶ እግዚእ ኢየሱስ፣ ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት፣ ወዘተ ይላል።
በ ጊዜ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ፣ በጥሬ ዘር፣ በሳቢ ዘር ይገኛል። ለምሳሌ በዕርገቱ፣ በምንዳቤሁ፣ በመዊያቱ፣ ይላል። ሙያቸው ጊዜ ነው።

፶፩. ፊት የሚሆኑ አገባባት

ፊት የሚሆኑ አገባባት ሁለት ሲሆኑ እነርሱም ቅድምና ፍጽም ናቸው። ቅድመ ፍጽመ ያለ እንደሆነ ፊትን፣ በፊት፣ ወደፊት ማለት ነው።
በዐረፍተ ነገር ሲገለጹ፣
ቅድመ ጠይቅ ወድኅረ ትጌሥጽ /አኅላማሽ ነው/
አነ አሐውር ፍጽመ፣ ቅድመ። /አኅላማሽ ነው/

ሐረ ቅድመ፣ ሐረ ፍጽመ ይላል /አነላማሽ ነው/

፱፪ ጥንት፣ መጀመሪያ የሚሆኑ አገባባት

አጎዝ፣ ጥንት፣ መሠረት መጀመሪያ፡ ጥንት ይሆናሉ።፡ አምስት አገባባት ይስማሟቸዋል እነርሱም በ፣ እም፣ አንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው፡፡ ቅጽልነት ይስማመቸዋል፡፡ አጎዝ ለሚገታ /ለሚታይ/ ነገር ሁሉ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ አጎዘ ነገር፣ አጎዘ ወርኅ፣ አጎዘ ማይ፣ ይላል፡፡ መሠረት የቤትና የነገር ነው፡፡ ለምሳሌ መሠረተ ቤት፣ መሠረተ ነገር ይላል፡፡ ጥንት ሲነገር ለተገኘው ሁሉ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ጥንተ ነገር፣ ጥንተ መሠረት፡ ጥንተ መድኃኒት ይላል፡፡ እለ፣ እንተ፣ ዘ በቅጽልነታቸው ይስማሟቸዋል፡፡ በገቢር በተገብሮ በ፲ ሠራዊት በዘመድ ይዘረዘራሉ፡፡ ቅጽልም በቂም ይሆናሉ፡፡

፱፫ መጨረሻ የሚሆኑ አገባባት

ተፍጻሜት፣ ተፍጻም፣ ፍጽም፣ ፍጻሜ፣ መጨረሻ ይሆናሉ፡፡ እንተ፣ እለ፣ ዘ፣ አስከ ይስማሟቸዋል፡፡ ሲነገሩም ተፍጻሜተ ሰማዕት፣ ፍጻሜ ሰማዕት፣ ተፍጻሜ ሰማዕት፣ ተፍጻመ ወልድ፣ ማለቱን ያሳያል፡፡ ተፍጻሜ ነገር፣ ፍጻሜ ነገር፣ ይላል፡፡ እንተ፣ እለ፣ ዘ ሲገቡ በቅጽልነታቸው ነው፡፡ እስከ መድረሻ ነው፡፡ ሲገባ እም መነሻ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ እም አጎዙ እስከ ተፍጻሙ፣ እመሠረቱ እስከ እስከ ተፍጻሜቱ፣ እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ይላል፡፡ ባለቤት ሲኖር ቅጽል፣ ባለቤት ሳይኖር በቂ ይሆናሉ፡፡

፱፬ ድሮ የሚሆኑ አገባባት

ትካት፣ ትማልም፣ ዓለም፣ ድሮ ይሆናሉ፡፡ ነባር ናቸው፡፡ በቀዳማይ፣ በካልአይ ይነገራሉ፡፡ ዓለም

ዘርፍ ከባለቤት ይሆናል። ትካት ዘርፍ፣ ትማልም የቅጽል መውደቂያ ሆኖ ዘርፍ ይሆናሉ። ሲነገሩም ሰብአ ዓለም፣ ዓለመ አበው ሲል ዘመን ነው። ሰብአ ትካት፣ ብእሴ ትካት፣ ዘትማልም ወዮም፣ እንተ ትማልም ወዮም፤ እደው እለ ትማልም ወዮም ይላል። ትካት፣ ትማልም በጽንዕ ይፈታል። ለምሳሌ መጽአ ትካት፣ ትማልም ይመጽእ ይላል። ዓለምን ዘ፣ እንተ፣ እለ ይስማሙታል። ቅጽልነታቸው ለዘመን ነው። ትማልምና ትካት ለገቢር ለተገብሮ ይከታሉ። ዓለም በገቢር ጊዜ ዓለመ ይላል።

፬ኛ አምና የሚሆኑ አገባባት

ትማልም፣ አስፈር፣ አሜር አምና ይሆናሉ። በቀዳማይ በካልአይ ይነገራሉ። እም፣ አስከ ይስማሟቸዋል። ሲነገሩም እምትማልም አስከ አስፈር፣ እስከ አሜር፣ እምዓለም አስከ አሜር፣ እምትካት እስከ አስፈር፤ ይላል። እንተ፣ አለ ዘ ይስማሟቸዋል። ቅጽልነታቸው ለዘመን ነው። አሜር፣ አስፈር፣ ገሪፍ ከመጻሕፍት ምስክር የላቸውም። ኀሪፍ ግን ኀድጋ ኀሪፊኒ እመ ትፈሪ ለዓሙ ይላል። ምንአልባት በሚመጣው ዓመት ብታፈራ አምና እንደተውካት ተዋት ማለት ነው።

፭ኛ ዘንድሮ የሚሆኑ አገባባት

ዮም፣ ኀሪፍ፣ ገሪፍ ዘንድሮ ይሆናሉ። በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ። ለምሳሌ እምትማልም ሠነየ ዮም፣ እምአሜር ይሴኒ ኀሪፍ፣ እምአስፈር ይሴኒ ገሪፍ ይላል። በገቢር ጊዜ አሜረ፣ አስፈረ፣ ገሪፈ ይላል።

፮ኛ ክርሞ፣ ነገ የሚሆኑ አገባባት

ጌሡም፣ ሳኒታ ከርሞ ይሆናለ።። በቀዳማይ፡ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራለ።። ለምሳሌ ኢትበለ ለጌሡም፣ ለሳኒታ ይላል።። ሳኒታ ተለይቶ ማግስት ወይም ነገ ይሆናል።። ለምሳሌ ነጋዲ ይመጽእ በሳኒታ ይላል።። ጌሡም በገቢር ጌሠመ ይላል።። ጌሡም፣ ሳኒታ ቅጽልም በቂም ይሆናሉ።።

፶፰ ዛሬ የሚሆኑ አገባባት

ዮም፣ ይእዜ ዛሬ ይሆናለ።። በቀዳማይ፡ በካልአይ፣ በሣልሳይ፣ በፊት በኋላ ይነገራለ።። ለምሳሌ መጽአ ዮም፣ ይእዜ ይመጽእ፣ ዮም ይመጽእ፣ ይእዜ ይመጽእ፣ ዮም ተወልደ ይላል።። ይእዜ የቀና ነው።። ዮም አርበኛ ነው አይለወጥም።። ዮም ለገቢር ለተገብሮ ይከታል።። በንጽጽር ሲታዩ ትማልም ትላንት፣ ዮም ዛሬ፣ ጌሡም ነገ የሚል ተከታታይ ትርጉም ይሰጣሉ።።

፶፱ አሁን የሚሆኑ አገባባት

ዓዲ፣ ዮም፣ ናሁ፣ ዮጊ አሁን ይሆናሉ።። በስም ነባር፣ በምሥጢር ጊዜ ናቸው።። በቀዳማይ፡ በካልአይ፣ በሣልሳይ፣ በሁለት ፀዋትው ይነገራሉ።። በአንድ ዖታ ሲነገሩ በተለየ ሰዋስው በዋዌ ይነገራሉ።። ይህም ናሁ ወጽአ ወናሁ አተወ ይላል።።
ዓዲ ሲገባ፣ ዓዲ ኢመጽአ፣ ዓዲ ኢይመጽእ፣ ዓዲ ይምጻእ፣ ይላል።።
ናሁ ሲገባ፣ ናሁ ዐርገ፣ ናሁ የዐርግ፣ ናሁ ይዕርግ ይላል።።
ዮጊ ሲገባ፣ ዮጊ በጽሐት፣ ዮጊ ትበጽሕ፣ ዮጊ ትብጻሕ ይላል።።
የዋዌ ነገር ከዚህ ይነገራል።። ሲነገርም ነጸረ ወርእየ ሲል የወ ፍቺ ፈጽሞ፣ ሙያው ጀምላይ።። ነጸረ

ወርእየ ተጀምላይ ናቸው። በሁለተኛው ዖታ ሲነገሩ በሁለት ይቤ ማለትም በጠያቂ በመላሽ እንዘ፣ ኢ መነሻ እየሆኗቸው ይገባሉ። ናሁ፣ ዮጊ፣ ነየ፣ ነዋ እነሆ ሲሆኑ ይቀድሙላቸዋል። ሲነገሩም ይቤሎ ለዘይቤሎ ወልድከኑ መጽአ፣ ነዋ፣ ናሁ፣ ዮጊ፣ ዬ፣ ነየ፣ እንዘ ኢይመውት። መጽአ ዓዲ ዮጊ፣ ናሁ፣ ይእዜ፣ ማለቱን ያሳያል። ይእዜን ሰዓት ቢያገናኘው ተናግረውታል እንጂ ፍቺው ዛሬ ነው። አሁን አይሆንም። አጎላማሽም ቢሉ አገባብ ሆነ ሰዋሰው ሁሉ በምሥጢር ከቅጽል የሚወጣ የለም። ለምሳሌ ናሁ ይመጽእ፣ ናሁ ዓዲ ይመጽእ ሲል ለጊዜያት ቅጽል ናቸው። በግልሳይ ሲነገር የተምኔት ይመስላል። ይህም ይቤ ነዳይ ንጉሥ ዮጊ ይምጻእ ይላል። ዮም ለገቢርም ለተገብሮም ይከታል።

፷፩ ዳግመኛ የሚሆኑ አገባባት

ዓዲ፣ ካዕበ፣ ዳግመ ዳግመኛ ይሆናሉ። ዓዲ ነባር፣ ካዕበ ዳግመ ጥሬ ናቸው። ማሠሪያዎቻቸው ቀዳማይ፣ ካልአይ ሣልሳይ ናቸው። ሲገቡም በተለየ ሰዋስው በዋዌ ይነገራሉ። በሁለተኛው ነገር ይነገራሉ። አንድ ሳይባል ሁለት አይባልምና። ይህም ይታወቅ ዘንድ ቀተለ ይሁዳ አባሁ፣ ወዓዲ አውሰበ እሞ፣ ወዓዲ ሰቀለ እግዚኡ፣ ወካዕበ ሰቀለ እግዚኡ ይላል። ዓዲ ተለይቶ አሁን ገና ዳግመኛ፣ እንደገና ይሆናል፣ እንደገና ሲሆን ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሳሙኤል ዓዲ ሥልሰ፣ ሳሙ ቀደ. 1፡ 8
በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራል። በሁለት ይቤ በጠያቂ በመላሽ ዘጠኝ አገባባት እየቀደሙለት እስከ፣ በአይ፣ በማእዜ እየገባ ይነገራል። አገባቦችም፣ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ እመ፣ አመ፣ ኀበ፣ ድኅረ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ፣ በዘ፣ ምስለ፣ እንዘ ናቸው። ዓዲ፣ ዮጊ፣ ናሁ፣ ዬ፣ ነየ፣ ነዋ እነሆ ሲሆኑ ይእዜ ዮም አሁን ሲሆኑ ይስማማሉ። እንዲሁም እንበለ፣ ቅድመ፣ ኢ ሳ

ሲሆኑ ይስማማሉ፡፡ ለምሳሌ ዓዲ መጽአ ይመጽእ፣ ዓዲ ይቤሎ ለዘይቤሎ እምቅድመ ይሙት፣ ኢይሙት ወልድከኑ መጽአ ናሁ ዮጊ ዓዲ ይእዜ፣ ዓዲ መጽአ ዓዲ ይመጽእ፣ ዓዲ ተንሥአ እስመ ይኤዝዝ እግዚአብሔር እመ ይኤዝዝ ፣ አመ ይኤዝዝ፣ ጎበ ይኤዝዝ፣ እንዘ ይኤዝዝ፣ ድኅረ ይኤዝዝ፣ አግዚአብሔር ይቤሎ ለዘይቤሎ እንበለ ይትመሀርኑ ወልድከ መጽአ ነዋ ዮጊ ናሁ ዬ ነየ ዓዲ ኢነጸርክዎ ለዘመጽአ፣ ለእንተ መጽአ ወዓዲ ኢተራከበ ምስሌየ በዘመጽአ ይላል፡፡
በአለቃ ታየ አገባብ መሠረት ዓዲ በተጨማሪም ም፣ እነሆ ዳግመኛ ይሆናል፡፡

፷፪ እንግዲህ፣ እንግዲያው፣ እንኪያው የሚሆኑ አገባባት

እንከ፣ እም ዮም፣ እም ይእዜ፣ እንግዲህ፣ እንግዲያው፣ እንኪያው ይሆናሉ፡፡ በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ፡፡ ለምሳሌ ዮምሰ፣ እምይእዜሰ ይኩን ፍሥሓ ወሰላም ኮነ ፍሥሓ ወሰላም ይላል፡፡ እንከ ተለይቶ በቀዳማይ፣ በካልኣይ በሣልሳይ፣ በጽድቅ፣ በአሉታ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ እንከሰ መጽአ፣ ኢይመጽእ፡ እንከሰ ሞት ሠራቂ እስመ አጽአቆ አምላክ ኃያል ይላል፡፡ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ አስረጅ፣ እመ፣ ሶበ፣ ቢ ባ፣ ሂ ኒ ትራስ እየሆኑ እስከ በዮም፣ በማእዜ እየገባ ሰ፣ ሳ፡ ስ፡ ማ፡ ሲሆን ይስማሟቸዋል፡፡ በሁለት ይቤ በጠያቂ በመላሽ ይነገራሉ፡፡ አራት አገባባት እየቀደሙላቸው ይነገራሉ፡፡ አ፣ ሶ፣ ኬ፣ ቃለ ትዕግሥት፣ ቃለ መልእክት፣ እም፣ ከመ፣ እምዘ፣ ከ፣ ካ ፣ ሲሆኑ አ፣ ትራስ፣ ሰ፣ ሳ፣ ስ፣ ማ ሲሆኑ ይስማሙታል፡፡ ለምሳሌ፤

ይቤሎ ለዘይቤሎ ኤልያስኑ ኢሞተ፣ እንከሰ እምዘ ኢሞተ አይቴ በጽሐ እስመ ተነብአ እምገጹ ለሞት።
ይቤሎ ለዘይቤሎ እስከ ማእዜኑ እሄሉ ምስሌከ እምዮም እምዘ ሀሎከ ምስሌየ ተብሀልኬ፣ ተብሀልአ፣ ተብሀልሶ ወልድየ።
ይቤሎ ለዘይቤሎ እስከ ማእዜኑ ይመጽእ ወልድየ እምይእዜሰ እም እንተ ኢመጽአ፣ እምዘ ኢመጽአ፣ እምከመ ኢመጽአ ሞተኬ።
ይቤሎ ለዘይቤሎ እስከ ማእዜኑ ትዜከሮ ለእግዚአብሔር እስከ ዮም፣ እም ዮምሰ እመ ኢተዘከርክዎ ለእግዚአብሔር አልብየኬ ተስፋ።
ይቤሎ ለዘይቤሎ ኦ ወልድየ ኢረዳእከኒ እምዮምሰ እመኢረዳእኩከ እነብር ምስለ ባዕዳን።
ይቤሎ ለዘይቤሎ ዮሐንስኒ ሞተ እንከሰ እምዘሞተ መኑ ዘገብረ ግዘተ በቅድመ ሄሮድስ ማለቱን ያሳያል።
ሂ፣ ኒ፣ ሰ፣ ትራስ ሆነው ጥሰሸ ይሆናሉ። የትራስን ነገር ከዚህ ይናገሩታል። ትራስ የሚሆኑ ቀለማት ፲፬ ናቸው። እነርሱም ሀ ሁ ሂ ኑ ኒ መ ሰ ሶ አ ኢ ኬ እንጋ ያ ዮ ናቸው። ሀ ሲነገር በመኑ ገቢር ይነገራል። መነሀ፣ ተነሥሡ፤ ሁ ሲገባ ምንትሁ፤ ሂ ሲገባ ምንትሂ፣ ሰ እና መ ወዳቂውን ያነሳሉ። ተነሽን ይጥላሉ። ለምሳሌ እፎኑመ፣ እፎሰ፣ ይላል። ሶ ሲነገር አድጎንሶ ይላል። ኑ ሲነገር እፎኑ፣ አ ሲነገር አኮአ ይላል። ኢ ሲነገር እፎኢ፣ ኬ ሲነገር ምንትኬ ሰብእ ይላል። እንጋ ሲነገር እፎ እንጋ ያልተስማማ፣ ያ ሲገባ ዘየሀይደኒያ፣ ዮ ሲገባ ሀበኒዮ፣ ኒ ሲገባ ምንትኒ ማለቱን ያሳያል። /ተደራቢ ዝርዝር ነው/።

፷፫ ልጅነት የሚሆኑ አገባባት

ንዕስ፣ ናዕስ፣ ንዕስና ልጅነት ይሆናሉ። በስም ዘር፣ በምሥጢር ጊዜያት ናቸው። ሰባት አገባባት ይስማሟቸዋል። አገባቦችም ኀበ፣ ከመ፣ አመ፣ እም፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው። ሲነገሩ ተመይጠ ኀበ ንዕስናሁ። ሕጻን ይበኪ እምንዕስናሁ፤ አመ ንዕስናሁ። አረጋዊ ይትአኀዝ ከመ ንዕሱ። ይሔሊ ብእሲ ነገረ ዘንዕሱ፣ እንተ ንዕሱ፣ ነገራተ እለ ንዕስናሁ፤ ኢትመንኑ አረጋዌ አመ ርሥእናሁ ማለቱን የሳያል።

፷፬ እርጅና የሚሆኑ አገባባት

ርሥእ፣ ርሥአን፣ ርሥእና እርጅና ይሆናሉ። በስም ዘር፣ በምሥጢር ጊዜያት ናቸው። ርሥእ ዘር፣ ርሥአን ርሥእና ምዕላድ ናቸው። ሰባት አገባባት ይስማሟቸዋል። እነርሱም እም፣ ከመ፣ እስከ፣ አመ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው። ሲገቡም ይትሜነን አረጋዊ አመ ርሥእናሁ። ኢትጎድገኒ በመዋዕለ ርሥእየ ይላል። ይትሜነን ነገር ዘርሥእና፣ ነገር እንተርሥእና፣ ነገራት እለ ርሥእና፣ እምንእስ እስከ ርሥእና፣ እምንእሱ አስከ ርሥአኑ ማለቱን ያሳያል። ከተስማማ በሌላ አገባባት ሁሉ ይገባል። ሲገባም አልቦቱ አምሳል ለርሥእና ይላል።

፷፭ በአጻፋ ማሰሪያ አንቀጽ የሚነገሩ አገባባት

፩ ፦ ተፍጻሜት፣ ፍጻሜ፣ ተፍጻም፣ መጨረሻ ሲሆኑ፣
፪ ፦ አንጻር፣ መንጸር፤ አፍዛኛ ሲሆኑ፣
፫ ፦ ተውላጥ፣ ውላጤ፤ ለውጥ ሲሆኑ፣
፬ ፦ ምስል፣ መምስል፣ አምሳል፣ አምሳያ፣ በቁም ቀሪ ሲሆኑ፣
፭ ፦ ትእምርት፣ እማሬ፣ ተአምር፣ አርአያ ምልክት ሲሆኑ፣

፮፥ ፍዳ፣ ብድራት ሲሆን፡ በአጻፋ ማሠሪያ አንቀጽ ይነገራሉ።።

ለሁሉም የሚስማሚቸው ግሶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።። ኮነ፣ ረሰየ፣ ገብረ፣ ተጸውዐ፣ ተሰምየ፣ ጸድቀ፣ ተመነየ፣ ተናፈቀ፣ ተሀበለ፣ ተሐሰወ፣ ተጠየቀ፣ ተለበወ፣ ተበአለ፣ ተአተተ፣ ተአውቀ፣ ተአምረ፣ ተርእየ፣ ተነጸረ፣ ተሐየጸ፣ ተከሥተ፣ ተግኀደ፣ ተመሰለ፣ ተርፈ ናቸው።።

ኮነ እና ረሰየ ተውላጠን ውላጤን ፍዳን ይስባሉ።።

ከላይ የተዘረዘሩት አገባባት በዐረፍተ ነገር እየገቡ ሲገለጹ ምን እንደሚመስሉ ከዚህ የሚከተሉትን ተመልከት።።

ተጸውዐ ጴጥሮስ ለስብከተ ወንጌል ምስሉሂ፣ አምሳሉሂ ተአውቀ ለመምህራን።። ወምስሎሂ፣ አምሳሎሂ፣ አእመሩ።።

ተሰምየ ዮሐንስ ሐዋርያ አርአያሁኒ ወእማሬሁ፣ ትእምርቶሂ አርዳኢሁ ገብሩ።። ጸድቀ ነገረ ጴጥሮስ ወተፍጻመ፣ ተፍጻሜቱሂ ተከሥተ ለኩሉ ወፍጻሜሁኒ፣ ተፍጻሜሁኒ መሀሩ አርዳኢሁ።።

ተመነየ አዳም ድኅነቶ ወአንጻሩ ተርእየ ለጊጉያን ወአንጻሮሂ ተለዉ ነሳሕያን።። ተሀበለ ይሁዳ ሠይጦተ ወልድ ወምስሉሂ ዐብየ በጊጉያን ወአምሳሎሂ ኢ፡ንደጉ ጊጉያን ።።

ተለበወ፣ ተአምረ፣ ተጠየቀ፣ ነገረ ኂቆዲሞስ ውላጤሁኒ ኮነ ድኅነተ ሕዝብ፣ ድኅነተኒ፣ ተውላጠኒ።።

ረሰየ ጴጥሮስ፣ ተሰአለ ጢባርዮስ ሞተ አምላክ ፍዳሁኒ ኮነ ሎቱ ትንሣኤሁ ለወልድ ወፍዳሁኒ ረሰዮ ካልአ ይላል።።

፷፮ ሁልጊዜ የሚሆኑ አገባባት

ኵሎ ሰዓተ፣ ኵሎ ጊዜ፣ ኵሎ አሚረ፣ ኵሎ ዕለተ፣ ኵላ ሰዓተ፣ ኵላ ጊዜ፣ ኵላ አሚረ፣ ኵላ ዕለተ፣

ሁልጊዜ ይሆናሉ። ለምሳሌ ይትናገር ኵሎ ጊዜ፣ ኵሎ ዕለተ፣ ኵላ አሚረ፣
ኵሎ አሚረ እባርክከ ወእሴብሕ ለስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ይላል።

፷፯ ዘወትር፣ እዘውትሮ የሚሆኑ አገባባት

ወትረ፣ ውቱረ፣ ዘልፈ፣ ዝሉፉ፣ ዝላፉ፣ ለዙሉፉ፣ ለዝላፉ፣ ዘልፍ፣ ወትር፣ ዘወትር አዘውትሮ ይሆናሉ። በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ። ዳዕሙ፣ ባሕቱ እንጅ፣ ወ ሊ ላ ል ሰ፣ ሳ ሲሆን እና ኢ በንዑስ አንቀጽ ገብቶ እንዳ እና ሳ ሲሆን ይስማሟቸዋል። ሲነገሩም ወትረ ውቱረ የሐውር። ዘልፈ፣ ዝሉፈ የሐውር ይላል። በአገባብ ሲገባ ባሕታዊ ይመጽእ ለዝሉፉ ለዝላፉ ባሕቱ ዳዕሙ ይተርፍ ወይትቀነይ ለእግዚአብሔር ወይገብር ፈቃዶ ለእዚአብሔር ኢይግበር ጌጋየ ተቀንዮቱሰ ኢይትነገር ይላል። ወትር፣ ዘልፍ ዘወትር ይሆናል። ስምዐነ እግዚአብሔር ጸሎተነ ዘወትር፣ ጸሎተነ ዘዘልፍ ይላል። እንዲሁም ወትረ ድንግል ማርያም ሲል ማርያም ምንጊዜም ድንግል ናት ማለት ይሆናል።

፷፰ አንድነት፣ አብሮ የሚሆኑ፣

ኀቡረ፣ ደርገ፣ ድርገተ አንድነት አብሮ ይሆናሉ። ኀቡራን፣ ድርገታት ተብለው በብዙ ይነገራሉ። ደርገ፣ ድርገተ ኀቡረ በሁሉ ይሆናሉ። ሲገቡም ብእሲ ሐረ ኀቡረ ምስለ ብእሲ፣ ሐረ ደርገ፣ የሐውሩ ኀቡራነ፣ የሐውሩ ድርገታተ፣ የሐውሩ ደርገ ይላል።

፷፱ አገባብ፣ የተገባ የሚሆኑ፣

መፍትው፣ ፍትሕ፣ ርትዕ፣ ርቱዕ፣ ድልወት፣ ኩነት፣ ጽድቅ አገባብ ወይም የተገባ ይሆናሉ። ኩነታት፣

ድልወታት በብዙ ሲሆኑ መፍትው በሩቅ በቅርብ ወንድ እየገባ አነ በሚለው ይነገራል። ፍትሑ፣ ድልወቱ፣ ጽድቁ እያለ ይዘረዝራል። መፍትው፣ ርትዕ አይዘረዝርም።በባለቤትነት የሚስማሟቸው፣ ንዑስ አንቀጽ፣ ሳቢ ዘር፣ ዘንድ አንቀጽ እመ፣ ሶበ ናቸው። በዘንድ አንቀጽ ሲገባ መፍትው ከመ ያድኅኖ ለአዳም አምላክ፣ በሳቢ ዘር ሲገባ፣ ጽድቅ ለአምላክ ዕርገተ ሰማይ፣ በዘንድ ሲገባ አምላክ ያድኅኖ ለአዳም ድልወቱ፣ እመ ሲገባ ድልወታት እመ ተነግሩ ስድስቱ ቃላተ ውንጌል ይላል። እነዚህም በየውህት በሁለት ፀዋትው በመሰርይ በአንድ ዖታ በአራት መዓርጋት በ፪፻፶ አናቅጽ ይረባሉ። የውእቱ አግባብ ይስማማቸዋል። መፍትው ከመ ያድኅኖ ለአዳም አምላክ እስመ መሐለ እንዘ ይምሕል ሎቱ። አምላክ ተሰቅለ እስመ ድልወቱ ከመ ያድኅኖ ለአዳም፡ማለቱን ያሳያል።

ከደቂቅ አግባባት ውስጥ ተውሳክ ግስ ሆነው የሚያገለግሉም አሉ። ተውሳክ ማለት ወሰከ ጨመረ ከሚለው ግስ የወጣ ባዕድ ዘር ሲሆን ተውሳክ ግስ ማለት በሰዋስው አነጋገር አንቀጽ አጎላማሽ ማለት ነው። ተውሳክ ግስ በግስ ላይ እየተጨመረ ግሱን በትርጉም የሚያጎላ ነው። ግሱ በዐረፍተ ነገር ሲገለጽ እንዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ የት፣ በምን ሁኔታ አንድ ድርጊት እንደተፈጸመ ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርገው ተውሳክ ግስ ነው። በዚህ መሠረት፣ ተውሳክ ግሶች ሁኔታን፣ ጊዜን፣ ቦታን፣ የነገር ድግግሞሽን፣ እርግጠኝነትን የሚገልጹ ቃላት ናቸው። ተውሳክ ግስ ከሚሆኑ ደቂቅ አግባባት መካከል፣ ቅድመ፣ ፍጽመ፣ ግድመ፣ ለፈ፣ ድኅረ ወዘተ የሚገኙ ሲሆን በምሳሌ ሲገለጽ፣ ሐረ ድኅረ፣ ሐረ ቅድመ ይላል። መፍትው፣ ፍትሕ፣ ርትዕ፣ ርቱዕ፣ ድልወት፣ ኩነት፣ ጽድቅ የመሳሰሉት በተጨማሪም ተውሳክ ግስ ሆነው ያገለግላሉ።

ለማሳያ ያህል እስከዚህ ድረስ የተዘረዘሩትን አቀረብን እንጂ ደቂቅ አገባባት እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ሌሎችም ደቂቅ አገባባት ሊኖሩ ይችላሉ።
ተፈጸመ ደቂቅ አገባብ።

፷፫. ደቂቅ ርባታ አገባብ

ሦስተኛው የአገባብ ክፍል ደቂቅ ርባታ ሲሆን በሁለት ይከፈላል። አንደኛው ደቂቅ ቅጽል /አፃፋና ቅጽል/ ሲሆን ሁለተኛው ነባር አንቀጽ ነው። በመጀመሪያ የምንመለከታቸው ዐፃፋና ቅጽል የሚሆኑ ደቂቅ አገባቦችን ነው። እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

፩ አጻፋና ቅጽል የሚሆኑ ደቂቅ አገባባት

አመልካች ደቂቅ ቅጽሎች በዐይን ጥቅሻ፣ በከንፈር ንክሻ የሚታዩ ናቸው። እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣

ውእቱ	ዝኩ	ዝስኩ	ዝክቱ
ውእቶሙ	እሙንቱ	እልክቱ	ይእቲ
እንትኩ	እንታክቲ	ውእቶን	እማንቱ
እልኩ	ዝ	ዝንቱ	እሉ
እሎንቱ	ዛ	ዛቲ	እላ
እላንቱ	እሎን	አንተ	አንቲ
አንትሙ	አንትን	አነ	ንሕነ
ለሊሁ	ኪያሁ		

ከዚህ የሚከተሉትም በደቂቅ ርባታ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን ባሕርያቸው ሲመረመር የአጻፋነት፣ የቅጽልነት፣ የነባር አንቀጽነት፣ የአንቀጽ አጎላማሽነት ይዘት ያላቸው ናቸው።።
ትእምርት እማሬ ተአምር መምስል፣ ምሳሌ ምስል አምሳል አርአያ ተውላጥ ውላጤ
ኢ አኮ ሐሰ ኮነ ሀሎ ቦ
አልቦ ባሕቱ ባሕቲቱ ዳዕሙ ዕራቁ
ኅቡረ ደርገ ድርገተ መፍትው ፍትሕ
ርትዕ ርቱዕ ድልወት ኩነት ጽድቅ፣
ናቸው።።

ደቂቅ ቅጽሎች

፩፥ ያ፣ ያው፣ ያኛው የሚሆኑ አገባባት፣

ውእቱ፣ ዝኩ፣ ዝስኩ፣ ዝክቱ፣ ያ፣ ያው፣ ያኛው ይሆናሉ።። ለርእይ የቀረቡ፣ ለሰሚዕ የራቁ ሲሆኑ የቅርብ ሩቅ ደቂቅ ቅጽሎች ናቸው።። ዐፃፋ ሲሆኑ፣ አዕረፈ እግዚእ በሳብዕት ዕለት እስመ ውእቱ፣ ዝኩ፣ ዝስኩ፣ ዝክቱ ፈጸመ ግብሮ ይላል።።
ሰመይዎ ስሞ ኢየሱስሀ እስመ ውእቱ፣ ዝኩ፣ ዝስኩ፣ ዝክቱ ያድኅን ሰብአ፣

፪፥ እኒያ፣ እሊያው የሚሆኑ አገባባት፣

ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እልክቱ እኒያ፣ እሊያ፣ እሊያው ይሆናሉ።። ለብዙ ሩቅ ወንዶች ቅጽልና ዐፃፋ ይሆናሉ።። ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ብዑዓን መሐርያን እስመ ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እልክቱ ይትሜሐሩ በመንግሥተ ሰማይ፣ ብዑዓን ገባርያነ ሰላም እስመ ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እልክቱ ይወርስዋ ለምድር፣ ሐዋርያት ቀሰምክምዋ ለዓለም እስመ አንትሙ ጌዉ ለምድር ይላል።።

፫፥ ያች፣ ያችው የሚሆኑ አገባባት፣

ይእቲ፣ እንትኲ፣ እንታክቲ፣ ያች፣ ያችው ይሆናሉ፡፡ ለአንዲት ሩቅ ሴት ቅጽል አጻፋ ሲሆኑ በዐይን ጥቅሻ፣ በከንፈር ንክሻ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ዮም ንወድሳ ለማርያም እስመ ይእቲ፣ እንትኲ፣ እንታክቲ፣ ተዐቢ እምኪሩቤል ይላል፡፡

፬፥ እሊያ፣ እሊያው የሚሆኑ አገባባት

ውእቶን፣ እማንቱ፣ እልኵ፣ እኂያ፣ እኂያው ይሆናሉ፡፡ ለብዙ ሴቶች ቅጽልና አጻፋ ይሆናሉ፡፡ ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ይፈትላ ወርቀ ወሜላተ አማንቱ ደናግል እስመ ውእቶን፣ እማንቱ፣ እልኵ፣ የአምራ ግብረ እድ ይላል፡፡

፭፥ ይህ፣ ይኸው የሚሆኑ አገባባት፣

ዝ፣ ዝንቱ፣ ይህ፣ ይኸው ይሆናሉ፡፡ ለወንድ የቅርብ ቅርብ ዐፃፋና ቅጽል ናቸው፡፡ ቅጽል ሲሆን ዝንቱ ሚካኤል፣ ዝንቱ ገብርኤል፣ ዝ ብእሲ፣ ዝንቱ ብእሲ ይላል፡፡ ባልታየ ነገር ሲገቡ በገቢር ተነስተው በተገብሮ፣ በተገብሮ ተነስተው በገቢር በአንቀጽ በዘርፍ በባለቤት በሰዋስው ሁሉ ይታጸፋሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ጊዮርጊስ መጽአ እስመ ለዝንቱ ጸውያ አምላኩ፡ እስመ ዘንተ ጸውዐ ንጉሥ ይላል፡፡ ጊዮርጊስ ርሀብ በልዐ ኀብስተ አሚን እስመ ዝንቱ ይሴንዮ ይላል፡፡

ገብረ ሕይወት ኢበልዐ እክለ እስመ ዝንቱ መነነ ዓለመ፡፡ ዝንቱሰ ይትርፍ ጥቀ ኢጠበወ ጥበ እሙ፡፡
ተአውቀ ስብከተ ጴጥሮስ እስመ ዝንቱ ይሴኒ በዙሉ፡፡
ሚካኤል ወረደ ኀበ ሙሴ እስመ ዝንቱ ያፈቅሮ ለዝንቱ ይላል፡፡
በአገባብ ሲሆን ሕሙም አተበ ገጸ በመስቀል እስመ ዝንቱ ውእቱ ፈዋሴ ድውያን፡፡
ሙሴ ሖረ ኀበ ግብፅ እስመ ዝ፣ ዝንቱ ተፈነወ ኀበ ፈርዖን፡፡
ሖረ ሙሴ ምስለ አሮን እስመ ዝ፣ ዝንቱ፣ ኮኖ አፈ ይላል፡፡

፮ እሊህ፣ እሊኽው የሚሆኑ አገባባት፣

እለ፣ እሎንቱ፣ እሊህ፣ እሊኽው ሆናለ፡፡ ለብዙ ወንዶች ዐፃፋና ቅጽል ይሆናለ፡፡ ባለቤት ሲኖር ጭብጥ ቅጽል፣ ባለቤት ሳይኖር አጻፋና በቂ ይሆናለ፡፡ ሲገቡም እለ ሰብእ፣ እሎንቱ ተጠምቁ ወእሎንቱ ተፈወሱ ይላል፡፡ እለ ለገቢር አይሆንም፡፡ እሎንቱ ግን እሎንተ ይላል፡፡ ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ይባርክዎ አድባር ወአውግር ለእግዚአብሔረ እስመ እለ፣ እሎንቱ ተፈጥሩ በእግዚአብሔር ይላል፡፡

፯ ይች፣ ይችው የሚሆኑ አገባባት፣

ዛ፣ ዛቲ፣ ይች፣ ይችው ይሆናለ፡፡ ለአንዲት ቅርብ ሴት ቅጽልና ዐፃፋ ይሆናለ፡፡ ሲነገርም ዛ አንቀጽ እንተ እግዚአብሔር፣ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም፣ ምስለ ዛቲ ትውልድ፣ ዛቲ ትውልድ ተንሣ ለሙ ይላል፡፡ በጊቢር ጊዜ ዛ፣

ዛተ ይላል። ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ጎረያ እግዚአብሔር ለጽዮን እስመ ዛ፣ ዛቲ ምዕራፉ ለዓለም ይላል።

፰ እሊህ፣ እሊኽው የሚሆኑ አገባባት፣

እላ፣ እላንቱ፣ እሎን፣ እሊህ፣ እሊኽው ይሆናሉ። ለብዙ የሩቅ ሴቶች በታየ ነገር ቅጽል፣ ባልታየ ነገር ዐፃፋና በቂ ይሆናሉ። ሲገቡም፣ በእላ ክልኤ ትእዛዛት ተሰቅሉ ኦሪት ወነቢያት ይላል። ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ያፈቅራ ደናግል ጠባባት ተግባረ እድ እስመ እላ፣ እላንቱ፣ እሎን ይፈትላ ወርቀ ወሜላት ይላል።
በገቢር ሲገቡ ደግሞ ወተዘመርነ እላ ክልኤተ ቃላተ ይላል። ?
፱ አንተ፣ አንቺ፣ እናንተ፣ እኔ፣ እኛ የሚሆኑ አገባባት፣

አንተ አንተ፣ አንትሙ እናንተ፣ አንቲ አንቺ፣ አንትን እናንተ፣ አነ እኔ፣ ንሕነ፡ እኛ፣ ይሆናሉ። በታየ ነገር ቅጽል፣ ባልታየ ነገር ዐፃፋ ይሆናሉ። የቅርብ ዐፃፋና ቅጽል ናቸው። ዐፃፋ ሲሆኑ፣ ትፈትን ልበ ወኵልያተ እስመ አንተ ተአምር ኵሎ፣ እሴብሐከ እግዚአብሔር እስመ አንተ ውእቱ ንጉሥየ ወአምላኪየ። ኦ ማርያም ብኪ ግርማ ራእይ እስመ አንቲ ተዐብዪ እምኪኑቤል። ኦ ደናግል ይደልዎክን ክብር እስመ አንትን ተጋደልክን ብዙኀ ይላል። ይቤ እግዚአብሔር ኩኑ ንጹሐነ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ ። ኦ አምላክ አትልወነ አስመ ንሕነ አግብርቲከ ንሕነ ይላል
አንተ በቁሙ አንተ፣ አነ፡ እኔ፣ ንሕነ፣ እኛ ሲሆኑ፡ በተገብሮ እንጂ በገቢር

አይሆኑም። ንዑስ አንቀጽ አይጫናቸውም። በታየ ነገር ቅጽል፣ ባልታየ ነገር
በቂ ሆነው ይነገራሉ፡ ይታጸፋሉ። የሚገሠግሡ አገባባት ይጫኗቸዋል። ሰባት አገባባትይስማሟቸዋል። አገባባቱም ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ዓዲ ም ሲሆኑ፣ ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ባሕቱ፣ ግን ሲሆኑ፣ ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ፣ ስንኳን፣ ሁ፣ ኑ፣ ን፣ ት፣ ሰ፣ ሳ፣ ስ ሲሆኑ ነው። ባሕቱ ተለይቶ ነገር ን ይሆናል። ገቢራቸው ኪያሁ፣ ኪያከ፣ ኪያየ፣ ኪያነ ናቸው።

፲ የደቂቅ ቅጽሎች የገቢርና የተገብሮ አጠቃቀም፣

ከላይ የተዘረዘሩት ደቂቅ ቅጽሎች በገቢርና በተገብሮ አጠቃቀም ጊዜ የተለያየ ባሕርይ አላቸው። ዝርዝር አጠቃቀማቸውን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።
በገቢር ጊዜ፣ ዝኩ፡ ዝኰ፣ ዝስኩ፡ ዝስኰ፣ ዝክቱ፡ ዝክተ፣ እንትኩ፡ እንትኰ፣ ዝ፣ ዘ፣ ዝንቱ፡ ዘንተ፣ እሎንቱ፡ እሎንተ ይላል። በሌላ በኩል ግን ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እልክቱ፣ ይእቲ፣ እንታክቲ፣ ውእቶን፣ እማንቱ፣ እልኩ፣ እላንቱ፣ እሎን፣ አንተ፣ አንትሙ፣ አንቲ፣ አንትን፣ አነ፣ ንሕነ ገቢር አይሆኑም። በለ ይሻሻላሉ እንጂ። ውእተ፣ ይእተ፣ ባለ ጊዜ ለጊዜ እንጂ ለሰው አይሆንም። ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ሁሉ ገቢራቸው ኪያሁ ነው። ኪያሁ፣ ኪያሆሙ፣ ኪያሃ፣ ኪያሆን፣ ኪያከ፣ ኪያክሙ፣ ኪያኪ፣ ኪያክን፣ ኪያየ፣ ኪያነ እያለ ይረባል።
ሁሉም አጻፋና ቅጽል ይሆናሉ። ቅጽል ሆነው በዐረፍተ ነገር ሲገቡም፣

> ውእቱ፣ ዝኩ፣ ዝስኩ ዝክቱ አረጋዊ መጽአ
> ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እልክቱ እደው መጽኡ፣
> ይእቲ፣ እንትኩ፣ እንታክቲ፣ ብእሲት መጽአት፣

ውእቶን፣ እማንቱ፣ እልኩ ደናግል መጽኣ በማለት ሁሉም እንደዚህ ይገባል።።
በቅርብ ቅጽል ሲገባ፣
አንተ ብእሲ መጻእከ፣
አንትሙ እደው መጻእክሙ፣
አንቲ ብእሲት መጻእኪ፣
አንትን አንስት መጻእክን፣
አነ መርድእ መጻእኩ፣
ንሕነ አርድእት አእመርነ ፈደለ ይላል።።
በዐረፍተ ነገር ሲነገርም፣ አሮን አሮን ግበር ለነ አማልክተ ዘወርቅ ዘየሐውሩ ቅድሜነ ወይመውዑ ፀረነ፣ እስመ ውእቱ ሙሴ፣ እስመ ዝኩሰ ሙሴ፣ እስመ ዝክቱ ሙሴ ዘአውጽአነ እምግብፅ ኢንአምር ዘኮነ።።
ሀለዉ እደው ነቢያት ውስተ ገነት እስመ ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እልክቱ፣ ኢጥዕምዎ ለሞት።።
ደናግል ያፈቅራ ግብረ እድ እስመ ውእቶን፣ እማንቱ፣ እልኩ ይፈትላ ወርቀ ወሜላተ።።
ተኮነነት ሔዋን እስመ ይእቲ፣ እንትኩ፣ መተረት እንትኩ ዕፀ በለስ።።
ይእቲ እንደ ውእቱ ይነግራል።።
ዝ፣ ዝንቱ ይህ፣ ይኸው ይሆናሉ።። የቅርብ ቅጽልና ዐፃፋይሆናል።። ሲገባም፣ ዝ ብእሲ፣ ዝ ሕዝብ፣ ዝ ቃል፣ ዝ መጽሐፍ ይላል።። ዝ በገቢር ጊዜ ዘ ይሆናል።። ሲገባም ትማልም አመ ተናገረ ዘ ቃለ፣ ዘንተ ቃለ ይላል።።

፲፩ የአመልካች ቅጽሎች የቅርብ አጠቃቀም፣

አንተ፣ አንትሙ፣ አንቲ፣ አንትን፣ አነ፣ ንሕነ የቅርብ ናቸው በዐረፍተ ነገር ሲገቡ፣
አንተ ብእሲ መጻእከ አነ መርድእ አእመርኩ ሰዋስወ

አንትሙ እደው መጻእክሙ ንህነ
አርድእት አእመርነ ፊደለ
አንቲ ብእሲት መጻእኪ
አንትን አንስት መጻእክን

፲፪ እሱ፣ ርሱ የሚሆን አገባብ

ውእቱ እሱ ርሱ ይሆናል። ሩቅ ድብቅ ነው። ነባር አንቀጽና ነባር ቅጽል ነው። በራሱም ሰዋሰው ይነገራል። እሱ ሲሆን ከአንድ ወደ ብዙ አይሄድም። ውእቱ ውእቱ፣ አንተ ውእቱ፣ ውእቶሙ ውእቱ፣ አንትሙ ውእቱ፣ ይእቲ ውአቱ፣ አንቲ ውእቱ፣ ውእቶን ውእቱ፣ አነ ውእቱ፣ ንህነ ውእቱ ይላል። ከአንድ ወደብዙ የሄደው የውእቱ ሰዋስው እንደሆነ አስተውል። የማይገሰግሱ አገባባት አይጫኑትም። በፊት እንደተነገረ አስተውል። ለዚህም ስድስት አገባባት ይስማሙታል። አሊህም ወ ኒ ሂ ጥቀ ስንኳን ሲሆኑ፣ ዓዲ ም ሲሆን፣ ባሕቱ ነገር ግን ሲሆን፣ ወ ሂ ኒ ጥቀ ስንኳን ሁ ኑ ት፣ን ሲሆን ሁ ሰ ስ ማ፣ ም ሲሆኑ ይስማሙታል። ይህም ይታወቅ ዘንድ ወረደ ሚካኤል እስመ ውእቱ ያድኅነ፣ ወውእቱ ዓዲ ውእቱ ውእቱሂ ውእቱኒ ተሰምየ ሊቀ መላእክት። አምላክ አጥፍኦሙ ለዳታን ወለአቤሮን ወውእቱ፣ ውእቱሰ፣ ባሕቱ ውእቱ ይሰመይ መሐሪ በላዕሌነ። ለምንት ኢፈርህዎ አሕዛብ ለእግዚአብሔር ወውእቱ፣ ውእቱሂ ውእቱኒ፣ ጥቀ ውእቱሂ ይትፈራህ ንጉሥ ምድራዊ ማለቱን ያሳያል። ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ ይእቲ፣ ውእቶን፣ እማንቱ፣ አነ፣ አንተ፣ አንትሙ፣ አንትን፣ ንሕነ እያለ በ፲ ሠራዊት ይዘረዘራል።
ቅጽል ሲሆን፣ ውአቱ ብእሲ፣ ይእቲ ብእሲት፣ ውእቶሙ እደው፣ ውእቶን አንስት፣ ይላል።
አጻፋ ሲሆን ውእቱ ይጸንዕ እምኔየ፣ ለምንት ኢፈርህዎ አሕዛብ ለእግዚአብሔር ወውእቱ፣ ውእቱሂ

ውእቱኒ፣ ጥቀ ውእቱሂ ይትፈራህ ንጉሥ ምድራዊ ይላል።።
ውእቱ ርሱ፣ እሱ ይሆናል።። ነባር ቅጽልና ነባር አንቀጽ ነው።። ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ ይእቲ፣ ውእቶን፣ እማንቱ፣ አነ፣ አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን፣ ንሕነ እያለ በ፲ ይዘረዝራል።። ቅጽል ሲሆን ውእቱ ብእሲ፣ ይእቲ ብእሲት፣ ውእቶሙ እደው፣ ውእቶን አንስት፣ ይላል።። ዐፃፋ ሲሆን ውእቱ ይጸንዕ እምኔየ ይላል።።

፲፫ እሱን/እርሱን፣ ያን፣ ያንን፣ ያኛውን፣ የሚሆን አገባብ

ኪያሁ እሱን/እርሱን፣ ያን፣ ያንን፣ ያኛውን፣ ይሆናል።። በ፲ ሠራዊት ይረባል።። ይህም ለገቢር እንጅ ለተገብሮ አይሆንም።። የውእቱ ተለዋጭ ነው።። ዘርፍ አይሆንም።። ተሳቢ፣ ዐጻፋ ነው እንጅ።። ሲነገርም ሚካኤል ወረደ ኀበ ሙሴ እስመ ኪያሁ ያድኅን ይላል።። ሲዘረዘርም ኪያሁ፣ ኪያከ፣ ኪያሆሙ፣ ኪያክሙ፣ ማለቱን ያሳያል።። ዝምድናው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።።

ውእቱ ኪያሁ አንትን ኪያክን አንተ
ኪያከ አነ ኪያየ ውእቶሙ ኪያሆሙ
ንሕነ ኪያነ ይላል።።

አንትሙ	ኪያክሙ
ይእቲ	ኪያሃ
አንቲ	ኪያኪ
ውእቶን	ኪያሆን

፲፬ እሱ ቅሉ የሚሆን አገባብ

ለሊሁ እሱ ቅሉ ይሆናል ። ዘርፍ አይሆንም። የማይገሰግሱ አገባባት አይጫኑትም። ለሊሁ፣ ለሊከ፣ እያለ በ፲ ሠራዊት ይዘረዘራል። ለዚህም የሚገሰግሱ አገባባት ይስማሙታል። እስመ አምላነ አኮኑ ለሊሁ ማለቱን ያሳያል። የለሊሁ ገቢር ኪያሁ ነው።
እገሌ፣ እከሌ፣ እንተኔ፣ እንተን ይሆናል። ሰውየው ታውቆ ስሙ ላልታወቀና ስሙ የታወቀውን ሰውዬ በመደበቅ የስም አጻፋ ምትክ ይሆናል።
እገሌ ለአንድ ለቅርብና ለሩቅ ወንድ ይሆናል፡
እገሊት ለሩቅና ለቅርብ ሴት ይሆናል
በብዙ እለ እገሌ፣ እለ እገሊት ይላል።
ለሰው ሲሆን በገቢር ጊዜ እገሌሀ፡ እገሊትሀ ይላል።
ለቦታ ሲሆን እገሌ፣ እገሊተ ይላል። ቅጽልም ዘርፍም እየሆነ ይነገራል። ቤተ እገሌ፣ ቤተ እገሊት ብሎ በዘርፍ ይነገራል።
ቅጽል ሲሆን ሑሩ ኀበ እገሊት ሀገር ይላል።
በቂ ሲሆን እለ ኢይብልዎሙ እገሌ ወእገሊት ይላል። እርሱም እርሷም ማለት ነው።

፲፮ ነው፣ ሆኖ ኖረ፣ ሆነ፣ ሆኖ ነበረ የሚሆን አገባብ

ውእቱ አንቀጽ ሲሆን፣ ነው፣ ሆኖ ኖረ፣ ሆነ፣ ሆኖ ነበረ ይሆናል። ይኖራል፣ ይባላል፣ ይሆን ነበር፣ ይኖር ነበር፣ ይባል ነበር፣ ይሁን፣ ይኑር፣ ይባል ብሎ ከውእቱ እስከ ንሕነ በ፲ ሠራዊት ይረባል። ነባር አንቀጽ ነው። ነባር መባሉ ለምንድን ነው ቢሉ በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በዘንድ፣ በሣልሳይ አንቀጽ ስለአለታየ ነው። እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ ቅጽል፣ ዘር፣ ሳቢ ዘር፣ ባዕድ ዘር፣ ስላልኖረው ነው።
እንደ አኮ፣ እንደ ቦ፣ እንደ አልቦ ለአንድ ለብዙ፣ ለሴት ለወንድ ይሆናል። በአንቀጽነት ሲነገር በየውሀት በሁለት ፀዋትው፣ በመሰርይ በሁለት ፆታ፣ በ፬ መዓርጋት በ፪፻፶ አናቅጽ ሰዋስው እየያዘ ይነገራል ። ሲነገርም በሁለት ፀዋትው ወንዶች

በአንድ ወገን ሴቶች፣ በአንድ ወገን በአንድ ያታ በአንተ አዋቂነት፣ በ፩ መዓርጋት፣ በ፪፻፵ አናቅጽ የውስጠዘ እርባታ፣ ፫ ቀዳማይ፣ ፫ ካልአይ፣ ፫ ሣልሳይ ነው። የአካል የግብር ለውጥ ይሆናል። በግብር ሲለወጥ **አንዱን በብዙ፣ ብዙውን በአንድ፣ የሴቶችን በወንድ፣ የወንዶችን በሴት ይለውጣል።** ለዚህም ፩ አገባባት ይስማሙታል። ማን ማን ናቸው ቢሉ ለ፣ በ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ ናቸው። ለምሳሌ፣
ኪሩቤል፣ ማርያም፣ በጸዊረ አምላክ።
ጴጥሮስ ብእሲት እምነ ፍርሐት።
ድንግል ገብርኤል በእንተ ንጽሕና።
አማኑኤል እም ለርኅራኄ ማለቱን ያሳያል።
በአካል ለውጥ ሲነገር አንዱን በአንድ፣ ብዙውን በብዙ፣ ሴቲቱን በሴት፣ ወንዱን በወንድ ይለውጣል። ሲነገርም ጴጥሮስ ፈርሀ ልብ፣ መላአክት ትጉሀን፣ ማርያም ንጽህት፣ ይላል።
ከዐሥሩ መደቦች አራቱ ሩቆች በቂና አንቀጽ እየሆኑ ራሳቸውን ይችላሉ። ምሳሌ፣
ውእቱ ዘፈጸመ ኵሎ ሕገ፣ ይእቲ እንተ ወለደት አምላከ፣
ውእቶሙ፣ እሙንቱ፣ እለ ሰበኩ ወንጌለ፣
ውእቶን፣ እማንቱ እለ ብዙኅ ተጋደላ፣
ዘ፣ እንተ፣ እለም፣ ባልገቡበት ቅጽልና ጥሬ ማሠሪያ ሲሆን፣
ውእቱ ሕያው፣ ወአኮ ምውት ፣
ውእቱ አብርሃም፣ ወይእቲ ሣራ፣ እሙንቱ ደቂቅ፣ ወእማንቱ አዋልድ ይላል።
ስድስቱ ቅርቦች፣ ግን የሩቅ አንቀጽ ውእቱን ይደርባሉ። ውእቱም ለዋጭ፣ ተለዋጭ እንደመሆኑ በወንድና በሴት በአንድና በብዙ የቅርብ አፈታት ይፈታል። ይህም፣
አንተ ውእቱ ዘትገብር መንክረ፣
አንቲ ውእቱ እንተ ወለድኪ አምላከ፣
አንትሙ ውእቱ እለ ያድክሙ አህጉረ ይላል።

ውእቱ ከአገባባት፣ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ ና ተብለው ሲፈቱ ከአናቅጽ፣ ቀዳማይ፣ ካልአይ፣ ሣልሳይ ሲቀሩ በአገባባት፣ በአናቅጽ በሰዋስው ሁሉ እየመረመረ ያሥራል። ለውእቱ አልቦቱ መካን እንዲል። ዘርዘር አድርገን ስንመለከተው፣

አንደኛ በአንድ ጊዜ አጻፋና አንቀጽ ሲሆን ዘወረደሂ፣ ወዘዐርገሂ ውእቱ ይላል።

የነባር፣ የጥሬ፣ የሳቢ ዘር፣ የንዑስ አንቀጽ ማሠሪያ ይሆናል። ሲነገርም ሀገረ ጴጥሮስ፣ ሀገረ ጳውሎስ ይላል። በጥሬ ሲገባ፣ ስላሔ ካህን ስመ እግዚአብሔር፣ በሳቢ ዘር ሲገባ፣ ምጽአተ ነፋሳት ምጽአተ ጎያላን፣ በንዑስ አንቀጽ ሲነገር መዊቶቱ ኢየሱስ፣ መዊቶቱ ናቡቴ ይላል።

ሁለተኛ አካሄድ በቅጽል ሲነገር አምላክ ክቡር፣ ንጉሥ ጠቢብ ማለቱን ያሳያል። በነባር ሲገባ ኤልያስ ነቢይ፣ አሮን ካህን ይላል። የቀረውን እንተ፣ እለ፣ ዘ በገቡበት አስገባ። ሲገቡም ብእሲ ዘከብረ፣ ብእሲ እንተ ከብረ፣ እደው እለ ከብሩ ይላል። ለዚህም ምሳሌ አለው። ገበሬ ሞፈር ሲሰበርበት እርፍ ሲላላበት ወሸል ያደርጋል። ደቀ መዝሙሩም ዜማ ሲሰብርበት ዘከብረ ብሎ ያቀናበታል። ይህም ሽብልቅ ይባላል። ዘ ለውእቱ አንደተሳበ አስተውል። ለዚህም ስምንት አገባባት ይስማሙታል። እነርሱም እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ እመ፣ እምዘ፣ እንዘ፣ ኀበ፣ እንተ፣ እለ ናቸው ። ሲገቡም አምላክ መጽአ ኀቤነ፣ እስመ ውእቱ እመ ውእቱ እምዘ ውእቱ፣ ኀበ ውእቱ፣ እንዘ ውእቱ፣ ያድኅነነ ይላል። በ፲ ሠራዊት ሲዘረዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ውእቱ ውእቱ	አንቲ ውእቱ
አንተ ውእቱ	ውእቶን ውእቱ
ውእቶሙ ውእቱ	አንትን ውእቱ
አንትሙ ውእቱ	አነ ውእቱ
ይእቲ ውእቱ	ንሕነ ውእቱ

ይላል።

ከሁለት ወደብዙ የሄደ የውእቱ ሰዋስው እንደሆነ አስተውል።
ሦስተኛም፣ አንትን ውእቱ እለ አፍቀርክን ንጽሐ፣ አነ ውአቱ ዘአምን በክርስቶስ፣ ንሕነ ውእቱ እለ ንትፋቀር በበይናቲነ፣
ወይም አንትሙ፣ እሙንቱ፣ አንትን፣ እማንቱ፣ ንሕነ እሙንቱ፣ አንቲ አንቲ፣ አንቲ ይእቲ፣ አንቲ ውእቱ፣ አንትሙ ውእቱ፣ አነ ውእቱ፣ ይላል። ሁለተኛም፣ ሩቁን ትተው ቅርቡን ብቻ ይደርባሉ። ምሳሌ፣ አንተ መኑ አንተ፣ አንቲሰ አብድ አንቲ፣ አንትሙ ኢለባውያን አንትሙ፣ አንትን ጠባባት አንትን፣ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ፣ ንሕነ አግብርቲከ ንሕነ ይላል።
አራተኛም፣ ሩቅና ቅርብ ሳይደርቡ ብቻቸውን ራሳቸውን ይችላሉ። ምሳሌ፣ አንተ ዘትፈትን ልበ ወኵልያተ፣ አንተ ካህኑ ለዓለም፣ አንቲ በአማን ምክሐ ዘመድነ፣ አንትሙ ፄዉ ለምድር፣ አንትን አዋልደ መኑ፣ አንሰ ቃለ ዐዋዲ ወንሕነ ሰማዕቱ ይላል። ደቂቅ ቅጽሎች በዚህ ተጠናቀቁ። ቀጥለው የሚቀርቡት ሌሎች ደቂቅ ርባታዎች ናቸው።

፲፮ አይደለም የሚሆኑ ነባር አናቅጽ

ኢ፣ አኮ፣ ሐሰ አይደለም ይሆናሉ። ኢ በጥሬ በነባር በሩቆች በፀ ይነገራል። ሲነገርም ኢ ሠናይ ስባሔ ተንባል ይላል። ኢ በነባር ሲገባ ኢ ሀገር ሀገረ አማሌቅ፣ በሩቆች ኢ ብዑዕ ይሁዳ፣ ኢ ብዑዐን ዳታን ወአቤሮን፣ ኢ ብፅዕት ኤልዛቤል፣ ኢ ብዑዓት አዋልደ ቃኤል ይላል።
ኢ በሁለት ንዑሳን አናቅጽ ይነገራል። በተጨማሪም ተለይቶ፣ ሆኖ ይሆናል። በሰዋስው ሁሉ ይነገራል።ማሠሪያው አለታ ነው።
በኢ ባለ፣ ለኢ ላለ፣ ዘኢ ያለ ይሆናሉ። በንዑስ አንቀጽ፣ በጥሬ ዘር፣ በሳቢ ዘር በአንድ አለታ፣

በሁለት አለታ ጽድቅ፣ በሦስት አለታ ጽድቅ፣ በአራት አለታ ይነገራል።።

በሁለት ሲነገር ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ኢጎደገነ ፍጹመ ንማስን ይላል።።

በአንድ ሲገባ ዘድንግል መናስግተ ኢያርሂዎ ይላል።።

በዘንድ ላይ ሲነገር ኢይሑር፣ ኢይጊሥ ይላል።። በትእዛዝ ኢሑር፣ ኢሑሩ፣ ሲል አልተገኘም ብለው ነቅፈውታል።።

ሁኖ ሲሆን አልቦ አምላክ ኢ በሰማይ ወኢ በምድር ዘእንበለ አምላክነ ይላል።።

በኢ ባለ ሆኖ ሲገባ በኢሐኒጸ መቅደስ ሰሎሞን ኢተግነ ይላል።።

ለኢ ላለ ሆኖ ሲገባ ለኢዐሪገ ሰማይ ኤልያስ ኢተግሀ ይላል።።

ዘኢ አማርኛ ከተገኘ ብሎ ነው እንጂ በተግባር ብዙ ጊዜ አይገኝም።። ሆኖም ገብርኤል ዘኢመዊት ብሎ በወራሽነት ይነገራል።። ያለመሞት መልአክ ገብርኤል ተብሎ ይተረጎማል።። ወራሽ የተባለው መልአክን ተክቶ ስለገባ ነው።። ይህም ማለት የዘን ወራሽነት ተከትሎ ስለገባ ነው።።

በጥሬ ዘር ሲገባ ጽድቁን አለታ፣ አለታውን ጽድቅ ያደርጋል።። ይህም ይታወቅ ዘንድ ልዮን መሀረ በኢጽድቅ፣ ጴጥሮስ መሀረ በኢሕሳዌ ይላል።። በአንድ አለታ ሲገባ ኢያፍቀረ፣ ኢያእመረ ይላል።። ያልተስማማ ግስ ይስማማበታል።። ለምሳሌ፣ ተፈሥሐ ወኢጎዘነ፣ ጸግበ ወኢርኀበ ማለቱን የሳያል።።

በሁለት አለታ ጽድቅ ሲገባ ኢይብል ነዳይ ኢይበልዕ ዕክለ ይላል

በሦስት አለታ ጽድቅ ሲገባ ኢይብል ገብር እንብየ ኢይትኤዘዝ ይላል

በአራት አለታ ጽድቅ ሲገባ ኢብሂል ኢያውጽኦት ምድር ሣዕረ፣ ኢብሂል ኢወለደት ቤርሳቤሕ ወልደ ማለቱን ያሳያል።።

ሐሰ ሎቱን ይዞ በ፲ ሠራዊት ይዘረዝራል። ሲገባም አምላክ ከመ ያጥፍአነ ሐሰ ሎቱ፣ ሐሰ ለክ ይላል። አንስት ይጎድጋ ርኅራኄ ሐሰ ሎን፣ ሐሰ ለክን፣ አነ ካህን እጎድግ ተፋቅሮ ሐሰ ሊተ ይላል። በአንድ ወገን ያለው ሲነገር አንድም ብዙም ሴትም ወንድም ሩቅም ቅርብም በአንድ ዘንድ በመነገራቸው ነው።
አኮ ከውእቱ በቦ ነገር ይለያል። ውእቱ በ፲ ሠራዊት፣ አኮ በአንድ ተነቦ በ፲ ይፈታል። ውእቱ አንደኛውን በአንደኛው ያነፅራል። አኮ በሁለት ያነፅራል። ውእቱ ከሰዋስው በኋላ ይነገራል። አኮ በፊት በኋላ ይነገራል፡ ፡ በሦስት ነገር መለየቱ ለዚህ ነው። ሲነገርም ማይ ወይን በቃና ይላል። ይህም ውእቱ ነው። አኮ ሲነገር ብእሲ አኮ ጎያል ወይም አኮ ኃያል ብእሲ ይላል።
ውእቱ በሰዋስው ኋላ ሲነገር ነገረ ብእሲ ምንት ውእቱ ይላል። ውእቱ የነገር ቅጽል ሲሆን ውእቱ ነገረ ብእሲ ምንት ውእቱ ይላል። ሶበን ይደርባል።ይህም ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ይላል።
ኢ በተጨማሪም ሳ፣ እንዳ፣ ላ፣ ሆኖ ይሆናል። በጎነፊ፣ በትንቢት፣ በዘንድ፣ በትእዛዝ ይገባል። በቦዝ አንቀጽ ላይም ይወድቃል። ለምሳሌ ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ይላል።
ሖረ ኢይብላዕ፣ ሳይበላ ሄደ። የሐውር ኢይብላዕ፣ ሳይበላ ይሄዳል፡ እያለ ይቀጥላል።
በአንቀጽነቱ ሲነገር፣ አልቦ በዝ መዋዕል መልአክ፣ ኢነቢይ፣ ወኢንጉሥ፣ ኢ ቁርባን፣ ወኢ መሥዋዕት ይላል። ትርጉሙ፣ መልአክ የለም፣ ንጉሥ የለም፣ ቁርባን የለም፣ መስዋዕት የለም ማለት ነው።
በአገባብነቱ ሆኖ ሲሆን፣ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበለ አምላክነ፡ ኢ በሰማይ ወኢ በምድር ይላል።

፲፮ ሆነ የሚል አንቀጽ

ኮነ ሆነ ይሆናል። አንድ ተገብሮ፣ አንድ ገቢር ይስባል።ይህም የውእቱ አድራጊ ነው። የአካል፣ የግብር ለውጥ ይሆናል። የውእቱን አገባቦች ይዞ በራሱ በባዕድ ይነገራል። በሩቅ በቅርብ ይለውጣል። በለውጥ ሲነገርም ኮነ ማይ ወይነ በቃና ዘገሊላ ይላል። ይህ ውእቱ ሲያደርግ ነው። አንቀጹ ግን ተገብሮ ነው። የውእቱ አገባብ ሲስማማው ጴጥሮስ ኮነ ብእሲተ እምፍርሀት ይላል። በራሱ ሲገባ ነው። በባዕድ ሲገባ ሙሴ ኮኖ ለአምላክ ዘመደ ይላል። ዝርዝሩ ዘመደን ሲያይ ነው። አገባቡ ከአምላክ ላይ ወድቋልና። አገባቡም ፈዛዛ ይባላል። በትርፍ አማርኛ ይነገራል። ይህም ጎያላን ኮኑ ማየ፣ አርድዕት ኮኑ እሳተ ይላ። ስትፈታም ብርቱዎች ደካማ ሆኑ፣ ተማሪዎች እሳትን ሆኑ በል።
ረሰየ፣ ገብረ አደረገ ይሆናሉ። የኮነ አድራጊዎች ናቸው። ሁለት ግእዝ ይስባሉ። ገብረ የውድ፣ ረሰየ፡ የግድ ናቸው። ለምሳሌ ኢየሱስ ማየ ረሰየ ወይነ ይላል። ኢየሱስ ረሰዮ ለማይ ወይነ፣ በሌላ በኩልም፣ ኢየሱስ ማየ ረሰየ ወይነ ወይም፣
ኢየሱስ ረሰየ ማየ ወይነ ወይም ኢየሱስ ረሰዮ ለማይ ወይነ ይላል። የአካል፣ የግብር ለውጥ ይሆናል።
ተጸውዐ፣ ተሰምየ፣ ተብህለ ተባለ ይሆናሉ። ግእዝና አንቀጽ ይስባሉ። ተሰምየ በነባር አንቀጽ፣ ተብህለ በዘማች አንቀጽ ይነገራሉ። ተጸውዐ የለውም። ሲገባም ጴጥሮስ ተብህለ ካህነ፣ አንቀጽ ሲስብ ተብህለ ካህን፣ ተጸውዐ፣ ተሰምየ ካህን፣ ካህነ ይላል።ግእዝ ሲስብ ነው። በነባር ሲገባ አብሥራ ለድንግል መልአክ ዘይሰመይ ገብርኤል፣ ወይም አብሥራ ለድንግል መልአክ ዘስሙ ገብርኤል ይላል።
የመተርጉምን ነገር ከዚህ ይናገሩታል። የሀገር ስም ተናቦ ስምና ስም ሳይናበብ የግብር ስም ከተጸውያ ስም ተናቦ ይነገራል። የሀገር ስም ሲነገር ደብረ ታቦር፣ ይላል። ሀገረ ኢየሩሳሌም፣ ሀገረ ገሊላ

ይላል። ሲፈታም ታቦር የተባለ ተራራ፣ ኢየሩሳሌም የተባለች አገር፣ ገሊላ የተባለች አገር ይባላል።
ስም ሲሆን ምልክአም ሙሴ፣ ዲዲሞስ ቶማስ ይላል። ሲፈታም ፀሐይ የተባለ ዲዲሞስ፣ ወይም መንታየ የተባለ ቶማስ፣ መልአክ የተባለ ሙሴ ይባላል።
የግብር ስም ሲገባ ነቢየ ሙሴ፣ ካህነ አሮን ይላል። ሲተረጎምም ሙሴ የተባለ ነቢይ፣ አሮን የተባለ ካህን ይባላል።
ዓዲ አማኑኤል ስሙ፣ ማርያም እሙ ይላል። ሲፈታም አማኑኤል የተባለ ስሙ፣ ማርያም የተባለች እናቱ ተብሎ ይፈታል። ገብርኤል ስሙ ዘአምኃ ለማርያም በማለትም ይነገራል። ስሙ ባለቤት እንደሆነ አስተውል።

፲፰ አለ፣ ኖረ፣ ይኖራል፣ ይኑር የሚሆኑ አገባባት፣

ቦ፣ ሀለወ፣ ሀሎ፣ አለ፣ ኖረ፣ ነበረ፣ ይኖራል፣ ይኑር፣ ይሆናል። ሀሎ አማርኛውን አይቶ ነው እንጅ ሌላ ፍች የለውም። ለቦ የውእቱ አገባብ ይስማማዋል። ሲገባ በውስጥ ያሉ እንደሆነ ሦስት ባለቤት፣ በውጭ ነው ያሉ እንደሆነ እስመን፣ አምጣነን፣ እንዘን ይደርባል። ለምሳሌ እስመ እንዘ ቦ፣ ይላል። ሀሎ አምጣነን ይደርባል። ለምሳሌ በአምጣነ ሀሎኩ እሜብሐከ ይላል። በዐሥር ሲዘረዘር ቦቱ፣ ብከ፣ ቦቶሙ፣ ብክሙ፣ ባ፣ ባቲ፣ ብኪ፣ ቦቱን፣ ብክን፣ ብየ፣ ብነ ይላል።
አልቦ፣ ኢ፣ የለም አልኖረም አይኖርም ነበር፣ አይኖርም፣ የለም ነበር፣ አልነበረም፡ አይኑር፣ ይሆናል። ኢን ከአኮ ጋር አሳይተናል። አልቦ ሳይዘረዝር በሩቆቹ በአራት፣ በብእሲ፣ በእደው፣ በብእሲት፣ በአንስት ሲዘረዝር በ፲ ሠራዊት እንደ ቦ ይረባል። የውእቱ አገባብ ይስማማዋል።

፲፱ ብቻ የሚሆኑ ደቂቅ ቅጽሎች፣

ባሕቲቱ፣ ባሕቱ፣ ዳዕሙ ብቻ ይሆናሉ። ባሕቲቱ፣ ባሕቱ፣ ጥሬ ዘር ናቸው። ዳዕሙ ነባር ነው። በቅጽል ይነገራሉ። ከዳዕሙ በስተቀር ተባሕተወ ካለው ግስ የወጡ ናቸው። ባሕቲቱ ቅጽል ሲሆን ለአምላክ ለባሕቲቱ ይላል። ቁራኛ ነው። ባሕቱ ቅጽል ሲሆን በዝንቱ ባሕቱ፣ ባሕቱ ዘንተ ረከብኩ /ይህን ብቻ/ ይላል። ባሕቱ ለገቢር ለተገብሮ ይሆናል። ለአብ ለባሕቲቱ ለዘይኴንን ዓለመ ። ለአብ ለዘፈጠሮሙ ብሎ ይቀጸላል። ስሙ ቁራኛ ይባላል። የሚቀጸለው ለ ሳይሆን ዘ ነው።
ለባሕቱ እንዘ ቸልታ ሲሆን ተሳቢነት ይስማማዋል። ለምሳሌ ባሕቲቶ ይበልዕ ይላል። የውእቱ አገባብ ይስማማዋል። በቅጽል በሰዋስው ሁሉ የሚገቡ ሰባት አገባባት ይስማሙታል። እነሱም አመ፣ ሶበ፣ ኀበ፣ እንዘ፣ እንበለ፣ ቅድመ፣ እም ናቸው። ሲገቡም ንጉሥ ኢይጌርም እንዘ ባሕቲቶ የሐውር፣ ሶበ የሐውር ባሕቲቶ፣ ብእሲ ይፈርህ አመ የሐውር ባሕቲቶ፣ አምላክ ነበረ ባሕቲቶ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፣ ዘእንበለ ይትፈጠር ዓለም ይላል።
ዳዕሙ ብቻ፣ ሆኖ ሲገባ ዳዕሙ እሉኑ ደቂቅከ አሴይ ይላል። ዳዕሙ ለወንድ ለሴት፣ ለአንድ ለብዙ ቅል ይሆናል። ሲገባም፣
ዳዕሙ ዝንቱ ወልድከ፣ ዳዕሙ ዛቲኑ ወለትከ፣ ዳዕሙ እሉኑ ደቂቅከ፣ ዳዕሙ እላኑ አዋልድከ ይላል።

፳ ራቁት የሚሆን

ዕራቁ ራቁት ይሆናል። ከባለቤት ሲቀርብ ቅጽል ይሆናል። ከባለቤት ሲርቅ ተሳቢ ይሆናል። ሲገባም ኢትስተይ ማየ ዕራቆ፣ ዕራቁ ደመና በማለት ቅጽል ይሆናል። ዕራቅየ ወጻእኩ እምከርሠ እምየ ወዕራቅየ

እገብእ ውስተ ከርሠ ምድር ሲል ደግሞ ተሳቢ ይሆናል። አገባቡ እንደባሕቲቱ ነው። ምሥጢሩ ብቻ ነው።

፭፩. እርስ በእርሱ የሚሆን አገባብ፣

በበይናቲሁ እርስ በእርሱ ይሆናል። አንተ፣ አንቲ፣ አነ ሲቀሩ በስተቀር በሰባት ይዘረዝራል። በበይናቲሁ፣ በበይናቲሆሙ፣ በበይናቲክሙ፣ በበይናቲሃ፣ በበይናቲሆን፣ በበይናቲክን፣ በበይናቲነ ይላል። ተደራራጊ፣ አደራራጊ በሚስቡበት ሰዋስው ይነገራል። ንትፋቀር በበይናቲነ፤ አስተፋቀረነ በበይናቲነ፣ ተፋቀሩ በበይናቲሆሙ ማለቱን ያሳያል። ሌሎችም እንደ ናሁ፣ ዮጊ፣ ዬ፣ ነዋ፣ እንጋ፣ ኦሆ፣ እንቋዕ፣ አይ፣ አህ፣ የመሳሰሉት በደቂቅ ርባታ ሊካተቱ ይችላሉ።
በዘመናዊ የአማርኛ ትምህርት አሰጣጥ ደቂቅ አገባብ መስተዋድድ እየተባለ ይጠራል። ደቂቅ አገባባት ከስም በፊት እየገቡ ቦታን፣ ጊዜን፣ ሁኔታንና ዘዴን የሚገልጹ ናቸው። የመስተዋድድ ሥራም ይሄው ነው። ተፈጸመ ደቂቅ ርባታ አገባብ።

፷.፬. ንዑስ አገባብ

ንዑስ አገባብ አራተኛው የአገባብ ክፍል ሲሆን በነባር፣ በዘማች፣ እንዲሁም በአቢይና በንዑስ አንቀጽ እየገባ ማሠሪያነትን የማያስለቅቅ፣ ጥያቄና አንክሮ፣ ደስታና ሐዘን፣ ልመናና ምኞት፣ አለታና አፍራሽ፣ እሽታና እምቢታ የሚያሳይ ፊደልና ቃል ንዑስ አገባ ይባላል /አለቃ ኪዳነ ወልድ/። የንዑስ አገባብን ቁጥር መወሰን ያስቸግራል። ምክንያቱም በርካታ ንዑሳን አናቅጽ ከዘር ወደ አገባብ የሚገቡ ስለሆነ ነው።

በዋድላ አገባብ ደግሞ ንዑስ አገባብ ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጿል፣
ንዑስ መባሉ፣
፩ኛ/ እንደ ዐበይት አገባባት ማሰሪያ ባለማስቀረቱ፡
፪ኛ/ አገባብ መባሉ ከሰዋስው ሁሉ በፊት እየተነገረ ቅጽል በመሆኑ፣
፫ኛ/ በአንቀጽ አጠገብ እየተነገረ አንቀጽ አጎላማሽ፣ ተሳቢ በመሆኑ ነው ይላል፡፡
በየጉባኤ ቤቱ ያሉት የንዑስ አገባባት ቁጥሮች የተለያዩ ቢሆኑም በአብዛኛው ዋና ዋና ተብለው የተለዩ ንዑስ አገባባቦች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩ ÷ አይ፣ምንት
፪ ÷ ኦ፣ ሚ
፫ ÷ አይ፣ መኑ
፬ ÷ አይ፣ አይቴ
፭ ÷ አይ፣ ማእዜ
፮ ÷ ስፍን፣እስፍንቱ
፯ ÷ እፎ
፰ ÷ እፎ፣ በእፎ
፱ ÷ ቦኑ
፲ ÷ ሁ፣ ኑ
፲፩ ÷ ኦ
፲፪ ÷ እስኩ፣ ዮጊ
፲፫ ÷ ነዋ፣ ነያ፣ ናሁ፣ ዬ
፲፬ ÷ አው፣ዮጊ፣ሚመ፣ እመ አኮ፣ ሶበ አኮ
፲፭ ÷ ምንት፣ አይ፣ ኦ፣ ሚ፣ እፎ፣ በእፎ፣
፲፮ ÷ ክመ
፲፯ ÷ ክመ፣ ጽመ፣
፲፰ ÷ ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ዓዲ

፲፱. ወ
፳. ወ፣ሂ፣ኒ፡ጥቀ
፳፩. ባሕቱ
፳፪. ሰ
፳፫. እስመ፣ ኀ
፳፬. እንጋ፣ እንዳኢ
፳፭. እወ፣ አማን
፳፮. እንብየ
፳፯. አሆ
፳፰. ኦ
፳፱. አሌ፣ ወይ፣ ሰይ፣ዬ
፴. ዕንቃዕ
፴፩. ነየ፣ ነዋ
፴፪. በሐ፣ ሐዊሳ
፴፫. አ
፴፬. ህንክ
፴፭. ሀብ፣ ነዐ
፴፮. አሀ፣ አሀሀ፣
፴፯. ኢ፣ አኮ
፴፰. ወ፣ ሰ

፴፱. እም ናቸው፡፡

አማራጭ	አው/ዮን	ሚመ/እመአከ	ሶበ አከ
አጫፋሪ	ወ/ሂ/ኒ	ዓዲ	
ከፋይ	ወ/ሂ/ኒ	ሰ	ባሕቱ
አገናኝ	ወ/ሂ/ኒ		ጥቀ

ከዚህ የሚከተሉት ንዑስ አገባብ ሆነው ለጊዜ ቅጽልና በቂ ይሆናሉ፡፡ ጊዜን የሚገልጹ ከመሆኑ በስተቀር ከሌሎቹ ንዑሳን አገባባት አይለዩም፡፡

ቅድመ/ቅድም	ለፍጻሜ	ትካት	ዓለም አሚር
ዮም ኀሪፍ	ገሪፍ	ይእዜ	ወትረ ዘልፈ
ጌሠም	ሳኒታ	ለዙሉፉ	ለዝላፉ ግሙራ

ለግሙራ ማእዜ ናሁ ናቸው

ምንጭ፣ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ እንደሚሉት ከላይ በተጠቀሱት አምሳል ንዑስ አገባብ እየሆኑ የሚነገሩ ቅጽሎች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ በዋድላ አገባብም ተመሳሳይ አገላለጽ ይገኛል፡፡

ንዑሳን አገባባት በዐረፍተ ነገር እየገቡ እንዴት እንደሚያገለግሉ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ተገልጸዋል፡፡

፩ ምን፣ ምንድን የሚሆኑ አገባባት

አይ፣ ምንት፣ ምን ምንድን ይሆናሉ፡፡ ቅጽል በቂ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ ቅጽል ሲሆኑ አይ ልሳን ዘይክል ነቢበ፣አይ ልቡና፣ ምንት ነገር ይላል፡፡ ለብዙ ሲሆኑ አያት፣ ምንታት እየተባሉ ይነገራሉ፡፡ አያት የአይ፣ ምንታት የምንት እርባታ ናቸው፡፡ በንባብ ቃለ ጥያቄ ሲሆኑ በምሥጢር አሉታ ናቸው፡፡

አይ፣ ምንት ባለቤት ሲቀር በቂ፣ ባለቤት ሲጠራ ቅጽል ይሆናሉ፡፡ በአይ፣ በምንት ተጸውዐ ገብር ይላል፡፡ አይ አይዘረዝርም በብዛቱ ግን በባዕድም በዘመድም ይዘረዝራል፡፡ ነገር ግን በጎንጅ አገባብ አይ ይዘረዝራል፡፡ ከአይቱ ጋርም ያመሳስለዋል፡፡

ለምሳሌ አይቴሁ፣ አይቴነ እንደሚለው አዩ፣ አይነ፣ እያለ እንደሚዘረዝር ይናገራል። በሌሎች አገባቦች ግን አይ አይዘረዝርም።
ምንት ከንዑሳን አገባባት ሁሉ በሁለት ነገር ይለያል። በምን በምን ቢሉ፣

፩ኛ፦ ምንት ምንታት ብሎ በራሱ በመብዛቱ
፪ኛ፦ ምንቱ፣ ምንትከ፣ ምንቶሙ፣ ምንትክሙ፣ ምንታ፣ ምንትኪ፣ ምንቶን፣ ምንትክን፣ ምንትየ፣ ምንትነ ብሎ በ፲ በመዘርዘሩ

ለምሳሌ አቤሴሎም ምንቱ ለዳዊት፣ ገብሩኑ ወሚመ ወዐሊሁ ባሕቱ ወልዱ ይላል።
አይ እና ምንት ነቃፊዎች ናቸው። የውእቱ አገባብ ይስማማቸዋል። ሲገባ ለምንት ለአይ እነግር ጎዘንየ ለሰብእኑ ወእመ አኮ ለባዕድ፣ ባሕቱ ለዘይሰምአኒ አምላኪየ ማለቱን ያሳያል። አይን ፣ ሁ፣ ኑ፣ ኬ፣ እንዲሁም ምንትን ፣ መ፣ ከኑ ጋራ ወይም ለብቻው፣ ኦ፣ ሁ፣ ኬ ያጋንኗቸዋል። ሲገቡም አይሁ፣ ምንትሁ፣ አይኑ፣ ምንትኑ፣ ምንትኬ፣ ምንተኑመ፣ እያሉ ትራስ ይሆናሉ። ምንተኑመ የቀና ትራስ ነው።
ሳድስ ቅጽል በአንድ ርእስ በአምስት ሠራዊት፣ ሳቢ ዘር በአንድ ርእስ በሁለት ሠራዊት ይነገራሉ። በሳድስ ቅጽል ሲገባ ፣ ክቡረ አይ፣ ክቡረ ምንት ይትሌዐል፣ ክቡረ እክልኑ ወእመ አኮ ክቡረ ላህም፣ ባሕቱ ክቡረ ወርቅ እስመ ይትፈታሕ እዴሁ በወርቅ ይላል። በሳቢ ዘር ሲገባ ምጽአተ ምንት ያፈርሆ ለሰብእ ምጽአተ ባዕድኑ ወእመ አኮ ምጽአተ ዘመድኑ ባሕቱ ምጽአተ እግዚአብሔር ይላል።
በሣልስ ቅጽል በንዑስ አንቀጽ በአምስት በአምስት ሠራዊት በአራት በሐውርት ይነገራል። በአራት በሐውርት ሲነገር አውራጆቻቸው ሁ፣ኑ ናቸው። ነቃፊዎቻቸው፣ ዮጊ፣ ሚመ፣ እመ አኮ፣ ሶበ አኮ፣ እመ፣ ሶበ፣ ከ፣ ካ ሲሆኑ፣ አጽዳቂዎቻቸው፣

/አፍራሾቻቸውም/ አላ፣ ዳዕሙ፣ ባሕቱ፣ እንበለ ናቸው። ለምሳሌ በአይ፣ በምንት ይጸድቅ ብእሲ በውሂበ ብሩርሁ ወእመ አኮ በውሂበ ወርቅ፡ አላ በውሂበ ዘነስአ እዴሁ፡ ይላል።
በሣልስ ቅጽል በአምስት አርእስት ሲገባ ተሰቃሌ አይ፣ ተሰቃሌ ምንት ያድጎን ሰብአ። ተሰቃሌ ዕብንኑ ወእመ አኮ ተሰቃሌ ኦም፡ ባሕቱ ተሰቃሌ መስቀል አምላክ።
ሰታዬ ምንት፣ ሰታዬ አይ ይትፌሣሕ፡ ስታዬ ማይኑ ወእመ አኮ ስታዬ ምዝር፤ ዳእሙ ስታዬ ወይን ይላል።
አብላጌ ምንት፣ አብላጌ አይ ሰብአ ያሌዕል ንጉሥ፡ አብላጌ ዶርሆኑ ወሚመ አብላጌ በግዕ አላ አብላጌ መግዝእ ይላል።
ተራዋጼ አይ፣ ተራዋጼ ምንት ይትፈቀር። ተራዋጼ አድግሁ ወእመ አኮ ተራዋጼ በቅል ዘእንበለ ተራዋጼ ፈራስ ይላል።
በአገባብ ሲገባ በይነ አይ፣ በይነ ምንት ይትፌሥሑ ነዳያን፡ በእንተ ወልዶሙሁ ወእመ አኮ በእንተ እግዚኦሙ፡ አላ በእንተ ዘፈጠሮሙ አምላክ።
ኀበ ምንት፣ ኀበ አይ የሐውር ነዳይ ፡ ኀበ ደይክኑ ወእመ አኮ ኀበ መርቄ፤ አላ ኀበ ዘተሠርአ ተስፋሁ።
ከመ አይ ከመ ምንት የሐውር ሐንካስ ከመ ነምርኑ ወእመ አኮ ከመ አንበሳ ባሕቱ ከመ ዝእብ።
ምስለ ምንት፣ ምስለ አይ ይሄሉ ገብረ ሕይወት ምስለ ወይጠልኑ ወሚመ ምስለ ሀየል ዳዕሙ ምስለ አንበሳ ወነምር ይላል።
በዘር ሲረባ ነገረ ምንት ያጸድቆ ለሰብእ ነገረ ፈያትኑ ወሚመ ነገረ ሰረቅት ዳዕሙ ነገረ ጻድቃን ይላል።
በሁለት በሐውርት ሲነገር ሂ፣ ኒ ትራስ እየሆኑ በደጊመ ቃል ይነገራሉ። ማሠሪያው አሉታ ነው። ለምሳሌ ምንተሂ፣ ምንተኒ ኢይበልዕ ነዳይ እስመ አልቦቱ ነዋይ በቤቱ። አይ፣ ምንት፣ በወንደም

በሴትም ለሚነገር ሰዋሰው ሁሉ ይቀጸላሉ። ምንተሂ፣ አየሂ፣ ምንተኒ፣ ምንተሂ፣አየሂ፣ አየኒ ግብረ ኢይገብር ገብር እስመ ተምዐ ንጉሥ። በደኒመ ቃል መባሉ ሲፈታ ምንም ምን ተብሎ ስለሚፈታ ነው። የአይ አና የምንት አገባብ በጣም ሰፊ ነው ይህን ያህል ካየን በቂ ነው።

፪ ምን፣ ምንድን የሚሆኑ አገባባት

አ፣ ሚ ምን ምንድን ይሆናሉ። በአለቃ ታየ አገባብ አይ፣ ምንት፣ አ፣ ሚ በአንድ ላይ ተጠቃለው ቀርበዋል። ነገር ግን አገባባቸው ስለሚለያይ ራሳቸውን አስችሎ ማቅረቡ ይመረጣል።
ሚ በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ በቅጽል ይነገራል። በጎንጅ አገባብ መሠረት ደግሞ በተጨማሪ በስም፣ በቦታ በግብር ይገባል። በቦታና በግብር ሲገባ መጠነን ይዞ ነው። ለምሳሌ ሚ መጠነ ዕክለ ተለቅሐ ይላል። በቦታ ሲገባ ሚ መጠነ ሀገረ ኮነነ ይላል። መጠነን ሳይዝም ሊገባ ይችላል በዐሥር ሠራዊት ይገባል።
ሚ በነባር በቀዳማይ በካልኣይ በሣልሳይም ይነገራል። አጎላማሽ ቅጽልም ይሆናል። በዋድላው ጌቱ ገሞራው አገባብ መሠረት ሚ በቀዳማይ ሲገባ መጠነን ይዞ ነው። ለምሳሌ ሚ መጠነ አምዕዕዋ ለነፍስየ ይላል።
ቅጽል ሲሆን ሚ መጠን ግርምንት ዕለት ይላል። ለገቢር ለተገብሮ ይከታል።
አጎላማሽ ሲሆን በቀዳማይ አይገባም። እግዚኦ ሚ በዝኑ ሲል ቢገኝ ተርጓምያን ይበዝኑ ብለው አቅንተው ይተረጉሙታልና።
በካልአይ ሲነገር ሚ ይሜኒ ላሕያ ለማርያም እስመ አልቦ ዘይትማሰላ ይላል። በሣልሳይ ሚ ጎብስተ ይብላዕ ክቡር ብእሲ ጎብስተ ሰገምኑ ወእመ አኮ ጎብስተ ተርሙስ አላ ጎብስተ ስርናይ ዘይሰመይ

ሥጋሁ ለክርስቶስ ይላል። በቀዳማይ ሲነገር ሚ መጠነ ኀብስተ በልዐ ብእሲ ክቡር እስመ ጸግበ ከርሱ ይላል። በመጠነ ሲገባ ሚ መጠነ ረከበ፣ ሚ መጠን ተረክበ፣ ይላል። በቀዳማይ ሲገባ በውእቱ ቀዳማይ ነው።
ኦ በቅጽል ሲነገር አኅላማሽ ነው። ይህም፣
ኦ እሙቅ ብዕለ ጥበቡ፣
ኦ ኃያል ነገረ አበው እስመ ይመውዕ ኵሎ ይላል።
ኦ መንክር ወዕፁብ ዝ ኀይለ ከርሣ ለድንግል።
ኦ መንክር ለሚአ ዐፅም እምገቦ አዳም።
ኦ ዝ መንክር ወዕፁብ ነሥአ አሐደ ዐፅመ እምገቦሁ ለአዳም ሲል ኦ ስመ አምላክ ሆኖ ተወስዶ ነው። መንገዱ ግን ኣጭር ነው። በቀዳማይ፣ በካልአይ በሣልሳይ ሲነገር ግን በውእቱ ቀዳማይ ካልኣይ ሣልሳይ ነው እንጅ በዘማች አንቀጽ አይደለም። በኀንጅ አገባብ መሠረት ኦ ቃለ አክብሮ፣ ቃለ አልዕሎ፣ ቃለ ምዕዳን፣ ቃለ ምክር፣ ቃለ ዘለፋ፣ ቃለ ተግሣጽ፣ ቃለ አስተዋርዶ፣ ቃለ አራኅርኖ፣ ቃለ ኢጋኖ፣ ቃለ አፍርሆ፣ ቃለ አኅዝኖ ይሆናል።
በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት ኦ ከላይ የተዘረዘሩትን የሚሆነው ምን በሚለው ትርጉሙ ሳይሆን በሌሎች አገባቦች ነው። ለምሳሌ ከዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፣
ኦ ቃለ አክብሮ ሲሆን ኦ ኢየሱስ ወልደ ዳዊት ተሣሀለነ ይላል።
ቃለ አፍቅሮ ሲሆን ኦ ማርያም በእንተ ዝ ናፈቅረኪ ወነዐብየኪ ይላል።
ቃለ አራኅርኖ ሲሆን ኦ መስተምሕርት አስተምሕሪ ኀበ ወልድኪ ይላል።
ቃለ ምክር ሲሆን ኦ ወልድየ ስምዐኒ ዘእብለከ ይላል።
ቃለ አፍርሆ ሲሆን ኦ ሀገረ ሰዶም ይላል።
ቃለ አኅስሮ ሲሆን ኦ ይሁዳ፣ ኦ ሐናንያ እፎ መልአ ሰይጣን ውስተ ልብከ ይላል።

ቃለ ወቀሳ ሲሆን ኦ አዳም ምንተኑ ረሰይናከ ይላል። በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት ኦ ምን ሲሆን ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጿል። ኦ ቃለ አንክሮ ነው፡ ለክፉም ለበጎም ይነገራል። ለ እየተከተለው ሳይከተለውም በቅጽል በጥሬ ይገባል። ለምሳሌ፣
ኦ ዝንቱ ምሥጢር፣ ኦ ዕሙቅ ብዕለ ጥበቡ፣ ኦ ለዝ ዝንጋዔ፣ ኦ ለዝ ሕሊና ይላል።
ኦ ወዮ ይብላኝ ሲሆን ቃለ ሰቈቃው ነው። እም እና ለ ይስማሙታል። ለምሳሌ ኦ ሞት፣ ኦ እምዝንቱ ሞት ዘሥሉጥ ላዕለ ወልደ ዕጓለ እመሕያው፣ ኦ ለይሁዳ እስመ ሜጠ ለእግዚኡ ይላል።
ኦ የሰሚ አገባብ ሲሆን ምሥጢሩ ከጽዋዔነት /ጥሪ/ አይወጣም። ሰሚዎቹም አራት ናቸው። አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን ናቸው። ዝርዝሮቻቸውም አራት ናቸው። እነርሱም፣ ከ፣ ኪ፣ ክሙ፣ ክን ናቸው። በዚህ መሠረት የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ስለ ኦ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ በዝርዝር ይተነትናል።

፫ ማን የሚሆኑ አገባባት

አይ፣ መኑ ማን ይሆናሉ። ከተጸውዖ እና ከተቀብዖ ስም በስተቀር በሰዋስው ሁሉ ይገባሉ። አዋጃቸው እንደ ምንት ነው። አየ መነ ያፈቅር ንጉሥ ባዕደኑ ወሚመ ዘመደ፣ ባሕቱ ዘይተቀነዮ ገብረ። ውዒለ መኑ፣ ውዒለ አይ ይኄይስ፡ ውዒለ አብድኑ ወሚመ ውዒለ ኖላዊ፡ ባሕቱ ውዒለ መስፍን እያለ ይሄዳል። ለሴትም ለወንድም ይሆናሉ። ለአይ ብዛት አለው፡ መኑ በእለ ይበዛል። ለምሳሌ እለመኑ ተጸውዑ፣ እለመኑ ተጸዋዕክሙ፣ እለመኑ ተጸዋዕክን ይላል። በገቢር ጊዜ መነ፣ አየ ይላል። ለምሳሌ መነ አየ ብእሲተ ጸውዐት ንግሥት ዕቤርተኑ ወእም አኮ መርዓተ አላ ዘትትለዐካ ወለተ ይላል።

በአለቃ ታየ አገባብ መሠረት፣ አይ እና መኑ ከዚህ እንደሚከተለው ተብራርተዋል። በንባብ ጥያቄ በምሥጢር አሉታ ናቸው። አውራጆቻቸው ሁ፣ ኑ ናቸው። ነቃፊዎቻቸው ሚመ፣ እመ አኮ፣ ሶበ አኮ ናቸው። አንጻሪዎቻቸው አላ፣ ደዕሙ፣ ባሕቱ፣ እንበለ ናቸው።
በዋድላ አገባብ መሠረት የአይ ብዜት አያት ነው። በአለቃ ታየ አገባብ ግን እለ አይ በማለት ያበዛዋል። ለምሳሌ እለ አይ ሐወጽዋ ለሴሎ፡ እለ አሮንሁ ወእመ አኮሁ እለ ሖር፣ እንበለ ዘሐወጽዋ እለ ኢያሱ ይላል። መኑ በእለ ሲበዛም እለ መኑ ፈነወ ሙሴ ውስተ ሴሎ እለ አልዓዛርኑ ወሶበ አኮኑ እለ አብድዩ፡ ዳዕሙ እለ ካሌብ ይላል።

፬ ወዴት፣ የት / ሔት የሚሉም አሉ/ የሚሆኑ አገባባት

አይ፣ አይቴ ወዴት የት ይሆናሉ። አምስት አገባባት ይስማሟቸዋል። እም መነሻ፣ ኀበ፣ እንተ፣ ውስተ፣ ለ፣ በ መግስገሻ እስከ መድረሻ፣ እንተ በቁም ቀሪ፣ እለ፣ ዘ ቅጽል ሲሆኑ ናቸው። አዋጃቸው እንደ አይ እና እንደ መኑ ነው። እስከ አሁን ምንትን ለነገር፣ አይን መኑን ለሰው ስንቀጽል መጥተን ነበር። እነዚህ ግን /አይ፣ አይቴ/ የቦታ ቅጽሎች ናቸው። ለቦታ ሲቀጸሉ አየ አይቴ የሐውር ንጉሥ ኀበ ገራህትኑ ወእመ አኮ ኀበ ሀለዉ ኖሎት ባሕቱ ኀበ ዐውደ ፍትሕ። በአይ በአይቴ ይትረከብ ክርስቶስ በባሕርኑ ወእመ አኮ በየብስ፡ ባሕቱ ምሉዕ በኩለሄ ይላል።
አያት የአይ ብዛት ሲሆን ማናቸው ማናቸዎች ይሆናል። አይ ከምንት ጋር ሲነገር ምንታት ባለው መሠረት አይንም አያት ብሎ አላበዛም ነበር። ከመኑ ጋር ሲነገርም መኑ በእለ ሲበዛ አይ አልበዛም ነበርና አሁን አያት ብሎ አበዛው። ሲገባም በእም ነቃፊነት ነው። ለምሳሌ፣

ንጉሥ ጸውዐ አያተ ዕደወ እም አኀው እለቆሙኑ ወእመ አኮሰ እለነበሩ ውስተ ቤት ባሕቱ እለ ርሕቁ፡፡
አያተ ጸውዐት ንግሥት እምደናግል፡ እለ ቆማኑ ወእመ አኮ እለ ነበራ ውስተ ቤት፡ ባሕቱ እለ ርሕቃ፡፡
አያት ሀልቁ እም አኀው ወአያት ተርፉ እለ ዐርጉኑ ወእመ አኮ እለ ነበሩ ውስተ ቤት፡፡
አያት ሀልቃ እምአኀት ወአያት ተርፉ፡ እለ ዐርጋኑ ወእመ አኮ እለ ነበራ ውስተ ቤት
አያት ሞቱ እም አኀው ወአያት ተርፉ እስመ ንጉሥ መጽአ ባሕቲቶ ይላል፡፡
አያት ሞታ እምአኀት ወአያት ተርፉ፡ እስመ መጽአት ንግሥት ባሕቲታ ይላል፡፡

፮ መቼም መች የሚሆኑ አገባባት

አይ፣ ማእዜ መቸም መች ይሆናሉ፡፡ አራት አገባባት ይስማሟቸዋል፡፡ እነርሱም እስከ፣ በ፣ እም፣ እለ፣ እንተ፣ ዘ /ሦስቱ እንደ አንድ/ ናቸው፡፡ ሲገቡም፤
አየ ማእዜ ይመጽእ ነጋዲ በሠለስትኑ ወእመ አኮ በቀትር ባሕቱ በመንፈቀ ሌሊት፡፡
እስከ አይ፣ እስከ ማእዜ ይመጽእ ነጋዲ እስከ ቀትርኑ ወእመአኮ እስከ ሠርክ፡ ዳዕሙ እስከ ዘይደክሙ አእዱጊሁ፡፡
እም አይ፣ እማእዜ ይመጽእ ነጋዲ እም ሰኑይኑ ወእመ አኮ እምሠሉስ ባሕቱ እምዘአትረፈ ምክብዕተ፡፡
በንዑስ አንቀጽ ሲገባ ተንሥኡተ አይ፣ ተንሥኡተ ማእዜ ያፈቅር ንጉሥ፡ ተንሥኡተ ረቡዕኑ ወእመ አኮ ተንሥኡተ ዐርብ ባሕቱ ተንሥኡተ ሠሉስ ይላል፡፡

፯ ስንት፣ ስንቱ፣ ስንቶች የሚሆኑ አገባባት

ስፍን፣ ስንት፣ ስንቱ፣ እስፍንቱ ስንቶች ይሆናሉ።። በሦስት በሐውርት በአነዝ ይነገራሉ።። ሰፈነ ገዛ ካለው ግስ የወጡ ናቸው።። ስፍን በአንድ፣ እስፍንቱ በብዙ ይነገራሉ።። ስፍን ዋሕድን፣ እስፍንቱ ክልኤቱን ይመስላሉ።። ክልኤቱ ዐዋጅ እንዳፈረሰ እስፍንቱም ዐዋጅ ያፈርሳል።። ወደ ግእዝ ተመልሶ ክልኤተ ቢል አስፍንተ ይላል።።ዳግመኛም ክልኤተ ብሎ ቢወድቅ እስፍንተ ብሎ ይወድቃል።። ዋሕደ ብሎ ቢነሳ ስፍነ ብሎ ይነሳል።። በዐረፍተ ነገር ሲገባም እንዲህ ይላል፣
ባዕል ስፍነ ጸመደ ጎምስተኑ ወእመ አኮ ሰመንተ ባሕቱ ዐሠርተ ወክልኤተ ይላል።።
በአንደኛው በሐውርት ሲነገር እም አኀው እስፍንቱ ሐልቁ ወእስፍንቱ ተርፉ ጎምስቱኑ ወእመ አኮ ስድስቱ።።
ሐቤ እስፍንቱ ያስተፈሥሕ ሰብአ ሐቤ አርባዓኑ ወእመ አኮ ሐቤ ጎምሳ፡ ባሕቱ ሐቤ ምዕት ይላል።።
፮ እንዴት፣ ምን፣ ምንኛ፣ ለምን፣ ምንድን፣ እረግ፣ እረምነው የሚሆን አገባብ
እፎ እንዴት፣ ምን፣ ምንኛ፣ ለምን፣ ምንድን፣ እረግ፣ እረምነው ይሆናል።። እንጋ፣ ኢ፣ ሁ፣ ኬ፣ መ፣ ኮ ያጋንኑታል።። ለምሳሌ፣
እፎ ሰቀልዎ አይሁድ ለእግዚእነ፡ ኢያእመሩኑ ከመ አጥፍኦሙ ለሰብአ ግብጽ ወእመ አኮ ኢያእመሩኑ ከመ አጥፍኦሙ ለዳታን ወለአቤሮን ባሕቱ ዕውራነ ልብ እሙንቱ ይላል።። ይህም ለምን፣ ምነው፣ እንዴት ሲሆን ነው።።
እፎ ርእዮ ውርዝው ለአረጋዊ ከመ ሕፃንኑ ወእመ አኮ ከመ ብእሲት ባሕቱ ጥብልለ እከይ ልቡ ሲል እንደምን ሲሆን ነው።።
እፎ ጎለፈ በቅድሜነ፡ ዝዕብኑ ወእመ አኮ ነምርኑ ባሕቱ ዘነበረ ነግድ ሲል ምንድን ሲሆን ነው።።
፯ ለምንድን፣ በምንድን የሚሆኑ አገባባት
እፎ፣ በእፎ፣ ለምንት ለምንድን፣ በምንድን ይሆናሉ።። በእፎ አርዳዒከ ኢይጸውሙ፡ በእፎ ትጼዕል ሊቀ

ካህናቲሁ ለእግዚአብሔር ይላል፡፡ እፎን ሁ፣ ኑ፣ ኬ፣ መ ከኑ ጋር፣ እንጋ ያጋንኑታል፡፡ በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ፣
እፎ በእፎ መጽአ፡ እፎሁ እፎኑ እፎኬ፡ እያለ ትራስ ይሆናል፡፡
እፎኑመ ሲል የተቃና ትራስ ነው፡፡ እፎ እንጋ ማሕጸነ ድንግል ያሮ ይላል፡፡ እፎ እንጋ ሲል ያልተስማማ ትራስ ነው፡፡ ምነው ቢሉ እርሱ ለብቻ ትራሱ ለብቻ ነውና፡፡ እፎ፣ በእፎ መጽአ፣ እፎ በእፎ ይመጽእ ይላል፡፡ በሦስቱ በሐውርት ይነገራል፡፡ በአንደኛው ብሔር ሲነገር እንዘ፣ እመ፣ ሶበ፣ እምከመ፣ እምዘ፣ ከመ፣ በየሙ.ያቸው ሲነገሩ ሰ፣ ሳ ሲሆን ሁ፣ ኑ፣ አኮኑ በየሙ.ያቸው ሲገቡ ይስማሙታል፡ ለምሳሌ እፎ ውርዝው ገብረ ኃጢአተ እምከመሰ፣ እምዘሰ ነስሐ፣ ሶበሰ ነስሐ ፣ እመሰ ነስሐ፣ እንዘሰ ይኄስሕ በኃጢአቱ እስመ ይድኅን፡፡
ኢ.ያእመረኑ ድኅነቶ ይሁዳ እምከመሰ ነስሐ በኃጢአቱ እምኢተኮነነ ወእመ አኮ ጴጥሮስ ተዘከረ ኃጢአቶ እምከመሰ ነስሐ እስመ ድኅነ እምኃጢአቱ ባሕቱ አበው እለ ሰምዑ ዘንተ ድኅኑ እምኃጢአቶሙ እምከመሰ ነስሑ እስመ ኮኑ ደናግለ ይላል፡፡
በሁለተኛው ብሔር ከመ ሲገባ እፎ ገብረ ካህን ኃጢአተ ኢ.ያእመረኑ ከመ ይትኴነን በኃጢአቱ ወእመ አኮ ዲ.ያብሎስ ከመ ወረደ ሲያለ በኃጢአቱ፡ ባሕቱ አዳም እምከመ ነስሐ ድኅነ ይላል፡፡
በሦስተኛው በሐውርት ሲነገር ባሕቱ ነገር ግን ሲሆን፣ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ በይነ፣ እንበይነ፣ ዘን/እንተን በር ከፋች ይዘው፣ ኀበ፣ እንዘ፣ በዘ ይስማማሉ፡፡
በአራተኛው ብሔር ሲነገር ባሕቱ ነገር ግን ሲሆን ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ እንኳን ሲሆኑ ሂ፣ ኒ፣ ወ፣ አዲ፣ ም፣ ሁ፣ ኑ ያት ሲሆኑ ይስማሟቸዋል፡፡
ምንተ ይለብሱ እሙንቱ መነኰሳት ይላል፡፡ በአምስተኛው ብሔር ሲነገር እፎ ተለይቶ በእመ፣ በእስመ በቀዳማይ ይነገራል፡፡ እስመ፣ አምጣነ፣

አኮኑና ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ፣ ስንኳን ሲሆኑ ይስማሙታል። ሲገባ እመሰ ይላል። ማንጸሪያም ይሆናል። ለምሳሌ እፎ ተእኅዘ ገብር እዴሁ ያፈቅርኑ ጽልአ ወእመ አኮ ተግሳጸ ባሕቱ ነሥአ እመ ይገብር ሠናየ ወኃጢአተ፣ ጥቀ ኃጢአተ፣ ኃጢአተሂ፣ ኃጢአተኒ እመ ያበዝኅ እስመ ይትማሠጥዎ ሑሎሙ ሕዋሳቲሁ ይላል። የማሠሪያ አጋቹር ሲሆን እፎ እስመ ተእኅዘ ገብር እዴሁ እስመ ገብረ ኃጢአተ ይላል። ሙያው አጎላማሽ ነው።

፱ በውኑ የሚሆን አገባብ

ቦኑ በውኑ ይሆናል። በነባር፣ በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ ይነገራል። እፎ፣ በእፎ፣ ለምንት፣ በምንት መነሻ ሲሆኑ ሰ፣ ሳ፣ ሲሆኑ ከአይ፣ ከምንት ጀምረው እሰከ እፎ ድረስ ላሉ አገባባት ሁሉ አስረጅ ነው። ሲገባም በምንት ወድቀ ይሁዳ ቦኑ ኢያእመረሰ ተጼውዎቶሙ ለአበው ወሚመ ኢተዘከረሰ ምጽአቶ ለጸሮሙ ሰናክሬም ባሕቱ መፍቀሬ ብሩር ይላል።

፲ ወይ የሚሆኑ አገባባት

ሁ፣ ኑ ወይ ይሆናሉ። በነባር፣ በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ። ከአይ ከምንት ጀምረው እስከ እፎ ላሉት አገባባት አውራጅ እየሆኑ ይነገራሉ። በይቤ ለሚገቡ አገባባት ይስማሟቸዋል። ይህም በአገባብነታቸው ነው፡ እንደ አገባባት በዐበይት አናቅጽ እየወደቁ ማሠሪያነትን ያስቀራሉና። ለምሳሌ ለምንት ወጽአ ነጋዲ ለሰቢረ ዕፅኑ ወእመ አኮ ለቀዲሐ ማይ ባሕቱ ለአትርፎ ወርቅ ማለቱን ያሳያል። የይቤ አገባብ አይስማማቸውም። እነርሱ ግን በይቤ ይገባሉ። ይህም ይቤሎ ለዘይቤሎ ካለው ተመልከት።

፲፩ ሆይ የሚሆን አገባብ

ኦ ሆይ ይሆናል፡፡ በቅርብ በአራት ሠራዊት ለወንድ ለሴት ለአንድ ለብዙ ይቀጸላል፡፡ ለምሳሌ ኦ መርድእ አእመርከ ምሥጢረ፣ ኦ አርድዕት አእመርክሙ ምሥጢረ፣ ኦ ብእሲት አእመርኪ ፈትለ ወጸብሐ፣ ኦ አንስት ዐቀብክን ድንግልናክን፣ አእመርክን ፈትለ ወጸብሐ በእዴክን ማለቱን ያሳያል፡፡ ለዚህም ሦስት አገባባት ይስማሙታል፡፡ እነርሱም እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ እስኩ፣ ዘ፣ ዮጊ ናቸው፡፡ ከንዑስም የሚስማሙ አለ፡፡ እነርሱም አሌ፣ ወይ፣ ሰይ፣ ሁ፣ ኑ፣ ከአይ ከምንት ጀምረው እስከ እፎ ድረስ ያሉ አገባባት ናቸው፡፡ ሳያስተያይም አስተያይቶም ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣

ኦ አበው ወልድክሙ ገብረ ሠናየ ግብረ እሰመ ያፈቅር ጽድቀ ይላል፡፡ ይህም ሳያስተያይ ነው፡፡

ኦ አበው አፍቀርክሙ ጽድቀ አምጣነ ሞዕክዎ ለዓለም ይላል፡፡ ይህ ሲያስተያይ ነው፡፡ ኦ አበው እስኩ ነጽሩ ዘይትገበር በላዕሌነ ይላል፡፡

አሌ ለክሙ ኦ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን እስመ ጌገይክምዎ ለእግዚአብሔር ይላል ይህ በአገባብ ሲያሰማ ነው፡፡ አሌ ባለቤት ነው፡፡ ሁ፣ ኑ ይገባሉም አይገቡም፡፡ ኦ ዳዊት ምንትከ አቤሴሎም ገብርከኑ ወእመ አኮ ወዐሊከ ባሕቱ ወልድከ ማለቱን ያሳያል፡፡

፲፪ እስኪ የሚሆኑ አገባባት

እስኩ፣ ዮጊ፣ እሰኪ ይሆናሉ፡፡ እስኩ በፊት በኋላ፣ ዮጊ በፊት በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራል፡፡ እፎ፣ በእፎ፣ ለምንት መነሻ ይሆናሉ፡፡ እወ፣ እመ አኮ፣ ሚመ፣ ሶበ አኮ፣ በውእቱ የሚገቡ አገባባት ይስማሟቸዋል፡፡ እስኩ ነጽር፣ እስኩ ትኬጽር፣ ዮጊ ትኬጽር፣ ረድ እስኩ እመስቀልከ ይላል፡፡

በጌቴ ገሞራው አገባብ መሠረት እስኩ እና ዮጊ አስኪ ሲሆኑ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ ከአይ ከምንት ጀምረው

እስከ እፎ ድረስ ያሉ አገባባት ይስማሙታል።
በዐረፍተ ነገር ሲገባ ይቤሎ አብርሃም ለገብሩ ነጽርኬ እስኩ፣ እስኩኬ ነጽር። ነጽር ዮጊ እመ ቦ ነግድ በአንቀጽነ እስመ ያጸድቀነ፣ እስመ ሰምዐ ትእዛዘ አምላኩ ማለቱን ያሳያል።
ሁለት አስረጅ ሲሆን እስመ ያጸድቀነ ለነጽር፣
እስመ ሰምዐ ደግሞ ለይቤሎ እንደሆነ አስተውል።

፲፫ እነሆ የሚሆኑ አገባባት

ነዋ፣ ነየ፣ ናሁ፣ ዬ እነሆ ይሆናሉ። ነዋ፣ ናሁ፣ ዮጊ፣ ነየ በፊት በኋላ ይገባሉ። ዬ በፊት በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ እንዘ፣ ኢ መነሻ እየሆኗቸው ይገባሉ። አዲ፣ ናሁ፣ ዮጊ ይእዜ አሁን ሲሆኑ፣ ስ ሳ ሲሆን ይስማማል።
እነዚህ አገባባት በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም ሆነ በአለቃ ታየ አገባብ ላይ አይገኙም። በጎንጅ አገባብ ግን ይገኛሉ።

፲፬ ወይስ፣ ባይሆን፣ ካልሆነ የሚሆኑ አገባባት

አው፣ ዮጊ፣ ሚመ፣ እመ አኮ፣ ሶበ አኮ ወይስ፣ ባይሆን፣ ካልሆነ ይሆናሉ። የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ አማራጭ ይላቸዋል። ከአይ ከምንት ጀምሮ ላሉ አገባባት ነቃፊ እየሆኑ በቀዳማይ፣ በካልአይ በሣልሳይ ይነገራሉ። ለምሳሌ ለምንት ዓለመ መነኑ ጻድቃን ለዘጊበ ወርቅኑ ወእመ አኮ ለዘጊበ ብሩር ባሕቱ ለዘጊበ ክብር አው ለመጻሕፍት እንጅ ለቅኔ አይገባም። ምነው አው በኢያእምሮ አው በገቢር እያለ ዝርው ያደርጋልና። አው፣ ዮጊ፣ እመ አኮ፣ ሶበ አኮ፣ ሚመ መድረሻ ይሆናሉ። ሚመ መነሻ ይሆናል ሚ ረከበ፣ ሚ መጠነ ረከበ፣ ሚ መጠን ግርምት ዛቲ

ሰዓት ይላል። ሚ ለመጠነ ቅጽል፣ በቂ ሆኖ የረከበ ተሳቢ ነው። ሚ ለገቢር ለተገብሮ ይሆናሉ።

፲፩ ምን የሚሆኑ አገባባት፣

ምንት፣ አይ፣ ኦ፣ ሚ፣ እፎ፣ በእፎ ምን ይሆናሉ። ኦ ተለይቶ ሆይ ምን ይሆናል። አይ፣ ዮጊ እሰኩ፣ ሁ፣ ኑ ለሚመ፣ ለእመ አኮ ለሶበ አኮ በውእቱ የሚገቡ አገባባት ሁሉ ይስማሟቸዋል።

፲፪ መቼም፣ መች፣ ዘወትር፣ ድንት፣ ዘለዓለም የሚሆን አገባብ፣

ክመ መቼም፣ መች፣ ዘወትር፣ ድንት፣ ዘለዓለም ይሆናል። ክመ መጽአ፣ ክመ ይመጽእ ይላል። እንዲያውም በቅርብ ይስማማል ብለው አንተሰ አንተ ክመ ይላል። እፎ፣ በእፎ፣ ለምንት መነሻ ሲሆኑ ይቀድሙለታል። ባሕቱ ነገር ግን ሲሆን በውእቱ የሚገቡ አገባባት ሁሉ ይከተሏቸዋል። ለምሳሌ እፎ፣ በእፎ ታፈቅር ንጉሥ ክመ ይመጽእ ክመ ገብር ባሕቱ ፈጻሜ ፈቃድከ እም አጎው ይላል። ክመን ሂ፣ ኒ ይጫኑታል። በይቤ ይነሳል። አለታ፣ ንዑስ አንቀጽ ሳ ሲሆን አላ፣ ዳዕሙ፣ ባሕቱ እንጅ ሲሆኑ ይስማሙታል። ለምሳሌ ይቤሎ ንጉሥ ለብእሲ ትፈንዎ ክመኒ፣ ክመሂ ኢያእርፍ ለገብርከ ባሕቱ፣ አላ፣ ዳዕሙ አልቦ ዘየአምራ ለምሥጢርከ ይላል።

ክመ ብቻ ይሆናል። ብቻ ሲሆን ቅጽል ይሆናል። ለምሳሌ አንተሰ አንተ ክመ፣ አንቲሰ አንቲ ክመ ይላል። ቅጽል ሲሆን ክመ አብርሃም እንተ ርእዮሙ ለሥላሴ ይላል። ለጊዜም ይቀጸላል። ለምሳሌ ወክመ ውእቱ እስከ ለዓለም ይላል። እስከ አሁን ያየነው መቸም መች ሲሆን ነው። ከዚህ የቀረ በሣልስ በይቤ ይነሳል። እስመ፣ እመ፡ ሶበ፣ እም፡ ከመ፣ እምዘ፣ ሰን ትራስ እያደረጉ፣ አላ፣ ዳዕሙ፣ ባሕቱ ነገር ግን ሲሆኑ ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ አዲ ም ሲሆኑ ይስማማሉ። ለምሳሌ

ይቤሎ ንጉሥ ለገብሩ ኢትትሌለየኒ ክመ ባሕቱ ኢይትአመር ዘእገበር ለከ ወንዋይየ አዲ፣ ንዋይየሂ፣ ንዋይየኒ ኢይሐልቅ ብየ እመሰ፣ ሶበሰ፣ እምከመሰ፣ እምዘሰ ወሀብኩከ ይላል።።
ክመ ድንት ይሆናል በነባር፣ በቀዳማይ፣ በካልኣይ በሣልሳይ ይነገራል።። በእም እየወደቀ ነው፡ ለዚህም እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ እመ፣ ሶበ ባሕቱ፣ ነገር ግን ሲሆን ይስማማለ።። ፣ እፎ፣ በእፎ በምንት፣ ለምንት መነሻ ይሆናሉ።። ለምሳሌ አብርሃም አብልዐ ክመ፣ ያበልዕ ክመ፣ ኢያበልዕ ክመ ጎብስቶ ለነዳይ ይላል።። በእም ሲገባ ሀካይ ብእሲ እምገብረ ክመ ጽድቀ እስመ ትሰምዕ እዝኑ፣ እመ ትሰምዕ እዝኑ፣ ሶ ትሰምዕ ዕዝኑ ፍትሐ ኩነኔ ባሕቱ አልቦቱ ልብ ይላል።። እፎ፣ በእፎ ለምንት ሀካይ ብእሲ ይጸድቅ በአፉሁ እሰመ ገብረ ክመ ኃጢአተ ይላል።።

፲፯ ዝም ብሎ የሚሆኑ አገባባት

ክመ፣ ጽመ ዝም ብሎ ይሆናሉ።። በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ።። እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ ንዑስ አንቀጽ ዘን ኢን ይዞ እንዳ፣ ሳ፣ ላ፣ ወ፣ ሊ፣ ላል ሲሆን ይስማሙታል።። ሲነገር ገብር ክመ መጽአ፣ ጽመ መጽአ፣ ይመጽእ፣ ይምጻእ ኢይትናገር ነገሮ፡ ወይትቀነይ ለእግዚኡ እሰመ ይትዔገስ ዙሎ ይላል።።

፲፰. ዋቄ የሚሆኑ አገባባት

ወ፣ ሂ፣ ኒ ዓዲ፣ ሰ ዋቄ ይሆናሉ።። በሰዋስው ሁሉ በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ።። ወ፣ ዓዲ፣ በፊት ሰ፣ ሂ፣ ኒ፣ በኋላ ይነገራሉ።። ለምሳሌ ወየሐውር ዓዲ፣ ዓዲ የሐውር፣ የሐውርሂ፣ የሐውርኒ፣ የሐውርሰ ይላል።።

ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ም. ግን. ስንኳን ይሆናሉ። ትርጓሚያቸው ም፤ ሙያቸው ዋዌ፣ ወይም ማሰሪያ ከፋይ ወይም አንጻር ነው። ምሥጢራቸው አጫፋሪነት፣ የምሥጢር ድንበር ከፋይነት፣ አንጻርነት አማራጭነት ይሆናል። በሰዋስው ማለትም በዘማች አንቀጽ፣ በነባር አንቀጽ፣ በባሕርይ ስም፣ በተጸውያ፣ በተቀብያ፣ በግብር፣ በመድበልስምና በቅጽል በብትን ሰዋስው ሁሉ እየገቡ ይነገራሉ። ሲገቡም አብርሃም ወለዶ ለይስሐቅ፣ ወይስሐቅ ወለዶ ለያዕቆብይላል።ወይቤላ መልአክ ለማርያም መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፣ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ ይላል።

ሂ እና ኒ ዘሂ ይትወለድዘኒ ይትወለድ እምኔኪቅዱስ ውእቱ።

ተደራርበው ሲከፍሉ አብርሃም ወለደ ይስሐቅሀ፣ ወይስሐቅሂ፣ ወይስሐቅኒ ወለደ ያዕቆብሀ ይላል።

ሰ፣ ወዌነቱን፤ ከፋይነቱን ሳይለቅ ግን፣ ሳ፣ ስ፣ ማ፣ ና ይሆናል። ምሥጢሩ አፍራሽ ነው። ግን ሲሆን ነስሐ አዳም በእንተ ዘክሕደ ፈጣሪሁ፣ ዲያብሎስሰ ኢነስሐ ይላል።

እስራኤል ዐደዉ ባሕረ ኤርትራ፣ ግብፃውያንሰ ተሰጥሙ ውስተ ባሕረ ኤርትራ ይላል።

ሳ፣ ስ፣ ማ፣ ና ሲሆን እንደሚከተለው ነው፣

ሳ፣ ስ፣ ሙሴ ኢቦአ ምድረ ርስት አሮንሰ ኢቦአኑ? ይቤ ኢያሱ እዎ ኢቦአ ይላል።

ማ፣ ስ ሲሆን የማናይ ቦአ ውስተ ገነት ፀጋማይሰ ኢቦአ ይላል።

፲፱. ወ ፲፪ ነገሮች ይሆናል

ወ ተለይቶ በ፲፪ ነገሮች ይነገራል። እነርሱም ጊዜ፣ ቅጽል፣ እየ፣ ማ፣ ውጥን ጨራሽ፣ ግን፣ እንጂ፣ ስንኳን፣ ዘተረስአ፣ ቸልታ፣ ል፣ ሊ፣ ላ፣ ሰ፣ ሲ፣ ሳ፣ ከ፣ ካ ናቸው።

ውጥጥን ጨራሽ ሲሆን ትኤምሐክሙ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወማርቆስ ወልድየ፣ ይሴርዎን እግዚአብሔር ለከናፍረ ጉህሉት፡ ወለልሳን እንተ ተዐቢ ነቢበ ይላል፡፡
ግን ሲሆን ያዕቆብሃ አፍቀርኩ ወኤሳውሃ ጸላእኩ፣ ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ ይላል፡፡
እንጅ ሲሆን ከጥቀ ጋር አሳይተናል፡፡
ዘተረስአ ሲሆን ሐመ ወሞተ ይላል፡፡
ቸልታ ሲሆን ሞተ ወሐመ ዐርገ ወተንሥአ፣ ትጸርሕ ወትብል የአምር እግዚአብሔር ይላል፡፡
ል ሲሆን ባሕታዊ ተንሥእ ወትትቀነይ ለእግዚአብሔር ወኢትግበር እኩየ ይላል፡፡ ላ ሲሆን ይትሊቃሕ ኃጥዕ ወኢይፈዲ ይላል፡፡
ስ ሲሆን ወእመ አኮ ብለን አሳይተናል፡፡
ሳ ሲሆን ወኢያውአያ እሳተ መለኮቱ ለድንግል ይላል፡፡
ከ፣ ሲሆን በአኃዝ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ኤልያስ ለኀመ ሰማየ ሠለስተ ዓመተ፣ ወስድስተ አውራኀ፡
ካ ሲሆን በሃምሳ ምዕት ወበኀምስቱ ምዕት ተወልደ እግዚእነ ኢየሱስ ክርሰቶስ ይላል፡፡
ሲ ሲሆን ከአይ ከምንት ጀምሮ እስከ እፎ ድረስ ባሉ አገባባት እየገባ ይነገራል፡፡

፷ ስንኳን የሚሆኑ አገባባት

ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ ስንኳን ይሆናሉ፡፡ በሰዋስው ይነገራሉ፡፡ መነሻዎቻቸው አምስት ናቸው፡፡ እነርሱም አኮ፣ አልቦ፣ ኢ፣ ኑ፣ ሁ ናቸው፡፡ ዳግመኛም ከአይ፣ ከምንት ጀምሮ እሰከ እፎ ያሉ አገባባት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ኢይትኤረይዋ ለማርያም ደናግል፣ ጥቀ መላእክት፣ ወመላእክት፣ መላእክትሂ፣ መላእክትኒ፣ ኢይትኤረይዋ፡፡ አልቦ ዘይመስላ ለማርያም እም አዋልደ እስራኤል ጥቀ ሔዋን ወሔዋን፣ ሔዋንሂ፣ ሔዋንኒ ኢትመስላ፡፡ አኮ

መልአክ ገበረ ሕይወት እስመ ሞተ በሥጋሁ ወነበ መቃበር ጥቀ፣ ኀበ መቃበርሂ፣ ኀበ መቃብርኒ ኢወረደ፡፡ ሞተትሁ፣ ሞተትኑ ማርያም ከመ ሰብእ እሰመ አልባቲ ጌጋይ ጥቀ ኢየሱስ፣ ኢየሱስሂ፣ ኢየሱስኒ ወኢየሱስ ኢተርፈ እሞት ማለቱን ያሳያል፡፡
ጥቀ ተለይቶ ስንኳን ሲሆን እፎ፣ በእፎ፣ ለምንት፣ በምንት መነሻ ሲሆኑ በንዑስ አንቀጽ ይነገራል፡፡ ባሕቱ ነገር ግን ሲሆን ይቀድምለታል፡ ፡ ወ፣ ሂ፣ ኒ ስንኳን ሲሆኑ ይከተሉታል፡፡ ዋዌነታቸውን አይለቁም፡፡ ለምሳሌ ሰሎሞን ጥቀ ኢለብሰ ከመ አሐዱ እምእሉ ይላል፡፡ እፎ፣ በእፎ ሖረ ባዕል ውስተ ቤተ ነዳይ ባሕቱ ኢመጽአ ነዳይ ውስተ ቤተ ባዕል ጥቀ ይብላዕ ጎብስተ ባዕል፣ ባዕል ጥቀ ወባዕል፣ ባዕልሂ፣ ባዕልኒ ኢርእየ ዐይኖ፡፡ ንጉሥ ጥቀ፣ ወንጉሥ፣ ንጉሥሂ፣ ንጉሥኒ ይሬኢ ዓይኖ ይላል፡፡

፳፩ ሳ፣ ስ፣ ማ የሚሆን አገባብ

ሰ ተለይቶ ሳ፣ ስ፣ ማ ይሆናል፡፡ ስ ሲሆን በመጀመሪያ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ጴጥሮስሰ መጽአ ወጳውሎስ ተርፈ ይላል፡፡
ማ ሲሆን በሁለት ይቤ በጠያቂና በመላሽ ይነገራል፡፡ ሲገባም በስምንት አገባብ ይነገራል፡፡ እነርሱም እመ፣ እስመ፣ እምዘ፣ አመ፣ ድኅረ፣ በዘ፣ እንዘ፣ ኀበ ናቸው፡፡ በጠያቂና በመላሽ በይቤ በሁለት አገባብ ላይ ሰ ትራስ እየሆነ ይነገራል፡፡ እም፣ ከመ፣ እምዘ ከ፣ ካ፣ ሲሆኑ እም ዮም፣ እም ይእዜ፣
እንከ እንኪያው እንግዲያው ሲሆን በአምስት አገባብ ከአይ ከምንት ጀምሮ እስከ እፎ ያሉት አገባባት ናቸው፡፡ ሁ፣ ኑ፣ ን ሲሆኑ እመ በ፣ ባ ሲሆን ይስማሙታል፡፡
ሶ፣ አ፣ ኬ ቃለ መልእክት ይሆናሉ፡፡ በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራሉ፡፡ ቃለ አጋኖ ሲሆኑ

በጠያቂና በመላሽ ይገባሉ። በስምንት አገባባት ይስማማሉ። እነርሱም ኡ፣ ኬ፣ ሶ ናቸው። በቀዳማይ፣ በካልኣይ፣ በሣልሳይ፣ ይነገራሉ። ከዐቢይ ከደቂቅ፣ ከንዑስ አሳይተናል።

፷፪ እኮን ብያ የሚሆኑ አገባባት

እስመ፣ ጓ እኮን፣ ብያ ይሆናሉ የይቤ ስምንት አገባባት ይስማማሉ። አላ፣ ደእሙ፣ ባሕቱ ይስማማሉ። ጓ በልዐ፣ ጓ ይበልዕ፣ ጓ ይብላዕ ይላል። ከለባትኒ ጓ ይበልዑ ተረፈ እግዚኦሙ ይላል። እስመ በሣልሳይ አይነገርም። ሲገባም እስመ እሳት ትነድድ እመዓትየ፣ እስመ ተማዕኩ፣ እመ ተማዕኩ፣ እምዘ ተማዕኩ ባሕቱ፣ አላ፣ ዳዕሙ ይከልአኒ ርኅራኄየ ይላል። በቀ ሲገባ እስመ በፈቃዱ ወበፈቃደ አቡሁ መጽአ ወአድነነነ ይላል። የእስመ፣ የእም፣ ስማቸው ማሠሪያ አጋቹር ይባላል።

፷፫ እንጅ የሚሆኑ አገባባት

እንጋ፣ እንዳኢ እንጅ ይሆናሉ። በምሥጢራቸው ኢየአምር ነው። ባለቤታቸው ከመ ነው። ሰዋስው ባለቤት አይሆንም። አልቦ ዕፅ ዘይፈሪ በመዋዕለ ሀጋይ ባሕቱ በመዋዕለ ክረምት ዘይፈሪ ከመ ውእቱ እንዳኢ፣ እንጋ ከመ ዘይፈሪ እንጋ ይላል። አልቦ ዘይመስላ ለማርያም ወገብርኤል ዘይመስላ ክመ ውእቱ እንዳኢ፣ እንጋ ከመ ዘይመስላ እንዳኢ ይላል።
እንዳኢ ተለይቶ ውጥን ጨራሽ ይሆናል። ሲገባ አልቦ ዘይመስላ ለማርያም ከመ ገብረኤል እንዳኢ ይላል። መምህራን ይህንንም አይሆንም ብለዋል!
እንጋ እንጃ ይሆናል። ይጥያቄ፣ ይጥርጥርና የአንክሮቃል ነው። ሲገባም፤
አሐዩኑ እንጋ እስከ እማንቱ መዋዕል?

መኑ ይክል ድኂነ እንጋ?ያለ ጥያቄ አንቀጽ ሲገባ እነሆ ይሆናል። ሲገባም፣
እንጋ በጽሑት ኀቤክሙ መንግሥተ እግዚአብሔር ይላል። እነሆ ሲሆን ነው። ትርጉሙ፣ እንጃ ወይም አላውቅም ማለት ነው። አሐዩኑ እንጋ እስከ እማንቱ መዋዕል በሚልበት ጊዜ አንቀጽ አጎላማሽ ነው።

፳፬ አወን፣ እውነት የሚሆኑ አገባባት

እወ፣ አማን አወን እውነት ይሆናሉ። ነባር አናቅጽ ናቸው። በይቤ ይነገራሉ። ምሥጢራቸው አእመርኩ ነው። ሲነገሩም ይቤ እግዚአብሔር እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ ይላል። አማን አማን መጽሐፈኛ ነው። ለምሳሌ አማን አማን እብለክሙ ይላል። በሰዋስው ግን አማነ አማነ እብለክሙ ይላል።

፳፭ እምቢ የሚሆን አገባብ

እንበ፣ እንብየ እምቢ ይሆናል። በስድስት ሠራዊት ይዘረዘራል። በይቤ ይነገራል። ምሥጢሩ ኢይገብር ነው። በአሉታ በካልአይ ይገባል። ይቤሎ ሀካይ ገብር ለአግዚኡ እንብየ ኢይገብር ለከ ፈቃደከ ይላል። በደኂመ ቃል ይነገራል። ይህም ይቤ ዔሊ ደቂቅየ እንቢክሙ እንቢክሙ ይላል። ሲዘረዘር እንቢከ፣ እንብየ፣ እንቢክሙ እንቢነ፣ እንቢኪ፣ እንቢክን፣ ይላል።

፳፮ በጀ፣ እሽ፣ በጎ የሚሆን አገባብ

ኦሆ በጅ፣ እሽ፣ በጎ ይሆናል። በይእዜ ይነገራል። ምሥጢሩ እግብር ነው። ሲነገርም ኦሆ በልዎ ለእግዚአብሔር ወእንብየ በልዎ ለሰይጣን። ይቤ ቅኑይ ገብር ኦሆ እገብር ለከ ፈቃደከ ይላል። በካልአይ በጽድቅ ይገባል። ለምሳሌ ይቤሎ ለእግዚኡ ገብር ጎር ኦሆ እገብር ለከ ፈቃደከ ይላል።

፷፯ ወዮ፣ ወዲያ፣ ይብላኝ የሚሆን አገባብ

ኦ ወዮ፣ ወዲያ፣ ይብላኝ ይሆናል። በይቤ ይነገራል። በደጊመ ቃልም ይነገራል። ምሥጢሩ ሐዘንኩ ነው። ወዲያ ሲሆን ሕዙን ብእሲ ይቤ ኦ ነዳይ ብእሲ፣ ኦ ሀካይ ብእሲ እስመ ይሜንን ሰብአ በልቡ ይላል። የኩራት ነው። ይብላኝ ሲሆን ይቤ ጴጥሮስ ኦ ለይሁዳ ዘአሰቀሎ ለእግዚኡ ይላል።

፷፰ ወዮ የሚሆኑ አገባባት

አሌ፣ ወይ፣ ሰይ፣ ዬ ወዮ ይሆናሉ። በይቤ ይነገራሉ። በዐሥር ሠረዊት በለ ዝርዝር ይነገራሉ። ምሥጢራቸውን በአንድ ያሳያሉ። እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ ና ኦ ሆይ ሲሆኑ ይስማማሉ። ምሥጢራቸው ሐዘን ነው። ያለ ይቤም ይነገራሉ። ሲነገሩም ኦ ጸሐፍት ፈሪሳውያን አሌ ለክሙ ወይ ለክሙ ሰይ ለክሙ እሰመ አስተማሰልክምዎ ለክርስቶስ ምስለ ፈያት ይላል። በይቤ ሲነገር ይቤ መምህር አሌ ሎሙ ለአርድዕት እስመ ንውማነ ኮኑ ይላል። አሌ ባለቤት፣ አሰሚው አገባብ፣ ማሠሪያው ይደሉ መሆኑን አስተውል። ሲዘረዝሩም የለን ዝርዝር ይዘው ነው። አሌ ሎቱ፣ ወይ ሎቱ፣ ሰይ ሎቱ እያለ ይዘረዝራል። ምሥጢሩን በአንድ ያሳያል ማለቱ በአንድም በብዙም አሌ ባለቤት ሆኖ ስለአልተለወጠ ነው።

፷፱ እሰይ እሰይ የሚሆን አገባብ

እንቋዕ እሰይ እሰይ ይሆናል። በጥንቱ አማርኛ እሶ እሶ፣ ውጭኝ ውጭኝ፣ ምን ፈቀድህ በሚል አነጋገር ይገለጻል። በደጊመ ቃል ይነገራል። ምሥጢሩ ተፈጣሕኩ ነው። ለምሳሌ እንዲህ ይላል፤

ወይቤሉ በልቦሙ እንቋዕ እንቋዕ ርኢናሁ በአዕይንቲነ ይላል።

ጉቡአን ሕዝብ ይቤሉ እንቋዕ እንቋዕ እንዘ ይሰትዩ ወይነ።

ይቤሎ ነዳይ ለባዕል እንቋዕ እንቋዕ እስመ ጸዐንከ ሥርጉተ በቅለ ማለቱን ያሳያል። ውጭኝ ውጭኝ አገውኛ ነው።

፴ እነሆ፣ እነሆኝ የሚሆን አገባብ

ናሁ፣ ነየ፣ ነዋ እነሆ፣ እነሆኝ ይሆናሉ። ምሥጢሩ ሀሎኩ ነው።በአራት ሠራዊት ንሕነ እስኪል፣ በዐሥር ሠራዊት ይረባል። ሲነገርም ነያ ለሴት ነዋ ለወንድ ይቀጸላል። ለምሳሌ ነየ አመቱ ለእግዚአ ኵሉ።

ነያ እምከ ወነዋ ወልድኪ ይላል።

ነየ ለወንድም ለሴትም ይቀጸላል። ለምሳሌ፣

ነየ ገብርከ/ለወንድ/፣ ነየ አመቱ ለእግዚአብሔር።

ትብል ቤተ ክርስቲያን ነዮሙ ውሉድየ መሀይምናን፣ ለብዙ ሴቶች ደግሞ ነዮን አዋልድየ ደናግል ጠባባት ይላል።

ነየ ውእቱን ይመስላል፡ የሚሉ አሉ። ቅጽል ነው እንጅ አንቀጽ አይሆንም።

አቤት ሲሆን ነየ እብለከ ገብርከ ይላል። አቤት ብሎ ሲቀጸል ትቤ ድንግል ነየ አመቱ ለእግዚአብሔር ይላል።

ናሁ ለወንድም ለሴትም ይቀጸላል። ለወንድ ሲሆን፣ እስመ ናሁ ንጉሥኪ በጽሐ ይላል። ለሴት ሲሆን፣ ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተ እምአዝማድኪ ይላል።

ለብዙ ሲሆን ናሁ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ኀበ እለ ይፈርህዎ ይላል።

፴፩ እንዴት ዋልህ፣ እንዴት አደርህ የሚሆን አገባብ

በሐ፣ ሐዊሳ እንዴት ዋልህ፣ እንዴት አደርህ፣ ቢሰኛህን ያጥፋልህ፣ የዋለውን አያሳድርብህ፣ ያደረውን አያውልብህ፣ ጠላትህን ያውድቅልህ ይሆናል። በሐ በቅርብ በአራት ሠራዊት ይዘረዝራል። በይቤ ይነገራል። ሐዊሳ ፍቅር ነው እንጅ ሌላ አይሆንም። ሲገባ በሐከ ይቤለከ ይላል። ሲዘረዘር በሐ በሐከ፣ በሐክሙ፣ በሐኪ፣ በሐክን፣ ማለቱን ያሳያል።

፴፪ ን፣ ሆይ የሚሆን አገባብ፣

ኦ ን፣ ሆይ ይሆናል። ሆይ ሲሆን በቅረብ በቅርብ በአራት ሠራዊት ይዘረዝራል። ን ሲሆን ይቤን ይፈልጋል። በደኂመ ቃል ይነገራል። ሳይደግምም ይሆናል። ይህም ይቤ መሓሊ ሰብእ ኦ ማርያምሀ ኦ ማርያምሀ፣ ኦ ጊዮርጊስሀ ኦ ጊዮርጊስሀ ይላል።
ኦ ሆይ ሲሆን በአራት ማለትም፣ በአንድ ቅርብ ወንድ፣ በብዙ ቅርብ ወንዶች፣ በአንዲት ቅርብ ሴት፣ በብዙ ቅርቦች ሴቶች እየገባ በቅጽልነት ይነገራል። ለምሳሌ ኦ ካህን አፍቀርከ ጽድቀ፣ ኦ አርድዕት አእመርክሙ ምሥጢረ፣ ኦ ብእሲት አእመርኪ ጸብኀ ወፈትለ፣ ኦ ደናግል ዐቀብክን ድንግልናክን ማለቱን ያሳያል። የሚዘረዝረው ሆይ ሲሆን መሆኑን አስተውል።

፴፫ እንካ የሚሆን አገባብ

ሕንክ እንካ ይሆናል። በይቤ ይነገራል። ዘንድን ይዞም ሳይዝም ይነገራል። ሲነገር ይቤሎ አብ ለወልዱ ሕንክ ጎብስተ ይላል። በብዙ ሲሆን ሕንኩ ብልዑ ይላል። ዘንድ ይዞ ሲነገር ይቤሎ አብ ለወልዱ ሕንክ ትብላዕ ጎብስተ ይላል። ሕንክ፣ ሕንኪ፣ ሕንኩ፣ ሕንክሙ፣ ሕንካ /ለብዙ ሴቶች/ እያለ ይዘረዝራል። ሕንክ ናም ይሆናል።

፴፬ ና የሚሆኑ አግባባት /መምጣት/፣

ሀብ፣ ነዐ፣ ሕንክ ና ይሆናሉ። ሕንክ፣ ሕንኩ፣ ሕንኪ፣ ሕንካ፣ ሀብ፣ ሀቡ፣ ሀቢ፣ ሀባ፣ ነዐ፣ ንዒ፣ ንዑ፣ ንዓ፣ ብለው በአራት በአራት ይዘረዝራሉ። ሕንክ ከሐነከ፣ ሀብ ከወሀበ የወጡ ናቸው። ነዐ የመጽአ ትእዛዝ ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን ትእዛዝ አይደለም። ነባር አንቀጽ ነው እንጅ። ይህም ይታወቅ ዘንድ ከሃይማኖተ አበው ምጻእ የሚል ትእዛዝ አንቀጽ ይገኛል። ኢሳይያስም ምጽኡ ሲል ይገኛል። ስለዚህ ምጻእ የመጽአ ትዕዛዝ አንቀጽ ከሆነ ነዐ ነባር አንቀጽ ነው። በአንድ ወንድ አይነሳም። የብዙዎች ሴቶች ግን ይነሳል።

፴፭ ኢሀ /አይ/ የሚሆን አግባብ

አሀ ኢሀ፣ አይ፣ አዬ፣ ዋይ፣ ወዮ፣ ወዲያልኝ ወዲያ ይሆናል። በደጊመ ቃል ይነገራል። በይቤም ይነገራል። ምሥጢሩ ኢታስተሐዝነኒ፣ ሐዘንኩ ነው። ይቤሎ አብ ለወልዱ ዕኩይ አሀ ይላል። በደጊመ ቃል ሲነገር ይቤሎ አብ ለወልዱ ሀካይ አሀ አሀ ይላል። የአንክሮና የደስታ የሐዘን፣ የጭንቅ፣ የነቀፋታ ቃል ነው። ለምሳሌ ለአንክሮና ለደስታ

ሲሆን አህ አህ አንደደኒ ፍቅርከ ይላል። ለሐዘንና ለቀፌታ ሲሆን አህ አህ /ወዲያ ወዲያ/ እምዛቲ ሕሥም፣ አህ አህ እምዛቲ ጎፍረት እያለ ይገባል።

፬ ና የሚሆኑ አገባባቱ

ወ እና ሰ ና ይሆናሉ። ወ ና የሚል ትርጉም ይዞ የሚገባው በሁሉም ዐበይት አናቅጽና በንዑሳን አናቅጽ እንዲሁም በስም መካከል ነው። ስሙ ማንኛውም ስም ሊሆን ይችላል። እስከ ሦስት ስም ድረስ ማገልገል ይችላል። ከሦስት ስም በላይ ግን ክልክል ነው። በሦስተኛው ስም ላይ የሚጫነው ወ ም፣ ወይም እንዲሁም የሚል ትርጉም ይዞ ይገባል። ለምሳሌ ሚካኤል ወገብርኤል ወሩፋል ሲል ሚካኤልና ገብርኤል፣ ሩፋኤልም ወይም እንዲሁም ሩፋኤል ተብሎ ይተረጎማል። በአንቀጽ ሲገባም ጊዮርጊስ በልዐ ህብስተ ሃማኖት እስመ ያፈቅር ግብረ ወንጌል ወይኤዝዝዎ ሥላሴ ወይትቀነይ ወይደክም በማለት ሦስት አናቅጽ ማውረዱን ያሳያል። ሙያው ዋዌ ውይም አውራጅ ይባላል።

ሰ ና የሚል ትርጉም ይዞ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚገባው በሁሉም ግስ ሳይሆን ከዚህ በሚከተሉት ስድስት ግሶች ግልሳይ አናቅጽ ላይ ብቻ ነው። አናቅጹም ተርፈ፣ ጸንሐ፣ ተጎድገ፣ ተዘንግዐ፣ ተረስአ፣ በዝኀ ናቸው። ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ጥቀ ስንኳን ሲሆኑ ራሱ ሰ በ፪ኛ ማሠሪያነት ስ ሲሆን ይቀድምላቸዋል። አገባቡም እንደሚከተለው ነው።

ገብረ ሕይወት ኢበልዐ እክለ አምጣነ መልአክ ውእቱ። ይጽናሕሰ፡ ይትርፍሰ ነገረ ዝንቱ ጥቀ ኢጠበወ ጥበ እሙ፡ ወጥበ እሙ፣ ጥበ እሙሂ፣ ጥበ እሙኒ ኢጠበወ ይላል።

በተጨማሪም ኢፈጸሙ አይሁድ ሕገ ወንጌል። ይትረሳዕሰ፣ ይዘንጋዕሰ፣ ይትርፍሰ፣ ይጽናሕሰ፣

ይትጎደግሰ፣ ዝንቱ ሕገ ኦሪትሂ፣ ሕገ ኦሪትኒ፣ ሕገ ኦሪት ጥቀ፣ ወሕገ ኦሪት ኢፈጸሙ።።
ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አገባባት በዋድላ፣ በጎንጅ፣ በአለቃ ታየ እና በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጻሕፍት የተካተቱ ስለሆነ በየአብያተ ጉባኤው ያለልዩነት አገልግሎት ይሰጣሉ።።

፴፯ በ፣ ባ፣ የሚሆን አገባብ፣

እም በ፣ባ፣ ይሆናል።። ሲገባም፣
እግዚአብሔር ጸባያት እመ ኢያትረፈ ለነ፣ ዘርዐ ከመ ሰዶም እምኮነ፣ ወከመ ገሞራ እመሰልነ ይላል።። /እመሰልነ እም-መሰልነ መሆኑን ማስተዋል ይገባል/።።
እም ምንም እንኳ በአንቀጽ ላይ የወደቀ ቢሆንም ማሠሪያ አጋዥ ሆኖ ስለገባ ንዑስ አገባብ እንጂ ዐቢይ አገባብ አይሆንም።። ትርጉሙ እግዚአብሔር ዘር ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን፣ እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር ነው።። ስለዚህ የማሠሪያ አንቀጹ ራሱ ስለሆነ ያስቀረው አንቀጽ የለም።።
እመ ኢሖረ ፈራህ ብእሲ ውስተ ቀትል እምኢረከቦ ሞት /የመጀመሪያው ሲተረጎም ሞት የሚፈራ ዘማች ወደጦር ግንባር ባይሄድ ኖሮ ባልሞተም ነበር/።።
እምኢሖረ ፈራህ ብእሲ ውስተ ዐውደ ቀትል አምጣነ፣ አኮኑ ረከቦ ሞት ግብተ ማለቱን ያሳያል /ሞ የሚፈራው ዘማች ወደጦር ሜዳ ባልሄደ ነበር ድንገተኛ ሞት አግኝቶታልና ተብሎ ይተረጎማል/።። ሁለቱም ጸጸት ነው።።
ተምኔት ሲሆን ነዳይ እመ ሖረ ውስተ ጽርሐ ንጉሥ እምረከበ ወርቀ ይላል።።
እም በተጨማሪም ኪ፣ ክ፣ ይሆናል።። ሲገባም፣
ክ ሲሆን ይቀልል ኅልፈተ ሰማይ ወምድር እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእምነቢያት፣
ወትኤምጽ እምትንብብ ጽድቀ ይላል።። /ፍቸው ክ ቢሆንም ምሥጢሩ ከ ማለት ነው/

፴፮ ከ፣ ኪ፣ ኪያ፣ ካ፣ ክ የሚሆኑ አገባባት፣

እም፣ ከ፣ ኪ፣ ኪያ፣ ክ፣ ካ ሲሆን፡ በትእዛዝ አንቀጽ ይነገራል፡፡ ሰባት አገባባት ይስማሙታል፡፡
አገባባቱም ቅድመ፣ ድኅረ፣ እንተ፣ እለ፣ ዘ፣ አመ፣ ከመ ናቸው፡፡ ማሠሪያቸው ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም አፍቀረ፣ ቀለ፣ ኀየሰ ናቸው፡፡ ሲነገርም፤
ይኄይስ ሐዊረ ፍቁር እምይሑር ብእሲ ቅድመ ጸሩ፣ ድኅረ ተበአሰ፣ እመ ተበአሰ፣ ኀበ ተበአሰ፣ ይላል፡፡
ይቀልል ኀልፈተ ሰማይ ወምድር እም ትደቅ አሐቲ ቃለ ወንጌል እንተ ተናገረ ወልድ፣ ዘተናገረ ወልድ፡፡
እም ይደቃ ቃላተ ወንጌል እለ ተናገሮን ወልድ፡፡
ይትፈቀር ተአርቆቱ ለብእሲ እም ይንበር ከመ ተጻብአ ምስለ ሰብእ ይላል፡፡
ወእደ ሲገባ መጽአ ኀቤሃ አሐዱ ወራዛ እምወእደ ይትኀባእ፣

፷፥፩. ተረፈ ንዑስ አገባባት፣

ተረፈ ንዑስ በሁለት ይከፈላል፡
፩. ቅጽል የሚሆኑ ተረፈ ንዑስ

፪፥ አኅላማሽነት ያላቸው ...ፈድፋደ፣ጥቀ፣ ሕቀ ወዘተ

በተለያዩ አገባባት ዝርዝራቸው የተለያየ ቢሆንም በአብዛኛው ተረፈ ንዑስ የሚባሉት አገባባት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡ በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ መሠረት ጥቅል ትርጉማቸው የብዙ ብዙ ወይም ጭራሽ ነው፡፡ እነርሱም፣

ጥቂ ለዓለም ጽመ ክመ
ፈድፋደ ለዙለፉ ፈድፋደ
በፍድፋዴ ብዙኀ ይሙኑ በሕቁ
እምድሩ በምልዑ ለግሙራ ስብዐ
በፍጻሜ ሲሆኑ ሌሎችም ተረፈ ንዑስ
አገባባት አለ፡፡ እነርሱም ከነመግለጫቸው
ቀርበዋል፡፡

፩፥ ጥቂት የሚሆኑ አገባባት

ውኅደ፣ ኅዳጠ፣ ሕቀ፣ ንስቲተ፣ ጥቂት
ይሆናሉ፡፡ /በዋድላ እና በአለቃ ታየ አገባብ
/ በሩቁ በቅርቡ አነ ባለው፣ እንዲሁም በካዕብ
በግልስ ይነገራሉ፡፡ ንስቲተ ለሴት እንጂ
ለወንድ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ መርዓት ትበልዕ
ንስቲተ ኅብስተ ይላል፡፡ ውኅደ ለወንድ እንጂ
ለሴት አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ብእሲ ውኅደ
ነገረ ተናገረ ይላል፡፡ ኅዳጠ ቅጽልም፣
አኅላማሽም ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ብእሲ ነበበ
ኅዳጠ ነገረ ሲል ቅጽል ነው፡፡ አኅላማሽ
ሲሆን ኅዳጠ ሐሚሞሙ ወብዙኀ ነስኡ
ዕሴቶሙ ይላል፡፡ ውኅዳን፣ ኅዳጣን በማለት
ይበዛሉ፡፡

ሕቀ ቅጽልም፣ አኅላማሽም ይሆናል፡ አምጽእ
ሊተ ሕቀ ማየ በግምኤ፣ ርእየ ሕቀ ደመና፣
እምድኅረ ሕቅ ዘመን፣ አንሰ ሕቅ ወንዑስ
በቅድሜከ ይላል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ተረፈ ንዑስ አገባባት በተጨማሪ
መድረሻቸው ግእዝ እየሆነ ወይም በ ወድቆባቸው
በሳድስነት ተረፈ ንዑስ አገባብ የሚሆኑ ከዚህ
የሚከተሉት ናቸው፡፡

ፍጹመ/በፍጹም ጥንቁቀ/በጥንቁቅ
ጥዩቀ/በጥዩቅ ሕቀ/በሕቅ
ህልወ/በህልው ጎዳጠ/በጎዳጥ
ድቡተ/በድቡት ውጉደ/በውጉድ
ህዱአ/በህዱእ ንስቲተ/በንስቲት
ክቡተ/በክቡት ፍድፋደ/በፍድፋድ
ጎቡአ/በጎቡእ ንሕኑሐ/በንሕኑሕ
ክሡተ/በክሡት ብዙኀ/ብብዙኀ
ግሁደ/በግሁድ ርቱዐ/በርቱዕ
መፍትወ/በመፍትው ድልወ/በድልው
አብ፣ እግዚኦ ናቸው፣

፪፥ አቤቱ የሚሆኑ አገባባት

አባ፣ እግዚኦ አቤቱ ይሆናል፡፡ በይቤ በቅርብ በአንድ ወንድ አጻፋ ይሆናል፡፡ ባሕቱ፣ አላ፣ ዳዕሙ እንጅ ሲሆኑ ይስማማቸዋል፡፡ እግዚኦ ለተገብሮ እንጅ ለገቢር አይሆንም፡፡ ሲገባ አባ አማሐጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ፡፡ ዕንባቆምኒ ይቤ እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራህኩ ይላል፡፡ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ ይላል፡፡

፫ አባ ብርቱ የሚሆን አገባብ

ማር አባ፣ ብርቱ ይሆናል፡፡ ተጸውዐ፣ ተሰምየ፣ ተብህለ በሚል አንቀጽ ይገባል፡፡ አዲ ገና፣ እንበለ፣ ቅድመ፣ ኢ ሳ ሲሆኑ ይስማሙታል፡፡ አባ ማር ተጸውዐ ጊዮርጊስ እምቅደመ ይኩን ዓዲ ሊቀ ሰማዕታት፡፡ መኰንን ተብህለ ማር ዓዲ አንበለ ያርኢ ኃይሎ፣ ኢያርኢ ኃይሎ ማለቱን ያሳያል፡፡

፬ አባት የሚሆኑ አገባባት

አብ፣ አባ አባት ይሆናሉ። አባ ለገቢር ለተገበሮ ይሆናል። አብ ለገቢር ሲሆን አበ ይላል። በዝርዝር ግን አብም ለገቢር ለተገብሮ ይከታል። ራሳቸውን ችለው በዐሥር ሠራዊት ይዘረዝራሉ። ለምሳሌ አብ አባሁ፣ አባክ፣ አቡየ፣ አባኑ፣ አቡክ አባን፣ አቡን፣ እስኪል ይዘረዝራል። በካዕብ አብ አቡሁ፣ አቡ አቡክ አብክ፣ አቡነ አብነ በማለት እንደሰየፈ አስተውል። ሌሎችም የዚህ ተመሳሳይ አሉ። ለምሳሌ ከሠተ አፉሁ ወመሀሮሙ ብሎ በካዕብ ይጎርዳል። የየን ራብዕ፣ የወን ካዕብ፣ ሲደርብ የወ ሳድስ ከረ ካዕብ ሲደረብ፣ የዘ ሣልስ ከአ ካዕብ ሲደረብ፣ ለፍጹማን ካዕብ ይሆናሉ። ይህም ሕያዊ ተንሥአ እሙታን፣ ዘዕውሩ ተወልደ፣ ይሁዳ ሜጠ እግዚኡ ይላል። እግዚአ ቢል ሩቅና ቅርብ ነው። መጻሕፍት ግን እጉሁ ብለው ካዕብ ያደርጋሉ። ይህ አይሆንም፡ ሳድስ ነው እንጅ። ይህም ሲነገር በሦስት ነገድ ነው። እጉ፣ እጎው ይላል። ኋላ በገቢር እኖ፣ እጎወ ይላል። በዝርዝር እጉሁ፣ እጉክ፣ ብሎ እጉን እጉየ፣ እጉነ እስኪል ድረስ ይዘረዝራል። በዐሥር ሠራዊት ይዘረዝራል። በገቢር በተገብሮ ይከታል። በባዕድ እንደሚዘረዘር አስተውል። ለምሳሌ እጎዋሁ፣ እጎዉ፣ ብሎ በዐሥር ሠራዊት ይዘረዝራል። በገቢር እጎው እጎወ፣ እጉ እኖ፣ ይላል።

፭ እንኳን የሚሆን አገባብ

እንቋዕ እንኳን ይሆናል። በቀዳማይ ይነገራል። እንበለ፣ ቅደመ፣ እም፣ ኢ፣ እሰመ፣ አምጣነ፣ ይስማማሉ። እም ከቅድመ ይደረባል። ሲገባ ይቤሎ ብእሲ ለእጉሁ እንቋዕ ረከብከ ወርቀ ወብሩረ እም ቅድመ ትዕርግ ላዕለ ወእንበለ ትረድ ታሕተ እስመ ያስተፈሥሕ ነዳያነ ማለቱን የሳያል።

፮ እጅግ፣ አብዛኛ፣ እምብዛ የሚሆኑ አገባባት፣

ለለ፣ ጥቀ እጅግ፣ አብዛኛ፣ እምብዛ ይሆናለ።። በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ ይነገራለ።። በጽድቅ በአለ.ታ ይገባለ።። እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ፣ እመ፣ ሶበ ይስማሚቸዋል።። ጥቀ ሲነገር በቀዳማይ በካልአይ ይነገራል።። ዳዕሙ፣ ባሕቱ እንጅ ሲሆኑ ንዑስ አንቀጽ ሳ ሲሆን ይስማሙታል።። ሲነገርም ሀካይ ገብር ጸግበ ጥቀ፣ ይጸግብ ጥቀ እስመ ጸዐለ እግዚኡ ይላል።። በአለ.ታ ሲነገር ሕሙም ብእሲ ኢየሐውር ጥቀ እስመ እገሪሁ ድውያት ባሕቱ ኢይቀድምዎ ጎያላን ኢይሩጹ፣ እንበለ ይሩጹ ይላል።። ለለ ለመጻሕፍት መግቢያ ታጥቶለት ቀርቷል።።

፮ እጅግ የሚሆኑ አገባባት

ሕቀ፣ በሕቁ፣ ፈድፋደ፣ ብዙኀ፣ እጅግ ይሆናለ።። በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በሣልሳይ በፊት በኋላ ይነገራሉ።። ሲነገሩም ሕቀ በጌታ አንጅ በሌላ አይሆንም።። ይህም ሕቀ አሕጸጽኮ እመላእክቲከ ይላል።። የቀሩት በሁሉም ይሆናሉ።። ሲገቡም ብዑላን ይበልዑ በሕቁ፣ ፈደፋደ ተለዐለ፣ ብዙኀ ተለዐለ፣ ትትሌዐል እምኵሉ አማልክት ይላል።። በብዙ ሲገባ ተለዐለ ፈድፋደ፣ ብዙኀ ሐዋርያት እምነቢያት ይላል።። ውስጠዘ ሲያኀላምስ ለአንድም ለብዙም ያኀላምሳል።። ብዙኀ፣ ፈድፋደ በሩቁ በ
ቅርቡ ወንድ ይነገራሉ።። ሲገቡም ወተለዐልኩ በኀበ ኵሎሙ ጸላእትየ፡ ወፈድፋደሰ በኀበ ጐርየ ብዙኀ ተለዐልኩ ማለቱን ያሳያል።።
ከተረፈ ንዑስ አገባባት መካከል ተውሳከ ግስ ወይም አንቀጽ አኅላማሽ የሚሆኑ አለ።። ለምሳሌ፣ ፍጹመ፣ ጥንቁቀ፣ ጥዩቀ፣ ሕቀ፣ ኀዳጠ፣ ድቡተ፣ ውኁደ፣ ንስቲተ፣ ክቡደ ወዘተ የመሳሰሉት ይገኙበታል።።
ተፈጸመ ንዑስ አገባብ።።

የብሂል አገባብ

ብሂል በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገባብ ዐቢይ አገባብ ሆኖ የተጠቀሰ ቢሆንም አንቀጽ እንዳያሥር የማድረግ ሳይሆን ባሕረዩ የመሳብ በመሆኑ ዐቢይ አገባብ ነው ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ ራሱን ችሎ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የጎንጅ አገባብ የብሂል አገባብን ሲገልጽ እንዲህ በማለት ይጀምራል፣ ባህል ዘር ነው። አይስብም፡ ይከተላል። እንበለ ዘርፍ አይነገርም። ለምሳሌ ባህለ ኢሳይያስ እያለ ነው። ከባህል ፱፰ ነገር ይወጣል። እነርሱም፣ ፲ ንዑስ አንቀጽ፣ ፳ ውስጠዘ፣ ፲፰ ዐበይት አናቅጽ፣ ፩ ቦዝ አንቀጽ፣ ፩ ዘንድ አንቀጽ፣ ናቸው። እነዚህ ሲደመሩ ኀምሳ አምስት ይሆናሉ። ከዘር ሳቢ ዘር፣ ከሳቢ ዘር ንዑስ አንቀጽ፣ ከንዑስ አንቀጽ ዐቢይ አንቀጽ፣ ከዐቢይ አንቀጽ ቅጽል፣ ከቅጽል ቦዝ አንቀጽና ዘንድ አንቀጽ ይወጣል።

ብሂል ብሂሎት ንዑስ አንቀጽ ነው። ለብሂል ለ፣ የለውም። ለብሂሎት ደግሞ ዘ የለውም። ብሂሉ ለእገሌ፣ ብሂሎት ዘእገሌ አይባልም። ብሂል ዘእገሌ፣ ብሂሎቱ ለእገሌ ይባላል እንጂ።

ብሂል አንቀጽ፣ ግብር፣ ስም፣ ቦታ ይተረጉማል። ስም ሲተረጉም አይናበብም። በሁለት አናቅጽ ይገባል። ምጸት፣ ነጠላ ፍላፃ፣ ድርብ ፍላፃ፣ ነጠላ ዝምድ፣ ድርብ ዝምድ፣ አጭር ዘርፍ፣ ረጂም ዘርፍ፣ ዐውደ ጥበብ ክብ፣ ጥምዝ፣ የለ፣ ዘርፍ፣ የዘ፣ ዘርፍ፣ የለ ድፋት፣ የዘ ድፋት ይሆናል።

ምጸት ሲሆን፣ ብሂል ወለደት ሜልኮል ወልደ ብሂል ወለደት በቅል በቅለ ይላል።

ነጠላ ፍላፃ ሲሆን፣ ጸአነ ቴዎድሮስ ፈረሰ ኢሳይያስ ብሂለ ድንግል ትወልድ ወልደ ይላል። ባዕል ሲጨመር ድርብ ፍላፃ ይሆናል።

ነጠላ ዝምድ ሲሆን፣ በልዐ ብሂለ ተወልደ አምላክ ኀብስተ ቁርሎስ ይላል። ባዕል ሲጨመር ድርብ ዝምድ ይሆናል።
አጭር ዘርፍ ሲሆን፣ ባዕለ እስክንድርያ ይላል። ሀገርን ሲጨምር ረጂም ዘርፍ ይሆናል።
ዐውደ ጥበብ ክብ ሲሆን፣ ብእሲ ተከለ ሐይመተ ብሂል ተወልደ አምላክ ንጉሥ ይላል።
ጥምዝ ሲሆን ኀብስተ ዘጴጥሮስ ብሂል ተሰቅለ አምላክ ይላል።
የለ ዘርፍ ሲሆን፣ ተመዝበረት ብሂል አልባቲ ሠራኢ ወመጋቢ ለዛቲ ዓለም ሀገሩ ለማኒ አማፂ ይላል።
የዘ ዘርፍ ሲሆን፣ ተፈቅረ ብሂል አድኅን ዓለመ መንግሥተ ዘአምላክ ሰሎሞን ይላል።
የለ ዘርፍ ሲሆን፣ ተበልዐ ለጳውሎስ ኀብስቱ ብሂል ተወልደ አምላክ ይላል።
የዘ ድፋት ሲሆን፣ ተሐንጸ ዘጴጥሮስ ባዕል ቤት ብሂል አምላክ አድኅነ ዓለመ ይላል።
ብሂልን የሚጫኑ አገባባት ፲፮ ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ ለ፣ ዘ፣ በ፣ አመ፣ ከመ፣ ቅድመ፣ ድኅረ፣ ምስለ፣ ማዕከለ፣ ኀበ፣ መንገለ፣ ላዕለ፣ እም፣ አስከ፣ መጠነ፣ በእንተ ናቸው።
ወቦ ካልዕ፤ /ሌሎችም አለ/፣ ተውላጠ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ ዐስበ፣ ዕሴተ፣ ናቸው። ሲገባም፣ ሐረ አኪማሆስ ለብሂል ሰሎሞን ተሰቅለ፣
ክርስቶስ ዘብሂል አድኅነ ዓለመ፣
ሞተ ጊዮርጊስ በብሂል ኢይኅድግ ሃይማኖትየ፣
ይትፌሥሑ ጻድቃን አመ ብሂል ንዑ ኀቤየ፣
አልቦ ዘየኅዝኖሙ ለኃጥአን ከመ ብሂለ አምላክ ሑሩ ውስተ ሲኦል፣
ፈጠረ ጽልመተ እግዚአብሔር ቅድመ ብሂል ለይኩን ብርሃን፣
ሰበኩ ሐዋርያት ድኅረ ብሂል ተንሥአ ብሂለ ዐርገ፣
ሰበኩ ሐዋርያት ማዕከለ ብሂል ተወልደ ወተጠምቀ ብሂለ ተሰቅለ፣

በጽሐ አርዮስ እስከ ብሂል ወልድ ፍጡር ፣
ሰበኩ ሐዋርያት ላዕለ ብሂል ተሰቅለ ብሂል ሞተ፣
ናቡቴ ሞተ እምብሂል ኢይኅድግ አፀደ ወይንየ፣
አቀመ ካህን አንብቦ መጽሐፍ ኀበ ይብል ለይኩን፣
ኢየአምር አብድ ካልአ ዘእበለ ብሂል እብላዕ ወእስተይ፣
አልቦ ዘያስተፈሥሐሙ ለነዳያን መጠነ ብሂል በጽሐ ማዕረር፣
ሞተ ቴዎድሮስ በእንተ ብሂል እትቄከፍ አክሊለ፣
እያለ ይቀጥላል።
ብሂል የሚጫናቸው አገባባት ፮ ናቸው። ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ እፎ፣ ለምንት፣ አይቴ፣ ማዕዜ፣ መኑ፣ እስፍንቱ፣ ናቸው። የሚገቡትም ተሰአሎን ይዘው ነው።
ብሂል ብሂሎት ንዑስ አንቀጽ ነው። እስመን፣ አምጣነን፣ አኮኑን፣ ባሕቱን፣ ይመስላል። ከስም በታች ሆኖ ስም ይተረጉማል። የዘር ባለቤት ይሆናል። ስም ሲተረጉም ሚካኤል ብሂል እጹብ ነገር፣ ገብርኤል ብሂል ወልደ እግዚአብሔር ይላል። እስመን ሲመስል ብሂለ ተወልደ፣ ብሂለ ይትወለድ ክርስቶስ ኢሳይያስ ተናገረ። ባሕቱን ሲመስል ብሂል ይትወለድ፣ ተወልደ ብሂል ወልድ ይላል። አኮኑን ሲመስል ብሂል ተወልደ፣ ብሂል ይትወለድ ይላል። ብሂል የወደቀበት የሌላ ባለቤት ሲሆን ብሂለ ክርስቶስ ተወልደ እም ድንግል ዜነወ ገብርኤል ይላል። ባለቤት ሲሆን ተራ ምሳሌ፣ ፍላጻ ዝምድ፣ ድፋት፣ ክብ፣ ምጸት፣ ይሆናል። የሙሻዘር አገባባት ይስማሙታል። ምጸት ሲሆን ብሂል አውጽአት ሰማይ ሳዕረ፣ ብሂል ወለደት በቅል ፈረሰ ይላል።
ተፈጸመ ተረፈ ንዑስ

፷.፮. የሰምና ወርቅ መንገድ፣

ስድስተኛው የአገባብ ክፍል የሰምና ወርቅ መንገድ ሲሆን በሰባት ሊከፈል ይችላል፡፡ እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩÷ አርእስት
፪÷ ብትን ሰዋስው
፫÷ ባለቤት ከዘርፍ
፬÷ ቅጽል ከባለቤት
፭÷ ሙሻዘር
፮÷ ተዘዋሪ/ ሠረዝ/
፯÷ አንጻር ናቸው /አለቃ ታየ ገብረ ማርያም፣ 1958፣ 306/፡፡

በስድስተኛው ድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ ጉባኤ ሰፍቶ ሰባት አገባብ ተፈጠራ ለማለት ከተቻለባቸው ምክንያቶች አንዱ፣

፩÷ በቀላል ሰምና ወርቅ ብቻ ሲነገር የነበረው የቅኔ መንገድ ውሱን የነበረውየቅኔ አቀራረብ ማስፋፋትና ወደጎዳና ቅኔዎች ማሳደግ
፪÷ ለመደበኛ ቅኔዎች መሠረት የሆነውን የጉት ቅኔ ማዘጋጀትና ስያሜ መስጠት ሲሆን ለሰምና ወርቅ እንዲሁም ለጎዳና ቅኔ ስያሜ መሠረት ከሆኑት መካከል ከዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፣

፩. ነጠላ ውስጠ ወይራ፣ ሮማውያን በልዑ ጎብስተ ጴጥሮስ፣
፪. ፍላፃ፣ ሀሊበ ደሙ አርግዐ በቀሱተ ሮሜ መስቀል፣
፫. ነጠላ ፍላፃ፣ ነጸረ ፀሐየ ራጉኤል ጸጋ ዐይነ ደብረ ዳሞ ዘሚካኤል፣
፬. ድርብ ፍላፃ፣ አንበሳ ግበ ሮም መስቀል፣
፭. አጭር ዘርፍ፣ ሰሐበት ንጽሐ ሐረገ ሱራፊ ገዳም ወለተ ኢያቄም እደ ኬንያ፣

፮. ክብ፣ ማርያም ሰሐበት ንጽሐ ሐረገ ሱራፊ ገዳም ይላል።።
ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን በሙሉ በዐዋጅና በሙሻዘር ከነምሥክራቸው በዝርዝር ያሳየን ስለሆነ እንደና እያንዳንዱን መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም።። በክፍል ሁለት የቀረበውን ትንተና ወደኋላ ሄዶ መመልከት ይቻላል።። ለምሳሌ፣ በአዋጁ ተራ ቁጥር ፲፣ ፲፩፣ ፲፫፣ ፲፬፣ ፳፱፣ እና ፴፩፣ ላይ ተናበውም ሆነ ሳይናበቡ ስለሚመሰሉና ስለማይመሰሉ፣ ስለዘርፍና ባለቤት፣ በሰምና ወርቅ መንገድ የባለቤትና የዘርፍ አጠቃቀም፣ ቅጽል በሰምና ወርቅ አካሄድ ያለው ቦታ፣ በዘርፍ ደፊና በዘርፍ አያያዥ የቅጽል አጠቃቀም፣ የውስጠ ወይራ፣ የዝምድ፣ የፍላፃ፣ የክብ አወቃቀር ምን እንደሚመስል በዝርዝር ተገልጿል።። በተራ ቁጥር ፴፩ ሥር ደግሞ ነገረ ሙሻዘር በሰፊው ተተንትኗል።። እንዲሁም በአለቃ ታየ መጽሐፈ ሰዋስው መጽሔተ አእምሮ ከገጽ 278 እስከ 301 ድረስ ያለውን መመልከት ይቻላል።።
ይልቁን ከሰምና ወርቅ መንገድ ጋር አያይዞ የሰምና ወርቅ እና የጎዳና ቅኔ አካሄድ በሦስቱ አብያተ ጉባኤ ምን እንደሚመስል ማሳየቱ የበለጠ ጠቃሚ ሆኖ ስለአገኘነው ትኩረታችንን በዚሁ ላይ አድርገናል።። መሠረተ ሐሳቡ ተመሳሳይ ቢሆንም የሰምና ወርቅ መንገድ አወቃቀር በመጠኑም ቢሆን በየጉባኤ ቤቱ ይለያያል።። ዝርዝሩ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።።

የቅኔ ዓይነቶች

የግእዝ ቅኔ ዓይነቶች በሁለት ታላላቅ ዘርፎች ሊከፈሉ ይችላሉ።። አንዱ ዘርፍ ሰምና ወርቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ ጎዳና ይባላል።። ጎዳና ከሰምና ወርቅ በተለየ ከበድ ብሎ ስለሚዘጋጅ ሰምና ወርቅ የለውም ማለት አይደለም።። እያንዳንዳቸው እንደገና በዝርዝር ይከፈላሉ።። አንዱ ቤተ ጉባኤ ከሌላው የበለጠ

ወደአንዱ ቢያደላም ሦስቱም አብያተ ጉባኤ ሰምና ወርቅንና ጎዳናን ይጠቀማሉ፡፡ ዋሽራ በሰምና ወርቅ ቅኔ የበለጠ ሲታወቅ፡ ዋድላ እና ጎንጅ ደግሞ በጎዳና ቅኔ ይበልጥ ይታወቃሉ፡፡ ዋድላና ጎንጅ መሠረታቸው አንድ ነው፡፡ ተዋነይ በጊዜ ሂደት የራሱን የቅኔ ፍልስፍና ቢጨምርበትም የዋድላ ተማሪ መሆኑ አይዘነጋም፡፡ የመጀመሪያው ድድቅ ወልደ ማርያም እና ተዋነይ የዋድላው ኤልያብ የአንድ ወንበር ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ለጎዳና ቅኔ የበለጠ ትኩረት የሰጡበት ምክንያትም ይሄው ነው፡፡ ዋድላና ጎንጅም ድንቅ የሆኑ የሰምና ወርቅ ቅኔዎችን ይቀኛሉ፡፡ እንደዚሁም ዋሽራዎች በተለይ በእነ ማዕበል ፈንቴ ዘመን የውስጠዘ ቅኔን አዳብረው ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ያሉ አንዳንድ መምህራን አገባብ ከየት እንደቀጸሉና አገባቡ የማን እንደሆነ ሲጠየቁ አገባቡን ከዋድላው ቤተ ጉባኤ ሊቅ ጌቴ ገሞራው መሆኑን ጠቅሰው ቅኔ የተማሩት ግን ከዋሽራ ቤተ ጉባኤ መምህራን እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በዚህ መሠረት በአሁኑ ጊዜ አንዱ ተማሪ ከሌላው እየቀላወጠ በሁሉም ቤተ ጉባኤ ተዘዋውሮ ስለሚማርና ቅኔዎች ስለተቀላቀሉ፡ ግልጽ መስመር ማስቀመጥ የሚያስቸግርበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ቀጥለን እያንዳንዳቸውን እንመልከት፡፡

፰.፮÷፩÷ ሰምና ወርቅ ቅኔ

ሰምና ወርቅ ቅኔ ሁለት ነገሮችን በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ አካቶ የያዘ ሲሆን ና የሚል ማያያዣ አያስፈልገውም፡፡ አንድ አንጥረኛ /ብርና ወርቅ ሠሪ/ በመጀመሪያ ሰሙን በሚፈልገው ቅርጽ ከአዘጋጀ በኋላ ወርቁን አቅልጦ እንደሚያፈስበት ሁሉ ባለቅኔውም ሊቀኝለት ለፈለገው ነገር /ወርቅ/ ተስማሚ ሰም ከፈለገ በኋላ ሁለቱን አዋሕዶ ወይም አጣምሮ በሚገልጽ አንቀጽ ይገልጻል ወይም

ያስተሳስራል፡፡ የሰምና ወርቅ ቅኔ እጅግ በጣም ተወዳጅና በቀላሉም ሰው የሚረዳው የቅኔ ዓይነት ነው፡፡ በሰምና ወርቅ ቅኔ ለወርቁ ሙያው በሚጠይቀው ደረጃ ተስማሚ ሰም ፈልጎ ማግኘት የግድ ይላል፡፡ የተገኘው ነገር ሁሉ ሰም አይሆንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሰሙ ወርቅ ወይም ከወርቁ ሰም ሊፈጠር ይችላል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰሙና ወርቁ በአንድ ቃል /ጎብር/ ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /1948፣ 170/ ሰምና ወርቅ ቅኔን ከዚህ እንደሚከተለው ገልጸውታል፤

ሰምና ወርቅ ማለት እንደወንድማማች በምሥጢር መንታ ሲሆኑ በንባብ ሳይጫፈሩ በስድስት ነገር ተባብረው፤ ተጣምረው አንድ ወጥ ቃል መስለው የሚነገሩ ተመሳሳዮች ማለት ነው፡፡ በተረትም ሰምና ወርቅ እንጀራና መረቅ ይባላል፡፡

በመምህራን ዘንድ የሚታወቁት የሰምና ወርቅ ቅኔ ዓይነቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

፩. ጎብር
፪. ሰም ገፊ
፫. ወርቅ ገፊ
፬. የመጽሐፍ ግስ /የመጽሐፍ ጥቅስ ቅኔ ማለት ነው ፣ ሰምና ወርቅ የሚያስተባብር/
፭. የሰዋስው ግስ /መደበኛው ሰምና ወርቅ ማለት ነው/
፮. ንጽጽር /አንጻር/
፯. ታሪክ /መደቡ ታሪክ ሆኖ በሰምና ወርቅ ይነገራል/፡፡

ይህ ማለት ከነዚህ ውጭ ሰምና ወርቅ የሚባል ቅኔ የለም ለማለት ሳይሆን አዘውትረው የሚነገሩና ብዙዎቹ የቅኔ መምህራን የሚስማሙባቸውን ዋና ዋና የሰምና ወርቅ የቅኔ ዓይነቶችን ለመግለጽ ነው፡፡

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ /አቡነ መልከጼዴቅ/ ደግሞ የሰምና ወርቅ ቅኔ ዓይነቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ይላሉ /1963/፡፡

1. ሰምና ወርቅ
2. ጎብር
3. ሰም ገፊ
4. ወርቃ ወርቅ
5. ሰም ረገፍ
6. ጽድቅ

ይህ አከፋፈል ችግር እንዳለበት በግልጽ ይታያል፡፡ ሰምና ወርቅ በስድስት ይከፈላል ብሎ ራሱን ሰምና ወርቅን በተራ ቁጥር አስገብቶና አንድ ብሎ መጀመር አያስኬድም፡፡ በሌላ በኩልም ሰም ገፊና ሰም ረገፍም አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ ስለዚህ አከፋፈሉ አይመችም፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ለሰምና ወርቅ ዝርዝር የለውም፡፡ ሰምና ወርቅ አንድና ያው ነው ይላሉ፡፡ የጥንት ቅኔዎችን ስንመለከት ግን የሰምና ወርቁ መጠሪያ ስም ተገልጸ እናገኘዋለን፡፡ የታሪክ ቅኔም በሰምና ወርቅ ተካቶ ሊገኝ ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት የመጀመሪያው አማራጭ በተግባር በአበው ቅኔ ተካቶ ስለተገኘ ተመራጭ ሆኗል፡፡

ቅኔ በየዘመኑ እያደገ የመጣ እንጂ በ፲ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ከዛሬው ቅኔ በጣም የተለየ ነው፡፡ እንደ ቤተ ጉባኤ ባይቆጠርም ጎንደርም በታላቁ ዐፄ ኢያሱ ጊዜ ለቅኔ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በተለይ በታላቁ ሊቅ በመምህር ክፍለ ዮሐንስ ይደረሱ የነበሩ ቅኔዎች የተለየ ጣዕም ነበራቸው፡፡ ለምሳሌ ከዚህ የሚከተለውን የመምህር ክፍለ ዮሐንስ የቀጠፋ ቅኔ እንመልከት፣

በእስጢፋኖስ አእላን እመ የጎልቁ፣
ዘበጠኒ ኢያሱ በወርቁ፣

ሰም ገፊ፣ ወርቅ ገፊ፣ ንፅዕር የተባሉ ቅኔዎች ይበልጥ ያደጉት በጎንደር ዘመን ነው፡፡ ምንም እንኳ በዘመኑ የተደረሱ በርካታ ቅኔዎች ቢኖሩም ለዘመኑ ቅኔ

ማሳያ ይሆኑ ዘንድ የተወሰኑ የመወድስ ቅኔዎችን አቅርበናል፡፡ የደብረ ኤልያሱ መምህር ገብረ ሥላሴም የእነ መምህር ክፍለ ዮሐንስ ቅኔዎችን የመሰለ የንጽጽር ቅኔዎችን በመቀኘት ሙያቸው ይታወቁ ነበር፡፡ ለምሳሌነትም ከተጠቀምንባቸው ቅኔዎች መካከልም የእርሳቸው ቅኔዎች ይገኙበታል፡፡ ቅኔዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፣
መወድስ ዘ መምህር ክፍለ ዮሐንስ /18ኛው ክፍለ ዘመን/

፩፥ እምከዊነ ካህን ይኄይስ ከዊነ ኖላዊ፣ ወኅለ እንስሳ ትትበደር እምቤተ መቅደስ ዐባይ፣
እስመ ቤተ መቅደስ ኮነት ቤተ ፈያታይ፣
ወበላዕለ ኖሎት ኢሀለወ፣ ላዕለ ካህናት ዘሀሎ እከይ፣
ትምእርተ ዝኒ ከመ ንርአይ፣ በኅለ እንስሳ ሠረቀ ዘኢየዐርብ ፀሐይ፣
ወኖሎት ተዛውዑ ምስለ ሐራ ልዑል ሰማይ፣
ዓዲ እምቅድመ ዝኒ በመካነ ኖሎት ወመራዕይ፣
ከመ ተጸውዑ ደምፀ ድምፀ ቃለ ዜና ሠናይ፣
ወልደ እንበረም ለምስፍና ወለቅብዐ መንግሥት ወልደ እሴይ፡፡

፪፥ መወድስ ቅኔ ዘተዋነይ ካልእ /18ኛው ክፍለ ዘመን/

ቦኑ ተአምር ከመ ይትቀነዩ፣ ለበረድ በረድ ወመብረቅ ለመብረቅ?
ለምንት ውእቱ ተቀንዮትከ በወርቅ
ዕሩቅ ብእሲ ለብእሲ ዕሩቅ
ዓለመ ሕይወቱ ዘየኀልቅ

ወሰማየ ዐፅሙ ይትከደን፣ ደመና-መቃብር ዕሙቅ
በኢዮር እንዘ ሀሎ አምላከ ኢዮር ምጡቅ
ዘይፈትሕ በኃጥዕ ወይፈትሕ ለጻድቅ
አምጣነ ጽጌ ዓለም ሠርፀ መደልዋን አዕጹቅ
ጽባሐ ይሠርፅ ወሠርከ ይወድቅ

፫፥ **መወድስ ዘተዋነይ /ከአድማሱ ጀንበሬ መጽሐፈ ቅኔ የተገኘ በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን/**

አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ፣ ወአይቴ እገይይ እምቅድመ ገጽከ አብ፣
እመኒ ዐረጉ መንገለ ሰማይ ርኂብ፣
ወእመ ወረድኩ ውስተ ምድር ጸባብ፣
እስመ አንተ ትትረከብ፣ ምስለ ኖኅ ባሕር ህየ ወህየ ምስለ ኮከብ፣
ባሕቱ ተዘከረኒ በምሕረትከ ፅጹብ፣
ከመ ኢያንሥኡ እደዊሙ ላዕሌየ አሕዛብ፣
ምሕረተከሂ ኢተርሳዕ እስከ ይመውት ኪሩብ፣
በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ወበእንተ ቅዱስከ ያዕቆብ።።

፬፥ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመምህር ገብረ ሥላሴ
ቦ ኃያል በዲበ ኃያል፣ እስመ እንዘ በለስ ይትሜካሕ በላዕለ አዳም ርእስ፣
መንፈይል ዝናም ንጉሠ ጢሮስ፣
ነሰተ ቤተ ልምላሜሁ ለመካሕ በለስ፣
ወእንዘ ይትሜካሕ በበለስ፣ ውእቱ ጠል ጎፍረ በኤልያስ፣
ኤልያስሰ እንዘ ውእቱ ቀታሌ ዝናም ነፍስ፣
ተንሥአ በላዕሌሁ ዘይመውየ ኃይለ ነፋስ
ወእንዘ ረሀብ ይጸርሕ ውስተ ዘኤልያስ ከርሥ፣
ለረሀብ ተበቀሎ ዘመደ መባልዕት ኢዮስያስ።።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቅኔዎች በይዘት ተመሳሳይ ሲሆኑ /ንጽጽር/ የተሟላ ወሰነ ሐረግና የዜማ ልክ ያላቸው ናቸው፡፡ በተለይ በዐፄ በካፋ ዘመነ መንግሥት የጎንደርን ቤተ መንግሥት ያዘወትር ነበር የሚባለው የተዋነይ ካልእ እና የመምህር ክፍለ ዮሐንስ ቅኔዎች፣ የዐፄ ኢያሱ /አድያም ሰገድ/ እና የዐፄ በካፋ /መሲሕ ሰገድ/ ዘመን ቅኔዎች በመሆናቸው ቅኔ በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በየዘመኑ የነበረውን የቅኔ ዕድገት በዝርዝር ለማሳየት አይደለም፡፡ ዓላማው ዛሬ ሦስቱ አብያተ ጉባኤ የሚለያዩባቸውንና አንድ የሚሆኑባቸውን የቅኔ አካሄዶች በሰምና ወርቅና በጎዳና ቅኔዎች በምሳሌ ማሳየት ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ቅኔዎች በጎንደር ዘመነ መንግሥት ቅኔ የደረሰበትን ደረጃ ማሳየታቸው አንድ ነገር ሆኖ የቅኔዎቹ ባሕርይ ሲመረመር መሠረቱ ከሦስቱ አብያተ ጉባኤ እንደማይወጣ ጥሩ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ጎንደር ሌላ ፬ኛ ቤተ ጉባኤ ሳይሆን በሦስቱ አብያተ ጉባኤ የሚጠቃለል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ግን ራሱን የቻለ ቤተ ጉባኤ አድርጎ አቅርቦታል፡፡

ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን የሰምና ወርቅ ዓይነቶች በሦስቱ አብያተ ጉባኤ ምን እንደሚመስሉ በምሳሌ እንመልከታቸው፤

፭፥፮፥፩ የሰምና ወርቅ ቅኔዎች በየቤተ ጉባኤው

ሀ. የዋሸራ ቤተ ጉባኤ የሰምና ወርቅ ቅኔዎች

፩. ጉባኤ ቃና ዘመሪጌታ አስካል /በበጌምድር የዋሸራ ቤተ ጉባኤ/

ኢትጎዝኒ እንከ ጉባኤ ቃና ድንግል
አምጣነ የአምር ለኪ ዘፈጠረኪ አስካል።።

፪. ዘአምላኪየ ቅኔ ዘዋሸራ ተክሌ
በቀራንዮ ተገብረ ዘያስተአጽብ ልሂቀ፤
እንዘ ደም አልቦ በኮከብ ዘወድቀ፤
ዘኢወድቀ ወርኅ አምጣነ በደም ተጠምቀ።።

፫. ጎብር ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመምህር ግ/ሥላሴ
ክንፉ፤ ዘደ/ኤልያስ
እስፍንተ ዕለተ ትጸውሪዮ <u>አመት</u>
ለወልድኪ ነቢየ ቴስብያ <u>ዘአልቦ ዕረፍት</u>
እስመ ይብል ዘልፈ <u>ኢይልክፈኒ መሬት</u>
በዚህ ቅኔ ውስጥ ሦስት ጎብረ ቃል አለ።። አመት /አገልጋይ ወይም ዘመን/፤ ዕረፍት/የማያርፍ ወይም የማይሞት/፤ ኢይልክፈኒ መሬት/ከምድር ላይ አልቀመጥም ማለት ወይም ሞቶ በመሬት አለመቀበር/።።

፬. ጉባኤ ቃና ዘመምህር ጥዑመ ልሳን ዘዋሸራ
እምጎበ መኑ ትፄወን ኢትዮጵያ ለተዋሕዶ
መርዓቱ
በዘመነ አውግስቶስ ያሩ አኮኑ አዕይንቲሃ
ክልኤቱ
ቅኔው የብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስንና የታላቁን መሪ የአቶ መለስ ሞትን የሚመለከት ነው።። እንደሚታወቀው ፓትርያርኩም ሆኑ ጠቅላይ ሚንስትሩ ያረፉት በነሐሴ ወር ነው።። መምህሩ ይህን ቅኔ የዘረፉት ለሁለቱ ታላላቅ ሰዎች በዋሸራ ገዳም ፍትሐት ሲፈታ ነው።።

፭. ጉባኤ ቃና ቅኔ ዘእመይቱ ገላነሽ ሐዲስ
ከበሮ ጻድቅ ትእዛዘ ወንጌል አቀበ
ክልኤተ ገጻተ እስመ ለተጸፍየ ወሀበ

ለ. የዋድላ ቤተ ጉባኤ የሰምና ወርቅ ቅኔዎች

ጉባኤ ቃና ዘመሪጌታ መሠረት ዐሥራት

፮. ማኅደረ እስራኤል ኢኮነት ኤርትራ፣ ሕንፃ እደ ሙሴ ኬንያ
በዓለ አፍራስ ፈርያን አኮኑ፣ ማኅደረ አፍራስ ረሲያ
፯ ፍድዩ ዮሴፍ ወሰሎሜ ወርቀ ተሰዶ ቀዲሙ፣
አምላነ አንትሙ ላሕመ ዘሰረቅሙ
አንትሙ።።
፰. ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ
ፈለግ ዮርዳኖስ ፈራህ፣ ፈራህ ፈራህ አንተ፣
በቅጽበት አምላነ ጐየይከ ጊዜ ፀብእ
ክልዔተ፤
ጊዜ ኢያሱ ፀጋመ ወጊዜ ኢየሱስ ድህሪተ፣
ይህ ቅኔ የታሪክ ሰምና ወርቅ ቅኔ ነው።።
፱ ዋዜማ ቅኔ ዘመምህር አብርሃም ወርቁ /ዋድላ/፣
አንቲ ምድረ ዋድላ፣ ድንግለ ሙሴ ወዮሴፍ
ዘልብሰ ጸጋ ለበስኪ፣
ሶሎሙ ነገሥታተ ምድር ይሰግዱ ለኪ፣
እንዘ ይልህሡ ዘንተ ፀበለ ዘቦ እግርኪ፣
አምላነ እለ ኀሠሡ ምሕረተ ወልድኪ፣
ዘፈጠረ ፈቃዶ ኪያኪ።።

ሐ. የጐንጅ ቤተ ጉባኤ ሰምና ወርቅ ቅኔዎች

፲፥ ጉባኤ ቃና ቅኔ ዘቁሰ ገበዝ በቃ ዘጎንጅ
መሰለ ዮሴፍ ዘያውዕያ ለግብጽ፣
አኮኑ ወረደ በነሲአ እሳት ወዕፅ

፲፩ ይእዜ ዕለት ፋኑኤልሃ ዘንጎን፣ /ዘሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው/

እስመ ጸውያቱ ድንግለ በመና ዘዘካርያስ ጎዲጎ፣
፲፪ ዘአምላኪየ ዘሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው፣

ቀበርዎ ዮም በዘሊቃውንት ምዕዋድ
ለዘሞተ ቅኔ መነኮስ ዋሕድ፣

የዋሓን አርዳእ ለዝንቱ እስመ አልቦቱ ዘመድ።

፷፥፮፥፪ የጎዳና ቅኔዎች

የጎዳና ቅኔ ከሰምና ወርቅ የሚለየው መደበኛውን የሰምና ወርቅ መንገድ ባለመከተሉና ከባድ በመሆኑ ነው። በአብዛኛው የጎዳና ቅኔ ፍልስፍና ይበዛበታል። ባለቅኔው በውስጡ ሰምና ወርቅን ሊጠቀም ይችላል። የጎዳና ቅኔ ቁጥሩ ይህን ያህል ነው ተብሎ አይወሰንም። አንዳንዱ ፭፱ ነው ይላል። ሌላው ደግሞ ከ፴፲፱ በላይ ነው ይላል። በአብዛኛው መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ግን ከ፱ የሚበልጡ አይደሉም ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ከዚህ የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፣

፲፥ ውስጠዘ ድርድር፣
፭፥ አገባብ ድርድር፣
፪፥ አንቀጽ ድርድር፣
፫፥ አሰናካይ፣
፬፥ ድርብ አሰናካይ፣
፮፥ ተመኩሳይ
፯፥ ውስጠ ወይራ
፰፥ አገናኝ፣
፷፥ አታላይ መንገድ፣
፲ አንባር፣
፲፭፥ ሙሻዘር፣

፲፪ ÷ ሠረገ፣
፲፫ ÷ ድርብ ሠረገ፣
፲፬ ÷ ዝምዝም ወርቅ፣
፲፭ ÷ የወፍ እግር፣
፲፮ ÷ ፀፀት፣
፲፯ ÷ ምጸት፣
፲፰ ÷ ጉት መንገድ፣
፲፱ ÷ ፍና ተሳልቆ፣
፳ አመጸኛ ዳኛ ወዘተ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጎዳና ቅኔ በቁጥር ይህ ነው ተብሎ ያልተወሰነና በጣም ብዙ ስለሆነ ለምሳሌ ያህል እነዚህን ካየን አሁን ደግሞ ከየጉባኤ ቤቱ ከዚህ የሚከተሉትን የጎዳና ቅኔ ምሳሌዎች እንመልከት፤

ሀ. የዋድላ ቤተ ጉባኤ

፩. ውስጠዘ ድርድር ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመሪጌታ መሠረት ዐሥራት
መራደ ከላውዴዎን ነድ ጊዜ ቀትለ ሰዶም ሐራ፤
መቅትል መስተቃትላነ መቅትለ ኤርትራ፤
ቀተልተ ሙሴ ፈርያነ ሙሴሀ ቀተልተ ገሞራ ገሞራ፡፡
፪. ውስጠዘ ድርድር ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ
ከለልተ አድባር ክሉለ መከልለ ዕድሜ ወዕድሜ፤
ደመና ደመና ደመና ወጊሜ፤
ማርያም አእመረት ፍኖታ፤ ወኢያእመረት ሰሎሜ፡፡
፫. አገባብ ድርድር መወድስ ቅኔ ዘመ/መሠረት ዐሥራት
ግርምተ ዘቦ ዘቦሙ ጎበ ተደለዉ፤
መሳክወ በርሃን ኪሩቤል አንስተ ደብረ ኮሬብ ጎበ ጸራ፤

ጎበ ጎበ አልቦ አፍራስ ጸረ አመ ኤልያስ ሐራ፤
ዘዓዲ ዘዓዲ ዘዓዲ ለዕዝራ፤
አመ አመ ያዕቆብ ያዕቆብ፤ ወርጎ ወርጎ ጌዴዎን
ኔሳን ወርጎ ወርጎ ምድያም ወሲሣራ
ለዓለም
ዮሐንስ ዘውግ ሙሴ ዘበ ሐብለ አሳት ገሞራ፤
ይስሕብ ማዕበላተ አፍራሰ ኤርትራ ጎበ ኤርትራ፤
ረሀበ ከነዓን ሰይፍ ዘከነዓናዊ አእመራ፤
ጎበ ሣቀየቶ ለቶማስ ቶማስ ተዘከራ
፬. ድርብ አሰናካይ መወድስ ዘመሪጌታ መሠረት
ዐሥራት
አመ ዘእግረ ላሕም አውግስቶስ ሐርጌ እንተ ርእያ፤
ወልደ አሞፅ ባሶር ደመና ኤዶምያስ
ሜጠ ዐይነ ሰቅል እሳት ቀላውትሞኖስ፤
በርእየተ ሙሴ ኤላውጠን፤ መብረቅ ወርቀ ደማስቆ
ናግራን ተርሴስ፤/ግ አይዋጥም/
ይገፍዓሁ እብነ ጌባል፤ ራማ አድማስ በረደ አድማስ
አድማስ፤
እማጎደረ ኤርሞን ኤርሞን ሄሮድያኖስ፤
ለኤልሳዕ ምዙናኑ ደመና ዐቀበ ፋርስ፤
እምርእስ ተበትከ ወአንጦድጦደ በርእስ፤
ደንገፀ ሰማዒሁ ሐመልማል ላእከ ጢሮስ፡፡
፭. ንጽጽር መወድስ ቅኔ ዘመሪጌታ መሠረት
ዐሥራት
ምሳሌ ሰማዕት ከመ ይትፈጸም፤ ወከመ ኢይትርፍ
ድኅረ በዘ ያዕቆብ ጠቢብ
ከመ እንበለ ዘርዕ ሞት ልደተ ኤልያስ ንህብ
እምነ ያዕቆብ አረጋዊ፤ ይሠርቅ ምሉአ ብርሃን ሰይፈ
ነድ ኮከብ
ወየአትት ጌጋያተ፤ ሥጋ ወዐፅመ እምኔሆሙ ለሕዝብ
ዐርገዚ ጠፈረ ሥጋ በቀርነ ስቃይ ዕፁብ
ሰይፈ ነድ ዘአፍቀረ ስኖ ለያዕቆብ
እመኒ ዓለም ጽልመተ ሊሊት ግልቡብ
ፀሐየ ተሰቅሎ አማኑኤል አኮኑ ኢየዐርብ

፮. አንቀጽ ድርድር ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመሪጌታ መሠረት

ወልደ ዮሴፍ ዮሴፍ እንተ ኢኬደ ዘኬደ፣
እብነ ጌባል እብነ ቢታንያ ክቡደ ክቡደ፣
አእባነ ምድረ ግብፅ አእባነ አስተዋደደ ሰገደ፣

፯. ጉባኤ ቃና ዘመሪጌታ መሠረት፣

ማርያም ዮሴፍ ዘእምዘእለ ዮሴፍ ሀሎ፣
መላዕክተ ዮሴፍ ዮሴፍ ሠረገላ ዚአኪ
አውሎ።።

፰. ሚ በዝኁ ዘመሪጌታ መሠረት፣

በሃሌ ዘራጉኤል ቃል ብሂል ኪሩቤል ለባሕረ
ውዳሴ አፍላጉ፣
ጎበ ወግረ ስኒን ታቦር የዐርጉ የዐርጉ፣
ገባዕተ ሙሴ መስቀል እደ ሐቅለ ሙሴ
የአስር በሐመልማላዊት ሐረጉ።።

፱፥ ዋዜማ ዘመሪጌታ መሠረት፣

መሰውር መሰውረ፣ ሰዋሬ መሰውር ክሡተ
ዐረፍተ ባቢሎን ታዕካ፣
መሰውረ ኢመሰውራነ ምህርካ ምህርካ፣
ዘካርያስ በሶር ኤጴሞሰ ዮሐንስ ዋካ፣
እስመ ለዘባረከ ሄኖክ ወልደ በረካ፣
ሰይፈ ነድ ሰይፈ ነድ ቀደስካ።።

፲፥ ሥላሴ ዘመሪጌታ መሠረት፣

አንቀልቀለ አንቀልቀለ፣ ያንቀልቅል ያሮክ
ናቡዛርዳን በሐጸ ምጉንጻ ዘአዴር ተመትሮ፣
ናህሰ ዛብሎን ገሊላ፣
ጎበ ቆመ አንቀጸ ቴቁሄ ኤዶምያስ ተድላ፣
ብሂለ ሰይፈ ዘዘቦ፣ ቢፀ ወልደ አብራም ዔላ፣
መስተፅዕን ዘናዳብ ሠረገላ፣
ለከርካ ዘርእዩ ናግራን ጽጌ ደንጎላ፣
አስካሎሙ ተሰዶ አስካላ።።

፲፩፥ ዘይእዜ ዘመሪጌታ መሠረት፣

ኢያሱ ወኤልሳዕ ገባዕተ ሙሴ፣ በዘያረ
ሐውልት አንሥአ ወበዘልህኩተ ያረ፣
ሐመልማላዊተ ኢያሪኮ፣ ሐመልማለ ገራህተ
ምሳሌ ወርህቅተ ባሕረ፣
አመ ከመ አብርሃም ያደ ወከመ ዕዝራ አመ
ነጸረ፣
ተሰወረ እብነ ወኢተሰወረ፣
እስመ ቁረ ጽዮን ፈርሀ ወቁረ ጽዮን
አግመረ።።

፲፪። ዘይእዜ ዘመሪጌታ መሠረት፣

ኬንያ ዘግብፅ ክፍለ ቴቁሄ፣ ዘዘእንተ ዮሴፍ
ዮሴፍ ዘዘናቡቴ ናቡቴ፣
መራደ አክዮር አሞናዊ፣ መራድ መራደ ገሞራ
ዘውረ ጌባል ጳርቴ፣
መራድ መራድ መራደ ያዕቆብ ኢያቡስቴ፣
ፀዋሬ ዘኢያዜር ቀርን ወምቅድሐ ስቴ፣
ጠየቀ ዮሴፍ ከመ ቤተ ዮሴፍ አይቴ።።

፲፫። መወድስ ዘመሪጌታ መሠረት፣
መኰንነ ግርማ ፋኑኤል ለዘካርያስ፣
ወሐሴቦናዊት ድንግል በዓመተ አልዓዛር
ዮርማሮዬቅ፣
ጎበ ተሰምዐ በሙሴ እጕለ ሱላግያ ማዕነቅ፣
ብሂል ብሂል ኢዮአካዝ፣ ፊልፆስ መዝገበ
አሐዱ ኢዮኢታም ወርቅ፣
በዘአርአያሁ ሰማግራዶስ ኢዮዛባድ ቂርቆስ
ኤልዩድ ዐምደ ባላቅ፣
ብሂል ሰይፈ ብሂል ጠፈረ ዳብራን መብረቅ፣
አድለቅለቀ አድለቅለቀ ያድለቀልቅ
ያድለቀልቅ፣
አድያመ ከላውዴዎን ባሕር በዘከላውዴዎን
ንድቅ፣

ሠረገላ ሜዶን ሠረገላ መልከጼዴቅ
መልከጼዴቅ።።
፲፬፥ መወድስ ዘመሪጌታ መሠረት፣
ደቂቀ ተአጽፎ ሜላተ አጸርግዮነ በከውረ
ዘካርያስ ወርቅ እንተ ነደ እሳት መንኮራኩሩ፣
መዋርስተ ሐዳስ ገለአድ እለ ቀትለ ገለአድ
ሠምሩ፣
ድኅረ እምውሳጣይ አንቀጸ ጋዛ፣ አሶርዮን
ዘዕንቈወራውሬ እስማኤል ጠፈሩ፣
ከሩናቶሙ ከሩናቶሙ ከሩናቶሙ ነስኡ ሐቅለ
ገለአድ ይሑሩ፣
በመልዕልተ ሰይፍ ዓምደ ገሊላ ለዘካርያስ
ማኅደሩ፣
መልበሶሙ መልበሶሙ መልበሶሙ ያነብሩ፣
በእግረ ሰማዕት አፍራስ እስመ ይትበደሩ፣
ኀበ እለ ሠምሩ ኪሩቤል መናስግተ ቀውስጦስ
እለሰምሩ።።
፲፯. መወድስ ዘመሪጌታ መሠረት፣
መብክያተ ኢያዜር ራሄል ማዕከለ ቴቁሄ፣ ኀበ
ውስተ ስፍሕት ኢያዜር ኀበ ኀበ ሳምሮን
ባሕረ ንትጋ፣
አጸፍተ ብሂል ዘጽዮን ጥልልተ ጽዮን ፈለጋ፣
ኀበ ኀበ ኢያኤል ወዲቦራ፣ ድልዋት መርሐ
ቤተ ሙሴ ለሙሴ መንሰጋ፣
አቀበ ደብረ ታቦር እንተ ሲና፣ መዋርስተ
ብሂል ብሂለ መዋርስተ ጋዛ መዝገበ ፀጋ፣
በእግረ አሶርዮን ሠረገላ አቀበ አሶርዮን ሥጋ፣
የዐርጉ የዐርጉ የዐርጋ የዐርጋ፣
ደናግለ ብሂል ኪሩቤል ዘእምርተ ኪሩቤል
ዘውጋ፣
አንገለጉ አንገለጉ አንገለጋ አንገለጋ።።

ለ. የኅንጅ ቤተ ጉባኤ፣

መወድስ ቅኔ ዘሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው
/የንዑስ አንቀጽ አሰካክና ግጭት መንገድ፣
፩. በአይ መካን ዘለዘሀሎነ፣ ዐጸደ ተርእዮ
እምቴማን ኢሳይያስ አቅሌስያ፣
ወዘዘአስተርአየት ዮሴፍ አመ አስተርአያ፣
ቅድመ ገጸ ጳውሎስ ጳውሎስ፣ ወጴጥሮስ
ቅድመ ያስተርእዮ አስተርአየት ነያ፣
ዜና ምሳሌ ግብፅ ናስተማስላ፣ ቦኑ በግብፅ
ወሚመ በሶርያ፣
ለዓለም
እንበለ ባቲ በኤፌሶን ከመ ዮሐንስ ጎረያ፣
እስመ እስመ ጎረዩ ባስልዮስ ኢትዮጵያዊ
ኢትዮጵያ፣
ወቴስብያዊ ኤልያስ ምድረ ቴስብያ፣
ከዊነ ነቢይ በኤልያስ ወከዊነ ጴጥሮስ
ሐዋርያ።
መወድስ ዘመሪጌታ መንግሥቱ

፪.ሰብአ ደማስቆ ጳውሎስ እመ ይመስሎ፣
ለሰብአ ቀራንዮስ ጴጥሮስ መፍትው
በድልወቱ፣
ዘይፈትዎ ጳውሎስ አምጣነ ጴጥሮስ ይፈቱ፣
ወተሐሥዮ ተሐሥዮተ፣ ጳውሎስ ሰብአ
ደማስቆ ወጴጥሮስ ክልኤቱ፣
በቅድመ ኪሩቤል አርባዕቱ፣ ምስለ አርባዕቱ
ኪሩቤል እስመ ተአኵቶ ተአኵቱ።
ጴጥሮስሂ ወጳውሎስ ለአማኑኤል አዕርክቱ፣
በሥምረተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ሠለስቱ፣
እስመ በዝኀነ ወፈድፈደ ፍቅሮሙ
ለእሙንቱ።

ዘመምህር ዜና ሥላሴ /ዘአቸፈር/

፫ ÷ ስርናይ ዘሪዐ ስርናየ ጴጥሮስ ዘሪዕ፣

ናሁ በጴጥሮስ ሰብአ ዘብውድ ጽርዕ

፬፥ ብሂል ዘባዕድ ታዴዎስ ፍና ታዴዎስ ዘሐሮ፣

ጴጥሮስ ጴጥሮስ ታዴዎስሃ ነጺሮ።።

፭፥ መቲር ሰይፈ ክሳደ ይስሐቅ አብእኮ፣

ምስራቅ አብርሃም እምታዕካ አምላከ አብራም
አምልኮ
፮ ዋዜማ ቅኔ ዘመምህር አበርሃም ወርቁ /ዋድላ/፣
ለዮሐንስ ዘለያሬድ፣ ዘለዘሚካኤል ሊቅ
ዘለመልከጼዴቅ ኮሮ፣
ቀደሶ ቀደሶ ቀደሶ አክበሮ፣
ንግደ ብሥራታዊ ገብርኤል መልአከ ሰላም አእምሮ፣
እስመ ለአእምሮት ንግድ ያምህሮ፣
ፈጣሪሁ ለሙሴ ማኅደሮ።።

፷፥፮፥፫. የቅኔ ሙያ አሰጣጥ

ቅኔ በሚደረስበት ጊዜ ሰምና ወርቅ ወይም ጎዳና መሆኑ ብቻውን በቂ አይደለም።። አናቅጽን፣ ነባርንና አገባብን አቀነባብሮ መነገሩ ቅኔን ቅኔ ለማድረግ በቂ አይደለም።። ቅኔ በውስጡ ከያዛቸው ጥበባት መካከል አንዱ ሙያ አሰጣጥ ነው።። በቅኔ ውስጥ ቤት ስለመታ ወይም ምሥጢር ስለጠበቀ ዝም ብሎ አይነገርም።። ሙያው በሚገባና ታስቦበት መዘጋጀት አለበት።። ቅኔ ፍልስፍና ወይም የምሥጋና ግጥም፣ እንዲሁም የተመጠነ የዜማ ልክ ያለው ብቻ ሳይሆን ሙያ የሚባል ረቂቅ ጥበብም አለው።። ለቅኔ ሙያ ታላቁን ሚና የሚጫወቱት አናቅጽና አገባቦች ናቸው።። አርዕስትና ቅጽልም የራሳቸው

ሚና አላቸው፡፡ በተለይ ውስጠ ተሳሳቢን መሠረት አድርገን ስንነሳ ሁሉም ነገር ተጠቃሎ ወደ አናቅጽ መሄዱ ስለማይቀር አናቅጽ የሙያ አሰጣጥ ወሳኞች ናቸው፡፡
ለቅኔ ምሁራን ይህ ተራ ነገር ቢሆንም መጽሐፉን ወጣንያንም አንብበው እንዲረዱት ለማድረግ ይቻል ዘንድ ሙያ አሰጣጥ በመጽሐፉ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳ መሠረታዊ ልዩነት ባይኖርም ሙያ አሰጣጥ በየጉባኤ ቤቱ ከዚህ እንደሚከተለው ተለይቶ ቀርቧል፡፡ የቅኔ ሙያ ምን እንደሚመስል በምሳሌ እንመልከተው፡፡

የዋሸራ ሙያ አሰጣጥ

ንባብ፣ ለጸብሕ ሞት ጸዋሚ መልአክ
ሰማይ ጎደጋ፤
ጸብሕ ሞት እስመ ተሠርዐት በሥጋ፤
ትርጉም፤ ሞት ወጥን የሰማይ መልአክ ጠመኛ ተዋት /አልበላትም/፡፡ ወጥ ሞት በሥጋ ተሠርታለችና፡፡
ሙያው፡- ለ - ደቂቅ አገባብ፣ ፍቺው ን ሙያው ተጠቃሽ
ጸብሕና ሞት ምሳሌ፣ ጸብሕ፡ ሰም፤ ሞት ወርቅ፤ ሙያው ተጠቃሽ የወደቀበት ተሳቢ፡፡
ጸዋሚ እና መልአክ ምሳሌ፤ ጸዋሚ፡ ሰም መልአክ ወርቅ፤ ሙያው ባለቤት /የቅኔው ወይም የአንቀጹ/
ሰማይ - የመልአክ ዘርፍ

ጎደጋ - ማሰሪያ ግሥ /አንቀጽ/
ጸብሕና ሞት - ምሳሌ፣ ጸብሕ ሰም ሞት ወርቅ፣ ሙያው የአስረጂ ባለቤት
እስመ- አቢይ አገባብ፣ ፍቺው ና፤ ሙያው - አስረጂ /አንቀጽን ማገድ/
ተሠርዐት - አንቀጽ፣ ፍችው ተሠራች፣ ተሠርዐት እንዳያስር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል።
በ - ደቂቅ አገባብ፣ ፍቺው - በቁሙ፤ ሙያው ማድረጊያ
ሥጋ- ማድረጊያ የወደቀበት ጎበር /የማድረጊያ ባለቤት/፣ /መምህር ይኄይስ ወርቁ ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት 1960/።

የጐንጅ ሙያ አሰጣጥ

ጉባኤ ቃና ዘመርጌታ ጥበቡ ደስታ

ንባብ፣ ለኮቤዝ ኮቤዝ ሶበ መግዘአ ገድል ሦዐ
ጸውዖ መልአከ እምራማ ወእምነ ዱዳሌብ ሰብአ

በጎንጂ ጉባዔ ቃና የመጀመሪያው ስንኝ ሁልጊዜ ግእዝ ብቻ ነው

ትርጉም፡- ኮቤዝ ገድል ፍሪዳን ባረደ ጊዜ ሰውን ከዱዳሌብ /ምድር/፣ መልአክን ከሰማይ መጥራት ለኮቤዝ ይገባዋል።

ርቃቄ /ርቀት/፡-

ሰም፡- ኮቤዝ ፍሪዳን ባረደ ጊዜ ሰውን ከዱዳሌብ መልአክን ከራማ /ሰማይ/ መጥራት ይገባዋል።
ወርቅ፡- ኮቤዝ /ገብረ መንፈስ ቅዱስ/ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ተጋድሎን በተቀበለ ጊዜ እንደ መልአክ ከምግብ ርቆ፣ እንደሰው ሰብአዊ ባሕርይን ተቆጣጥሮ ገድልን መፈጸም ይገባዋል።
ሙያ፡- ለ፤ ደቂቅ አገባብ ሆኖ፣ ይደሉ የሚለውን ግስ ያመጣል። ይደሉ ያለው ማሰሪያ፣

ኮቤዝ /ሁለተኛው ኮቤዝ የሰው ስም/ ሰም ሲሆን ለ የወደቀበት አቀባይ ነው። ሁለኛው ኮቤዝ የሃዐ ባለቤት ሶበ፤ አቢይ አገባብ ሲሆን ፍቺው ጊዜ ምሥጢሩም ጊዜ ነው። ሙያው ማንጸሪያ ወይም ማድረጊያ ነው። ሃዐ ያለው አንቀጽ ያሥር ነበር ሶበ ወድቆ አስቀርቶታል። መግዝአ እና ገድል ምሳሌ፣ መግዝእ ሰም፥ ገድል ወርቅ፣ ተመስሎ ለገቢር አንቀጹ ለሃዐ ተሳቢ ይሆናል። ጸውያ የይደለ ባለቤት፣ እም ደቂቅ አገባብ፣ ሙያው መነሻ፤ ራማ እም የወደቀበት መነሻ፣ ወይም የመነሻ ባለቤት።

መልአክ የጸውያ ተሳቢ፤ ወ አውራጅ ፤ እም እንዳለፈው፣ ነ፡ ትራስ፣ ዱዳሌብ እም የወደቀበት መነሻ፤ ሰብአ የጸውያ ተሳቢ።

ውስጠ ተሳሳቢ

ይህን ቅኔ በውስጠ ተሳሳቢ ጊዜ በሁለት ከፍለን አናየዋለን። ርቱዕ ተሳቢ /ቀጥተኛ ተሳቢ/ የሆነው አያጠያይቅም። ርቱዕ ተሳቢ ለሆነው ተሳቢ ነው። ከጸውያ በላይ ያለ አገበባትም ርቱዓን ተሳቢዎች በጸውያ ይሳባሉ። ሁለኛውን ኮቤዝ ጨምሮ የሃዐ ርቱዕ ተሳቢ ይባላል። ሶበ በአቢይ አገባብነቱ ሃዐንና ባለቤቱን ጨምሮ በጸውያ ይሳባል። ጸውያ የወደቀበት ኮቤዝን ጨምሮ በይደለ ይሳባል።

ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመሪጌታ ገዳሙ አያሌው

አርዌ ምሳሌ መፍርህ ዘዘነቢያት ሀገር
በሐውልት ኢያሱ ወአሮን በበትር
እመ ቀጥቀጥዎ ወድቀ ዲቤሃ፡ ለዘኢሳይያስ ምድር

ትርጉም፡-

በነቢያት አገር የሚፈራ አውሬ ምሳሌ፣ ኢያሱ በድንጋይ፣ አሮን በበትር ቢቀጠቅጡት ከኢሳይያስ ምድር ላይ ተዘረጋ /ወደቀ/
ርቃቄ /ማመሥጠር/፡-
በሰም፡- በነቢያት አገር የሚፈራ አውሬ እያሱ በድንጋይ፣ አሮን በበትር
ቢቀጠቅጡት ከኢሳይየስ ምድር ላይ ወደቀ የሚለው ሰም ነው፡፡
በወርቅ፡- በነቢያት ዘመን በትንቢት በተነገረ ምሳሌ ኢያሱ ሐውልተ ስምዕ፣
አሮን፡- በትር እንተ ሠረጸት እምስርወ እሴይ እያለ ለእመቤታችን የሰጡት ምሳሌ በኢሳይያስ፣ ምድር ጽንዕት ዘኢሳይያስ እየተባለ ተነገረ ማለት ነው፡፡
ሙያ፡- አርቄ ምሳሌ ተመስሎ፣ አርቄ ሰም፣ ምሳሌ ወርቅ ሆኖ የወድቀ ባለቤት፣
መፍርህ የአርቄ ምሳሌ ቅጽል፣ ዘዘነቢያት የመጀመሪያ ዘ ዘርፍ አያያዥ፣ ሁለተኛው ዘ ዘርፍ ደፊ ሲሆን ጠቅላላ ንባቡ መፍርህ ሀገረ ነቢያት ማለት ሆኖ ሀገር የመፍርህ ዘርፍ፣ ነቢያት የሀገር ዘርፍ ይሆናል፡፡
በ ፣ ደቂቅ አገባብ ሲሆን በቁም ቀሪ ሆኖ ሙያው ማድረጊያ፣ ሐውልት በ የወደቀበት ማድረጊያ፣ ወ፣ አውራጅ፣
አሮንና ኢያሱ የቀጥቀጥዎ ባለቤቶች፣ በ እንዳለፈው፣ በትር በ የወደቀበት ማድረጊያ፣ ይባላል፡፡
እመ አቢይ አገባብ ሲሆን ሙያው ማንጸሪያ ቀጥቀጥዎ ያለው ያሥር ነበር አመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡ ወድቀ ያለው ማሰሪያ፡፡ ዲቤሃ ደቂቅ አገባብ፣ ፍችው ላይ ሙያው ማንጸሪያ፣ ሃ

ዝርዝር ለ ፤ ተጠቃሽ፤ ዘኢሳይያስ፡- ዘ ዘርፍ ደፊ፡፡ ጠቅላላ ንባቡ ዲበ ምድረ ኢሣይያስ ማለት ነው፡፡ ምድር ዲበ የወደቀበት ማንጸሪያ፣ ኢሳይያስ የምድር ዘርፍ ይሆናል፡፡
ውስጠ ተሳሳቢ፡-
በውስጠ ተሳሳቢ ጊዜ ይህ ቅኔ በ3 ይከፈላል፡፡ አርቄ ምሳሌ እስከ መፍርህ በወድቀ ይሳባል፡፡ ዘዘነቢያት ሀገር በመፍርህ ይሳባል፡፡ ኢያሱ አሮን፣ ሐውልት በትር ደቂቅ አገባቡን ጨምሮ በቀጥቀጥዎ ይሳባሉ፡፡ ከዲቤሃ እስከ ምድረ ኢሳይያስ በወድቀ ይሳባል/ሊቀ አእላፍ ገዳሙ አያሌው/፡፡

የዋድላ ሙያ አሰጣጥ

በሙያ አሰጣጥ የዋድላ ምሑራንም ከዋሸራና ከጎንጅ መሠራታዊ ልዩነት የላቸውም፡፡ ከዚህ የሚከተሉትን ቅኔዎች በማሳያነት እንመልከት፤

ጉባኤ ቃና ዘመሪጌታ መሠረት ዐሥራት ንባብ፣

ማኅደረ እስራኤል ኢኮነት ኤርትራ፤ ሕንፃ እደ ሙሴ ኬንያ
በዓለ አፍራስ ፈርያን አኮኑ፤ ማኅደረ አፍራስ ረሰያ

ፍችው፤ ሙሴ በእጁ የሠራት ኤርትራ ቤትየእስራኤል ማደሪያ አልሆነችም፤ የፈረሶች ባለቤት የሆነው ፈርያን የፈረሶች ማደሪያ አድርጓታልና፡፡
ሙያው፤ ማኅደር የኢኮነት ተሳቢ፤ እስራኤል የማኅደር ዘርፍ፤ ኢኮነት ማሠሪያ

አንቀጽ፤ አንቀጹ ይስባል እንጂ አይሳብም፡፡ ኤርትራ ሕንጻ ምሳሌ፤ ሕንጻ ሰም ኤርትራ ወርቅ፤ ሙያው ባለቤት፤ /ምሥጢሩ የአንቀጹ፤ የኢኮነት ተሳቢ ነው/፡፡

በዓል ፈርያን ምሳሌ፤ በዓል ሰም፤ ፈርያን ወርቅ፤ ሙያው የአስረጅ ባለቤት፤ /ምሥጢሩ የረሰያ ተሳቢ/ ፤ አፍራስ የበዓል ዘርፍ፤ አኮኑ ዐቢይ አገባብ፤ ፍችው ና፤ ሙያው አስረጅ፤ ማኅደር የረሰያ ተሳቢ፤ አፍራስ የማኅደር ዘርፍ፤ ረሰያ እንዳያስር አኮኑ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ዘአምላኪየ ቅኔ ዘመሪጌታ መሠረት ዐሥራት

መራደ ከላውዴዎን ነድ ጊዜ ቀትለ ሰዶም ሐራ፤
መቅትል መስተቃትላነ መቅትለ ኤርትራ፤
መቅትለ ሙሴ ፈርያነ ሙሴሃ፤ ቀተልተ ገሞራ ገሞራ

ፍችው፤ ፈርያንን በሙሴ ያስገደለ ኤርትራ፤ ኤርትራን ያስገደለ ሙሴ፤ ሙሴን ከገዳዮቻቸው ጋር ያገዳደሉ ገሞራውያን፤ የከላውዴዎን ወታደር እሳት በሰዶም ጦርነት ጊዜ ገሞራውያንን የገደለ ነው፡፡

ሙያው፤ መራድ ነድ ምሳሌ፤ መራድ ሰም ነድ ወርቅ፤ ሙያው ባለቤት /የመቅትል ተሳቢ/ ከላውዴዎን የመራድ ዘርፍ፤ ጊዜ ደቂቅ አገባብ፤ ወይም ጊዜ የወጣበት፤ ቀትለ የጊዜ ዘርፍ፤ ሰዶም ሐራ ምሳሌ፤ ሐራ ሰም ሰዶም ወርቅ፤ ሆኖ የቀትለ ዘርፍ፤ መቅትል ውእቱን መርምሮ ማሠሪያ አንቀጽ፡ መስተቃትላን የገሞራ ቅጽል፤ መቅትለ የሙሴ /ሙሴሃ/ ቅጽል፤ ኤርትራ የመቅትል ተሳቢ፤ መቅትል የኤርትራ ቅጽል፤

ሙሴ ሙሻ ዘር የወጣበት እና የመቅትል ዘርፍ፤ ሙሴ የመስተቃትላን ተሳቢ፤ ቀተልት ምስለ የወጣበት /የገሞራ ቅጽል/፤ ገሞራ ተሳቢ ዘርፍ /ሙሻዘር/፤ ሁለተኛው ገሞራ በቂ ሆኖ የመቅትል ተሳቢ፡፡
ሁሉም ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ያለው ቅኔ ሙያ አለው፡፡ ያለሙያ የሚደረስ ቅኔ
አይኖርም፡፡

፷፥፮፥፬. የሦስቱ አብያተ ጉባኤ ዋና ዋና መለያዎች

በብዙ ነገር ተመሳሳይ ቢሆኑም በሦስቱ አብያተ ጉባኤ መካከል ግልጽ ልዩነቶች አሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹን ከዚህ ቀጥለን እንመልከት፤
፩. የዜማ ልክ /የጉባኤ ቃና ሐረጎችና ሌሎችም
ሀ. ዋሽራዎች በዕዝል ጉባዔ ቃና ሁለተኛው ቤት /ስንኝ/ የመሀል ሐረግ ሦስቱም ንባባት ማለትም ተነሽ፤ ተጣይ፤ ሰያፍ ልክ እንደመጀመሪያው ቤት ከ4-5 እና ወዳቂ ከ3-5 እንዲገባ ይፈቅዳሉ፡፡
ለ. እንዲሁም የመጀመሪያው ቤት መነሻ ሐረግ ተነሽና ተጣይ አምስትን፤ ሰያፍ ደግሞ ስድስትን ነክተው፤ ሰያፍን 4 ሰያፍ፤ ተጣይና ተነሽን ደግሞ 3 ተነሽና ተጣይ ይቀበላቸዋል፡፡ ይህ በሌሎች ጉባኤ ቤቶች ተቀባይነት የለውም፡፡ ሰበረ ተብሎ ጩኸት ይፈጠርበታል፡፡ በመሠረቱ ልማድ ስለሆነ ነው እንጂ ዜማውን መጮህ አያስቸግርም፡፡ ጸናጽልና ዝማሜም ተሠርቶለታል፡፡ ይህን ትንሽ ነገር በጋራ ተነጋግሮ

የጋራ ማድረግ ባለመቻሉ የተለያዩ ጉባኤ ቤቶች ተማሪዎች ሲገናኙ ዱላ ይማዘዙበታ።።
ሐ. የመጀመሪያውን የጉባኤ ቃና ስንኝ ዋሽራዎች በዘአምላኪየ መንደርደሪያ እስከነ ቤት መምቻው የሚያስነሱ ሲሆን በሌሎች ጉባኤ ቤቶች የተለመደ አይደለም።።
መ. ዋሽራዎች የጉባኤ ቃና መነሻን በመነሻ መደብ ተቀባይ ይጀምራሉ።።
ሠ. የልውጥ ሚበዝኑ ቤት መምቻ መደብ፣ በመነሻው ልዩነት ባይኖርም በተቀበዩ ላይ ልዩነት አለ።። የቤት መምቻው፣ በዋሽራ የሦስቱም ንባባት ማለትም የተነሽ፣ የተጣይና የሰያፍ ተቀባይ ከ፬ እስከ ፰ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ የተነሽና የሰያፍ ተቀባይ አራት ብቻ ነው ይላሉ።። ተነሽንና ሰያፍን ፰ ከተቀበለ ዜማው ሰበረ ብለው ይጮህሉ።። ይህ የሚ በዝኑ ቤት መምቻ በብዙ ቅኔዎች ላይ የዜማ ልክ እየሆነ ያገለግላል።። ለምሳሌ፣ በዘይእዜ ሦስተኛው ቤት መድረሻ፣ በመወድስ በአንደኛው ቤት መምቻ፣ በአረተኛው ቤት መነሻና ቤት መምቻ፣ በስድስተኛው ቤት መነሻና መድረሻ በስምንተኛው ቤት መነሻና መድረሻ፣ በዕዝል ዕጠነ ሞገር የሦስተኛው ቤት መነሻው እስከ ተቀባዩ፣ የአራተኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ ወዘተ የዜማ ልክ ሆኖ ያገለግላል።። በመነሻው ላይ ስምምነት ከሌለ ከላይ በተጠቀሱት ሁሉ ስምምነት የለም ማለት ነው።። የሚቀበሉም አሉ።። ከዋድላ ቤተ ጉባኤ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው አምስት የሚለውን አይቀበሉም።። ሌሎቹ የዋድላ ቤተ ጉባኤ ሊቃውንት ግን እንደ ዋሽራዎች አምስትን በአማራጭ የተነሽና የሰያፍ ተቀባይ አድርገው ይጠቀሙበታል።።
ረ. በጎንጆች ደግሞ በጉባኤ ቃና ሁለተኛው ቤት የመሀል ሐረግ፣ ወዳቂ ሦስት ሦስት ከመሆኑ ውጭ በግእዝ እና በዕዝል ጉባኤ ቃና መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም።። ዕዝል ጉባኤ ቃና በተናባቢ ሐረግ በረጂሙ አይጀምርም።። በዘአምላኪየም

እንደዚሁ ሦስተኛው ቤት የመነሻ መደቡ የሚጀምረው በግእዝ ጉባኤ ቃና ብቻ ነው። ዘይእዜ ላይም ይሄው ይሠራል። ማለትም በዘይእዜ መጀመሪያ ቤት መነሻውና ከኃይለ ቃሉ ቀጥሎ ያለው መነሻ ሐረግ የሚጀምረው በግእዝ ጉባኤ ቃና ብቻ ነው። በሌሎቹ ግን በግእዝም በዕዝልም ይነሳል።

ሰ. ዋድላዎች የሁለቱንም አይቀበሉም። ጎንጅም የዋሸራን አይቀበልም። ሆኖም ዋድላዎች ከላይ በሐ እና በመ፣ ሥር የተጠቀሱትን በመደበኛነት ባይሆንም በጉባኤ ቤት ደረጃ ይቀበሏቸዋል። በሠ ሥር የተብራራውንም በመደበኛነት ይቀበሉታል።

፪. የቅኔ መነሻዎች

ቅኔ በተገኘው አገባብ፣ ዘር ወይም ነባር ሁሉ በዘፈቀደ አይጀመርም። በዚህ ሁሉም አብያተ ጉባኤ ይስማማሉ ነገር ግን ቅኔን በሚያስጀመሩና በማያስጀምሩ አገባቦች ወይም ሌሎች አጠቃቀሞች ግልጽ ልዩነቶች አሉ።

ሀ. በዋድላ የቅኔ መነሻ የሚሆኑ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

፩÷ ከዐበይት አገባባት ጊዜ የሚሆኑ አገባባት፣ አመ፣ ሶበ፣ ጊዜ ዕለተ፣ ዓመተ፣ መዋዕለ፣ በቂ እየሆኑ ጊዜን፣ ዕለትን፣ ዓመትን፣ ዘመንን በሚያመጡበት ጊዜና ደቂቅ አገባብ በሚሆኑበት ጊዜ ያስጀምራሉ።

፪÷ ኀበ፣ መንገለ፣ ወእደ በቂ ሆነው ቦታን በሚያመጡበት ጊዜ ብቻ ያስጀምራሉ።

፫፥ መጠነ፣ አምጣነ፣ ልክ፣ ያህል እየሆኑ ሲተረጎሙና ደቂቅና ዘር ሆነው በሚገቡበት ጊዜ ያስጀምራሉ፡፡

፬፥ የነገር አገባባት፣ እመ፣ በዘ፣ ያስጀምራሉ፡፡

፭፥ ለሁሉም ቅጽልና በቂ የሚሆኑት ዘ፣ እንተ፣ እለ በቂ ወይም ስም ወራሽ በሚሆኑበት ጊዜ፣ በተጨማሪም እለ ስም አብዝር በሚሆንበት ጊዜ፣ ያስጀምራሉ፡፡ አስተውል፣ ከ፪ እስከ ፭ የተዘረዘሩት በዐቢይ አገባብነታቸው ቅጽል ሆነው በሚነገሩበት ጊዜ የቅኔ መጀመሪያ አይሆኑም፡፡

፮፥ በነባር ውስጥ የሚካተቱ ነባር አናቅጽ፣ የተፈጥሮ ስም፣ የተጸውዖ ስም፣ የተቀብዖ ስም፣ ብትን ሰዋስው፣ ቅኔ ያስጀምራሉ፡፡

፯፥ ሕገ፣ አርአያ፣ አምሳለ፣ ፍዳ፣ ቤዛ፣ ዐስበ እና የመሳሰሉት በዘርነታቸው ቅኔ ያስጀምራሉ፡፡ በአገባብነታቸው ግን አያስጀምሩም፡፡

፰፥ ከደቂቅ አገባባት ዝየ፣ ለፌ፣ ህየ፣ ከህ፣ የመሳሰሉት ቅኔ አያስጀምሩም፡፡

፱፥ ከደቂቅ አገባባት መነሻ፣ ማድረጊያ፣ አቀባይና የመሳሰሉት ለምሳሌ፣ እም፣ በ፣ ለ፣ ላዕለ፣ ታሕተ፣ ቅኔ ያስጀምራሉ፡፡

በነባር ውስ የሚካተቱ ዐበይት አገባባት ከ፪ እስከ ፭ ከተዘረዘሩት በስተቀር ሌሎቹ ቅኔ አያስጀምሩም፡፡

ከዚህ የሚከተሉት ደግሞ ቅኔ አያስጀምሩም

፲፥ በዘማች አናቅጽ የሚካተቱ ዘንድ አንቀጽና ቦዝ አንቀጽ አያስጀምሩም፣

፲፩፥ አዳማቂ ወይም በር ከፋች ሆነው የሚገቡ ደቂቅ አገባቦች፣ ለ፣ በ፣ እም፣ ከመ፣ አመ ወዘተ፣ አያስጀምሩም።

፲፪፥ የስም አጻፋዎች /አመልካች ደቂቅ አገባቦች/ ከፊት ለፊታቸው ስም ከሌለ፣ ማለትም በቂ ሆነው ከገቡ፣ ለምሳሌ ዝንቱ፣ ኩሉ፣ ዝኩ፣ እና ዐሥሩ መራሕያን ከአነና ከንሕነ በስተቀር/አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን፣ ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ ይእቲ፣ ውእቶን፣ ብቻቸውን ገብተው ቅኔ አያስጀምሩም። ቅጽል ቢሆኑም አያስጀምሩም።

፲፫፥ ዘ፣ እንተ፣ እለ ቅጽል /የ/ እና ዘርፍ ደፊ ሆነው ሲገቡ

፲፬ ከሰሚና አሰሚ፣ የአገባብ፣ የዘር፣ የዘርፍ አሰሚዎች ቅኔ አያስጀምሩም ፣ ከባለቤት ወይም ከአንቀጽ በፊት የገባ የብትን ሰዋስው፣ የደቂቅ አገባብ፣ የንዑስ አገባብ ዝርዝር ሁሉ አያስጀምርም። ለምሳሌ ጎቤከ፣ እምኔከ፣ ከማከ፣ በእንቲአከ፣ ዘርፍን በተመለከተ፣ ደመ ገቦከ፣ ውለደ ውለድከ፣ ወዘተ

፲፭. አስረጂዎች፣ እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ አያስጀምሩም።

፲፮፥ መገስገሻ፣ መድረሻ፣ አብሮ፣ ያለ፣ አንጻር፣ ተፎካካሪ፣ አብነትና የመሳሰሉት፣ ለምሳሌ፣ ጎበ፣ መንገለ፣ ወእደ፣ ምስለ፣ እንበለ፣ እስከ፣ ከመ ቅኔ አያስጀምሩም።

፲፯፥ ወ ዋዌ ወይም አውራጅ ሆኖ ሲገባ፣ እና ሂ፣ ኒ ደጋሚ ሲሆኑ አያስጀምሩም።

፲፰ ባሕቱ፣ ዳዲ ዳግመኛ ሲሆኑ አያስጀምሩም።

፲፱. እንበለ፣ ዳእሙ እንጂ ሲሆኑ አያስጀምሩም።

፳፥ ከንዑስ አገባባት አው፣ ዮጊ፣ ሚመ፣ እመ አኮ፣ ሶበ አኮ፣ ጥቀ፣ ሐዊሳ፣ እስኩ፣ እንጋ፣ ክመ፣ ጽመ፣ ጓ፣ እንቋ፣ እንከ፣ አህ፣ አሀህ አያስጀምሩም።

፳፩፥ ከደቂቅ እርባታ አገባብ፣ በበ፣ ዘዘ፣ እየ፣ በየ

ሲሆኑ የቅኔ መጀመሪያ አይሆኑም።።
፳፪፥ በር ከፋች ይዘውም ሆነ ሳይዙ የሚገቡ ስለ የሚሆኑ ዐበይት አገባባት በሙሉ አያስጀምሩም፣ ምሳሌ፣ በእንተ፣ በይነ፣ እንበይነ፣ ህየንተ፣ ፍዳ፣ ተውላጠ፣ ዐስበ፣ በቀለ ወዘተ።።

ለ. በጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መነሻ የሚሆኑ

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር ሌሎች አገባባት ቅኔ አያስጀምሩም
በ፣ ለ፣ አመ፣ እመ፣ እም፣ ዘ እና እለ የስም ወራሽ ሲሆኑ ብቻ ቅኔ ያስጀምራሉ።። ከነዚህ ውጭ ያሉት አገባቦች በሙሉ ቅኔ አያስጀምሩም።።

ሐ. በዋሸራ ቅኔ የማያስጀምሩ

አስረጂዎች እና ቅጽሎች / ዘ፣ እንተ፣ እለ/ ቅኔ አያስጀምሩም።። ከነዚህ ውጭ በዋሸራ ቅኔ የማያስጀምር ሕግ የለም።። የዚሁ የሰምና ወርቅ ቅኔ አካል በሆነው በእመይቴ ገላነሽ ተዋረድም ከላይ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ደጋሚ የሚባሉት ማለትም ሂ፣ ኒ፣ ወ ቅኔ አያስጀምሩም።። ዋሸራዎች ብዙ ጊዜ በዐሥሩ መራሕያን ቅኔ ስለሚጀምሩ ከሌሎች አብያተ ጉባኤ ተማሪዎች ጋር ግጭት ይፈጥራሉ።። ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ቅኔ በሚያስጀምሩና በማያስጀምሩ አገባባት፣ ወይም ሰዋስው ዙሪያ በጣም ሰፊ ልዩነት አለ።። የተለያዩ አብያተ ጉባኤ ተማሪዎችን ለማነታረክ እነዚህ ብቻ በቂ ማሳያዎች ናቸው።።

፫. ዋሸራ በውስጠ ተሳሳቢ የሚለይባቸው ነጥቦች፤

ዋሽራ በውስጠ ተሳሳቢ ከሁለቱ የሚለይባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. በውስጠ ወይራ ጊዜ የሰም ዘርፍን አስቀድመው ወርቅን ያስከትላሉ፡፡ ለምሳሌ ጎብስተ ባዕል ጴጥሮስ ብለው የጴጥሮስ ባለጸጋ እንጀራ ሃይማኖት በማለት ውስጠ ወይራ ያወጣሉ፡፡ በዋድላና በጎንጅ ሥርዓት መሠረት መባል ያለበት ጎብስተ ጴጥሮስ ባዕል ነው፡፡ ይህ በጣም መሠረታዊ ልዩነት ነው፡፡ በዐዋጅም በግልጽ ይታወቃል፡፡

ለ. አንቀጽን አለፈው ይስባሉ፡፡ ለምሳሌ፤ ይቤልዎ ሕዝብ ቀላያተ ግብፅ፤ ምንተ ኮንከ ለፈርያን ባሕቲቶ የሚል ቅኔ አላቸው፡፡ በዋድላና በጎንጅ ይትበሀል መሠረት ቢሆን ኖሮ መባል የነበረበት ይቤልዎ ሕዝብ ቀላያተ ግብፅ ለፈርያን ባህቲቱ ምንተ ኮንከ ነው፡፡ በዋድላ፣ ይህም ዐዋጅ የጣሰ ነው፡፡ ሌላ ምሳሌም አለ፡፡

በኖኅተ ሕዝቅኤል ባዕድ እመትገብር ነቢረ፤
አሮን አንሥኦተ በትሩ እስመ ብኪ ገብረ፤

ኖኅተ የሚሳበው በነቢረ ስለሆነ በመሀል እመትገብር መግባት አልነበረበትም፡፡ ትገብር እመ የተባለው ዐቢይ አገባብ ቢወድቅበትም አንቀጽ ነው፡፡ በኖኅተ ሕዝቅኤል ባዕድ ነቢረ እመ ትገብር ቢል አንቀጹን ስለማይዘል ይቃናል፡፡ ይህ አስተያየት የተሰጠው በዋድላ ዐዋጅ መሠረት እንጅ በራሱ በዋሽራ ትክክል ነው፡፡

ሐ. የግስ እርባታን በተመለከተም ልዩነት አለ፡፡ ለምሳሌ፣

፩/ አእመረ የሚለውን ግስ ዋሽራዎች ሲያረቡ፤ አእመረ ብለው የአምር ይላሉ፡፡ ከዚያም ያእምር ያእምር ይላሉ፡፡ ነገር ግን በሁለተኛ እርባታ ያአምር፣ ይእምር፣ ይእምር ብለው ያቃኑታል፡፡ በዋድላ ቀመረ ግስ መሠረት መባል የነበረበት፤ አእመረ ያአምር፣ ያእምር፣ ያእምር ብቻ ነው፡፡ ካላዩን የአምር ካሉ ግሱ አመረ መሆን ነበረበት፡፡

ሲረባም አመረ፣ የአምር፣ ይእምር፣ ይእምር ነው። ምክንያቱም ግሱ አመረ ከሆነ የሚረባው በቀተለ ቤት ነው። አእመረ ግን አስደራጊ ስለሆነ በአድራጊ ሊረባ አይችልም። ይህ መሠረታዊ ልዩነት ነው።
፪/ ዋሽራዎች ከግሱ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የሌለው ውስጠዘ ወይም ምዕላድ ያወጣሉ። ለምሳሌ በርሀ ብለው ቶማስ ውስጠዘ፣ ቶማስስ በብዙ ይላሉ። እንዲሁም ተፈሥሐ ከሚለው ግስ ሐና እና ዮሐንስ ውስጠዘ ሆነው ይወጣሉ ይላሉ። ምዕላድ አወጣጥን በተመለከተ ደግሞ ከርመ ብሎ ቲቶ፣ በርሀ ብሎ ኡራኤል፣ ድጎነ ብሎ ኢየሱስ፣ ጎየለ ብሎ ኤልያስ፣ ገዘመ ብሎ ኦም ምዕላድ ሆነው ይወጣሉ ይላሉ። እንደዚህ ዓይነቱ ርባታ በዋድላ ቤተ ጉባኤ ተቀባይነት የለውም።

፬. ጐንጅ ከሌሎች የሚለይባቸው ነጥቦች፤

ሀ. ቅኔ የሚያስጀምሩ አምስት አገባቦች ብቻ መሆናቸው፣ እነርሱም፣ በ፤ ለ፤ አመ፤ እመ፤ እም፤ ዘ እና እለ የስም ወራሽ ሲሆኑ ብቻ ያስጀምራሉ። ከነዚህ ውጭ በጎንጅ ቤተ ጉባኤ ሌሎች አገባባት ቅኔ አያስጀምሩም። በተለይ መራሕያንና ሌሎች አመልካች ደቂቅ ቅጽሎች በጎንጅ ፊደሞ ቅኔ አያስጀምሩም።
ለ. የጉባኤ ቃና የመጀመሪያው ስንኝ፣ የዘአምላኪያ የመጀመሪያው ቤት መነሻ ሐረግ፣ የሥላሴ ከአጎበሩ ቀጥሎ ያለውና ከመንደርደሪያው ቀጥሎ ያለው ቤት የመነሻ ሐረግ፣ የዘይእዜ የመጀመሪያው ቤት ከኃይለ ቃሉ በፊት ያለውና ቀጥሎ ያለው መነሻ ሐረግ መደቡ ከነተቀባዩ ምንጊዜም የግእዝ ጉባኤ ቃና የዜማ ልክ ብቻ መሆኑ፣

ሐ. የታሪክ ሰምና ወርቅ ቅኔ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ፣ ወይም እንደ ቅኔ የማይቆጠር መሆኑ፣
መ. ለቅኔ መነሻና በመሀልም ቁምር ንዑስ አንቀጽን ማዘውተሩ፣
ሠ. በቅኔያቸው ውስጥ አገባቦችን በተደራቢ ትርጉማቸው ወይም በትርፍ አማርኛ በመጠቀም ቅኔን ለማክበድ የሚያዘወትሩ መሆናቸው።

፭. ቀመረ ግስን በተመለከተ ያሉ ልዩነቶች፤

የቅኔ ዐረፍተ ነገር የሚሠራው ግስንና አገባብን በመጠቀም ነው። ግስ ደግሞ የራሱ ቀመር አለው። ዋናዎቹ አርእስትና ሠራዊት ናቸው። እነርሱን በማገዝ ቀመረ ግሱን የተሟላ የሚያደርጉ ሌሎች ከ፲፭ እስከ ፳፰ የሚደርሱ ቀመሮችም አሉ። እያንዳንዱ ቤተ ጉባኤ የሚጠቀምባቸው አርእስተ ግሶችና ሠራዊት የተለያዩ ናቸው። በጉባኤ ቤቶች መካከል ቀርቶ በአንድ ቤተ ጉባኤ መምህራን መካከልም ልዩነት አለ።
አርእስተ ግስ ከስድስት እስከ አስራ አንድ የደረሱ ሲሆን የሠራዊት ቁጥር ደግሞ ከ፲፮ እስከ ፱ ደርሷል። በእነዚህ አካሄድ አንድነት ካልተፈጠረ ቅኔን የበለጠ ማዳከሙ አይቀርም። የዋሽራን ከመጽሔተ አእምሮ፣ የዋድላንና የጎንጅን ከየቀመረ ግሳቸው ማየት ይቻላል። በሊቀ ሊቃውንት ያሬድ መጽሐፍም በገጽ ፬፻፷፭ ላይ የተገለጸው ከዋድላ ቀመረ ግስ ጋር አንድ ዓይነት ነው። በመምህር ደሴ ቀለብ መጽሐፍ መሠረት ደግሞ ፲፭ እንደሚደርሱ ከዝርዝራቸው ጋር ተገልጿል /ትንሣኤ ግእዝ፣ 2007፣ 177-178/።
በሦስቱ ጉባኤ ቤቶች መካከል ያሉት ልዩነቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም። ዝርዝር ጥናት የሚጠይቁ ሌሎችም ልዩነቶች አሉ። ከሦስቱ አብያተ ጉበኤ የዋሽራ ቤተ ጉባኤ በሁሉም ነገር ክልከላ

አይበዛበትም፡፡ ለቀቅ ያለና እንደልብ የሚያንቀሳቅስ ነው፡፡ ዋድላና ጎንጅ ክልከላ ይበዛባቸዋል፡፡ ጸያፍ ይጠነክርባቸዋል፡፡

፷፥፮፥ አጎዝ፣

በስድስተኛው ድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ ጉባኤ ሰፍቶ አገባብ ሰባት ደርሶ ነበር በሚለው የአበው ትምህርት መሠረት ሰባተኛው አገባብ አጎዝ ነው፡፡ አጎዝ ማለት መያዣ፣ ዐረቦን ወይም ጅምርና ውጥን ማለት ነው በማለት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ተርጉመውታል /1948፣ 104/፡፡ አጎዝ ዘርና ነባር ነው፡፡ በዝርዝር ፊደል ሲጻፍ ዘር፣ በቁጥር ሲጻፍ ደግሞ ነባር ይሆናል፡፡
ስለአጎዝ በተብራራ መንገድ የጻፉት አለቃ ታየ ገብረ ማርያም ናቸው /1958፣ 302/፡፡ በአለቃ ታየ አተረጓጎም መሠረት አጎዝ ማለት መጀመሪያ፣ መቋሚያ፣ መያዣ፣ ዋስ፣ ቁጥር ማለት ነው፡፡ ወአጎዘ ይጎልቅ ማይ እምድር ወይም እጎዝሂ ወእፈጽም ሲል መጀመሪያ፣ አጎዝ እግዚአ መዋግደ ጸጋከ ሲል መቋሚያ፣ ወልቃሕሰ ይደሉ ከመ ይኩን አጋዝ ሲል ዋስ ወይም መያዣ፣ ኢይነብር ንዋዩ ለባዕል ዘእንበለ አጎዝ ሲል ቁጥር፣ ይሆናል /አለቃ ታየ፣ 1958/፡፡
አጎዝ ከባለቤት በፊት እየገባ ቅጽል ይሆናል፡፡ ባለቤት ሳይኖር ደግሞ በቂ ይሆናል፡፡ በገቢር በተገብሮ ይነገራል፡፡ ለብትን ሰዋስው ሁሉ ይሆናል፡፡ በደጊመ ቃል በከፊል ይበቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ማሠሪያዎቹ ውእቱ፣ ኮነ፣ ረሰየ፣ መሰለ፣ ተመሰለ፣ ተማሰለ፣ ተጸውዐ፣ ተሰምየ፣ ተብህለ፣ መደራረግ ናቸው፡፡ በደጊመ ቃል ሲበቃ፣

ልብሱ ለነዳይ አሐዱ አሐዱ፣
ረሰየ ነዳይ ልብሶ አሐደ አሐደ፣
ኮነ ለነዳይ ልብሱ አሐደ አሐደ፣

በከፊል ሲበቃ፣

ኮነ ሰብአ አሐዱ እምነሥላሴ፣
አሐዱ ገጸ ሰብእ ውእቱ እምነኪሩቤል
ይላል።።

አምስት ቀለማት በአጎዝ ይዋረሳሉ።። እነርሱም፣ ግእዝ፣ ካዕብ፣ ሣልስ፣ ጎምስ፣ ሳድስ ናቸው።። ሁለቱ ወራሾች፣ ሦስቱ ተወራሾች ናቸው።። ካዕብንና ሳድስን ግእዝ ይወርሳቸዋል።። ሣልስን ግእዝም ጎምስም ይወርሱታል።። ምሳሌ፣

ካዕቡን ግእዝ ሲወርሰው፣ አሐዱ፣ ክልኤቱ፣ ሠለስቱ ያለውን አሐደ፣ ክልኤተ፣ ሠለስተ፣

ሳድስን ግእዝ ሲወርሰው፣ ዋሕድ ያለውን ዋሕደ ይላል፣

ሣልሱን ግእዝ ሲወርሰው፣ አሐቲ ያለውን አሐተ፣ ክልኤቲ ያላውን ክልኤተ ይላል፣

ሣልሱን ጎምስ ሲወርሰው፣ ሣልሳዊ ያለውን ሣልሳዌ ይላል።።

አጎዝ ቁጥር ሲሆን ወይም የመቁጠሪያ ቁጥር ሆኖ ሲገባ ምን እንደሚመስል በገጽ ፮ እና ፮ ላይ ስለተጻፈ ወደኋላ ሄደህ ተመልከት።።

አገባብ ተፈጸመ

መጽሐፉ በጥናት ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ስለሆነ ለማገናዘቢያነት የቀረቡትን መጻሕፍት በማየት ሙያውን ማዳበር ይቻላል።። የሚሰጠንን ገንቢ አስተያየት ሁሉ ለመቀበልና በሚቀጥለው እትም መጽሐፉን ለማዳበር ዝግጁ ነን።።

፱. ዋቢ መጻሕፍትና የአብነት መምህራን፤

ማርያም ወርቅነህ /ሊቀ ሥልጣናት /፡፡ (1963)፡፡ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ (መሪጌታ)፡፡ (1989)፡፡ ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ NA፡፡

ሥርግው ገላው (ዶ/ር)፡፡ /2008/፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በአለቃ ገብረ ኢየሱስ ዋቅጂራ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

በላይ መኮንን (ሊቀ ጎሩያን)፡፡ (2006)፡፡ ዕሴተ ትሩፋት ዘቅዱስ ያሬድ ፡ ወትምህርተ ቃል፡፡ አዲስ አባባ፡፡ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡

_____ (2007)፡፡ ሕያው ልሳን፣ ግእዝ-
አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡
አፍሪካ ማተሚያ ኃላ/የተ/የግል ማህበር፡፡

ቡሩኬ (የዋድላ የቅኔ የአብነት መምህር)፡፡
አገባብ፡፡ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ፡፡
ተ/ሃይማኖት ወልዱ፡፡ (ሊቀ ጉባኤ)፡፡ (2003)፡፡
ቀላል የግእዝ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፡፡ አዲስ
አበባ፡፡ NA፡፡
ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ (1953)፡፡ የኢትዮጵያ
ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፡፡
አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡
ታየ ገ/ማርያም /አለቃ/፡፡ (1943)፡፡ መጽሐፈ
ሰዋስው፣ ብሔራዊ ቋንቋ ዘኢትዮጵያ፣ መጽሔተ
አእምሮ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ቤት፡፡
ነቢየ ልዑል በጽሐ /አለቃ/፡፡ የዋሸራ ታሪክ፡፡
በዋሸራ የሚገኝ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ፡፡
አማን በላይ /መሪራስ/፡፡ (2000)፡፡ መጽሐፈ
አብርሂት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ Askale Printers፡፡
_____ /2009/ ፡፡ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ
ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ Nebadan Publication፡፡
አድማሱ ጀምበሬ (መልአከ ብርሃን)፡፡ (1963)፡፡
መጽሐፈ ቅኔ፡ ዝክረ ሊቃውንት፡፡ አዲስ አበባ፡፡
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ በት፡፡
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፡፡ (1980)፡፡
የግእዝ ቅኔያት የስነ ጥበብ ቅርስ፡፡ አዲስ አበባ፡፡
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡
የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፪፡፡ /2000/፡፡
አዲስ አበባ፡፡
ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ /በደስታ ተ/ወልድ
አሳታሚነት/፡፡ (1948)፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ

ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ።
አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።
ዓለማየሁ ሞገስ። (1967)። የግእዝ ቅኔ ዜማ።
አዲስ አበባ። ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
ያሬድ ሽፈራው (ሊቀ ሊቃውንት)። (2002)።
መጽሐፈ ግስ ወሰዋስው መርኖ መጻሕፍት።
ባሕር ዳር። ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት።
ይኄይስ ወርቁ (መምህር)። (1960)። ንባብ
ወትርጓሜ ዘቅኔያት፤ አዕማደ ምሥጢራት።
አዲስ አበ። ንግድ ማተሚያ ቤት።
ደሴ ቀለብ። (2006)። ትንሣኤ ግእዝ፤ አቡጊዳ
ሄውዞ። አዲስ አበባ። ማኅበረ ቅዱሳን።
ገብረ ሕይወት /መምህር/። የጎንጅ አገባብ፤
ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ።
ገዳሙ አያሌው /የጎንጅ ቅኔ የአብነት
መምህር/። (1979)። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ
ትምህርት፤ የመመረቂያ ጽሑፍ። ሰዋስወ ብርሃን
ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ።
ጌቴ ገሞራው /የዋድላ የቅኔ የአብነት መምህር/።
አገባብ፤ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ።
ጥዑመ ልሳን ካሳ /ርእሰ ደብር/። (1981)።
ያሬድና ዜማው። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ዘጉባኤ
ማተሚያ ቤት።
ፍሥሓ ያዜ። (2003)። የኢትዮጵያ የ5ሺ
ዓመት ታሪክ፤ ከኖኅ እስከ ኢሕአዴግ። አዲስ
አበባ። አልፋ አታሚዎች።

ከሊቃውንት ጋር የተደረጉ ውይይቶች

ከሀብታሙ በለገ /መልአከ ጽዮን /። የቀድሞው
የዋድላ ቤተ ክህነት ኃለፊ ጋር በስልክ የተደረገ
ውይይት። የካቲት 2008።

ከሃይማኖት አድማስ /መሪጌታ/፡፡ በደብረ ጽዮን በሰላም አርጊው ማርያም ቤተ ክርስቲያን የጎንጅ ቅኔ መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥር/2008፡፡

ከመንግሥቱ ዘለዓለም /መሪጌታ/፡፡ የሽምብጥ ፊለገ ፀሐይ አንድነት ገዳም የቅኔ መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ መጋቢት 2008፡፡

ከቅዱስ ያሬድ/መሪጌታ/፡፡ በመንበረ ስብሐት ቅ/ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፣ ባሕር ዳር፣ የዋድላ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ መጋቢት 2008፡፡

ከባሕር ዳር ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች /በቁጥር 24/ ጋር በሥልጠና ላይ እንዳሉ፣ በቡድን የተደረገ ውይይት፡፡ ጥር/2008፣

ከተውህቦ ዘውዴ /መሪጌታ/፡፡ የዋድላ ወረዳ የስብከተ ወንጌል ኀላፊ ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥቅምት/2009፣

ከትክክል ማረፊያው /አቶ/፡፡ የዋድላ ወረዳ የማስታወቂያ ባለሙያ ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥቅምት 2009፡፡

ከአብርሃም ወርቁ /መሪጌታ/፡፡ በዋድላ ቁራ አንበሳ፣ የዋድላ ቅኔ የአብነት መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥቅምት 2009፡፡

ከአንተነህ ከፋለ /መምህር/፡፡ የሽምብጥ ፊለገ ፀሐይ ገዳም አገልጋይ ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ሚያዚያ 2008፡፡

ከአእመረ ፀወቀ /መጋቤ ሐዲስ/፡፡ የዋድላ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥቅምት 2009

ከዋሸራ ሊቃውንት ጋር ስለቁራ ገዳልና የራጉኤል ዋሻ የተደረገ ውይይትና ጉብኝት በፎቶ ግራፍ የተደገፈ፡፡ መጋቢት 2008፡፡

ከዓለሙ አስማረ /መልአከ ገነት/፡፡ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ ጋር በስልክ የተደረገ ውይይት፡፡ መጋቢት/2008፡፡

ከኪዳኑ አበራ /መሪጌታ/፡፡ የጎርደማ ብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፡ ባሕር ዳር፤ የሰምና ወርቅ የቅኔ መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ መጋቢት/2008፡፡

ከዜና ሥላሴ /መመህር/፡፡ በሰሜን አቸፈር ወረዳ ሊበን ከተማ በሚገኘው መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር ከሆኑት ጋር በቦታው የተደረገ ውይይት፡፡ ኅዳር 2009፡፡

ከገዳሙ አያሌው /ሊቀ አእላፍ/ ፤ የጎንጅ ቤተ ጉባኤ የቅኔ መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ 2008፡፡

ከጥላሁን ብርሃኔ /መሪጌታ/፡፡ የየነጃ ሚካኤል ሰበካ ጉባኤ ጸሓፊ ጋር በገብለሞ መንደር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥቅምት 2009፣

ከጥዑመ ልሳን ልየው /መምህር/፡፡ የዋሸራ የቅኔ አብነት መምህር ጋር የተደረገ ውይይት፡፡ ጥርና መጋቢት 2008፡፡



ድልድይ ወንዝ እንደሚያሻግር ሁሉ ማዕዶት የተባለው ይህ መጽሐፍም ካለማወቅ ወደማወቅ የሚያሸጋግር የዕውቀት ድልድይ ነው። መጽሐፉ በውስጡ ጥልቅ ሐሳቦችን ይዟል። በተባጠሰ መልኩ አልፎ አልፎ ሲቀርብ ከመታየቱ በስተቀር

እንደዚህ በጥናት ላይ ተመሥርቶ በተደራጀ አግባብ የመምህራን ሐረገ ትውልድ ቀርቦ አያውቅም። ይህ መጽሐፍ የሦስቱንም አብያተ ጉባኤ ማለትም የዋሸራ፣ የጎንጅና የዋድላ መምህራን ሐረገ ትውልድ አጠቃሎ ከመያዙም በላይ በፎቶ ግራፍ ተደግፎ በየጉባኤ ቤቱ ቅኔ የተጀመረባቸውን ቦታዎች ማሳየቱ ልዩ ያደርገዋል። ቅኔ መቸ እንደተጀመረና እንዴት እያደገ እንደመጣ መጽሐፉ አዲስ ግኝት ይዞ ቀርቧል።

ቅኔን ቅኔ የሚያደርጉት ዐዋጅና አገባብ ናቸው። እነዚህን ሙያዎች ለመማርና የመምህራንን ፈቃድ አግኝቶ ለመጻፍ ምን ያህል አስቸጋሪና ጊዜ ወሳጅ እንደነበር የሙያው ሊቃውንት ያውቁታል። ዐዋጅና አገባብ ለመቀጸልና ለመጻፍ አሰቸጋሪ ከመሆኑም የተነሳ በቅኔ ጥበብ ላይ አለታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ ግልጽ ነው። በብዙ ድካምና ጥረት ፈቃድ ተገኝቶ ቢገለበጥም እንኳ የጥራት ችግር ስላለበት መልሰው ሲያነቡት አደናጋሪ ከመሆን አያልፍም። በተለይ በስድስተኛው ድድቅ ወልደ ማርያም ጊዜ ጉባኤ ሰፍቶ አገባብ ሰባት ደረሰ የሚባለውን በጥናት ላይ ተመሥርተው ሊቃውንቱ አዘጋጅተው ማቅረባቸው በዕውቀት ጎዳና ብዙ ርቀት ያስኬደናል።

የሦስቱ አብያተ ጉባኤ ተማሪዎች ሲገናኙ ከመናቆር በስተቀር በምን እንደሚለያዩና ምን አንድ እንደሚያደርጋቸው ለይተው ለማወቅ የሚችሉበት ዕድል አልገጠማቸውም። ይህ መጽሐፍ ጉባኤ ቤቶቹ የሚለያዩባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች በመተንተኑ ልዩነትን ዐውቆ ለመግባባት ያስችላል። የቅኔውን ደረጃም ያሳድገዋል።

እነዚህ የታወቁ የቅኔ ሊቃውንት /የቀለም አባትና ልጅ/ ይህን መጽሐፍ በብዙ ድካምና ጥረት በጥናት ላይ ተመሥርተው አዘጋጅተው አቅርበውልናል። ከእኛ የሚጠበቀው መጽሐፉን ማንበብና ዕውቀታችንን ማዳበር ወይም አዲስ ዕውቀት

ማግኘትና ልበ ሙሉ መሆን ነው፡፡ በተለይ መምህራን ቀሳውስትና በትምህርት ላይ የምትገኙ ደቀ መዛሙርት መልካም አጋጣሚውን ተጠቀሙበት፡፡

ጥበብ ወደልብህ ትገባለችና ዕውቀትም ነፍስህንደስ ታሰኛለችና፤ ምሳ. 2፡10

አባ ማርቆስ የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ በመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሊቀ ጳጳስ፣ እንዲሁም የመግናኛ ብዙኃን ድርጅት ቦርድ ሰብሳቢ





“...በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ አለኝ፥ እኔም በላሁት፥ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ፥” ሕዝ. 3፡3፡፡ ደቀ መዛሙርት ያለምንም ድካም የሚማሩበት፣ ሊቃውንት ድካማቸውን እንደመስታወት የሚያዩበት፣ የታሪክ መጣረስ የተስተካከለበት፣ የቅኔ ታሪካዊ አመጣጥ በተጨባጭ የተተረከበት፣ ሦስቱ ጉባኤ ቤቶች፣ ዋሸራ፣ ጎንጅ፣ ዋድላ ከፍ ብለው የታዩበት፣ ልዩነታቸውና አንድነታቸው የተተነተነበት፣

ከዚህ በፊት በጎትመት ያልዋለ ዐዋጅ የተዋጀበት፣ ዐቢይ አገባብ፣ ደቂቅ አገባብ፣ የደቂቅ ርባታ አገባብ፣ ንዑስ አገባብ፣ ተረፈ ንዑስ አገባብ፣ የሰምና ወርቅ መንገድ አገባብ፣ የአጋዝ አገባብ በየሙያቸውና በየዘርፋቸው ተስተካክለው የሰፈሩበት፣ በስም አጠራሩ ማዕዶት፣ በውስጥ ስሙ መጽሐፈ ዐዋጅ ወአገባብ የሚለው መጽሐፍ በመንፈሳዊም ሆነ በዘመናዊ የዕውቀት ዓለም የተመሰከረላቸው ታላቁ ሊቅ መጋቤ ምሥጢር ስማቸው ንጋቱ የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ኰኵነ ሃይማኖት የመምህራንና ካህናት ማሠልጠኛ መምህር ከመምህራቸው ከመሪጌታ መሠረት ዐሥራት ጋር አዘጋጅተው አቅርበውልናል። በዚህ መጽሐፍ የዕውቀት ጥማችሁን አርኩበት፣ ራሳችሁን እዩበት፣ የጎደላችሁን አስተካክሉበት።

አባ አብርሃም፣ የባሕር ዳር፣ የም/ንጀም፣ የአዊና የመተከል አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል።

